
መሸወዲ ኣለኽ መቼ



ALI IBN SEID

2017

መግቢያ

የተከበራችሁ አንባቢያን በሙሉ ይህንን PDF መጽሃፍ ሳዘጋጅ የማንኛውንም አምነትና አመለካከት ለመጋፋት ወይም ለማጥላላት በማሰብ ሳይሆን ይልቁንስ ሁሉም ወገን አውነት የት አንዳለች ተገንዝቦ ትክክለኛ የህይወትን ኡደት አስተካክሎ ለስኬት እንድበቃ በማሰብ ነው።

በዚህ መጽሃፍ ውስጥ በርካታ አርእስቶች የተካተቱ ሲሆን በቂና ግልጽ በሆነ መረጃ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል።እነዚህ አርእስቶች በተለያዩ ማህበራዊ ሚድያዎች ተነስተው በውድ ወንድሞችና እህቶች የተዳሰሱ ናቸው።

በዚህ መጽሃፍ ዝግጅት የኔ ሚና መረጃዎችን ከነዚህ የተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች በመሰብሰብ፥ ተመሳሳይ አጀንዳ ላይ የተነሱ ሃሳቦችን ወደ አንድ ርእስ በማምጣት ኢዲት ማድረግ ነው።ይህንም ያደረኩት የመረጃዎች ተደራሽነት አንዲሰፋ በማሰብ ነው።

በመጨረሻም ይህ መጽሃፍ የሚደርሳችሁ ወገኖች በሙሉ ልትገነዘቡዋቸው የሚገቡ ነጥቦች:-

~ በጽሁፉ ውስጥ የተጠቀሱ አረበኛ መረጃዎች edit ሳደርግ ሊዛቡ ስለሚችሉ ትርጉሙን አንብባችሁ መረዳት ትችላላችሁ or በተጠቀሱት ምንጮች ማየት ይቻላል።

~ ይህ መጽሃፍ የደረሰው ሁሉ ላልደረሳቸው በሙሉ በማዳረስ እውነትን ለሁሉም እናድርስ።

አላህ ሃቅ ላይ ያጽናን።አሚን!

Ali Ibn Seid

(Ibnseidhussen@gmail.com)

ማውጫ

1. አህለል ኪታብ.....7
2.ቅዱሱ መንፈስ.....19
መላእክት እና መንፈሱ.....19
"ታማኙ መንፈስ".....20
3.የእየሱስ(ዓ.ሰ) ጉዳይ.....24
ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?.....24
ኢየሱስ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ?.....26
ኢየሱስ ለሰው ልጅ ታጢያት ሲል ተሰቅሏልን?.....27
አማላጅ ማን ነው?.....28
እውን እየሱስ እግዛብሄር ነውን ?.....30
ኢየሱስ አማላጅ ወይስ ተማላጅ?.....31
እውን የመርየም ልጅ ዒሳ ሊፈርድ ይመጣልን?.....33
ሁሉን ዐዋቂ አይደለም!!.....35
ኢየሱስ(አሰ) ነቢይ ነው.....37
ኢየሱስ (ዒሳ(ዐ.ሰ)) የተገለጸበት ንጽጽር.....38
4.ስቅለት.....41
እውን ኢየሱስ ተሰቅሏልን?.....41
የእየሡሥ ባሪያነት በቁርአን & በመፅሐፍ ቅዱስ.....44
ኢየሱስ ማን ነዉ ?.....46
ኢየሱስ ክርስቶስ የፈፀማቸው አስደናቂ የሆኑ ታዓምራቶች.....46
ኢየሱስ ክርስቶስ አልተሰቀለም አልሞተም። ወይስ ተሰቅሏል ሞቷልም?.....48
ተላኪውን (እየሱስ) እና ዕውነታው በራሱ አንደበት ባይብል.....49
ተአምራትን መስራት የአምላክነት መለኪያ ይሆናልን?.....52
ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ለማን ህዝብ? ለምን አላማ ተላከ/መጣ?.....58
ኢየሱስ (ዐሰ)& ማሪያም(ዐሰ) በእስራኤላውያን መፅሀፍ ቅዱስ(ታልሙድ) እና በቅዱስ ቁርአን.....60
1) መርየም [አሰ] በቅዱስ ቁርአን የተሰጣት ክብር.....60
5. የሚስጢረ ሥላሴ ምስጢር.....64
ስላሴ ከየት ወዴት?.....65
" የሚስጢረ ሥላሴ ምስጢር".....66
6. ብዙ ሚስት.....69

እውን ብዙ ሚስት ማግባት በክርስትና ክልክል ነውን?....72
በእስልምና ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ለምን ተፈቀደ?....72
ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት በክርስትና ክልክል(ሀጢያት) ነውን?....77
7.ሴቶችና ማህበራዊ....79
ሴቶች እና ህፃናት በእስልምና & በክርስትና....79
የሴት ልጅ አለባበስ በእስልምና እና በክርስትና ምን ይመስላል?....84
ኒቃብ (አይነርግብ) በመፅሀፍ ቅዱስ....85
የሴት ልጅ የውርስ መብት በእስልምና እና በክርስትና ምን ይመስላል?....89
ሴት ዐዘቅትና የጠበቦች ጉድጎድ ናት!!....91
8.የመፅሀፍ ቅዱስ ዳሰሳ....93
መጽሐፍ ቅዱስ እንደተበረዘ እና የአምላክ ቃልነትን የማልቀበልበት ምክንያት....93
ማጎበረ ቅዱሳን ወይስ ማጎበረ ሰይጣን....96
9.እስልምና....99
"ኢስላም ማለት ምን ማለት ነው?....99
ኢስላም የተፈጥሮ እምነት ነው!!....102
10.የጾም ትርጉም....112
የረመዳን ፆምን እንድንፆም ማነው ያዘዘን? ማስረጃውስ ምንድነው?....112
«እስልምናን ለክርስቲያኑ»....117
11.. ኢትዮጵያችን....120
የክርስትና አመጣጥ በክርስትያን እይታ....120
~~እስልምናና ክርስትና (ኦርቶዶክስ) በኢትዮጵያ~~....122
ኦርቶዶክስ ማለት ምን ማለት ነው? አስተምህሮቷስ ምንድነው?....125
'ኢትዮጵያ ወዲህ መጽሃፉ ወዲያ ' ለምን ይዋሻል ግን?....126
የ"ዘመን መለወጫ" ስህተቶች....126
12..ሽብርተኛው ማነው?....130
ምነው ለሙስሊሙ ሲሆን ትርጉሙ ተቀየረሳ....131
13.ወንጌሎችን ማን ፃፋቸው?....135
①) የሉቃስ ወንጌል....135
②)የማርቆስ ወንጌል ማን ጻፈው?:-....137
③)የማትዮስ ወንጌል ማን ጻፈው?:-....138
④)የዮሃንስ ወንጌል ማን ጻፈው?....140
ኦርጂናል የኢየሱስ(አሰ) ወንጌል (ኢንጂል) የት ነው ሚገኘው?....142
14.የቁርዓን አወራረድ....145

ቁርኣንን ማን አወረደ ? አላህ ወይስ ጂብሪል ? 145
ቁርኣን እንዴት ተጻፈ? 147
ቁርኣን እንዴት ተሰበሰበ? 151
"የቁርአን ተአምራቶች" 154
15.የነቢያት ማንነትና አስተምህሮአቸው 161
«የነብያት ደረጃዎች በመፅሀፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁርአን» 168
16.ነብዩ ሙሃመድ(ሶ.ዐ.ወ) 173
ነቢዩ ሙሐመድ(ሰዐወ) በመፅሀፍ ቅዱስ 173
❤ይህ ትንቢት ለማን የተነገረ ትንቢት ነው?❤ 177
ነቢዩ ሙሀመድ(ሰዐወ) አኢሻን በልጅነቷ ለምን ነበር ያገቧት? ምክንያታቸውስ ምን ነበር? 178
ነቢዩ ሙሃመድ(ሰዐወ) የማደጎ ልጃቸው የነበረውን የዘይድ ኢብን ሃሪስ ሚስት ለምን አገቧት? 180
መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ!! 183
የውሻው ተረት ተረት 186
17.ተመልሷል 189
የጠበቀ ሚስማርን በጣት መንቀል አይቻልም!! 189
በህይወት ያለው ከሞተው አይበልጥም!! 193
“”የማያዳግም ምላሽ ለህዝበ ክርስትያን”” 196
የእምዬን ወደ አብዬ! 198
የዓኢሻ (ረ.ዓ.) ቤት 202
አዳም ላጠፋው ጥፋት ንሰሃ ገብቶ እግዚአብሄርን ይቅር እንዳለው ያውቃሉን? 205
ማነው የጨዋይቱ ልጅ? ማንስ ነው የባሪያይቱ ልጅ? 205
የአደም ሚስት ሥሟ ማነው? 208
አላህ(ሱወ) የሰዉ ልጅ በመጀመርያ ሲፈጠር የት እንዲኖር ነበር የፈጠረዉ? 215
የቀረችዋ አንዲ ጣኦት!! 216
18.አታስቀኝ 221
አሰቃቂና አፀያፊ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች 221
ዳጉ (የአፋር ባሕላዊ ኢንተርቪው) 222
ሀጅ ያሲን (አይ) 222
ማን ይሞክር ? 223
እቺ አነዋር መስጂድ የተፃፈች መፅሃፍ ቅዱስ ነች አለኝ 225
አጃቢዎቹስ? 228
19.ንጽህና 230
የኃጢአት ስርየት 230

ትጥበት እና ሃይማኖታዊ ብያኔው! 233
20. ስለ ፈጣሪ 237
የእግዚአብሔር ባህሪ በመፅሀፍ ቅዱስ 237
21..ስለ ሰይጣን 245
እዉን ሴይጣን መላእክ ነበረን ? 245
የሰይጣን፣የይሁዳ እና የሮም ወታደሮች ውለታ እንዴት ተዘነጋ? 247
ግብረ-ሰዶም 249
የጨረቃ ጥቅም በእስልምና እና በክርስትና 254
የእስራኤል እና የቡድሂስት መነኮሳት ወዳጅነት 256
የባሃኢ Bahá'u'lláh ዕምነት (ሃይማኖት) 257

1. አህለል ኪታብ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።።

ክፍል አንድ

3:71 የመጻሐፉ ሰዎች ሆይ! “እዉነቱን በዉሸት” ለምን *ትቀላቅላላችሁ? “እዉነቱንም” እናንተ የምታወቁ ስትሆኑ ለምን *ትደብቃላችሁ*?

تَعْلَمُونَ وَأَنتُمْ ٱلْحَقَّ وَتَكْتُمُونَ بِٱلْبَٰطِلِ ٱلْحَقَّ تَلْبِسُونَ لِمَ ٱلْكِتَٰبِ يَٰٓأَهْلَ

“አህለል ኪታብ” لَ أَهْ ٱلْكِتَابِ መነሻ ቅጥያው “አህል” لْ أَهْ ሲሆን፡-

“አህለ” لَ أَهْ በፈትሃ ሲመጣ ተሳቢ ሙያን፣

“አህሊ” لِ أَهْ በከስራ ሲመጣ አገናዛቢ ሙያን ፣

“አህሉ” لُ أَهْ በደማ ሲመጣ ባለቤት ሙያን የሚያመልክት ሲሆን ትርጉሙ “ህዝብ” አሊያም “ባለቤት” የሚል ፍቺ አለው፣ “ኪታብ” كِتَٰب ደግሞ “መጽሐፍ” ማለት ነው፣ በጥቅሉ “አህለል ኪታብ” ማለት “የመጻሐፉ ሰዎች” “የመጻሐፉ ህዝብ” “የመጻሐፉ ባለቤት”The People of the Book” ማለት ነው፣ ይህ ቃል በቁርአን 49 ጊዜ ተደጋግሞ መጥቷል።

የመጽሐፉን ባለቤቶች የተባሉት ክርስቲያንና አይሁዳውያን እንደሆኑ እሙንና ቅቡል ነው፡-

3፣71 የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! *”እውነቱን በውሸት ለምን ትቀላቅላላችሁ”* እውነቱንም እናንተ የምታውቁ ስትኾኑ ለምን *”ትደብቃላችሁ”*?። تَعْلَمُونَ وَأَنتُمْ ٱلْحَقَّ وَتَكْتُمُونَ بِٱلْبَٰطِلِ ٱلْحَقَّ تَلْبِسُونَ لِمَ ٱلْكِتَٰبِ يَٰٓأَهْلَ

5፣68 እናንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! *”ተውራትንና ኢንጂልን ከጌታችሁም ወደ እናንተ የተወረደውን”* እስከምታቆሙ ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም» በላቸው። ۗ رَّبِّكُم مِّن إِلَيْكُم أُنزِلَ وَمَآ وَٱلْإِنجِيلَ ٱلتَّوْرَىٰةَ تُقِيمُوا۟ حَتَّىٰ شَىْءٍ عَلَىٰ لَسْتُمْ ٱلْكِتَٰبِ يَٰٓأَهْلَ قُلْ ٱلْكَٰفِرِينَ ٱلْقَوْمِ عَلَى تَأْسَ فَلَا ۗ وَكُفْرًا طُغْيَٰنًا رَّبِّكَ مِن إِلَيْكَ أُنزِلَ مَّآ مِّنْهُم كَثِيرًا وَلَيَزِيدَنَّ

29፣46 የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ። ከእነርሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር። በሉም *”በዚያ ወደ እኛ በተወረደው ወደ እናንተም በተወረደው”* አመንን። አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው። እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን። إِلَيْكُمْ وَأُنزِلَ إِلَيْنَا أُنزِلَ بِٱلَّذِىٓ ءَامَنَّا وَقُولُوٓا۟ ۖ مِنْهُمْ ظَلَمُوا۟ ٱلَّذِينَ إِلَّا أَحْسَنُ هِىَ بِٱلَّتِى إِلَّا ٱلْكِتَٰبِ أَهْلَ تُجَٰدِلُوٓا۟ وَلَا مُسْلِمُونَ لَهُۥ وَنَحْنُ وَٰحِدٌ وَإِلَٰهُكُمْ وَإِلَٰهُنَا

በተናጥል የመጽሐፉን ባለቤቶች የተባሉት አይሁዳውያን እንደሆኑ ይህ አንቀፅ ያስረዳል፡-

4፣153 የመጽሐፉ ሰዎች በነሱ ላይ ከሰማይ መጽሐፍን እንድታወርድ ይጠይቁሃል። ከዚያም የከበደን ነገር ሙሳን በእርግጥ ጠይቀዋል። «አላህንም በግልጽ አሳየን» ብለዋል። በበደላቸውም መብረቅ ያዘቻቸው። ከዚያም ተዓምራቶች ከመጡላቸው በኋላ ወይፈኑን አምላክ አድርገው ያዙ። ከዚያም ይቅር አልን። ሙሳንም ግልጽ ስልጣንን ሰጠነው። كِتَٰبًا عَلَيْهِمْ تُنَزِّلَ أَن ٱلْكِتَٰبِ أَهْلُ يَسْـَٔلُكَ

ٱلۡبَيِّنَٰتُ جَآءَتۡهُمۡ مَا بَعۡدِ مِنۢ ٱلۡعِجۡلَ ٱتَّخَذُواْ ثُمَّ ۚ بِظُلۡمِهِمۡ ٱلصَّٰعِقَةُ فَأَخَذَتۡهُمُ جَهۡرَةً ٱللَّهَ أَرِنَا فَقَالُوٓاْ ذَٰلِكَ مِن أَكۡبَرَ مُوسَىٰٓ سَأَلُواْ فَقَدۡ ۚ ٱلسَّمَآءِ مِّنَ مُّبِينٗا سُلۡطَٰنٗا مُوسَىٰ وَءَاتَيۡنَا ۚ ذَٰلِكَ عَن فَعَفَوۡنَا

በተናጥል የመጽሐፉን ባለቤቶች የተባሉት ክርስቲያኖች እንደሆኑ ይህ አንቀፅ ያስረዳል፦

4፥171 እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፡፡ በአላህም ላይ እውነትን እንጅ አትናገሩ፡፡ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ የአላህ መልክተኛ ወደ መርየም የጣላት «የኹን» ቃሉም ከእርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው፡፡ በአላህና በመልክተኞቹም እመኑ፡፡ «ሦስት ነው» አትበሉም፡፡ ተከልከሉ፤ ለእናንተ የተሻለ ይኾናልና፡፡ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው፡፡ ለእርሱ ልጅ ያለው ከመኾን የጠራ ነው፡፡ በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው፡፡ መመኪያም በአላህ በቃ። يَٰٓأَهۡلَ ٱلۡكِتَٰبِ لَا تَغۡلُواْ فِي دِينِكُمۡ وَلَا تَقُولُواْ عَلَى ٱللَّهِ إِلَّا ٱلۡحَقَّ ۚ عِيسَى ٱلۡمَسِيحُ إِنَّمَا ۚ مِّنۡهُ وَرُوحٞ مَرۡيَمَ ٱبۡنُ عِيسَى ٱلۡمَسِيحُ إِنَّمَا ۚ ٱلۡحَقَّ إِلَّا ٱللَّهِ عَلَى تَقُولُواْ وَلَا دِينِكُمۡ فِي فَـَٔامِنُواْ ۖ مِّنۡهُ وَرُوحٞ مَرۡيَمَ إِلَىٰ أَلۡقَىٰهَآ وَكَلِمَتُهُۥٓ ٱللَّهِ رَسُولُ مَرۡيَمَ ٱبۡنُ عِيسَى ٱلۡمَسِيحُ إِنَّمَا ۚ ٱلۡحَقَّ إِلَّا ٱللَّهِ عَلَى تَقُولُواْ وَلَا دِينِكُمۡ فِي ۖ ٱلۡأَرۡضِ فِي وَمَا ٱلسَّمَٰوَٰتِ فِي مَا لَهُۥ ۥ وَلَدٞ لَهُۥ يَكُونَ أَن سُبۡحَٰنَهُۥٓ ۖ وَٰحِدٌ إِلَٰهٞ ٱللَّهَ إِنَّمَا ۚ لَّكُمۡ خَيۡرٗا ٱنتَهُواْ ۚ ثَلَٰثَةٌ تَقُولُواْ وَلَا ۖ وَرُسُلِهِۦ وَكِيلٗا بِٱللَّهِ وَكَفَىٰ

ነብያችን”ﷺ” ከመጽሐፉ ሰዎች የምንሰማውን ሁሉ መቀበልና ማስተባበል እንደሌለብን ነግረውናል፤ ከተቀበልን የጨመሩት ጉዳይ ስላለ ጥሩ አይመጣም፤ ካስተባበልን መለኮታዊ ቅሪት ውስጡ ስላለው ጥሩ አይመጣም፦

ኢማም ቡኻሪይ መጽሐፍ 65 , ሐዲስ 4485:

አቢ ሁረይራህ”ረ.ዐ” እንደተረከው፤ የመጽሐፉ ሰዎች ተውራትን በዕብራይስጥ ያነቡ ነበር፤ ለሙስሊሙ ደግሞ በዐረቢኛ ያብራሩ ነበር፤ የአላህም መልእክተኛ”ﷺ” አሉ፦ “የመጽሐፉን ሰዎች አትመኗቸው፤ አታስተባብሏቸውም። ነገር ግን “በአላህ እና ወደ እኛ በተወረደው አመንን” በሉ። عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ـ رضى الله عنه ـ قَالَ كَانَ أَهْلُ الْكِتَابِ يَقْرَءُونَ التَّوْرَاةَ بِالْعِبْرَانِيَّةِ، وَيُفَسِّرُونَهَا بِالْعَرَبِيَّةِ لأَهْلِ الإِسْلاَمِ فَقَالَ رَسُولُ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم ” لاَ تُصَدِّقُوا أَهْلَ الْكِتَابِ وَلاَ تُكَذِّبُوهُمْ، وَقُولُوا {آمَنَّا بِاللَّهِ وَمَا أُنْزِلَ} الآيَةَ”

የመጻሐፉ ሰዎች አይሁድና ክርስቲያኖች የአላህን ንግግር ከሰው ንግግር ጋር በመቀላቀል መጨመር እና የአላህን ንግግር በመደበቅ አፖከራፉ አድርጎ ቀንሰዋል፦

3:71 የመጻሐፉ ሰዎች ሆይ! “እዉነቱን በዉሸት” ለምን *ትቀላቅላላችሁ*? “እዉነቱንም” እናንተ የምታወቁ ስትሆኑ ለምን *ትደብቃላችሁ*? يَٰٓأَهۡلَ ٱلۡكِتَٰبِ لِمَ تَلۡبِسُونَ ٱلۡحَقَّ بِٱلۡبَٰطِلِ وَتَكۡتُمُونَ وَأَنتُمۡ تَعۡلَمُونَ

“እውነት” የተባለው ከአላህ የወረደው ኪታብ ነው፦

34:48 ፦ጌታዬ “እውነትን” ያወርዳል፤ ሩቅ የኾኑትን ሚስጢሮች ሁሉ ዐዋቂ ነው በላቸው። قُلۡ إِنَّ رَبِّي يَقۡذِفُ بِٱلۡحَقِّ عَلَّٰمُ ٱلۡغُيُوبِ

“ውሸት” የተባለው ደግሞ የሰው ንግግር በእጆቻቸው ፅፈው «ይህ ከአላህ ዘንድ ነው» ብለው የቀጠፉት ጭማሬ ነው፦

2:79 ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት «ይህ ከአላህ ዘንድ ነው» ለሚሉ ወዮላቸው:: ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው:: ለነሱም ከዚያ ከሚያፈሩት ኃጢኣት ወዮላቸው:: يَكْتُبُونَ لِّلَّذِينَ فَوَيْلٌ يَكْسِبُونَ مِّمَّا لَّهُم وَوَيْلٌ أَيْدِيهِمْ كَتَبَتْ مِّمَّا لَّهُم فَوَيْلٌ ۙ قَلِيلًا بِهِۦ لِيَشْتَرُوا۟ ٱللَّهِ عِندِ مِنْ هَٰذَا يَقُولُونَ ثُمَّ بِأَيْدِيهِمْ ٱلْكِتَٰبَ

የነብያችን""ቅርብ ባልደረባ ኢብኑ ዓባስ"ረ.አ." የሱረቱል በቀራ 2:79 አንቀጽ ሲፈስረው እንዲህ ይላል:-

ኢማም ቡኻሪይ መጽሐፍ 52, ሐዲስ 46:

ኢብኑ አባስ ሲናገር:- ሙስሊሞች ሆይ ለምን የመጽሐፉ ሰዎችን ትጠይቃላችሁ? በተመሳሳይ መጽሐፋችሁ ከአላህ ዘንድ ለነቢዩ የተወረደው ወቅታቂ ንግግርና የምትቀሩት እያለ? መጽሐፉ አልተበረዘምን? አላህ ለእናንተ የመጽሐፉ ሰዎች በእጆቻቸው በርዘው «ይህ ከአላህ ዘንድ ነው» እንደሚሉ አውርዷል። عَبْدِ بْنِ اللَّهِ عُبَيْدِ عَنْ شِهَابٍ، ابْنِ عَنِ يُونُسَ، عَنْ اللَّيْثُ، حَدَّثَنَا بُكَيْرٍ، بْنُ يَحْيَى حَدَّثَنَا صلى نَبِيِّهِ عَلَى أَنْزَلَ الَّذِي وَكِتَابُكُمُ الْكِتَابِ، أَهْلَ تَسْأَلُونَ كَيْفَ الْمُسْلِمِينَ، مَعْشَرَ يَا قَالَ ـ عنهما الله رضى ـ عَبَّاسٍ ابْنِ عَنِ عُتْبَةَ، بْنِ اللَّهِ هُوَ فَقَالُوا الْكِتَابَ، بِأَيْدِيهِمُ وَغَيَّرُوا اللَّهُ كَتَبَ مَا بَدَّلُوا الْكِتَابِ أَهْلَ أَنَّ اللَّهُ حَدَّثَكُمُ وَقَدْ يُشْبَ، لَمْ تَقْرَءُونَهُ بِاللَّهِ، الأَخْبَارِ أَحْدَثُ وسلم عليه الله أُنْزِلَ الَّذِي عَنِ يَسْأَلُكُمْ قَطُّ رَجُلاً مِنْهُمْ رَأَيْنَا مَا وَاللَّهِ وَلاَ مُسَاءَلَتِهِمْ، عَنْ الْعِلْمِ مِنَ جَاءَكُمْ مَا يَنْهَاكُمْ أَفَلاَ قَلِيلاً ثَمَنًا بِهِ لِيَشْتَرُوا اللَّهِ، عِنْدِ مِنْ عَلَيْكُمْ.

የመጽሐፉ ሰዎች ጋር ያሉት መጽሐፍት ሙሉ ለሙሉ እውነትን ነው ብለን እንደማንቀበል ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ሐሰት ነው ብለን አናስተባብልም፤ ቁርአን ከወረደበት ግብና አላማ፣ ፋይዳና ሚና አንጹ ከእነርሱ ጋር ያለውን መለኮታዊ እውነት ለማረጋገጥ እና ቀጥፈው የጨመሩትን ሐሰት ሊያርም ነው፤ ከእነርሱ ጋር ያለውን እውነትን ስለሚያረጋግጥ "ሙሰዲቃን" مُصَدِّقًا "አረጋጋጭ" ሲባል፤ የሰዎች ንግግር የገቡበትን በማረሙ ደግሞ "ሙሃይሚን" مُهَيْمِنًا "አራሚ" correcter" ወይም "ተቆጣጣሪ"supervisor" የሚል ስም አለው:-

5:48 ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ "አረጋጋጭ" እና በእርሱ ላይ "ተጠባባቂ" ሲሆን በእውነት አወረድን፤ عَلَيْهِ وَمُهَيْمِنًا ٱلْكِتَٰبِ مِنَ يَدَيْهِ بَيْنَ لِّمَا مُصَدِّقًا بِٱلْحَقِّ ٱلْكِتَٰبَ إِلَيْكَ وَأَنزَلْنَآ

ቁርአን ከእርሱ በፊት ወደ ነብያት የተወረደውን የሚያረጋግጥ እና በውስጡ ያለውን የሚዘረዝር ሲሆን ከዓለማቱ ጌታ የተወረደ ነው:-

10፥37 ይህም ቁርአን ከአላህ ሌላ ከሆነ ፍጡር የተቀጠፈ ሊሆን አይገባውም:: ግን ያንን *"ከእርሱ በፊት ያለውን"* የሚያረጋግጥ እና *"በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን የሚዘረዝር"* በእርሱ ጥርጣሬ የሌለበት ሲሆን ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው:: هَٰذَا كَانَ وَمَا ٱلْعَٰلَمِينَ رَّبِّ مِن فِيهِ رَيْبَ لَا ٱلْكِتَٰبِ وَتَفْصِيلَ يَدَيْهِ بَيْنَ ٱلَّذِى تَصْدِيقَ وَلَٰكِن ٱللَّهِ دُونِ مِن يُفْتَرَىٰ أَن ٱلْقُرْءَانُ

ከአላህ ዘንድ ወደ ነብያት የወረዱት መጽሐፍት በውስጡ የነበረውን የትምህርት ጭብጥ ቁርአን በመዘርዘር ያረጋግጣል፤ ካረጋገጠው ጭብጥ ለናሙና ያክል ወደ ነብያቱን ሲያወርድ የነበረው ወሐይ በዐቂዳህ ነጥብ:- "እነሆ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም" ማለትን ሲሆን በፊቅህ ነጥብ ደግሞ "መልካም ሥራዎችን መሥራትን፣ ሶላትንም መስገድን፣ ዘካንም መስጠትን" ነው:-

16፥2 ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ መላእክትን ከራእይ ጋር በፈቃዱ ያወርዳል ከሓዲዎችን በቅጣት አስጠንቅቁ፤ *"እነሆ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ፍሩኝም"* ማለትን አስታውቁ በማለት ያወርዳል። لُ يُنَزِّ ٱلْمَلَٰٓئِكَةَ بِٱلرُّوحِ مِنْ أَمْرِهِۦ عَلَىٰ مَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦٓ أَنْ أَنذِرُوٓا۟ فَٱتَّقُونِ أَنَا۠ إِلَٰهَ لَآ أَنَّهُۥ

21፥73 *"ወደ እነርሱም መልካም ሥራዎችን መሥራትን፣ ሶላትንም መስገድን፣ ዘካንም መስጠትን አወረድን"*። فِعْلَ إِلَيْهِمْ وَأَوْحَيْنَآ ٱلزَّكَوٰةِ وَإِيتَآءَ ٱلصَّلَوٰةِ وَإِقَامَ ٱلْخَيْرَٰتِ

ክፍል ሁለት

5፥5 ዛሬ መልካሞች ሁሉ ለእናንተ ተፈቀዱ። *የእነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ ያረዱት ለእናንተ የተፈቀደ ነው። ምግባችሁም ለእነሱ የተፈቀደ ነው*። ከምእመናት ጥብቆቹም *ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት ሴቶች ጥብቆቹም፤ ዘማዊዎችና የምስጢር ወዳጅ ያዢዎች ሳትኾኑ ጥብቆች ኾናችሁ መህሮቻቸውን በሰጣችኋቸው ጊዜ ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው*። ከእምነትም የሚመለስ ሰው በእርግጥ ሥራው ተበላሸ። በመጨረሻም ቀን እርሱ ከከሳሪዎቹ ነው። ٱلطَّيِّبَٰتُ لَكُمُ أُحِلَّ ٱلْيَوْمَ إِذَآ قَبْلِكُمْ مِن ٱلْكِتَٰبَ أُوتُوا۟ ٱلَّذِينَ مِنَ وَٱلْمُحْصَنَٰتُ ٱلْمُؤْمِنَٰتِ مِنَ وَٱلْمُحْصَنَٰتُ ۖ لَّهُمْ حِلٌّ وَطَعَامُكُمْ لَّكُمْ حِلٌّ ٱلْكِتَٰبَ أُوتُوا۟ ٱلَّذِينَ وَطَعَامُ ۖ ٱلْخَٰسِرِينَ مِنَ ٱلْءَاخِرَةِ فِى وَهُوَ عَمَلُهُۥ حَبِطَ فَقَدْ بِٱلْإِيمَٰنِ يَكْفُرْ وَمَن ۚ أَخْدَانٍ مُتَّخِذِىٓ وَلَا مُسَٰفِحِينَ غَيْرَ مُحْصِنِينَ أُجُورَهُنَّ ءَاتَيْتُمُوهُنَّ

አምላካችን አላህ በእርሱ ላይ ሌሎች ማንነትንና ምንነትን የሚያጋሩ ሙሽሪኮችን እንዳናገባ እና ከእርሱ ስም ውጪ በሌላ ፍጡር ስም ተባርኮ የታረደን እርድ እንዳንበላ ከልክሏል፦

2፥221 *አጋሪ የሆኑ ሴቶች እስከሚያምኑ ድረስ አታግቡዋቸው*። ከአጋሪይቱ ምንም ብትደንቃችሁም እንኳ ያመነችው ባሪያ በእርግጥ በላጭ ናት። *ለአጋሪዎቹም እስከሚያምኑ ድረስ አትዳሩላቸው*። ከአጋሪው ጌታ ምንም ቢደንቃችሁ ምእምኑ ባሪያ በላጭ ነው። *እነዚያ አጋሪዎች ወደ እሳት ይጣራሉ። አላህም በፈቃዱ ወደ ገነትና ወደ ምሕረት ይጠራል*። ሕግጋቱንም ለሰዎች ይገልጻል እነርሱ ሊገሰጹ ይከጀላልና። تُنكِحُوا۟ وَلَا ۚ أَعْجَبَتْكُمْ وَلَوْ مُّشْرِكَةٍ مِّن خَيْرٌ مُّؤْمِنَةٌ وَلَأَمَةٌ ۚ يُؤْمِنَّ حَتَّىٰ ٱلْمُشْرِكَٰتِ تَنكِحُوا۟ وَلَا بِإِذْنِهِۦ وَٱلْمَغْفِرَةِ ٱلْجَنَّةِ إِلَى يَدْعُوٓا۟ وَٱللَّهُ ۖ ٱلنَّارِ إِلَى يَدْعُونَ أُو۟لَٰٓئِكَ ۗ أَعْجَبَكُمْ وَلَوْ مُّشْرِكٍ مِّن خَيْرٌ مُّؤْمِنٌ وَلَعَبْدٌ ۚ يُؤْمِنُوا۟ حَتَّىٰ ٱلْمُشْرِكِينَ يَتَذَكَّرُونَ لَعَلَّهُمْ لِلنَّاسِ ءَايَٰتِهِۦ وَيُبَيِّنُ ۖ

6፥121 *በእርሱም ላይ የአላህ ስም ካልተጠራበት ነገር አትብሉ*። እርሱም በእርግጥ አመጽ ነው። ሰይጣናትም ወደ ወዳጆቻቸው በክትን በመብላት ይከራከሯችሁ ዘንድ ያሾከሹካሉ። *ብትታዘዙዋቸውም እናንተ በእርግጥ አጋሪዎች ናችሁ*። لَمْ مِمَّا تَأْكُلُوا۟ وَلَا لَمُشْرِكُونَ إِنَّكُمْ أَطَعْتُمُوهُمْ وَإِنْ ۗ لِيُجَٰدِلُوكُمْ أَوْلِيَآئِهِمْ إِلَىٰٓ لَيُوحُونَ ٱلشَّيَٰطِينَ وَإِنَّ ۗ لَفِسْقٌ وَإِنَّهُۥ عَلَيْهِ ٱللَّهِ ٱسْمُ يُذْكَرِ

"ሺርክ" شِرْك የሚለው ቃል "አሽረከ" أَشْرَكَ ማለትም "አጋራ" ከሚል ግስ የመጣ ሲሆን "ማጋራት" ማለት ነው፤ የሚያጋራው ሰው ደግሞ "ሙሽሪክ" مُشْرِك ማለትም "አጋሪ" ይባላል፤ እንዲሁ በአላህ ላይ የሚያጋሩት ማንነትና ምንነት "ሽሪክ" شِرْك ማለትም "ተጋሪ" ይባላሉ፤ ከአህለል ኪታብ ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም ከነሳራዎች አበይት የሚባሉት ሙሽሪኪን ናቸው፦

5፤72 *እነዚያ «አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው» ያሉ በእርግጥ ካዱ*። አልመሲህም አለ፦ «የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ።» *እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በእርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ*።

መኖሪያውም እሳት ናት:: ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም:: يَا الْمَسِيحُ وَقَالَ ۖ مَرْيَمَ ابْنُ الْمَسِيحُ هُوَ اللَّهَ إِنَّ قَالُوا الَّذِينَ كَفَرَ لَقَدْ أَنصَارٍ مِنْ لِلظَّالِمِينَ وَمَا ۖ النَّارُ وَمَأْوَاهُ الْجَنَّةَ عَلَيْهِ اللَّهُ حَرَّمَ فَقَدْ بِاللَّهِ يُشْرِكْ مَن إِنَّهُ ۖ وَرَبَّكُمْ رَبِّي اللَّهَ اعْبُدُوا إِسْرَائِيلَ بَنِي

እነዚያ «አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው» ያሉ በእርግጥ ካዱ፤ እነሆ ይህ ንግግራቸው ማጋራት ነውና አላህ በእርሱ ላይ የሚያጋራ ነኝትን በእርግጥ እርም አደረገ፤ መኖሪያውም እሳት ናት:: ይህ ጥቅላዊ መልእክት "ሙጅመል" مجمل ወይም "ዓም" عام ይባላል፤ ነገር ግን አላህ ከሙሽሪኪን አህለል ኪታቦችን በተናጥል "ሙፈሰል" مُفَصَّل ወይም "ኻስ" خاص በማድረግ ለያቸው፤ ይህም ሙሽሪኪን እና አህለል ኪታብ በሚሉ ቃላት መካከል "ወ" ማለትም "እና" የሚል መስተጻምር አስቀምጧል፡-

98፥1 እነዚያ ከመጽሐፉ ባለቤቶች እና ከአጋሪዎቹም የካዱት ግልጹ አስረጅ እስከ መጣላቸው ድረስ ተወጋጆች አልነበሩም:: يَكُنِ لَمْ الْبَيِّنَةُ تَأْتِيَهُمْ حَتَّىٰ مُنفَكِّينَ وَالْمُشْرِكِينَ الْكِتَابِ أَهْلِ مِنْ كَفَرُوا الَّذِينَ

"በእርሱም ላይ የአላህ ስም ካልተጠራበት ነገር አትብሉ" የሚለው "ዓም" عام ሆኖ ከመጣ በኃላ "የእነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ ያረዱት ለእናንተ የተፈቀደ ነው" "ኻስ" خاص ሆኖ እንደመጣ ኢብኑ ዐባሥ"ረ.ዐ" ተናግሯል፡-

ሱነን አቢ ዳውድ :መጽሐፍ 16, ሐዲስ 30

ኢብኑ ዐባሥ"ረ.ዐ" እንደተናገረው፡- 6፥118 "የአላህ ስም በእርሱ ላይ ከተወሳበት እንስሳ ብሉ" የሚለው አንቀጽ እና 6፥116 "በእርሱም ላይ የአላህ ስም ካልተጠራበት ነገር አትብሉ" የሚለው አንቀጽ ኢስቲስናዕ በመሆን "የእነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ ያረዱት ለእናንተ የተፈቀደ ነው" በሚለው ተነሥኻል" ابْنِ عَنِ ،عَبَّاسٍ قَالَ { عَلَيْهِ اللَّهِ اسْمُ ذُكِرَ مِمَّا فَكُلُوا } وَلاَ { لَهُمْ حِلٌّ وَطَعَامُكُمْ لَكُمْ حِلٌّ الْكِتَابَ أُوتُوا الَّذِينَ وَطَعَامُ } فَقَالَ ذَلِكَ مِنْ وَاسْتَثْنَى فَنُسِخَ { عَلَيْهِ اللَّهِ اسْمُ يُذْكَرِ لَمْ مِمَّا تَأْكُلُوا } .

ይህንን ሪዋያህ ሼኹል አልባኒ ሐሠን ነው ብለውታል፤ "ወኢሥተስና" وَاسْتَثْنَى የሚለው ይሰመርበት፤ "ኢሥቲስናዕ" اِسْتِثْنَاء ማለት "ግድባዊ ቃል"Exceptional word" ነው፤ ከዚህ ሐዲስ የምረዳው አምላካችን አላህ ከጥቅላዊ መልእክት ተናጥሏዊ መልእክት ይህንን አንቀጽ ማውረዱ ነው፡-

5፥5 ዛሬ መልካሞች ሁሉ ለእናንተ ተፈቀዱ:: *የእነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ ያረዱት ለእናንተ የተፈቀደ ነው:: ምግባችሁም ለእነሱ የተፈቀደ ነው*:: ከምእመናት ጥብቆቹም *ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት ሴቶች ጥብቆቹም፤ ዘማዊዎችና የምስጢር ወዳጅ ያዢዎች ሳትኾኑ ጥብቆች ኾናችሁ መህሮቻቸውን በሰጣችኋቸው ጊዜ ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው*:: ከእምነትም የሚመለስ ሰው በእርግጥ ሥራው ተበላሸ:: በመጨረሻም ቀን እርሱ ከከሳሪዎቹ ነው:: ٱلطَّيِّبَٰتُ لَكُمُ أُحِلَّ ٱلْيَوْمَ إِذَآ قَبْلِكُمْ مِن ٱلْكِتَٰبَ أُوتُواْ ٱلَّذِينَ مِنَ وَٱلْمُحْصَنَٰتُ ٱلْمُؤْمِنَٰتِ مِنَ وَٱلْمُحْصَنَٰتُ ۖ لَّهُمْ حِلٌّ وَطَعَامُكُمْ لَّكُمْ حِلٌّ ٱلْكِتَٰبَ أُوتُواْ ٱلَّذِينَ وَطَعَامُ ۖ ٱلْخَٰسِرِينَ مِنَ ٱلْءَاخِرَةِ فِى وَهُوَ عَمَلُهُۥ حَبِطَ فَقَدْ بِٱلْإِيمَٰنِ يَكْفُرْ وَمَن ۚ أَخْدَانٍ مُتَّخِذِىٓ وَلَا مُسَٰفِحِينَ غَيْرَ مُحْصِنِينَ أُجُورَهُنَّ ءَاتَيْتُمُوهُنَّ

አላህ ለሙስሊም ወንድ ከአህለል ኪታብ ሴትን የፈቀደበት ሂክማ ሴት በቀጥታ ሙስሊም ቤት ስለምትገባ ነው፤ በተቃራኒው ሴት ሙስሊም ወንድ ካፊርን ማግባት ያልፈቀደበት ሴቷ ሙስሊም ሙሽሪክ ቤት ስለምትገባ ነው።

ክፍል ሦስት

1፥7 የእነዚያን በእነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን፣ በእነርሱ ላይ *"ያልተቆጣህባቸውን እና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ ምራን"*፤ በሉ። ٱلضَّآلِّينَ وَلَا عَلَيْهِمْ ٱلْمَغْضُوبِ غَيْرِ عَلَيْهِمْ أَنْعَمْتَ ٱلَّذِينَ صِرَٰطَ

በክፍል ሁለት በሙሽሪክ እና በአህለል ኪታብ "ኢሥቲስናዕ" ٱسْتِثْنَاء ማለት "ግድባዊ ቃል"Exceptional word" በመሆን ስለ "ዓም" عام ማለትም "ጥቅላዊ መልእክት" እና ስለ "ኻስ" خاص ማለትም "ተናጥሏዊ መልእክት" አይተን ነበር፤ ይህ አንደኛው የዐሊሞቻችን እይታ"dimension" ነው፤ ስለ አህለል ኪታብ ሁለተኛው የዐሊሞቻችን እይታ" ደግሞ "ሢያቅ" سِيَاق ማለትም "አውዳዊ መልእክት"context" ነው። ይህንን እስቲ ነጥብ በነጥብ እንመልከት፦

ነሳራ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፤

አምላካችን አላህ ለዒሳ ወንጌልን ሰጠው፤ በዚያ ወንጌል ውስጥ፦ "የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ" የሚል መመሪያ አለ፦ 5፥46 በፊለጎቻቸውም ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን፣ አስከተልን፤ *ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሣጭ ሲሆን ሰጠነው*። وَنُورٌ هُدًى فِيهِ ٱلْإِنجِيلَ وَءَاتَيْنَٰهُ ۖ ٱلتَّوْرَىٰةِ مِنَ يَدَيْهِ بَيْنَ لِّمَا مُصَدِّقًا مَرْيَمَ ٱبْنِ بِعِيسَى ءَاثَٰرِهِم عَلَىٰٓ وَقَفَّيْنَا لِّلْمُتَّقِينَ وَمَوْعِظَةً وَهُدًى ٱلتَّوْرَىٰةِ مِنَ يَدَيْهِ بَيْنَ لِّمَا وَمُصَدِّقًا

5፥48 የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ *አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ*፤ فِيهِ ٱللَّهُ أَنزَلَ بِمَآ ٱلْإِنجِيلِ أَهْلُ وَلْيَحْكُمْ

"ቀፈይና" قَفَّيْنَا ማለትም "አስከተልን" እና "አተይናሁ" ءَاتَيْنَاهُ ማለትም "ሰጠነው" የሚሉት ያለቁ አላፊ ግስ ናቸው፤ "ልየሕኩም" ۟لْيَحْكُمْ ማለትም "ይፍረዱ" የሚለው ትዕዛዛዊ ግስ መነሻ ላይ "ወ" ﻭ ማለትም "እና" የሚል አያያዥ መስተጻምር አለ፤ ያ ማለት "ይፍረዱ" የሚለው ትዕዛዛዊ ግስ "አስከተልን" እና "ሰጠነው" ከሚሉት ግስ ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑ "አልን" የሚል ሙስጠጢር ማለትም ህቡዕ ግስ‘’headen verb‘’ አላፊ ሆኖ መጥቷል፣ ስለዚህ ‘’የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ አልን‘’ የሚል ፍቺ ይኖረዋል። ተፍሲሩል ጀላለይን በዚህ መልኩ ነው የፊሰረው፤ ለናሙና ያክል ሌላ ተጨማሪ ጥቅስ ብንመለከት ነገሩን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል፦

19:12 የሕያ ሆይ! መጽሐፉን በጥብቅ *ያዝ*፣ ጥበብንም በሕጻንነቱ *ሰጠነዉ*። صَبِيًّا ٱلْحُكْمَ وَءَاتَيْنَٰهُ ۖ بِقُوَّةٍ ٱلْكِتَٰبَ خُذِ يَٰيَحْيَىٰ

"ሁዚ" خُذِ ማለትም "ያዝ" የሚለቅ ትዕዛዛዊ ግስ ነው፤ "አተይናሁ" ءَاتَيْنَاهُ ማለትም "ሰጠነው" የሚለው ቃል ደግሞ ያለቀ አላፊ ግስ ነዉ፣ "አተይናሁ" ከሚለው ቃል በፊት "ወ" ﻭ ማለትም "እና" የሚል አያያዥ መስተጻምር አለ፤ ያ ማለት "ያዝ" የሚለው ትዕዛዛዊ ግስ "ሰጠነው" ከሚለው ግስ ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑ "አልን" የሚል ሙስጠጢር አላፊ ሆኖ መጥቷል፣ ስለዚህ ‘’መጽሐፉን በጥብቅ ያዝ አልነዉ‘‘’ የሚል ፍቺ እንደሚኖረው ሁሉ ከላይ ያለውንም በዚህ ሒሳብ እንረዳዋለን።

አምላካችን አላህ የኢንጅል ባለቤቶችን ከነበሩት ከዒሳ ቀዳማይ ጋር የከበደ ኪዳን አድርጓል፦

5፥14 ከእነዚያም እኛ *ክርስቲያኖች* ነን ካሉት የጠበቀ ቃል ኪዳናቸውን ያዝን፡፡ *በእርሱም ከታዘዙበት ነገር ፈንታን ተውት*፡፡ ስለዚህ እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ *በመካከላቸው ጠብንና ጥላቻን ጣልንባቸው*፡፡ አላህም ይሠሩት የነበሩትን ሁሉ በእርግጥ ይነግራቸዋል፡፡ ۚ الْقِيَامَةِ يَوْمِ إِلَىٰ وَالْبَغْضَاءَ الْعَدَاوَةَ بَيْنَهُمُ فَأَغْرَيْنَا بِهِ ذُكِّرُوا مِمَّا حَظًّا فَنَسُوا مِيثَاقَهُمْ أَخَذْنَا نَصَارَىٰ إِنَّا قَالُوا الَّذِينَ وَمِنَ يَصْنَعُونَ كَانُوا بِمَا اللَّهُ يُنَبِّئُهُمُ وَسَوْفَ

"ክርስቲያኖች" ተብሎ የተቀመጠው ቃል "ነሳራ" نَصَارَىٰ ነው፤ "ነስራኒይ" نَصْرَانِيّ የሚለው ቃል በነጠላ ሲሆን በብዜት ደግሞ "ነሳራ" نَصَارَىٰ ነው፤ ይህም ቃል "ነሰረ" نَصَرَ ማለትም "ረዳ" ከሚል ግስ መደብ ወይም "ነስር" نَصْر ማለትም "እርዳታ" ከሚል ከስም መደብ የረባ ሲሆን ቋንቋዊው ፍቺው "ረዳቶች" ማለት ነው። "ነሲር" نَصِير ወይም "ናሲር" نَاصِر ማለትም "እረዳት"፣ "መንሱር" مَنصُور ማለትም "የተረዳ"፣ "ሙንተሲር" مُنتَصِر ማለትም "ተረጂ" የሚሉት ቃላት ልክ እንደ "ነሳራ" ቃል "ነሰረ" ከሚል ግስ መደብ ወይም "ነስር" ከሚል የስም መደብ የረቡ ናቸው፤ ይህ ስም በቁርኣን 15 ጊዜ ተውስቷል፤ እነዚህ የአላህ እና የመልእክተኛ የዒሳ እረዳቶች ሐዋርያት ናቸው፡-

60፥14 እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የመርየም ልጅ ዒሳ ለሐዋርያቶቹ «ወደ አላህ *ረዳቴ* ማነው?» እንዳለ ሐወርያቶቹም «እኛ የአላህ *ረዳቶች* ነን» እንዳሉት የአላህ ረዳቶች ኹኑ፡፡ ከእስራኤልም ልጆች አንደኛዋ ጭፍራ አመነች፡፡ ሌላይቱም ጭፍራ ካደች፡፡ እነዚያን ያመኑትንም በጠላታቸው ላይ አበረታናቸው፤ አሸናፊዎችም ኾኑ፡፡ ٱبْنُ عِيسَى قَالَ كَمَا ٱللَّهِ أَنصَارَ كُونُوا۟ ءَامَنُوا۟ ٱلَّذِينَ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ فَأَيَّدْنَا ۖ طَّآئِفَةٌ وَكَفَرَت إِسْرَٰٓءِيلَ بَنِىٓ مِّنۢ طَّآئِفَةٌ فَـَٔامَنَت ۖ ٱللَّهِ أَنصَارُ نَحْنُ ٱلْحَوَارِيُّونَ قَالَ ۖ ٱللَّهِ إِلَى أَنصَارِىٓ مَنْ لِلْحَوَارِيِّـۧنَ مَرْيَمَ ظَٰهِرِينَ فَأَصْبَحُوا۟ عَدُوِّهِمْ عَلَىٰ ءَامَنُوا۟

3፥52 ዒሳ ከእነርሱ ክህደት በተሰማውም ጊዜ፡- «ወደ አላህ *ረዳቶቼ* እነማን ናቸው» አለ፤ ሐዋርያት፡- «እኛ የአላህ *ረዳቶች* ነን፤ በአላህ አምነናል፤ እኛም ትክክለኛ ታዛዦች መኾናችንን መስክር» አሉ፡፡ ٱللَّهِ إِلَى أَنصَارِىٓ مَنْ قَالَ ٱلْكُفْرَ مِنْهُمُ عِيسَىٰ أَحَسَّ فَلَمَّآ مُسْلِمُونَ بِأَنَّا وَٱشْهَدْ بِٱللَّهِ ءَامَنَّا ٱللَّهِ أَنصَارُ نَحْنُ ٱلْحَوَارِيُّونَ قَالَ ۖ

አላህ ከእነዚህ የእርሱ እና የመልእክተኛ እረዳቶች ጋር የከበደ ቃል ኪዳን አድርጓል፤ ይህምም ቃል ኪዳን "በእኔ እና በመልክተኛዬ እመኑ» በማለት አዟል፤ አነዚህ የዒሳ ሐዋርያትም ይህንን ቃል አምነው ሙስሊሞች መሆናቸውን አስመስክረዋል፡-

5፥11 ወደ *ሐዋርያትም* «በእኔ እና በመልክተኛዬ እመኑ» *በማለት ባዘዝኩ* ጊዜ አስታውስ፡፡ *«አመንን፤ እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክር»* አሉ፡፡ مُسْلِمُونَ بِأَنَّنَا وَٱشْهَدْ ءَامَنَّا قَالُوٓا۟ وَبِرَسُولِى بِى ءَامِنُوا۟ أَنْ ٱلْحَوَارِيِّـۧنَ إِلَى أَوْحَيْتُ وَإِذْ

3:52 ዒሳ ከእነርሱ ክሕደት በተሰማዉም ጊዜ ፡-ወደ አላህ *ረዳቶቼ እነማን ናቸዉ? አለ፤ ሐዋሪያት ፡ -እኛ የአላህ ረዳቶች ነን፤ በአላህም አምነናል፤ እኛም ትክክለኛ ”ታዛዦች”* መሆናችንን፥ መስክር፥ አሉ። ٱللَّهِ إِلَى أَنصَارِىٓ مَنْ قَالَ ٱلْكُفْرَ مِنْهُمُ عِيسَىٰ أَحَسَّ فَلَمَّآ ۖ

ነገር ግን ከሐዋርያት ህልፈት በኃላ ያሉት ነስራኒይዎች በእርሱም ከታዘዙት ፈንታ ትተው በአላህ ላይ በመቅጠፍ "ሦስት ነው" በማለት ወሰን አልፈዋል፡-

4፥171 እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፡፡ በአላህም ላይ እውነትን እንጅ አትናገሩ፡፡..... *ሦስት ነው* አትበሉም፡፡ ተከልከሉ፤ ለእናንተ የተሻለ ይኾናልና፡፡ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው፡፡ تَقُولُوا۟ وَلَا دِينِكُمْ فِى تَغْلُوا۟ لَا ٱلْكِتَٰبِ يَٰٓأَهْلَ ثَلَٰثَةٌ تَقُولُوا۟ وَلَا ۖ وَرُسُلِهِۦ بِٱللَّهِ فَـَٔامِنُوا۟ ۖ مِّنْهُ وَرُوحٌ مَرْيَمَ إِلَىٰ أَلْقَىٰهَآ وَكَلِمَتُهُۥٓ ٱللَّهِ رَسُولُ مَرْيَمَ ٱبْنُ عِيسَى ٱلْمَسِيحُ إِنَّمَا ۚ ٱلْحَقَّ إِلَّا ٱللَّهِ عَلَى وَكِيلًا بِٱللَّهِ وَكَفَىٰ ۗ ٱلْأَرْضِ فِى وَمَا ٱلسَّمَٰوَٰتِ فِى مَا لَّهُۥ ۘ وَلَدٌ لَهُۥٓ يَكُونَ أَن سُبْحَٰنَهُۥٓ ۖ وَٰحِدٌ إِلَٰهٌ ٱللَّهَ إِنَّمَا ۚ لَّكُمْ خَيْرًا ٱنتَهُوا۟ ۚ

አላህ የኢየሱስን ቀዳማይ ተከታይ በእነዚያ ኢየሱስን በካዱት አይሁዳውያን ላይ ሲያበልጣቸው በተቃራኒው በሁለተኛው ክፍለ-ዘመን ያሉት ተከታዮቹ ግን አላህ ያልተናገረውን ምንኩስና የእርሱን ውዴታ ለመጠበቅ ሲሉ ፈጠሯት፡-

3፥55 አላህም ባለ ጊዜ አስታውስ፡፡ ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጂህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ፡፡ ከነዚያም ከካዱት ሰዎች አጥሪህ ነኝ *እነዚያንም የተከተሉህን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ከነዚያ ከካዱት በላይ አድራጊ ነኝ*፡፡ مِنَ وَمُطَهِّرُكَ إِلَيَّ وَرَافِعُكَ مُتَوَفِّيكَ إِنِّي عِيسَىٰ يَا اللَّهُ قَالَ إِذْ الْقِيَامَةِ يَوْمِ إِلَىٰ كَفَرُوا الَّذِينَ فَوْقَ اتَّبَعُوكَ الَّذِينَ وَجَاعِلُ كَفَرُوا الَّذِينَ

57፥27 ከዚያም በዱካዎቻቸው ላይ መልክተኞቻችንን አስከታተልን፡፡ የመርየምን ልጅ ዒሳንም አስከተልን፡፡ ኢንጂልንም ሰጠነው፡፡ *በእነዚያም በተከተሉት ልቦች ውሰጥ መለዘብንና እዝነትን፣ አዲስ የፈጠሩዋትንም ምንኩስና አደረግን፡፡ በእነርሱ ምንኩስናን አልጻፍናትም፡፡ ግን የአላህን ውዴታ ለመፈለግ ሲሉ ፈጠሩዋት፡፡ ተገቢ አጠባበቋንም፤ አልጠበቋትም*፡፡ ከእነርሱም ለእነዚያ ላመኑት ምንዳቸውን ሰጠናቸው፡፡፡ ከእነርሱም ብዙዎቹ አመጸኞች ናቸው፡፡ مَرْيَمَ ابْنِ بِعِيسَى وَقَفَّيْنَا بِرُسُلِنَا ءَاثَارِهِم عَلَىٰ قَفَّيْنَا ثُمَّ حَقَّ رَعَوْهَا فَمَا اللَّهِ رِضْوَانِ ابْتِغَاءَ إِلَّا عَلَيْهِمْ كَتَبْنَاهَا مَا ابْتَدَعُوهَا وَرَهْبَانِيَّةً وَرَحْمَةً رَأْفَةً اتَّبَعُوهُ الَّذِينَ قُلُوبِ فِي وَجَعَلْنَا الْإِنجِيلَ وَءَاتَيْنَاهُ فَاسِقُونَ مِّنْهُمْ وَكَثِيرٌ ۖ أَجْرَهُمْ مِنْهُمْ ءَامَنُوا الَّذِينَ فَآتَيْنَا ۖ رِعَايَتِهَا

ከዒሳ ተከታዮች ብዙዎቹ አመጸኞች ናቸው፤ ነገር ግን አላህ ከእነርሱም ለእነዚያ ላመኑት ምንዳቸውን ሰጣቸው፤ በእነርሱ ላይ ቁርአን በሚነበብላቸውም ጊዜ «በእርሱ አምነናል፡፡ እርሱ ከጌታችን የኾነ እውነት ነው፤ እኛ ከእርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን» ይላሉ፡-

28፥52 እነዚያ ከእርሱ በፊት መጽሐፍን የሰጠናቸው እነርሱ *በእርሱ ያምናሉ*፡፡ يُؤْمِنُونَ بِهِ هُم قَبْلِهِ مِن الْكِتَابَ آتَيْنَاهُمُ الَّذِينَ

28፥53 በእነርሱ ላይ በሚነበብላቸውም ጊዜ «በእርሱ አምነናል፡፡ እርሱ ከጌታችን የኾነ እውነት ነው፡፡ *እኛ ከእርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን*» ይላሉ፡፡ مُسْلِمِينَ قَبْلِهِ مِن كُنَّا إِنَّا رَبِّنَا مِن الْحَقُّ إِنَّهُ بِهِ آمَنَّا قَالُوا عَلَيْهِمْ يُتْلَىٰ وَإِذَا

ልብ አድርግ "እኛ ከእርሱ ማለትም ከቁርአን መውረድ በፊት ሙስሊም ነበርን" ማለታቸው ምክንያታዊ ነው፤ ሙስሊም" مُسْلِم ትርጉሙ "አቢድ" عَابِدٌ ማለትም "አምላኪ" አሊያም "ቃኒት" قَانِتٍ ማለትም "ታዛዥ" ማለት ነው። እንደሚታወቀው ከመጽሐፉ ሰዎች ብዙዎቹ አመጸኞች ናቸው፤ አይሁዳውያን አላህ የተቆጣባቸው ሲሆኑ ክርስቲያኖች ደግሞ የተሳቱተት ናቸው፡-

ጃምዒ አት-ተርሚዚ መጽሐፍ 47, ሐዲስ 3212

ዐዲይ ኢብኑ ሓቲም እንደተረከው ነብዩም"ﷺ" አሉ፡- አይሁዳውያን የተቆጣባቸው ናቸው፤ ክርስቲያኖች የተሳቱተት ናቸው። عَنْ ضُلاَّلٌ وَالنَّصَارَى عَلَيْهِمْ مَغْضُوبٌ الْيَهُودُ " قَالَ وسلم عليه الله صلى النَّبِيِّ عَنِ حَاتِمٍ، بْنِ عَدِيِّ " .

ነገር ግን ከአይሁዳውያን ጥቂት ያልተቆጣቸው፤ እንዲሁ ከክርስቲያኖች ጥቂት ያልተሳሳቱ ነበሩ፤ እኛም ከመንገዱ እንዳንስት የእነዚያን በእነርሱ ላይ በጎ የዋለላቸውን መንገድ ምራን ብለን እንቀራለን፡-

1፥7 የእነዚያን በእነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን፣ በእነርሱ ላይ *"ያልተቆጣህባቸውን እና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ ምራን"*፤ በሉ። ٱلضَّآلِّينَ وَلَا عَلَيْهِمْ ٱلْمَغْضُوبِ غَيْرِ عَلَيْهِمْ أَنْعَمْتَ ٱلَّذِينَ صِرَٰطَ

ኢማም ቡኻርይ : መጽሐፍ 65, ሐዲስ 4475

አቢ ሁረይራህ”ረ.ዐ.” እንደተረከው የአላህ መልእክተኛ”” አሉ፦ "ኢማሙ፦ "ያልተቆጣህባቸውን እና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ ምራን” ባለ ጊዜ አሚን በሉ፤ غَيْرِ} الإِمَامُ قَالَ إِذَا " قَالَ وسلم عليه الله صلى اللَّهِ رَسُولَ أَنَّ ـ عنه الله رضى ـ هُرَيْرَةَ أَبِي عَنْ الْمَغْضُوبِ وَلاَ عَلَيْهِمْ الضَّالِّينَ} قُولُوا فَ آمِينَ.

"አሚን" آمين ማለት ተስማምቻለው "ይሁን" "ይደረግ" ማለት ነው፤ አላህ ሆይ! " ያልተቆጣህባቸውን እና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ ምራን፤ አሚን።

የኢስራኢል ልጆች

አምላካችን አላህ ኢብራሂም ጣዖታውያንን እና የሚያመልኩትን በራቀ ጊዜ እርሱን እና ሉጥንም ወደዚያች፤ በውስጧ ለዓለማት በረከትን ወደ አደረግንባት ወደ ሻም ምድር ወሰደው፤ በዚያ ቦታ ለእርሱም ኢስሐቅን ልጅ ያዕቆብንም የልጅ ልጅ አድርጎ ሰጠው፤ ሁሉንም መልካሞች እና ነቢይ አደረጋቸው፦

21፥71 እርሱን እና ሉጥንም ወደዚያች፤ *በውስጧ ለዓለማት በረከትን ወደ አደረግንባት ምድር በመውሰድ አዳን*። وَلُوطًا وَنَجَّيْنَاهُ لِلْعَالَمِينَ فِيهَا بَارَكْنَا الَّتِي الْأَرْضِ إِلَى

21፥72 *ለእርሱም ኢስሐቅን ያዕቆብንም ተጨማሪ አድርገን ሰጠነው። ሁሉንም መልካሞች አደረግን*። وَيَعْقُوبَ إِسْحَاقَ لَهُ وَوَهَبْنَا صَالِحِينَ جَعَلْنَا وَكُلًّا ۖ نَافِلَةً

19፥49 *እነርሱንና ከአላህ ሌላ የሚያመልኩትን በራቀ ጊዜ *ለእርሱ ኢስሐቅንና ያዕቆብን ሰጠነው። ሁሉንም ነቢይ አደረግንም*። نَبِيًّا جَعَلْنَا وَكُلًّا ۖ وَيَعْقُوبَ إِسْحَٰقَ لَهُ وَهَبْنَا ٱللَّهِ دُونِ مِن يَعْبُدُونَ وَمَا ٱعْتَزَلَهُمْ فَلَمَّا

"የዕቁብ" يَعْقُوبُ የሚለው ስም 16 ጊዜ በቁርአን የተወሳ ሲሆን ያዕቁብም ልጆቹን እናንተ “ሙስሊሞች” ኾናችሁ እንጂ አትሙቱ» አላቸው፤ እነርሱም አምላክህንና የአባቶችህን የኢብራሂምን የኢስማዒልንና የኢስሐቅንም አምላክ አንድ የኾነውን አምላክ እኛ ለእርሱ ፍፁም “ታዛዦች” አሉ፦

2:132 በእርሷም በሕግጋቲቱ ኢብራሂም ልጆቹን አዘዘ። ያዕቁብም እንደዚሁ ልጆቹን አዘዘ። «ልጆቼ ሆይ! አላህ ለእናንተ ሃይማኖትን መረጠ፤ ስለዚህ እናንተ *”ሙስሊሞች”* ኾናችሁ እንጂ አትሙቱ» አላቸው። إِنَّ بَنِيَّ وَيَعْقُوبُ بَنِيهِ إِبْرَٰهِۦمُ بِهَا وَوَصَّىٰ مُّسْلِمُونَ وَأَنتُم إِلَّا تَمُوتُنَّ فَلَا ٱلدِّينَ لَكُمُ ٱصْطَفَىٰ ٱللَّهَ

2:133 ያዕቁብን ሞት በመጣበት ጊዜ ለልጆቹ ከእኔ በኋላ ማንን ታመልካላችሁ? ባለ ጊዜ ቀራቢዎች ነበራችሁን? እነርሱም አምላክህንና የአባቶችህን የኢብራሂምን የኢስማዒልንና የኢስሐቅንም አምላክ አንድ የኾነውን አምላክ እኛ ለእርሱ ፍፁም *”ታዛዦች”* ኾነን እናመልካለን አሉ። مُسْلِمُونَ لَهُۥ وَنَحْنُ وَٰحِدًا إِلَٰهًا وَإِسْمَٰعِيلَ وَإِسْحَٰقَ وَءَابَآئِكَ إِبْرَٰهِۦمَ إِلَٰهَ نَعْبُدُ قَالُوا بَعْدِى مِنۢ تَعْبُدُونَ مَا لِبَنِيهِ قَالَ إِذْ ٱلْمَوْتُ يَعْقُوبَ حَضَرَ إِذْ شُهَدَآءَ كُنتُمْ أَمْ وَإِلَٰهَ

የየዕቁብ ሌላው ስሙ "ኢስራኢል" ነው፤ ይህንን አምላካችን አላህ፦ "እስራኤል በራሱ ላይ እርም ካደረገው" በማለት ይነግረናል፦

3፥93 ተውራት ከመወረድዋ በፊት *እስራኤል በራሱ ላይ እርም ካደረገው ነገር በስተቀር ምግብ ሁሉ ለእስራኤል ልጆች የተፈቀደ ነበር*:: እውነተኞችም እንደኾናችሁ ተውራትን አምጡ አንብቡዋትም በላቸው:: حَرَّمَ مَا إِلَّا إِسْرَائِيلَ لِّبَنِي حِلًّا كَانَ الطَّعَامِ كُلُّ ۗ التَّوْرَاةُ تُنَزَّلَ أَن قَبْلِ مِن نَفْسِهِ عَلَىٰ إِسْرَائِيلُ صَادِقِينَ كُنتُمْ إِن فَاتْلُوهَا بِالتَّوْرَاةِ فَأْتُوا قُلْ ۖ

"ኢሥራኢል" إِسْرَائِيل ማለት የሁለት ቃላት ውቅር ነው፤ ሁለቱ ቃላት "ኢሥራ" إِسْرَا እና "ኢል" ئِيل ናቸው፤ "ኢሥራ" إِسْرَا የሚለው ቃል "ሣረ" سَارَ ማለትም "ተጓዘ" እና "አሥራ" أَسْرَىٰ ማለትም "አስጓዘ" ከሚል ግስ የመጣ ሲሆን "ሠያራህ" سَيَّارَة ማለትም "ተጓዥ" ማለት ነው፤ "ሠይር" سَيْر ማለት "ጉዞ" ማለት መሆኑ አንባቢ ልብ ይለዋል፤ "ኢል" ئِيل ማለት ደግሞ "ኢላህ" إِلَٰه ማለትም "አምላክ" ማለት ነው፤ "ኢሥራኢል" ማለት "በአምላክ ምሪት ተጓዥ" ማለት ነው፤ ይህ ስም 43 ጊዜ ተወስቷል፤ የዕቁብ ከሻም ምድር ወደ ምስር ማለትን ወደ ግብጽ ምድር በልጁ በዩሱፍ ምክያት ተጉዟል፦

12፥93 «ይህንን ቀሚሴን ይዛችሁ ሊዱ:: *በአባቴ ፊትም ጣሉት የሚያይ ሆኖ ይመጣልና:: ቤተሰቦቻችሁንም ሰብስባችሁ አምጡልኝ*» አላቸው:: أَجْمَعِينَ بِأَهْلِكُمْ وَأْتُونِي بَصِيرًا يَأْتِ أَبِي وَجْهِ عَلَىٰ فَأَلْقُوهُ هَٰذَا بِقَمِيصِي اذْهَبُوا

12፥99 በዩሱፍ ላይም በገቡ ጊዜ ወላጆቹን ወደ እርሱ አስጠጋቸው:: «በአላህም ፈቃድ ጥበቆች ስትኾኑ *ምስርን ግቡ*» አላቸው:: آمِنِينَ اللَّهُ شَاءَ إِن مِصْرَ ادْخُلُوا وَقَالَ أَبَوَيْهِ إِلَيْهِ آوَىٰ يُوسُفَ عَلَىٰ دَخَلُوا فَلَمَّا

በመቀጠል አላህ ሙሳን መጽሐፉን ሰጠው፤ ለእስራኤልም ልጆች መሪ አደረገው፤ "ከእኔ ሌላ መጠጊያን አትያዙ" አላቸው፦

17፥2 *ሙሳንም መጽሐፉን ሰጠነው:: ለእስራኤልም ልጆች መሪ አደረግነው*:: "ከእኔ ሌላ መጠጊያን አትያዙ" አልናቸውም:: وَكِيلًا دُونِي مِن تَتَّخِذُوا أَلَّا إِسْرَائِيلَ لِّبَنِي هُدًى وَجَعَلْنَاهُ الْكِتَابَ مُوسَى وَآتَيْنَا

አላህ ከእስራኤልን ልጆች የጠበቀ ቃል ኪዳን በእርግጥ ያዘ፤ ከእነርሱም በየዕቁብ ልጆች ልክ ዐስራ ሁለትን አለቆች አስነሳ፤ ይህም የከበደ ኪዳን፦ "አላህን እንጂ ሌላን አታምልኩ፤ በወላጆችም በጎን ሥራ አድርጉ፤ በዝምድና ባለቤቶችም፣ በየቲሞችም፣ በምስኪኖችም በጎ ዋሉ፤ ለሰዎችም መልካምን ተናገሩ፤ ሶላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ፤ ዘካንም ስጡ" የሚል ነበር፦

5፥12 *አላህም የእስራኤልን ልጆች የጠበቀ ቃል ኪዳን በእርግጥ ያዘባቸው:: ከእነርሱም ዐስራ ሁለትን አለቆች አስነሳን*:: أَخَذَ وَلَقَدْ نَقِيبًا عَشَرَ اثْنَيْ مِنْهُمُ وَبَعَثْنَا إِسْرَائِيلَ بَنِي مِيثَاقَ اللَّهُ

2፥83 *የእስራኤል ልጆችንም ጥብቅ ኪዳን አላህን እንጂ ሌላን አታምልኩ፤ በወላጆችም በጎን ሥራ አድርጉ፤ በዝምድና ባለቤቶችም፣ በየቲሞችም፣ በምስኪኖችም በጎ ዋሉ፤ ለሰዎችም መልካምን ተናገሩ፤ ሶላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ፤ ዘካንም ስጡ በማለት በያዝንባቸው ጊዜ አስታውሱ*:: ከዚያም ከእናንተ ጥቂቶች ሲቀሩ ሸሻችሁ እናንተም ኪዳንን የምትተዉ ናችሁ:: أَخَذْنَا وَإِذْ وَآتُوا الصَّلَاةَ وَأَقِيمُوا حُسْنًا لِلنَّاسِ وَقُولُوا وَالْمَسَاكِينِ وَالْيَتَامَىٰ الْقُرْبَىٰ وَذِي إِحْسَانًا وَبِالْوَالِدَيْنِ اللَّهَ إِلَّا تَعْبُدُونَ لَا إِسْرَائِيلَ بَنِي مِيثَاقَ مُّعْرِضُونَ وَأَنتُم مِّنكُمْ قَلِيلًا إِلَّا تَوَلَّيْتُمْ ثُمَّ الزَّكَاةَ

በመቀጠል አላህ የእስራኤልንም ልጆች ባሕሩን አሻገራቸው:: ለእነርሱ በኾኑ ጣዖታት መገዛት ላይ በሚዘወትሩ ሕዝቦች ላይ አለፉም፦

7፥138 *የእስራኤልንም ልጆች ባሕሩን አሻገርናቸው፡፡ ለእነርሱ በኾኑ ጣዖታት መገዛት ላይ በሚዘወትሩ ሕዝቦች ላይ አለፉም*፡፡ «ሙሳ ሆይ፡- *ለእነርሱ አማልክት እንደ ሏቸው ለእኛም አምላክን አድርግልን*» አሉት፡፡ «እናንተ የምትሳሳቱ ሕዝቦች ናችሁ፤» አላቸው፡፡ قَالَ ۚ اَلِهَةٌ لَهُمْ كَمَا إِلَـٰهًا لَّنَا اجْعَل مُوسَى يَا قَالُوا ۚ لَّهُمْ أَصْنَامٍ عَلَىٰ يَعْكُفُونَ قَوْمٍ عَلَىٰ فَأَتَوْا الْبَحْرَ إِسْرَائِيلَ بِبَنِي وَجَاوَزْنَا تَجْهَلُونَ قَوْمٌ إِنَّكُمْ

በሻም ምድር የሚኖሩትን ደካሞች የነበሩትን ሕዝቦችና በውስጧ በረከት ያደረገባትን የሻም ምድር ምሥራቆችዋንም ምዕራቦቿንም አወረሳቸው፡-

7፥137 *እነዚያንም ደካሞች የነበሩትን ሕዝቦች ያችን በውስጧ በረከት ያደረግንባትን ምድር ምሥራቆችዋንም ምዕራቦቿንም አወረስናቸው፡፡ የጌታህም መልካሚቱ ቃል በእስራኤል ልጆች ላይ በመታገሳቸው ተፈጸመች*፡፡ ፈርዖንና ሰዎቹም ይሠሩት የነበረውን ሕንጻ ዳስ ያደርጉትም የነበረውን አፈረስን፡፡ بَارَكْنَا الَّتِي وَمَغَارِبَهَا الْأَرْضِ مَشَارِقَ كَانُوا الَّذِينَ الْقَوْمَ وَأَوْرَثْنَا يَعْرِشُونَ كَانُوا وَمَا وَقَوْمُهُ فِرْعَوْنُ يَصْنَعُ كَانَ مَا وَدَمَّرْنَا ۖ صَبَرُوا بِمَا إِسْرَائِيلَ بَنِي عَلَىٰ الْحُسْنَىٰ رَبِّكَ كَلِمَتُ وَتَمَّتْ ۖ فِيهَا

የጌታህም መልካሚቱ ቃል በእስራኤል ልጆች ላይ በመታገሳቸው ተፈጸመች፤ አላህ ለእስራኤል ልጆችም መጽሐፍንና ሕግን፣ ነቢይነትንም በእርግጥ ሰጣቸው፡፡ ከመልካም ሲሳዮችም ለገሳቸው፤ ጣዖታት መገዛት ላይ በሚዘወትሩ ሕዝቦች እና ደካሞች በነበሩትን በሻም ሕዝቦች ላይ አበለጣቸው፡-

46፥15 *ለእስራኤል ልጆችም መጽሐፍንና ሕግን፣ ነቢይነትንም በእርግጥ ሰጠናቸው፡፡ ከመልካም ሲሳዮችም ለገስንላቸው፡፡ በዓለማት ላይም አበለጥናቸው*፡፡ الْعَالَمِينَ عَلَى وَفَضَّلْنَاهُمْ الطَّيِّبَاتِ مِّنَ وَرَزَقْنَاهُم وَالنُّبُوَّةَ وَالْحُكْمَ الْكِتَابَ إِسْرَائِيلَ بَنِي آتَيْنَا وَلَقَدْ

ቁርኣን በሚወርድበት ጊዜ አንዱን አምላክ ብቻ የሚያመልኩ የእስራኤል ልጆች ነበሩ፤ “ዋሒድ” وَاحِد ማለት “አንድ” ማለት ሲሆን “ተውሒድ” تَوْحِيد ማለት ደግሞ “አንድነት” ማለት ነው፤ በአላህ አንድነት የሚያምን ሰው “ሙዋሒድ” مُوَحِّد ይባላል፤ የተውሒድ እሳቤ በእኛ እና በመጽሐፉ ባለቤቶች መካከል ትክክል የኾነች የጋራ ቃል ናት፤ ከበመጽሐፉ ባለቤቶች በእነርሱ ላይ ቁርኣን በሚነበብላቸውም ጊዜ «በእርሱ አምነናል፡፡ እርሱ ከጌታችን የኾነ እውነት ነው፤ እኛ ከእርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን» ይላሉ፡-

28፥52 እነዚያ ከእርሱ በፊት መጽሐፍን የሰጠናቸው እነርሱ *በእርሱ ያምናሉ*፡፡ يُؤْمِنُونَ بِهِ هُم قَبْلِهِ مِن الْكِتَابَ آتَيْنَاهُمُ الَّذِينَ

28፥53 በእነርሱ ላይ በሚነበብላቸውም ጊዜ «በእርሱ አምነናል፡፡ እርሱ ከጌታችን የኾነ እውነት ነው፡፡ *እኛ ከእርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን*» ይላሉ፡፡ مُسْلِمِينَ قَبْلِهِ مِن كُنَّا إِنَّا رَبِّنَا مِن الْحَقُّ إِنَّهُ بِهِ آمَنَّا قَالُوا عَلَيْهِمْ يُتْلَىٰ وَإِذَا

ልብ አድርግ “እኛ ከእርሱ ማለትም ከቁርአን መውረድ በፊት ሙስሊም ነበርን” ማለታቸው ምክንያታዊ ነው፤ ሙስሊም” مُسْلِم ትርጉሙ “አቢድ” عَابِد ማለትም “አምላኪ” አሊያም “ቃኒት” قَانِت ማለትም “ታዛዥ” ማለት ነው።

መደምደሚያ

ነገር ግን ከሙሳ እና ዒሳ ተከታዮች ብዙዎቹ አመጸኞች ናቸው፤ ነገር ግን አላህ ከእነርሱም ለእነዚያ ላመኑት ምንዳቸውን ሰጣቸው፤ በእነርሱ ላይ ቁርአን በሚነበብላቸውም ጊዜ «በእርሱ አምነናል፡፡ እርሱ ከጌታችን የኾነ እውነት ነው፤ እኛ ከእርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን» ይላሉ፡-

28፥52 እነዚያ ከእርሱ በፊት መጽሐፍን የሰጠናቸው እነርሱ *በእርሱ ያምናሉ*፡፡ يُؤْمِنُونَ بِهِ هُم قَبْلِهِ مِن الْكِتَابَ آتَيْنَاهُمُ الَّذِينَ

28፥53 በእነርሱ ላይ በሚነበብላቸውም ጊዜ «በእርሱ አምነናል፡፡ እርሱ ከጌታችን የኾነ እውነት ነው፡፡ *እኛ ከእርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን*» ይላሉ፡፡ مُسْلِمِينَ قَبْلِهِ مِن كُنَّا إِنَّا رَّبِّنَا مِن الْحَقُّ إِنَّهُ بِهِ آمَنَّا قَالُوا عَلَيْهِمْ يُتْلَىٰ وَإِذَا

ልብ አድርግ “እኛ ከእርሱ ማለትም ከቁርአን መውረድ በፊት ሙስሊም ነበርን” ማለታቸው ምክንያታዊ ነው፤ ሙስሊም” مُسْلِم ትርጉሙ “አቢድ” عَابِدُ ማለትም “አምላኪ” አሊያም “ቃኒት” قَانِتِ ማለትም “ታዛዥ” ማለት ነው። እንደሚታወቀው ከመጽሐፉ ሰዎች ብዙዎቹ አመጸኞች ናቸው፤ አይሁዳውያን አላህ የተቆጣባቸው ሲሆኑ ክርስቲያኖች ደግሞ የተሳቱተት ናቸው፡-

ጃምዒ አት-ተርሚዚ መጽሐፍ 47, ሐዲስ 3212

ዐዲይ ኢብኑ ሓቲም እንደተረከው ነብዩም”ﷺ” አሉ፡- አይሁዳውያን የተቆጣባቸው ናቸው፤ ክርስቲያኖች የተሳቱተት ናቸው። عَنْ ضُلاَّلٌ وَالنَّصَارَى عَلَيْهِمْ مَغْضُوبٌ الْيَهُودُ “ قَالَ وسلم عليه الله صلى النَّبِيِّ عَنِ حَاتِمٍ، بْنِ عَدِيِّ ” .

ነገር ግን ከአይሁዳውያን ጥቂት ያልተቆጣባቸው፤ እንዲሁ ከክርስቲያኖች ጥቂት ያልተሳሳቱ ነበሩ፤ እኛም ከመንገዱ እንዳንስት የእነዚያን በእነርሱ ላይ በጎ የዋለላቸውን መንገድ ምራን ብለን እንቀራለን፡-

1፥7 የእነዚያን በእነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን፣ በእነርሱ ላይ *”ያልተቆጣህባቸውን እና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ ምራን”*፤ በሉ። ٱلضَّآلِّينَ وَلَا عَلَيْهِمْ ٱلْمَغْضُوبِ غَيْرِ عَلَيْهِمْ أَنْعَمْتَ ٱلَّذِينَ صِرَٰطَ

ኢማም ቡኻርይ : መጽሐፍ 65, ሐዲስ 4475

አቢ ሁረይራህ”ረ.ዐ.” እንደተረከው የአላህ መልእክተኛ”ﷺ” አሉ፡- "ኢማሙ፡- "ያልተቆጣህባቸውን እና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ ምራን” ባለ ጊዜ አሚን በሉ፤ غَيْرِ } الإِمَامُ قَالَ إِذَا " قَالَ وسلم عليه الله صلى اللَّهِ رَسُولَ أَنَّ ـ عنه الله رضى ـ هُرَيْرَةَ أَبِي عَنْ آمِينَ فَقُولُوا {الضَّالِّينَ وَلاَ عَلَيْهِمْ الْمَغْضُوبِ.

ስለዚህ ከመጽሐፉ ሰዎች በተውሒድ ያሉትን የኢስራኢል ልጆች እና ነሳራዎች ያረዱትን መብላትን እና በሃላል ሴቶቻቸውን ማግባት ተፈቅዷል፡- 5፥5 ዛሬ መልካሞች ሁሉ ለእናንተ ተፈቀዱ፡፡ *የእነዚያም መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች ምግብ ያረዱት ለእናንተ የተፈቀደ ነው፡፡ ምግባችሁም ለእነሱ የተፈቀደ ነው*፡፡ ከምእመናት ጥበቆቹም *ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት ሴቶች ጥበቆቹም፤ ዘማዊዎችና የምስጢር ወዳጅ ያዢዎች ሳትኾኑ ጥበቆች ኾናችሁ መህሮቻቸውን በሰጣችኋቸው ጊዜ ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው*፡፡ مِنَ وَٱلْمُحْصَنَٰتُ ۖ لَّهُمْ حِلٌّ وَطَعَامُكُمْ لَّكُمْ حِلٌّ ٱلطَّيِّبَٰتُ لَكُمُ أُحِلَّ ٱلْيَوْمَ ۖ ٱلَّذِينَ وَطَعَامُ ٱلْكِتَٰبَ أُوتُواْ ٱلَّذِينَ مِنَ وَٱلْمُحْصَنَٰتُ ٱلْمُؤْمِنَٰتِ مِن وَٱلْمُحْصَنَٰتُ ۚ أُجُورَهُنَّ ءَاتَيْتُمُوهُنَّ إِذَآ قَبْلِكُمْ مِن ٱلْكِتَٰبَ أُوتُواْ ٱلَّذِينَ مِنَ مُسَٰفِحِينَ غَيْرَ مُحْصِنِينَ أُجُورَهُنَّ ءَاتَيْتُمُوهُنَّ إِذَآ قَبْلِكُمْ مِن ٱلْكِتَٰبَ أُوتُواْ ٱلَّذِينَ مِنَ وَٱلْمُحْصَنَٰتُ ٱلْمُؤْمِنَٰتِ يَكْفُرْ وَمَن ۚ أَخْدَانٍ مُتَّخِذِى وَلَا مُسَٰفِحِينَ غَيْرَ مُحْصِنِينَ أُجُورَهُنَّ ءَاتَيْتُمُوهُنَّ إِذَآ قَبْلِكُمْ مِن ٱلْكِتَٰبَ أُوتُواْ ٱلَّذِينَ مِنَ وَٱلْمُحْصَنَٰتُ ٱلْمُؤْمِنَٰتِ ٱلْخَٰسِرِينَ مِنَ ٱلْـَٔاخِرَةِ فِى وَهُوَ عَمَلُهُۥ حَبِطَ فَقَدْ بِٱلْإِيمَٰنِ

"መጽሐፍን የተሰጡት" በሚለው ቃል መነሻ ቅጥያ ላይ "ሚን" مِنَ ማለትም "ከ" የሚል መስተዋድድ አለ፤ ያ የሚያሳየው ከአህለል ኪታብ መካከል ያሉትን ያላሻረኩ፣ የፍጡር ስም ሳይሆን የአላህን ስም ብቻ የሚጠሩ እና ከዝሙት ብልቶቻቸውን ጥብቆች የሆኑ ሴቶች ማግባት ሙባህ ነው። ይህ ሁለተኛው እይታ ነው። ሁለቱም እይታዎች ቁርአናዊ ናቸው፤ መርጦ መቀበል የግል ምርጫ ነው።

✍ከወንድም ወሒድ ዑመር

ወሰላሙ አለይኩም

2.ቅዱሱ መንፈስ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።።

16፥102 እነዚያን ያመኑትን ለማረጋጋት ሙስሊሞቹንም ለመምራትና ለማብሰር *ቁርአንን ቅዱሱ መንፈስ እውነተኛ ሲኾን ከጌታህ አወረደው* በላቸው።። لِلْمُسْلِمِينَ وَبُشْرَىٰ وَهُدًى آمَنُوا الَّذِينَ لِيُثَبِّتَ بِالْحَقِّ رَّبِّكَ مِن الْقُدُسِ رُوحُ نَزَّلَهُ قُلْ

"ሩሑል ቁዱስ" رُوحُ الْقُدُسِ ማለት "ቅዱሱ መንፈስ" ማለት ሲሆን ቁርአን ላይ "ሩሑል ቅዱስ" የሚለው ቃል 4 ጊዜ ተጠቅሷል፤ ሚሽነሪዎች፡- "እናንተ ቁርአናችሁን አትቀበሉትም እንጂ አላህ ታማኝ መንፈስ ወይም ቅዱስ መንፈስ ነው ይላል" ብለው በጥራዝ ነጠቅ መረጃ ከራሳቸው እሳቤ ጋር ለማጣጣም ይሞክራሉ፤ ይህንን ስሁት ሙግት ድባቅ ለማስገባት በኢስላም ስለ ቅዱስ መንፈስ ያለውን እሳቤ ጥልልና ጥንፍፍ አድርገን ኢንሻላህ እናያለን፡-

መላእክት እና መንፈሱ

ሚሽነሪዎች ቅዱሱ መንፈስ ከመላእክት "ወ" وَ ማለትም "እና" በሚል መስተጻምር ተቀምጧል፤ ስለዚህ ከመላእክት የተለየ ደግሞ ፈጣሪ ነው የሚል ስሁት ሙግት ያቀርባሉ፡-

97፥4 በእርሷ ውስጥ *መላእክት እና መንፈሱ* በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ይወርዳሉ።። مِّن رَبِّهِم بِإِذْنِ فِيهَا وَالرُّوحُ الْمَلَائِكَةُ تَنَزَّلُ أَمْرٍ كُلِّ

78፥38 *መንፈሱና መላእክቶቹም* የተሰለፉ ኾነው በሚቆሙ ቀን አል-ረሕማን ለእርሱ የፈቀደለትና ትክክለኛን ቃል ያለ ሰው ቢኾን እንጅ መነጋገርን አይችሉም።። صَوَابًا وَقَالَ الرَّحْمَٰنُ لَهُ أَذِنَ مَنْ إِلَّا يَتَكَلَّمُونَ لَا ۖ صَفًّا وَالْمَلَائِكَةُ الرُّوحُ يَقُومُ يَوْمَ

70፥4 *መላእክቱና መንፈሱም* ልኩ አምሳ ሺሕ ዓመት በኾነ ቀን ውስጥ ወደ እርሱ ያርጋሉ።። يَوْمٍ فِي إِلَيْهِ وَالرُّوحُ الْمَلَائِكَةُ تَعْرُجُ سَنَةٍ أَلْفَ خَمْسِينَ مِقْدَارُهُ كَانَ

ልብ አድርግ መንፈሱ ከመላእክት ጋር በጌታ አላህ ፈቃድ የሚወርድ እና ወደ አላህ የሚያርግ የሚያርግ ከሆነ የሚወርደውና የሚያርገው ቅዱስ መንፈስ እና አላህ ይለያያሉ። በተጨማሪም "ወ" ተብሎ በመስተጻምር መቀመጡ እልቅናና ክብርን ያመለክታል እንጂ ቅዱስ መንፈስ መልአክ አለመሆኑ መረጃ አይሆንም። ለምሳሌ ሱረቱል ፋቲሓህ ከቁርአን "እና" በሚል መስተጻም ተለይቷል፡-

15፥87 *ከሚደጋገሙ የኾኑን ሰባትን እና ታላቁንም ቁርአን በእርግጥ ሰጠንህ*።። الْعَظِيمَ وَالْقُرْآنَ الْمَثَانِي مِّنَ سَبْعًا آتَيْنَاكَ وَلَقَدْ

የሚደጋገሙ ሰባት አንቀጾች ሱረቱል ፋቲሓህ ከቁርአን "እና" በሚል መለየቱ ሱረቱል ፋቲሓህ ክብር ያላት ሱራ መሆኗን ለማሳየት እንጂ ቁርአን አለመሆኗ እንደማያሳይ ሁሉ በተመሳሳይም ቅዱስ መንፈስ ከመላእክት ክብር መኖሩን ያሳያል እንጁ መልአክ አለመሆኑን አያሳይም፤ እሩቅ ሳንሄድ ጂብሪልና ሚካኤል ከመላእክት "ወ" በሚል መስተዋድድ ተነጥለዋል፤ ያ ማለት ጂብሪልና ሚካኤል መላእክት አይደሉም ማለት አይደለም፡-

2፥98 ለአላህና ለመላእክቱ ለመልክተኞቹም ለጂብሪልም ለሚካልም ጠላት የኾነ ሰው አላህ ለእነዚህ ከሓዲዎች ጠላት ነው።። مَن لِّلْكَافِرِينَ عَدُوٌّ اللَّهَ فَإِنَّ وَمِيكَالَ وَجِبْرِيلَ وَرُسُلِهِ وَمَلَائِكَتِهِ لِّلَّهِ عَدُوًّا كَانَ

66፥4 በእርሱም ላይ ብትረዳዱ አላህ እርሱ ረዳቱ ነው:: *ጂብሪልም ከምእምናንም መልካሙ ከዚህም በኋላ መላእክቱ* ረዳቶቹ ናቸው:: ذَٰلِكَ بَعْدَ وَالْمَلَائِكَةُ ۖ الْمُؤْمِنِينَ وَصَالِحُ وَجِبْرِيلُ مَوْلَاهُ هُوَ اللَّهَ فَإِنَّ عَلَيْهِ تَظَاهَرَا وَإِن ۖ قُلُوبُكُمَا صَغَتْ فَقَدْ اللَّهِ إِلَىٰ تَتُوبَا إِن ظَهِيرٌ

ለምሳሌ፦ "ሚካኤል እና መላእክቱ" ተብሎ ሚካኤል ከመላእክት "እና" በሚል መነጠሉ ሚካኤል መልአክ አልነበረም ማለት አይደለም፦ ራእይ 12፥7 በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ *ሚካኤል እና መላእክቱ* ዘንዶውን ተዋጉ።

"ታማኙ መንፈስ"

ይህ ቅዱስ መንፈስ ከጌታ አላህ ቁርአንን ማውረዱ በራሱ ቅዱስ መንፈስ ከአላህ ተለይቶ ተቀምጧል፦

16፥102 እነዚያን ያመኑትን ለማረጋጋት ሙስሊሞቹንም ለመምራትና ለማብሰር *ቁርአንን ቅዱሱ መንፈስ እውነተኛ ሲኾን ከጌታህ አወረደው* በላቸው:: لِلْمُسْلِمِينَ وَبُشْرَىٰ وَهُدًى آمَنُوا الَّذِينَ لِيُثَبِّتَ بِالْحَقِّ رَّبِّكَ مِن الْقُدُسِ رُوحُ نَزَّلَهُ قُلْ

“ረቢከ” رَّبِّكَ ማለትም “ጌታህ” ከሚለው ቃል መነሻ ቅጥያ ላይ “ሚን” مِن ማለትም “ከ” የሚል መስተዋድድ አለ፤ ይህ የሚያሳየው ታማኙ መንፈስ ከነብያችን”ﷺ” ጌታ ከአላህ በታማኝነት ቁርአንን እንዳወረደው ነው፦

26፥193 እርሱን *ታማኙ መንፈስ* አወረደው፤ الْأَمِينُ الرُّوحُ بِهِ نَزَلَ

ቅዱስ መንፈስ የዙፋኑ ባለቤት በሆነው በአላህ ዘንድ የእርሱ ባለሟል ነው፤ የአላህ ታማኝ መልእክተኛ ነው፦

81፥20 የጎይል ባለቤት በዙፋኑ ባለቤት ዘንድ *ባለሟል* የኾነ:: مَكِينٍ ٱلْعَرْشِ ذِى عِندَ قُوَّةٍ ذِى

81፥21 በዚያ ስፍራ ትእዛዙ ተሰሚ፤ *ታማኝ የኾነ ነው*:: أَمِينٍ ثَمَّ مُّطَاعٍ

ቅዱስ መንፈስ “ባለሟል” እና “ታማኝ” መባሉ በራሱ ላኪ እንዳለው ያሳያል፤ ይህም ታማኝ መንፈስ መልእክተኛ ተብሏል፦

19፥17 ከእነሱም መጋረጃን አደረጉች:: *መንፈሳችንምም ወደ እርሷ ላከን*:: ለእርሷም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰለላት:: فَاتَّخَذَتْ سَوِيًّا بَشَرًا لَهَا فَتَمَثَّلَ رُوحَنَا إِلَيْهَا فَأَرْسَلْنَا حِجَابًا دُونِهِمْ مِن

19፥19 «እኔ ንጹሕን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ *የጌታሽ መልክተኛ ነኝ*» አላት:: زَكِيًّا غُلَامًا لَكِ لِأَهَبَ رَبِّكِ رَسُولُ أَنَا إِنَّمَا قَالَ

"መልእክተኛ" ከሆነ ላኪው አላህ ነው፤ ስለዚህ ቅዱስ መንፈስ ፈጣሪ አይደለም፤ አላህ ይህንን ቅዱስ መንፈስ ለእልቅናና ለክብር ወደራሱ በማስጠጋት በአገናዛቢ ቃል "መንፈሳችን" ይለዋል፤ ይህ ቅዱስ መንፈስ ደግሞ መለኮት እንዳልሆነ የምንረዳው የራሱ ጌታ አለው፤ ይህም ጌታው አላህ ነው፤ ነብያችን"ﷺ" ወደ አላህ በሩኩዕና በሡጁድ ጊዜ አላህን "የመላእክትና የመንፈስ ጌታ" ብለው ጠርተውታል፦

ኢማም ሙስሊም መጽሐፍ 4, ሐዲስ 253

ዓኢሻህ"ረ.ዐ." እንደተረከችው የአላህ መልእክተኛ"ﷺ" ሩኩዕና ሡጁድ ላይ፡- "ጥራት የሚገባህ ቅዱስ የመላእክት እና የሩሕ ጌታ" ይሉ ነበር። " وَالرُّوحِ الْمَلاَئِكَةِ رَبُّ قُدُّوسٌ سُبُّوحٌ " وَسُجُودِهِ رُكُوعِهِ فِي يَقُولُ كَانَ وسلم عليه الله صلى اللَّهِ رَسُولَ أَنَّ نَبَّأَتْهُ عَائِشَةَ، أَنَّ

"ማበረታቻ"

አምላካችን አላህ በዚህ ቅዱስ መንፈስ ሰዎችን ያበረታል፤ ማበረታቻው ቅዱስ መንፈሱ ከሆነ የሚያበረታታው አላህ ከሆነ አላህ እና ቅዱስ መንፈሱ ይለያያሉ፡-

2፥87 ሙሳንም መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው፡፡ ከበኋላውም መልክተኞችን አስከታተልን፡፡ የመርየምን ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው፡፡ *በቅዱሱ መንፈስም አበረታነው*፡፡ مَرْيَمَ ابْنَ عِيسَى وَآتَيْنَا ۖ بِالرُّسُلِ بَعْدِهِ مِن وَقَفَّيْنَا الْكِتَابَ مُوسَى آتَيْنَا وَلَقَدْ الْقُدُسِ بِرُوحِ وَأَيَّدْنَاهُ الْبَيِّنَاتِ

2፥253 እነዚህን መልክተኞች ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ አበለጥን፡፡ ከእነርሱ ውስጥ አላህ ያነጋገረው አልለ፡፡ ከፊሎቻቸውንም በደረጃዎች ከፍ አደረገ፡፡ የመርየምን ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው፡፡ *በቅዱሱ መንፈስም አበረታነው*፡፡ الرُّسُلُ تِلْكَ الْقُدُسِ بِرُوحِ وَأَيَّدْنَاهُ الْبَيِّنَاتِ مَرْيَمَ ابْنَ عِيسَى وَآتَيْنَا ۘ دَرَجَاتٍ بَعْضَهُمْ وَرَفَعَ ۖ اللَّهُ كَلَّمَ مَّن مِّنْهُم ۘ بَعْضٍ عَلَىٰ بَعْضَهُمْ فَضَّلْنَا

5፥110 አላህ በሚል ጊዜ አስታውስ፡- «የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! በአንተና በእናትህ ላይ የዋልኩላችሁን ጸጋዬን አስታውስ፡፡ በሕፃንነት እና በከፈኒሳነት ሰዎችን የምትናገር ስትኾን *በቅዱስ መንፈስ ባበረታሁህ ጊዜ*፤ ... ያደረግሁልህን ውለታ አስታውስ፡፡ ۚ إِذْ الْكِتَابَ عَلَّمْتُكَ وَإِذْ ۖ وَكَهْلًا الْمَهْدِ فِي النَّاسَ تُكَلِّمُ الْقُدُسِ بِرُوحِ أَيَّدتُّكَ إِذْ وَالِدَتِكَ وَعَلَىٰ عَلَيْكَ نِعْمَتِي اذْكُرْ مَرْيَمَ ابْنَ عِيسَى يَا اللَّهُ قَالَ بِإِذْنِي وَالْأَبْرَصَ الْأَكْمَهَ وَتُبْرِئُ ۖ بِإِذْنِي طَيْرًا فَتَكُونُ فِيهَا فَتَنفُخُ بِإِذْنِي الطَّيْرِ كَهَيْئَةِ الطِّينِ مِنَ تَخْلُقُ وَإِذْ ۖ وَالْإِنجِيلَ وَالتَّوْرَاةَ وَالْحِكْمَةَ مُّبِينٌ سِحْرٌ إِلَّا هَٰذَا إِنْ مِنْهُمْ كَفَرُوا الَّذِينَ فَقَالَ بِالْبَيِّنَاتِ جِئْتَهُم إِذْ عَنكَ إِسْرَائِيلَ بَنِي كَفَفْتُ وَإِذْ ۖ بِإِذْنِي الْمَوْتَىٰ تُخْرِجُ وَإِذْ ۖ

"አበረታነው" ለሚለው ቃል የመጣው "አይየድናሁ" ዓይደናህ ሲሆን "አበረታሁ" ለሚለው ቃል ደግሞ 'አይየድቱከ" أَيَّدْتُكَ ነው።

ይህንን ቃላት ሌላ አንቀጽ ላይ "አበርትቷቸዋል" ለሚለው ቃል "አይየደሁም" أَيَّدَهُمْ በሚል መጥቷል፡-

58፥22 በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑትን ሕዝቦች አላህንና መልክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች፤ አባቶቻቸው፣ ወይም ልጆቻቸው፣ ወይም ወንድሞቻቸው፣ ወይም ዘመዶቻቸው ቢኾኑም እንኳ የሚወዳጁ ኾነው አታገኛቸውም፡፡ እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል፡፡ *ከእርሱም በኾነ መንፈስ አበርትቷቸዋል*፡፡ اللَّهَ حَادَّ مَنْ يُوَادُّونَ الْآخِرِ وَالْيَوْمِ بِاللَّهِ يُؤْمِنُونَ قَوْمًا تَجِدُ لَّا مَّنْهُ بِرُوحٍ وَأَيَّدَهُم الْإِيمَانَ قُلُوبِهِمُ فِي كَتَبَ أُولَٰئِكَ ۚ عَشِيرَتَهُمْ أَوْ إِخْوَانَهُمْ أَوْ أَبْنَاءَهُمْ أَوْ آبَاءَهُمْ كَانُوا وَلَوْ وَرَسُولَهُ

ይህ የሚያበረታው ቅዱስ መንፈስ ጂብሪል መሆኑ በዚህ ሐዲስ ላይ መረዳት ይቻላል፤ ይህ ሐዲስ ፍንትውና ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው ሩሑል ቅዱስ ጂብሪል መሆኑን ነው፡-

ኢማም ቡኻርይ : መጽሐፍ 78, ሐዲስ 178-179

አቢ ሰለማህ እንደተረከው፡- ሐሰን ኢብኑ ሳቢት አቢ ሁረይራህን ምስክር እንዲሆነው መጠየቁን እንዲህ ሲል ሰምቻለው፡- አቢ ሁረይራህ ሆይ! በአላህ አለምንሃለው፤ የአላህ መልእክተኛ"ﷺ"፡- "ሐሰን ሆይ! ለአላህ መልእክተኛ መልስ ስጥ! አላህ ሆይ! በቅዱስ መንፈስ አበርታው" ሲሉ ሰምተሃልን? አቢ ሁረይራህም አዎ አለ። ثَابِتٍ بْنَ حَسَّانَ سَمِعَ أَنَّهُ عَوْفٍ، بْنِ الرَّحْمَنِ عَبْدِ بْنِ سَلَمَةَ أَبِي عَنْ

عَنْ أَجِبْ حَسَّانُ يَا " يَقُولُ وسلم عليه الله صلى اللَّهِ رَسُولَ سَمِعْتَ هَلْ بِاللَّهِ نَشَدْتُكَ هُرَيْرَةَ أَبَا يَا فَيَقُولُ هُرَيْرَةَ أَبَا يَسْتَشْهِدُ الأَنْصَارِيَّ، نَعَمْ هُرَيْرَةَ أَبُو قَالَ ". الْقُدُسِ بِرُوحِ أَيِّدْهُ اللَّهُمَّ اللَّهِ، رَسُولِ

አልበራዕ"ረ.ዐ" እንደተረከው ነብዩም"ﷺ" ለሐሰን፡- " በቃላት ይቅርታ አድርግላቸው፤ ጂብሪል ከአንተ ጋር ነው" አሉት። عَنِ مَعَكَ وَجِبْرِيلُ ـ هَاجِهِمْ قَالَ أَوْ ـ اهْجُهُمْ " لِحَسَّانَ قَالَ وسلم عليه الله صلى النَّبِيَّ أَنَّ ـ عنه الله رضى ـ الْبَرَاءِ ".

"መልእክተኛ"

ሌሎች ጥቅሶች ላይ ቁርአንን ቅዱስ እና ታማኝ መንፈስ በነብያችን"ﷺ" ልብ ላይ አወረደው ሲል ሌላ ቦታ ላይ ጂብሪል በነብያችን"ﷺ" ልብ ላይ አወረደው ይለናል፡-

16፥102 እነዚያን ያመኑትን ለማረጋጋት ሙስሊሞቹንም ለመምራትና ለማብሰር *ቁርአንን ቅዱሱ መንፈስ እውነተኛ ሲኾን ከጌታህ አወረደው* በላቸው:: لِلْمُسْلِمِينَ وَبُشْرَىٰ وَهُدًى آمَنُوا الَّذِينَ لِيُثَبِّتَ بِالْحَقِّ رَّبِّكَ مِن الْقُدُسِ رُوحُ نَزَّلَهُ قُلْ

26፥193-194 እርሱን *ታማኙ መንፈስ* አወረደው፤ ከአስጠንቃቂዎቹ ትኾን ዘንድ *በልብህ ላይ አወረደው*። الرُّوحُ بِهِ نَزَلَ الْمُنذِرِينَ مِنَ لِتَكُونَ قَلْبِكَ عَلَىٰ الْأَمِينُ

2፥97 ለጂብሪል ጠላት የኾነ ሰው በቁጭት ይሙት በላቸው:: *እርሱ ቁርአኑን ከበፊቱ ለነበሩት አረጋጋጭ ለምእመናን መሪና ብስራት ሲኾን በአላህ ፈቃድ በልብህ ላይ አውርዶታልና*:: بَيْنَ لِّمَا مُصَدِّقًا اللَّهِ بِإِذْنِ قَلْبِكَ عَلَىٰ نَزَّلَهُ فَإِنَّهُ لِّجِبْرِيلَ عَدُوًّا كَانَ مَن قُلْ لِلْمُؤْمِنِينَ وَبُشْرَىٰ وَهُدًى يَدَيْهِ

ይህ ቅዱስ መንፈስ የወሕይ መልአክ ነው፤ አላህ ወደ ነብያት ወሕይ የሚያወርድበት መንገድ ሦስት ናቸው፤ እነርሱም፡- በራዕይ፣ ወይም “ከግርዶ ወዲያ”፣ ወይም “መልክተኛን መልአክን” የሚልክ እና በፈቃዱ የሚሻውን ያወርዳል፡-

42:51 ለሰው” አላህ *“በራእይ”፣ ወይም “ከግርዶ ወዲያ”፣ ወይም “መልክተኛን መልአክን” የሚልክ እና በፈቃዱ የሚሻውን “የሚያወርድለት” ቢሆን እንጅ በገሃድ “ሊያናግረው” ተገቢው አይደለም*፤ እርሱ የበላይ ጥበበኛ ነውና። يُكَلِّمَهُ أَن لِبَشَرٍ كَانَ وَمَا حَكِيمٌ عَلِيٌّ إِنَّهُ ۚ يَشَآءُ مَا بِإِذْنِهِۦ فَيُوحِيَ رَسُولًا يُرْسِلَ أَوْ حِجَابٍ وَرَآئِ مِن أَوْ وَحْيًا إِلَّا ٱللَّهُ

እዚህ አንቀጽ ላይ "ቢኢዝኒሂ" ማለትም "በፈቃዱ" የሚለው ሃይለ-ቃል ይሰመርበት፤ “ረሱል” رَسُول የሚለው ቃል “ተላላኪ” ማለት ሲሆን “መለክ” مَلَك ማለትም “መልአክ” የሚለው ቃል ተለዋዋጭ”inter-change” ሆኖ የመጣ ነው፤ ይህም የወህይ መልአክ ጂብሪል”አ.ሰ.” ነው፤ አላህ በሦስተኛው መንገድ ነው ቁርአን ለነብያችን”ﷺ” ያወረደው፤ “መልአክን የሚልክ እና በፈቃዱ የሚሻውን የሚያወርድለት ቢሆን እንጅ” የሚለው ይሰመርበት፤ ጂብሪልም መልአክ እንደመሆኑ መጠን ከአላህ ወደ ነብያችን”ﷺ” ቀልብ ቁርአንን በአላህ ፈቃድ አውርዶታል፤ "ቢኢዝኒል ሏህ" بِإِذْنِ اللَّهِ ማለትም "በአላህ ፈቃድ" የሚለው ሃይለ-ቃል ይሰመርበት፤ መልእክተኛ ደግሞ ከሰው ወይም ከመላእክት ነው የሚመረጠው፡-

2፥97 ለጂብሪል ጠላት የኾነ ሰው በቁጭት ይሙት በላቸው:: *እርሱ ቁርአኑን ከበፊቱ ለነበሩት አረጋጋጭ ለምእመናን መሪና ብስራት ሲኾን በአላህ ፈቃድ በልብህ ላይ አውርዶታልና*:: بَيْنَ لِّمَا مُصَدِّقًا اللَّهِ بِإِذْنِ قَلْبِكَ عَلَىٰ نَزَّلَهُ فَإِنَّهُ لِّجِبْرِيلَ عَدُوًّا كَانَ مَن قُلْ لِلْمُؤْمِنِينَ وَبُشْرَىٰ وَهُدًى يَدَيْهِ

22፥75 *አላህ ከመላእክት ውስጥ መልክተኞችን ይመርጣል፡፡ ከሰዎችም እንደዚሁ*፤ አላህ ሰሚ ተመልካች ነው፡፡ مِنَ يَصْطَفِي اللَّهُ بَصِيرٌ سَمِيعٌ اللَّهَ إِنَّ ۚ النَّاسِ وَمِنَ رُسُلًا الْمَلَائِكَةِ

ማጠቃለያ

ሚሽነሪዎች ጂብሪል ቅዱስ መንፈስ መባሉ እና አላህ፡- "መንፈሶችን" ማለቱ ይገርማቸዋል፤ ለምሳሌ "መንፈስ በነጠላ ሲሆን በብዜት መናፍስት ይሆናል፤ ወደ ባይብሉ ስናጠቃልል መላእክት ቅዱሳን መናፍስት ናቸው፡-

ዕብራውያን 1፥14 ከቶ ለማን ብሎአል? ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ *የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት* አይደሉምን?

ቅዱስ መንፈስ በነጠላ ሲሆን በብዜት ቅዱሳን መናፍስት ይባላሉ፤ መላእክት የፈጣሪ መንፈሶች ተብለዋል፡- ራእይ 5፥6 *እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው*።

ስለዚህ በነጠላ ገብርኤል ቅዱስ መንፈስ መባሉ እና አላህ ወደራሱ በማስጠጋት በአገናዛቢ "መንፈሶችን" ማለቱ አያስደንቅም።

✍ከወንድም ወሒድ ዑመር

ወሰላሙ አለይኩም

3.የእየሱስ(ዓ.ሰ) ጉዳይ

ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

ኢየሱስ ክርስቶስ በመፅሀፍ ቅዱስ በማያሻማና በማያጠራጥር አገላለፅ "እኔ ኢየሱስ አምላክ ነኝ አምልኩኝ ተገዙኝ ወይም ደግሞ እኔ ኢየሱስ ፈጣሪ ነኝ" ብሎ የተናገረበት አንድ ጥቅስ የለም።መፅሀፍ ቅዱስና ቅዱስ ቁርአን በኢየሱስ ማንነት ዙሪያ ላይ

_ ኢየሱስ እሚያመልከው አምላክ እንደነበረው በግልፅ ይናገራሉ።

_ ኢየሱስ የተከበረ ባሪያ,የተከበረ መልእክተኛ,የተከበረ ነብይ,የተከበረ ሰው እንደነበር ያስተምራሉ።

_ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ብሎ እንዳልተሰቀለና እንዳልሞተ ፍንትው አድርገው ያሳያሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ እሚያመልከው አምላክ እንደነበረው ብዙ መፅሀፍ ቅዱሳዊና ቅዱስ ቁርአናዊ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላል ለናሙና ያክል, ኢየሱስ ክርስቶስ እሚያመልከው አምላክ እንደነበረው ከመፅሀፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁርአን ማስረጃዎችን እያጣቀስን እንመልከት:

ከቅዱስ ቁርአን:

• ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) እውነተኛውን አምላክ አላህን ሲያመልክ እንደነበር,አላህን በብቸኝነት ማምለክ እውነተኛውና ቀጥተኛው መንገድ ነው ብሎ እንዳስተማረ ቅዱስ ቁርአናችን በግልፅ ይናገራል።

ለምሳሌ ያክል ማስረጃዎችን ብንመለከት:

1• «አላህ ጌታዬና ጌታችሁ ነው፤ ስለዚህ ተገዙት፤ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው» (አላቸው)።"(3:51)

2• (ዒሳ አለ) «አላህም ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው።»"(19:36)

3• «አላህ ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው።»"(43:64)

ከመፅሀፍ ቅዱስ

መፅሀፍ ቅዱስም ኢየሱስ እሚያመልከው አምላክ እንደነበረው በግልፅ ይናገራል። ለምሳሌ ያክል ማስረጃዎችን ብንመለከት

1• የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ማነው ?

"የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። (2ኛ ቆሮንጦስ 1:3)

"ለዘላለም የተባረከ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት እንዳልዋሽ ያውቃል። (2ኛ ቆሮንጦስ 11:31)

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:3)

የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:17)

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ (1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:3-5)

ከላይ ያየናቸው የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች,ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደነበረው "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት" በማለት በግልፅ ያስረዳሉ።

የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ማነው?

እንደ ክርስትያኖች እምነት ኢየሱስ አምላክ ከሆነ,ለአምላክ ሌላ አምላክ እንዴት ይኖረዋል? ለአምላክ ሌላ አምላክ ካለው,አምላክ ስንት ነው?

2• ኢየሱስን የላከ እውነተኛውና ብቸኛው አምላክ ማነው ?

"እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።"(የዮሀንስ ወንጌል 17:3) ይህ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ በግልፅ እንደሚናገረው,ኢየሱስን የላከ እውነተኛና ብቸኛ አምላክ እንዳለ ነው።

ኢየሱስን የላከ እውነተኛውና ብቸኛው አምላክ ማነው?

3•ለኢየሱስ ሁሉን ያስገዛለት ማነው ?

"ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል። (1ኛ ቆሮንጦስ 15:28) በዚህ ጥቅስ መሰረት,በስተመጨረሻ ኢየሱስ ሁሉን ላስገዛለት ተገዢ ባሪያ እንደሚሆን በግልፅ ያስረዳል።

ለኢየሱስ ሁሉን ያስገዛለት,በስተመጨረሻም ኢየሱስ ለእርሱ ተገዢ እሚሆንለት አካል ማነው? ኢየሱስ አምላክ ከሆነ,አምላክ ገዢ ነው ወይስ ተገዢ? አምላክ ለማን ነው ተገዢ የሚሆነው?

4•የኢየሱስ አምላክ ማነው ?

"ኢየሱስም፦ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ። እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት።"(የዮሀንስ ወንጌል 20:17)

ኢየሱስ በዚህ ጥቅስ ላይ "ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ" ብሎ ሲናገር:

አንደኛው ነጥብ:ኢየሱስ ሲናገር ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ ብሎ ተናገረ። እንደ ክርስትያኖች እምነት ኢየሱስ አምላክ ከሆነ,የአምላክ ወንድሞች እነማን ናቸው? አምላክ ተጋሪ የሌለው አንድና ብቸኛ ነው።

ሁለተኛው ነጥብ: ኢየሱስ አምላክ እንዳለው "ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ" በማለት በግልፅ ተናግሯል። አምላኩ ማነው? አምላኬ እያለ እሚጠራው ማንን ነው?

5• ኢየሱስ,አምላኬ አምላኬ እሚለው ማንን ነው?

"በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሄ፥ ኤሎሄ፥ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጓሜውም አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ? ማለት ነው።"(የማርቆስ ወንጌል 15:34)

"በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም። አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ? ማለት ነው።"(የማቴዎስ ወንጌል 27:46)

ኢየሱስ እራሱ አምላክ ከሆነ,ማንን ነው አምላክ አምላኬ ስለምን ተውከኝ እያለ እሚጠራው?

6•ኢየሱስ ቸር አይደለምን?

"ኢየሱስም፦ ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።"(የማርቆስ ወንጌል 10:18)

"ኢየሱስም፦ ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።"(የሉቃስ ወንጌል 18:19)

ኢየሱስ ቸር አለመሆኑን በራሱ አንደበት በግልፅ ከተናገረ,ቸር ያልሆነ አካል እንዴት አምላክ ሊሆን ይችላል?

ኢየሱስ ቸር ካልሆነ,እግዚአብሄር ቸር ከሆነ,ቸር የሆነው እግዚአብሄር,ቸር ያልሆነው ኢየሱስ እንዴት ሊሆን ይችላል?

7• ኢየሱስ ምንን አስተማረ?

"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥"(የማርቆስ ወንጌል 12:29)

ኢየሱስ አምላክ እንዳለው "ጌታ አምላካችን" በማለት በግልፅ አስተምሯል።ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ለምን ግልፅ በሆነ ቋንቋ "እኔ ነኝ አምላካችሁ" አላለም?

8• ኢየሱስን ጌታ የሚል አይድንም።

"በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። "(የማቴዎስ ወንጌል 7:21)

ኢየሱስ ጌታ ስላልሆነ,ጌታ ያልሆነን አካል ጌታ ብለህ ማመንና ጌታ ብለህ መጥራት እንደማያድን በግልፅ እየተናገረ ነው።

ኢየሱስ ጌታ አለመሆኑ በግልፅ ከተናገረ,ጌታ ያልሆነን አካል ጌታ እያሉ በመጥራት የአምላክን ደረጃ መስጠት ለምን አስፈለገ?

ኢየሱስ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ?

ሰው(ኢየሱስ)ን ፍጹም አምላክ ነው ስንል አምላክን ሰው ነው እያል ነው፡፡ ይህ ታዲያ አምላክ ሰው እንዳልሆነ የተገለጸውን መፃረር አይሆንምን?

ሌላው መፅሀፍ ቅዱስ ላይ ኢየሱስ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ ነው የሚል አንድም ማስረጃ የለም። ቤተክርስትያን ናት ከራሷ(ከኪሷ) ጨምራ ነው ያስተማረችው እንጂ ኢየሱስ "እኔ በፍፁም ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው ነኝ" ብሎ አስተምሮ አያውቅም ።

እግዚአብሔር ሰው እንዳልሆነ ተገልጻል

☞“ይዋሽ ዘንድ እግዚአብሔር #ሰው_አይደለም፤ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም”፡፡ (ዘኁልቁ 23፡19)

እኔ በመካከላችሁ ያለሁ ቅዱስ አምላክ ነኝ እንጂ #ሰው_አይደለሁና በቁጣ አልመጣም፡፡ (ትንቢተ ሆሴዕ 11፡9).እንዲሁም 1ኛ ሳሙኤል 15፡29 ላይ

☞“የእስራኤል ክብር የሆነው #እግዚአብሔር አይዋሽም፤ አይፀፀትም፤ እርሱ ይፀፀት ዘንድ #ሰው_አይደለምና፡፡ ይላል

ስለዚህ ኢየሱስ በፍፁም አምላክ ሊሆንም፣ሊባልም አይችልም። ምክንያቱም ኢየሱስ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ ነው አልን ማለት ፈጣሪን እንደመሳደብ ይቆጠራልና።

ኢየሱስ ለሰው ልጅ ኃጢያት ሲል ተሰቅሏልን?

በዚህች ጊዜያዊ "ምድራዊ" ህይወትም ሆነ በመጪው የዘላዓለማዊ ሕይውት የሰው ልጅ ሁሉ ለሰራው መልካም ሥራ እንደሚመነዳና "ወሮታ እንደሚከፈለው" በተቃራኒውም ለሰራው ኃጢያት "ወንጀል" መጠየቁና መቀጣቱ የማይቀር ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ነው።

አባት ለሰራው መጥፎ ስራ ልጅ ወይም ሌላ ሰው አይጠየቅም ። ልጅም ላጠፍው ጥፍት እህት ወይም እናት አትጠየቅም። ማንም ሰው ለፈፀመው ክፉ ተግባር የሚጠየቀውም ሆነ የሚቀጣው ራሱ ብቻ ነው።

ይሁን እንጂ ይህን እውነታ በገሃድ እየታወቀ ኢየሱስ ለኛ ኃጢያት ሲል ተሰቀለልን ሞተልን "ኢየሱስ አዳኝ ነው" ብሎ በእሱ ያመነ ኃጢያቱ ይሰረዝለታል ፣ ገነትን ይወርሳል እነዚህንና የመሳሰሉትን መፈክር በማስተጋባት በየ አደባባዮችና በየ መንገዱ መጽሐፍ ቅዱስን በመሸከም መንገደኛውን አናሳልፍም የሚሉ ግለሰቦች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ ይገኛል ።

ነገር ግን መልካም ስራም የሰራ ለራሱ እንደሆነና ኃጢያትም የሰራ ለራሱ እንደሚጠየቅበት የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ያብራራሉ።

"ልጆቻቸው በሰሩት ወንጀል ወላጆች መቀጣት የለባቸውም፤ ወላጆች በፈጸሙት ወንጀል ልጆቻቸው በሞት አይቀጡም፤ እያንዳንዱ ሰው በሰራው ወንጀል በሞት ይቀጣል።" ኦሪት ዘዳግም 24፡16

"ንምዛዘ የወይን ፍሬ የሚበላ ሰው ሁሉ የገዛ እራሱን ጥርስ ብቻ ያጠርሳል ፤ እያንዳንዱ በገዛ ራሱ ኃጢያት ይሞታል።" ትንቢተ ኤርሚያስ 31፡30

"ሞት የሚገባው ኃጢያት ለሚሰራ ሰው ብቻ ነው። ልጅ ስለ አባቱ ኃጢያት አይቀጣም፤ አባትም ስለ ልጁ ኃጢያት አይቀጣም ፤ ደግ ሰው በደግነቱ መልካም የዋጋውን ያገኛል፤ ክፉ ሰውም በክፋቱ ይቀጣል ትንቢተ ሕዝቅኤል 18፡20

ኢየሱስም እንዲህ አለ፦ በእውነት እላቸሁአለሁ ካልተመለጣቹህና እንደህፃን ካልሆናቹህ ወደ ሰማይ ከቶ አትገቡም።" የማቴዎስ ወንጌል 18፡13

ለአንዱ ኃጢያት ሌላው አይጠየቅም "በቁርአን"

"ኃጢያትን ተሸካሚም "ነፍስ" የሌላዋን ሸክም አትሸከምም ፤ የተከበደችም "ነፍስ" ወደ ሸክሟ ብትጣራ "ተጠሪው" የቅርብ ዝምድና ባለቤት ቢሆንም እንኳ ከእርሷ አንዳችም. የሚሸከምላት አታገኝም" አል.ፍጢር 18

መልካም የሰራ ሰው ለነፍሱ ነው ፤ ያጠፋም ሰው በርሷ ላይ ነው ፤ጌታም ለባሮቹ በዳይ አይደለም ። አል.ፉሲለት 46

"የተመራ" ሰው የሚመራው ለራሱ ብቻ ነው ። የተሳሳተም ሰው የሚሳሳተው "ጉዳቱ" በርሷ ላይ ነው። ተሸካሚም "ነፍስ" የሌላኛይቱን ኃጢያት አትሸከምም" አል ኢስራእ 15።

አማላጅ ማን ነው?

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

መግቢያ

“ሸፋዓ” شَفَعَ ማለት “ምልጃ” ማለት ሲሆን ምልጃ ሶስት ሃልዎትን ያቅፋል፤ አንዱ የሚማለድለት ማንነት፣ ሁለተኛው የሚማለደው ተማላጅና ሶስተኛው የሚማልደው አማላጅ ናቸው፤ አላህ የሁሉም ነገር ፈጣሪና አስተናባሪ በመሆኑ የሚማለድ ተማላጅ ሲሆን ከፍጡሮቹ መካከል ደግሞ እርሱ የፈቀደላቸው ፍጡሮቹ ደግሞ አማላጆች ናቸው፤ ሆነም ቀረ ለመማለድም ሆነ ለማማለድ የአላህ ፈቃድ ያስፈልጋል ይህ ሂደት “ምልጃ” ሲባል ይህ የምልጃ ፈቃድ የአላህ ብቻ ነው፡-

39:44 “ምልጃ” الشَّفَاعَةُ መላውም የአላህ ብቻ ነው፤ 34:23 “ምልጃም” الشَّفَاعَةُ እርሱ ለፈቀደለት ሰው ብቻ ቢሆን እንጂ እርሱ ዘንድ ምንም አትጠቅምም፤

20:109 ለርሱ አልረህማን የፈቀደለትንና ለርሱም ቃልን የወደደለትን ሰው ቢሆን እንጅ “ምልጃ” الشَّفَاعَةُ አትጠቅምም።

ነጥብ አንድ

“አማላጅ””

ሸፊዕ” شَفِيعٍ ማለት “አማላጅ” ማለት ሲሆን በአላህ ፈቃድ የሚያማልዱት መላእክት፣ ነቢያት፣ ሙዑሚን ናቸው፤ እነርሱም ቢሆን የሚያማልዱት አላህ ለፈቀደለት ሰው ብቻ ነው፡-

2:255 አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ሕያው ራሱን ቻይ ነው፡፡ ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም፡፡ በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው፡፡ “ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ “የሚያማልድ” يَشْفَعُ ማነው”?

53:26 በሰማያት ውስጥ ካለ መልአክም ብዙዎች ሊማለዱለት ለሚሻውና ለሚወደው ሰው “ከፈቀደ በኋላ ቢሆን እንጅ “ምልጃቸው” شَفَاعَتُهُمْ ምንም አትጠቅምም።

21:28 በፊታቸው ያለውንና በኋላቸው ያለውንም ሁሉ ያውቃል፤ “ለፈቀደውም ሰው እንጅ ለሌላው “አያማልዱም” وَيَشْفَعُونَ፤

34:23 “ምልጃም” الشَّفَاعَةُ እርሱ ለፈቀደለት” ሰው ብቻ ቢሆን እንጂ፣ እርሱ ዘንድ ምንም አትጠቅምም፤

19:87 “አልረሕማን ዘንድ ቃል ኪዳንን የያዘ ሰዉ ቢኾን እንጂ “ማማለድን” الشَّفَاعَةَ አይችሉም።

ነጥብ ሁለት

“አማላጅ የለም”

ከላይ በግልፅና በማያሻማ መልኩ አላህ የፈቀደለት አማላጅ እና የሚማለድለት ሰው እንዳለ ተቀምጧል፤ ነገር ግን ሚሽነሪዎች ቁርአንን ምን ጥላሸት እንቀባው በማለት ጭራሽኑ ለመስሊሙ ኡማ ጥያቄ ሆኖ የማያውቀውን የተንሸዋረረና የተውረገረገ ጥያቄ፡- “”አማላጅ አላህ ነው፤ ወደ ማን ነው የሚያማልደው? አማላጅ የሚባል የለም፣ ካለስ ከላይ ጥቅስ ጋር አይጋጭምን?”” ብለው ይፎትታሉ፤ እኛ ደግሞ በተቃራኒው ይህ ፉተታ የቁርአንን አውድ፣ ሰዋስው፣ ቋንቋ ያማከል አይደለም ብለን እንሞግታለን፤ እስቲ ሙግቱ በእማኝነትና በአስረጅነት እናቅርብ፡-

32:4 አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸውም ያለውን ሁሉ በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ፣ ከዚያም በዐርሹ ላይ የተደላደለ ነው፤ “ከርሱ ሌላ ለናንተ ረዳትም አማላጅም ምንም የላችሁም” مَا لَكُمْ مِنْ دُونِهِ مِنْ وَلِيٍّ وَلَا شَفِيعٍ ፤ አትገሠጹምን?

6:51 እነዚያንም “ከእርሱ ሌላ ረዳትና አማላጅ የሌላቸው” لَيْسَ لَهُمْ مِنْ دُونِهِ وَلِيٌّ وَلَا شَفِيعٌ ሲኾኑ ወደ ጌታቸው መሰሰብሰብን የሚፈሩትን ይጠነቀቁ ዘንድ በርሱ በቁርአን አስጠንቅቅ፡፡

6:70 በእርሱም በቁርአን ነፍስ በሠራችው ሥራ እንዳትጠፋ አስታውስ፡፡ ለእርሷ “ከአላህ ሌላ ረዳትና አማላጅ የላትም” لَيْسَ لَهَا مِنْ دُونِ اللَّهِ وَلِيٌّ وَلَا شَفِيعٌ፡፡

ሶስቱም ጥቅሶች ተመሳሳይ አቀማመጥ ስላላቸው ከሶስቱ የመጀመሪያውን ለናሙና ያክል ማየት ይቻላል፡-

ሙግት አንድ

“ረዳት የላችሁም”

“ማ ለኩም ሚን ዱኒሂ ሚን ወሊዩን” مَا لَكُمْ مِنْ دُونِهِ مِنْ وَلِيٍّ ማለት “ከርሱ ሌላ ለናንተ ረዳት የላችሁም” ማለት ነው፤ እውነት ነው ከአላህ ውጪ በጀነት ለመጥቀምና በጀሃነም ለመቅጣት የሚችል ማንም ሆነ ምንም “ረዳት” የለም፤ “ሚን ዱኒሂ” مِنْ دُونِهِ ማለትም “ከርሱ ሌላ” የሚለው ተሳቢ ተውላጠ-ስም ያለበት ገላጭ ስም”genitive noun” ከሰዋስው አንፃር አላህ ብቻ ረዳት መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፤ ይህንን አንቀፅ መደገፊያ ሎሎችን ጥቅሶች መመልከት ይቻላል፡-

13:16 ለነፍሶቻቸው ጥቅምንም ጉዳትንም የማይችሉን “ረዳቶች” أَوْلِيَاءَ ከርሱ ሌላ” ያዛችሁን?

42:9 “ከርሱ ሌላ ረዳቶችን” أَوْلِيَاءَ ያዙን? አላህም ረዳት الْوَلِيُّ እርሱ ብቻ ነው።

18:26 ለነርሱ “ከርሱ በቀር ምንም “ረዳት” وَلِيٍّ የላቸውም”፤ በፍርዱም አንድንም አያጋራም።

7:197 እነዚያ “ከርሱ በቀር የምትገዙዋቸው፣ “ሊረዱዋችሁ” يَتَوَلَّى አይችሉም”፤ ነፍሶቻቸውንም አይረዱም።

ሙግት ሁለት

“አማላጅ የላችሁም”

“ወላ ሸፊዒን” وَلَا شَفِيعٍ ማለት “እና አማላጅም የላችሁም” ማለት ሲሆን ከመጀመሪያው ሀረግ ለመለየት “ወ” وَ የሚል ሐርፉ ዓጠፍ” حرف عاطفة ማለትም “ለይ መስተጻምር”prefixed conjunction” ይጠቀማል፤ ያ ማለት በተጨማሪም አማላጅም የላችሁም ማለት ነው፤ “ላ” لَا የሚለው “ሐርፉ ነፍይ” حرف نفي ማለትም “አፍራሽ ቃል”negative particle” ነው፤ ስለዚህ በመጀመሪያው ሀረግ ላይ “ማ” مَا የሚለው መስደሪያ አፍራሽ ቃል ሆኖ ገብቶ በተጨማሪ በሁለተኛው ሃረግ ላይ ላ” لَا የሚለው አፍራሽ ቃል መደገሙ ጣኦታውያን ጣኦቶቻቸውን ረዳቶች አድርገው ስላመለኩ አላህ ከእርሱ ሌላ ረዳት እንደሌላቸው ከተናገረ በኃላ በሁለተኛው ሀረግ ደግሞ ወደ አላህ በማማለድ ያቀርቡናል ብለው የሚናገሩላቸውን ጣኦታት አማላጆች አለመሆናቸውን ለማሳየት “አማላጅ የላችሁም” በማለት ዘግቶታል፤ ይህን በሌሎች ጥቅሶች በአፅንኦትና በአንክሮት ማየት ይቻላል፡-

30:13 ለነርሱም ከሚያጋሩዋቸው “አማላጆች” شُفَعَاءُ “አይኖሩዋቸውም”፤

10:18 ከአላህም ሌላ የማይጎዳቸውን የማይጠቅማቸውንም ይገዛሉ:: «እነዚህም አላህ ዘንድ “አማላጆቻችን” شُفَعَاؤُنَا ናቸው» ይላሉ::

39:3 እነዚያም ከርሱ ሌላ ረዳቶች የያዙት “ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን” እንጅ ለሌላ አንግገዛቸውም ይላሉ፤

አላህ በሱረቱ አሰጅዳህ 32:4 ላይ አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸውም ያለውን ሁሉ በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ፣ ከዚያም በዐርሹ ላይ የተደላደለ ነው፤ ብሎ ከተናገረ በኃላ "ከርሱ ሌላ ለናንተ ረዳትም አማላጅም ምንም የላችሁም" ሲል "አማላጅም ምንም የላችሁም" ማለት ምን ማለት እንደሆነ በሌላ አንቀፅ ያስቀምጠዋል፡-

10:3 ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠረ፣ በዐርሹም ላይ ራሱን የተደላደለ ነው። ነገሮችን ሁሉ ያስተናብራል፣ ይመራል። "ከርሱ ፈቃድ በኋላ" ካልሆነ በቀር የሚያማልድ አንድም "አማላጅ" شَفِيعٍ የለም።

ስለዚህ "አማላጅም ምንም የላችሁም" ማለት "ከርሱ ፈቃድ በኋላ ካልሆነ በቀር እናንተ ከምታጋሯቸው የሚያማልድ አንድም "አማላጅ" የለም" ማለት ነው እንጂ በአላህ ፈቃድ የሚያማልዱ አማላጆች የሉም ማለት አሊያም አላህ አማላጅ ነው ማለት አይደለም።

ከአላህ ሌላ ከቅጣት ሊያድናቸው የሚችል ረዳት የላቸውም እንዲሁ ቅጣት እንዳይገቡ ወደ አላህ የሚያማልዳችሁ አማላጅ የለም ማለት ነው፤ ሙፈሲሮችም በዚህ መልኩ ነው ተረድተው ያስቀመጡት:-

Tafsir Ibn Kathir 32:4

""You have none, besides Him, as a protector or an intercessor means, only He is the Sovereign Who is in control of all affairs, the Creator of all things, the Controller of all things, the One Who is able to do all things. There is no Creator besides Him, ""no intercessor except the one to whom He gives permission""

Tafsir al-Jalalayn 6.70

""it has no protector, [no] helper, besides God, other than Him, ""and no intercessor, to ward off the chastisement from it;""

እውን እየሱስ እግዛብሄር ነውን ?

By:-Riyad Abdulhakim

✔የእግዚአብሔርንና የኢየሱስን ማንነት በተመለከተ በተለይ የከረሩና ሚዛናቸውን ያልጠበቁ በዚህም ምክንያት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ የሰዎች አመለካከቶች አሉ።

ኢየሱስ ራሱ ያ አንዱ እግዚአብሔር ነው ማለት እንዳልሆነ ብዙ የመፅሃፍ ቅዱስ ጥቅሶች ያሳያል ። ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አንዱ እግዚአብሔር ሲናገር እግዚአብሔርንና ኢየሱስን በአንድነት አብሮ አንድ እግዚአብሔር እያለ አይደለም የሚጠራቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይም ይሁን በአዲስ ኪዳን ስለ አንዱ እግዚአብሔር ወይም ስለ አንዱ አምላክ ሲናገር ብዙዎቻችን እንደሚመስለን ስለ ስላሴ ሳይሆን የሚያወራው ስለ *አብ* ብቻ ነው። ስለዚህ እየሱስ እራሱ የቻለ ማንነት ሲኖረው እግዛብሄርም እንዲሁ ሌላ እራሱ የቻለ ማንነት አለው ።

„አንድ እግዚአብሔር አለና፣ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፣ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፣5

„መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድርም ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ፥ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።“ 1ኛ ቆሮንቶስ 8፣5-6

„በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖርአንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።“ ኤፌሶን 4፣4-6

ብዙ ግዜ በመፅሃፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን (አብ)ን ብቻ አባታችን ተብሏል ስለዚህ የሁሉም አባት የተባለው (አብን) ነው እንጂ ወልድን አይደለም ፥ከእግዚአብሔር *ከአባታችን* ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።“ ፊልጵስዩስ 1፣2

„ኢየሱስም፦ ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።“ የሉቃስ ወንጌል 18፣19: የማርቆስ ወንጌል 10፣18

ከላይ በተመለከትነው መርጃ መሰረት እግዛብሄር እየሱስ እንዳልሆነ ነው ። ሌላ እግዛብሄር እየሱስ ነው የሚል አንድ መፅሃፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ያለው ሜዳውም ፈረሱም ይሄው ነው ?

ኢየሱስ አማላጅ ወይስ ተማላጅ?

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡

መግቢያ

ባለፈው በነበረን ቆይታ እግዚአብሔር ኢየሱስ እንዳልሆነና ሰው እንደሆነ ጥልልና ጥንፍፍ ባለ መልኩ ስንዳስስ ነበር፣ ዛሬ ደግሞ ኢየሱስ አማላጅ ወይስ ተማላጅ የሚለውን እንዳስሳለን፣ ተማላጅ ከሆነ እሰየው እግዚአብሔር ነው ብለን እንደመድማለን፣ አማላጅ ነው ካልን ደግሞ እርማችንን አውጥተን ሰው ብቻ መሆኑን እንቀበላለን፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ወደ እግዚአብሔር ካማለደ ሁለት እግዚአብሔር ሊሆን ነዋ፣ ምልጃ ሁለት ማንኑቶችን ያቅፋል፣ እነርሱም አማላጅና ተማላጅ ናቸው፣ ኢየሱስ አማላጅ ወይስ ተማላጅ ወደሚለው መደምደሚያ ሊያደርሱን የሚችሉ አንዳንድ ነጥቦችን እንመልከት፡-

ኢየሱስ አማላጅ ነው ?

ሮሜ 8.33-34 እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው? የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ἐντυγχάνει ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

ይህ ጥቅስ ኢየሱስ በግልጽና በማያሻማ መልኩ ኢየሱስ አማላጅ መሆኑ አስቀምጧል፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚኮንና የሚያጸድቅ መሆኑ ካረጋገጠ ወዲያ በመቀጠል δὲ *ይልቁስን* moreover የሚል ለዪ መስተጻምር በመጠቀም ኢየሱስን ከኮናኙና ከአጽዳቂው እግዚአብሔር ይለየዋል፣ የሚማልደው የሚለው የግሪኩ ቃል ኢንትይንች ἐντυγχάνει ሲሆን የሚፈርደው እያሉ ለሚቀያይሩት ሰዎች ማምለጫ መንገድ የላቸውም፣ ኢንትይንች ἐντυγχάνει የሚለው ቃል ግስ ሲሆን ኢንቲአኖ ἐντυγχάνω አማለደ ከሚለው ስርወ-ግንድ የመጣ ነው፣ አሁን ምን ይዋጣቸው ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ለሚሉት?

NAS Exhaustive Concordance of the Bible with Hebrew-Aramaic and Greek Dictionaries

Copyright © 1981, 1998 by The Lockman Foundation

እግዚአብሔር ተማላጅ ነው?

ዕብራውያን 7.25 ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል፣ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ἐντυγχάνειν ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ።

New International Version

Therefore he is able to save completely those who come to God through him, because he always lives to intercede for them.

ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚመጡት በክርስቶስ ነው ካለን፣ እግዚአብሔር ተማላጅ ነው ማለት ነው፣ በክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር ለሚመጡት ሰዎች ደግሞ ክርስቶስ ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ይለናል፣ ሊያማልድ የሚለው የግሪኩ ቃል ኢንቲቻኔን ἐντυγχάνειν ሲሆን ኢንቲአኖ ἐντυγχάνω አማለደ ከሚለው ስርወ-ግንድ የመጣ ነው፣ አሁን ምን ይዋጣቸው ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ለሚሉት?

መደምደሚያ

ኢየሱስ ተማላጅ ነው የሚል ባይብል ላይ የለም ፣ ከሌለ ደግሞ ክርስቶስ እግዚአብሔር አይደለም ማለት ነው፣ እግዚአብሔር ወደ እግዚአብሔር ይጸልያልን? ፦

ሉቃስ 6.12 ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ።

እግዚአብሔር እግዚአብሔርን ቀባውን?

ሐዋርያት ሥራ 10.38 እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥

እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር የበላይ ነውን?

1ኛ ቆሮ 11.3 የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልታውቁ እወዳለሁ።

እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ነውን?

1ኛ ቆሮ 3.23 ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር፦ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ ይላልን?

ዮሐንስ 14.1 ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ።

እውን የመርየም ልጅ ዒሳ ሊፈርድ ይመጣልን?

በአላህ ሥም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው

ክብርና ምሥጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2) የአላህ ውዳሴና ሰላም የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለኾኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)።

ከአቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "ነፍሴ በእጁ በኾነችው ይሁንበኝ! በናንተ ላይ የመርየም ልጅ ፍትሐዊ ዳኛ ኾኖ ሊወርድ ይቃረባል። መስቀልንም ይሰባብራል። አሳማዎችንም ይገድላል። ግብርንም ይተዋል። ገንዘብንም የሚቀበለው ሰው እስኪጠፋ ድረስ ይበራከታል። ለአላህ የሚደረግ አንድ ሱጁድ ዱንያና በውስጧ ከያዘችው ኹሉ የበለጠና የተሻለ ይኾናል" ከዚያም አቡ ሁረይራህ፡ ‹‹ከፈለጋችሁ ይህን አንቀጽ አንብቡ›› አለ። ‹‹ከመጽሐፉም ሰዎች ከመሞቱ በፊት በእርሱ (በዒሳ) በእርግጥ የሚያምን እንጅ (አንድም) የለም። በትንሣኤም ቀን በነሱ ላይ መስካሪ ይኾናል።››። (ቡኻሪይ 3448፣ ሙስሊም 406፣ አሕመድ 7471፣ ቲርሚዚይ 2398)።

በዚህ ታላቅ ሐዲሥ ውስጥ ‹‹የመርየም ልጅ ፍትሐዊ ዳኛ ኾኖ ሊወርድ ይቃረባል›› የሚለውን ቃል በመምዘዝ፡ ወገኖቻችን፡- ‹‹እናንተም ሙስሊሞች በመጨረሻው ቀን ዒሳ ፈራጅ እንደኾነ ታምናላችሁ! ሐዲሣችሁም ይናገራል እኮ!›› ይሉናል። የኛስ መልስ ምንድነው? እውን የሐዲሡ መልእክት እነሱ እንዳሉት ነውን? ፈራጅስ ማነው? መጠነኛ ምላሹን ይከታተሉ።

1/ ፍርድ የአላህ ነው። የጌትነቱ መገለጫውም ነው። በባሮቹ ላይ የሚፈርደው እሱ ነው። ቀድሞውኑም ይህን አድርጉ ትእዛዝ ነው! ያን ደግሞ አትቅረቡ እርም ነው! በማለት በባሮቹ ላይ ህግን ያወጣውና የደነገገው እሱ ነውና። የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ህግን አላወጣም አልደነገገምም። እሱ ራሱ የአምላክ ህግ ከሚመለከታቸው የአምላክ ባሪያና ነቢያት ከኾኑት ውስጥ አንዱ ነውና። በምን መልኩ ነው ታዲያ፡ ህግ ያወጣው አላህ፡ የሚተሳሰበውና የሚፈርደው ደግሞ ዒሳ የሚኾነው? የመርየም ልጅ ዒሳ በአላህ ባሮች ላይ በመጨረሻው ቀን ይፈርዳል ካልን፡ በምን ህግ ነው የሚፈርድባቸው? ትእዛዝን እሱ አልሰጣቸው! ይህን ሥሩ ዋጂብ ነው! ያን ደግሞ አትቅረቡ ሐራም ነው! ብሎ በሰዎች ላይ ህግን አልደነገገም። በማያውቀውና ባልደነገገው ህግ ይፈርዳል ማለት ጤናማ አስተሳሰብ አይደለም። አላህ ግን በባሮቹ ላይ ከአደም ዘመን ጀምሮ እስከ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂም ወሰለም) ድረስ የነበሩ ነቢያትን፡ የመረጠውና የላከው፣ መጽሐፍትንም ያወረደውና ህግ የደነገገው እሱ ስለነበር፡ በመጨረሻው ቀንም ባሮቹን የሚተሳሰባቸው እሱ ብቻ ነው። ህጌን የት አደረጋችሁ በማለትም ይጠይቃቸዋል፡ እንደ ሥራቸው መጠንም ይፈርድባቸዋል። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

"መልክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን። ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ መጽሐፎችንና ሚዛንን ወደእነርሱ አወረድን…" (ሱረቱል ሐዲድ 57፡25)።

"አላህ መልክተኞቹን የሚሰበስብበትንና «ምን መልስ ተሰጣችሁ» የሚልበትን ቀን (አስታውስ)። «ለእኛ ምንም ዕውቀት የለንም አንተ ሩቆችን በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህ» ይላሉ፡።" (ሱረቱል ማኢዳህ 5፡109)።

"የሚጠራቸውንና ለመልከተኞቹስ ምንን መለሳችሁ» የሚልበትን ቀን (አስታውስ)።" (ሱረቱል ቀሶስ 28፡65)።

"...ፍርዱ ለአላህ ብቻ ነው። እውነትን ይፈርዳል። እርሱም ከፈራጆች ሁሉ በላጭ ነው» በላቸው።" (ሱረቱል አንዓም 6፡75)፡

"ከእርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸውን ስሞች እንጅ አትገዘዙም። አላህ በእርሷ ምንም አስረጅ አላወረደም። ፍርዱ የአላህ እንጅ የሌላ አይደለም። እርሱን እንጅ ሌላን እንዳትገዙ አዟል። ይህ ትክክለኛው ሃይማኖት ነው። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም።" (ሱረቱ ዩሱፍ 12፡40)።

"እርሱም አላህ ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። ምስጋና በመጀመሪያይቱም በመጨረሻይቱም ዓለም ለእርሱ ብቻ ነው። ፍርዱም የእርሱ ብቻ ነው። ወደእርሱም ትመለሳላችሁ።" (ሱረቱል ቀሶስ 28፡70)።

2/ የፍርድ ቀን የሚባለው ሁላችንም እንደምናውቀው የውሙል ቂያም (የትንሳኤው ዕለት) ነው። ማለትም፡- በምድር ያሉ ሕያዋን ፍጥረታት በጠቅላላ ሞተው፡ ከአፈር በታች (በመቃብር) ኾነው፡ ከዚያም በኋላ መልአኩ ኢስራፊል (ዐለይሂ-ሰላም) በጡርንባው አንዴ ሲነፋ ምድር ሽክሞቿን በጠቅላላ ታራግፋለች። ሙታን በጠቅላላ ዳግም ነፍስ ዘርተው ሕያው ኾነው ይቀሰቀሳሉ። ወደ ጌታቸው አላህ ፍርድ ሚዛንም ለምርመራና ለፍርድ ይቀርባሉ። ይህ ቀን ነው የፍርድ ቀን የሚባለው። የዚህ የፍርዱ ቀን ባለቤት ደግሞ አላህ ብቻ ነው (ማሊኪ የውሚ-ዲን) የተባለው እርሱ አይደለምን?። የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ግን ወደዚህ ምድር የሚወርደው ከቂያም ቀን መከሰት በፊት ነው። እንደውም የሱ መምጣትና መውረድ፡ ለቂያም ቀን እጅግ መቃረብ ምልክት ነው ተብሎ በቁርኣን ተነግሮናል (ሱረቱ-ዙኽሩፍ 43፡61 ተመልከት)። ታዲያ ከፍርዱ ቀን በፊት፡ በምድር ያሉ ሕያዋንም ጨርሰው ከመሞታቸው፡ ሙታንም ከመቃብራቸው ከመቀስቀሳቸው በፊት ወደዚህ ምድር ዒሳ የሚመጣው በሰዎች ላይ ለመፍረድ ነው ብሎ ማሰብ ምንኛ ነው? የትንሳኤው ፍርድ ቀኑ ተቀየረ እንዴ? ደግሞስ ሊፈርድ ከመጣ በወቅቱ በሕይወት ባሉት ሰዎች ላይ ብቻ ሊኾን ነውን? በመቃብር ከዚህ በፊት የሞቱትስ ከፍርድ አመለጡ ማለት ነውን? እነዚህ ፍርድን የተቀበሉትስ ሞት ሊቀርላቸው ነው ወይስ ከፍርድም በኋላ ድጋሚ ሞት ይኖር ይኾን? ይህ ሁሉ የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) የሚመጣው በሰዎች ላይ ለመፍረድ ነው የሚለውን አስተሳሰብ ራቁቱን የሚያስቀር ነው።

3/ የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) በአላህ ቃል ውስጥ እንደተገለጸው፡ በትንሳኤው ቀን በባሮቹ ላይ የሚፈርደው አላህ ራሱ መኾኑን በአንደበቱ መመሥከሩን ነው። የአላህ ቃል ስለ ዒሳ ምሥክርነት ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

"«በእርሱ ያዘዝከኝን ቃል ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም። በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጣባቢ ነበርኩ። በተሞላኸኝም ጊዜ (ባነሳኸኝ ጊዜ) አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ። አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ።» «በትቀጣቸው እነርሱ ባሮችህ ናቸው። ለነርሱ ብትምርም አንተ አሸናፊው ጥበበኛው ነህ» (ይላል)።" (ሱረቱል ማኢዳህ 5፡117-118)።

በዚህ አንቀጽ መሠረት፡- የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) በዚህ ምድር ላይ አላህ የሱና የሰዎቹ ጌታቸው እንደኾነ ማስተማሩን ይመሠክራል። ወደ አላህም ከመነሳቱ (ከመወሰዱ) በፊት በሰዎቹ ጉዳይ ተጠባባቂ እንደነበርና፡ አላህ ወደራሱ ካነሳው በኋላ ግን ምንም የሚውቀው ነገር እንደሌለ፡ ይልቁኑ አላህ ተጠባባቂ እንደነበረና አላህም በሁሉም ነገር ዐዋቂ መኾኑን ይመሠክራል።

አያይዞም፡- እነዚህን እስራኤላውያን አመጸኞቹን ቢቀጣቸው የራሱ ባሮች ስለኾኑ መብቱ እንደኾነ፡ ቢምራቸው ደግሞ አሸናፊውና ጥበበኛው እሱ ብቻ እንደኾ በመግለጽ ፍርድ የአላህ ብቻ መኾኑን ይናገራል፡፡ የፈለገውን የሚምር የፈለገውን የሚቀጣ አላህ ብቻ ከኾነ፡ የመርየም ልጅ ወደዚህ ምድር የሚወርደው ሊፈርድ ነው ማለት ፍጹም ስህተት ነው!፡፡

4/ ከላይ መግቢያችን ላይ ወደጠቀስነው ሐዲሥ ስንመለስ፡ የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ወደዚህ ምድር ሲወርድ ‹‹ፍትሐዊ ዳኛ›› ወይም ‹‹ፍትሐዊ ፈራጅ›› ኾኖ ይወርዳል የሚለው፡ በአላህ ሸሪዐና ህግ ማስተዳደሩን ለመግለጽ እንጂ፡ የጀነት እና የጀሀነም ጉዳይን በኃላፊነት ተሸክሞ፡ አንዱን ለጽድቅ አንዱን ለኩነኔ አድርጎ በመለየት ለመፍረድ አይደለም አይኾንምም፡፡ በዚህ በቡኻሪይ ሐዲሥ ላይ የተጠቀሰውን፡ ኢማም አል-ቀስጦላኒይ፡ ኢርሻዱ-ሳሪይ በተሰኘው የቡኻሪይ መጽሐፍ ማብራሪያቸው ላይ፡ ይህን ሐዲሥ እንዲህ ይፈቱታል፡-

(حكمًا) حاكمًا أي بفتحتين (مقسطًا) عادلاً يقال أقسط إذا جار وقسط عدل إذا لا المحمدية الشريعة بهذه الأمة هذه حكام من حاكمًا ناسخة وشريعة مستقلة برسالة نبيًّا السارى إرشاد 105/4.

‹‹ፍትሐዊ ዳኛ/ፈራጅ›› ማለት፡- በነቢዩ ሙሐመድ ሸሪዓህ ከሚፈርዱ የዚህ ኡምመት ዳኞችና አስተዳዳሪዎች ውስጥ እሱም አንዱ ዳኛ ይኾናል፡፡ በዚሁ ሸሪዓህ እንጂ፡ በአዲስ መልኩ ነቢይና መልክተኛ ኾኖ አዲስ ሸሪዓም ይዞ አይደለም›› ይላሉ፡፡

5/ በአላህ ቃል ውስጥ፡ በጌታቸው ሸሪዓህ እንዲፈርዱ ስልጣን የተሰጣቸው ብዙ ነቢያቶች አሉ፡፡ ከሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም) በኋላ የመጡ ትእዛዝን የተቀሉ የእስራኤል ነቢያቶች በተውራት ህግ እንዲፈርዱ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል (ሱረቱል ማኢዳህ 5፡44 ተመልከት)፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) አላህ ባወረደው በቁርአን ህግ እንዲፈርዱ ታዘዋል (ሱረቱል ማኢዳህ 5፡ 48-49 ተመልከት)፡፡ እነዚህ ነቢያቶች ‹‹ይፈርዳሉ›› ማለት ግን፡ መዳኘትና ማስተዳደር፡ ህዝቡን ወደ ቀናው ጎዳና ማመላከት እንጂ፡ ስለ ጀነት እና ጀሀነም ፍርድ መስጠት አይደለም፡፡ የመርየም ልጅ ዒሳም (ዐለይሂ-ሰላም) ‹‹ይዳኛል ይፈርዳል›› ማለት ፡ በአላህ ህግና ስርአት ህዝቦቹን መምራት እንጂ፡ በሙታን እና በሕያዋን ላይ ለፍረድ አቅርቦ ውሳኔ መስጠት አይደለም፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

ሁሉን ዐዋቂ አይደለም!!

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና የሚለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ የተገባ ነው፡፡ የአላህ ውዳሴና ሰላም፡ የሰላም አለቃና መምህር ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ ይሁን፡፡ ድልና የበላይነት ሐቅን ለማንገስና ሀሰትን ለማርከስ፡ በደልን አጥፎቶ ፍትህን ለማስፈን ዕውቀታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ህይወታቸውን መስዋእት በማድረግ ለሚታገሉት ይሁን፡፡

"...مُؤْمِنِينَ كُنْتُمْ إِنْ لَكُمْ لَآيَةً ذَلِكَ فِي إِنَّ بُيُوتِكُمْ فِي تَدَّخِرُونَ وَمَا تَأْكُلُونَ بِمَا وَأُنَبِّئُكُمْ" عمران آل سورة 49

"...የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፤ የምታምኑ እንደሆናችሁ ለእናንተ በዚህ ዉስጥ በእርግጥ ታምር አለበት" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 49)፡፡

ከወገኖቻችን ዘንድ ይህን የቅዱስ ቁርአን አንቀጽ መሰረት በማድረግ የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ሁሉን እንደሚያውቅ መረዳት ይቻላል የሚል ድምጽ ይሰማል። ይህ ግን ፍፁም የተሳሳተ ግንዛቤ ነው። እንዴት ካሉም፡-

1ኛ/ ሁሉን ዐዋቂነት የጌታ አላህ ብቸኛ መለኮታዊ ባህሪው ነው። ይህን አምላካዊ ባህሪ ማንም ሊጋራው አይችልም። "አል-ዐሊም፣ አል-ዐልላም፣ አል-ኸቢር" በሚባሉ መለኮታዊ ስሞቹም የሚታወቀው እሱ ብቻ ነውና። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" يُبْعَثُونَ أَيَّانَ يَشْعُرُونَ وَمَا اللَّهُ إِلَّا الْغَيْبَ وَالْأَرْضِ السَّمَاوَاتِ فِي مَنْ يَعْلَمُ لَا قُلْ " النمل سورة 65

"በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ ሩቅ ምስጢር አያውቅም፤ ግን አላህ (ያውቀዋል)፤ መቼ እንደሚቀሰቀሱም አያውቁም በላቸው።" (ሱረቱ-ነምል 27፡65)።

" هُوَ إِلَّا يَعْلَمُهَا لَا الْغَيْبِ مَفَاتِحُ وَعِنْدَهُ..." الأنعام سورة 59

"የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው። ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም..." (ሱረቱል አንዓም 6፡59)።

" بِالنَّهَارِ وَسَارِبٌ بِاللَّيْلِ مُسْتَخْفٍ هُوَ وَمَنْ بِهِ جَهَرَ وَمَنْ الْقَوْلَ أَسَرَّ مَنْ مِنْكُمْ سَوَاءٌ * الْمُتَعَالِ الْكَبِيرُ وَالشَّهَادَةِ الْغَيْبِ عَالِمُ " سورة الرعد 10-9

"ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ ታላቅ የላቀ ነው። ከናንተ ውስጥ ቃሉን ዝቅ ያደረገ ሰው፥ በርሱ የጮኸም ሰው፥ እርሱ በሌሊት ተደባቂም፥ በቀን (ተገልጾ) ኺያጅም የሆነ ሰው፥ (እርሱ ዘንድ) እኩል ነው።" (ሱረቱ-ረዕድ 13፡9-10)።

2ኛ/ ጌታ አላህ ለመረጣቸው ነቢያቱና መልክተኞቹ ከዚህ የሩቅ ዕውቀት (ሚልሙል-ገይብ) የፈለገውን ያህል ያሳውቃቸዋል። የዕውቀት ሁሉ ምንጭ እሱ ነውና። ይህንንም የአላህ ቃል እንዲህ ይመሰክራል፡-

" رَصَدًا خَلْفِهِ وَمِنْ يَدَيْهِ بَيْنِ مِنْ يَسْلُكُ فَإِنَّهُ رَسُولٍ مِنْ ارْتَضَى مَنِ إِلَّا * أَحَدًا غَيْبِهِ عَلَى يُظْهِرُ فَلَا الْغَيْبِ عَالِمُ " الجن سورة 27-26

"(እርሱ) ሩቁን ሚስጢር ዐዋቂ ነው፣ በሚስጢሩ ላይ አንድንም አያሳውቅም። ከመልክተኛ ለወደደው ቢሆን እንጅ (ለሌላ አይገልጽም)..." (ሱረቱል ጂን 72፡26-27)።

"...يَشَاءُ مَنْ رُسُلِهِ مِنْ يَجْتَبِي اللَّهَ وَلَكِنَّ الْغَيْبِ عَلَى لِيُطْلِعَكُمْ اللَّهُ كَانَ وَمَا..." عمران آل سورة 179

"...አላህም ሩቁን ነገር የሚያሳውቃችሁ አይደለም፤ ግን አላህ ከመልክተኞቹ የሚሻዉን ይመርጣል..." (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡ 179)።

3ኛ/ የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) እሱም ቢሆን ለነቢይነቱና ለመልክተኛነቱ ማስረጃና አጋዥ ይሆነው ዘንድ ከፊል የሩቅ ሚስጥር ከጌታው አላህ ዘንድ ተሰጠው እንጂ፡ ሙሉ የሆነ ዕውቀት የለውም። ከላይ መግቢያ ላይ የተጠቀሰውም ማስረጃ ይህንኑ ሀሳብ የሚደግፍ እንጂ ሁሉን አዋቂነቱን የሚገልጽ አይደለም፤ እንዴት የሚሉ ከሆነም፡-

ሀ/ በአይነቱ የተገደበ መሆኑ፡- የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) እነግራችኋለሁ! እያለ ያለው ስለሚመገቡት ምግብ ብቻ ነው። ስለሚያስቡት፣ ነገ ስለሚደርሳቸው/ስለሚደርስባቸው፣ ስለሚወለደው/ስለሚሞተው... አይደለም። ከምግብ ጋር ብቻ የተገናኘ ነው። ይህም በአንድ ነገር ላይ የተገደበ ዕውቀት ብቻ ነው።

ለ/ በቦታ የተገደበ መሆኑ፡- የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) የምትበሉትን እና የምታደልቡትን እንግራችኋለሁ በማለት እየተናገረ ያለው በወቅቱ የተነበሩትን የሱን ቃል የሚሰሙትን ህዝቦች እንጂ፡ በሌላ የምድር ወለል ላይ የሚኖሩ ህዝቦችን አይደለም። ስለነሱ ማወቅ አይችልምና። ስለሆነም ‹‹የምትበሉትን›› አለ እንጂ ‹‹የሚበሉትን›› ብሎ ስለሌላው አልተናገረም።

ሐ/ በጊዜ የተገደበ መሆኑ፡- የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ሰዎቹ ከዚህ በፊት ስለ ተመገቡት ነገር አውቃለሁ አላለም፡፡ ከዚህም በኋላ እስከመጨረሻው የሚበሉትን አውቃለሁ አላለም፡፡ እሱ ያለው "የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም" ብቻ ነው፡፡ ማደለብ ማለት፡- ለነገ ለከነገወዲያ የሚሆን ምግብን ቀድሞ ማከማቸት ማለት ነው፡፤ ለዕድሜ ልክ የሚል ትርጉም ፈፅሞ አይኖረውም፡፡

4ኛ/ የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) በአንደበቱ እንደሚመሰክረው፡- እሱ አላህ ዘንድ ያለውን እንደማያውቅና በተቃራኒው ጌታው አላህ ግን በሱ ዘንድ ያለውን ሁሉ እንደሚያውቅ ነው፡፡ ስለዚህ ዒሳ ሁሉን ዐዋቂ አልነበረም፡፡ አይደለምም፡፤ አይሆንምም፡-

"...الْغُيُوبِ عَلَّامُ أَنْتَ إِنَّكَ نَفْسِكَ فِي مَا أَعْلَمُ وَلَا نَفْسِي فِي مَا تَعْلَمُ" المائدة سورة 116

"...በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፤ ግን ዘንድ ያለውን አላውቅም፤ አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና" (ሱረቱል ማኢዳህ 5፡116)፡፡

ኢየሱስ(አሰ) ነቢይ ነው

ቁርአን ሲናገር፡-

- 19:30 ሕፃኑም አለ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፤ መጽሐፍም ሰጥቶኛል ነቢይም አድረጎኛል።
- 61:6 የመርየም ልጅ ዒሳም የ እስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደናንተ የተላክሁ የአላህ መልክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልፅ ድግምት ነው አሉ።

ባይብል ሲናገር፡-

- Matthew 13:57 ኢየሱስ ግን፡- ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው።
- Mark 6:4 ኢየሱስም። ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ዘመዶቹ ከገዛ ቤቱም በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው።
- ሉቃ4:24 እንዲህም አለ። እውነት እላችኋለሁ፥ ነቢይ በገዛ አገሩ ከቶ አይወደድም።
- ዮሐ.4:44 ነቢይ በገዛ አገሩ እንዳይከበር ኢየሱስ ራሱ መስክሮአልና።
- ሉቃ13:33 ዳሩ ግን ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ አይገባውምና ዛሬና ነገ ከነገ በስቲያም ልሄድ ያስፈልገኛል።
- Matthew 21:11 ሕዝቡም።፡- ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው አሉ።
- ሉቃ7:16 ሁሉንም ፍርሃት ያዛቸውና። ታላቅ ነቢይ በእኛ መካከል ተነሥቶአል፥ ደግሞ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ጐበኘ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።
- ሉቃ24:19 እርሱም። ይህ ምንድር ነው? አላቸው። እነርሱም እንዲህ አሉት። በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየሱስ፤
- ዮሐ.4:19 ሴቲቱ። ጌታ ሆይ፥ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ።
- ዮሐ.6:14 ከዚህ የተነሣ ሰዎቹ ኢየሱስ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ። ይህ በእውነት ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ነው አሉ።
- ዮሐ.7:40 ስለዚህ ከሕዝቡ አያሌ ሰዎች ይህን ቃል ሲሰሙ። ይህ በእውነት ነቢዩ ነው አሉ፤
- ዮሐ.9:17 በመካከላቸውም መለያየት ሆነ። ከዚህም የተነሣ ዕውሩን። አንተ ዓይኖችህን ስለ ከፈተ ስለ እርሱ ምን ትላለህ? ደግሞ አሉት። እርሱም። ነቢይ ነው አለ።
- እየሱስ አላቸዉ እኔ ከእግዚአብሄር ወጥቸ መጥቻለሁና እሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁም። (የዩሀንስ ወንጌል 8:42)

እየሱስ ጌታ(አምላክ) አለመሆኑ

ከብዙ በትንሹ:

- ከእእግዚአብሄር የሰማሁትን የነገርኩዋቸሁን ሰዉ ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ። (የዩሀን ወንጌል 8:40)
- እኔ ከራሴ አልተናገርኩምና ነገር ግን የላከኝ አብ የሚለዉን የሚናገረዉንም ትእዛዝ ሰጠኝ። (የዩሀንስ ወንጌል 12:49)
- የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነዉ እንጂ የኔ አይደለም። (የዩሀንስ ወንጌል 14:24)
- ከኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር ። (የዩሀንስ ወንጌል 14:28)
- ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ። (የዩሀንስ ወንጌል 20:17)
- አንተ እንደላከኝ አለም ያምን ዘንድ። (የዩሀንስ ወንጌል 17:20)
- ስለዚህ እየሱስ እንዲህም አላቸዉ እዉነት እዉነት እላችሃለሁ።አብ ሲያደርግ ያየዉን እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም። (የዩሀንስ ወንጌል 5:19)
- እኔ ከራሴ አንዳች ነገር ላደርግ አይቻለኝም። እንደሰማሁ እፈርዳለሁ። ፍርዴም ቅን ነዉ። የላከኝ ፍቃድ እንጂ ፍቃዴን አልሻምና። እኔ ስለራሴ ብመሰክር ምስክሬ እዉነት አይደለም። (የዩሀንስ ወንጌል 5:30-32)
- አብ ልፈፅመዉ የሰጠኝ ስራ ይህን የማደርገዉ ስራ እንደላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራል። የላከኝ አብም እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል። (የዩሀንስ ወንጌል 5:39)
- እየሱስ መልሶ ይህ የእግዚአብሄር ስራ እርሱ በላከዉ እንድታምኑ ነዉ። (የዩሀንስ ወንጌል 6:29)
- ስለዚያች ቀንናስለዚያች ሰአት ግን ከአባት ብቻ በቀር መላክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን አያዉቁም። (ማቴዎስ ወንጌል 24:36)

ኢየሱስ (ዒሳ(ዐ.ሰ)) የተገለጸበት ንጽጽር

(ቅዱስ ቁርዓን) vs (በባይብል) (ቁጥር 1)

ኢየሱስ ከሰይጣን ጋር ያለው ንጽጽር

(በባይብል)

‹‹አርባ ቀን በዲያብሎስ (በሰይጣን) ተፈተነ። በነዚያም ቀኖች ምንም አልበላም፥ ከጨረሱም በኋላ ተራበ። ሉቃስ 4፡2

‹‹አምላክ በዲያብሎስ ›› በሰይጣን ተፈትኖዋል? መልሳቸው ነው ፤ በዚህ ሳያበቃ ሰይጣን ሲያዘዋውረው ነበርም ይላል ባይብል

☞‹‹ዲያብሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ። (ማቴ 4፡5-10)

(ቅዱስ ቁርዓን)

እንደቁርዓን ዒሳ(ዐ.ሰ) ኢየሱስ ሆነ እናቱን አላህ ከዲያቢሎስ(ከሰይጣን) ጠብቋቸዋል።መርየም(ማርያም) በተወለደች ጊዜ እናቷ እንዲህ ስትል አላህን ለመነች

‹‹…እኔም እስዋንም ዝርያዋንም ከተረገመው ሰይጣን በአንተ እጠብቃቸዋለሁ» አለች።›› (ኢምራን 36)

የባሪያዎቹን ጸሎት ከንቱ የማያደረገው አምላካችን አላህ(ሱወ) ልመናዋን ሰማ….. ቁጥር 37 ላይ መልሱን ሲናገር

☞‹‹ጌታዋም በደህና አቀባበል ተቀበላት። በመልካም አስተዳደግም አፋፋት።. ..››(ኢምራን 37)

ኢየሱስ ከሰይጣን የተጠበቀ(ቁርአን) ≠ ኢየሱስ በሰይጣይ የተፈተ፤ የተወሰደ (መፅሐፍ ቅዱስ)

ኢየሱስ (ዒሳ (ዐ.ሰ)) የተገለጸበት ቁጥር 2

የመጀመሪያ የኢየሱስ ተዐምር ባይብል ውሃን ወደ ወይን ጠጅ መቀየር ነው ይለናል የዮሐንስ ወንጌል 2፡1-11: 7 ኢየሱስም፡- ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው።

8: አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው፤ ሰጡትም።

9: አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር፤ አሳዳሪው ሙሽራውንጠርቶ።

10: ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው።

11:ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ። (የዮሐንስ ወንጌል 2፡1-11)

ይህ ‹‹ተአምር›› በእርግጥ በቅዱስ ቁርዓን እውቅና ይለውም በመሰረቱ አስካሪ መጠጥ መጠጣት ፤ማጠጣት፤ መሸጥ፤መተባበር … አርም ስለሆነ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ባይበል ላይ መጠጥ የሚፈቀድም የሚከለክሉ አንቀፆች ይገኛሉ፡፡

ቅዱስ ቁርዓን እንደሚታወቀው ኢየሱስ የተጸነሰው የለአባት ነው ታዲያ ቅድስት መርየም (ማርያም) ልጁ ተሸክም ስትመጣ እነዚያ

ጋጠ ወጥ አይሁዶች አፈጠጡባት ልጁት ከየት አመጣሽው? እናትሽ አመንዝር አይደለችም; የቃላት ወርጅብኝ ከቀኝ ከግራ ተወረወረባት። በሀሰት ለመወንጀል አሰፈሰፉ ታዲያ ምንም ቢባሉ የማይሰሙ እነዚህ ሰዎችን ትታ ወደ ልጁን(ኢሳን (አሰ)) አመለከተቻቸው ‹‹ ወደርሱም ጠቀሰች፡፡ «በአንቀልባ ያለን ሕጻን እንዴት እናናግራለን!» አሉ፡፡ መርየም 19፡ 29-37

በዚ ወሳኝ ሰዓት ነው እጅግ አስደማሚ የሆነ ተዓምር የተከሰተው ለቁርዓን ቦታውን ልልቀቅ

‹‹(ሕፃኑም) አለ «እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፡፡ መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል፡፡» (መርየም 19፡30)

«በየትም ስፍራ ብሆን ብሩክ አድርጎኛል፡፡ በሕይወትም እስካለሁ ሶላትን በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል፡፡» (መርየም 19፡ 31)

«ለእናቴም ታዛዥ (አድርጎኛል) ፡፡ ትዕቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም፡፡ (መርየም 19፡32)

«ሰላምም በእኔ ላይ ነው፡፡ በተወለድሁ ቀን፣ በምሞትበትም ቀን፣ ሕያው ሾኜ በምቀሰቀስበትም ቀን፡፡» (መርየም 19፡33)

‹‹ ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው፡፡ ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው፡፡›› (መርየም 19፡34)

‹‹ ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም፡፡ (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ፡፡ ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው «ኹን» ነው ወዲያውም ይኾናል፡፡ (መርየም 19፡35)

‹‹(ዒሳ አለ) «አላህም ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት፡፡ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው፡፡» (መርየም 19፡36)

‹‹ከመካከላቸውም አሕዛቦቹ በእርሱ ነገር ተለያዩ፡፡ ለእነዚያም ለካዱት ሰዎች ከታላቁ ቀን መጋፈጥ ወዮላቸው፡፡ (መርየም 19፡ 37).ይህ ደግሞ ባይብል ላይ የለም ። ቁርዓን ላይ ግን አለ፡፡

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፡፡ (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና፡፡ 5፡90

- ኢየሱስ የመጀመሪያ ተአምር ውሃን ወደ ወይን መቀየር (የዮሐንስ 2፡1-11) VS ኢየሱስ የመጀመሪያው ተአምር በአንቀልባ ላይ እያለ መናገሩ(ማውራቱ) (ሱረቱል መርየም 19፡ 29-37)

የትኛውን ይመርጣሉን?

4.ስቅለት

እውን ኢየሱስ ተሰቅሏልን?

ኢየሱስ ክርስቶስ በፍላንቱ ነውን የተሰቀለው?

**እንደ ክርስቲያኖች እምነት ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ ሆኖ ነው የመታው ተሰቅሎ በመሞት አለምን አድኗል ይህ ከሆነ የመታበትን ዓላማ ያውቃልና ቀጥታ ዓላማውን አስረድቶ መሰቀል ነበረበት ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንደምንረዳው ኢየሱስ ክርስቶስ ያለፍላንቱ ተፈልጎ በይሁዳ ተሸጦ ነው የተሰቀለው፡፡ ታዲያ ሳይወድ የተሰቀለ ከሆነ እንዴት ለኛ ሲል ተሰቅሎ ምህረትን አደረገ በማለት እሱ ይመለካል? ቢሆን እንኳ የላከው እግዚአብሔር ብቻ ነው መመስገንም በብቸኝነት መመለክም የሚገባው፡፡ በተጨማሪም የኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀል ለሰው ልጆች ሀጢያት መሰረይና መዳን ትልቅ ቦታ ካለው፤ ስቅለት ከሌለ መዳን የለም የሚባልም ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወዶ አልተሰቀለም ይልቁንም ይሁዳ ነው ክዶት በ30 ብር አሳልፎ ሰጥቶት እንዲሰቀል ያደረገው፡፡ ታዲያ ይሁዳ አይደል ህ ሁሉ የእምነቱ ተከታይ ድኜበታለሁ ብሎ የሚያስበውን የኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት ተፈጻሚ እንዲሆን በማድረግ መዳን እውን እንዲሆን ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረገው፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መሸሸ ሊቀር የነበረውን የስቅለት ምህረት ይሁዳ አሳልፎ በመስጠት እውን እንዲሆን በማድረጉ ዋነውን ስራ ሰርቷል ታዲያ ይሁዳ ለምን ይነቀፋል፤ ይጠላል፤ ከሀዲ ይባላል? ይሁዳ ባይክድ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሰቀል ነበርን?

የሚከተሉትን የኢየሱስን ያለፍላንት መሰቀል የሚያሳዩ ጥቅሶች እንመልከት፡-

≠ ዮሐንስ 7፡1 ‹‹ከዚያም በኃላ ኢየሱስ አይሁዶች ሊገድሉት ይፈልጉት ነበር በይሁዳ ሲመላለስ አልወደደም ነበርና በገሊላ ይመላለስ ነበር፡፡››ፈርቶ በሌላ ከተማ ተመላለሰ ለምን?

≠ዮሀንስ 11፡53-54 ‹‹እንግዲህ ከዚያን ቀን ጀምሮ ሊገድሉት ተማከሩ ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ በአይሁድ መካከል ተገልጦ አልተመላለሰም››^^^ ፈርቶ ተሸፋፈነ ለምን?

≠ዮሐንስ 10፡39 ‹‹ደግመው ሊይዙት ፈለጉ ከእጃቸው ወጣ››አመለጣቸው ለምን?

≠ ዮሐንስ 18፡22-23 ‹‹ኢየሱስ መልሶ ክፉ ተናግሬ እንደሆንኩ ስለ ክፉ መስክር መልካ ተናግሬ እንደሆነ ግን ለምን ትመታኛለህ? አለ››^^^ እንዳይመቱት ተማፀነ ለምን?

≠ ማቴዎስ 27፡46 እንዲህ ይላል “በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም። አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ? ማለት ነው።”በሌላም ቦታ በማቴዎስ ወንጌል 26፡39 ላይ እየሱስ “አባት ሆይ! ቢቻል ይህ ፅዋ ከእኔ ይለፍ፤^^^ የእርዳታ ጥሪ አቀረበ ለምን?

ሌሎችም በርካታ ሳይፈልግ መሰቀሉን የሚያሳዩ ጥቅሶች ያሉ ሲሆን ከጥቅሶቹ በግልጽ የምንረዳው ያለፍላንቱ የደረሰበት መከራ ነው፡ ፡አንዳንድ የሀይማኖቱ ተከታዮች ትህትና ለማሳየት ብሎ ነው ይላሉ ትህትናን ማሳየት መፍራት፤ መሸሽ፤ ማምለጥ …..ወዘተ ምን አገናኘው ለማሳየት የሚደርስበትን ነገር ሁሉ በጸጋ መቀበል ነው እንጂ በማለጥ፤ በመፍራ ፤ በመደበቅ፤ ብሎም በሌላ ጥቆማ ደርሶበት እስኪያዝ መጠበቅ ነው እንዴ? ኢየሱስ ክርስቶስ እውን ትንቢቱን አማልቷልን?

አይሁዳዊያን ነብያትን የመፈታተን ባህሪ ስለነበራቸው ኢየሱስ ክርስቶስም እንዲሁ ተፈታትነውታል፡፡በመሆኑም ከሱ ምልክት ማየት አጥብቀው ሲጠይቁት

ማቴዎስ ወንጌል 12፡40 ላይ ‹‹አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል ከነብዩ ዮናስ በላይ ምልክት የለም ነብዩ ዮናስ በአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ ሶስት ቀንና ለሶስት ሌሊት እንደነበረው የሰው ልጅም በምድር ልብ ውስጥ ለሶስት ቀንና ለሶስት ሌሊት ይኖራል›› ብሎ ተንብዮአል፡፡ ይህንን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢት ከሞት መነሳቱ ጋር በማያያዝ

ማቴዎስ ወንጌል 27፡63 ‹‹ጌታ ሆይ ያ አሳች በሕይወት ገና ሳለ ከሶስት ቀን በኃላ እነሳለሁ እንዳለ ትዝ አለን››

ሉቃስ 24፡46 ‹‹ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሶስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሳል›› ተብሎ ተጽፏል

****ነገር ግን ዋናው ጥያቄ ትንቢቱ ተፈጽሟል ወይ ነው እስኪ እንመልከት፡- መጀመሪያ ትንቢቱን እናብራራ ነብዩ ዮናስ በአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ ለሶስት ቀናትና ለሦስት ሌሊቶች ህያው ነበር አልሞተም ከአሳው ነባሪ ሆድ ውስጥም ሲወጣ ህያው ነበር አልሞተም ነበር ኢየሱስም የሰው ልጅ ሳይሞት በምድር ልብ ውስጥ ለሶስት ቀናትና ሌሊቶች ይቆያል ብሏል፡፡ ይህ ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ ተነሳ ለማለት ከዛ በላይ በምድር ልብ ውስጥ መቆየት አለበት ማለት ነው፡፡

****እውን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ ተነሳ ለማለት በምድር ልብ ውስጥ ለሶስት ናትና ሌሊቶች ቆይቷልን? የሚከተለውን ሰንጠረዥ በማየት የራሳችንን ፍርድ እንስጥ አርብ ኢየሱስ ማምሻ ላይ ተቀበረ፣ እሁድ ጠዋት መቃብር ውስጥ አልነበረም

በሰንጠረዡ እንደምንመለከተው አንድ ሙሉ ቀንና ሁለት ሌሊቶችን ነው ኢየሱስ በምድር ልብ ውስጥ የቆየው ትንቢቱ አአልተሟላም ማለት ነው፡፡ በሰዓታት እንመልከት 3 ቀንና 3 ሌሊት 72 ሰዓታት ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ግን በመቃብር ውስጥ የቆው አርብ ሌሊት ብቻ 12 ሠዓት ቅዳሜ ቀንና ሌሊት 24 ሠዓት እሁድ ምንም በጠቅላላው 36 ሠዓታት ብቻ ነው በምድር ልብ ውስጥ የቆየ፡፡ ታዲያ ኢየሱስ ትንቢቱን አልፈጸመም ማለት ነው?

ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ትንቢተ የተነበየው ሞቶ አለመነሳቱን ለማሳየት ብቻና ብቻ መሆኑን ልብ ይሏል!!

ማሳረጊያ

“ኢየሱስ ተሰቅሏል” የሚለው እምነት ለመልስ አዳጋች የሆኑ አያሌ ጥያቄዎችን ያስነሳል:: አንዳንዶቹንም እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡-

1. ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ መስጠቱ ወንጀል ነውን? ለመሆኑ ማን እንደ ይሁዳ መልካም ሰራ ? እርሱ ኢየሱስን አሳልፎ ባይሰጠው ይሰቀል ነበርን? ታድያ በኢየሱስ መሰቀል ክርስትያኖች “ዳንን ” ይሉ የለ? ይህ ሁሉ ክርስትያን “ገነት እንዲገባ” ምክንያት የሆነው የይሁዳ ስራ አይደለምን? ታዲያ ይወገዝ ወይስ ይወደስ? እንደ ክርስትና አስተሳሰብ ሰው ሁሉ የዳነው እና ከገሀነም ነፃ የሆነው በኢየሱስ መሰቀል ነው። ታዲያ እንደ ክርስትና አስተምህሮት ክርስትያን ሁሉ በይሁዳ ትከሻ ላይ አይደል ገነት የገባው?
2. በማቴዎስ 9:13 ላይ “ከመስዋዕት ይልቅ ምህረትን እወዳለሁ” ይላል። አምላክ “ከመስዋዕት ይልቅ ምህረትን እወዳለሁ” እያለ እንዴት ዓለም በሰራው ሀጢያት ምህረት ማድረግ ሲችል ኢየሱስን በማሰቃየት መሰዋት አደረገው?
3. “እግዚአብሄር ወልድ” ሞቷልን? ክርስቲያኖች “አዎን” ይላሉ? ታዲያ አምላክ (እግዚአብሔር) ይሞታል? የአምላክ ክፍልና አካል ይሞታል? እንዲያው እንዴት ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን “እግዚአብሔር ወልድ” ብሏልን? እስቲ የቱ ጋር?

4. ከ2000 አመት በፊት እየሱስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ቤዛ ሆኖ ከተሰቀለ፣ ዛሬም ከስቅሉ በኃላ እንዴት “የሰው ልጆች ሁሉ በሀጢአት ውስጥ ናቸው” ይባላል?
5. ኢየሱስ ለዓለም ቤዛ ሆኖ ሰውን ነፃ ለማውጣት ከመጣ ስለ ኢየሱስ ጭራሽ ያልሰሙት ከርሱ መወለድ በፊት የነበሩ ህዝቦች በምን ሊድኑ ነው?
6. . ምንም ቢሰሩ ሁሉም ክርስትያኖች በኢየሱስ መሰቀል በማመን ብቻ መንግስተ ሰማያት የሚገቡ ከሆነ የኢየሱስ አስተምህሮት ምኑ ላይ ነው ጥቅሙ? ኢየሱስ “መልካም” “እኩይ” እያለ ሲያብራራቸው የነበሩት አስተምህሮቶች ሁሉ ምን ይፈይዳሉ? ካላችሁ በኢየሱስ መሰቀል አምነው እየሱስ «ክፉ» ያላቸውን ተግባራት ቢፈጽሙና ባይፀፀቱ ገሀነም የገባሉ ማለት ነውን?
7. ክርስቲያኖች ወደር የለሹና የማይቀየረው አምላክ በመስቀሉ ላይ ስቃይን ሞትን ተቀበሏልን? የሚል ደረቅ ጥያቄ ሲቀርብላቸው መልሳቸው “የክርስቶስ ሰብአዊ ህሊናና ነፍስ ነው የሞትን ጣእር የቀመሰው እንጂ መለኮታዊ ገፅታው አይደለም” የሚል ነው። ታዲያ በምን አይነት ሁኔታ ነው ወደር የለሽ የሆነው አካል ለኛ ሲል ስቃይና ሞትን ተቀብሏል ለማለት የደፈሩት?
8. ኢየሱስ መሰቀል ላይ ሆኖ “አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውከኝ” ብሎ ሲለምን አምላክ ነበር ወይስ ሰው? ሰው ከሆነ የሞተው ኢየሱስ የተባለው ግለሰብ ነበር ማለት ነው:: እንዴትስ አምላክ ሌላ አምላክ የለምናል? የማይሞተው እግዚአብሔር አምላክ ሞተ ይባላልን?
9. ዮሐንስ 13: 13 “ልጆቼ ሆይ! ከእናንተ ጋር የምቆየው ለጥቂት ግዜ ነው እናተም ትፈልጉኛላችሁ: ለአይሁድ እኔ ወደምሄድበት ልትመጡ አትችሉም ” እንዳልኳችሁ: አሁን ለእናተ ይህንኑ እላችኃለሁ:: ይላል በዚህ ጥቅስ ላይ ኢየሱስ ለአይሁዶች “እኔ ወደ ምሄድበት ልትመጡ አትችሉም” ብሏል:: ታድያ እንዴት ያለበት ድረስ መጥተው “ያዙት” “ሰቀሉት” ሊባል ቻለ? ወይስ ኢየሱስ ዋሸ? አሊያም እንደሚያዝ አያውቅም ነበርን?
10. ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ “በዘጠኝም ስዓት ኢየሱስ: ኤሎሄ: ኤሎሄ ለማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ: »ትርጓሜውም “አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ?” ማለት ነው:: (የማርቆስ ወንጌል 15: 34 እና ማቴዎስ 27: 46) ሲል አምላክ ከስቅለቱ እንዲያድነው በጩኸት ለምኗል:: በማቴዎስ 26: 53 ላይ “ካስፈለገ አባቴን ብጠይቀው ከዐስራ ሁለት ከፍል ሰራዊት የሚበልጡ መላእክት የማይሰድልኝ ይመስልሃል?” ሲል ተናግሮ ነበር:: ታድያ ኢየሱስ ‘አምላኬ’: አምላኬ ለምን ተውከኝ? ብሎ በጩኸት እየለመነ: እንዴት የተባለው ጦር መጥቶ ከስቅለት ሳያድነው ቀረ?
11. ሎቃስ 22: 36 “እርሱም እንዲህ አላቸው: “አሁን ግን ኮሮጆም ከረጢትም ያለው ሰው ይያዝ: ሰይፍ የሌለውም ልብሱን ሽጦ ይግዛ::” ይላል:: ኢየሱስ በዚህ ጥቅስ ላይ “ሰይፍ የሌለውም ልብሱን ሽጦ ይግዛ” ብሏል:: ለምን? በሰይፍ እንዳይሰቀል እንዲከላከሉለት? ሊሰቀል “መጣ” የተባለው ሰው እንዴት ሃሳቡን ሊቀይር ቻለ?
12. ማቴዎስ 4: 17 “ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ፦ መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ: እያለ ይሰብክ ጀመረ::” ይላል:: ክርስትና መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ “ኢየሱስ ለኛ ሲል ተሰቅሎ መሞቱን ማመን ግዴታና ብቸኛው መዳኛ ነው” ሲል ያስተምራል:: ኢየሱስ ”መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ” በማለት ከሚሰብክ ብቸኛው መዳኛ እርሱ ለሰው ልጅ ኃጢአት ቤዛ ሆኖ መሰቀሉንና መሞቱን ማመን ከሆነ “መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና እኔ ለእናንተ ተሰቅዬ ልሞት መሆኑን እመኑ” በማለት እንዴት ሳይሰብክ ቀረ?
13. መዝሙር 34: 17 ላይ “ቅኖች”ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉ እርሱም ይሰማቸዋል ከችግራቸውም ሁሉ ያድናቸዋል::” ይላል:: ታዲያ «አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውከኝ? »እያለ ኢየሱስ ሲጮህ «ቅን» ስላልሆነ ነው ያልተሰማው? ከሞትስ ያላዳነው? ወይስ ቅን ስለሆና ከሞት ድኗል?
14. ማቴዎስ 8: 17 ኢሳያስ 53: 12: ኢሳያስ 53: 4: ሎቃስ 2: 30: ኢሳያስ 52: 10 እና ሉቃስ 22: 32 ላይ «ይመጣል»

ተብሎ የተተነበየው መሲህ ኢየሱስ ከነበረ ይህ መሲህ እንደማይገደልም ተገልጿል:: ታድያ እንዴት ኢየሱስ «ሊገደል ቻለ »ተብሎ ይታመናል?

15. የሰው ልጅ አደም በፈፀመው ኃጢአት ምክንያት ኃጢአት የመስራት ዝንባሌንና ባህሪን ከወረሰ እንዲሁም ይህ ዝንባሌ በኢየሱስ ስቅለት በደሙ ከነፃ: ለምን ያ ዝንባሌ አሁንም ቀጥሎ ሰው ወንጀል እየሰራ ሊቀጥል ቻለ?

ኢየሱስ(ኢሳ)(ዐሰ) ተመልሶ ይመጣል

ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር(ረ.ዐ) ነብዩ ሙሐመድ ሰዕወ የሚከተለውን ሲናገሩ ሰምተዋል የመርያም ልጅ የሆነው ኢየሱስ ወደ መሬት ይመለሳል።ትዳር ይመሰርታል።ልጆችም የወልዳል።ለ አርባ ዓመታትም ይኖራል።ከዚያም ይሞታል፣ከኔ ጎንም ይቀበራል(በዕለተ ት ንሳኤም) ከ አቡበከርና ከዑመር ከሚገኘው መካነ መቅብራችን እኔና ኢየሱስ በ አንድነት እንቀሰቀሳለን(ኢብኑ አልጀውዚ ኪታቡ አል ወፍ)

አቡ ሁራይራ እንደዘገቡት የ አላህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ተናግረዋል፥ ”እኔ የእየሱስ በዚህ ዓለምም ሆነ በተከታዩ ዓለም እጅግ በጣም ቅርብ ወዳጁ ነኝ።ነብያት ወንድማማቾች ናቸው።አባታቸውም አንድ ሲሆን እናቶቻቸው ይለያያሉ። ሃይማኖታቸው ግን አንድ ነው። በእኔና በእየሱስ መካከል ሌላ ነብይ የለም።”(ቡኻሪ እና ሙስሊም ዘግበውታል)

የእየሡሥ ባሪያነት በቁርአን & በመፅሐፍ ቅዱስ

● በመጀመሪያ *ባሪያ* ማለት ተገዢ ፤ አምላኪ ፤ ለፈጣሪ መታዘዝን ያመለክታል ።ባሪያ የሚለው ቃል በመፅሐፍ ቅዱስም ይሁን በቁርአን በተደጋጋሚ ተጠቅሷል ። እንደውም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ 966 በላይ ግዜ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል ። ከመጠቀስም አልፎ በርካቶች የእግዛብሄር ባሪያ ተሰኝተዋል ፥

ለምሳሌ ፦ መዝሙረ ዳዊት 18:1፥ ለመዘምራን አለቃ ከሳኦል እጅና ከጠላቶቹ ሁሉ እጅ እግዚአብሔር ባዳነው ቀን በዚህ መዝሙር ቃል ለእግዚአብሔር የተናገረው *የእግዚአብሔር ባሪያ* የዳዊት መዝሙር።

ትንቢተ ኤርሚያስ 33:26 ፥ እኔም ደግሞ በአብርሃምና በይስሐቅ በያዕቆብም ዘር ላይ ገዦች ይሆኑ ዘንድ ከዘሩ እንዳልወስድ፥ የያዕቆብንና *የባሪያዬን* የዳዊትን ዘር እጥላለሁ፤

¤ በቁርአን ሁሉም ፍጥረት እየሱስንም ጨምሮ የአላህ ባሪያ እንደሆንን ይነግረናል ፦

Surah 19 Ayah 93 በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአልራሕማን *ባሪያ* ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም::

Surah 4, Ayah 172 አልመሲሕ (ኢየሱስ) *ለአላህ ባሪያ* ከመኾን ፈጽሞ አይጠየፍም:: ቀራቢዎች የኾኑት መላእክትም (አይጠየፉም)::

Surah 19, Ayah 30 ሕፃኑም) አለ «እኔ *የአላህ ባሪያ* ነኝ:: መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል::»

¤ አንዳንድ ክርስቲያን ነን ባዮች እራሳቸውን ከባሪያነት ነፃ ወጥተናል ይላሉ ፤ በእርግጥ ለአምላክ መታዘዝ ፥ ተገዢ መሆን የሚያኮራ እንጂ የሚያሳቅቅ አይደለም። የሚገርመው የክርስትና ሐይማኖት መምህሮች መፅሐፍ ቅዱስ ላይ እንደፈለጉ የሚጨምሩ የሚቀንሱ ሲያሻቸው ብዙ ታሪኮችን የሚያዘበራርቁ እንደሆኑ በርካታ ግዜ ለመግለፅ ሞክረናል ። እነሆ ዛሬ ባሪያ የሚለው ቃል እነዚህ አካላቶች በመፅሃፍ ቅዱስ ብላቴና ብለው ቀይረውታል ።የእንግሊዘኛ መፅሃፍ ቅዱስ እንኳ my servant (ባሪያዬ) ብሎታል የእንግሊዘኛው መፅሃፍ ቅዱስ ባሪያ ብሎ ገልፆ አማርኛው ትርጉም ላይ ብላቴና ማለቱ ለምን አስፈለገ ??

እነሆ ደግፌ የያዝሁት *ባሪያዬ* ፤ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ፤ትንቢተ ኢሳያስ 42:1

Isaiah: 42. 1. Behold *my servant,* whom I uphold; mine elect, in whom my soul delighteth; I have put my spirit upon him: he shall bring forth judgment to the Gentiles

● ተመልከቱ ጉድ እንግዲህ የአማርኛ መፅሃፍ ቅዱስ ትርጉም ብላቴናዬ ይላል የእንግሊዘኛው መፅሃፍ ቅዱስ ትርጉም my servant (ባሪያዬ) ይላል ፤ ምን ያህል መፅሃፍ ቅዱስን እንደተቀየር መታዘብ ይቻላል ፤

የማቲዎስ ወንጌል 12:18 እነሆ የመረጥሁት #ብላቴናዬ፥ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ወዳጄ፤ መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፥

Matthew: 12. 18. Behold my #servant, whom I have chosen; my beloved, in whom my soul is well pleased: I will put my spirit upon him, and he shall shew judgment to the Gentiles.

የሐዋሪያት ሥራ 4:29-30 አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ #ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፥ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው።

Acts: 4. 29. And now, Lord, behold their threatenings: and grant unto thy * servants,* that with all boldness they may speak thy word,

የአብርሀምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ፥ የአባቶቻችን አምላክ፥ እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትንና ሊፈታው ቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችሁትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው። የሐዋሪያት ስራ 3:13

።። በተረፈ አሏህ ቅኑን መንገድ ይምራችሁ በአንድነት ውስጥ ሶስትነት የሌለው ፤ የማይሞት የዘላለም ህያው ፤ ሐያል የሆነው አሏህ ትክክለኛ መንገድ ወደ ኢስላም እንዲመራችሁ ምኞቴ ነው።

ኢየሱስ ማን ነዉ ?

ይህንን ጥያቄ ኢየሱስ ማን ነዉ የሚለውን ጥያቄ ኢየሱስ ራሱ መልሶታል የፈጣሪ መልዕክተኛ ነዉ ::

የሚከሉትን ጥቅሶች እንመልከት

(1ኛ) ዩሐንስ 17፡3) " እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያወቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት። " ኢየሱስ መልክተኛ መሆኑን " የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ" እያለ የአንዱ አምላክ መልክተኛ መሆኑን ግልጽ አድርጓል

(2ኛ) ዩሐንስ 5፡24 "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።" ኢየሱስ ክርስቶስ " የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ " እያለ መልክተኛ መሆኑን ግልፅ አድርጎ አስተምሯል ።

(3ኛ)ዩሐንስ 14፡24 "የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፤ የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።"

"የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።" ኢየሱስ እዚህ ጋ የላከዉም ማን እንደሆነ ግልጽ አድርጓል " የላከኝ የአብ ነው " ኢየሱስ መቸም ወልድ እንደሆነ ግልጽ ነዉ ደቀመዛሙርቱ እና ሐዋርያት ክርስቶስን ማነው ብለው አመኑ ?

መልሱን ለመጽሐፍ ቅዱስ እንተወው::

(4)(ዩሐንስ 17፡6-11) ፡- " 6 ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው። የአንተ ነበሩ ለእኔም ሰጠሃቸው፤ 7 ቃልህንም ጠብቀዋል። የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ አሁን ያውቃሉ፤ 8 የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፥ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፥ አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ። 9 እኔ ስለ እነዚህ እለምናለሁ፤ ስለ ዓለም አልለምንም ስለ ሰጠኸኝ እንጂ፤ የአንተ ናቸውና፤ "ደቀመዛሙርት ክርስቶስን መልክተኛ ነዉ ብለው ልክ እንደ ሙስሊሞች አመኑ ። እምነታቸውን ኢየሱስም አፅድቆታል የእግዚአብሔርን ቃል የጠበቁ ብሎም አወድሷቸዋል ።

የእግዚአብሔር ቃል የጠበቁ ብሎ ኢየሱስ ያወዳሳቸው ማንን ነዉ ? ኢየሱስን ጌታ ነዉ ብለው ያመኑትን ነዉ እንዴ ? አይደለም የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፥ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፥ አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ። " የእግዚአብሔር መልክተኛ ነዉ ያሉትን ።

ኢየሱስ ክርስቶስ የፈፀማቸው አስደናቂ የሆኑ ታዓምራቶች

ለዚህ መልስ የሚሆነው ኢየሱስ በአንደበቱ የተናገረው ነዉ(ዩሐንስ 5፡36) "እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክር የሚበልጥ ምስክር አለኝ፤ አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ፥ ይህ የማደርገው ሥራ፥ አብ እንደ ላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራልና። የላከኝ አብም እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል። ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም፥ መልኩንም አላያችሁም፤" ኢየሱስ ሲፈፅማቸውና ሲያደርጋቸው የነበሩ ታአምራቶችና ከስተቶችእነዲሁም አስገራሚ የነበሩ ነገሮች ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ሳይሆን የሚያሳዩት ኢየሱስ በአንደበቱ እንደተናገረው መልክተኛ መሆኑን ነዉ የሚያሳየው " አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ፥ ይህ የማደርገው ሥራ፥ አብ እንደ ላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራልና። " (ዩሐንስ 5፡36)

"እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና።" (ዩሐንስ 8፡42) ይላል ኢየሱስ ልብ ይበሉ ክርስቶስ አምላክ ሊሆን ቀርቶ በራሱ ስልጣን እንኳ አልመጣም ክርስቶስ የሚሠራቸው ሥራዎች በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር ለመላኩ ምስክሮች ናቸዉ ማለት ነው ።የፈጣሪ ነብይ ነዉ ።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ስለ ነብይነቱ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል እንመልከት ፦ ቅድሚያ ኢየሱስ ስለ እራሱ ነብይነት ከተናገረው እንጀምር (ሉቃስ 13፡33) "ዳሩ ግን ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ አይገባውምና ዛሬና ነገ ከነገ በስቲያም ልሄድ ያስፈልገኛል " እዚህ ክርስቶስ ነብይ ነኝ እና ወደ ኢየሩሳሌም ልሄድ ያስፈልገኛል እያለ ነዉ ።

አሁንም ክርስቶስ ወደ ሀገሩ ገብቶ በሚያስተምርበት ሰዓት ህዝቡም በተቃወመ ሰዓት ነብይነቱን እንዲህ ሲል ገለፀ (ማቴዎስ 13፡ 57) "ኢየሱስ ግን። ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው።" ክርስቶስ ይህንን ካለ ነብይ መሆኑ አወዛጋቢ አይደለም ።

በመቀጠል ስለ ኢየሱስ ታላቅ ምስክር ሊሆኑ የሚችሉ የክርስቶስ ተዐምር ያዩ እና የተመለከቱ ንግግሩን ያደመጡት ናቸዉ ። ታዲያ የክርስቶስ ተዐምር ያዩ እና የተመለከቱ ኢየሱስን ምን አሉት ፦ (ሉቃስ 7፡14- 16) " ቀርቦም ቃሬዛውን ነካ፥ የተሸከሙትም ቆሙ፤ አለውም። አንተ ጕበዝ፥ እልሃለሁ፥ ተነሣ። የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ ሊናገርም ጀመረ፥ ለእናቱም ሰጣት። ሁሉንም ፍርሃት ያዛቸውና። ታላቅ ነቢይ በእኛ መካከል ተነሥቶአል፥ ደግሞ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ጐበኘ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

ኢየሱስ በእግዚአብሔር ፈቃድ ና ሐይል የሞተን ሲያስነሳ የተመለከቱ ሠዎች ልክ እንደ ሙስሊሞች ኢየሱስን ነብይ ነዉ ብለዉታል ታዲያ ይህንን ተቃርኖ አምላክ ነዉ ማለት ኢየሱስንም ሆነ በጊዜው የነበሩ አማኞችን መቃረን አይሆንም ?

በኢየሱስ ዘመን የነበሩ ሠዎች ከንንግሩ (ከትምህርቱ) ምን ተረዱ ካልን መልሱን (ዩሐንስ 7፡40) "ስለዚህ ከሕዝቡ አያሌ ሰዎች ይህን ቃል ሲሰሙ። ይህ በእውነት ነቢዩ ነው አሉ፤" ምክኒያቱም ኢየሱስ የሚያስተምረዉ ትምህርት ከራሱ አይደለም "ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም፤›" (ዩሐ 7፡16) አሁንም ተመሳሳይ(ዩሐንስ 6፡14) "

ስለዚህ አከማቹ፥ ከበሉትም ከአምስቱ የገብስ እንጆራ የተረፈውን ቀሩስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ። ከዚህ የተነሣ ሰዎቹ ኢየሱስ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ። ይህ በእውነት ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ነው አሉ።" ልብ ይበሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ተዓምር ያዩ ሰዎች ነብይ ነዉ ብለውታል ተጨማሪ ኢየሱስ ነብይ ለመሆኑ ፦

ዮሐ.9:17 "በመካከላቸውም መለያየት ሆነ። ከዚህም የተነሣ ዕውሩን። አንተ ዓይኖችህን ስለ ከፈተ ስለ እርሱ ምን ትላለህ? ደግሞ አሉት። እርሱም። ነቢይ ነው አለ" ልብ ይበሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዉየዉ ተዐምር ሰርቶለት መመልከቻዉን አይኑን አብርቶለት ክርስቶስን አምላክ ነዉ አይደለም ያለዉ የአምላክ ነብይ እንጂ

ማቴዎስ ወንጌል ላይም እንደዚሁ (ማቴዎስ 21፡11)"ወደ ኢየሩሳሌምም በገባ ጊዜ መላው ከተማ። ይህ ማን ነው?ብሎ ተናወጠ። ሕዝቡም። ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው አሉ። ልብ ይበሉ ኢየሱስን ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ኢየሱስን ያላወቁት ይህ ማን ነው? በማለት ጠየቁ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያውቁት ምን ብለው መለሱ "ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው አሉ። " ክርስቶስን የሚያዉቀዉት ነብይ ብለዉታል ።ኢየሱስን የሚያዉቁት ንግግሩን ያደመጡት ተዐምራቱን ያዩት ነብይ ነዉ ብለዉ አምነውበታልም ነብይ ነዉ ብለው ተናግረዋልም ታዲያ ይህንን መቃረን ክርስቶስን መካድ አይሆንምን ?

ቁርአን ሲናገር፦

19:30 ሕፃኑም አለ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፤ መጽሐፍም ሰጥቶኛል ነቢይም አድረጎኛል።

61:6 የመርየም ልጅ ዒሳም የ እስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደናንተ የተላክሁ የአላህ መልክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልፅ ድግምት ነው አሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ አልተሰቀለም አልሞተም። ወይስ ተሰቅሏል ሞቷልም?

ኢየሱስ ላለመሰቀሉና ላለመሞቱ ሌላው ማስረጃ,በስቅለት ዙሪያ የተፃፉ ፅሁፎች መጋጨታቸው ነው።

1•ኢየሱስ የመጣው ተሰቅሎ እኛን ለማዳን ከሆነ,ላለመሰቀልና ላለመሞት ፀሎት ማድረግ ለምን አስፈለገ?

"እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት"(ወደ ዕብራውያን 5:7)

2• ለመሞት ከመጣ,ይህችን ጽዋ ከኔ ውሰድ እያለ መፀለይ ለምን አስፈለገው?

"ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም። አባት ሆይ፥ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።"(የሉቃስ ወንጌል 22:41_42)

3• ኢየሱስ መቼ ተሰቀለ?መቼ ሞተ?መቼ ተነሳ?3 ቀንና 3 ሌሊት ቆጥሮ እሚያስረዳን ክርስትያን ካለ?

"በዚያን ጊዜ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ መለሱና። መምህር ሆይ፥ ከአንተ ምልክት እንድናይ እንወዳለን አሉ።እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው። ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም።ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል። "(የማቴዎስ ወንጌል 12:38_40)

4•መስቀሉን የተሸከመው ኢየሱስ ወይስ ስምዖን ?

• ስምዖን "ሲወጡም ስምዖን የተባለው የቀሬናን ሰው አገኙ፤ እርሱንም መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት"(የማቴዎስ ወንጌል 27:32)

• ኢየሱስ "ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፤ መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ"(የዮሀንስ ወንጌል 19:17)

5• የተሰቀለው 3 ሰዓት ላይ ወይስ 6 ሰዓት ላከባቢ???

• 3 ሰዓት "በሰቀሉትም ጊዜ ሦስት ሰዓት ነበረ"(የማርቆስ ወንጌል 15:25)

• 6 ሰዓት "ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበረ፤ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ፤ አይሁድንም። እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው።እነርሱ ግን። አስወግደው፥ አስወግደው፥ ስቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም። ንጉሣችሁን ልስቀለውን? አላቸው። የካህናት አለቆችም። ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት።ስለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።"(የዮሀንስ ወንጌል 19:14_16)

6• የሰጡት የወይን ጠጅ ቀምሶታል ወይስ አልተቀበለም?

• ላልተቀበለም "ከርቤም የተቀላቀለበትን የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት፤ እርሱ ግን አልተቀበለም።"(የማርቆስ ወንጌል 15:23)

• ቀምሶታል "በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት፤ ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም።"(የማቴዎስ ወንጌል 27:34)

7• ፈልገው ካላገኙት,እሱ ወዳለበት መምጣት ካልቻሉ የት አግኝተው ሰቀሉት?

"ኢየሱስም። ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር እቆያለሁ ወደ ላከኝም እሄዳለሁ። ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝምም፤ እኔም ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አለ።"(የዮሀንስ ወንጌል 7:34)

ተላኪውን (እየሱስ) እና ዕውነታው በራሱ አንደበት ባይብል

1. ትምህርቱ ከራሱ እይደለም

‹ለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፦ ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም፤› ዩሐ 7፡16

ላኪና ተላኪ?

2. ማንነቱ እራሱ ሲገልጽ ((ነቢይ))

‹ዳሩ ግን ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ አይገባውምና ዛሬና ነገ ከነገ በስቲያም ልሄድ ያስፈልገኛል።›

(ሉቃስ 13፡33)

‹ኢየሱስ ግን፦ ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው። ›ማቴ 13፡57

3. አምላክ አላው (ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ)

‹ኢየሱስም፦ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ። እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት።›› ዩሐ 20፡17

‹‹እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት። የዮሐንስ ወንጌል 17፡3

4. ለዚህ አምላክ ይጸልይ ነበር

‹‹ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ።..› ማቴ 26፡39

5. የተላከው

‹‹እርሱም መልሶ፦ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ። ማቴ 15፡24

6. ሰው ነው

‹የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር

በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፤ ›(የሐዋሪያስራ 2፡ 22)

7. ከራሱ ምንም ማድረግ አይችልም

‹እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።› ዩሐንስ ወንጌል 5፡30

‹ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡- የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው።›ዩሐ 4፡34 ታዲያ ለምን ይሆን የተላከ መልክተኛ (ረሱል) ነው ማለታችን መወገዙ ?

8. የመጀመሪያ ያስተማረው ትዕዛዝ

‹ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፤ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥ ማር 12፡ 29 -->አዎ የሱ የኛም የጋራ አምላክ ‹‹አምላካችን›› ማለቱ ለዚያ ነው

9. ዕውቀቱ ከአምላክ ጋር ይነጻጸር ይሆን ?

‹ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም። › ማር 13፡ 32

10. ለማን መሰገድ አንዳለበት ሲያስተምር

‹ኢየሱስም መልሶ፡- ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል አለው። ›ሉቃስ 4፡8

11. እየሱስ እራሱን

* ዩሐ 7፡16፤ ዩሐ 16፡5፤ሉቃስ 10፡ 16፤ዩሐ 7፡29 .. .. ..ከ10 ያላነሱ ቦታዎች እንደ ሌሎች መልክተኛ (ረሱል) መሆኑን ይገልጻል፡፡

12. ወደፊትም ይችላል የሚል ካለ ወደፊት ያውቃል

‹..እኔ እሆን ዘንድ አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ። ›ዩሐ8፡28

13. ጌታ ነው የሚለው ሁሉ ((የሚለኝ ሁሉ))

‹‹ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።›› ማቴ 7፡21 ጀምሮ ተመልከቱ በጣም የሚገርማችሁ ይህን የተባሉት በስሙ ትንቢት የሚናገሩ፤አጋንንት የሚያወጡ …ወዘተ አሁን አንደምናየው እልል የሚባልላቸው እንጂ ተራ አማኞች አለመሆኑ ነው ልክ ነኝ ?

14. በተጨማሪም ከንቱነታቸው ሲገለጽ

*ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ።ማቴዎስ 15፡8-9

15. ቸር ሲባል፡-ቸር ማን መባል አንዳለበት ሲያስተምር

‹‹ኢየሱስም፡- ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።›› ማቴ 10፡18 ሉቃስ 18፡19

አልገደሉትም አልሠቀሉትምም!!!

☞ ክርስቲያኖች አሥተውላችሁ አንብቡት!!

ማሥተዋል ጥበብ ሲሆን አለማሥተዋል ጥበት ነው። በክርሥቲያኖች ዘንድ በሥፋት የሚታየው የጳውሎሥና የአየሡሥ ማንነታቸው ፣ እውነትነታቸው እና ተልዕኮዋቸውን አለማሥተዋላቸው ከእውነት እንዲርቁ አድርጓቸዋል፡፡ ይህንም ያልኩበት ምክንያት አብዛኛውን ክርስቲያን ከአየሡሥ ንግግር ይልቅ ቦታ ሚሠጠው ለባለ ራዕይ ፣ ለባለ ደራሢ እና ለጳውሎሥ ወሬዎችን ነው፡፡ በአየሡሥ ካመንክ የሚናገረውን ነገር ውሸት አድርገህ አትቁጠር ወይም ችላ ብለህ አትለፈው ። ምክንያቱም በመፅሐፍ ቅዱሥ ሌላ ሠው የሚናገረው ንግግር ከአየሡሥ ንግግር ጋር ሥለሚጋጭ፡፡

ወደ ርዕሱ ልመለሥ ፡-እንደ መፅሐፍ ቅዱስ አየሡሥ ሥለ ራሡም ሆነ ሌላ ብዙ መልዕክት ለሀዋርያቱ አሥተላለፈ ። በጊዜው ከእሡና ከፈጣሪ ውጭ ሥለ ራሡ የሚያውቅ የሠይጣን መልዕክተኛ ነው ።

#መዝ፡ዳ፡ም 118 ÷ 17 አየሡሥ " አልሞትም በህይወት እኖራለሁ እንጂ ፣ የእግዚአብሔርንም ሥራ እናገራለሁ "፣ ይላል እንግዲህ ሥለ ራሡ ሚያወራ ።የትም ቦታ ላይ አግኝተው እንደማይዙት ፣ እንደማይሠቅሉት እና እንደማይሞት እንዲሁም ወደሚሄድበት ሥለሚያውቅ በፍፁም አታገኙኝም ይላቸው ነበር ለሀዋርያቶቹ ።

#ዮህ፡ወ፡ም 16 ÷ 5 አሁን ግን ወደላከኝ እሄዳለሁ

#ዮህ፡ወ፡ም 7÷34 ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝም ፣ እኔም ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም ። ብሏል ።

[[[[ጥያቄ 1]]]] የት አግኝተው ያዙት?

ይህ እንዲህ ሆኖ እያለ ግን አንድ ሠው እንደሚሠቀል ያውቅ ሥለነበር

((ማቲ 20÷18-19) የሠው ልጅም ለካህናት አለቆች ይሠጣል ፣ ይገረፉታልም ይሠቅሉታልም...) ብሎ ነገራቸው ። እንዳለውም አንድ ሠው ይዘው ደብድበው ሠቀሉ ።

የዚህን የተሠቀለው ሠውዬ ማንነት እሥኪ እናጣራ፡-

ማቲ፡ወ 27÷32 [[ስምኦን]] የተባለ የቀሬና ሠው አገኙ ፣ መሥቀሉን አሸክመው((የራሰ ቅል))ስፍራ ወሠዱት

ማርቆ፡ወ 15÷21 [ስምኦን]]መሥቀሉን ተሸክሞ ((ጎልጎታ)) ስፍራ ወሠዱት

ዮህ፡ወ 19÷17 [[አየሡሥ]] መሥቀሉን ተሸክሞ ጎልጎልታ ወደ ተባለው የራሥ ቅል ሥፍራ ወሠዱት ። እሺ አሁን እዚህ ቦታ ላይ ምዕራፎቹ ይጋጫሉ።

[[[ጥያቄ 2]] ማንን ነው የሠቀሉት???

ለማሥተዋል

#ዮህ፡ወ 13÷30 ሥምኦን ቁራሹን ከበላ በኋላ በለሊት ወጥቶ ሄደ፡፡ ከዚህ በኋላ ዳግም ከእነ አየሡሥና ሀዋርያቶች ጋር ሣይገናኝ ነዉ ድርጊቱ ሚጀምረው!!! አየሡሥ በተደጋጋሚ ሄጂ ተመልሼ እመጣለሁ እመጣለሁ እኔ ሀያው ነኝ በድጋሚ እታያችኃለሁ ቢልም ክርስቲያነኖች ግን ንግግሩን ችላ አሉት፡፡

ዮሀ፡ወ 14÷19 እኔ ህያው ነኝ...

ከዚህም በተጨማሪ ክርስቲያኖች ለእየሱሥ ክብር የላቸውም ባይ ነኝ ምክንያቱም ፡-

ወደገላትያ ሠዎች 3÷13 በእንጨት የሚሠቀል የተረገመ ነዉ ተብሎ ተፅፏል...በመጨረሻም ከእየሱሥ ንግግር አንድ ላከልና ላገባድድ

#ዮሀ፡ወ 17÷12 ከጥፋት ልጅ በሥተቀር ማንም ከእነርሱ አልጠፋም ።

ለማጠቃለያ

ቁርዓን ሡረ - ኒሣዕ (ምዕ 4) ÷157 "እኛ የአላህን መልዕክተኛ የመርየም ልጅ አልመሢህ ኢሣን ገደልን በማለታቸው ረገምናቸው {{ አልገደሉትም አልሠቀሉትም}}።ግን ለእነርሡ የተገደለው ሠው በኢሣ ተመሠለ... ። ይላል ሀያሉና ጥበበኛው ጌታችን አሏህ በተከበረው ቁርዓን!!። ጥራት ይገባህ ጥበበኛው ጌታዬ!!!

ተአምራትን መስራት የአምላክነት መለኪያ ይሆናልን?

ብዙን ጊዜ በክርስቲያኖች በኩል የኢየሱስ ማንነት አጨቃጫቂ የሆነውና ከጥቂቶች በስተቀር ኢየሱስን በነብይነት የሚቀበል የለም እና ብዙውን ጊዜ ኢየሱስ አምላክ ለመሆኑ አንደ ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡት ተአምራትን በመስራቱ ነው፡፡

የሞተን ሰው ማስነሳቱ : አውርን ማዳኑ ለምጻምን መፈወሱ እንዲሁም ወ.ዘ.ተ. በ አምላክ ጎራነት አንዲመደብ አድርጎታል፡፡

በአርግጥ እኛ ሙስሊሞች እየሱስ ተአምራት መስራቱን አንክድም ነገር ግን ተአምራት በመስራቱ አንደ አምላክ ወይም ፈጣሪ አድርገን አንመለከተውም፡፡ እየሱስን የምናየው አላህ(ሱ.ወ) ከሰው የመረጠው መልዕክተኛ አንጂ ሌላ አለመሆኑን ነው፡፡

አላህም በ ቁርዐኑ እንዲህ ይላል ምዕራፍ 57፡25 (ሱረቱል ሀዲድ) ‹‹መልዕክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን›› አንዲሁም በምዕራፍ 40፡78 ‹‹… ለማንኛውም መልዕክተኛ በአላህ ፈቃድ ካልሆነ ታምርን ሊያመጣ አይገባውም የአላህም ትእዛዝ በመጣ ጊዜ በውነት የፈርዳል አዚያ ዘንድም አጥፊዎች ይከስራሉ›› ይለናል፡፡

ስለዚህ አየሱስም ሆነ ሌሎችም ነቢያት ተአምር የሰሩት በራሳቸው ስልጣን ሳይኖን በአላህ ፈቃድ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ምንም ማድረግ አይችሉም፡፡ ለመጥቀስ ያህል እየሱስ

በሱራ ኢምራን ምዕራፍ 3፡49 ‹‹፡-እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣኋችሁ። እኔ ለናንተ ከጭቃ አንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ፤ በርሱም እተነፍስበታለሁ፤ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይሆናል…›› እንዲሁም በመጽሀፍ ቅዱስ ዉስጥ ከራሱ ምንም ማድረግ አንደማይችል ይናገራል በዩሐንስ ወንጌል 5፡30 ‹እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም…›› ይለናል፡፡ ይህ ማለት የግድ አንድ

አድራጊ ሀይል እንዳለ ያስረዳናል፡፡ መልእክተኛውም እየሱስን ጨምሮ ተዕዛዝን ከዚህ ሐይል እየተቀበሉ ይፈጽሙታል ለማንኝውም በጥቂቱ አንዳንዱን ተአምራት አየሱስ ካደረገው ጋር አናገናዝብ

1ኛ ከእየሱስ ተአምራቶች አንዱ ኢይነ ስውርን መፈወሱ ነው፡፡

በቁረዓን 3:49 ‹‹በአላህም ፈቃድ ዕዉር ሆኖ የተወለደን፥ ለምጻኛንም፥ አድናለሁ…እንዲሁም በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ማርቆስ ወንጌል 7:31 እየሱስ ኢይነ ስውር መፈወሱን ይነግረናል፡፡ እና ዐይነ ስውርን ያዳነው እየሱስ ብቻ ነው ወየስ ሌሎችም ይህን ተአምር ሰርተዋል?

መጽሀፈ ነገስት ካልዕ 6:17 ‹‹ኤልሳዕም አቤቱ ያይ ዘንድ አይኖቹን አባክህ ግለጥ ብሎ ጸለየ እግዚአብሄርም የ ብላቴናውን አይኖች ገለጠ አየም››

እንዲሁም በመጽሀፈ ነገስት ካልዕ 6:18 መጽሀፈ ነገስት ካልዕ 6:20 ኤልሳዕ ተአምራትን እንደሰራ ያሳየናል እየሱስ እንዳደረገው ሁሉ ኤልሳዕም አድርጓል፡፡ አኛ ክርስቲያኖችን የምንጠይቃቸው ኤልሳዕ እየሱስ እንዳደረገው የአምላክነት ደረጃ ለምን አልተሰጠውም??

2 .እየሱስን አምላክ ሊያስኘው ከቻለው ሌላው ሙታንን ማስነሳቱ እንደሆነ ክርስቲያኖች ይተርካሉ፡፡

እውን እሱ ብቻ ነው ሙታንን የቀሰቀሰው በቁርዐን 3:49 ‹‹…በአላህም ፈቃድ ዕዉር ሆኖ የተወለደን፥ ለምጻኛንም፥ አድናለሁ፤ ሙታንንም አስነሳለሁ…››

በመጽሀፍ ቅዱስ ቀለል ባለ አማርኛ ትረጉም በ 1980 ዓ.ል እትም ዩሀንስ ወንጌል 11:41-44 ‹‹አባት ሆይ ስለሰማኽኝ አመሰግንካለሁ ሁልጊዜም እንደምትሰማኝ አውቃለሁ ነገር ግነ ይህን ያልሁት እዚህ የቆሙት ሰዎች አንተ እንደላከኝ እንዲያውቁ ብዬ ነው አለ እየሱስም ይህንን ከተናገረ በኋላ አላዛር ና ውጣ ብሎ በታላቅ ድምጽ ጮኸ››

እዚህ ላይ በቁርሃንም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ የምንረዳው ሞቶ የነበረውን ሰው መቀስቀሱን ነው ሌሎችስ ይህንን ታምር ሰርተዋል ወይስ አልሰሩም ?? በመጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ 17፤22 ‹‹…እግዚአብሔርም የ ኤሊያስንም ድምጽ ሰማ፡፡ የብላቴናውም ነፍስ ወደ አርሱ ተመለሰች አርሱም ዳነ››

እነዲሁም ኤሊያስ አንዳደረገው ሁሉ ኤልሳዕም ህጻኑ ሞቶ ቀስቅሶታል በመጽሀፈ ነገስት ካልዕ 4:33-34 ‹‹…ወደ እግአበሄር ጸለየ መጥቶም ህጻኑ ላይ ተኛ አፉንም በ አፉ አይኑንም በ አይኑ እጁንም በ አጁ ላይ አድርጎ ተጋደመበት የህጻኑምገላ ሞቀ…››

በተጨማሪም ኤልሳዕ ከሞተ በኑላ አጽሙ የሌላውን ሬሳ በሚነካበት ጊዜ ሬሳው ነፍስ እንደዘራ እንረዳለን

መጽሀፈ ነገስት ካልዕ 13፡20-21 ‹‹ኤልሳዕም ሞተ ቀበሩትም፡፡...ሰዎችም አንድ ሰው ሲቀበሩ አደጋ ጣዮችን አዩ ሬሳውን በኤልሳም መቃብር ጣሉት የኤልሳዕንም አጥንት በነካ ጊዜ ሰውየው ድኖ በእግሩ ቆመ››እንዲሁም በትንቢተ ሕዝቅኤል 37፡1-10 ብትመለከቱ

በአንድ ሸለቆ ውስጥ ያሉትን ብዙ አጥንቶች (አጽሞች) ጅማት ሰጥቷቸው ስጋም አውጥቶባቸው ቆዳንም ዘርግቶባቸው ትንፋሽንም ዘርቶባቸው በህይወት አኑሯቸዋል፡፡ ይህንንም ሲያደርግ እንደ ኢየሱስ በእግዛበሄር ፍቃድ ነው እና የህንን ስናየው ከእየሱስ በበለጠ ሁኔታ ብዙ አጥንቶችን ነው ህያው ያደረገው፡፡ ስለዚህ ለምን የአምላክ ደረጃ አልተሰጠውም?

ለምንስ ለኛ የተመቸንን አምላክ ያልተመቸንን እንዲሁ እንተዋለን? እኛ ሙስሊሞች እንደምንረዳው ለየትኛውም ነብይ የአምላክነት ስልጣን አንሰጥም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ተአምር ከመስራታቸው በፊት ወደ አንዱ ፈጣሪ ጸልየዋልና፡፡

3ኛ ከእየሱስ ተአምራት ሌላው ለምጻምን መፈወሱ፡፡

በቁርዐን 3፡49 እንዲሁም በማርቆስ ወንጌል 1፡40-42 ይህ ተአምር ማድረጉን እናገኛለን፡፡ሌሎችም ይህን አድርገዋል!!

መጽሀፈ ነገስት ካልዕ 5፡14 ‹‹... የእግዚአብሔር ሰው እንደተናገረው በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ ብቅጥልቅ አለ ስጋውም እንደገና አንደ ትንሽ ብላቴና ስጋ ሆኖ ተመለሰ፡፡ ንጹህም ሆነ››

መቼም አእምሮ ላለው ሰው ሁሉ ነገር ግልጽ ነው፡፡ እየሱስ እንደፈወሰው አዚህም ጋ ከለምጽ መፈወሱን እንረዳለን፡፡ አኛ ፍርዱን ለእናንተ ትተናል፡፡ የሚገርመው ሌሎች ነብያትም እንደየ ዘመናቸው ተአምር ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሙሴን ብንመለከት አላህ በትሩን ስእንዲጥል ባዘዘው ጊዜ የሆነውን ብንመለከት (ሱረቱ ጣሃ) 20፡ 19-20 ‹‹አላህም ሙሳ ሆይ! ጣላት አለው፡፡ ጣላትም ወዲያውም እርሷ የምትሮጥ እባብ ሆነች›› እነዲሁም በሱረቱል ጣሃ 20፡22-23 ይመልከቱ፡፡ለ ሰለሞን (ሱለየማን) ሱረቱ ነምል 27፡16 ሱሌይማንም ዳውድን ወረሰ አለም ሰዎችም ሆይ የበራሪ ንግግር (የወፍቋንቋ) ተስተማርን ከነገሩ ሁሉ ተሰጠን ይለናል፡፡

የእየሱስ የአፈጣጠር ሁኔታ አምላክ የሚያሰኘው ከሆነ አዳም በ አፈጣጠር ሁኔታ ይበልጠዋል ምክንያቱም አዳም የተፈጠረው ያለ እናት እና አባት ነው፡፡

እንዲየውም ከእየሱስ እና ከአዳም የሚበልጥ ሰው በመጽሀፍ ቅዱስ ዉስጥ ተጠቅሷል፡፡ ወደ አብራዊያን 7፡1-3 መልከ ጻዲቅ አባት እና አናት ወይም የትውልድ ሃረግ የለውም ለዘመኑም መጀመሪያ ለሂወቱም መጨረሻ የለውም ይህም መልከ ጼዲቅ የአግዛበሄር ልጅ ምሳሌ በመሆን ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል...››

በአጠቃላይ አላህ እያንዳንዱን ነብይ ሲልክ ከተአምራት ጋር ነው፡፡ ማንኛውም ነብይ ከራሱ የሚያደርገው ነገር በፍጹም የለም ስለዚህ ሁሉም ነብያት እያሱስን ጨምሮ በነብይነታቸው እንወዳቸዋለን እናከበራቸዋለን አንጂ አናመልካቸውም፡፡

ለምንስ ለኛ የተመቸንን አምላክ ያልተመቸንን እንዲሁ እንተዋለን?

እኛ ሙስሊሞች እንደምንረዳው ለየትኛውም ነብይ የአምላክነት ስልጣን አንሰጥም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ተአምር ከመስራታቸው በፊት ወደ አንዱ ፈጣሪ ጸልየዋልና፡፡

3ኛ. ከእየሱስ ተአምራት ሌላው ለምጻምን መፈወሱ፡፡

በቁረዐን 3፡49 እንዲሁም በማርቆስ ወንጌል 1፡40-42 ይህ ተአምር ማድረጉን እናገኛለን፡፡

መጽሀፈ ነገስት ካልዕ 5፡14 ‹‹…የእግዚአብሔር ሰው እንደተናገረው በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ ብቅጥልቅ አለ ስጋውም እንደገና አንደ ትንሽ ብላቴና ስጋ ሆኖ ተመለሰ፡፡ ንጹህም ሆነ››

መቼም አእምሮ ላለው ሰው ሁሉ ነገር ግልጽ ነው፡፡ እየሱስ እንደፈወሰው አዚህም ጋ ከለምጽ መፈወሱን እንረዳለን፡፡ አኛ ፍርዱን ለእናንተ ትተናል፡፡ የሚገርመው ሌሎች ነብያትም እንደየ ዘመናቸው ተአምር ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሙሴን ብንመለከት አላህ በትሩን ስእንዲጥል ባዘዘው ጊዜ የሆነውን ብንመለከት (ሱረቱ ጣሃ) 20፡ 19-20 ‹‹አላህም ሙሳ ሆይ! ጣላት አለው፡፡ ጣላትም ወዲያውም እርሷ የምትሮጥ እባብ ሆነች›› እነዲሁም በሱረቱል ጣሃ 20፡22-23 ይመልከቱ፡፡ ለ ሰለሞን (ሱለየማን) ሱረቱ ነምል 27፡16 ሱሌይማንም ዳውድን ወረሰ አለም ሰዎችም ሆይ የበራሪ ንግግር (የወፍቋንቋ) ተስተማርን ከነገሩ ሁሉ ተሰጠን ይለናል፡፡

የእየሱስ የአፈጣጠር ሁኔታ አምላክ የሚያሰኘው ከሆነ አዳም በ አፈጣጠር ሁኔታ ይበልጠዋል ምክንያቱም አዳም የተፈጠረው ያለ እናት እና አባት ነው፡፡ እንዲየውም ከእየሱስ እና ከአዳም የሚበልጥ ሰው በመጽሀፍ ቅዱስ ዉስጥ ተጠቅሷል፡፡ ወደ አብራዊያን 7፡ 1-3 መልከ ጻዲቅ አባት እና አናት ወይም የትውልድ ሃረግ የለውም ለዘመኑም መጀመሪያ ለሂወቱም መጨረሻ የለውም ይህም መልከ ጼዲቅ የአግዛበጌር ልጅ ምሳሌ በመሆን ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል…››

በአጠቃላይ አላህ እያንዳንዱን ነብይ ሲልክ ከተአምራት ጋር ነው፡፡ ማንኛውም ነብይ ከራሱ የሚያደርገው ነገር በፍጹም የለም ስለዚህ ሁሉም ነብያት እያሱስን ጨምሮ በነብይነታቸው እንወዳቸዋለን እናከበራቸዋለን አንጂ አናመልካቸውም፡፡ለምንስ ለኛ የተመቸንን አምላክ ያልተመቸንን እንዲሁ እንተዋለን?

እኛ ሙስሊሞች እንደምንረዳው ለየትኛውም ነብይ የአምላክነት ስልጣን አንሰጥም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ተአምር ከመስራታቸው በፊት ወደ አንዱ ፈጣሪ ጸልየዋልና፡፡ የከርስትና እምነት ተከታዮችን የምናመለክታቸው ነገር ቢኖር እየሱስ እንደማንኛውም ነብይ ተአምራቶችን ነው የደረገው እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ እየሱስም እንዲህ ይላል አል ኢምራን 3፡51‹‹…አላህ ጌታየና ጌታችሁ ነዉ፤ ስለዚህ ተገዙት (አላቸው)›› ለማጠቃልል ያህል እየሱስ ተአምራትን ሰርቷል እያልን አምላክ አድርገን እየሱስን ጌታ ነው እያልን ራሳችንን ከምናታልል እና ከምናሞኝ የእየሱስን ጌታ ጌታ አድረገን ብንቀበል ይበጀናል፡፡

ተሰሎነቄ 5፡21 ሁሉንም ፈትኑ መልካሙንም ያዙ

ቁርዐን ሱረቱ ኢምራን 3፡85 ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰዉ፣ ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለዉም፤ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎች ነዉ።

እውን ይህ ትንቢት ነብዩ ሙህመድን አይጠቁምም? እስቲ ይህችን አጭር ጽሁፍ በጥሞና አንብበው አራስዎ ፍርዱን ይስጡ…

ከ2ሺ አመታት በፊት ስለ መጥምቁ ዩሀንስ የሰሙ አይሁዶች ካህናትና ሌዋውያንን ወደ እየሩሳሌም በመላክ ማንነቱን ማጣራት ፈለጉ! ምክንያቱን በብሉይ ኪዳን የተጠቀሱትና ይመጣሉ ተብለው ከሚጠቀቁት አካላት አንዱ መሆኑን ማወቅ ፈልገዋልና ነው፡፡ ካህናቱም መጥምቁ ዩሀንስን ማነህ ሲሉ ጠየቁት፥ ዩሀንስም፡-

"እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ። እንኪያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? ብለው ጠየቁት። አይደለሁም አለ። #ነቢዩ ነህን? አይደለሁም ብሎ መለሰ።" (ዮሀ 1፥20~21)

እዚህጋ ሶስት ማንነቶች ተጠቅሰዋል

• ክርስቶስ(አይደለሁም)

• ኤልያስ(አይደለሁም)

• ነብዩ(አይደለሁም)

ነጣጥለን እንያቸው፡-

1) ስለእየሱስ መምጣት በብሉይ ኪዳን በብዙ ቦታ ተጠቅሶዋል፡፡ ለዛም ነው ካህናቱ ክርስቶስ ነህን? ሲሉ የጠየቁት፡፡ የዩሀንስ ምላሽም "አይደለሁም" የሚል ነበር፡፡

2) ስለኤሊያስ ዳግም መምጣትም አይሁዶች ይጠባበቁ ነበር፡፡ ክርስቲያኖችም ወደፊት ልክ እንደዩሀንስ ሁሉ ለመሲሁ መንገድ ጠራጊ ሆኖ ኤልያስ ዳግም እንደሚመጣ ያምናሉ፡፡ ባይብል ኤልያስ እንደሚመጣ እንዲህ ሲል ይናገራል፡-

"እነሆ፥ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ።" (ትንቢተ ሚልኪያ 4፥5)

3) በአይሁዶቹ አፍ "ነብዩ" የተባለው እኛ ሙስሊሞች ያለጥርጥር ነብዩ ሙሀመድን(ሰዐወ) ናቸው ብለን እንሞግታለን፡፡ ምክንያቱም፡-

• እንደክርስቲያኖች እምነት የመጨረሻው ነብይ መጥምቁ ዩሀንስ ነው ተብሎ ስለሚታመንና ዩሀንስ ግን አይሁዶቹ ሲጠይቁት እኔ እናንተ ምትጠብቁት ነብይ አይደለሁም ስላለ

• ከዩሀንስና ከክርስቶስ ቡሀላ የመጣው ነብይ ነብዩ ሙሀመድ(ሰዐወ) ስለሆኑ ያለጥርጥር ነብዩ የተባሉት ነብዩ ሙሀመድ(ሰዐወ) ናቸው እንላለን!

"እነዚያ መጽሐፍን የሰጠናቸው ወንዶች ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል፡፡ ከነሱም የተለዩ ክፍሎች እነርሱ የሚያወቁ ሲኾኑ እውነቱን በእርግጥ ይደብቃሉ፡፡" (አል በቀራህ 2:146)

"ለእነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለኾኑት በእርግጥ እጽፍለታለሁ።" (7:157) "ከዚህ ማኅበር መካከል ፈቀቅ በሉ"። (ኦሪት ዘሁልቁ 16:45)

የተወዳጁ ኢሳ (እየሱስ) (ዐሰ) የመጀመሪያ ተዐምር የትኛው ነው ?

ባይብል ላይ የተጠቀሱት ኢሳ(እየሱስ) የሰራቸው ተዓምራት ከመጀመሪያው ውጭ በአብዘሀኛው ቁርዓን ከማረጋገጥ በሻገር ባይብል ላይ የማይገኙ ተጨማሪ ተአምራቶችን እናገኛለን:: (ምሳሌ በማኢዳ 5፡110) ሌሎችም ቦታዎች ላይ

በአላህ ፍቃድ የሰራቸው ተዘርዝረዋል የዚ ፁሑፍ አላማ ልዩነት ያለበትን አንዱ የመጀመሪያውን ተዓምር ማሰያት ስለሆነ እነሆ ባይብል የመጀመሪያ የእየሱስ ተዓምር ውሃን ወደ ወይን ጠጅ መቀየር የዮሐንስ ወንጌል 2፡1-11

1. በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ፥ የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች፤

2.ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ።

3. የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት። የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው።

4. ኢየሱስም፦ አንቺ ሴት፥ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት።

5. እናቱም ለአገልጋዮቹ። የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው።

6. አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር፥ እያንዳንዳቸውም ሁለት

ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር።

7. ኢየሱስም፦ ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው።

8. አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው፤ ሰጡትም።

9. አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች

ግን ያውቁ ነበር፤ አሳዳሪው ሙሽራውን ጠርቶ።

10. ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው።

11.ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ።

***ይህ ‹‹ተአምር›› በእርግጥ በቀርዓን እውቅና ይለውም በመሰረቱ አስካሪ መጠጥ መጠጣት ፤ማጠጣት፤ መሸጥ፤መተባበር … አርም ስለሆነ፡፡

*** በዚህ አጋጣሚ ባይበል ላይ መጠጥ የሚፈቀድም የሚከለከሉ አንቀጹች ይገኛሉ፡፡

ቁርዓን የመጀመሪያ የኢሳ(እየሱስ) ተዓምር

እንደሚታወቀው እየሱስ የተጸነሰው የለአባት ነው ታዲያ ቅድስት መርየም (ማርያም) ልጁ ተሸክም ስትመጣ እነዚያ ጋጠ ወጥ አፈጠጡባት ልጁት ከየት አመጣሽው? እናትሽ አመንዝር አይደለችም::

… የቃላት ወርጅብኝ ከቀኝ ከግራ ተወረወረ በሀሰት ለመወንጀል አሰፈሰፉ ታዲያ ምንም ቢባሉ የማይሰሙ እነዚህ ሰዎችን ትታ ወደ ልጁን አመለከተቻቸው

‹‹ ወደርሱም ጠቀሰች፡፡ «በአንቀልባ ያለን ሕጻን እንዴት እናናግራለን!» አሉ፡፡ መርየም 19፡ 29-37

በዚ ወሳኝ ሰዓት ነው እጅግ አስደማሚ የሆነ ተዓምር የተከሰተው ለቁርዓን ቦታውን ልልቀቅ

‹‹ (ሕፃኑም) አለ «እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፡፡መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል፡፡» ቁ 30

«በየትም ስፍራ ብሆን ብሩክ አድርጎኛል፡፡በሕይወትም እስካለሁ ሶላትን በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል፡፡» ቁ 31

«ለእናቴም ታዛዥ (አድርጎኛል)፡፡ ትዕቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም፡፡ ቁ 32

«ሰላምም በእኔ ላይ ነው፡፡ በተወለድሁ ቀን፣ በምሞትበትም ቀን፣ ሕያው ኾኜ በምቀሰቀስበትም ቀን፡፡» ቁ 33

‹‹ ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው፡፡ ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው፡፡›› ቁ 34

‹‹ ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም፡፡(ከጉድለት ሁሉ) ጠራ፡፡ ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው «ኹን» ነው ወዲያውም

ይኾናል፡፡ ቁ 35

‹‹(ዒሳ አለ) «አላህም ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት፡፡ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው፡፡» ቁ 36

‹‹ከመካከላቸውም አሕዛቦቹ በእርሱ ነገር ተለያዩ፡፡ ለእነዚያም ለካዱት ሰዎች ከታላቁ ቀን መጋፈጥ ወዮላቸው፡፡ ቁ 37

**ይህ ደግሞ ባይብላይ የለም ቁርዓን ላይ አለ፡፡ የትኛው ይሻላል አልላችሁም ይታወቃልና፡፡

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፡፡ (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና፡፡ 5፡90

ሰላም ቅኑን በተከተለ ላይ ይሁን ::

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ለማን ህዝብ? ለምን አላማ ተላከ/መጣ?

ኢየሱስ(ዐ.ሰ) ለእስራኤል (ለአይሁድ) ሀገር ህዝቦች ብቻ የተላከ የአላህ ነብይ ነው ::ነጥብ፣ እኛ ደግሞ ኢትዮጵያውያን።ማቴዎስ ወንጌል 15፡ 21

እየሱስ(ዐ.ሰ) ለእስራኤል ህዘቦች ብቻ ከተላኩ ነበያት ውስጥ እንደሆን ከቁርአን ሆን ከባይብል ላይ ብዙ መረጃዎችን ማቀርብ ይቻላል፡፡ ልክ ሙሴ እስራኤሎችን ከግብጽ አስወጥቶ አላህ በሰጠው ህግና መመሪያ(ተውራት) መሰረት እንዳስተዳደራቸው ሁሉ ኢየሱስም(አሰ) ከነብያት መንገድ ለቀው በስሜትና በባእድ አምልኮ የተጨማለቀውን የእስራኤል ህዝቦች ወደ ሀቅ አንዲመራቸው(ኢንጂል) ተሰጥቶት እንደተላከ ኢስላም ያስተምራል:::

ቁርአን 5:75" #የመርየም_ልጅ_አልመሲሕ_ከበፊቱ_መልክተኞች_በእርግጥ_ያለፉ_የኾነ_መልክተኛ_እንጅ_ሌላ_አይደለም ::
ቁርአን 3፡49 ’’ ወደ እስራኤልም ልጆች መልእክተኛ ያደርገዋል፡፡…’

ባይብል ላይ ስንመለከት ተመሳሳይ ነገሮችን በግልጽ እናገኛለን፡፡

ወንጌል 15፡21 ጀምሮ እንመልከተው።

ማቴዎስ ወንጌል 15፡ 21 ኢየሱስም ከዚያ ወጥቶ ወደ ጢሮስና ወደ ሲዶና አገር ሄደ።

22 እነሆም፥ ከነናዊት ሴት ከዚያ አገር ወጥታ። ጌታ ሆይ፥ የዳዊት ልጅ፥ ማረኝ፤ ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞአታል ብላ ጮኸች።

23 እርሱ ግን አንዳች አልመለሰላትም። ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው። በኋላችን ትጮኻለችና አሰናብታት እያሉ ለመኑት።

24 እርሱም መልሶ።#ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር #አልተላክሁም አለ።

እዚህ ጋር በግልፅ እንደምናየው ኢየሱስ ሴትየዋ ከነአናዊ ስለሆነች ነው እኔ የተላኩት ለእስራኤል ለጠፉ በጎች ነው

ያለው።በሌላም ምዕራፍ እየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲያስተምሩ ሲልካቸው ከእስራኤል ህዝቦች ውጭ ወደ ሌላ እንዳይሄዱ እንዲህ በማለት አሰጠንቅቋቸው ነበር።።

ማቴ 10:1-8" ኢሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ፥ እንዲያወጡአቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው።...

5 እነዚህን ኢሥራ ሁለቱን ኢየሱስ ላካቸው፥ አዘዛቸውም፥ እንዲህም አለ። በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፥ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ፤

6 ይልቅስ የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ እንጂ። "በዚህኛውም በግልፅ እንደምንረዳው እየሱስ ሀዋርያቶቹን ወደ አህዛብ እንዳይሄዱ ወደ ሳምራዊያን ከተማም እንዳይገቡ ኣጥብቆ ሲያስጠነቅቅና ወደ እስራኤል የጠፉ በጎች ብቻ እንዲሄዱ ሲያዛቸው በግልፅ ያሳያል።

ስለዚህ በግልፅ እንደምንረዳው ኢየሱስ የተላከው ለጠፉ ለእስራኤል በጎች ብቻ ነው። ቁርአንም ይህን ያረጋግጣል።አንዳንድ የክርስትና እምነት ተከታይ ወገኖች እስራኤል ማለት ህዝብ ማለት ነው ብለው መከራከሪያ ነጥብ ያመጣሉ።።በየትኛው ዲክሽነሪ ወይም ኢንሳይክሎፒዲያ ነው ይህ የተባለው?

በተጨማሪም እስራኤል ማለት ህዝብ ማለት ነው ቢባል እንኳ መጀመርያ ያየነውን ጥቅስ በደንብ ለተመለከተ ሰው ከከነአን የመጣች ሴት ህዝብ አካል አይደለችም ማለት ነውን? አህዛቦችና ሳምራዊያንስ ህዝብ አይደሉም?

እንዴት ወደ እነዚህ ሰዎች ሄዳችሁ አታሰተምሩ ይላል? ምክኒያቱን ስናየው እሱ የተላከው ለእስራኤሎች ብቻ በመሆኑ ነው።።

ክርስቲያኖች አምላክ ነው የምትሉት እየሱስ አምላክ እንዴት አገር ለይቶ ይመጣል?

ለእስራኤል ብቻ የተለካ እንዴት የአለማት አዳኝ ተባለ?

እስራኤል የሚለው ትክክለኛ ትርጉሙ በመፅሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ሰፍሯል ቃሉን ብንሰነጥቀው እንደሚከተለው ነው።

እስራ -ኤል

☞እስራ ማለት ታገለ ፤ ኤል ማለት እግዚአብሔር ማለት ነው ለዛም ነው ያእቆብ እስራኤል የተባለው እግዚአብሔርን ታግሎ ስላሸነፈ።

የሚከተለውን ማረጋገጫ እንመልከት።

አለውም። ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል፤ ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና። ኦሪት ዘፍጥረት 32 : 28 ከያዕቁብ የወጡ 12 ነገዶች እስራኤላዊ ይባላሉ። ስለዚህ እስራኤል ትክክለኛ ትርጉሙ ይህ ነው። እየሱስም የተላከው ለእስራኤል ብቻ ነው። ኢየሱስ ተላኩኝ የሚለው ለእስራኤል ለጠፉ በጎች ሆኖ ሳለ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ እና ከእስራኤል ውጭ ያሉ የተቀሩ ሀገራት እንዴት ወንጌልን ይሰብካሉ ? ይሄ ትልቅ ስህተትና የእየሱስን ትእዛዝ መጣስ ነው።።

በሌላ በኩል ይሄን ለማረጋገጥ እየሱስ ለአለም እንደተላከ የተናገረበት አለ ወይ ተብለው ሲጠየቁ አንዳንድ ክርስቲያኖች የሚያቀርቡት መረጃ እየሱስ ካረገ ቦሀል ተገልጦላቸው ለሀዋሪያት ወንጌልን ለአለም ሰበኩ ብሏል የሚል ነው።።ይሄ አባባል ሆን ተብሎ የተፈጠረ ፈጠራ መሆኑን በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል።

1. እየሱስ በህይወት ምድር ላይ እያለ ለእስራኤሎች ብቻ እንደተላከ በተደጋጋሚ በራሱ አንደበት ሲናገርና ሲያረጋግጥ አንድም ግዜ ለአለም ህዝብ ስለመላኩ አልተናገረውም። ስለዚህ ተገልጦ አንዲህ አለ የተባለው ማረጋገጫ የሌለው ውሸት ነው ማለት ነው።

2. እየሱስ ካረገ ቦሀላ ከምድር ሰዎች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደማይኖረውና ወደ እውነት የሚመራቸው ሌላ አካል እንደሆነ እንዲህ በማለት ተናግሯል።

☞ "የምነግራችሁ ገና ብዙ ላለኝ ነገር ግን ላሁን ልትሸከሙት አትችሉም ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኃል የሚሰማውን ሁሉ ይነግራችኃል… ዩሐንስ ወንጌል 16:12_13። ስለዚህ እየሱስ ሳይሆን የታያቸው ሌላ ነገር ነው ማለት ነው። ምክኒያቱ እየሱስ በህይወት እያለ ከተናገረው የሚቃረን የሚናገራው ያ ስውር አጀንዳ ያለው አካል ነውና።

በመጨረሻም እየሱስ እንደተናገረው ብዙ ያላስተማረው ነገር እንዳለና ከሱ ቦሀላ የሚመጣው የእውነት መንፈስ(ነብያት የእውነት መንፍስ ተብለው ይጠራሉ 1ዩሀንስ 4: 1) ሁሉን እንደሚያስተምር እና ሰዎችን ወደ እውነት እንደሚመራቸው ተናገሮ ነበር የኢየሱስ ትንቢት (በነቢዩ ሙሀመድ(ሰአወ) ፍፃሜውን አግኝቷልና አልሀምዱሊላህ።ይህ ከእሱ ቦሀላ ሰውን ወደ ነብያት እምነት የመለሰና ሀቅን ያነገሰ ከነብዩ ሙሀመድ(ሰ.አ.ወ) ውጭ ማን አለ? ከኢስላም ውጭስ የተሟል የህይወት ዘይቤስ የት ይገኝል። 3፥19 አላህ ዘንድ የተወደደ ሃይማኖት "ኢስላም" ብቻ ነው።

"የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም። እናቱም በጣም እውነተኛ ናት። (ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ፤ አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሓዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት ከዚያም (ከእውነት) እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት" (አል -ማኢዳህ 75)።

ኢየሱስ (ዐሰ)& ማሪያም(ዐሰ) በእስራኤላውያን መፅሀፍ ቅዱስ(ታልሙድ) እና በቅዱስ ቁርአን

1) መርየም [አሰ] በቅዱስ ቁርአን የተሰጣት ክብር

☞‹‹መላእክትም ያሉትን (አስታውስ)፦-መርየም ሆይ አላህ በእርጥ መረጠሽ አነጻሽም በአለማት_ሴቶችም ላይ መረጠሽ መረየም ሆይ ለጌታሽ ታዘዥ ስገጅም ከአጎንባሾቹም ጋር አጎንብሽ…፣

-ጌታዬ ሆይ! ሰው ያልነካኝ ስኾን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል አለች ነገሩ እንደዚህሽ ነው አላህ የሚሻውን ይፈጥራል አንዳችን በሻ ጊዜ ለርሱ ኹን ይለዋል ወዲያውኑም ይኾናል አላት።።›› ሱራ 3፡42-47

ዒሳ አለይሂሰላም በአንቀልባ ሳሉ የተናገሩት: (ሕፃኑም) አለ «እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ። መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል።» (30) «በየትም ስፍራ ብሆን ብሩክ አድርጎኛል። በሕይወትም እስካለሁ ሶላትን በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል።» (31)

«ለእናቴም ታዛዥ (አድርጎኛል)። ትዕቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም። (32)

«ሰላምም በእኔ ላይ ነው። በተወለድሁ ቀን፣ በምሞትበትም ቀን፣ ሕያው ኾኜ በምቀሰቀስበትም ቀን።» (33)

ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው፡፡ ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው፡፡ (34) ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም፡፡ (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ፡፡ ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው «ኹን» ነው ወዲያውም ይኾናል፡፡ (35)

(ዒሳ አለ) «አላህም ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት፡፡ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው፡፡» (36) ከመካከላቸውም አሕዛቦቹ በእርሱ ነገር ተለያዩ፡፡ ለእነዚያም ለካዱት ሰዎች ከታላቁ ቀን መጋፈጥ ወዮላቸው፡፡ (37)

በሚመጡን ቀን ምን ሰሚ ምንስ ተመልካች አደረጋቸው! ግን አመጸኞች ዛሬ (በዚህ ዓለም) በግልጽ ስህተት ውስጥ ናቸው፡፤ (38)

2) ኢየሱስ (አሰ) በታልሙድ መፅሀፍ

እየሱስ ክርስቶስ(ዐሰ) በ እስራኤላውያን TALMUD ቅዱስ መጽሃፍ ውስጥ አንዲህ ተብሎ ተቀምጥዋል ፥፥

እየሱስ በዝሙት የተወለደ ዲቃላ ነው ::(Yebamoth 49b, p.324).

ማርያም ዝሙተኛ ሸርሙጣ ነበረች::

እየሱስ ከይሲ ርኩስ ሰው ነበር ::(Sanhedrin 106a &b, p.725).

እየሱስ መተታም አስማተኛ አጭበርባሪ ሌባ ,ሀሰተኛ ነቢይ ነበር :: ማርያም ዝሙተኛ ነበረች (Shabbath 104b, p.504).

THE TALMUD AND JESUS AND MARY.

"Jesus was a bastard born of adultery." (Yebamoth 49b,p.324).

"Mary was a whore: Jesus (Balaam) was an evil man." (Sanhedrin 106a &b, p.725).

"Jesus was a magician and a fool.Mary was an adulteress".(Shabbath 104b, p.504).

በቶራ (ኦሪት) ስለ መሲህ ኢየሱስ መወለድ ትንቢት አለ ቶራህ (ኦሪት) ኢየሱስንና እናቱ ማሪያምን እንደ "ታልሙድ" አያንቋሸሻቸውም አያስረከሳቸዉም ፣ ቶራህ ላይ አይሁዶች ኢየሱስን ዲቃላ ብለው ነው የሚጠሩት። እናቱን ማሪያምን ደግሞ ዝሙተኛ፣አመንዛሪ፣የተዋረደች፣ክብረቢስ ወዘተ እያሉ ነው በአይሁድ መፅሀፍ ቅዱስ ታልሙድ እና ቶራህ ላይ የሰፈረው። እንዴት በቶራ በኦርት ነው የምንመራው ትላላችሁ ?

ተመልከቱ☞"yashu' [derogatory for 'Jesus is in hell being boiled in hot excrement (Gittin 57 a)

☞"yashu' is an acronym for the Jewish curse may his (Jesus) name be wiped out forever more

"Yashu' (Jesus) was sexually immoral and worshipped a bricks (Sanhedrin 107 b)

☞"Miram the hairdresser had sex with many men" (shabbath 104 Hebrew edition)

ይህ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እጅግ አስነዋሪ ቃላቶችን የ አስራኤላውያን አምላክ በኢየሱስና በማሪያም ላይ ይናገራል ::

3) ኢየሱስ (ዐሰ) በቅዱስ ቁርአን

ነብዩ እየሱስ (ዐ.ሰ) ከኡሉል አዝም ነብያት አራተኛው መጽሐፍና ህግ (ሸሪዓ) የተሰጠው ነብይ ነው፡፡ የነብዩ እየሱስ (ዐ.ሰ) መወለድ ሁናቴ ያልተለመደና የተለየ ነበር፡፡ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም (መርየም) በእየሩሳሌም ውስጥ አላህን በመገዛት ላይ እያለች ሩህ አልቁድስ ወይም ጂብሪል (ገብርኤል) ከሰማይ ወርዶ ነብዩ እየሱስ (ዐ.ሰ) እንደምትወልድ ብስራት ነገራት፡፡ በጅብሪል ትንፋሽም መርየም ነብዩ እየሱስን (ዐ.ሰ) ፀነሰች፡፡

ቁርዓን እንዲህ ያብራራል፡

“በመፅሐፉ ውስጥ መርየምንም ከቤተሰቧ ወደ ምስራቃዊ ስፍራ በተለየች ጊዜ(ኾነውን ታሪኳን) አስታውስ፡፡ከነርሱም መጋረጃን አደረገች መንፈሳችንንም (ጂብሪልን) ወደርሷ ላክን፤በርሷም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰለላት፡፡-እኔ በአንተ በአልራህማን እጠበቃለሁ፤ ጌታህን ፈሪ እንደኾንህ (አትቅረበኝ) አለች፡፡እኔ ንፁህን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ የጌታሽ መልክተኛ ነኝ አላት፡፡(ቢጋብቻ) ሰው ያልነካኝ ኾኜ አመንዝራም ሳልኾን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል! አለች፡፡አላት፡- (ነገሩ) እንደዚህ ነው፤ ጌታሽ እርሱ በእኔ ላይ ገር ነው ፤ለሰዎችም ታምር ከኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህንን ሥራን) የተፈረደም ነገር ነው አለ፤(ነፋባትም)፡፡”(ቁርአን 19፡16-21)

ከተወለደ በኋላ እየሱስ (ዐ.ሰ) ገና አንቀልባ ውስጥ እያለ በእናቱ ላይ የሚነዙ አጉል የስም ማጥፋት ወሬዎችን በመቃወም መልስ ይሰጥ ነበር፡፡ በነብይነት ተልዕኮ ስለመላኩና ስለ ሰማያዊው መጽሐፍ (ኢንጂል/ወንጌል) ይነግራቸው ነበር፡፡ በኋላም በወጣትነቱ ዘመን ለህዝቡ ጥሪ ማድረግ ጀመረ፡፡ የሙሳንም ህግ መጠነኛ ለውጥ በማድረግ ተቀበለ፡፡ ከደቀ መዛሙርቱ (ሐዋሪያቱ) መሀል የሃይማኖት ልኡካንን ወደ አካባቢው ህብረተሰብ ላከ፡፡ ጥሪውና ትምህርቱ በህዝቡ ውስጥ ከተሰራጨ በኋላ አይሁዶች (የሚሳ ህዝቦች) ነብዩ እየሱስን (ዐ.ሰ) ለመግደል አሴሩ፡፡ ነገር ግን አላህ እየሱስን (ዐ.ሰ) ከአይሁዶች ሴራ አዳነ፡፡

አላህም በቁርአኑ እንዲህ ይላል….

«እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን(እየሱስን) ገደልን» በማለታቸውም (ረገምናቸው)፡፡ አልገደሉትም አልሰቀሉትምም፡፡ ግን ለእነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ፡፡ እነዚያም በእርሱ ነገር የተለያዩት ከእርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፡፡ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በእርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፡፡ በእርግጥም አልገደሉትም፡፡ ሱረቱ አን-ኒሳእ 157

እየሱስ(ዐሰ) የፍርድ ቀን ከመቃረቡ በፊት ወደ ምድር ይወርዳል ፍትህንም ያሰፍናል ፤መስቀሎችን ይሰባብራል፤ትዳር ይመሰርታል። ልጆችም የወልዳል።ለ አርባ ዓመታትም ይኖራል።ከዚያም ይሞታል ..ሃዲሱም እንዲህ ያላል:-

አቡ ሁራይራ (ረ.ዐ)እንደገለጹት የ አላህ መልዕክተኛ ሶ.ዐ.ወ እንዲህ ብለዋል ነፈሴ በእጁ በሆነቺው ጌታዬ እምላለሁ።ኢየሱስ የማርያም ልጅ በናንተ መካከል እንደ ፍትሃዊ ዳኛ ይመጣል።መስቀሎችንም ይሰባብራል ።አሳማዎችን ያጠፋል።ጂዝያንም ያስቀራል። ኃብትም ይትረፈረፋል- ተመጽዋች እስከ ሚታጣ ድረስ።አንድ ሱጁድ(በሰላት ውቅት ግንባርን መሬት ማስነካት) ከዚህች አለምና በውስጧ ካለው ነገር ሁሉ የበለጠ ግምትና ዋጋ ይሰጠዋል።አቡ ሁራይራ ይህንን ሐዲስ ተናግረው እንደጨረሱ የምትሹ ከሆነ ይህንን አንቀጽ አንብቡ ይሉ ነበር።

“ከመጽሃፍ ባለቤቶች ውስጥ በዒሳ ከመሞቱ በፊት የማያምን አንድም የለም።የትንሳኤ ቀንም ዒሳ በነርሱ ላይ መስካሪ ይሆናል 4:159

ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር(ረ.ዐ) ነብዩ ሙሐመድ ሰዕወ የሚከተለውን ሲናገሩ ሰምተዋል የመርያም ልጅ የሆነው ኢየሱስ ወደ መሬት ይመለሳል።ትዳር ይመሰርታል።ልጆችም የወልዳል።ለ አርባ ዓመታትም ይኖራል።ከዚያም ይሞታል፣ከኔ ጎንም ይቀበራል(በዕለተ ትንሳኤም) ከአቡበከርና ከዑመር ከሚገኘው መካነ መቅብራችን እኔና ኢየሱስ በ አንድነት እንቀሰቀሳለን(ኢብኑ አልጀውዚ ኪታቡ አል ወፍ)

አቡ ሁራይራ እንደዘገቡት የ አላህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ተናግረዋል፥ ”እኔ የእየሱስ በዚህ ዓለምም ሆነ በተከታዩ ዓለም እጅግ በጣም ቅርብ ወዳጁ ነኝ።ነብያት ወንድማማቾች ናቸው።አባታቸውም አንድ ሲሆን እናቶቻቸው ይለያያሉ። ሃይማኖታቸው ግን አንድ ነው። በእኔና በእየሱስ መካከል ሌላ ነብይ የለም።”(ቡኻሪ እና ሙስሊም ዘግበውታል)

ቅዱስ ቁርአን ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተከበረ የአላህ መልእክተኛ እንደሆነ በግልፅ ያስተምራል። ለናሙና ያክል ቅዱስ ቁርአናዊ ማስረጃዎችን ብንመለከት:

"ወደ እስራኤልም ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል።"(3:49)

"የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም።።"(5:75)

"የመርየም ልጅ ዒሳም፡- «የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን ወደእናንተ (የተላከሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ»"(61:6)

"እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ።። በአላህም ላይ እውነትን እንጅ አትናገሩ።። የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ የአላህ መልክተኛ ወደ መርየም የጣላት «የኹን» ቃሉም ከእርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው።።"(4:171)

ከነዚህ ቅዱስ ቁርአናዊ ጥቅሶች የምንወስደው ትምህርት ቢኖር

አንደኛ: ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተከበረ የአላህ መልእክተኛ መሆኑን።

ሁለተኛ:ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተላከበት ማህበረሰብ ወደ እስራኤል ልጆች እንደነበር እውነተኛው አምላካችን አላህ,ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተከበረ "ነቢይ" እንደሆነ በግልፅ ነግሮናል። ለዚህ ቁርአናዊ ማስረጃው:

"(ሕፃኑም) አለ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፤ መጽሐፍም ሰጥቶኛል ነቢይም አድረጎኛል።"(19:30)

"እርሱ በርሱ ላይ የለገስንለት ለእስራኤል ልጆች ታምር ያደረግነው የሆነ ባሪያ እንጂ ሌላ አይደለም።"(43:59)

«አላህ ጌታዬና ጌታችሁ ነው፤ ስለዚህ ተገዙት፤ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው» (አላቸው)።።"(3:51) (ዒሳ አለ) «አላህም ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት።። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው።።»"(19:36)

«አላህ ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት።። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው።።»"(43:64)

5. የሚስጢረ ሥላሴ ምስጢር

- ሥላሴ ማን ነው?
- ሥላሴ ማን ነው ወይሥ ማን ናቸው?
- መቼ መመለክሥ ጀመረ?
- ዕውንሥ እየሱሥ ሥለ ሥላሴ አሥቦሥ ያቃል?

1. የሥነ-መለኮት ምሁር የሆኑት ዶክተር ፓውል እንዝ “ታሪካዊ ሥነ-መለኮት አመጣጡና ትንተናው” በሚለው

መጽሐፋቸው ላይ “ዩኒቅያው (Nicea) ጉባኤ በ 325 ዓ.ም ታሪካዊውን አስተምህሮ-ሥላሴ አፀደቀ። በዚህም መሠረት ክርስቶስ ከአብ ጋር የባሕርይ እኩልነት ያለው መሆኑ ግንዛቤ አገኘ። ሲሉ ጽፈዋል። በኒቅያው ጉባኤ መሠረት “ክርስቶስ ከአብ ጋር የባሕሪይ እኩልነት ያለው መሆኑ” ግንዛቤ ሳያገኝ በፊት ቤተክርስቲያን የሥላሴን እምነት ሳይሆን የአንድን አምላክ ኃያልነትና ብቸኝነት ሥታስተምር ተሳስታ ነበርን? ከኒቂያ ጉባኤ በፊት የነበሩት አማኞችና ሐዋርያትና የኢየሱስን በባህሪ ከአብ ጋር መስተካከል ሳይረዱትና ግንዛቤውን ሳያገኙ ቆይተው በኒቅያ ጉባኤ ተገኝተው በድምጽ ብልጫ የወሰኑት 300 ጳጳሳት ግንዛቤውን አገኙን? እምነት የሚጸድቀው እንደ ፖለቲካ ፓርቲ በጉባኤ ነው ወይስ በ አምላክ ትእዛዝ?

2. ዶክተር ፓውል እንዝ ከላይ በጠቀስነው መጽሐፋቸው ላይ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፦ ” በአርዮስ ትምህርት የተነሳ የተፈጠረውን ውዝግብ ለመፍታት በ325 ዓ.ም ኒቅያ በተባለው ስፍራ አንድ ጉባኤ ተካሄደ ።በጉባኤው ላይ 300 ጳጳሳት ተገኝተው ነበር ። ጉባኤው አርዮስንም ሆነ አርዮሳዊነትን የሚቀበሉትን ሁሉ አውግዟል። በንጉሱ ካስፀዳቀ በኃላም የሚከተለውን የሃይማኖት መግለጫ አወጣ ።

“ሁሉን በሚችል ፣ የሚታየውንና ፣ የማይታየውን በፈጠረ ፣ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ።

የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በአንዱ በጌታ በእየሱስ ክርስቶስ ፣ ከአብ ብቻውን በተገኘው ከአብ ጋር መገኛው (” ኡሲያስ ” / ousias) አንድ በሆነው ፣ ከአምላክ በተገኘው አምላክ ፣ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን ፣ ከእውነትኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ ፣ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፣ ከአብ ጋር በማንነት (Homoousion) አንድ በሆነ ፣ ሁሉ በእርሱ በሆነ ፣ በሰማይም ይሁን በምድር ባለው ፣ ለእኛ ለሰው ልጆች ደህንነት ወርዶ ሥጋ በሆነ ፣ ሰውም በሆነ ፣ መከራን በተቀበለበት በሦስተኛውም ቀን በተነሳ፣ ወደ ሰማይ ባረገ ፣ በሙታንና በሕያዋን ላይ ሊፈርድ በሚመጣው እናምናለን ።” (ዶክተር ፓወል እንዝ፣ ታሪካዊ ሥነ- መስኮት አመጣጡና ትንተናው ፣ ገጽ 33– 34)

ስላሴ ከየት ወዴት?

ስላሴ የሚባለው አስተምህሮት በስብሰባ እና በውይይት የተፈጠረ እንጂ እየሱስ ያመጣው አይደለም እነዚህ ውይይቶችና ክርክሮች 4 ናቸው ።

በ325 የኒቂያ ጉባኤተኛ ኢየሱስ ክርስቶስ

አምላክ አይደለም በሚለው የአርዮስ መከራከሪያ አጀንዳ ላይ ተፋልሞ በፍፁም ክርስቶስ የስላሴ አንድ አካል ነው አምላክም ነው ብሎ በመደንገግ የሐይማኖት መግለጫ በማውጣት ተጠናቀቀ። ልብ በሉ ውሳኔው የፀደቀው በውይይት ነው : :

በ381 ዓ.ም የቆስጠንጢኖሱ ጉባኤ

እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነውየስላሴም አንዱ አካል ነው ተብሎ በአንድድምፅ በማፅደቅ የአሪዮስንና የብጤዎቹን ፍልስፍና ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ አክስሎ ተለያየ ልብ በሉ ይህም በውይይት ነው።

የ431 ዓ.ም የኤፌሶኑ ጉባኤ

እንዲሁ ሰው ሁሉ ሀጢያተኛ ነው በክርስቶስ የማዳን ሐይል ግን ከኃጥኣቱ ይፀድቃል ብሎ አወጀ። ልብ አድርጉ አሁንም ውሳኔ የተሰጠው በውይይትና በጉባኤ(በድምፅ ብልጫ) ነው።

በ451 ዓ.ም የተካሔደው የቃልኪዳን

ጉባኤም ክርስቶስ ፍፁም ሠው ፍፁም አምላክ በሚለው መሠረታዊ የወንጌል እውነት ላይ ተስማምተው ተለያዩ አሁንም ጉባኤው በውይይት ነው ስምምነት ላይ የደረሰው (ኪቃለ ሕይወት ቁጥር 15:1990 የተወሰደ።

ከዚህ የምንማረው የአየሱስ አምላክነትና የስላሴ አካል መሆን የተወሰነው በመፅሐፍ ቅዱስ አስተምህሮት ወይም (በኢየሱስ አስተምህሮት) ሳይሆን በውይይት ነው ይሔ ደግሞየአየሱስን አምላክነትና የስላሴ አካልነትን ተቀባይነት ያጣ ያደርገዋል።ስላሴ የሚለው አስተህምሮት እና የእየሱስ አምላክነት የታወጀው በአንድ ሀይማኖት ጥላ ስር የተሰበሰቡ የአለም አብያተ ክርስትያናትን በወከሉ ሰዎች ባደረጉት አራት የተለያዩ ጉባኤዎች ነው እንጂ በፍፁመረ በመፅሐፍ ቅዱስ አልታወጀም።ስለዚህ

ስላሴን ☞ ኢየሱስ አያውቀውም

ስላሴን☞ መፅሀፍ ቅዱስ አያውቀውም

ስላሴን ☞ ነቢያት አላስተማሩም

ስላሴን ☞ እውነተኞች የኢየሱስ ሀዋሪያት አላስተማሩም።ታድያ ከየት መጣ?

ነገር ግን ኢየሱስ ካረገ ከ 300 አመታት በሁዋላ በተደረገ ስብሰባና ውይይት(ጉባኤ) ወይም በድምፅ ብልጫ ስላሴን ከኢየሱስ አስተምህሮት አንዱ ነው ብለው በድምፅ ብልጫ አፀደቁት ማለት ነው ስላሴን።

ቅዱስ ቁርአን ስለ ስላሴ ምን ይላል?

እነዚያ አላህ የሶስት ሶስተኛ ነው ያሉ (በስላሴ ያመኑ) በእርግጥ ካዱ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጅ ሌላ የለም ከሚሉትም ነገር ባይከለከሉ ከነሱ እነዚያን የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል:: ወደ አላህ አይመለሱምና ምህረትን አይለምኑትምን አላህም መህሪ አዛኝ ነው (አል ማኢዳህ73-74)

የአላህ ሰላም፣እዝነት፣በረከትና ርህራሄ ቀጥተኛውን መንገድ በተከተለ ላይ ሁሉ ይስፈን።

” የሚስጢረ ሥላሴ ምስጢር”

1 የሥነ-መለኮት ምሁር የሆኑት ዶክተር ፓውል እንዝ “ታሪካዊ ሥነ-መለኮት አመጣጡና ትንተናው” በሚለው መጽሐፋቸው ላይ “ዩኒቅያው (Nicea) ጉባኤ በ 325 ዓ.ም ታሪካዊውን አስተምህሮ-ሥላሴ አፀደቀ። አንድ በሉ ውየሱስ ክርስቶስ ከሞተ ከ325 አመታት በኃላ ነበር ክርሥቲያኖች አምላካቸን 3 ናቸው ማለት የጀመሩት አ sorry 3 ናቸው አይባልም ለካ፤ እሺ እንደነሱ አባባል 3 ሆነ። አማርኛ ያላየው የብዙ ቁጥር መግለጫ ሆ አለ ያገሬ ሰው!በዚህም መሠረት ክርስቶስ ከአብ ጋር የባሕርይ እኩልነት ያለው መሆኑ ግንዛቤ አገኘ። ሲሉ ገልዋል።

"የስላሴ(የሶስትዮሽ) አስተምህሮት በቁርአንም ሆነ በመፅሀፍ ቅዱስ ተቀባይነት የለውም"

እውነተኛው አምላክ አንድ ነው,በአንድነቱ ውስጥ ሁለትነት ወይም ሦስትነት የለበትም።

ቁርአናዊ ማስረጃው

1•አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም:: (እርሱ) እጅግ በጣም ርኅሩህ አዛኝ ነው::" (2:163)

2•አምላካችሁ በእርግጥ አንድ ነዉ።" (37:4)

3•በል፦ እርሱ አላህ አንድ ነው"(112:1)

4•አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው"(16:22)

መፅሀፍ ቅዱሳዊ ማስረጃው

1•እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤"(አሪት ዘዳግም 6:4)

2•መካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ግን አንድ ነው"(ገላትያ 3:20)

3•አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው"(1ኛ ጢሞቴዎስ 2:5)

4•ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው"(የማርቆስ ወንጌል 12:29)

5•እንግዲህ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ስለ መብላት፥ ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደ ሆነ ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን።"(1ኛ ቆሮንጦስ 8:4)

6•ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን"(1ኛ ቆሮንጦስ 8:6)

7•አሁንም እኔ ብቻዬን እኔ እንደ ሆንሁ፥ ከእኔም በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፤ እኔ እገድላለሁ፥ አድንማለሁ፤ እኔ እመታለሁ፥ እፈውስማለሁ፤ከእጄም የሚያድን የለም።"(አሪት ዘዳግም 32:39)

ታዋቂው የቀድሞው የአርሰናል ፣የሪያል ማድሪድ፣ የቶተንሃም ወዘተ ...እግር ኳስ ተጫዋች የነበረው ኢማኑኤል አዲባየር ኢስላምን ለመቀበል ያስገደዱኝ 13 እውነታዎች ብሎ የዘራረዘራቸው ነጥቦች:-

1. ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው (የማርቆስ ወንጌል 12:29፤)

☞ኢስላምም ፈጣሪ አንድ እንደሆነ አበክሮ ያስተምራል

2. የአሳማ ስጋ ከልክል እንደሆነ 6:145 ቁርአን ይናገራል።መፅሀፍ ቅዱስም ይህንኑ ያስተምራል። እርያም ሰኮናው ተሰንጥቋል፥ ነገር ግን ስለማያመሰኳ በእናንተ ዘንድ ርኩስ ነው።"(አሪት ዘሌዋውያን 11:7፤)

3.ሻሎም አለይኩም ይላል እየሱስ (ዐ፣ሰ) ሰላምታ ሲሰጥ ነበር። (የዮሐንስ ወንጌል 20:21፤) ሙስሊሞችን እንደዚሁ ተመሳሳይ "አሰላሙ አለይኩም ወረህመቱላሂ ወበረካቱሁ" ብለው ሰላምታ ነው የሚጠቀሙበት

4. እየሱስም (ዐ፣ሰ) አንድ ነገር ከመስራቱ(; በፊት ቅድሚያ ኢንሻ አላህ ይላል☞ "እኔሰሪ ነኝ" አይልም።ቁርአንም ላይ 18:23_ ይህ ትእዛዝ አለ።

5. እየሱስ (ዐ፣ሰ) ከመፀለዩ በፊት ፊቱን እጁን እግሩን ይታጠብ ነበር። ሙስሊሞችን በዚሁ መልኩ ወደ ሶላት ከመቅረባቸው በፊት ትጥበት ይፈፅማሉ።

6. ሌሎች ነብያት ሆኑ እየሱስም (ዐ ሰ) ወደ አምላካቸው ሲፀልዩ በግንባራቸው መሬት ይደፉ ነበር።ሙስሊሞች በተመሳሳይ መልኩ በግንባራቸው ይደፋሉ (የማቴዎስ ወንጌል 26:39፤

7. እየሱስ (ዐ፣ሰ) እና ሙስሊሞች የሚያደርጉትን አለባበስ ይለብስና ሱናውን በተመሳሳይ ያከብር ነበር ።ሙስሊሞችም እንደዚያው።

8. እየሱስ (ዐ፣ሰ) የቀደሙትን ነብያት ህግና ትእዛዝ ያከብር ነበር።

እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።"(የማቴዎስ ወንጌል 5:17፤) ቁርአንም 3:84 ይህንን ይነገራልየሁሉም ነብያት ህግና ትእዛዝ አንድ አይነት እንደሆነ (2:285)

9.ማርያም (ዐ፣ሰ) ሙሉ ሰውነቷን በሂጃብ ትሸፍን ነበር። ሙስሊሞችም እንደዚያው እሄን ይፈፅማሉ በቁርአንም ይህኑ ያስተምራል (33:59)

10. መፅሀፍ ቅዱስ ላይ እየሱስ (ዐ፣ሰ) እና ነቢያቶች (፣ዐ፣ሰ) እንደፆሙ ይናገራል።

☞ ኦሪ ዘፀ 34: 28

☞ትንቢተ ዳንኤል 10:2_ 3 ።

ቁርአንም ላይ እንደዚያው አለ ቁርአንም (2:183) ሙስሊሞች እሄን ሲተገብሩ ክርስቲያኖች ግን አይተገብሩም። ለምን?

11 እየሱስ (ዐ፣ሰ) ወደ አንድ ቤት ሲገባ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ።" ብሎ እየሱስ (ዐ፣ሰ) ያስተምር ነበር። (የሉቃስ ወንጌል 10:5፤) ቁርአንንም ይህንን በተመሳሳይ መልኩ ያስተምራል። (24:61)

12 እየሱስ (ዐ፣ሰ) ተገርዟል ሉቃስ2:21 የአብርሀምን ህግ ተከትሎ ሙስሊሞችም እንደዚያው አብርሀምን ህግ ይከተላሉ ግርዛትን ይፈፅማሉ። ቁርአን 16:123

13 እየሱስ (ዐ፣ሰ) በአረማይክ ቋንቋ አምላኩን #ኢላሂ ይል ነበር። በተመሳሳይ መልኩ ሙስሊሞች አምላካቸውን ሲጠሩ #አላህ ይላሉ።ስለዚህ እየሱስን (ዐ፣ሰ) እና የቀደሙት ነብያቶች (ዐ፣ሰ) የምትወዱ ከሆነ ሞት ሳይቀድማቹ ዛሬውኑ ሙስሊም ሁኑ። የቀደምት ነቢያት በሙሉ ሙስሊም ነበሩና እኔም ሙስሊም ሆኛለሁ። አላህ ቀጥተኛውን መንገድ ይምራን።

አላሁመ አሚን።

6. ብዙ ሚስት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

መግቢያ

ስለ ጋብቻ የሚያጠናው የትምህርት ዘርፍ በምሁራን ዘንድ ማትሪሞኒ"matrimony" ይባላል፤ ይህም ስነ-ጋብቻ ጥናት የሚያጠኑ ምሁራን በዋነኝነት ለሁለት ይከፍሉታል፡-

1. ተመሳሳይ ፃታ ግንኙነት ሆሞ-ሴክሹአል"homosexual"

2. ተቃራኒ ፃታ ሄትሮ-ሴክሹአል"Heterosexual" ይባላሉ። መቼም ተመሳሳይ ፃታ ግንኙነት ለጊዜው አርስታችን ስላልሆነ ወደ ተቃራኒ ፃታ ጋብቻ እንሂድ፤ ተቃራኒ ፆታ ጋብቻ እራሱ በአራት ይከፈላል፤ እነርሱም፡-

1ኛ. አንድ ወንድ ለአንድ ሴት አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ሲሆን ሞኖጋሚ"Monogamy" ይባላል፤ "Monogamy" የግሪክ ቃል ነው፥ "mono" ማለት "ብቻ" ማለት ሲሆን "gamy" ደግሞ "ጋብቻ" ማለት ነው።

2ኛ. አንድ ወንድ ለብዙ ሴት አንዲት ሴት ለብዙ ወንድ ሲሆን ፓሊጋሚ"Polygamy" ይባላል፤ "polygamy" የግሪክ ቃል ነው፥ "poly" ማለት "ብዙ" ማለት ሲሆን "gamy" ደግሞ "ጋብቻ" ማለት ነው።

3ኛ. አንድ ወንድ ለብዙ ሴት ሲሆን ፓሊአንድሪ"Polyandry" ይባላል፤ "Polyandry" የግሪክ ቃል ነው፥ "poly" ማለት "ብዙ" ማለት ሲሆን "andry" ደግሞ "ወንድ" ማለት ነው።

4ኛ. አንዲት ሴት ለብዙ ወንድ ሲሆን ፓሊጂኒ"Polygyny" ይባላል፤ "Polygyny" የግሪክ ቃል ነው፥ "poly" ማለት "ብዙ" ማለት ሲሆን "gyny" ደግሞ "ሴት" ማለት ነው፤ ይህኛው ጋብቻ በማህበራዊ ጥናት"sociology" ላይ የተቀመጠ መረጃ እንጂ ስነ-መለኮታዊ ጥናት"theology" ላይ አልተቀመጠም።

ይህን በግርድፉ እና በሌላ ካየን ዘንዳ ደርዝና ፈርጅ ባለው መልኩ ስለ አንድ ወንድ ለብዙ ሴት"Polyandry" ከቁርአን እና ከባይብል እናያለን፡-

"ብዙ ሚስት በቁርአን"

"አሕካም" أحكام "የሑክም" حُكْم ብዙ ቁጥር ሲሆን "ፍርድ" ወይም "ህግ" ማለት ነው፤ በኢስላም "ህጎች" በአምስት ይከፈላሉ፤ እነርሱም፡- 1ኛ. "ፈርድ" فرض ማለትም "የታዘዘ"

2ኛ. "ሙስተሐብ" مستحب" ማለትም "የተወደደ"

3ኛ. "ሙባሕ" مباح ማለትም "የተፈቀደ"

4ኛ. "መክሩህ" مكروه" ማለትም "የተጠላ"

5ኛ. "ሐራም" حرام" ማለትም "የተከለከለ ናቸው።

ይህ “ፊቅህ” فقه የተባለውን የስነ-ህግ ጥናት ዋቢና ታሳቢ ያደረገ ነው፤ “ፊቅህ” ስነ-ህግ ጥናት”the study of law” ሲሆን ህግ አዋቂ ደግሞ “ፈቂህ” فقيه ይባላል፤ ይህንን ነጥብ ያነሳሁት ስለ አሕካም ለመዳሰስ ሳይሆን አንድ ወንድ ለብዙ ሴት”Polyandry” የተባለው የጋብቻ አይነት በኢስላም በኒያ ሙስተሐብ ሲሆን በፍትህ ሙባሕ ነው፤ ነገር ግን ፈርድ አይደለም፡-

4:3 በየቲሞችም ማግባት አለማስተካከላችሁን ብትፈሩ፣ ዝሙትንና ከተወሰነላችሁ በላይ ማግባትንም ፍሩ፤ ከሴቶች ለእናንተ የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት፣ ሦስት ሦስትም፣ አራት አራትም አግቡ። አለማስተካከልንም ብትፈሩ፣ “”አንዲትን ብቻ””፣ ወይም እጆቻችሁ ንብረት ያደረጉትን ያዙ፤ ይህ ወደ አለመበደል በጣም የቀረበ ነው።

በኢስላም በፍትህ ማስተካከል ከተቻለ እስከ አራት ማግባት ይቻላል፤ ነገር ግን ያ ካልሆነ አንዲት ብቻ ነው ማግባት ያለበት፤ እዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጥያቄ አላህ የጋብቻን ገደብ እስከ አራት ካለ ለምንድን ነው ነብያችን እስከ ዘጠኝ ያገቡት? የሚል ነው፤ አንደኛ ምላሽ የሚሆነው አምላካችን አላህ ስለፈቀደ ነው፤ ሁለተኛ እንደሚታወቀው ቁርአን በአንድ ጊዜና ቦታ የወረደ ግህደተ-መለኮት ሳይሆን በሒደት የወረደ ግህደተ-መለኮት ነው፤ መካ ላይ ለአስር ዓመታትን ሲወርድ መዲና ላይ ደግሞ ለአስራ ሶስት ዓመታትን ወርዷል፤ የዓለማቱ ጌታ አላህ ጋብቻን የመጨረሻ ገደብ አራት ብቻ መሆኑን የሚያበስረው አንቀፅ ሲያወርድ ነብያችን ቀደም ብለው ዘጠኝ ሚስቶች ነበሯቸው፤ ይህ የቁርአን ታሪካዊ ዳራ ከአለመረዳት የሚመጣ ጥያቄ ነው።

“ብዙ ሚስት በባይብል”

ከአንድ በላይ ማግባት በባይባል የተከለከለበት አንድ ጥቅስ የለም፤ ከዚያ ይልቅ ከአንድ በላይ ያገቡ ነቢያት በቁና ሰፍሯል፡-

ዘፍጥረት 31፥17 ያዕቆብም ተነሣ፥ ልጆቹንና “ሚስቶቹንም” በግመሎች ላይ አስቀመጠ፤

መሣፍንት 8፥30 ለጌዴዎንም “ብዙ ሚስቶች” ነበሩትና ከወገቡ የወጡ ሰባ ልጆች ነበሩት።

1ኛ ሳሙኤል 1፥2 ሕልቃ…””ሁለትም ሚስቶች” ነበሩት፤ የአንዲቱ ስም ሐና የሁለተኛይቱም ስም ፍናና ነበረ፤

1ኛ ሳሙኤል 25፥43 ዳዊትም ደግሞ ኢይዝራኤላዊቱን አኪናሆምን ወሰደ፤ “”ሁለቱም ሚስቶች” ሆኑለት።

1ኛ ነገሥት 11፥3 ለእርሱም ወይዛዝር የሆኑ “”ሰባት መቶ ሚስቶች”” ሦስት መቶም ቁባቶች ነበሩት፤

1ኛ ዜና መዋዕል 4፥5 ለቴቁሔም አባት ለአሹሑር ሔላና ነዕራ “”የተባሉ ሁለት ሚስቶች”” ነበሩት።

1ኛ ዜና መዋዕል 14፥3 ዳዊትም በኢየሩሳሌም “”ሚስቶችን”” ጨምሮ ሌሎችን ወንዶችንና ሴቶችን ልጆች ወለደ።

አይ እነርሱ አደረጉት እንጂ ፈጣሪ አልፈቀደላቸውም ከተባለ ፈጣሪ አንድ ሰው ሁለት ሚስቶች ካሉት እንዴት መንከባከብ እንዳለበት የተናገረው ሳይፈቅድ ነውን? እስቲ እንይ፡-

ዘዳግም 21፥15-17 ለአንድ ሰው አንዲቱ የተወደደች አንዲቱም የተጠላች “”ሁለት ሚስቶች”” ቢኖሩት፥ ለእርሱም የተወደደችው ደግሞም የተጠላችው ልጆችን ቢወልዱ፥ በኵሩም ከተጠላችው ሚስት የተወለደው ልጅ ቢሆን፥ ለልጆቹ ከብቱን በሚያወርስበት ቀን ከተጠላችው ሚስት በተወለደው በበኵሩ ፊት ከተወደደችው ሚስት የተወለደውን ልጅ በኵር ያደርገው ዘንድ አይገባውም፤ ነገር ግን ከከብቱ ሁለት እጥፍ ለእርሱ በመስጠት ከተጠላችው ሚስት የተወለደው ልጅ በኵር እንደ ሆነ ያስታውቅ። የኃይሉ መጀመሪያ ነውና በኵርነቱ የእርሱ ነው።

እግዚአብሔር ከአንድ በላይ ማግባት ቢከለክል ኖሮ ለዳዊት ለዛውን የሰውን ሚስቶችን ይሰጠው ነበርን? የጌታው የሳኦን ሚስቶች ሰቶት ነበር፤ ከዚያ የበለጠም ካስፈለገ እንደሚጨምርለት ቃል ገብቶለታል፦ 2ኛ ሳሙኤል 12 : 8 የጌታህንም ቤት ሰጠሁህ፥ "''የጌታህንም ሚስቶች'' በብብትህ "''ጣልሁልህ''"፤ የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ፤ "''ይህም አንሶ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ እጨምርልህ ነበር''"።"

ሌላው የአዲስ ኪዳን ነብይ ኢየሱስ ነው፤ ኢየሱስ ከአንድ በላይ ማግባት ክልክል ነው አላለም፤ በብሉይ የነበረውን ህግ አልሻረም። ሌላው እራሳቸውን የሚያስጠብት ጳውሎስ ነው፤ ሲጀመር ጳውሎስ ነብይ አይደለም፤ ሲቀጥል የሚናገረው በሞኝነት እንጂ ጌታ አዞት አይደለም፤ ንግግሩ የራሱ እንጂ የጌታ አይደለም፦

1ኛ ቆሮ 7፥12 ሌሎችንም "''"እኔ እላለሁ፥ ጌታም አይደለም"''፤ ከወንድሞች ወገን ያላመነች ሚስት ያለችው ቢኖር እርስዋም ከእርሱ ጋር ልትቀመጥ ብትስማማ፥ አይተዋት፤"

2ኛ ቆሮ 11፥17እንደዚህ ታምኜ ስመካ "''የምናገረው፥ በሞኝነት እንጂ ጌታ እንዳዘዘኝ አልናገርም"''።"

ሲሰልስ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ባል ይኑራት አለ እንጂ ለእያንዳንዱ ለራሱ አንድ ሚስት ትኑረው አንድ ባል ይኑራት አላለም፦

1ኛ ቆሮ 7፥2 ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት።"

ከአንድ በላይ ማግባት ክልክል ነው ያሉት ምዕራባውያን እንጂ ባይብል አይደለም፤ ምዕራባውያን ከአንድ በላይ ማግባት ቢከለክሉም ከአንድ በላይ ዝሙት ማድረግ የአንድ ሰው መብቱና ነፃነቱ ነው የሚል መርህ አላቸው፤ ምዕራባውያን በ 17ኛው ክፍለ-ዘመን ሰው እንዲዋለድና እንዲባዛ ስላልፈለጉ እንጂ የመጡበትን ዳራ መሰረት አድርገው አይደለም፤ ለዛ ነው ግብረ-ሰዶም እንዲስፋፋ የተፈለገው፤ ይህንን እንደ ሥልጣኔ ቤተ-ክርስቲያን ግብረ-ሰዶም ታጋባለች፤ ይህ ደግሞ መሠልጠን ሳይሆን መሰይጠን ነው፤ ሥልጣኔ በምጣኔ ካልሆነ ጥፋት ነው፤ ምዕራባውያን ከአንድ በላይ ዝሙት ሲፈቅዱ ኢስላም ደግሞ ከአንድ በላይ በሃላል ኒካ ማድረግ ይፈቅዳል፦

24:32 ከእናንተም ትዳር የሌላቸውን አጋቡ፤ "ከወንዶች ባሮቻችሁ" عِبَادِكُمْ እና "ከሴቶች ባሮቻቹሁም" وَإِمَائِكُمْ ለጋብቻ ብቁ የሆኑትን "አጋቡ" وَأَنْكِحُوا፤ ድሆች ቢሆኑ፤ አላህም ከችሮታው ያከብራቸዋልና፤ አላህም ስጦታ ሰፊ ዓዋቂ ነው።

2:221አጋሪ የሆኑ ሴቶች እስከሚያምኑ ድረስ "አታግቡዋቸው" وَلَا تَنْكِحُوا :: ከአጋሪይቱ ምንም ብትደንቃችሁም እንኳ "ያመነችው ባሪያ" مُؤْمِنَةٌ وَلَأَمَةٌ በእርግጥ በላጭ ናት:: ለአጋሪዎቹም እስከሚያምኑ ድረስ "አትዳሩላቸው" وَلَا تُنْكِحُوا :: ከአጋሪው ምንም ቢደንቃችሁ "ምእምኑ ባሪያ" مُؤْمِنٌ وَلَعَبْدٌ በላጭ ነው::

4:25 ከእናንተም ውስጥ "ጥብቆች" ምእምናት" الْمُؤْمِنَاتِ الْمُحْصَنَاتِ የሆኑትን "ለማግባት" يَنْكِحَ ሀብትን ያልቻለ ሰው፣ "እጆቻችሁ ካደረጓቸው" مَلَكَتْ أَيْمَانُكُمْ ከምእመናት "ባሪያን" فَتَيَاتِكُمُ الْمُؤْمِنَاتِ "ያግባ"፤

እውን ብዙ ሚስት ማግባት በክርስትና ክልክል ነውን?

☞ይህም አንሶ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ እጨምርልህ ነበር።" መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 12 : 8) እግዛብሄር ለነቢዩ ዳዊት የሰጠህ ሚስቶች ካነሱህ እጨምርልሃለው ጠይቀኝ እያለው ነው።

☞"የጌታህንም ቤት ሰጠሁህ፥ የጌታህንም ሚስቶች በብብትህ ጣልሁልህ፤ የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ፤ #ይህም_አንሶ_ቢሆን_ኖሮ_ከዚህ_የበለጠ_እጨምርልህ_ነበር።" መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 12 : 8)

God said to David, "And #I #gave #you your master's house, and #your # master's #wives into your bosom, and gave you the house of Israel and of Judah; and if [that had been] too little, I would moreover have given to you such and such things." (2 Samuel 12 : 8)

ታድያ ክርስቲያን ወገኖች ለምን ይሆን ነብይ ዳዊት ከ አንድ በላይ ሚስት ያገባው በእግዛብሄር ፍቃድ ሳይሆን በራሱ ፍቃድ ነው ብለው የሚሚግቱን? እግዛብሄር እኮ ለዳዊት ያለው እኮ☞ከሰጠሁህ ሚስቶች ይህም አንሶ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ እጨምርልህ ነበር።" መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 12 : 8)

ስለዚህ ከ አንድ በላይ ሚስት ማግባት እንደሚፈቀድ ከነቢዩ ዳዊት እንማራለን ማለት ነው።እውን ብዙ ሚስት ማግባት ክልክል ነውን?

በእስልምና ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ለምን ተፈቀደ?

ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት (Polygamy) ከአንድ በላይ የትዳር ጓደኛ መያዝ የሚቻልበት የጋብቻ ስርዓት ነው፡፡ይህ አይነቱ ጋብቻ በሁለት አበይት ከፍሎች ይከፈላል፡፡

ሀ. አንድ ወንድ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት የሚቻልበት ስርአት

ለ. አንዲት ሴት ከአንድ ባል በተጨማሪ ማግባት የምትችበት ሥርዓት ናቸው፡፡

እስልምና ለአንድ ወንድ ከአንዲት ሴት በላይ ማግባትን በወሰን የፈቀደ ሲሆን ፣አንዲት ሴት ከአንድ በላይ ከሆኑ ወንዶች ጋር የምታደርገው ጋብቻም ሆነ ማንኛውም መሰል ግንኙነት በጥብቅ ያወግዛል፡፡ወደ ዋናው ጥያቄ እንምጣና እስልምና ለምድነው ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ለወንዶች የፈቀደው የሚለውን እንይ፡፡

1.«አንድ ብቻ አግቡ»የሚል ቃል በብቸኛነት ሰፍሮ የሚገኘው በቁርአን ብቻ ነው፡፡

ሀ. በምድራችን ላይ ያለ የትኛውም ሀይማኖት ጋብቻን ጋብቻን በተመለከተ የስቀመጠው ወሰን የለም፡፡የትኛውም የሐይማኖት መጽሐፍ በጥቅሉ የጋብቻን ቅዱስነትና የመሳሰሉትን ከመጥቀስ ባለፈ አንድ ወንድ አንድ ሴት ብቻ ያግባ ወይም ብዙ ያግባ በሚል የጋብቻ ወሰን አላስቀመጠም፡፡መጽሐፍ ቅዱስ ፣በቬዳስ ፣በራማያን፣በማህባራት ፣በጊታም (የሕንድ ቅዱሳን መጽሐፍት ናቸው) ሆነ በታልሙድ (የአይሁዶች መጽሐፍ) የዚህ አይነቱን ወሰን አናገኝም፡፡በሌላ አባባል የነዚህ ሀይማኖት ተከታይ የሆነ ሰው የፈለገውን

ያህል ሚስት ቢያገባ ማንም ከልካይ አልነበረበትም፡፡ ከጊዜ ብዛት ግን ከባህልና ለአንዳንድ ውጫዊ ተጽዕኖዎች የተነሳ የሒጁዱና የክርስቲያን ቀሳውስት ከአንድ ሚስት በላይ ማጋባትን ከለከሉ፡፡

ለ. ጥንታዊያን ክርስቲያኖች የፈለጉትን ያህል ሚስት ያገቡ ነበር ፡፡ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ሌሎች ቅዱሳን መጽሐፍት በዚህ ጉዳይ ላይ ያስቀመጡት ክልከላ ስላልነበረ ነው፡፡ከጥቂት መቶ ዓመታት በፊት ግን ቤተ-ክርስቲያን ለክርስቲያን ወንዶች ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን ክልክል ያደረገውን ሕግ አወጣች፡፡

ሐ. ወደ አይሁዶች ስንመጣ ከ950-1030 የኖረው ራቢ ጌርሾም ቤን የሁዳ ወንድ ከአንድ ሴት በላየ እንዳያገባ የሚከለክለውን ሕግ እስካወጣበት ጊዜ ድረስ ይህ ጋብቻ ቀጥሎ ነበር፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ አብርሀም ሁለት ሚስቶች ሰለሞን ደግሞ 700 ሚስቶች ነበሩት ይላል፡፡በስፔንና ፓርቹጋል እንዲሁም በሙስሊም አገሮች የሚኖሩ የአይሁድ ማህበረሰቦች በ1990 ዋናው የእስራኤል ራቢኔት እስከከለከለበት ጊዜ ድረስ ከአንድ በላይ ሚስቶችን ያገቡ ነበር፡፡

2. ቁርአን ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ከወሰን ጋር ይፈቅዳል፡፡

ቀደም ሲል እንደጠቀስነው አንድ ብቻ አግቡ የሚል ሐረግ የያዘ የሀይማኖት መጽሐፍ ቁርአን ብቻ ነው፡፡«ከሴቶች ለናንተ የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት ፣ ሦስት ሦስትም ፣አራት አራትም አግቡ፡፡አለማስተካከልንም ብትፈሩ አንዲት ብቻ አግቡ፡፡» {ሱረቱ አል ኒሳእ፡3)

ከቁርአን መውረድ በፊት በሚስት ቁጥር ላይ በየትኛውም ሀይማኖት ሕግ ምንም አይነት ገደብ አልነበረም ፡፡ ብዙ ሰዎች በርካታ ሚስቶችን ያገቡ ነበር ፡፡እንደውም አንዳንድ ወንዶች በመቶዎች የሚቆጠሩ ሚስቶችን ያገቡ ነበር፡፡እስልምና ግን የሚስቶችን ቁጥር እስከ አራት ብቻ ብሎ ወሰን አበጀለት፡፡አንድ ሙስሊም ወንድ በተገቢው ሁኔታ ሳያዳላ ሊያስተዳድራቸው የሚችል ከሆነ ሁለትም ሦስትም ሆነ አራት ሴቶችን ማግባት ይችላል፡፡በዚያው አል-ኒሳእ ምዕራፍ ቁጥር 129 ላይ እንዲህ ይላል፡፡

«በሴቶች መካከል ምንም እንኳን ብትጓጉ(በፍቅር) ለማስተካከል አትችሉም፡፡»{ሱረቱ አል ኒሳእ፡ 129)

ስለዚህ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት በእስልምና የተለየ ፈቃድ (Exceptional Permission) እንጂ ብዙ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች እንደሚያስቡት ሕግ ወይም ትእዛዝ አይደለም፡፡

በእስልምና የፈቃድና የክልከላ ህግጋት በአምስት ይከፈላሉ፡፡

ፈርድ ..... ግዴታ

ሙስታህብ ...የሚበረታታ ወይም የሚወደድ

ሙባህ ..... የሚፈቀድ

መከሩህ .....የተጠላ ወይም የማይበረታታ

ሀራም.....የተከለከለ

ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት በሦስተኛው ሙባህ ወይም የሚፈቀድ ከሚለው ሕግ ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ፣ብዙ ሚስቶች ያሉት አንድ ሙስሊም አንድ ሚስት ብቻ ካለው ሌላ ሙስሊም የሚሻልበት ምንም ምክንያት አናገኝም።ምክንየያቱም ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ወደ ሁለተኛው ወይም የሚበረታታ እና የሚወደድ ከሚለው ሕግ ውስጥ ገብቶ እንኳ አናገኘውምና ነው።

ሴቶች በተፈጥሮ ከወንድ የበለጠ ረጅም እድሜ ይኖራሉ።በተፈጥሮ ሴቶችና ወንዶች በተመሳሳይ መጠን ይወለዳሉ።ነገር ግን በሕፃንነት እድሜ ከሚሞቱት ወንዶች ሕጻናት አንፃር ሲታይ በሕፃንነት የሚሞቱ ሴት ህፃናት ቁጥር ዝቅተኛ ሆኖ እናገኘዋለን። ሴት ሕፃናት ከወንድ ሕፃን የተሸለ በሽታንና ጀርምን መዋጋት የሚችሉ ሲሆኑ ይህም በቁጥር ከወንዶች በልጠው እንዲገኙ ያደርጋቸዋል። በተጨማሪም አለማችን በተለያዩ ጦርነቶችና ሰው ሰራሽ ሆነ በተለያዩ አደጋዎች የተከበቦች ናት። በዚህ የተነሳ በጦርነትም ሆነ በተለያዩ አደጋዎች የሚሞቱት ወንዶች ቁጥር ከሴቶቹ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ከፍተኛ ሆኖ ይገኛል።

በአለማችን የሴቶች ቁጥር ከወንዶች የበለጠ ነው።

- በአሜሪካ አገር የሴት አሜሪካዊያን ቁጥር ከወንዶች በ7.8 ሚሊዮን ይበልጣል።ሌላው ቀርቶ በኒውዮርክ ከተማ ብቻ 1 ሚሊዮን ትርፍ ሴቶች ይገኛሉ።ከጠቅላላው የኒውዮርክ ከተማ ሕዝብ ውስጥ አንድ ሶስተኛው ወንድ ግብረሰዶማውያን (ጌይ)ናቸው። በአሜሪካ ደግሞ 25 ሚሊዮን ግብረሰዶማውያን ይገኛሉ። ይህ ማለት ከጠቅላላው የአሜሪካ ወንዶች ውስጥ 25 ሚሊዮን ሚስት ማግባት የማይፈልጉ (የማይችሉ) ወንዶች አሉ ማለትነው።
- በእንግሊዝ ሀገር 4 ሚሊዮን ትርፍ ሴቶች ሲኖሩ ጀርመን ውስጥ ደግሞ 5 ሚሊዮን ባል ሊያገቡ (ሊያገኙ) የማይችሉ ሴቶች አሉ። ሩሲያ ደግሞ 9 ሚሊዮን የጋብቻ ያለህ የሚሉ ሴቶችን ለዓለማችን አበርክታለች። በዚህ እንቀጥል ካልን ዓለማችን ላይ በአጠቃላይ ምን ያህል ከፍተኛ የሆነ የወንዶች ችግር እንዳለ ሊያውቅ የሚችል አላህ (ሱ.ወ) ብቻ ነው ማለት ነው። ሁሉንም ወንድ ከአንድ በላይ እንዲያገባ መከልከል በተግባር ሊፈፀም አይችልም።

ከላይ እንዳየነው ሁሉም ወንዶች አንድ ሚስት ብቻ ያግቡ የሚል ሕግ ብናወጣና ይህንን ህግ ተፈፃሚ ብናደርግ በአሜሪካ ብቻ 30 ሚሊዮን ትዳር አልባ ሴቶች እንፈጥራለን።ከላይ ያየናቸውን የእንግሊዝ እና ሩሲያ ትርፍ ሴቶች ብናከልበት ደግሞ ቁጥሩ የትየለሌ ይሆናል።

እስቲ የኔና ያንተ እህቶች ባል ማግባት ካልቻሉ 30 ሚሊዮን ሴቶች መካከል እንደሆኑ አድርገን እናስብ ከነዚህ ሴቶች መካከል የተቃራኒ ፆታ ፍላጎት ያላቸው ሴቶች የሚኖራቸውን አማራጭ እንመልከት።ባጭሩ ሁለት አማራጭ ብቻ የሚኖራቸው ሲሆና ፣

- አንደኛው ሁለተኛ ሚስት ሆኖ መኖር ሲሆን፣
- ሁለተኛው ቀሪ አማራጭ ደግሞ«የብዙሀን ሚስት» ወይም «የሕዝብ ንብረት» (አመንዝራ) ፣ሴተኛ አዳሪ መሆን ነው። መቼም ማንኛዋም ጨዋና ጤነኛ ሴት የመጀመሪያውን ትመርጣለች ተብሎ ይታሰባል።እርግጥ ነው አብዛኛዎቹ ሴቶች ባሎቻቸውን ከሌሎች ጋር መጋራትን አይወዱም። ነገር ኢስላም ሁኔታዎች አስገዳጅ ሲሆኑ እና ሴቶች «የሕዝብ ንብረት» ይሆናሉ ተብሎ በሚፈራበት አስቢ ሁኔታ ውስጥ አማኝ ሴቶች ትንሽ የሆነን ግላዊ ጉዳት እንዲታገሉ ስለሚያደርግ ነው ይህ አይነቱን ጋብቻ የፈቀደው።የህዝብ ንብረት ከመሆን ይልቅ ያገባን ወንድ በተደራቢነት ማግባት እጅጉን የተሸለ ነው።

በምዕራቡ ዓለም እቁባትና ቅምጥ ከጋብቻ ውጭ መማገጥ የተለመደና ተራ ነገር ነው። በዚህ ሕይወት ውስጥ ያለች ሴት ምንግዜም የተዋረደና ዋስትና የሌለው ኑሮ እንደምትኖር የታወቀ ነው።የሚገርመው ግን የምዕራቡ ዓለም ሴት ልጅ ክብሯ ተጠብቆላትና የሚስትነት ዋስትናዋ አግኝታ በሁለተኛ ሚስትነት የምትኖረው ህይወት አልዋጥለት ያለው መሆኑ ሲታሰብ በጣም አሳፈሪና ግራ የሚያጋባ የስጋዊ ምኞት ብቻ የተደላደለ የሥነ -ምግባር ዝቅጠት የከበበው ማህበረሰብ መሆኑን እንረዳለን።

እንግዲህ ባጠቃላይ ሲታይ አሁን ከዘረዘርናቸው ምክንያቶች በተጨማሪ እስልምና ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ሲፈቅድ ሌሎች ብዙ ምክንያቶች በተጨማሪ እስልምና ከአንድ ሚስት በላ ማግባትን ሲፈቅድ ሌሎች ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩትም በዋነኛነት ግን የሴቷን ክብር ጠብቆ ለማቆየት ሲባል ነው።።

ወደ ሳይንሱ ዓለም ጎራ እንበል እስኪ

በቅርቡ የተካሄዱ ሳይንሳዊ ጥናቶች ወንድ ዘንድ የሚገኘው የፍቅር ቅመም ሴትዋ ዘንድ ከሚገኘው የፍቅር ቅመም የሚለይ መሆኑን አረጋግጠዋል። ይህም አያሌ የሳይንስና የምርምር ተቋማትን በወንድና በሴት መካከል በሚገኙት የፍቅር ስሜቶች ልዩነቶች ላይ ጥልቅ ምርምር እንዲያደርጉ ገፋፍቷቸዋል። ሳይንቲስቶቹ የደረሱበት ውጤት በጣም አስደማሚ ሲሆን፣የወንድ ጂኖች ብዙ ግንኙነቶች እንዲኖሩት ሲገፋፉት የሴቷ ጂኖች ደግሞ ወደ መረጋጋትና ወደ ነጠላ ግንኙነት ይገፋፏታል። ወንድ ከአንድ በላይ ሴቶችን በአንድ ጊዜ ለአንዷ ያለው ፍቅር ለሌላዋ ባለው ፍቅር ላይ ምንም ተጽእኖ ሳይፈጥርበት ማፍቀር የሚችል መሆኑን ዘመናዊው ሳይንስ በተጨባጭ አረጋግጧል።

- የ CNN ድረገጽ በዮታ እስቴት ዩኒቨርሲቲ የሳይኮሎጂ ፕሮፌሰር የሆኑትን ሊዛ ዳይመንድን በመጥቀስ እንዳስነበበው፣ የወንዶች ወሲባዊ ግንኙነት ከአንድ በላይ ሴት ጋር የመሆኑ ሁኔታ ከአካላዊ አፈጣጠራቸው የሚመነጭ ስለመሆኑ ስነሕይወታዊ ማስረጃዎች መኖራቸው ተረጋግጧል።

የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የተመራማሪዎች ቡድን በ2007 ባካሄደው አንድ ምርምር ሴቶች ከወንዶች በተቃራኒ፣ ዋነኛ ትኩረታቸው የሚያነጣጥረው በሰውነቶቻቸው ላይ ወይም በልጆቻቸው እንክብካቤ ላይ መሆኑንና ይህም ከልጆቻቸው ጋር ያላቸውን የመተሳሰር ስሜት በሚጨምረው አክስቶሲን ሆርሞን ምክንያት መሆኑን ደርሰውበታል።የተወሰኑ የወንዶች የአንጎል ክፍሎች ከሴቶቹ በእጥፍ ያህል የሚበልጡ መሆናቸውን፣በተባዕትና በእንስት አንጎል መካከል ያለው ትልቁ ልዩነትም፣በወንዶች ዘንድ ላለው ወሲባዊ ፍላጎት ተጠያቂ የሆነው የአንጎል ክፍል፣ከሴቶቹ ተመሳሳይ የአንጎል ክፍል በሁለት ተኩል እጥፍ ያህል የሚበልጥ መሆኑ ነው።እነዚህ ሳይንሳዊ መረጃዎች ትክክለኛነት ስለተረጋገጠ ተጽእኖ ማሳደራቸው እሙን ነው።

አንዳንድ የዋህ ሰዎች ባለማወቅ ይህ ብዙ ሚስት ማግባት እኮ በጥንቱ ዘመን የነበረ ነው እንጂ፣ዛሬ ግን የሰው ልጅ በሥልጣኔ ተራምዷልና ብዙ ሚስት ማግባት ክልክል ነው ይሉናል።

✔ዕድገትና ሥልጣኔ እኮ ከሰው ልጆች ተፈጥሮ ጋር በመላተም፣ለፍላጎቶቻቸው ምላሽ ባለመስጠትና ከጥቅሞቻቸው በላይ በመሆን እውን አይሆንም። የሰው ልጅ በጥንቱ ዘመን የከብት ሥጋ ይበላ ወይም የበጎችን ሱፍ ይለብስ ነበር ተብሎ ዛሬ ሥጋ መብላትንና ሱፍ መልበስን ኋላቀርነትና አለመሰልጠን አድርጎ መገመት የሚታሰብ አይደለም . . ማለት የሚቻለው የሰው ልጅ ሥልጣኔና ዕድገት እነዚህ ነገሮች ለሰው ልጅ ፍላጎቶችና ለጥቅሞቹ ይበልጥ ምላሽ የሚሰጡና ኑሮውን ይበልጥ የተመቻቸ ማድረግ የሚችሉ መሆናቸውን ነው . . ይህ ደግሞ የእስላም ተልእኮ ነው።

እኮ እንዴት? ካሉም

✔ በምዕራቡ ሕብረተሰቦች ውስጥ ከጋብቻ ማእቀፍ ውጭ የሆኑ የፍቅርና የወሲብ ግንኙነቶች የተስፋፉ መሆናቸውን ግልፅ እውነታ ነው ። እውነቱን ለመናገር በሴቶች ላይ የሚፈጸም ግፍና በደል ማለት፣ለስነልቦናዊ መረጋጋት የማያበቃ፣ሙብትን የማያስከብርና ጤናማ ማህበረሰብን የማይፈጥር እንዲህ ዓይነቱ ግንኙነት ነው። በጥንታዊ ሥልጣኔዎች ውስጥ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ያለ ምንም ገደብና መቆጣጠሪያ የነበረ ሲሆን፣ ኢስላም ሲመጣ ግን አንዱን ባል ሕጋዊ ባል አድርጋ ኃላፊነት ባለው መንገድ እንድትጋራ በማድረግ ለሴቷ ፍላጎት ፍትሐዊ ምላሽ ሰጥቷል። ይህ ክቡር ማሕበራዊ ተቋም - ጋብቻና ቤተሰብ - የበለጠ የስኬታማነት ዋስትና ይኖረው ዘንድ እስላም በዚህ ባል ላይ የተለያዩ ግዴታዎችንና ገደቦችን ጥሏል።

እስላም የሴት ልጅ ጥቅሞችን አስጠብቆ፣ከአንድ በላይ በማግባት የሕጋዊ ጋብቻ ማእቀፍ ውስጥ የወንዱን ሥጋዊ ፍላጎቶች በማፈንና ልቅ በማድረግ መካከል ሚዘናዊነትና መቻቻል እንዲኖር አድርጓል። በዚህም ሌሎች ዘንድ በአውሮፓ በከፍተኛ ደረጃ ለፈረካከሰው ማሕበራዊ ተቋም - ለቤተሰብ መበተን፣ለፍቺ መበራከት- ከፍተኛ ጥቢቃና እንክብካቤ አድርጓል።

ሌላው የሴቶች አማካይ የመኖር ዕድሜ ከወንዶች አማካይ ዕድሜ ከፍ ያለ መሆኑንም መረጃዎቹ ያረጋግጣሉ።

በምዕራቡ ዓለም ወንድ በአማካይ ከሴቷ በ7 ዓመት ያነሰ ዕድሜ ይኖራል። ይህ ልዩነት ባለፈው ምእተ ዓመት በቀጣይነት እየጨመረ መጥቷል። ለምሳሌ ያህል በጀርመን፣የሴት አማካይ ዕድሜ 80 ዓመት ሲሆን፣የወንድ አማካይ ዕድሜ ግን 70 ዓመት ነው። ይህ ልዩነት በ1900 ዓመተ ልደት ሁለት ዓመት ብቻ ነበር።

የሚሸገን ዩኒቨርሲቲው ሳይንቲስት ዳንኤል ክሮጀር እንደሚሉት፣በአብዛኞቹ የዓለም አገሮች ወንዶች ከሴቶች ያነሰ ዕድሜ ይኖራሉ። ከዚህ ልዩነት መንስኤዎች አንዱ በወንድና በሴት መካከል ያለው የሆርሞኖች ልዩነት ሲሆን፣የወንድ ሆርሞኖች የልብና የደም ዝውውር በሽታዎችን የሚያስከትሉ ጂኖችን ያነቃቃሉ።

በተጨማሪም ግጭቶችና ውጥረቶች በነገሱባቸው አገሮች ውስጥ በሚቀጣጠሉ ጦርነቶች፣በአደጋ የታጠሩ ከባድና አስቸጋሪ ሥራዎች፣ በጦርነቶች፣የትራፊክ አደጋን በመሳሰሉ ማሕበራዊ ክስተቶች . . ምክንያት በሚደርሰው ሞት አብዛኞዎቹ ሰለባዎች ወንዶች ናቸው ።ይህም በሕብረተሰቡ ውስጥ የሴቶች ቁጥር ከወንዶች በልጦ ይገኛል ማለት ነው። ይህ በአብዛኞቹ የዓለም አገራት ውስጥ የሕዝብ ቆጠራ መረጃዎች የሚያረጋግጡት እውነታ ነው። እየተስፋፋ የመጣው የፈቶችና ባል የሞተባቸው ሴቶች ቁጥርም ሌላው ነው ።

እናም ባል የሌላቸው ሴቶች የስነልቦናዊ፣ ማሕበራዊና ስነምግባራዊ ችግሮች ሰለባ ሆነው መቅረት አለባቸውን? ወይስ በራሳቸውም ሆነ በሕብረተሰቡ ደህንነት ላይ አፍራሽ ተጽእኖ በሚያስከትል ሁኔታ፣መብታቸውን እንዲለምኑና ተፈጥሯዊ ፍላጎታቸውን በስውር እንዲያረኩ ወደ ዝሙት፣ሴተኛ አዳሪነት፣ወንዱን አስገድዶ መድፈር ወዘተ ....መገፋፋት አለባቸውን? ወይስ የሁሉንም ፍላጎት ያገናዘበ፣በሕጋዊ ደንብና ገደቦች የታጠረ፣የሰው ልጆችን አቅምና ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ፣ማንንም የማይበድልና በሁሉም ወገኖች ላይ ጫና በማይፈጥር ፍትሐዊ ማእቀፍ ውስጥ ለሁሉም ወገኖች ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥ ማሕበራዊ ሥርዓት መደንገግ?! ኢስላምም ይህን ኢ ፍትሃዊነትን ለማስወገድ ሲል ነው አንድ ወንድ ከቻለ እስከ 4 ሚስቶችን በማግባት ሴቶች ከዚህ አይነት ችግሮች እንዲወጡ ያደረጋቸው።

ፈረንሳዊው የስነሕብረተሰብ ሊቅ ዶክተር ጉስታፍ ሊቦን፡- ‹‹ከአንድ በላይ ሚስት ማግባትን የሚፈቅደው የምሥራቁ (እስላማዊው ማለታቸው ነው) የጋብቻ ሥርዓት፣ለሚከተሉት ሕዝቦች ስነምግባራዊ ደረጃን ከፍ የሚያደርግ መልካም ሥርዓት ነው፤የቤተሰብን ትስስር ያጠብቃል፤ለሴት ልጅ አውሮፓ ውስጥ የማታያቸውን አክብሮትና ደስተኝነትን ያጎናጽፋል።›› በማለት ለጥያቄው መልስ ሰጥተዋል። ልብ አድርጉ ይህን ያለው ጉስታፍ ሊቦን ሙስሊም አይደለም።

ብዙ ሚስት የማግባት ሥርዓት በእስላም የተጀመረ አይደለም። ከአንድ በላይ ሴት ማግባት በሁሉም ጥንታዊ ሥልጣኔዎች ዘንድ የተለመደ ነው። ለዚያውም የተወሰነ ቁጥር ተለይቶ ሳይታወቅና ገደብ ሳይኖረው ነው። ብዙ ሚስት የማግባት ሥርዓት በሁሉም መለኮታዊ ሃይማኖቶች ውስጥም የሚታወቅ ነው።

☞በአይሁድ ሃይማኖት ውስጥ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን፣ራቢ ገርሹም አሽከናዚ (960-1040) ከአንድ በላይ ማግባትን ክልክል እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የተፈቀደ ሆኖ ቆይቷል።

☞በክርስቲያኑ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ግን ብዙ ሚስት ማግባት ከአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ እንጂ ክልክል ተደርጎ አያውቅም። እስከ ዛሬም ድረስ ሞርሞንን በመሳሰሉ አንዳንድ ቤተክርስቲያኖች ዘንድ እንደ ተፈቀደ ቀጥሏል።

ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት በክርስትና ክልክል(ሀጢያት) ነውን?

በኢስላም አንድ ወንድ ከቻለ እስከ አራት ሴት የሚያገባበት አግባብ እንዳለ የሚታወቅ ነው፡፡ በርካታ ክርስቲያኖች ይህን መነሻ በማድረግ ኢስላምን ሲያብጠለጥሉ መስማት የተለመደ ነው፡፡ ይህ አካሄዳቸው ሰዎቹ ምን ያክል ለመፅሐፎቻቸው ወይ ባይተዋር ወይ ደግሞ ሽፍታ እንደሆኑ በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡እንጂ በመፅሐፎቻቸው ይሄ ጉዳይ እጅግ በተጋነነ እና ኢስላም ከሚፈቅደውም በራቀ መልኩ የሚገኝ ነው፡፡ ነብያት ሳይቀሩ ብዙ ሚስቶች እንነበራቸው ተገልጿል፡፡

ለምሳሌ ያክል፡-

1.”ለአንድ ሰው አንዲቱ የተወደደች፣ አንዲቱም የተጠላች ሁለት #ሚስቶች ቢኖሩት…” [ዘዳግም 21:15]

2. “ዔሳው ከከነዓን ልጆች #ሚስቶችን አገባ፡፡” [ኦሪት ዘፍጠረት 36፡2]

3. “ላሜሕም #ለሚስቶቹ ለዓዳና ለሴላ አላቸው..” [ኦሪት ዘፍጥረት 4፡23]

4. “ለጌዴዎንም #ብዙ_ሚስቶች ነበሩትና…” [መፅሃፈ መሳፍንት 8:30]

5. “የአብራም ሚስት ሦራ ግብፃዊት ባሪያዋን አጋርን ወስዳ ለባልዋ ለአብራሀም ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው።”

[ኦሪት ዘፍጠረት 16:3]

6. “ዳዊትም ከኬብሮን ከመጣ በኋላ ሌሎቹን #ቁባቶቹንናሚስቶቹን ከእየሩሳሌም ወሰደ፣…” [መፅሐፈ ሳሙኤል ካልእ፡ 5፡13]

7. “ያዕቆብም ተነሳ፣ ልጆቹንና #ሚስቶቹንም በግመሎች ላይ አስቀመጠ፡፡” [ኦሪት ዘ ፍጥረት 31፡ 17]

8. 14 ሚስቶች!!! “አብያም ጸና፣ #አስራአራትን #ሚስቶች አገባ…” [መፅሐፈ ዜና መዋእል ካልእ 13፡21]

9. “ሮብአምም ከሚስቶቹና ከእቁባቶቹ ሁሉ የአቤሴሎምን ልጅ ሞአብን ወደደ #18ሚስቶች #60 እቁባቶች ነበሩት፡፡”

[መፅሃፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 11:21]

10. 700 ሚስቶች እና 300 ቁባቶች ለሰሎሞን!!! “ለእርሱም ወይዛዝር የሆኑ #700ሚስቶች #300 ምቁባቶች ነበሩት፤ ሚስቶቹም ልቡን አዘነበሉት።” [መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 11:3]

ክርስቲያኖች ሆይ! ይቺ ነገር የሙሐመድ ብትሆን እንዴት እንደምታራግቧት እስኪ ህሊናችሁን ጠይቁ!! እምነታችሁ እንዲህ

አይንት ፍርደ ገምድልነትን ያዛችኋልን?

7.ሴቶችና ማህበራዊ

ሴቶች እና ህፃናት በእስልምና & በክርስትና

① ህፃናት እና ሴቶች በክርስትና

ህፃንን ከመቅጣት ቸል አትበል በበትር ብትመታው አይሞትምና ።[መፅሃፈ ምሳሌ 24:13] በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው #ልጁን ይጠላል ልጁን የሚወድ ግን ተግቶ ይገስፀዋል። (መፅሃፈ ምሳሌ 13:24)

#ሕፃናቶቻሽን ይዞ በአለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው።» (መዝሙር ዳዊት 137:8-9)

«በሰይፍ ይወድቃሉ፥ #ሕፃኖቻቸውም ይፈጠፈጣሉ፥ እርጉዞቻቸውም ይቀደዳሉ።» (ትንቢተ ሆሴዕ 13:16)

«…ጠላቶቻችሁን ለመውጋት ትቀርባላችሁ፤ ልባችሁ አይታወክ አትፍሩ አትንቀጥቀጡ በፊታቸውም አትደንግጡ፤ አምላክህ እግዚአብሔር በእጅህ አሳልፎ በሰጣት ጊዜ በእርሷ ያሉ ወንዶችን ሁሉ በሰይፍ ስለት ትገድላቸዋለህ፤ ነገር ግን

☞ሴቶቹንና

☞ህጻናትን እንሰሶቹንም በከተማይቱም ያለውን ምርኮ ሁሉ በዝብዘህ ለአንተ ትወስዳለህ፤…»ኦሪት ዘዳግም 20፡3

«…አሁን አማሌቅን ም ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ አትማራቸውም ወንዱንና

☞ሴቱን፤ ህጻኑን፤ ብላቴናውና፤ በሬውንና በጉን፤ግመሉንና አህያውን ግደል፡» (መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15፡3)

«እንደገናም እግዚአብሔር ሌሎቹን ሰዎች እንዲህ ሲላቸው ሰማሁ በሉ እናንተም እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ ውስጥ በመዘዋወር ሁሉን ግደሉ፤ ለማንም በመራራት ምሕረት አታድርጉ፡፡

☞ሽማግሌ ሆነ ወጣት፤አሮጊት ሆነች ኮረዳ፤ሕጻናትም ሳይቀሩ ሁሉንም ግደሉ፡፡ …»(ትንቢተ ሕዝቅኤል 9፡5-6 ቀለል ባለ የአማርኛ ትርጉም 1980 እትም)

«ስለዚህ ጉባኤው ወደ ያቤሽ ሄዳችሁ

☞#ሴቶችንና

☞#ልጆችን ጭምር ሁሉንም ግደሉ፤

ወንዶችንና ድንግል ያልሆኑ ☞ሴቶችን በሙሉ ግደሉ የሚል መመሪያ በመስጠት ከመካከላቸው ምርጥ የሆኑትን ዐሥራ

ሁለት ሺህ ሰዎችን ላኩ፡፡»መጽሐፈ መሳፍንት 21፡10-11 ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ 1980 እትም

«በሰባተኛው ዙር ካህናቱ መለከት ሲነፉ በሚዘጋጁበት ጊዜ ወ ደሮቹ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲደነፉ ኢያሱ እንዲህ

የሚል ትዕዛዝ ሰጠ … ከዚህም በኋላ ሰራዊቱ ኮረብ ውን ወጥቶ ሰተት ብሎ ወደ ከተማይቱ በመግባት በቁጥጥሩ ስር

አደረጋት፤ ሰይፋቸውንም መዝዘው በከተማይቱ የተገኘውን ወንዱንም

☞ሴቱንም

☞ህፃናትን

ወጣቱንና ሽማግሌውን ሁሉ ገደሉ፤የከብት፤የበግና የአህያውን መንጋ ሁሉ ፈጁ::» (መጽሐፈ ኢያሱ 6፡16-21 ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ 1980 እትም)

አዎን! ሙስሊሞች የሚከተለውን የአላህ መልዕክተኛ ንግግር ያከብራሉ፦

« وَإِنَّ رِيحَهَا تُوجَدُ مِنْ مَسِيرَةِ أَرْبَعِينَ عَامًا ، مَنْ قَتَلَ مُعَاهَدًا لَمْ يَرِحْ رَائِحَةَ الجَنَّةِ »

-› «(የሰላም) ቃል ኪዳን የተገባለትን የገደለ የጀነትን ሽታ እንኳ አያሸትም፤ የርሷ ሽታ የአርባ አመታት የጉዞ ርቀት ላይ ይገኛል!» [አል-ቡኻሪይ በቁጥር 3166 ከአብዱ'ላህ ኢብኑ ዐምር ዘግበውታል።]

1- «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ አማሌቅ በመንገድ እየተቃወመ ያደረገበትን እበቀላለሁ። አሁንም ሄደህ አማሌቅን ምታ፣ ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፣ አትማራቸውም፤ ወንዱንና

☞#ሴቱን

ብላቴናውንና

☞ህጻኑን

በሬውንና በጉን፤ ግመሉንና አህያውን ግደል።»[መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15:2-3]

2- በዚያን ጊዜም ከተሞቹን ሁሉ ወሰድን የተቀመጡባቸውንም ሰዎች ሁሉ

☞ሴቶችንም

☞ሕፃናቶችንም አጠፋን፤ አንዳችም አላስቀረንም!»(ኦሪት ዘዳግም ምዕ. 2:31-34)

3- «..አምላክህ እግዚአብሔር እንዳዘዘህ ኬጢያዊውን: አሞራዊውንም :ከነዓናዊውንም:ፌርዛዊውንም:ኤዊያዊውንም

ኢያቡሳዊውንም ፈጽመህ ታጠፋቸዋለህ። »[ኦሪት ዘዳግም ምዕ. 20፡ 16-18]

4- « በከተማይቱም የነበሩትን ሁሉ፥ ወንዱንና

☞ሴቱን፥

☞ሕፃኑንና

ሽማግሌውን፥በሬውንም፤ በጉንም ፤አህያውንም፥ በሰይፍ ስለት ፈጽመው አጠፉ። » [መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 6:21] በከተማይቱ መካከል እለፉ ግደሉም፤ ዓይናችሁ አይራራ አትዘኑም፤ ሽማግሌውንና ጐበዙን ቄንጆይቱንም

☞ሕፃናቶቹንና

☞ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ [ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕ. 9:4-7]

6- «የእስራኤልንም አምላክ እግዚአብሔርን የማይፈልግ ታናሽ ወይም ታላቅ፣ ወንድ ወይም ሴት ቢሆን ይገደል ዘንድ ማሉ። »[መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 15:13]

7- «አንቺ ወራዳ የባቢሎን ልጅ ሆይ! ስለተበቀልሽን የሚበቀልሽ የተመሰገነ ነው። #ሕፃናቶችሽን ይዞ በአለት ላይ የሚፈጠፍጣቸውየተመሰገነ ነው።» [መዝሙር ዳዊት 137:8-9]

8- «ሰማርያ በአምላክዋ ላይ ዐምፃለችና በደልዋን ትሸከማለች፤ በሰይፍ ይወድቃሉ፥ ሕፃኖቻቸውም ይፈጠፈጣሉ፥ እርጉዞቻቸውም ይቀደዳሉ።

እስልምናችን የሚያስተምረው የሚከተለውን ነው።

#ነፍስን_የገደለ_ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው ። (አል-ማኢዳ 5፤ 32)

“ያቺንም አላህ ያወገዛትን ነፍስ ያለ ሕግ #አትግደሉ ።” (አልኢስራእ 17፤33)

“ያቺንም አላህ ያወገዛትን ነፍስ ያለ ሕግ #አትግደሉ።” (አል- ኢስራእ 17፤33)

በሃዲስ ላይ ደግሞ እንዲህ ተገልፆል: አብዱላህ ኢብኑ ዑመር ባስተላለፉት ሐዲስ ነብያችን እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል።

☞ “ሙአሂድን (በሙስሊሞች ጋር ስምምነት አድርጎ በሙስሊሞች ጥበቃ ሥር የሚኖር ግለሰብን) የገደለ ሰው ሽታዋ አርባ ቀናት ከሚያውደው ጀነት_ጠረን እንኳ አይደርሰውም።” (ቡኻሪ፤ ሐዲስ 3166) ይህም ማለት አንድ ሰው አንድን ነብስ ያለአግባብ ካጠፋ(ከገደለ) ጀነት(ገነት) አይገባም(የጀነትን ሽታ) አያገኝም ማለት ነው።

አላህ ሱወ በቅዱስ ቁርዓኑ ይህ አለን

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁን በመካከላችሁ ያለ አግባብ አትብሉ። ግን ከእናንተ በመዋደድ የኾነችውን ንግድ (ብሉ)። #ነፍሶቻችሁንም_አትግደሉ ። አላህ ለእናንተ አዛኝ ነውና።” (አኒሳእ 4፤29)

#ነፍስን_የገደለ_ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው ። ”

(አል-ማኢዳ 5፤32)

②→ሴቶች እና ህፃናት በእስልምና

እስልምና እንኳን ሴት ልጅን እና ህፃናትን ለመግደል ይቅርና የሙስሊሙን ህልውና ለመፋቅ ሰይፋቸውን ከመዘዙ ጠላቶች ጋር በሚደረግ የጦር ሜዳ ፍልሚያ ላይ እንኳ ወሰን ማለፍን የሚከለክል ነው! አላህ እንዲህ ብሏል፦

ٱلْمُعْتَدِينَ يُحِبُّ لَا ٱللَّهَ إِنَّ تَعْتَدُوٓاْ وَلَا يُقَٰتِلُونَكُمْ ٱلَّذِينَ ٱللَّهِ سَبِيلِ فِي وَقَٰتِلُواْ

☞= {እነዚያ የሚጋደሏችሁን በአላህ መንገድ ላይ ተጋደሏቸው፤ ወሰንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና።} [አል-በቀረህ 2 : 190]

አዎን! “ለሚጋደሏችሁ አንገታችሁን ስጡ!” አልተባልንም! ግን ራስን በመከላከል ሂደትም ቢሆን የትኛውንም የፍትህና የሰብዓዊነት ወሰን ማለፍን ተከልክለናል!

-› “ወሰንም አትለፉ!” የሚለውን የአንቀፁን መልዕክት ታዋቂው የመልዕክተኛው ባልደረባ ዐብዱ’ላህ ኢብኑ ዐብ-ባስ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፦

اعتديتم فقد هذا فَعلتم فإن يَده، وكفَّ السَّلَمَ إليكم ألقى منْ وَلا الكبير الشيخ ولا الصِّبيان ولا النساء تقتلوا لا :يقول.

☞«”#ሴቶችን፣ #ህፃናትን፣ አዛውንትን፣ እርቅን ወደናንተ ያቀረበንና እጁን የሰበሰበንም አትግደሉ! ይህን ካደረጋችሁ ወሰን አልፋችኋል!” ማለቱ ነው!»

☞[አጥ-ጠበሪ – “ጀሚዑ’ል-በያን..”

☞(“ተፍሲሩ’ጥ-ጠበሪ”) (3/563)፣

☞ኢብኑ አቢ ሓቲም – “አት-ተፍሲር” (1/325) ቁጥር 1721]

ያስተውሉ! ይህ ሁሉ ገደብ በጦርነት ላይ ነው።

* እንዲሁም ነብያችን ዘማቾችን ለውጊያ በሚልኩበት አጋጣሚ ዘወትር ከሚመክሯቸው ምክሮች መካከል፦

وَلِيدًا تَقْتُلُوا وَلَا تَمْثُلُوا وَلَا تَغْدِرُوا وَلَا...

-› «ቃል ኪዳን አታፍርሱ፤ ሬሳንም አትቆራርጡ፤ #ህፃንም አትግደሉ..» የሚል አደራ ይገኝበታል።

☞[ሙስሊም የዘገቡትና ቡረይደህ ያስተላለፉት ሐዲሥ ነው፤ ሰሂህ ሙስሊም – ቁጥር (1731)]

☞ እንዲሁም ዐብዱ’ላህ ኢብኑ ዑመር የሚከተለውን አስተላልፈዋል፦

وسلم عليه الله صلى اللَّهِ رَسُولُ فَأَنْكَرَ مَقْتُولَةً، وسلم عليه الله صلى اللَّهِ رَسُولِ مَغَازِي بَعْضِ فِي وُجِدَتْ امْرَأَةً، أَنَّ :عمر بن اللَّهِ عَبْدِ عَنْ وَالصِّبْيَانِ النِّسَاءِ قَتْلَ

-› «በመልዕክተኛው አንድ ዘመቻ ላይ አንዲት የተገደለች #ሴት ተገኘች፤ እርሳቸውም ሴቶችንና ህፃናትን መግደልን አወገዙ።»

[☞[አል-ቡኻሪይ – ቁጥር (3014) ፤ ሙስሊም – ቁጥር (1744)]

* አል-ኢማም ኢብኑ ዐብዲ’ል-በር ይህንን ዘገባ ባብራሩበት አጋጣሚ እንዲህ ብለዋል፦

أَطْفَالِهِمْ وَلَا الْحَرْبِيِّينَ نِسَاءِ قَتْلُ عِنْدَهُمْ يَجُوزُ وَلَا الْحَدِيثِ هَذَا بِجُمْلَةِ الْقَوْلِ عَلَى الْعُلَمَاءُ وَأَجْمَعَ

«የኢስላም ሊቃውንት የዚህን ሐዲሥ ጥቅል መልዕክት በመቀበል ላይ ተስማምተዋል፦ እናም እነርሱ ዘንድ የተዋጊ ጠላቶችን ሴቶችና ህፃናትን መግደል አይፈቀድም ክልክል ነው..»

☞[ኢብኑ ዐድቢ'ል0በር – "አት-ተምሂድ" (16/138)] በተመሳሳይ መልኩ አል-ኢማም አን-ነወዊ እንዲህ ብለዋል፡-

يُقَاتِلُوا لَمْ إِذَا وَالصِّبْيَانِ النِّسَاءِ قَتْلِ وَتَحْرِيمِ الْحَدِيثِ بِهَذَا الْعَمَلِ عَلَى الْعُلَمَاءُ أَجْمَعَ...

« ይህ ሐዲሥ የሚተገበር ስለመሆኑና #ሴቶችና #ህፃናትም እስካልተጋደሉ ድረስ እነርሱን መግደል እርም ስለመሆኑ ሊቃውንት ተስማምተዋል..»

☞[አን-ነወዊ – "ሸርሑ ሰሂህ ሙስሊም" (12/48)]

* እንዲሁም አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዳስተላለፉት ነብያችን(ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፡-

" امْرَأَةً وَلَا صَغِيرًا وَلَا طِفْلًا وَلَا فَانِيًا شَيْخًا تَقْتُلُوا وَلَا اللَّهِ، رَسُولِ مِلَّةِ وَعَلَى وَبِاللَّهِ اللَّهِ بِاسْمِ انْطَلِقُوا .. "

-› «በአላህ ስም፣ በአላህ ታግዛችሁ በመልዕክተኛው መንገድ ላይ ጉዞ ጀምሩ፤ ያረጀ ሽማግሌን፣ #ህፃንን፣ (ያልደረሰ) ልጅንና #ሴትን አትግደሉ! ..»

☞[አቡ ዳዉድ – ቁጥር (2614)]

☞እንዲሁም ረባሕ ኢብኑ አር-ረቢዕ ባስተላለፉት ዘገባ ደግሞ ነብያችን እንዲህም ብለዋል፡-

عَسِيفًا وَلَا ذُرِّيَّةً، تَقْتُلُوا لَا

-› «..#ልጆችንና ተቀጣሪ #ሰራተኛን አትግደሉ!»

☞[አሕመድ – ቁጥር (15992) ፤ አቡ ዳዉድ (2669)]

☞እንዲሁም በሌላ ዘገባ ከመልዕክተኛው ህልፈት በኋላ የመጀመሪያው የሙስሊሞች መሪ የሆኑት ታላቁ ኸሊፋ አቡበክር አስ-ሲድ-ዲቅ በአንድ አጋጣሚ የዚድ ኢብኑ አቢ ሱፍያንን ለዘመቻ ሲልኩት እንደሚከተው እንደመከሩት ተዘግቧል፡-

"..وَلَا شَاةً، تَعْقِرَنَّ وَلَا عَامِرًا، تُخَرِّبَنَّ وَلَا مُثْمِرًا، شَجَرًا تَقْطَعَنَّ وَلَا هَرِمًا، كَبِيرًا وَلَا صَبِيًّا، وَلَا امْرَأَةً، تَقْتُلَنَّ لَا :بِعَشْرٍ مُوصِيكَ وَإِنِّي تَجْبُنْ وَلَا تَغْلُلْ، وَلَا تُغَرِّقَنَّهُ، وَلَا نخلا، تَحْرِقَنَّ وَلَا لِمَأْكَلَةٍ، إِلَّا بَعِيرًا

-› «..አስር ነገሮችን አደራ እልሃለሁ፡-

☞#ሴትን፣

☞#ህፃንንም፣

☞ ያረጀ ሽማግሌንም እንዳትገድል፤

☞የሚያፈራ ዛፍን እንዳትቆርጥ፤

☞ ግንባታዎችን እንዳታፈራርስ፤

☞በግን

☞ፍየልንና

☞ግመልን በአግባቡ ለመብላት ካልሆነ በቀር እንዳትገል (እንዳታቆስል)

☞ የተምር ዘንባባን (አንዳንድ መዛግብት ላይ፡-

☞የንብ ቀፎን..) እንዳታቃጥል፤

☞ በውሃም እንዳታሰምጠው፤

☞ የምርኮ ንብረትንም ሳይከፋፈል እንዳትወስድ፤ እንዳትፈራም!»

⇄☞[አል-ኢማም ማሊክ – በ“አል-ሙወጥ-ጠእ” ቁጥር (1627) ላይ ከየሕያ ኢብን ሰዒድ አስተላልፈውታል።

አል-ኢማም አል-አውዛዒይ ይህን አስመልክቶ የሚከተለውን ብለዋል፡-

بَعْدَهُ الْمُسْلِمُونَ بِذَلِكَ وَعَمِلَ عَامِرًا، يُخَرِّبَ أَوْ مُثْمِرًا، شَجَرًا يَقْطَعَ أَنْ [يزيدَ] الصِّدِّيقُ بَكْرٍ أَبُو وَنَهَى

«አቡ በክር አስ-ሲድ-ዲቅ

☞ የሚያፈራ ዛፍን እንዳይቆርጥና

☞ መኖሪያ ግንባታን እንዳያፈራርስ [የዚድን] ከልክለዋል፤ ሙስሊሞችም ከርሳቸው በኋላ ይህንን (መመሪያ) ተግብረዋል።»

☞[ሱነኑ’ት-ቲርሚዚይ – አብዋቡ’ስ-ሲየር – ከቁጥር 1552 ቀጥሎ የሰፈረ ነው።]

አዎን! ይህ ነው የኛ ኢስላም ለህፃናት እና ለሴቶች ጠበቃ!

الْهُدَى اتَّبَعَ مَنِ عَلَى وَالسَّلَامُ

“እወቁ! ሙአሂድን (ከሙስሊሞች ጋር በቃልኪዳን የሚኖርን ሠው) የጨቆነ፣ መብቱን የነፈገ፣ (አገልጋዩ ከሆነ ደግሞ) ከአቅሙ በላይ ያሰራ፣ ያለስምምነቱ ንብረቱ የያዘበት ከሆነ በዕለተ ትንሳዔ ከተበዳዩ ጋር እሆናለሁ (እደግፈዋለሁ)።” (ሱነን አቡ ዳውድ፣ ሐዲስ 3053) አልሃምዱሊላህ ይህ ነው የኛ ኢስላም

የሴት ልጅ አለባበስ በእስልምና እና በክርስትና ምን ይመስላል?

የሴቶች አለባበስስ በእስልምና ምን መሆን አለበት?

“አንተ ነብይ ሆይ ለሚስቶችህ ለሴት ልጆችህም ለምዕመናን ሚስቶችም ከመከናነቢያዎቻቸው በላያቸው ላይ እንዲለቁ ንገራቸው። ይህ እንዲታወቁና (በባለጌዎች) እንዳይደፈሩ ለመሆን በጣም የቀረበ ነው።(አልዓህዛብ 33፥59)

☞ የአደም ልጆች ሆይ! ጎፍረተ ገላችሁን የሚሸሸግን ልብስሸጌጥንም በእርግጥ በናንተ ላይ አወረድን። አላህን የመፍራትም ይህ የተሻለ ነው። ይህ ከአላህ ተዓምራቶች ነው። ይገሰጽ ዘንድ አወረደላቸው። ቁርዓን ☞24:31

☞ ለምእምናትም ንገራቸው :- ዓይኖቻቸውን ይከልክሉ፤ ብልቶቻቸውንም ይጠብቁ፤ ጌጣቸውንም ከርሷ ግልጽ ከሆነው በስተቀር አይግለጡ፤ ጉፍታዎቻቸውንም በአንገትጌዎቻቸው ላይ ያጣፉ፤ (የውስጥ) ጌጦቻቸውንም ለባሎቻቸው ወይም ለአባቶቻቸው፣ ወይም ለባሎቻቸው አባቶች፣ ወይም ለወንዶች፤ ልጆቻቸው፣ ወይም ለባሎቻቸው ወንዶች ልጆች፣ ወይም ለወንድሞቻቸው ወንድ ልጆች፣ ወይም ለእኅቶቻቸው ወንዶች ልጆች፣ ወይም ለሴቶቻቸው፣ (1) ወይም እጆቻቸው ለያዙት (ባሪያ) ወይም ከወንዶች ለሴት ጉዳይ የሌላቸው ለሆኑ ተከታዮች ወይም ለነዚያ በሴቶች ሐፍረተ ገላ ላይ ላላወቁ (1) ሕጻናች ካልሆነ በስተቀር አይግልጹ፣ ከጌጣቸውም የሚሸፍኑት ይታወቅ ዘንድ በእግሮቻቸው አይምቱ፤ ምእምናኖች ሆይ! ትድኑ ዘንድ ሁላችሁም ወደ አላህ (በመመለስ) ተጸጸቱ። (1) ለሃይማኖት ወገኖቻቸው (2) አካለ መጠን ላልደረሱ። (አል ቁርዓን 33:59)

☞ አንተ ነቢይ ሆይ ለሚስቶችህ፣ ለሴቶች ልጆችህም፣ ለምእምናን ሚስቶችም፣ ከመከናነቢያቸው በላያቸው ላይ እንዲለቁ ንገራቸው፤ ይህ እንዲታውቁና (በበለጌዎች) እንዳይደፍሩ ለመሆን በጣም የቀረበ ነው፤ አላህም መሐሪ አዛኝ ነው።

☞ “የሴት ልብስ የሚለብስን ወንድ እና የወንድ ልብስ የምትለብስን ሴት ነብዩ ረግመዋል። (አቡ ዳውድ እና ሀኪም የዘገቡት)

የሴት ልጅ አለባበስ በክርስትና ምን መሆን አለበት?

ብዙ ክርስቲያኖች ሙስሊም ሴቶች ሰውነታቸውን በሚገባ ስለሚሸፋፈኑ ይህን የሙስሊም ሴቶች አለባበስ ሲተቹት ይታያል እንደውም አንድ መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን የተባሉ አዛውንት በአንድ መጽሃፋቸው ላይ ይህን የሙስሊም ሴቶች አለባበስ አረባዊ መጋረጃ ሲሉ ይኮንኑታል። ነገር ግን በጣም የሚያሳዝነው እኚህ ታላቅ ምሁር (ቄስ) መጽሃፍ ቅዱሳቸውን በሚገባ ስላላነበቡት ነው እንጂ ይህን የሙስሊም ሴቶች አለባበስ መጽሃፍ ቅዱስ እንዲለበስ ከማዘዙም በላይ የነብያት (የሚስት እና ቤተሰባቸው አለባበስ) መንገድ እንደሆነ አስቀምጦት ይገኛል።

“ ሴትም ራሷን ባትሸፈን ጸጉሯን ደግሞ ትቆረጥ ለሴት ግን ጸጉሯን መቁረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፍን” (፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፩፥፭) “ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ ወንድም የሴት ልብስብ አይልበስ ይህን የሚያደርግ በኣምላክ በእግዛአብሔር ዘንድ የተጠላ ነውና።”(ኦሪት ዘዳግም ፳፪፥፭)

ኒቃብ (አይነርግብ) በመፅሀፍ ቅዱስ

ኒቃብ(ፊትን ጨምሮ መላ አካላትን የሚሸፍነው አለባበስ) በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ:- ይህ አይነቱ አለባበስ የኣሁን ጊዜ ሙስሊም ሴቶች አለባበስ ብቻ ሳይሆን የቀደምት ሙስሊም ሴቶችም አለባበስ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል።የሴት ልጅ መሸፈን ከጥንት ጀምሮ የነበረ ነው::

ዘፍጥረት 24፤ 64፤ ርብቃም ዓይኖችዋን አቀናች፥ ይስሐቅንም አየች፥ ከግመልም ወረደች። 65፤ ለሎሌውንም። ሊገናኘን በሜዳ የሚመጣ ይህ ሰው ማን ነው? አለችው። ሎሌውም። እርሱ ጌታዬ ነው አላት፤ እርስዋም መሸፈኛ ወስዳ ተከናነበች። 66፤ ለሎሌውም ያደረገውን ነገር ሁሉ ለይስሐቅ ነገረው።67፤ ይስሐቅም ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን አገባት፥ ርብቃንም ወሰዳት፥ ሚስትም ሆነችው፥ ወደዳትም፤ ይስሐቅም ከእናቱ ሞት ተጽናና።

ብዙ ክርስቲያኖች ሙስሊም ሴቶች ሰውነታቸውን በሚገባ ስለሚሸፋፈኑ ይህን የሙስሊም ሴቶች አለባበስ ሲተቹት ይታያል እንደውም አንድ መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን የተባሉ አዛውንት በአንድ መጽሃፋቸው ላይ ይህን የሙስሊም ሴቶች አለባበስ አረባዊ መጋረጃ ሲሉ ይኮንኑታል።ነገር ግን በጣም የሚያሳዝነው እኚህ ታላቅ ምሁር (ቄስ) መጽሃፍ ቅዱሳቸውን በሚገባ ስላላነበቡት ነው እንጂ ይህን የሙስሊም ሴቶች አለባበስ መጽሃፍ ቅዱስ እንዲለበስ ከማዘዙም በላይ የነብያት (የሚስት እና ቤተሰባቸው አለባበስ) መንገድ እንደሆነ አስቀምጦት ይገኛል።

“ ሴትም ራሷን ባትሸፈን ጸጉሯን ደግሞ ትቆረጥ ለሴት ግን ጸጉሯን መቁረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፍን” (፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፩፥፭) “

ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ ወንድም የሴት ልብስብ አይልበስ ይህን የሚያደርግ በኣምላክ በእግዛአብሔር ዘንድ የተጠላ ነውና።”

(ኦሪት ዘዳግም ፳፪፥፭)

በመፅሀፍ ቅዱሥ እንዲህ ይለናል።

1)☞በአይነ ርግብ መሸፈኛሽ ውስጥ ጉንጭሽን እንደተከፈለ ሮማን ናቸው። (መሀልየ ዘሰለሞን 6፡7)

2)☞እርሥዋ መሸፍፈኛ ወሥዳ ተከናነበች። (ዘፍጥረት 24፡66)

3)☞ከተማይቱን የሚዞሩት አገኙኝ መቱኝ አቆሰሉኝ ቅጥር ጠባቂወችም የአይነ ርግብ መሸፈኛየን ወሰድት።(መሀልየዘሥለሞን 5፡6)

4)☞በአይነ ርግብ መሸፈኛሽ ውስጥ አይኖችሽ እንደርግብ ናቸው ። (መሀልየ ዘሥለሞን 4፡1) ማንኛዋም ሴት የሰውነቷን ቅርፅ የሚያሳይ ወይም ክፍትፍት ልብስ ለብሳ መሄዷ የሁሉንም ወንዶች ስሜት መፈታተኗ እርግጥ ነው።ይህ ደግሞ ለኃጢያት ኣጋልጦ ይሰጣል፡፡ እዚህ ላይ የተሳሳተው በራሱ ደካማነት ነው ብሎ ምክንያት መስጠት አይቻልም ፈጣሪ የሚጠይቀው በማን ተሰናከለ የሚለውን ጭምር ነውና በክርስትና ደግሞ ሰውን ማሰናከል እጅግ የከፋ ኃጢያት ነው ይለናል፡-

☛“ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባህር መስጠም ይሻለው ነበር፡፡” (ማቴ. 18፡6) ☚

አንዳንድ ሴቶች እግዚአብሔር ምን ሰራሽ እንጂ ምን ለበስሽ አይለኝም ይላሉ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል፡-

☛☛“እንግዳ ልብስ የሚለብሱትንም ሁሉ እቀጣለው፡፡” (ትን.ሶፎ. 1፡18) ☚☚ አለቀ።

እንግዲህ የሴቶቹን እንቀበል ወይስ የእግዚአብሔርን ምርጫው ያንቺው ነው እህቴ መጽሐፍ ግን እንዲህ ይላል፡-

☛☛“ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል፡፡”(የሐዋ. 5፡29) ☚☚ በሴቶችና በወንዶች መካከል የአለባበስ ልዩነት ሊኖር ይገባል ይላል መፅሃፉ ሚያነበው ና ሚተገብረው ሰው ባይኖርም

☛☛“ሴት የወንድን ልብስ አትልበስ ወንድም የሴትን ልብስ አይልበስ ይህን የሚያደርግ በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው፡፡” (ዘዳ. 22፡5) ☚☚

ታዲያ ቀሚስን የወንድ ሱሪን የሴት ማን አደረገው? ይህ የሰነፍና ለስህተታቸው ምክንያትን የሚሹ ሴቶች የሚያነሱት ጥያቄ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ክርስትያን ወገኖች የፈጣሪን ቃል ሰምታችሁና አውቃችሁ ልትፈፅሙ እንጂ በቃሉ ላይ እንደፈለጋቹ ለራሳቹ በሚመቻቹ መንገድ ልትተረጉሙት አይደለም ለነገሩ እውነታችሁን ነው መፅሀፍ ቅዱስን አንድበአንድ ብትተረጉሙትና ብትፈፅሙት ሙስሊም ትሆኑ ነበር። ግን ደግሞ ተፈጥሯችንን ብቻ በማየት ህሊናችን እራሱ ቢናገር ሱሪ የሴት ነውን? ቀሚስስ የወንድ ነው እንዴ ?

☞☞"ተፈጥሮ እንኳን አያስተምራችሁምን? (1ኛ ቆሮ. 11፡14)

☞☞"ዳሩ ግን ማንም ሊከራከር ቢፈቅድ እኛ ወይም የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ያለ ልማድ የለንም፡፡" (1ኛ. ቆሮ. 11፡16) ☜☜

እዚህ ላይ ግን ቀሚስ ሲባል ከውስጥ ሱሪ የማይሻለውን ብጣሽ ጨርቅ እንዲሁ ቁመቱ ረዥም ሆኖ ከሰውነት ጋር የሚጣበቀውን አይነት አለባበስ ማለት እንዳልሆነ ልብ እንበል፡፡ እህቶቻችን ሆይ ማስተዋልን ትላበሱ ዘንድ እንለምናችኋለን መሰልጠንና መሰይጠንም ትለዩ ዘንድ ይሁን ሰውነትሽ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነውና ሁሉን በአግባብና በሥርዓት አድርጊለት፡፡ ደግሞም ክርስትና ራስ ወዳድነትን አብዝታ ትጠላለች ምንም ነገር ስናደርግ ስለ ሌላው ሰው ልናስብ ያስፈልገናል እኛስ ሰውን ወደ ዝሙት ሊያመራው ስለሚችል አለባበሳችን እጅግ ተጨነቅን ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ በሴቶች ቅጥ ባጣ አለባበስ ምክንያት ወንድማቻችንን ስለማሰናከል ምን ተባለ? ☞☞"ሙበል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ወንድሜን እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም፡ ፡" (1ኛ.ቆሮ 8፡13)

Summary

ኒቃብ ወይም አይነ ርግብ(ኒቃብ) በመፅሀፍ ቅዱሥ እንዲህ ይለናል።

1) ☞ በአይነ ርግብ መሸፈኛሽ ውስጥ ጉንጭሽን እንደተከፈለ ሮማን ናቸው።(መሀልየ ዘሰለሞን 6፡7)

2) ☞ እርሥዋ መሸፍፈኛ ወሥዳ ተከናነበች።(ዘፍጥረት 24፡66)

3) ከተማይቱን የሚዞሩት አገኙኝ መቱኝ አቆሰሉኝ ቅጥር ጠባቂወችም የአይነ ርግብ መሸፈኛየን ወሰድት።(መሀልየዘሠለሞን 5፡6)

4) ☞ በአይነ ርግብ መሸፈኛሽ ውስጥ አይኖችሽ እንደርግብ ናቸው ።(መሀልየ ዘሠለሞን 4፡1)

ማንኛዋም ሴት የሰውነቷን ቅርፅ የሚያሳይ ወይም ክፍትቅት ልብስ ለብሳ መሄዷ የሁሉንም ወንዶች ስሜት መፈታተኗ እርግጥ ነው።ይህ ደግሞ ለኃጢያት አጋልጦ ይሰጣል፡፡ እዚህ ላይ የተሳሳተው በራሱ ደካማነት ነው ብሎ ምክንያት መስጠት አይቻልም ፈጣሪ የሚጠይቀው በማን ተሰናከለ የሚለውን ጭምር ነውና በክርስትና ደግሞ ሰውን ማሰናከል እጅግ የከፋ ኃጢያት ነው ይለናል፡-

☞"ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባህር መስጠም ይሻለው ነበር፡፡" (ማቴ. 18፡6) ☜

አንዳንድ ሴቶች እግዚአብሔር ምን ሰራሽ እንጂ ምን ለበስሽ አይለኝም ይላሉ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል፡-

☞☞"እንግዳ ልብስ የሚለብሱትንም ሁሉ እቀጣለው፡፡" (ትን.ሶፎ. 1፡18)☜☜አለቀ።

እንግዲህ የሴቶቹን እንቀበል ወይስ የእግዚአብሔርን ምርጫው ያንቺው ነው እህቴ መጽሐፍ ግን እንዲህ ይላል፡-

☞☞“ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል።” (የሐዋ. 5፡29)☜

በሴቶችና በወንዶች መካከል የአለባበስ ልዩነት ሊኖር ይገባል ይላል መፅሃፉ ሚያነበው ና ሚተገብረው ሰው ባይኖርም ☞☞“ሴት የወንድን ልብስ አትልበስ ወንድም የሴትን ልብስ አይልበስ ይህን የሚያደርግ በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው።” (ዘዳ. 22፡5) ☜☜

ታዲያ ቀሚስን የወንድ ሱሪን የሴት ማን አደረገው? ይህ የሰነፍና ለስህተታቸው ምክንያትን የሚሹ ሴቶች የሚያነሱት ጥያቄ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ክርስትያን ወገኖች የፈጣሪን ቃል ሰምታችሁና አውቃችሁ ልትፈፅሙ እንጂ በቃሉ ላይ እንደፈለጋቹ ለራሳቹ በሚመቻቹ መንገድ ልትተረጉሙት አይደለም ለነገሩ እውነታችሁን ነው መፅሀፍ ቅዱስን አንድበአንድ ብትተረጉሙትና ብትፈፅሙት ሙስሊም ትሆኑ ነበር።ግን ደግሞ ተፈጥሯችንን ብቻ በማየት ህሊናችን እራሱ ቢናገር ሱሪ የሴት ነውን? ቀሚስስ የወንድ ነው እንዴ ?

☞☞“ተፈጥሮ እንኳን አያስተምራችሁምን? (1ኛ ቆሮ. 11፡14)

☞☞“ዳሩ ግን ማንም ሊከራከር ቢፈቅድ እኛ ወይም የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ያለ ልማድ የለንም።” (1ኛ. ቆሮ. 11፡16)☜☜

እዚህ ላይ ግን ቀሚስ ሲባል ከውስጥ ሱሪ የማይሻለውን ብጣሽ ጨርቅ እንዲሁ ቁመቱ ረዥም ሆኖ ከሰውነት ጋር የሚጣበቀውን አይነት አለባበስ ማለት እንዳልሆነ ልብ እንበል። እህቶቻችን ሆይ ማስተዋልን ትላበሱ ዘንድ እንለምናችኋለን መሰልጠንና መሰይጠንም ትለዩ ዘንድ ይሁን ሰውነትሽ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነውና ሁሉን በአግባብና በሥርዓት አድርጊለት። ደግሞም ክርስትና ራስ ወዳድነትን አብዝታ ትጠላለች ምንም ነገር ስናደርግ ስለ ሌላው ሰው ልናስብ ያስፈልገናል እኛስ ሰውን ወደ ዝሙት ሊያመራው ስለሚችል አለባበሳችን እጅግ ተጨነቅን ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ በሴቶች ቅጥ ባጣ አለባበስ ምክንያት ወንድማቻችንን ስለማሰናከል ምን ተባለ?

☞☞“መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ወንድሜን እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም።” (1ኛ.ቆሮ 8፡13)

ነገር ግን ለሴት መሸፋፈን ያስፈለገበትን ምክንያት በተመለከተ በእስልምና እና በክርስትና መካከል ሰፊ ልዩነት ያለ ሲሆን ያንን ማወቁን ለአንባቢያን ትቼዋለሁ።

“እንግዳ ልብስ የሚለብሱትንም ሁሉ እቀጣለው።”

(ትን.ሶፎ. 1፡18)

የአስትሪያው ቅን ፕሬዝዳንት እህቶቻችን፣ እናቶቻችን እና ሴት እህቶቻችን የሚለብሱትን ሒጃብ አስመልክቶ ደስ የሚል አስተያየት ሰጥቶ ኢስላምን የሚጠሉ ሰዎችን አሳምሟቸዋል።

☞“እንደ እኔ እምነት ማንም ሴት የፈለገችውን መልበስ ትችላለች።" ብሎ ሚዛናዊ ንግግሩን ጀመረ የአስትሪያው ቻንስለር ክርስትያን ከርን።አስከትሎም "በነገራችን ላይ ማንም ሴት ኒቃብን መልበስ ትችላለች(ሙስሊም ያልሆነች ሴትን ጨምሮ)" ካለ በኋላ ደግሞ "ሁሉም ሴቶች ለሙስሊም እህቶቻቸው ያላቸውን አክብሮት ለማሳየት ሒጃብን ይልበሱ" ሲል ከፍቅር የመነጨ አስተያየቱን አስደምጧል።

የሴት ልጅ የውርስ መብት በእስልምና እና በክርስትና ምን ይመስላል?

የሴት ልጅ የዉርስ መብት በእስልምና :-

ሀ/ ሴት ልጅ ወንድ ልጅ የሚወርሰውን ግማሽ ትወርሳለች፣

ለ/ ሚስት ባሏ ሲሞት አንድ ስምንተኛ የምትወርስ ሊሆን ባል ደግሞ ሚስቱ ስትሞት አንድ አራተኛ ይወርሳል /ይህ ግን ልጆች ከወለዱ ነው::/

ሐ/ ሚስት ባሏ ሲሞት አንድ አራተኛ ትወርሳለች፣ ባል ሚስቱ ስትሞት ደግሞ አንድ ሁለተኛ ይወርሳል /ይህ ደግሞ ልጆች የሌላቸው ከሆነ ነው/

መ/ ሟች ልጆችም ወላጆችም ከሌለው የሟቹ እህት የሟቹ ወንድም ከሚያገኘው ድርሻ በግማሽ ያነሰ ይደርሳታል::

ወንድ የሴቷን እጥፍ እንዲወርስ የተደረገው ገንዘብ ነክ ሃላፊነት ስለተጣለበት ነው::እንደሚታወቀው በእስልምና ሴት ምንም አይነት የገንዘብ ግዴታ የለባትም:: ስለሆነም ለቤተሰቡ ሰርቶ ገንዘብ የማምጣት ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ በወንዱ ትከሻ ላይ ይወድቃል::

አንድ ሴት እስክታገባ ድረስ እርሷን የመቀለብ የማልበስና መጠለያ የመስጠት ግዴታ የሚጣለው በአባቷ ወይም በወንድሟ ላይ ነው: : ካገባች በኃላ ደግሞ ይኸው ግዴታ በባሏ ወይም በልጅ ትከሻ ላይ ይወድቃል::ስለዚህ ወንዱ ማንኛውንም ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን ለቤተሰቡ የማሟላት ግዴታ እንዳለበት እስልምና ያስተምራል ማለት ነው::

እስላማዊ ህግ ወንድ ልጅ ከሴቷ እጥፍ የውርስ ድርሻ እንዲኖረው የደነገገው ይህንን ግዴታውን ይወጣ ዘንድ ነው::

ለምሳሌ አንድ ሰው አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ(150,000) ብር ጥሎ ሞተ እንበል::ይኸው ሰው አንዲት ሴትና አንድ ወንድ ልጅ ቢኖረው ወንዱ መቶ (100,000) ሺህ ሲወርስ ሴቷ ደግሞ ሀምሳ (50,000)ሺ ትወርሳለች ማለት ነው::ስለዚህ ወንዱ ከወረሰው መቶ ሺህ (100,000) ብር ላይ ወንድ ስለሆነ ቀለብ እየሰፈረ ቤተሰቡን ያስተዳድራል:: ያወጣውን አውጥቶ እሱ ጋር ሀያ (20,000) ሺህ ብር ተረፈለት አንበል:: በሌላ በኩል ግን ሴቷ ምንም አይነት የገንዘብ ኃላፊነቶች ስለሌለባት ከወረሰችው ሃምሳ ሺህ (50,000) ብር ላይ አምስት ሳንቲም እንኳን የማውጣት ግዴታ የለባትም::ታዲያ እርስዎ መቶ ሺህ (100,000) ብር ወርሶ ሰማንያ ሺህ ብር (80,000)ብር ማውጣት ይመርጣሉ፣ ወይስ ሃምሳ ሺህ (50,000) ብር ወርሶ ምንም ሳያወጡ እንደለ ማስቀረት? ይህ ነው እስልምና።መልሱን ግን ለህሊናዎ

የሴት ልጅ የመውረስ መብት በክርስትና:-

በክርስትና ወንዶች ልጆች እያሉ ከወንዶቹ ጋራ ሴቶች ልጆች የመውረስ እኩል መብት አላቸው?

ከሰብአዊ መብቶች ውስጥ አንዱ ስለሆነው *ስለውርስ መብት* መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ክርስትና ለሴቶች የሰጠው መፍትሔስ ምንድ ነው?

☞ ከሰብአዊ መብቶች ውስጥ አንዱ ስለሆነው ስለውርስ መብት ባይብል ወይም ክርስትና ለሴቶች የሰጠው መፍትሔ ምንድ ነው? ብለን ስናጤነው ወንድ ካለ ሴቶች እያማራቸው እርማቸውን እንዲያወጡ የሚያደረግ ኢ-ሰብዓዊ የሆነና የሴቶችን የመውረስ መብት ያፈነ ሆኖ እናገኘዋለን። ባይብል የሚያስተምረው ወንድ ልጅ ብቻ የርስት መብት ባለቤት እንደሆነ ነው የሚያስተምረው።

ሴት የምትወርሰው ወንድ ወራሽ ከሌለ ብቻ ነው።ይህ እንዲህ በመፅሀፍ ቅዱስ ታዟል NIV፡-...፤ርስቱም ለወንድ ልጆቹ ብቻ የሚተላለፍ ይሆናል፤የእነርሱም ነው። (ሕዝቅኤል 46:16-18)

አረ ሌላም ተጨማሪ አለ ። ባይብል እንዲህ ይላል፡-

•" ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው። ሰው ቢሞት ወንድ ልጅም ባይኖረው ፥ ርስቱ ለሴት ልጁ ይለፍ፤" (ኦሪት ዘኍልቍ 27:8)

•" ሴት ልጅም ባትኖረው ርስቱን ለወንድሞቹ ስጡ ፤" (ኦሪት ዘኍልቍ 27:9)....

❖ይህ ምዕራፍ እግረ መንገዱን ሚስት፣የሟች እህቶችና የአባቱ እህቶች ስላላቸው የመውረስ መብት ምንም ያስቀመጠው ድርሻ የሌለ ሲሆን ለሴት ልጅም ውርስ የሚተላለፈው ከላይ እንደተጠቀሰው *ወንድ ልጅ ከሌለ ብቻ መሆኑን ያስተምራል።

❖እነዚህን ጥቅስ አስመልክቶ የክርስትና ምሁራን ሲያስረዱ፡-"በተጨማሪም በቤት ውስጥ ወንዶች ልጆች ከሌሉ ርስትን የማውረስ ጉዳይ ለሴት ልጆች እንደሚተላለፍ....የተሰጡ ህግጋትን እናገኛለን።"በማለት እውነታውን በእሸኩርሙሜሽን ገልጸውታል።

=>ቲም ፊሎስ፣የብሉይ ኪዳን የጥናትና መምሪያና ማብራሪያ፣ገጽ 391

❖እንደወም ይህ #ወንድ ልጅ #ከሌለ ብቻ ርስት ለሴት ልጅ የማስተላለፉ ህግ ራሱ የተደነገገው በአምስት እህትማማች ሴቶች ጠያቂነት መሆኑን የክርስትያን ምሁራን ይገልጻሉ።

ምንጭ=>አድነው ተሾመ፣ሕግህ ለእግሬ መብራት፣የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም (አምስቱ የሙሴ መጻህፍት)፤ ክፍል አንድ፣ገጽ167-168)

❖እዚህ ላይ ትኩረት ሊቸረው የሚገባው ነጥብ ባይብል ወንድ ሳይኖር ሲቀር እንዲወርሱ ማድረጉ ሳያንስ እድለኛ ሆነው ወንድ ካልተወለደበት ቤተሰብ የተወለዱ ሴቶች ከቤተሰባቸው ያገኙት ርስት ከነገዳቸው ውጪ ቢያገቡ ርስታቸውን እንደሚያጡ ያትታል፡-

❖እኛ የአዲስ ኪዳን ልጆች ነን የአሮጌው ህግ ተገዢ አይደለንም ለሚሉ አንጃዎች ጉዳዩ ከድጡ ወደማጡ ነው የሚሆንባቸው ምክንያቱም ስለ ኦሪት ህግ ይህን ተብሏልና

☞ “” ከ ኦሪት አንድ ቃል ከምትወድቅ ሰማይና ምድር ቢያልፉ ይቀላል” (ሉቃ 16፡16-17)

☞ኢየሱስም እንዲህ አለ” ህግ እና ነብያትን ልሽር የመጣሁ አይምሰላችሁ…….” (ማት 5፡17-20)

✔በአዲስ ኪዳን እንኳን ለሴቷ ለወንዱም የተቀመጠ የወርስ መብትን የሚያስጠብቅ አንድም መፍትሔ የለም።ምክንያቱም የሰውን ልጅ ተፈጥሮና የሕብረተሰብ ትስስርን ግምት ውስጥ የሚያስገባ ሐይማኖት ሳይሆን "በአንድ ግለሰብና በጌታው መሐከል ብቻ ያለ

ግንኙነት የሚያሳይ የሃይማኖት አድማስ ያለው ስለሆነ ነው። አይ ተሳስተሐል የሚል አካል ካለ ቀጣዮቹን ጥያቄዎች በተጨባጭ ማስረጃ መመለስ ግድ ይላል፡-

❶ጥያቄ፡-ክርስትና ተግባራዊ መፍትሄዎች ያሉት ሐይማኖት ከሆነ ከወንድ ልጆች ጋራ የተወለዱ ሴት እህቶቻችን ውርስ ማግኘት ይችላሉ? ለዚህ ችግርስ ምንስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔ አለው?

❷ጥያቄ፡-ውርስ ቅድሚያ ለወንድ ልጆች ብቻ ከሆነ ለምንድነው አምለክ ለሴት ልጆች ፍታሐዊ ያልሆነው?ለምንስ ይህንን ሰብዓዊ መብቶን ነፈጋትት?

❸ጥያቄ፡- ከሰብአዊ መብቶች ውስጥ አንዱ ስለሆነው *#ስለውርስ መብት* ባይብል ወይም ክርስትና ለሴቶች የሰጠው መፍትሔ ምንድ ነው? በተጨባጭ ለማህበረሰቡ መፍትሔ ከሌላው ለምንድነው በከንቱ የምትዳክሩት?

ሴት ዐዘቅትና የጠበበች ጉድጓድ ናት!!

Km km

ክርስቲያን እህቶቻችንና እናቶች እኔ ይደለሁም እንዲህ በአደባባይ የሞለጭኳቹ ይወክለኛል ማንነቴን ይገልጽልኛ ብላቹ ምድር ሰማዩን ዕምትቧጥጡለት ባይብላቹ ነው በትክክልም ማንነታችሁን የገለፀው።

፡-ባይብል ለሴቶች ምንም ክብር የማይሰጥ ሲሆን፤ ከደንጋይ፣ከሚያንጠባጥብ ቤት፣ከምድረ በዳ፣ከአውሬና ከዱር አራዊት በማመሳሰል ማንነቷን አዋርዶና አንቋሾ ከሰውተራ አስወግዶ ከእንስሳት ጎራ እንዲህ ያስቀምጣችዃል።

፡-•"ከጠበኛ ሴት ጋር በአንድ ቤት ከመቀመጥ በውጪ #በቤት_ማዕዘን_ላይ_መቀመጥ_ይሻላል።"(ምሳሌ፡21:9)

•"ከጠበኛና ከቁጡ ሴት ጋር ከመቀመጥ #በምደረ_በዳ_መቀመጥ_ይሻላል።" (ምሳሌ፡21:19)

•"በዝናብ_ቀን_የሚያንጠባጥብ_ቤትና ጠበኛ ሴት አንድ ናቸው።(ምሳሌ፡27:15)

•"ጠበኛም ሚስት እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ ናት።"(መ.ሲራክ፡19:13)

•"ከደረቅ ሴት ጋራ ከምትኖር ከምድር #አውሬዎችና_ከአንበሶች_ጋር_መኖር_ይሻላል።"(ሲራክ፡25:16)

•" ጋለሞታ ሴት የጠለቀች #ዐዘቅት_ናትና፣ ሌላይቱም ሴት የጠበበች #ጉድጓድ_ናትና። "(ምሳሌ 23:27)

፡-

☞አይ ይህ መጽሐፍ ማንነቴንና ክብሬን አንቋሿል፤ከዱር አራዊት በታች አይደለሁምና ይህ ለ21ክፍለ ዘመን የማይመጥን ሓላ ቀር ባይብል እኔን አይወክልም ለምትሉ እህቶችና እናቶች?መፍትሔው ኢስላም ብቻ ነው፡-

=>>ኢስላም ሰው አንዲትን ሴት ቢጠላ ጥላቻው ወደ መለያየት እንዳያመራ ትዕግስትን ያስተምራል፤ ይመክራል።ይህንን አስመልክቶ

ነብዩ ሙሐመድ (صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ) አንዲት ሴት መጥፎ ባህሪያት ቢኖርባት በድፍኑ መጥላት እንደሌለብንና ሌሎች መልካም ባህሪያቶችዋን መመልከት እንዳለብን አስተምሯል

"አንድ አማኝ ወንድ አንዲት አማኝ ሴትን አይጥላ፤ አንድን ባህሪዋን ቢጠላ ሌላውን ይወደዋልና"(ሙስሊም 2137)

لا يفرك مؤمن مؤمنة إن كره منها خلقا رضي منها آخر (رواه أحمد ومسلم2137)

ሐያሉ አምላካችን አላህ በቁርአን እንዲህ ይመክራል፡-

"...በመልካም ተኑዋኑሩዋቸው፤ ብትጠሏቸውም(ታገሱ) አንዳችን ነገር ልትጠሉ አላህም በርሱ ብዙ ደግ ነገር ሊያደርግ ይችላልና። "(አል-ኒሳዕ፡4:19)

...فَإِنْ كَرِهْتُمُوهُنَّ فَعَسَىٰ أَنْ تَكْرَهُوا شَيْئًا وَيَجْعَلَ اللَّهُ فِيهِ خَيْرًا كَثِيرًا (19)

ኢስላም እንዲህ ዘመናዊና የሴቶችን ስብዕ አልቆ ክብራቸውን ጠብቆ እንዲወደዱ ያስተምራል። እንኳን ቁርአን እንኳንስ ሐዲስ የተኛውም ልብ ወለድ፤ የተኛውም ደራሲ የደረሰው መጽሐፍ ሴት ልጅን ጠባብ ጉድጎድናት፣ ከሷ ይልቅ የዱር አራዊትና አንበሳ ይሻላል፣ አዘቅት ናት ብሎ ያዘቀጣት መጽሐፍ ከባይብል ውጪ አላየሁም ሊኖርም አይችልም።

✍ጥያቄ፡-

--->>ይሔ ነው እንግዲ ለሴት ልጅ ክብር መስጠት?

--->>ሴት ክርስቲያኖች እውነትም የዘቀጣቹ ከልሆናቹ በስተቀር ፤እውነትም ጠባብ ጉርጎድ የሆነ አዕምሮ ከሌላቹ በስተቀር እንዲህ ማንነታችሁን የሚያዘቅጥ፣ ክብራችሁ የሚያዋርድና ለሴት ልጅ ጸር የሆነው የጨለምተኛ መጽሐፍ እንዴት ለኛ ለሴቶች ይሻለናል ትላላችሁ?

✿ ❀ ✿ ~~------->> ✿ ❀ ✿ <<---------~~ ✿ ❀ ✿

8.የመፅሀፍ ቅዱስ ዳሰሳ

መጽሐፍ ቅዱስ እንደተበረዘ እና የአምላክ ቃልነትን የማልቀበልበት ምክንያት

መጽሐፍ ቅዱስ እንደተበረዘ ቁርዓን ሳይነግረኝ በፊት መጽሐፍ ቅዱስን ቢያቀርቡልኝ ኖሮ እንደ አምላክ ቃልነት የማልቀበልበት ምክንያት ከብዙ ጥቂቶቹን ምክንያቶቼን እጅግ በጣም አሳጥሬ ;

1) መጽሃፎቹ የተሰጡት ለባለቤቶቹ አለመሆኑ

ለምሳሌ፡- ኦሪት ዘዳግም 34፡6 (ሙሴ ሞተ ተብሎ ተጽፏል) ኦሪትን ለሙሴ መሰጠት ሲገባው ከሙሴ በኋላ ያለሰው እንደ ፃፈው የሚያሳይ ነው ፣ ወንጌል ለእየሱስ መሰጠት ሲገባው እየሱስ ካረገ በኋላ የተፃፉ ወንጌሎች ናቸው::እንዳውም እየሱስን አይቶትም ሰምቶትም በማያውቀው ሉቃስ (ሉቃስ 1፡1) ፣እየሱስን አይቶት በማያውቀው እንዳውም አማኞችን ለመግደል ሲያሳድድ/ሲፈልግ በነበረው ጳውሎስ (የሀዋሪያት ስራ 9፡1 ጀምሮ) ከ39ኙ የአዲስ ኪዳን መፃህፍት 14ቱ በጳውሎስ የተፃፉ ደብዳቤዎች ናቸው::

2) በተለያዩ ጊዜ የታተሙና የተተረጎሙ መጽሀፍ ቅዱሶች የጥቅሶች መቀነስና መጨመር

ለምሳሌ፡- በ1950ዎቹና 60ዎቹ የታተሙት መጽሀፍ ቅዱሶች ላይ ኦሪት ዘፍጥረት 23፡1 ላይ "ቁላው የተቀጠቀጠ፤ብልቱም የተቆረጠ…" ከሚለው አንቀጽ በ1980 በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ "ቁላው የተቀጠቀጠ" የሚለው ሃረግ እንዲወጣ ተደርጓል::በተጨማሪም ዘፍጥረት 18፡20 ላይ "…እንዲሁም ባይሆን አውቀዋለሁ" የሚለው እንዲወጣ ተደርጓል::ሌሎችም በርካታ የቁጥር ልዩነቶች አሉት

3) ለአምላክ የማይገቡ ባህሪያትን በመያዙ

ለምሳሌ፡-ኦ.ዘፍጥረት 32፡24-30-(ያቆብ እግዛብሔርን ታግሎ አሸነፈ)፣ትንቢተ ኢሳያስ 7፡20 "በዚያን ቀን እግዛብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉስ የራሱንና የእግሩን ፀጉር ይላጨዋል፤…"፣ ት.ኢሳያስ 54፡4-5,ት.ህዝቅኤል 16፡ከ1 ጀምሮ በተለይ ቁጥር 8ና ት.ህዝቅዔል 23፡1 ጀምሮ በተለይ ቁጥር 4 (እግዛብሔር ሚስት አግብቶ እንደወለደ ይገልፃል)፣

መዝ 73፡20,መዝ 44፡23ና መዝ 78፡65 "እግዛብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሳ፤የወይን ስካር እንደተወወው እንደ ሃያልም ሰው ሆነ::"፣1 ሳሙ 15፡35 ና ኦሪት ዘፍጥረት 6፡6 "እግዛብሔር ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ"፣

ኦ.ዘፍ 2፡2-3,ኦ.ዘጸ 20፡11ና ኦ.ዘጸ 31፡17 " ፣ ዘጸዐት 31፡17 "እግዚአብሔር… ከስራው ስላረፈና ስለተነፈሰ፤"ሌሎችም

4) ፍትህ ያልተሞላበት ፍርድ በመስጠቱ

ለምሳሌ፡-ኦሪት ዘዳግም 23፡1-3 "ቁላው የተቀጠቀጠ….::ዲቃላ …..እስከ አስር ትውልድ ድረስ ወደ እግዛብሔር ጉባዔ አይግባ:: "-›ኦሪት ዘፍ 38፡24-30 (ፋሬስ ዲቃላ ነው)--› ማቴ 1፡3-8 (ዳዊትና ሰለሞን የዲቃላው ፋሬስ ትውልድ 9ኛና 10ኛ ትውልድ ናቸው::) ፣ 2ኛ ሳሙኤል 12፡15 (ዳዊት የወለደውን ዲቃላ ቀሰፈው)፣ መ.መሳፍንት 14፡5-9 (የእግዛብሔር መንፈስ ቁማር ተጫወተ)፣…ሌሎችም

5) አስፀያፊና የተምታታቱ ነገሮች በውስጡ መያዙ

ምሳሌ፡- 2ኛ መ.ነገስት 18፡27ና ት.ህዝቅዔል 4፡9-13 (የሰው ፋንድያ (ኩስ) ለምግብነት)::2ኛ ዜና 21፡16-20 ና 22 ፡1-2 (ልጅ አባቱን በሁለት አመት ይበልጠዋል::)፣ት.ህዝቅዔል 23፡20…..ሌሎችም

6) የግለሰብና የሰላምታ ደብዳቤዎችን በውስጡ በመያዙ

ምሳሌ፡-ሉቃስ 1፡1 ጀምሮ “የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ…“፣1ኛ ጢሞቲዎስ 4፡9 ፣ የሀዋ 15፡23 ,ሮሜ 16 ፡ 3-23 ,2ኛ ቆሮንጦስ 13፡13 ,ፊልጵስ 4፡21-22 , ቆላስያስ 4፡10-18 … (ሰላምታ አቅርቡልኝ፣ ሰላም ብለዋችኋል፣…)፣1ኛ ቆሮንጦስ 16፡21 “እኔ ጳውሎስ ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ ጽፌዋለሁ፡፡“

7) ነብያቶችን (የአምላክ መልዕክተኞችን) አርዓያ መሆናቸው ቀርቶ የመጥፎ ስራ ሰሪዎች ቁንጮ ማድረጉ

ምሳሌ፡-2ኛ መ.ሳሙ 11፡2-27(ዳዊት ኦሪዮን እንዲገደል አድርጎ ሚስቱን ቀምቶ ዝሙት ፈጸመ፡፡) ፣ኦ.ዘጸዓት 32፡2-4(አሮን ለአምልኮ ጣዖት ሰራ፡፡) ፣ 1ኛ መ.ሳሙ 18፡24-27 (ዳዊት የሳዖልን ልጅ ለማግባት ለጥሎሽ 100 ወንዶችን ገድሎ ሸለፈታቸውን ‹ሰለባቸውን› ለሳዖል በጥሎሽ ቆጥሮ አስረከበው፡፡) ፣ መ.መሳፍንት 16፡1-3 (ሶምሶን ዝሙተኛ ነው) ፣ኦሪት ዘፍጥረት 19፡30-38 (ሎጥ በልጆቹ ላይ ዝሙት ፈፀመ ልጆቹም ፀነሱ፡፡)፣መ.መሳፍንት 15፡1-5 (ሳምሶን ሚስቱ ሚዜውን ስላገባች ተናዶ ለበቀል የሃገሩን እህል አቃጠለው፡፡)…..ሌሎችም

8) የዝሙት ማባባበያና የወሲብ ስሜት ቀስቃሽ ጽሁፎችን በውስጡ ስለያዘ

ለምሳሌ፡-መሀልየ መሀልይ ዘሰለሞን 1፡1 ጀምሮ “…በአፉ መሳምን ይሳመኝ፤….ዘይትህ መልካም መዓዛ አለው፤….ስለዚህ ደናግሎች ወደዱህ፡፡…..ወዴ ለእኔ በጡቶቼ መካከል እንደሚያርፍ እንደተቋጠረ ከርቤ ነው፡፡“ ፣ መ.መ.ዘሰለሞን 3፡1 ጀምሮ “…ሌሊት በምንጣፌ ላይ ነፍሴ የወደደችውን ፈለግኩት፤ፈለግኩት አላገኘሁትም፡፡“ ፣መሀ.መ.ዘሰለሞን 7፡1 ጀምሮ “…እግሮችሽ በጫማ ውስጥ እንዴት ውቦች ናቸው፡፡ዳሌዎችሽ በአንጥረኛ እጅ እንደተሰሩ እንደ እንቁዎች ይመስላሉ፡፡እንብርትሽ የወይን ጠጅ እንደማይጎድልበት እንደ ተነጠጠ ጽዋ ነው፡፡…ሁለቱ ጡቶችሽ እንደ ሁለቱ መንታ ሚዳቋ ግልገሎች ናቸው፡፡…ወዳጄ ሆይ እንዴት የተዋብሽ ነሽ! … ጡቶችሽም የወይን ዘለላ ይመስላሉ፡፡ውዴ ሆይ፡- ና ወደ መስክ እንውጣ በመንደሮችም እንደር፡፡ወደ ወይኑ ቦታ ማልደን እንሂድ….በዚያ ውዴን እሰጥሃለሁ፡፡.ውዴ ሆይ፡- ሁሉን ላንተ ጠበቅሁልህ፡“…..ሌሎችም

9) እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ሃሳቦችን በመያዙ (በሺዎች የሚቆጠሩ)

ለምሳሌ፡-ስለ እግዛብሔር መኖሪያ 1ኛ ነገስት 8፡12-13 ና 2ኛ ዜና 6፡1“ሰለሞንም፡፡እግዚአብሔር፡-በጨለማ ውስጥ እኖራለሁ ብሏል፡፡“ እንዲሁም በ1ኛ ጢሞ 6፡16 ና 1ኛ ዩሐንስ 1፡5 “እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፡፡አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤…“ ፣ ስለ ይሁዳ አማሚትና መሬቱን ማን ገዛ? ማቴ 27፡3-8 “ብሩን በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ፡፡…የሸክላ ሰሪውን መሬት ለእንግዶች መቃንር ገዙበት፡፡“ ና ሀዋ ስራ 1፡19 “ይህ ሰው(ይሁዳ) በአመጽ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ፡፡“ ፣ ከእየሱስ ጋር ስለተሰቀሉት 2ቱ ሰዎች እየሱስን የነቀፈው/የነቀፉት ሉቃስ 23፡39 (እየሱስን አንዱ ነቀፈው አንዱ ደገፈው) ና ማርቆስ 15፡32 (ሁለቱም ነቀፉት)…….ሌሎችም

10) ያልተፈፀሙ ትንቢቶች መኖራቸው

ለምሳሌ፡- በማቴዎስ ወንጌል 12፡40 “ዮናስ በአሳ አንባሪ ሆድ ውስጥ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት እንደነበረ፤እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ይኖራል፡፡“ ከሜርብ ማታ እስከ እሁድ ማለዳ--› 3ቀን ሲደመር 3 ሊሊት እኩል አይሆንም ≠ 1ቀን ሲደመር 2 ሌሊት…….ሌሎችም

1.ልጇን ቀቅላ የበላች እናት መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ6፡26-29

2.ባሏ ስለሞተባት ሴት ወንድሙን ታግባ፤በስሙይጠራ፤እንቢካለ ፊቱ ላይትትፋ ኦሪት ዘዳግም25፡5-10

3.በልጁ ላይ ዝሙት ሉጥ (ኦሪት ዘፍጥ 19.30-38 (ይሁዳ ኦሪት ዘፍጥ 38.15-24)

4.እግዚአብሔር በግብጽ ወንዝ ዳርቻ ያለውን ዝምብ በአሦርም አገር ያለውን ንብ በፉጨት ይጠራል። ትንቢተ ኢሳይያስ 7:18

5.ዝሙት አንደ መብት (ኦሪት ዘፍጥ 35.22 & 49.4)

6.ሶስት አመት በራቁቱ የሄደ ነብይ ትንቢተ ኢሳያስ 20፡1-3

7.ለጸሎት የጥጃ ምስል ጣኦት የሰራ ነብይ አሮን (ኦሪት ዘጽአት 32.2-4)

8.የግል ደብዳቤ እኔ ጋር እንድትመጣ፤የስቀመጥኩትን አምጣልኝ.. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ 4፡9-13

9.የ 100 ሰዎች ሞት ለዳዊት ጥሎሽ (መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 18:25-27)

10.በባሎቻቸው ስለሚጠረጠሩ ሴቶች የተሰጠ የመመርመሪያ ዘዴ ኦሪት ዘኁልቁ 5፡12-25 (1980 የተሻለ)

11.የማይሰራበት ጥቅስ ከግብረስጋ ግንኙነት ቡኃላ (ኦሪት ዘሌዋውያን 15.16-18)

12.ስካር በእርቃን (ኖህ፤ዳዊት..) (ኦሪት ዘፍጥ 9.20-25) (1 ኛ መጽ ሳሙኤል 19:23-34)

13.በዚያም ቀን ግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጕር ይላጨዋል ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላል ትንቢተ ኢሳይያስ 7:20

14. እግዚአብሔር ሚስት አላውን ? (ትንቢተ ህዝቄኤል 16: 1-5 & 23.1-5) ትንቢተ ኢሳያስ 54፡5

15.እንደዚህ ታምኜ ስመካ የምናገረው፥ በሞኝነት እንጂ ጌታ እንዳዘዘኝ አልናገርም።2ኛ ቆሮንቶስ 11:17

16.‹…ከእናንተ ጋር ኾሳቸውን ይበሉ ዘንድ ሸንታቸውንም ይጠጡ ዘንድ..›መጽ ነገሥት ካልዕ 18:27

17. ሥጋቸውም እንደ አህዮች ሥጋ ዘራቸውም እንደ ፈረሶች ዘር የሆነውን… ትንቢተ ሕዝቅኤል 23:20

18 ‹…ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም› ወደ ዕብራውያን 12:8

19. የጳውሎስ ዘረኝነት ፡‹እኛ በፍጥረት አይሁድ ነን ኃጢአተኞችም የሆኑ አሕዛብ አይደለንም፤ ገላቲያ 2፡15

20‹ቍላው የተቀጠቀጠ ብልቱም የተቈረጠ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ።ኦሪት ዘዳግም 23፡1

21. ሙሴ ኦሪትን ጽፎዋል? መሞቱን አንዴት ሊጽፍ ቻለ‹.. በዚያ በሞዓብ ምድር ሞተ። ዘዳግም 34፡5

ማኅበረ ቅዱሳን ወይስ ማኅበረ ሰይጣን

(አዲስ መጽሐፍ ከዲያቆን ሙሉጌታ ወልደ ገብርኤል)

ለሞት እንዳልተኛ ዓይኖቼን አብራ! መጽሐፉ ምንም እንኳን የዛሬ አንድ ዓመት ከሦስት ወራት በፊት ሙሉ ዝግጅቱ ተጠናቅቆ ወደ ማተሚያ ቤት አምርቶ የነበረ ቢሆንም በአንዳንድ ምክንያቶች የሕትመት ሂደቱ ተቋርጦ አንዲዘገይ ግድ ብለዋል። በዚህ ቆይታ መካከል መጽሐፉ በአራት የሥነ መልኮት መምህራን፣ የሥነ ጽሑፍና የህግ ባለ ሞያዎች እንዲታይና እንዲገመገም ዕድል ፈጥሯል። መጽሐፉ በይዘቱ 262 ገጽ ሲኖረው በርካታ ጥልቀት ያላቸውን ርዕሰ ጉዳዮች አንሥቶ የሚያትትና የሚያብራራ ነው።ከሞላ ጎደል በእያንዳንዱ ምዕራፍ የመጀመሪያ ገጽም የምዕራፉን አጠቃላይ ይዘት በዐጭሩ ያስቃኛል። በህትመት ረገድም በከፍተኛ ይዘትና የህትመት ጥራት በምእራቡ ዓለም የህትመት ደረጃ በላቀ ጥራት በአሜሪካን አገር ቺካጎ ከተማ በሚገኘው ትልቁ የህትመት ድርጅት የታተመ ሲሆን እስከ ድህረ ሞት ቅዱስፓትሪያሪክ ጳውሎስ ያለውን የማኅበሩ መሰሪ እንቅስቃሴ አካቶ በብዙ ተግዳሮትና ፈተናዎች አልፎ በዛሬው ዕለት ለንባብ መብቃቱን ይፋ ሳደርግ በታላቅ ደስታ ነው።

መጽሐፉ የማኅበሩ (ማኅበረ ቅዱሳን) ከአስመራ እስከ ደቡብ አሜሪካ የዘረጋውን የልዩ ተልእኮ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ጨምሮ በዋናነት አስራ ሦስት ዓበይት ርዕሰ ጉዳዮችን አንስቶ ይዳስሳል።

በተጨማሪም መጽሐፉ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ ከአህጉረ ስብከቶች እንዲሁም ከካህናት ጉባኤና ሊቃና ጳጳሳት "የሕግ ያለህ!" ሲሉ በማኅበረ ቅድሳን ላይ በጥብቅ የተጻፉትን ማኅበሩ የሞት ሽረት ትግል ታግሎ ከመዝግብ ቤት እንዲወጡና ደብዛቸው እንዲጠፉ ያደረጋቸው ለሰሚ ጆሮ ጭው የሚያደርጉ ልብ የሚሰብሩ የስምታና የዋይታ ደብዳቤዎች ከጸሐፊው ሰፊና የላቀ ትንተና ይዟል። ብጽእ አቡነ መልከ ጸዲቅ - "እኔ ለሕዝብ የማስተላልፈው መልእክት፣ ይህ በስም የተሸፈነ ማኅበር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ከሥሯ መንግሎ የሚጥላት ከባድ ጠላት መሆኑን ዐውቆ ዐወቅንብህ!

የጥፋት ተልእኮህንም ዐውቀንብሃልና ከእኔ ራቅ እንዲለው ያስፈልጋል። ሊወገድ ይገባል!" ሲሉ ስመ ጥሩ የወንጌል አርበኛው አባ ወልደ ትንሳኤም -

"የሃይማኖት ካባ ለብሶ በረቀቀ ሁኔታ የግል ጥቅሙን የሚያሳድድ: በመግደል እግዚአብሔርን አስደስታለሁ ብሎ የሚያምን"በማለት በልዩ መልኩ ከመጽሐፉ አዘጋጅ ጋር ባደረጉት ቆይታ ጆሮ ያለው መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት! ሲሉ ተማጽኖዋል።

የሌሎች ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የምህጽንታ ሙሉ ቃልም በመጽሐፉ ያገኙታል:: ይህ መጽሐፍ አስቀድሞ ከፊታችን አደጋ እንዳለ ጠቋሚ በመሆን እንዲያገለግልና ክፉው ቀን እንደ ወጥመድ ሳይደርስብን ዛሬ ላይ የዳኛ ያለህ!

የትድግና ያለህ! ብሎ የዜግነት ኀላፊነቱን ለመወጣት እግዚአብሔር በሰጠው መንፈሳዊ ዐደራም የራሱን ድርሻ ለማበርከት ጥረት ከሚያደርግ አንድ ኢትዮጵያዊ የተበረከተ ለኢትዮጵያና ለቤተ ክርስቲያን እድገት ሰላም፣ ለኢትዮጵያውያን አንድነት፣ ፍቅርና እኩልነት ከሚቆረቆር ሰው የተሰጠ በመሥዋዕትነት የቀረበ በረከት ነው::

መንግሥትና ሕግ ባለበት ሀገር ሕጋዊ የሚያስመስል ጭንብል ለብሶ፣ ሕጋዊ እንድሆን ፈቃድ ሰጥቶኛል ለሚለው አካል እንኳ የማይገዛ፣ በሀገሪቱ ዘመናዊ ትምህርታቸውን በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚከታተሉ የአገር ተስፋ የሆኑ ዜጎችን ያለከልካይ እየመለመለ ለከፉ ዓላማው በማደራጀት ከቤተ ክርስቲያን አልፎ ለመንግሥትና ለሀገር ሥጋት የሆነ በልዩ ልዩ ሕገወጥ በሆኑ መንገዶች ከሀገር ውስጥና ከውጪው ዓለም የሚሰበስበውን፣ ከፍተኛ ገንዘብ ለምን, ዓላማ እያዋለው እንደሆነ፣ ለማንም ሊታወቅ ባልተፈለገ ሁኔታ፣ ተጠያቂነት በሌለበት ለ20 ዓመታት ኡዲት ሳይደረግ የሚንቀሳቀስ ተቋም በኢትዮጵያ መኖሩ ይደንቃል:: ያውም በማኅበሩ ሰይጣናዊ ሥራ ስማቸው የጠፋ፣ ከአገልግሎትና ከሥራ የተፈናቀሉ፣ የተደበደቡና የተሰደዱ፣ የተደፈሩና የተገደሉ … ብዙ ንጹሐን ዜጎች የፍትሕ ያለህ!! የትድግና ያለህ!! እያሉ ከፍተኛ ጩኸት እያሰሙ አቤት የሚል የዜጎችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚያስከብር መታጣቱ ይገርማል!!!

እኔ ከጅምሩ መንፈሳዊ ዓላማን አንግቦ መንፈሳዊ ሆኖ ለመሥራት አስቦ እንዳልተነሣ ከቁጥር አንድ ጀምሮ በጻፍኳቸው መጻሕፎቼ ለመግለጽ ሞክሬያለሁ::

አዎ እየሱስ ሰው ነው። የራስዋ አሮባት የሰው ታማስላለች ወገኔ የራስህ መጻፍ ቅዱስ ነው እየሱስ ሰው መሆኑን የሚነግርህ ኢየሱስ በተደጋጋሚ ለአምላኩ ሲፀልይ ነበር:: ይህም በማቴ.26:39፤ ማቴ.26:42፤ ማቴ.26:44፤ ማርቆስ 14:35 ማርቆስ 1:35 ማርቆስ 14:39፤ ሉቃስ 5:16፤ ሉቃስ 6:12 ፤ ዮሐንስ 17:1-3፤ እና ዕብራዊያን 5:7 ላይ ተገልጻል ::

ኢየሱስና አምላክ እኩል ቢሆኑ ኖሮ እየሱስ ለአምላኩ ጸለየን? አምላክ የሚጸለይለት ሌላ አምላክ አለውን? ይፀልያልን ? ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ለማን ነው ልመናን ያቀረበው ?

“አምላክ ከሆነ ለራሱ ነው ልመናውን ያቀረበው ማለት ነውን ? ተላኪውን (እየሱስ) እና ዕውነታው በራሱ እንደበት ባይብል

1.ትምህርቱ ከራሱ እይደለም

‹ ለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው:- ☞ ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም፤› ዩሐ 7:16 ላኪና ተላኪ ?

2. ኢየሱስ ማንነቱ እራሱ በአንደበቱ ሲገልጽ

☞ ((ነቢይ)) ነኝ ብሏል ‹ዳሩ ግን ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ አይገባውምና ዛሬና ነገ ከነገ በስቲያም ልሄድ ያስፈልገኛልና።›ሉቃስ 13:33

‹ኢየሱስ ግን:- ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው። ›ማቴ 13:57

3. ኢየሱስ አምላክ አላው (ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ) ‹ኢየሱስም:- ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና

አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ። እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ 0አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት።›› ዩሐ 20:17

☞‹‹እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት። (የዮሐንስ ወንጌል 17:3)

4. ኢየሱስ ለፈጠረው አምላኩ ይጸልይ ነበር

☞‹‹ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ።..› [ማቴ 26:39]

5. የተላከው ኢየሱስ

‹‹እርሱም መልሶ፡- ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ። [ማቴ 15፡24]

6. ኢየሱስ ሰው ነው።

‹የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳቸሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ #ሰው ነበረ፤› የሐዋሪያስራ 2፡22

7. ኢየሱስ ከራሱ ምንም ማድረግ አይችልም።

☞‹እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።› [ዩሐንስ ወንጌል 5፡30]

☞‹ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡- የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው።›

[ዩሐ 4፡34] ታዲያ ለምን ይሆን የተላከ መልክተኛ (ረሱል) ነው ማለታችን መወገዙ ?

8. ኢየሱስ መጀመሪያ ያስተማረው ትዕዛዝ

☞‹ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥

[ማር 12፡29]

-->አዎ የሱ የኛም የጋራ አምላክ ‹‹አምላካችን›› ማለቱ ለዚያ ነው

9. ኢየሱስ ዕውቀቱ ከአምላክ ጋር ይነጻጸር ይሆን?

☞‹ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም። › [ማር 13፡32]

10. ኢየሱስ ለማን መሰገድ አንዳለበት ሲያስተምር

☞‹ኢየሱስም መልሶ፡- ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል አለው። ›(ሉቃስ 4፡8)

9.እስልምና

"ኢስላም ማለት ምን ማለት ነው?

"ኢስላም ማለት የአላህ አንድነትን በማወቅና በማመን ለርሱ እጅ መስጠት ለፍላጎቱና ትዕዛዛቱ ማደር ተግባራዊ ለማድረግም በታዛዥነት መንፈስ መንቀሳቀስ ከሽርክ(በአምልኮ ሌላን አካል ከርሱ ጋር ከማጋራት)መጽዳት ነው።

አላህ እንዲህ ይለናል፡- እንደውም፤ እርሱ በጎ ሰሪ ሆኖ ፊቱን ለአላህ የሰጠ (ፍጹም ታዛዥ የሆነ) ሰው ለርሱ በጌታው ዘንድ ምንዳው አለው (በእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎችም) በነሱም ላይ ፍርሃት የለባቸውም እነሱም አያዝኑም'' ይለናል፡፡ (2:112) ይህም አላህ(ሱብሃነሁ ወተዓላ)ያዘዛቸውን ነገሮች በመፈጸምና የከለከላቸውን ደግሞ በመራቅ ይረጋገጣል።

☞ኢስላም የሚለው ጥሬ ቃል'3' ትርጉሞችን ያዘለ ሆኖ እናገኘዋለን። እነሱም፡-

- " ከግልጽ ወይም ስውር ከሆኑ ጉድለቶች ፍጹም ነጻ የመሆን እና የመጥራት
- "እርቅ እና እርጋታ
- "ሰሚነት እና ቅን ታዛዥነት የሚለውን ትርጉም አዝሎ ይገኛል ።

ኢስላም ደግሞ ትእዛዛቱን እና አምልኮዎቹን በተመለከተ በቁርአንና በሃዲስ በግልፅ የተጠቀሰ ነው፡፡ ትክክለኛው እምነት ኢስላም ስለመሆኑ አላህም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ብቸኛና እውነተኛ ሃይማኖት ነው። አላህ (بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ) እንዲህ በማለት ገልፆልናል፡-

“አላህ ዘንድ(የተወደደ)ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው።” (አሊ-ዒምራን 3፤91)

በእስልምና ከአላህ ሌላ ያለን ነብይም ሆነ ወልይን መጥራትና መለመን አይቻልም። ምክንያቱም ሁሉንም ነገር ማድረግ የሚችለው አላህ ብቻ ነውና! ከሱ ሌላ ያሉት ግን ሙታኖች ናቸው፡፡ ለዚህ ማስረጃ አላህ(بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ)እንዲህ ይለናል፡-

“እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትጠሯቸው ምንንም አይፈጥሩም፤ እነሱ ግን ይፈጠራሉ፤ ህያው ያልሆኑ ሙታን ናቸው፤ መቼም እንደሚቀሰቀሱ አያውቁም” ይለናል፡፡(16:20)

ነብዩም ሙሀመድ (ﷺ)እሳቸውም የነብዮች መቋጫ ሲሆኑ ከሳቸው ቀጥሎ የሚመጣ ነብይም ሆነ መልዕክተኛ(ረሱል) አይኖርም፡፡ ይህን አስመልክቶ አላህ(بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ)እንዲህ ይላል፡-

“ሙሀመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም ግን የአላህ ምልዕክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው። (33:40)

ስለዚህ ከአሁን በኋላ መለኮታዊ ትእዛዛ ሊያስተላልፍን የሚችል አንድም ነብይ መልዕክተኛ አይመጣምና የእርሳቸው ፈልግ(ሱና)በመከተል ፅኑ አቋም ሊኖረን ይገባል።

ነብዩ (ﷺ)መጀመሪያ ጥሪ ሲያደርጉ ህዝቡን የተጣሩት ወደ ተውሂድ ነው፡፡ ይህም"ላ ኢላሃ ኢለላህ"ሲሆን ፍቺው "ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም ማለት ነው፡፡ አንድ ሙስሊም "ላ ኢላህ ኢለላህ" ካለ አላህን በብቸኝነት ሊያመልክ ከሱ ውጪ ማንንም ምንንም ላይገዛ ቃል ገብቷል እንደማለት ነው፡፡ ከአላህ ውጪ ያለው በጠቅላላ አምልኮ የማይገባው የሃሰት አማልክት መሆኑን አውቆ ከማምለክ መቆጠብ ይኖርበታል፡፡

አላህ በሰማይም ሆነ በምድር ብቻውን የሚመለክ እውነተኛ አምላክ መሆኑ ሲገልፅ እንዲህ ይለናል፦

"እርሱም ያ በሰማይ ውስጥ ሊገዙት የሚገባው፣ በምድርም ውስጥ ሊገዙት የሚገባው አምላክ ነው፤ እርሱም ብልሀተኛው ዐዋቂው ነው።"(43: 84)

አላህም እሱን ብቻ(ዱዓ እንዲያደርጉ) እንዲለምኑና በዘመናቸው በኢጋሪዎች ይደረግ ከነበረው በተለየ አላህን ሲለምኑ ከአላህ ጋር ሌላን ማንንም እንዳይጠሩና እንዳያጋሩ አዟቸዋል፡፡

አላህ (بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ) እንዲህ ይላል ፦ ‘‘እኔ የምለምነው ጌታዬን ብቻ ነው በሱም አንድንም አላጋራም በላቸው’’(72:40)

ነብያችን (ﷺ)በሀዲሳቸው ላይ (‘‘ዱዓ (ልመና)ሚባዳ(አምልኮ) ነው’’) ብለዋል፡፡ ማነኛውም ሰው ሲለምን(ዱዓ ሲያደርግ) አላህን ብቻ ሊጠራና ሊለምን ይገባዋል፡፡

ብዙ የሀገራችን ክርስቲያኖች እስራኤል (አይሁዶች) የሙስሊሞች ጠላት የክርስቲያኖች ደግሞ ወዳጅ አድርገው ያስባሉን ፣ ነገር ግን እውነታው በተቃራኒው ነው። አይሁዶች ሙስሊሞችን ከሚጠሉት በላይ ክርስትያኖችን ይጠላሉ፣ እስራኤሎች(አይሁዶች) ኢየሱስን በዝሙት የተወለደ ብለው ነው ሚያምኑት፣ ለዛም ነው ያሰቃዩት፣የገረፉት፣የገደሉት፣የሰቀሉት(እንደ ክርስትና እምነት) ማሪያምን ደግሞ ዝሙተኛ፣ሴሰኛ፣ ዲቃላ ወልዳ መጣች ብለው ነው የሚከሷት፣ከማህበረሰቡም ያገለሏት እነዚሁ አይሁድ እስራኤላውያን ናቸው።

እስራኤሎች ከነቢዩ ሙሴ ውጪ ኢየሱስም ሆነ ሙሀመድ(ሰዐወ) አልተላኩም፣ አናቃቸውም ብለው ነው ሚያምኑት።

እስራኤሎች በሙስሊሞች ጉዳይ ቢዚ ሆና ነውንጂ የክርስትና እምነት ከስሩ ነቅላ ከመጣል ወደኋላ እንደማትል የታወቀ ነገር ነው። እስራኤላውያን የተረገሙና፣ የተጣመሙ በኃጢዓታቸው ወሰን ያለፉ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ለምን እስራኤላዊ ነብይ ? –ስለ እስራኤላዊ የተናገሩ በቂ ምክንያቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ከትንቢት ሕዝቄል፡ ዘካሪያስና ሚልክያስ በሚገባ ተቀምጠዋል እስራኤል ማለት እግዚአብሔርን የካደ ሕዝብ ነውና፡፡

1/ ለምሳሌ ትንቢት ሚልክያስ 1: 11 እግዚአብሔር ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያው ድረስ ስሜ ከአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናል፡፡

2/ ሚልክያስ 1: 5-6 እናንተም እግዚአብሔር በእስራኤል ዳርቻ ወዲያ ታላቅ ይሆን ትላላችሁ እናንተ ስሙን የምታቃልሉ ካህናት ሆይ!

3/ ሚልክያስ 1:14 ስሜ በአሕዛብ ዘንድ የተፈራ ነውና ይላል። እግዚአብሔር

4/ ኢርሚያስ 2: 30 ሰይፋችሁ እንደሚሰብር አንበሳ ነብያቶቻችሁን በልቷል ትውልድ ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ።

5/ ኤርሚያስ 33: 17 በእስራኤል ቤት ዙፋን ላይ የሚቀመጥ ሰው ከዳዊት ዘንድ አይታጣም።

6/ ሆሲህ 9:1 እስራኤል ሆይ ከአምላክ ተለይተህ አመንዝረሃልና እንደአሕዛብ ደስ አይበልህ።

ይህ የሚያስረዳው አሕዛብ ከእግዚአብሔር መንገድ አልጠፋም ማለት ነው። እስራኤል ግን የጠፋ ሕዝብ በመሆኑ ከጥፋት ይገሰጽ ዘንድ እየሱስ ተላከባቸው ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ፍሬ ሀሳቦች በመጠኑም ቢሆን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መልዕክት ለእስራኤል ወገን ብቻ መላክ እንዲሁም ደግሞ እስራኤላውያን የተረገሙና በኃጢዓታቸው ወሰን ያለፉ በዓለም ላይ ካሉት ሕዝቦች የተጣመሙ በተዓምራዊ

አፈጣጠር ተፈጥሮ ኢየሱስ ቢላክባቸውም ፡ የኢየሱስን ነብይነት ያልተቀበሉ መሆናቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል።ይህ በመሆኑም እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝቦች ፊቱን በማዞር ቃል ኪዳኑን ከእስማኤላዊ ዝርያ ጋር ለማድረግ በመወሰኑ ነብዩ መሀመድ (ሰ,ዐ ,ወ) ከአረቡ ምድር ሊነሱ ችለዋል።

ይህንኑ የሚያረጋግጡ መልዕክቶችና ጥቅሶችን ወደ ፊት በዚህ ፅሑፍ ውስጥ በስፋት የምንመለከት ሆኖ አሁን እስራኤላውያን በአላህ ፊት ምን እንደሚመስሉ ማወቅ ጠቃሚ ስለ ሆነ ይህንኑ እንመልከት ።

ትንበተ ኤርሚያስ 31: 36- 37 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ይህ ሕግ ከበፊቴ ቢወገድ ይላል እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ ደግሞ የእስራኤል ዘር በፊቴ ሕዝብ እንዳይሆን ለዘላለም ይቀራል። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ሰማይ በላይ ቢከነዳ የምድርም መሠረት በታች ቢመረመር በዚያን ጊዜ ስላደረጉት ነገር ሁሉ የእስራኤልን ዘር ሁሉ እጥላለሁ።

እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ከእስማኤላውያን ጋር በሚጀመርበት ጊዜ እስራኤላውያን የነብዩ ኢሳንና የነብዩ መሀመድ (ሰ,ዐ,ወ) መልዕክቶች ተራ በተራ ስላልተቀበሉ ቀጥሎ የአላህ ሕግ ነብያቶችን መሀመድ (ሰ,ዐ,ወ) ከተላኩበት ጊዜ ጀምሮ እስከዘላለም ይቆያል

ማለት ነው።

እስራኤል ግን ዛሬም የሁለቱንም ነብያት መልዕክቶች ያልተቀበለ ሕዝብ በመሆኑ ለዘለዓለም የተጠላ ሕዝብ በመሆን በግልጽ ያስረዳል። በትንቢቱን ተግባራዊነት በእስራኤል የሁለት ነብያትን መልዕክት አለመቀበል ይፋ ያደርገዋል።

የማቲዎስ ወንጌል 21:42 ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እሱ የማዕዘን ራስ ሆነ ይህ ከጌታ ዘንድ ሆነ ለዓይናችንም ድንቅ ነው የሚለውን ከቶ ከመጽሐፍ አላነበባችሁምን ? ስለዚህ እላችኋለሁኝ የእግዚአብሔር መንግስት ከናንተ ትወሰዳለች፡፡ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች በዚህም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ይቀጠቀጣል፡፡

ይህም የሚያመለክተው የእግዚአብሔር መንግስት ከእስራኤል ልጅ ተወስዶ ፍሬዋን ለሚያደርግ ለአረብ ለእስማኤላውያን ወገን) እንደሚሰጥ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ተገቢውን ትኩረት የሚሻ ጉዳይ በመሆኑ ክርስቲያን ወገኖቻችን በሞት ከመያዛቸው በፊት በታቻለ መጠን ጥናታቸውን ማስተካከል አለባቸው።

አንዳንድ ሰባኪዎች ስብከታቸውን ሲያቀርቡ እራሱን እስራኤል አድርጎ ያመነ ሰው በሙሉ መንፈሳዊ እስራኤል ሆኗል በማለት ነው፡፡ ዘሩ በሙሉ የተጣለ ለዘለዓለም የማይድን ከሆነ ወደ መንፈሳዊ እስራኤል የመለወጥ ትርፉ ምንድነው?

እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ምን ጊዜም አልታረቅም እስከዘላለም ድረስ እጣላለሁ እያለ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲያስተምር የእስላም ትምህርትን ለመማር ልባቸው ስላልፈቀደ ቢያዙት መንገድ የሚገፉ ብዙዎች ናቸው፡፡

ኢስላም የተፈጥሮ እምነት ነው!!

በአቡ ሀይደር

በአላህ ሥም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ክፍል አንድ

ምስጋና የዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ የተገባ ነው፡፡ የአላህ ውዳሴና ሰላም፡ የሰላም አለቃና መምህር ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ ይሁን፡፡ ድልና የበላይነት ሐቅን ለማንገስና ሀሰትን ለማርከስ፡ በደልን አጥፍቶ ፍትህን ለማስፈን ዕውቀታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ህይወታቸውን መስዋእት በማድረግ ለሚታገሉት ይሁን፡፡

ኢስላም ሰው የተፈጠረበት ጎዳና፣ ነቢያት የተላኩበት ዋና ዓላማ፣ መለኮታዊ መጽሐፍት የወረዱበት ሚስጥር ነው፡፡ ጀነትና ጀሀነምም የተሰየሙት በዚሁ የኢስላም አስተምህሮ ሰበብ ነው፡፡ ያመነው ለጀነት የካደውም ለጀሀነም ይታጭ ዘንድ፡፡

ከዚህ በመቀጠል በተከታታይ ክፍሎች ኢስላም የሰው ተፈጥሮአዊ እምነትና የነቢያት አስተምህሮ መሆኑን የሚገልጹ አስረጂዎችን አላህ በፈቀደው መጠን እንመለከታለን ኢንሻአላህ፡-

1ኛ. ኢስላም የነቢያት ሃይማኖት እና ሰው የተፈጠረበት ጎዳና መሆኑን ለማወቅ የስሙን ትርጓሜ ማወቅ ብቻ በራሱ አንድ መረጃ ነው፡፡ ስለሆነም፡- ኢስላም ማለት ምን ማለት ነው? ብለን ጥያቄ እናንሳ፡፡

ኢስላም ማለት ቀጥታ ፍቺው፡- መታዘዝ፣ መማረክ፣ እጅ መስጠት ማለት ነው፡፡ ሃይማኖታዊ ፍቺው ደግሞ፡- ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ እሱን ብቻ በመገዛት፣ ከአላህ ውጪ የሚመለኩ በሆኑ፡ የጣኦት አምልኮ በመራቅ፣ በአላህ ትእዛዝ ስር ማደርና መኖር ማለት ነው፡፡ በቀላሉ በሌላ አገላለጽ፡- አላህን እሱ ባዘዘን መንገድ ለፈቃዱ አድሮ መገኘት ማለት ነው፡፡ ይህን ሃሳብ ሊገልጹ ከሚችሉ የቅዱስ ቁርአን ትምህርቶች አንዱን ለአብነት እንመልከት፡-

" قَالَ أَسْلِمْ رَبُّهُ لَهُ قَالَ إِذْ * الصَّالِحِينَ لَمِنَ الْآخِرَةِ فِي وَإِنَّهُ الدُّنْيَا فِي اصْطَفَيْنَاهُ وَلَقَدِ نَفْسَهُ سَفِهَ مَنْ إِلَّا إِبْرَاهِيمَ مِلَّةِ عَنْ يَرْغَبُ وَمَنْ الْعَالَمِينَ لِرَبِّ أَسْلَمْتُ " البقرة سورة 131-130

"ከኢብራሂምም ሕግጋት ነፍሱን ያቄለ ሰው ካልኾነ በስተቀር የሚያፈገፍግ ማነው? (የለም)፤ በቅርቢቱም ዓለም በእርግጥ መረጥነው፡፡ በመጨረሻይቱም ዓለም እርሱ ከመልካሞቹ ነው፡፡ ጌታው ለርሱ ታዘዝ ባለው ጊዜ (መረጠው)፡፡ ለዓለማት ጌታ ታዘዝኩ አለ፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 130-131)፡፡

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ለዓለማት ጌታ ‹‹ታዘዝኩ›› ለሚለው ቃል በዐረብኛው የተቀመጠው ‹‹አስለምቱ›› የሚለው መሆኑን ልብ ይበሉ፡፡ በመሆኑም ነቢያት ሁሉ አላህን በብቸኝነት በመገዛት ለሱ የታዘዙ በመሆናቸው ሙስሊሞች ናቸው!! ሙስሊም ያልሆነ ነቢይ የለም፡፡ አንድ ነቢይ ሙስሊም አይደለም ማለት፡ የቀረው ምርጫ እሱ ከሀዲ (ካፊር) ነው ማለት ብቻ ነው፡፡ ሰዎች ከእምነት አንጻር ለሁለት ነውና የሚከፈሉት፡፡ ወይ አማኞች ናቸው ካልሆነም ከሀዲያን ናቸው፡፡ ሶስተኛ ምድብ የለም፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" بَصِيرٌ تَعْمَلُونَ بِمَا وَاللَّهُ مُؤْمِنٌ وَمِنْكُمْ كَافِرٌ فَمِنْكُمْ خَلَقَكُمْ الَّذِي هُوَ " التغابن سورة 2

"እርሱ ያ የፈጠራችሁ ነው፤ ከእናንተም ከሐዲ አለ፤ ከእናንተም አማኝ አልለ፡፡ አላህም በምትሠሩት ሁሉ ተመልካች ነው።" (ሱረቱ-ተጋቡን 2)፡፡

ታዲያ የአላህ ነቢያትን እና የሰው ተፈጥሮን ኢስላም ነው ካላልን ክህደት ነው እንበለው? የሚፈርዱት ፍርድ ምንኛ ከፋ!!

ነቢያት በጠቅላላ አላህን በብቸኝነት በመገዛት ለአላህ እጅ መስጠትን (መታዘዝን) በማስተማርም በመተግበርም ሙስሊም መሆናቸውን በተጨባጭ አሳይተዋል፡፡ የአላህ ቃልም እንዲህ ይመሰክርላቸዋል፡-

" فَاتَّقُونِ أَنَا إِلَّا إِلَهَ لَا أَنَّهُ أَنْذِرُوا أَنْ عِبَادِهِ مِنْ يَشَاءُ مَنْ عَلَى أَمْرِهِ مِنْ بِالرُّوحِ الْمَلَائِكَةَ يُنَزِّلُ " النحل سورة 2

"ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ መላእክትን ከራእይ ጋር በፈቃዱ ያወርዳል፤ (ከሐዲዎችን በቅጣት) አስጠንቅቁ፤ እነሆ ከኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም ፍሩኝም ማለትን (አሳታውቁ በማለት ያወርዳል)።" (ሱረቱ-ነሕል 2)፡፡

" الطَّاغُوتَ وَاجْتَنِبُوا اللَّهَ اعْبُدُوا أَنِ رَسُولًا أُمَّةٍ كُلِّ فِي بَعَثْنَا وَلَقَدْ... " النحل سورة 36

"በየሕዝቡም ሁሉ አውስጥ አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ፤ በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል…" (ሱረቱ-ነሕል 36)፡፡

" فَاعْبُدُونِ أَنَا إِلَّا إِلَهَ لَا أَنَّهُ إِلَيْهِ نُوحِي إِلَّا رَسُولٍ مِنْ قَبْلِكَ مِنْ أَرْسَلْنَا وَمَا " الأنبياء سورة 25

"ከአንተ በፊትም፣ እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ፣ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢሆን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም።" (ሱረቱል አንቢያእ 25)፡፡

2ኛ. አሁንም በድጋሚ ሰው በተፈጥሮው በኢስላም ጎዳና ላይ ሁኖ እንደሚወለድ ማስረጃ ካስፈለገ ቀጣዩ አንቀጽ በቂ ነው፡-

" يَعْلَمُونَ لَا النَّاسِ أَكْثَرَ وَلَكِنَّ الْقَيِّمُ الدِّينُ ذَلِكَ اللَّهِ لِخَلْقِ تَبْدِيلَ لَا عَلَيْهَا النَّاسَ فَطَرَ الَّتِي اللَّهِ فِطْرَتَ حَنِيفًا لِلدِّينِ وَجْهَكَ فَأَقِمْ " الروم سورة 30

"ወደ እውነት ተዘንባይ ሆነህም ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፤ የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዙዋት)፤ የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም፤ ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው፤ ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያውቁም።" (ሱረቱ-ሩም 30)፡፡

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ሁላችንም የተፈጠርንበትን ሃይማኖት እንድንከተልና፣ ሃይማኖቱን ሳንለውጥ ፈታችንን ለእምነቱ ቀጥ ማድረግ እንዳለብን ተነግሮናል። ይህ ሃይማኖት ደግሞ ኢስላም ለመሆኑ በነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ንግግር እንዲህ ይብራራል፡-

أَوْ يُنَصِّرَانِهِ، أَوْ يُهَوِّدَانِهِ، فَأَبَوَاهُ الفِطْرَةِ، عَلَى يُولَدُ مَوْلُودٍ كُلُّ» :وَسَلَّمَ عَلَيْهِ اللهُ صَلَّى النَّبِيُّ قَالَ :قَالَ عَنْهُ، اللَّهُ رَضِيَ هُرَيْرَةَ أَبِي عَنْ يُمَجِّسَانِهِ....» رواه البخاري ومسلم وغيرهما.

ከአቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው፡ የአላህ ነቢይ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "ማንም የሚወለድ ሰው በፊጥራ (በኢስላም ጎዳና) ላይ ሆኖ እንጂ አይወለድም። ወላጆቹ ግን አይሁዳዊ ያደርጉታል፣ ወይም ክርስቲያን ያደርጉታል። ወይም መጁሳ (ዞሮስቲያንስ) ያደርጉታል እንጂ…" (ቡኻሪይ 1385፣ ሙስሊም 2658፣ አቡ ዳዉድ 4716፣ ቲርሚዚይ 2287፣ ነሳኢይ 2138)።

በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ልብ ልትሉ የሚገባው፡- ወላጆቹ እንደ እምነታቸው አይሁዳዊ ወይም ክርስቲያን ወይም መጁሳ ያደርጉታል ሲባል፡ ነገር ግን ወላጆቹ ሙስሊም ያደርጉታል የሚል ቃል አለመጠቀሱን ነው። ለምን ብለን ጥያቄም ካነሳን መልሱ ግልጽ

ነው። እሱም፡- ኢስላም የሰው ተፈጥሮአዊ እምነት ስለሆነ ነው። የቤተሰብ አስተዋጽኦ አይፈልግም። በሌላም ሐዲሥ ላይ ተጨማሪ ምስክርነትን እናገኛለን። ሐዲሡ እንዲህ ይላል፡-

سِنِينَ سَبْعِ أَبْنَاءُ وَهُمْ بِالصَّلاَةِ أَوْلاَدَكُمْ مُرُوا » -وسلم عليه الله صلى- اللَّهِ رَسُولُ قَالَ قَالَ جَدِّهِ عَنْ أَبِيهِ عَنْ شُعَيْبٍ بْنِ عَمْرِو عَنْ الْمَضَاجِعِ فِى بَيْنَهُمْ وَفَرِّقُوا سِنِينَ عَشْرِ أَبْنَاءُ وَهُمْ عَلَيْهَا وَاضْرِبُوهُمْ ». رواه داود أبو وأحمد.

ዐምሩ ኢብኑ ሹዐይብ ከአባቱ እንዲሁም ከአያቱ ባስተላለፈልን ዘገባ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- ‹‹ልጆቻችሁ ሰባት አመት ሲሞላቸው ሶላት እንዲሰግዱ እዘዟቸው። አስር ሆኗቸው ካልታዘዟችሁ ደግሞ ቅጧቸው። በመሀከላቸውም በመኝታ ለያዩዋቸው›› (አቡ ዳዉድ 495፣ አሕመድ 6756)።

በዚህ ሐዲሥ መሰረት ለልጆች የሚተላለፈው የመጀመሪያው ትእዛዝ ሶላት እንዲሰግዱ መሆኑን በግልጽ እንረዳለን። የኛ ጥያቄ ደግሞ፡- አንድ ሰው ሶላቱ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ሙስሊም መሆን አለበት። እስልምናው ያልተስተካከለ ሰው፣ ወይም ሙስሊም ያልሆነ ሰው ቢሰግድ ከድካም ውጪ ምንም ትርፍ የለውም።

ቅድሚያ በሸሀደተይን (የአላህን ብቸኛ አምላክነትና የነቢዩ ሙሐመድን የመጨረሻ መልክተኝነት በመመስከር) ወደ ኢስላም መግባት አለበት። ታዲያ ልጆቻችሁን ሶላት እንዲሰግዱ እዘዙ! የሚለው ነቢያዊ አስተምህሮ፣ እነሱ በፍጥረታቸው ሙስሊም መሆናቸውን አያስረዳምን? ሙስሊም ባይሆኑ ኖሮ ቅድሚያ ሸሀደተይንን አስይዟቸው አይባልም ነበርን? በርግጥም ይህ የሚያሳየው ሰው የተፈጠረው በኢስላም ጎዳና ላይ መሆኑን ነው!!

በተጨማሪም ሌላ አንድ ሐዲሡል ቁድሲይ ልጨምርላችሁ። እንዲህ ይላል፡-

مَا أُعَلِّمَكُمْ أَنْ أَمَرَنِي رَبِّي إِنَّ أَلَا " :خُطْبَتِهِ فِي يَوْمٍ ذَاتَ قَالَ وَسَلَّمَ، عَلَيْهِ اللهُ صَلَّى اللهِ رَسُولَ أَنَّ الْمُجَاشِعِيِّ، حِمَارٍ بْنِ عِيَاضِ عَنْ أَحْلَلْتُ مَا عَلَيْهِمْ وَحَرَّمَتْ دِينِهِمْ، عَنْ فَاجْتَالَتْهُمُ الشَّيَاطِينُ أَتَتْهُمُ وَإِنَّهُمْ كُلَّهُمْ، حُنَفَاءَ عِبَادِي خَلَقْتُ وَإِنِّي ،...هَذَا، يَوْمِي عَلَّمَنِي مِمَّا جَهِلْتُمْ، سُلْطَانًا بِهِ أُنْزِلْ لَمْ مَا بِي يُشْرِكُوا أَنْ وَأَمَرَتْهُمْ لَهُمْ، " رواه مسلم والنسائي وأحمد.

ዒያድ ኢብኒ ሒማር አል-ሙጃሺዒይ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደነገረን የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) አንድ ቀን በኹጥባቸው መሀል እንዲህ አሉን፡- ‹‹አዋጅ! ጌታዬ እናንተ የማታውቁትን ለኔ ዛሬ ካሳወቀኝ ነገር እንዳስተምራችሁ አዘዘኝ። (አላህ

እንዲህ ይላል)፡- እኔ ባሮቼን በጠቅላላ በቀጥተኛው መንገድ ላይ ፈጠርኳቸው፡፡ ሰይጣናት ደግሞ ከቀጥተኛው ሃይማኖታቸው አስወጧቸው፡፡ ለነሱ የፈቀድኩትንም ነገር እርም አደረጉባቸው፡፡ እኔ ምንም አስረጂ ባላወረድኩት ነገርም በእኔ ላይ እንዲያጋሩ አዘዟቸው…›› (ሙስሊም 2865፣ አሕመድ 17623፣ ነሳኢይ ሱነኑል ኩብራ 8071)፡፡

በዚህም ሐዲሥ መሰረት፡ ሁላችንም ስንፈጠር በቀጥተኛውና በተስተካከለው የኢስላም እምነት ላይ እንደሆነ በቀላሉ እንረዳለን፡፡

ዶክተር ሷሊሕ አል-ፈውዛን (ሐፊዘሁላህ) በጉዳዩ ላይ እንዲህ ይላሉ፡-

لها يزين ما ذلك عن بها وينحرف يفسدها ولكن .شيئا به تشرك لا تعبده، لله محبة بالألوهية، لله مقرة كانت تركت إذا بفطرتها والنفس عليها ودخيل طارئ والشرك .الفطر في مركوز فالتوحيد .غرورا القول زخرف بعض إلى بعضهم يوحي بما والجن الإنس شياطين .التوحيد كتاب :الباب الأول :الانحراف في تعالى الله قال: (الله لخلق تبديل لا عليها الناس فطر التي الله فطرة حنيفا للدين وجهك فأقم). البشرية حياة

‹‹ማንኛይቱም ነፍስ በተፈጥሮዋ ብትተው (ምንም አይነት ሃይማኖታዊ ተጽእኖ ባይደረግባት) አላህን በውዴታና በፍቅር ምንም ሳታጋራበት ያመለከቻው ሆና ባደገች ነበር፡፡ ግን ከጂንና ከሰው የሆኑ ሰይጣናት በሚያጌጡላት ብልጭልጭ ነገራትና የሀሰት ትምህርቶች በመሳብ ከእውነት ጎዳና በመዘንበል ትበላሻለች እንጂ፡፡

ተውሒድ (አላህን በብቸኝነት አምልኮ መገኘት) በሰው ተፈጥሮ ውስጥ የተቀመጠ ነገር ሲሆን፡ ሺርክ (በአላህ ላይ ማጋራት) ግን ከጊዜ በኋላ የሚመጣ ውጫዊ ከስተትና ሰርጎ-ገብ ነው፡፡ አላህም በቃሉ፡- "ወደ እውነት ተዘንባይ ሆነህም ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፤ የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዙዋት)፤ የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም…" ብሏልና፡፡›› (ኪታቡ-ተውሒድ፡ የመጀመሪያው ባብ ላይ)፡፡

ጌታችን አላህ ሆይ! በኢስላም መንገድ ላይ ሙስሊም አድርገህ እንደፈጠርከን፡ ሙስሊም አድርገህ አቆይተህ፡ ሙስሊም አድርገህ ግደለን፡፡ አሚን፡፡

ክፍል ሁለት

3ኛ. ሌላው ኢስላም ሰው የተፈጠረበት መንገድ፡ የነቢያት ሃይማኖትና ስብከት መሆኑን የምንረዳው፡- በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ የተወሰኑ ነቢያትን በስም በመጥቀስ ሙስሊም እንደነበሩ መናገሩ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የነቢያት መደምደሚያና መጨረሻው በመሆናቸው ከሳቸው በፊት የነበሩ ነቢያት ‹ሙስሊም› ነበሩ ተብሎ መነገሩ ኢስላም ጅማሬው ከጥንት እንጂ ከሳቸው እንዳልሆነ በግልጽ ያስረዳናል፡፡ ሙስሊም እንደነበሩ ለናሙና የተጠቀሱ ነቢያትም፡-

ሀ/ ኑሕ (ዐለይሂ-ሰላም)፡-

በዚህ ምድር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ መልክተኛ (ረሱል) ሆኖ የተላከ ሰው ነው፡፡ ከበፊቱ የነበሩት ነቢይ ብቻ ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው ረሱል ኑሕ (ዐለይሂ-ሰላም) ህዝቦቹን ወደ አንድ አምላክ አምልኮ (ወደ ላ ኢላሀ ኢለላህ) ነው የተጣራው፡፡ (አል-አዕራፍ 7፡59፣ ሁድ 11፡25-26፣ አል-ሙእሚኑን 23፡23፣ ኑሕ 71፡1-3)፡፡

ይህ የአላህ መልክተኛ ከህዝቦቹ የተቃውሞ ምላሽ በገጠመው ጊዜ፡ እሱ በአላህ ላይ መመካቱንና ሙስሊም መሆኑን አውጇል፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" الْمُسْلِمِينَ مِنَ أَكُونَ أَنْ وَأُمِرْتُ اللَّهِ عَلَى إِلَّا أَجْرِيَ إِنْ أَجْرٍ مِنْ سَأَلْتُكُمْ فَمَا تَوَلَّيْتُمْ فَإِنْ " ونس سورة 72

"«በትሸሹም (አትጎዱኝም)፡፡ ከምንዳ ምንንም አልለምናችሁምና፡፡ ምንዳዬ በአላህ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም፡፡ ከሙስሊሞች እንድሆንም ታዝዣለሁ፡፡»" (ሱረቱ ዩኑስ 10፡72)፡፡

ለ/ ኢብራሂም (ዐለይሂ-ሰላም)፡-

በወቅቱ የነበሩትን ጣኦታትን በመሰባበር፡ አላህ በብቸኝነት እንዲመለክ ወደ አላህ መንገድ ከተጣሩት መልክተኞች አንዱ ነው፡፡ በተለይ ኢብራሂምን ሙስሊሞች፣ አይሁዶችና ክርስቲያኖች ራሳቸውን ወደሱ በማስጠጋት መጥራት ይወዳሉ፡፡ የሚያመልኩትም የኢብራሂምን አምላክ እንደሆነ መግለጽ ይወዳሉ፡፡ እንግዲያውስ ኢብራሂም እምነቱ ምን ነበር? የአላህ ቃል መልስ አለው፡፡ እንዲህ ይላል ቃሉ፡-

" تَعْقِلُونَ أَفَلَا بَعْدِهِ مِنْ إِلَّا وَالْإِنْجِيلُ التَّوْرَاةُ أُنْزِلَتِ وَمَا إِبْرَاهِيمَ فِي تُحَاجُّونَ لِمَ الْكِتَابِ أَهْلَ يَا " عمران آل سورة 65

"እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በኢብራሂም ለምን ትከራከራላቹሁ? ተዉራትና ኢንጂልም ከርሱ በኋላ እንጅ አልተወረዱም፤ ልብ አታደርጉምን? በላቸዉ።" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡65)፡፡

ይህ አንቀጽ የወረደበት ምክንያት (ሰበበ-ኑዙል) አለው፡፡ ምክንያቱም፡- ነሳራ ነጅራን (በየመን ጠረፍ ይኖሩ የነበሩ ክርሲቲያኖች) እና የአይሁድ ሊቃውንቶች ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ጋር ተሰበሰቡ፡፡ ከዛም በመሀከላቸው በኢብራሂም (ዐለይሂ-ሰላም) ጉዳይ ክርክር ተነሳ፡፡ ሁሉም የራሱን እምነት ወደ ኢብራሂም ማስጠጋት ስለሚፈልግ፡ አይሁዶችም እንዲህ አሉ፡- ኢብራሂም በእምነቱ ይሁዳዊ እንጂ ሌላ አልነበረም፡፡ ክርስቲያኖችም በበኩላቸው፡- ኢብራሂም ክርስቲያን እንጂ ሌላ አልነበረም አሉ፡፡

ጌታ አላህ ባወረደው መለኮታዊ ቃሉ አማካኝነት ደግሞ ሁለቱም ስህተት ላይ መሆናቸውን ነገራቸው፡፡ አይሁዶች አይሁዳዊ ነን የሚሉት የተውራት ተከታይ ነን ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ አባባላቸው መሰረት ኢብራሂምን (ዐለይሂ-ሰላም) አይሁዳዊ ለማድረግ እሱ የተውራት ተከታይ መሆን ነበረበት፡፡ እሱ የነበረበት ዘመን ደግሞ ሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ከመወለዱና ተውራት ከመውረዱ ረጅም ዘመን ቀድሞ የነበረ በመሆኑ፡ ተውራትም የወረደው ከሱ በኋላ እንጂ ከበፊቱ ባለመሆኑ እሱን አይሁዳዊ ማድረጉ ስህተት ነው አላቸው፡፡

ክርስቲያኖቹ ደግሞ እኛ ክርስቲያን ነን የሚሉት የዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ተከታይ እና የኢንጂል አማኝ ነን በማለታቸው ነው፡፡ ጉዳዩ እንደዛ ከሆነ ኢብራሂምንም ክርስቲያን ነበር ብሎ ለመጥራት እሱ ከዒሳ በኋላ የመጣ ሰው ሆኖ ኢንጂልን የተከተለ መሆን ነበረበት፡፡ ግና እሱ የነበረበት ዘመን ከዒሳ መፈጠርና ከኢንጂል መውረድ ረጅም ዘመን የቀደመ በመሆኑ እሱ ‹ክርስቲያን› ነበር የሚለው ሚዛን የማይደፋ እንደሆነ ነገራቸው፡፡ ታዲያ ይህን ልብ አታደርጉምን! ሲልም ገሰጻቸው፡፡

አሁን የቀረው ጥያቄ፡- ኢብራሂም በእምነቱ አይሁዳዊም ሆነ ክርስቲያን ካልነበር እንግዲያውስ ምን ነበር? የሚለው ነው፡፡ አንቀጹ ወረድ ይልና ለዚህ ጥያቄ እንዲህ በማለት መልስ ይሰጣል፡-

" الْمُشْرِكِينَ مِنَ كَانَ وَمَا مُسْلِمًا حَنِيفًا كَانَ وَلَكِنْ نَصْرَانِيًّا وَلَا يَهُودِيًّا إِبْرَاهِيمُ كَانَ مَا " عمران آل سورة 67

"ኢብራሒም ይሁዳዊም ክርስቲያንም አልነበረም ግን ወደ ቀጥተኛዉ ሃይማኖት የተዘነበለ #ሙስሊም ነበረ፤ ከአጋሪዋችም አልነበረም።" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡67)፡፡

ሐ/ የኢብራሂምና የየዕቁብ ኑዛዜ፡-

የአላህ ነቢይ የሆኑት ኢብራሂምና የልጅ ልጁ የዕቁብ (ዐለይሂማ-ሰላም) ለልጆቻቸው ያዘዙት የመጨረሻ ምክርና ኑዛዜ፡- እነሱ በኢስላም መንገድ ላይ ሙስሊም ሆነው እንዲሞቱ ነው፡፡ እነሱ ሙስሊም የሆኑ ነቢያት ባይሆኑ ኖሮ ልጆቻቸውን በኢስላም ላይ ጸንተው እንዲሞቱ ወሲያ (ኑዛዜ) ያደርጉ ነበርን? የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" مُسْلِمُونَ وَأَنْتُمْ إِلَّا تَمُوتُنَّ فَلَا الدِّينَ لَكُمُ اصْطَفَى اللَّهَ إِنَّ بَنِيَّ يَا وَيَعْقُوبُ بَنِيهِ إِبْرَاهِيمُ بِهَا وَوَصَّى " البقرة سورة 132

"በርሷም (በሕግጋቲቱ) ኢብራሂም ልጆቹን አዘዘ፡፡ ያዕቁብም (እንደዚሁ ልጆቹን አዘዘ)፡፡ «ልጆቼ ሆይ! አላህ ለናንተ ሃይማኖትን መረጠ፤ ስለዚህ እናንተ ሙስሊሞች ኾናችሁ እንጂ አትሙቱ» (አላቸው)፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡132)፡፡

በተለይ ነቢዩላህ የዕቁብ (ዐለይሂ-ሰላም) ሞት በመጣበት ጊዜ፡ ልጆቹን በመሰብሰብ የጠየቃቸው ጥያቄ የጉዳዩን እውነተኝነት ያጎላዋል፡፡ መልካም አባትም ለልጆቹ ይህን ማድረግ እንዳለበት ከዚህ ታላቅ ነቢይ ትምህርት ይቀስማል፡፡ ይህ ነቢይ ልጆቹን

፡- ከኔ (ጎልፈት) በኋላ ማንን ታመልካላችሁ? በማለት ጥያቄን አቀረበ፡፡ የልጆቹም መልስ እንደሚከተለው ነበረ፡-

" قَالُوا بَعْدِي مِنْ تَعْبُدُونَ مَا لِبَنِيهِ قَالَ إِذْ الْمَوْتُ يَعْقُوبَ حَضَرَ إِذْ شُهَدَاءَ كُنْتُمْ أَمْ "

" مُسْلِمُونَ لَهُ وَنَحْنُ وَاحِدًا إِلَهًا وَإِسْحَاقَ وَإِسْمَاعِيلَ إِبْرَاهِيمَ آبَائِكَ وَإِلَهَ إِلَهَكَ نَعْبُدُ البقرة سورة 133

"ያዕቁብን ሞት በመጣበት ጊዜ ለልጆቹ ከኔ በኋላ ማንን ትገዛላችሁ ባለ ጊዜ ቀራቢዎች ነበራችሁን? (እነርሱም) አምላክህንና የአባቶችህን የኢብራሂምን የኢስማዒልንና የኢስሐቅንም አምላክ አንድ የኾነውን አምላክ እኛ ለርሱ #ፍፁም-ታዛዦች ኾነን እናመልካለን አሉ፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡133)፡፡

በዚህ የአማርኛ ትርጉም ውስጥ ‹‹ፍጹም ታዛዦች›› የሚለው ቃል፡ በዋናው ዐረብኛ ቁርኣን ላይ ‹‹ሙስሊም›› ማለቱን ልብ ይበሉ፡፡ ስለዚህ የዕቁብና ልጆቹ (ዐለይሂሙ-ሰላም) ሙስሞች ነበሩ!!፡፡

መ/ ሉጥ (ዐለይሂ-ሰላም)፡-

ነቢዩላህ ሉጥ (ዐለይሂ-ሰላም) ከጥቂት ተከታዮቹ (ቤተሰቡ) ጋር ለጌታው አላህ እጅ የሰጠ ሙስሊም ነቢይ መሆኑ በቁርኣን ተጠቅሷል፡-

" الْمُسْلِمِينَ مِنَ بَيْتٍ غَيْرَ فِيهَا وَجَدْنَا فَمَا * الْمُؤْمِنِينَ مِنَ فِيهَا كَانَ مَنْ فَأَخْرَجْنَا الذاريات سورة 36-35

"ከምእመናንም፤ በርሷ (በከተማቸው) ውስጥ የነበሩትን አወጣን። በውስጧም #ከሙስሊሞች ከአንድ ቤት (ቤተሰቦች) በስተቀር አላገኘንም።" (ሱረቱ-ዛሪያት 51፡35-36)፡፡

ሠ/ ዩሱፍ (ዐለይሂ-ሰላም)፡-

ይህ የአላህ መልከተኛ በመጨረሻ ህይወቱ ከጌታው አላህ የከጀለው ነገር፡ ሙስሊም እንደሆነ በዛው እንዲገድለውና ከመልካም የአላህ ባሮች ጋር እንዲያነፃቡተው ነበር፡-

" وَأَلْحِقْنِي مُسْلِمًا تَوَفَّنِي وَالْآخِرَةِ الدُّنْيَا فِي وَلِيِّي أَنْتَ وَالْأَرْضِ السَّمَاوَاتِ فَاطِرَ الْأَحَادِيثِ تَأْوِيلِ مِنْ وَعَلَّمْتَنِي الْمُلْكِ مِنَ آتَيْتَنِي قَدْ رَبِّ بِالصَّالِحِينَ يوسف سورة 101

"ጌታዬ ሆይ! ከንግስና በእርግጥ ሰጠኸኝ፤ ከሕልሞችም ፍች አስተማርከኝ፤ የሰማያትና የምድር ፈጣሪ ሆይ! አንተ በቅርቢቱና በመጨረሻይቱ ዓለም ረዳቴ ነህ፤ #ሙስሊም ሆኜ ግደለኝ፤ በመልካሞቹም አስጠጋኝ፤ (አለ)።" (ሱረቱ ዩሱፍ 12፡101)፡፡

ረ/ ሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም)፡-

ከበኒ ኢስራኢል ነቢያት መሀከል በገናናቱ የሚታወቀው የአላህ መልክተኛ የሆነው ሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ህዝቦቹን ከፊርዐውን አደጋ መትረፍን ከፈለጉ በአላህ ላይ መመካት እንዳለባቸው ሲገስጻቸው እንዲህ ነበር ያለው፡-

" مُسْلِمِينَ كُنْتُمْ إِنْ تَوَكَّلُوا فَعَلَيْهِ بِاللَّهِ آمَنْتُمْ كُنْتُمْ إِنْ قَوْمِ يَا مُوسَى وَقَالَ " ونس سورة 84

"ሙሳም አለ፡- «ሕዝቦቼ ሆይ! በአላህ አምናችሁ እንደ ሆነ በርሱ ላይ ተጠጉ፡፡ #ታዛዦች እንደ ሆናችሁ (በአላህ ላይ ትመካላችሁ)፡፡»" (ሱረቱ ዩኑስ 10፡84)፡፡

በዚህ አንቀጽ ስር ‹ታዛዦች› ለሚለው የአማርኛ ትርጉም በዐረብኛው ቁርአን የተቀመጠው ቃል ‹‹ሙስሊም›› የሚለው ነው፡፡

ሰ/ የፊርዐውን አስማተኞች፡-

በሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ድንቅ ተአምር በመማረክ፡ በትሮቻቸውን በሰዎች አይን ፊት እባብ ያስመስሉ የነበሩት የፊርዐውን ደጋሚዎች በመጨረሻም ለዓለማቱ ጌታ እጅ ሰጡ፡፡ በአላህ ጌትነትና በሙሳም ነቢይነት አመኑ፡፡ እነሱም ሙስሊም መሆናቸውን በማወጅ፡ አላህም ፍጻሜያቸውን አሳምሮ ሙስሊም አድርጎ እንዲገድላቸው ተማጸኑት፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይነበባል፡-

" مُسْلِمِينَ وَتَوَفَّنَا صَبْرًا عَلَيْنَا أَفْرِغْ رَبَّنَا جَاءَتْنَا لَمَّا رَبِّنَا بِآيَاتِ آمَنَّا أَنْ إِلَّا مِنَّا تَنْقِمُ وَمَا * مُنْقَلِبُونَ رَبِّنَا إِلَى إِنَّا قَالُوا " الأعراف سورة 126-125

"አሉ፡- እኛ ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን፤ የጌታችንም ታምራቶች በመጡልን ጊዜ ከማመናችን በቀር ከኛ አትጠላም፤ ጌታችን ሆይ! በኛ ላይ ትግስትን አፍስስ፤ #ሙስሊሞች ሆነን ግደለን።" (ሱረቱል አዕራፍ 7፡125-126)፡፡

ሸ/ ሱለይማን (ዐለይሂ-ሰላም)፡-

የዳዉድ (ዐለይሂ-ሰላም) ልጅ የሆነው ነቢዩላህ ሱለይማን (ዐለይሂ-ሰላም) ሙስሊም እንደነበረ ይመሰክራል፡፡ በወቅቱ ፀሀይ አምላኪ የነበረችውንም መሊከቱ ሰበአ (የሰበአ ንግስት) ቢልቂሳን ወደ ኢስላም ጥርሪ አድርጎላታል፡፡ እሷም በአላህ እገዛ ሙስሊም ሆናለች፡፡ ቅዱስ ቁርአን እንዲህ ይነግረናል፡-

" فَلَمَّا .....مُسْلِمِينَ وَأْتُونِي عَلَيَّ تَعْلُوا أَلَّا * الرَّحِيمِ الرَّحْمَنِ اللَّهِ بِسْمِ وَإِنَّهُ سُلَيْمَانَ مِنْ إِنَّهُ * كَرِيمٌ كِتَابٌ إِلَيَّ أُلْقِيَ إِنِّي الْمَلَأُ أَيُّهَا يَا قَالَتْ مُسْلِمِينَ وَكُنَّا قَبْلِهَا مِنْ الْعِلْمَ وَأُوتِينَا هُوَ كَأَنَّهُ قَالَتْ عَرْشُكِ أَهَكَذَا قِيلَ جَاءَتْ النمل سورة 31.42-29

"(እርሷም በደረሳት ጊዜ) አለች፡- እላንተ መማክርት ሆይ! እኔ ክብር ያለው ጽሁፍ ወደኔ ተጣለ፤ እርሱ ከሱለይማን ነው፤ እርሱም በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኀሩኀ፣ በጣም አዛኝ በሆነው፤ በእኔ ላይ አትኩሩ፡፡ ታዛዦችም ኾናችሁ ወደኔ ኑ፤ (የሚል ነው)፡፡ ….በመጣች ጊዜ፡- «ዙፋንሽ እንደዚህ ነውን» ተባለች፡፡ «እርሱ ልክ እርሱ ነው መሰለኝ» አለች፡፡ (ሱለይማን) «ከእርሷ በፊትም ዕውቀትን ተሰጠን #ሙስሊሞችም ነበርን፤» (አለ)፡፡" (ሱረቱ-ነምል 27፡ 29-31.42)፡፡

ቀ/ የሚሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ሐዋሪያት፡-

" مُسْلِمُونَ بِأَنَّا وَاشْهَدْ بِاللَّهِ آمَنَّا اللَّهِ أَنْصَارُ نَحْنُ الْحَوَارِيُّونَ قَالَ اللَّهِ إِلَى أَنْصَارِي مَنْ قَالَ الْكُفْرَ مِنْهُمُ عِيسَى أَحَسَّ فَلَمَّا آل عمران سورة 52

"ዒሳ ከነርሱ ክሕደት በተሰማውም ጊዜ ፡-ወደ አላህ (ተጨምረዉ) ረዳቶቼ እነማን ናቸዉ? አለ፤ ሐዋሪያት ፡ -እኛ የአላህ ረዳቶች ነን፤ በአላህም አምነናል፤ እኛም #ትክክለኛ ታዛዦች መሆናችንን፥ መስክር፥ አሉ።" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡52)፡፡

" مُسْلِمُونَ بِأَنَّنَا وَاشْهَدْ آمَنَّا قَالُوا وَبِرَسُولِي بِي آمِنُوا أَنْ الْحَوَارِيِّينَ إِلَى أَوْحَيْتُ وَإِذْ " المائدة سورة 111

"ወደ ሐዋርያትም በኔና በመልክተኛዬ እመኑ በማለት ባዘዝኩ ጊዜ (አስታውስ) አመንን፤ እኛም #እስላሞች መሆናችንን መስክር አሉ።" (ሱረቱል ማኢህ 5፡111)።

ማጠቃለያ፡-

ከላይ ለናሙና በተመለከትናቸው ዘጠኝ ነጥቦች ውስጥ ነቢያትና ተከታዮቻቸው ሙስሊሞች መሆናቸውን በሚገባ አውቀናል። ሙስሊም ማለት ደግሞ፡- ለአላህ ትእዛዝ ያደረ፣ እጅ የሰጠ ማለት እስከሆነ ድረስ፡ ነቢያትን ሙስሊም አልነበሩም ብሎ መከራከር፡- እነሱ ለጌታቸው ታዛዥ ያልነበሩ፡ አመጸኛና ከሀዲ ነበሩ ከማለት የማይተናነስ ንግግር ነው!!

ወሰላሙ ዐለይኩም ወራሕመቱላሂ ወበረካቱሁ

ክፍል ሶስት

ዛሬ አላህ ፈቃዱ ከሆነ የምንመለከተው በዚህ ጉዳይ ላይ የሚነሱ ብሹታዎች ላይ ምላሽ መስጠትን ነው ኢንሻአላህ፡-

ብሹታ ቁ1.፡-

" الْمُسْلِمِينَ أَوَّلُ وَأَنَاْ أُمِرْتُ وَبِذَلِكَ لَهُ شَرِيكَ لاَ *الْعَالَمِينَ رَبِّ لِلّهِ وَمَمَاتِي وَمَحْيَايَ وَنُسُكِي صَلاَتِي إِنَّ قُلْ " الأنعام سورة 163-162

"«ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል። «ለእርሱ ተጋሪ የለውም። በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ። እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (በል)።" (ሱረቱል አንዓም 6፡162-163)።

" الْمُسْلِمِينَ أَوَّلَ أَكُونَ لِأَنْ وَأُمِرْتُ *الدِّينَ لَّهُ مُخْلِصًا اللَّهَ أَعْبُدَ أَنْ أُمِرْتُ إِنِّي قُلْ " الزمر سورة 12-11

"በል፡- እኔ አላህን ሃይማኖትን ለርሱ ያጠራሁ ሆኜ እንድግገዛው ታዘዝኩ፤ የሙስሊሞችም መጀመሪያ እንድሆን ታዘዝኩ።" (ሱረቱ-ዙመር 39፡11-12)።

በነዚህ ሁለት ቁርአናዊ ጥቅሶች ውስጥ ‹‹የሙስሊሞች መጀመሪያ›› የሚል ቃል አልለ። ወገኖቻችንም ይህን ቃል በመያዝ፡ እስልምና የተጀመረው በነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነው። እሳቸው የመጀመሪያ ሙስሊም ተብለዋልና። ይህ ደግሞ ከሳቸው በፊት ሙስሊም እንዳልነበረ ይጠቁማል እያሉን ነው። የኛም ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡-

1/ ኢስላም የነቢያት ሃይማኖት ለመሆኑና፡ ነቢያትም ሙስሊሞች ለመሆናቸው በክፍል ሁለት ትምህርታችን ላይ ዘጠኝ ምሳሌዎችን ለአብነት አቅርበናል። ይህ በራሱ እናንተ የሄዳችሁበትን አካሄድ ውድቅ የሚያደርግ ነው። እሳቸውን የመጀመሪያ ሙስሊም ናቸው ስንል ከሳቸው በፊት የነበሩት ነቢያት ሙስሊም አልነበሩም ማለትን ካስያዘን፡ ታዲያ ነቢያትን ካፊሮች (ከሀዲያን) ነበሩ እንበላቸው? ሌላ ሶስተኛ ምርጫ የለምና!! ወይ ሙስሊም ወይንም ደግሞ ካፊር ማለት!። ዓለም ላይ ያለ ሰው ከነዚህ ሁለቱ አይወጣም (ሱረቱ-ተጋቡን 64፡2)።

2/ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ከላይ ባየናቸው ሁለት ቁርአናዊ አንቀጾች መሰረት ‹‹የሙስሊሞች መጀመሪያ›› ተብለው መጠራታቸው፡ ከሳቸው በፊት ሙስሊም አለመኖሩና ሳይሆን የሚያመላክተው፡ እሳቸው ለዚህ ኡምማ ፈር ቀዳጅና ብርሀን ሰንጣቂ፡ የመጀመሪያው ሙስሊም መሆናቸውን ነው። ይህ መጀመሪያነታቸው ከተላኩበት ማኃበረሰብ አንጻር ነው ሊታይ የሚገባው እንጂ፡ ከአጠቃላይ የሰው ዘር አንጻር መሆን የለበትም።

ታላቁ የቅዱስ ቁርአን ተንታኝ (መፈሲር) አል-ሓፊዝ ኢብኑ ከሢር (701-770) ረሒመሁላህ፡ በዚህ ዙሪያ እንዲህ ይላሉ፡-

" قال ، 12 ، 11/ الزمر) الْمُسْلِمِينَ أَوَّلَ أَكُونَ لِأَنْ وَأُمِرْتُ * الدِّينَ لَهُ مُخْلِصًا اللَّهَ أَعْبُدَ أَنْ أُمِرْتُ إِنِّي قُلْ) : قوله في السدي وقال : وسلم عليه الله صلى أمته من يعني كثير ابن تفسير". " (7 /89) .

አል-ኢማም ሱድዲይ (ረሒመሁላህ) ‹‹የሙስሊሞችም መጀመሪያ እንድሆን ታዘዝኩ›› የሚለውን አንቀጽ፡- ከኡምመታቸው (ከተላኩበት ማኅበረሰብ) አንጻር ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ (ተፍሲር ኢብኑ ከሢር፡ ሱረቱ-ዙመር 12)፡፡

ኢማሙል ቁርጡቢይም (ረሒመሁላህ) በበኩላቸው እንዲህ ይላሉ፡-

قاله ؛ ملته أهل من المسلمين أول أنه : ومنها ... أجوبة عنه قلنا ؟ قبله والنبيون إبراهيم أوليس : قيل فإن ": الله رحمه القرطبي وقال انتهى " وغيره قتادة قول وهو ، العربي ابن .

"القرآن لأحكام الجامع" (7 /155) ، وينظر : "الطبري تفسير" (21 /270) .

‹‹እሳቸው የሙስሊሞች መጀመሪያ ሲባሉ፡ ኢብራሂምና ሌሎች ነቢያት ከበፊታቸው አልነበሩምን? ከተባለም፡ ለዚህ ምላሾች ይኖረናል፡፡ አንደኛው፡- እሳቸው ‹‹የሙስሊሞች መጀመሪያ›› የተባሉት፡ ከተላኩበት ማኅበረሰብና (ኡምመት) ከተከተላቸው ህዝብ አንጻር ነው የሚል ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ኢብኑል-ዐረቢ እንደዘሁ ገልጸውታል፡፡ እንዲሁም የታቢዒዩ ቀታደህ እና የሌሎችም አቋም ነው›› (ቁርጡቢይ፡ አል-ጃሚዑ ሊአሕካሚል-ቁርአን 7/155)፡፡ በተጨማሪም ተፍሲር ኢብኑ ጀሪር አጥ-ጠበሪይ (ጃሚዑል በያን 21/270) ይመልከቱ፡፡

አዎ! የሳቸው ‹‹የሙስሊሞች መጀመሪያነት›› ለተላኩለት ለዚህ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ሌላው ሙስሊም ሙስሊም የተሰኘውና የሐቅን ጎዳና ያገኘው በሳቸው ሰበብ ነውና፡፡ በተጨማሪም ይህ ‹‹የመጀመሪያ›› የሚለው አነጋገር በአንጻራዊነት ሊቀርብ እንደሚችል፡ የቅዱስ ቁርአን ድጋፍ አለን፡፡ እሱም ሌላ ማጠናከሪያ ይሆነናል፡፡ ቀጣዩን ምሣሌ እንመልከት፡-

ሀ/ ሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም)፡-

" فَلَمَّا تَرَانِي فَسَوْفَ مَكَانَهُ اسْتَقَرَّ فَإِنِ الْجَبَلِ إِلَى انظُرْ وَلَكِنِ تَرَانِي لَن قَالَ إِلَيْكَ أَنظُرْ أَرِنِي رَبِّ قَالَ رَبُّهُ وَكَلَّمَهُ لِمِيقَاتِنَا مُوسَى جَاء وَلَمَّا الْمُؤْمِنِينَ أَوَّلُ وَأَنَاْ إِلَيْكَ تُبْتُ سُبْحَانَكَ قَالَ أَفَاقَ فَلَمَّا صَعِقًا موسَى وَخَرَّ دَكًّا جَعَلَهُ لِلْجَبَلِ رَبُّهُ تَجَلَّى " الأعراف سورة 143

"ሙሳም ለቀጠሯችን በመጣና ጌታውም ባነጋገረው ጊዜ፡- ጌታዬ ሆይ! (ነፍስህን) አሳየኝ ወደ አንተ እመለከታለሁና አለ (አላህም) ፡- በፍጹም አታየኝም፣ ግን ወደ ተራራው ተመልከት፤ በስፍራውም ቢረጋ በእርግጥ ታየኛለህ አለው፤ ጌታውም ለተራራው በተገለጸ ጊዜ ንኩትኩት አደረገው፤ ሙሳም ጮኾ ወደቀ፤ በአንሰራራም ጊዜ ጥራት ይገባህ፤ ወዳንተ ተመለስኩ፤ እኔም (በወቅቱ) የምእመናን መጀመሪያ ነኝ አለ።" (ሱረቱል አዕራፍ 7፡143)፡፡

በዚህ አንቀጽ ስር ሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ‹‹የምእመናን መጀመሪያ ነኝ›› እያለ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን፡ ከሱ በፊት የነበሩት እነ፡- ዩሱፍ፣ የዕቁብ፣ ኢስሐቅ፣ ኢስማዒል፣ ሉጥ፣ ኢብራሂም፣ ኑህ... ሙእሚን አልነበሩም ማለቱ አይደለም፡፡ ሊልም አይችልም፡፡ ማለት የተፈለገው ግን፡ ከህዝቦቹ በማመን ቀዳሚው እሱ መሆኑን መግለጹ ነው፡፡ ወይንም ደግሞ በተራራው ላይ የተፈጸመውን አስደናቂ ሁኔታ ከተመለከተ በኋላ፡ አላህ በዚህ ምድር ላይ በፍጹም ሊታይ እንደማይችል ቀድሞ ያመነ እሱ ነው ማለት ነው፡፡ ከሱ ጋር የነበሩት ሰባዎቹ ግን አላህን ካላየነው በስተቀር አናምንልህም ብለውት ነበርና (አል-በቀራህ 5

5-56)፡፡ ይህ መጀመሪያነት ምክንያትን መሰረት ያደረገ እንጂ፡ ሌላ አይደለም፡፡

ለ/ የፊርዐውን ደጋሚዎች፡-

" الْمُؤْمِنِينَ أَوَّلُ كُنَّا أَن خَطَايَانَا رَبُّنَا لَنَا يَغْفِرَ أَن نَطْمَعُ إِنَّا *مُنقَلِبُونَ رَبِّنَا إِلَى إِنَّا ضَيْرَ لَا قَالُوا " الشعراء سورة 51-50

"(እነርሱም) አሉ «ጉዳት የለብንም፡፡ እኛ ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን፡፡ «እኛ የምእምናን መጀመሪያ በመኾናችን ጌታችን ኀጢአቶቻችንን ለእኛ ሊምር እንከጅላለን፡፡»" (ሱረቱ-ሹዐራእ 26፡50-51)፡፡

እነዚህ አስማተኞች በሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም) በኩል የተፈጸመውን የበትርዋን ተአምር ካዩ በኋላ እጅ ሰጡ፡፡ በሙሳና በሀሩን ጌታ አመኑ፡፡ ፊርዐውንም እኔ ሳልፈቅድላችሁ እንዴት ታምናላችሁ በማለት፡ እጅና እግራቸውን አፈራርቆ በመቁረጥ በስቅላት እንደሚቀጣቸው ዛተባቸው፡፡ እነሱም፡- እኛ ወደ አላህ ተመላሾች በመሆናችን የፈለከውን ብታደርግ ምንም ጉዳት የለብንም፡፡ አሁን የምእመናን መጀመሪያ ሆነናልና በማለት ቁርጡን ነገሩት፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ፡- እኛ ‹‹የምእመናን መጀመሪያ ነን›› ሲሉ፡ ምን ማለታቸው ነው? የሚለው ነው፡፡ መቼም ለነሱ መስለም ሙሳ ሰበብ እንደሆናቸው የማይካድ ሐቅ ነው፡፡ ታዲያ እነሱ በአላህ ተውፊቅ (እገዛ)፣ በሙሳ ሰበብ መስለማቸውን እያወቁ ‹‹እኛ የምእመናን መጀመሪያ ነን›› ማለታቸው ትርጉሙ፡- ከፊርዐውን ህዝቦች መካከል ተአምሩ ከተገለጸላቸው በኋላ እውነትን በፍርሀት ሳይደብቁ የመጣው ይምጣ! በማለት ያመኑ ቀዳሚዎች ናቸው ማለት እንጂ፡ ከሰው ዘር ሁሉ የመጀመሪያ አማኝ እነሱ ነበሩ ማለትን በፍጹም አያስይዝም፡፡

ሐ/ በቁርአን የካዱት፡-

" فَاتَّقُونِ وَإِيَّايَ قَلِيلاً ثَمَناً بِآيَاتِي تَشْتَرُواْ وَلاَ بِهِ كَافِرٍ أَوَّلَ تَكُونُواْ وَلاَ مَعَكُمْ لِّمَا مُصَدِّقاً أَنزَلْتُ بِمَا وَآمِنُواْ " البقرة سورة 41

"ከናንተ ጋር ያለውን (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ ሆኖ ባወረድኩትም (ቁርአን) አመኑ፡፡ በርሱም የመጀመሪያ ከሓዲ አትሁኑ፡፡ በአንቀጾቼም ጥቂትን ዋጋ አትለውጡ፡፡ እኔንም ብቻ ተጠንቀቁ፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡41)፡፡

ሱረቱል በቀራህ በመዲና የወረደ ሱራ ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ ላይም እያናገረ ያለው አይሁዶችን ነው፡፡ ቁርአን ተውራትን የሚያረጋግጥ መጽሐፍ ሁኖ ሳለ፡ እናንተ ግን ለምን በቁርአኑ የመጀመሪያ ከሀዲዎች ሆናችሁ? በማለት እየወቀሳቸው ነው፡፡ አይሁዶች ‹የመጀመሪያ ከሀዲ› ተብለው የተገለጹት፡ ስለሳቸው ነቢይነት ዕውቀቱ እያላቸው፡ በመጽሐፋቸውም ምልክቱ ተነግሮ ሳለ፡ እውነቱን ደብቀው ባለማመናቸው ከአህሉል ኪታብ (ከመጽሐፉ ሰዎች) የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚ ከሀዲያን በመሆናቸው ነው፡፡ ከአጠቃላይ ሰው አንጻር ከታየማ፡ በቁርአኑ መጀመሪያ የካዱት በመካ የነበሩት ሙሽሪኩ ቁረይሽ ነበሩ፡፡

ስለዚህ ‹‹መጀመሪያነት›› በሁኔታዎች፣ በጊዜና በአይነት ሊከፋፈል ይችላል ማለት ነው፡፡

መ/ አቡ ሀይደር የመጀመሪያው የፌስቡክ ተጠቃሚ ነው! የሚል ጽሁፍ ብታነቡ፡ ስህተት ነው ብላችሁ ከመቃወማችሁ በፊት ‹መጀመሪያነቱ› ከምን አንጻር ነው ብላችሁ ጥያቄ ማንሳቱ ነው አግባብነቱ፡፡ ፌስቡክ ከተከፈተ ጀምሮ ማለት ነውን? ወይንስ ከኢትዮጵያዊያኖች አንጻር ማለቱ ነውን? ወይንስ ከሙስሊሞቹ በኩል ማለቱ ነው? ወይስ ምን? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡

ነቢዩ ሙሐመድም (ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም) ‹‹የሙስሊሞች መጀመሪያ›› ተብለው መገለጻቸው፡ ይህ መጀመሪያነት ለተላኩበት ማኃበረሰብ (ለዚህ ኡምማ) የመጀመሪያው ብርሀን ሰንጣቂ ነቢይ በመሆናቸው እንጂ፡ ከአጠቃላይ የሰው ዘር አንጻር አይደለም፡፡ ከሳቸው በፊት የነበሩት ነቢያት ሁሉ ሙስሊሞች ነበሩና!!! አላህ የበለጠውን ዐዋቂ ነው፡፡

ወሰላሙ ዐለይኩም ወራሕመቱላሂ ወበረካቱሁ።

10.የጾም ትርጉም

ጾም በኢስላም ያለው ትርጉም፡ ጎሕ ከቀደደበት ሰዓት ጀምሮ፣ ፀሐይ እስክትጠልቅ (የመግሪብ ሠላት አዛን የሚባልበት ወቅት) ድረስ ከምግብ፣ ከመጠጥ፣ ከግብረ ስጋ ግንኙነትና ከሌሎችም ጾምን ከሚያበላሹ ነገሮች እራስን በመቆጠብና በማገድ አላህን መገዛት ነው::

የረመዳን ፆምን እንድንፆም ማነው ያዘዘን? ማስረጃውስ ምንድነው?

☞ብዙ ክርስቲያን ወገኖቻችን እናንተ ሙስሊሞች እኮ የረመዳን ፆም ማንም ሳያዛችሁ በራሳችሁ ነው የምትፆሙት በማለት ይሞግቱናል።

C⋆ የረመዷን ፆም እንድንፆም መታዘዛችን የሚያሳዩ መረጃዎች ከቁርአን እና ከሃዲስ እንመልከት C⋆

ረመዷንን መጾም በቁርዓን፣ በሐዲስ እና በዑለሞች ስምምነት(ኢጅማዕ) ግዴታ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

ከቁርዓን ብንጀምር፡- አላህ እንዲህ ይላል፡-

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት(ሕዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ(ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና። (አል-በቀራህ 183)

شَهۡرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلۡقُرۡءَانُ هُدٗى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٖ مِّنَ ٱلۡهُدَىٰ وَٱلۡفُرۡقَانِۚ فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهۡرَ فَلۡيَصُمۡهُۖ

“(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች(አንቀጾች) ሲኾን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው። ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይፁመው።”(አል-በቀራህ 185)

ወደ ሐዲስ ስንዞር ደግሞ ተከታዩን የነብዩ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ንግግር እናነኛለን፡-

بني الاسلام على خمس شهادة : أن لا إله إلا الله ، وأن محمدا رسول الله ، وإقام الصلاة ، وإيتاء الزكاة ، وصيام رمضان وحج ، ” . البيت

“እስልምና በአምስት ማእዘኖች ተገንብቷል። ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩን እና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን በመመስከር ላይ፣ ሶላትን በመስገድ፣ ዘካን በመስጠት፣ ረመዷንን በመጾም እና በቤቱ ሐጅ በማድረግ።”

የረመዷንን ወር መጾም ግዴታ በመሆኑ ላይ ሙስሊሞች ሁሉ ይስማማሉ።የኢስላም አንዱ ማዕዘን በመሆኑም ላይ ልዩነት የለም። ይኸውም ከዲን እንደሚቆጠር በተለምዶ የሚታወቅ (አል-ማዕሉም ቢደሩራ) በመሆኑ እርሱን ያስተባበለ ይከፍራል፤ ከሃዲም ይባላል።የረመዷን ግዴታነት የተደነገገው ሰኞ ዕለት ከሻዕባን ወር ሁለት ቀን ቀርቶት ከሂጅራ ቡኋላ ሁለተኛው ዓመት ላይ ነው።

ምንጭ፡- ሰዩድ ሳቢቅ- “ፊቅህ አስ-ሱና”

Al-Baqarah 2:185

عَلَىٰ أَوْ مَرِيضًا كَانَ وَمَن فَلْيَصُمْهُ ٱلشَّهْرَ مِنكُمُ شَهِدَ فَمَن وَٱلْفُرْقَانِ ٱلْهُدَىٰ مِّنَ وَبَيِّنَٰتٍ لِّلنَّاسِ هُدًى ٱلْقُرْءَانُ فِيهِ أُنزِلَ ٱلَّذِى رَمَضَانَ شَهْرُ تَشْكُرُونَ وَلَعَلَّكُمْ هَدَىٰكُمْ مَا عَلَىٰ ٱللَّهَ وَلِتُكَبِّرُوا۟ ٱلْعِدَّةَ وَلِتُكْمِلُوا۟ ٱلْعُسْرَ بِكُمُ يُرِيدُ وَلَا ٱلْيُسْرَ بِكُمُ ٱللَّهُ يُرِيدُ أُخَرَ ۖ أَيَّامٍ مِّنْ فَعِدَّةٌ سَفَرٍ

The month of Ramadhan [is that] in which was revealed the Qur'an, a guidance for the people and clear proofs of guidance and criterion. So whoever sights [the new moon of] the month, let him fast it; and whoever is ill or on a journey - then an equal number of other days. Allah intends for you ease and does not intend for you hardship and [wants] for you to complete the period and to glorify Allah for that [to] which He has guided you; and perhaps you will be grateful.

(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲኾን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፡፡ ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው፡፡ በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት፡፡ አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በእናንተም ችግሩን አይሻም፡፡ ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህን ደነገግንላችሁ)።እውነትን ለሚሻ ሰው አንድ ማስረጃ በቂው ነው ፣ በተቃራኒው ደግሞ 1000 ማስረጃ ብታቀርብለት አይቀበልህም።

አላህ(ሱወ) ቀጥተኛውን መንገድ ይምራን።

የረመዳን ወር በላጭነት

የረመዳን ወር፣ በኢስላማዊው ቀመር ዘጠነኛው ወር ነው፡፡ ረመዳን ዓመቱ ወራት ሁሉ በላጩ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ከተቀሩት ወራት በበርካታ ነገሮች አልቆታል፡፡ ከነዚህ ብልጫዎች መካከል የሚከለተሉት ይገኙበታል፡፡

1. አላህ (ሱ.ወ) የተከበረውንና እጅግ የላቀውን መጽሐፍ -

ቁርኣንን- በውስጡ በማውረድ የመረጠው ወር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡፡-

‹‹(እንድትጾሙ የተፃፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ፣ ከቅን መንገድና (ውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲሆን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፡፡ ከናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው፡፡››(አል በቀራ 185)

2. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ረመዳን ሲገባ የጀነት በሮች ይከፈታሉ፤ የጀሀነም በሮች ይዘጋሉ፤ ሰይጣናት ይታሰራሉ ፡›› (አል ቡኻሪ 3103/ ሙስሊም 1079) አላህ (ሱ.ወ) መልካምን በመሥራትና ከመጥፎ በመራቅ ባሮቹ ወደርሱ የሚመለሱበትን ሁኔታ አመቻችቷል፡፡

3. ቀኑን የጾመና ሌሊቱን በመስገድ ቆሞ ያሳለፈ ሰው ያለፉት ወንጀሎቹ ይማሩለታል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በእምነትና አላህ ዘንድ ያለውን ምንዳ በማሰብ የረመዳንን ወር የጾመ፣ ቀደም ሲል የሠራው ወንጀል ይማርለታል፡፡›› (አል ቡኻሪ 1910 /ሙስሊም 760)

‹‹በእምነትና አላህ ዘንድ ያለውን ምንዳ በማሰብ በረመዳን ወር (ተራዊሕና ተሃጁድን በመስገድ) የቆመ ሰው ቀደም ሲል የሰራው ወንጀል ይማርለታል፡፡›› (አል ቡኻሪ 1905/ ሙስሊም 759)

4. በረመዳን ውስጥ የዓመቱ ትልቅ ሌሊት ይገኛል፡፡ ይህች ሌሊት አላህ (ሱ.ወ) በመጽሐፉ፣ በዚች በርሷ ውስጥ የሚሠራ መልካም ሥራ፣ ለረኸም ዓመታት ከሚሠራ መልካም ሥራ እንደሚሻልና እንደሚበልጥ የተናገረላት ነች፡፡ አላህ (ሱ.ወ):-

‹‹መወሰኛይቱ ሌሊት ከሺህ ወር በላጭ ናት፡፡›› ብሏል (አል ቀድር 3) እናም ይህችን ሌሊት በእምነትና አላህ ዘንድ ያለውን ምንዳ በማሰብ በመስገድ ቆሞ ያሳለፈ ሰው ቀደም ሲል የሰራው ወንጀል ይማርለታል፡፡ እርሷ በረመዳን ወር በመጨረሻዎቹ አስርት ሌሊቶች ውስጥ የምትገኝ ነች፡፡ ይህችን ሌሊት፣ ማንም ሰው በእርግጠኝነት በዚህ ዕለት ትሆናለች ብሎ መወሰንና መናገር አይችልም፡፡

የጾም ሚስጥር

አላህ ሱ.ወ፣ በበርካታ ዓለማዊና መንፈሳዊ ምክንያቶች ጾምን ግዴታ አድርጓል፡፡ከነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል

1 ✡ የአላህን ፍራቻ ማጽናት

ጾም፣አንድ ባሪያ የሚወዳቸውን ነገሮች ወይም ፍላጎቶቹን በመተው፣ ስሜቱን በመጫን፣አላህን የሚገዛበት አምልኮ በመሆኑ፣ በሁሉም ስፍራና ወቅት፣ በድብቅም ሆነ በይፋ ነፍሱን በአላህ ፍራቻ እንዲያንጽና የአላህን ምርመራ እንዲያስተነትን ያደርገዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)፡- ‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡›› ብሏል (አል በቀራ 183)

2 ✡ ከወንጀልና ከሃጢኣት በመራቅ ላይ ስልጠና ወይም ልምምድ መስጠት

አንድ ጾመኛ ሐላል ነገሮችን በመከልከል የአላህን ትዕዛዝ ማክበር ከቻለ፣ የወንጀልና የሀጢኣት ስሜቱን በመለጎሙና አላህ ከገደበው ወሰን በመጠበቁ፣ በስህተት ላይ ባለመዘወተር የበለጠ ቻይ ይሆናል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹የሐሰት

ንግግርንና በሱም መሥራትን ያልተወ ሰው፣ አላህ (ሱ.ወ) ምግብና መጠጡን ከመተዉ ጉዳይ የለውም፡፡›› (አል ቡኻሪ 1804) ውሸት ማውራትና በውሸት መሥራት ያልተወ ሰው፣ ለጾም የተደነገገለትን ዓላማ በስራ ላይ አላዋለም ማለት ነው፡፡

3 ✡ ችግረኞችን ማስታወስና መደገፍ

ጾም፣ የተራቡና የተቸገሩ ሰዎችን ሕይወት የሚካፈሉበትና ዓመቱን ሙሉ በችግርና በሰቆቃ የሚያሳልፉትን ድሆች ሁኔታ የሚያስታውሱበት የአምልኮ ዘርፍ ነው፡፡ ትክክለኛ የአላህ ባሪያ፣ ድሃ ወንድሞቹ ምን ያህል በረሃብና በጥማት እንደሚቸገሩ ያስታውሳል፣በመሆኑም ለነርሱ የእርዳታ እጁን በመዘርጋት የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

የጾም ትሩፋት

ጾም በኢስላማዊው ሕግ የተደነገጉ በርካታ ትሩፋቶች አሉት። ከነዚህም መካከል፡-

1. በአላህ አምኖ፣ ትዕዛዙንም አክብሮ፣ በረመዳን ትሩፋት ዙሪያ የተላለፉ ጉዳዮችን እውነት ብሎ ተቀብሎ እንዲሁም አላህ ዘንድ የሚያገኘውን ምንዳ በመከጀል ረመዳንን የጾመ፣ ቀደም ሲል የሰራው ወንጀሉ ይማርለታል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ረመዳንን፣ በአላህ አምኖ የሚያስገኝለትን ምንዳ አስቦና ከጅሎ የጾመ ሰው ቀደም ሲል የሰራው ወንጀል ይማርለታል።›› (አል ቡኻሪ 1910 / ሙስሊም 760)

2. ጾመኛ፣ ከአላህ ጋር ሲገናኝ በመጾሙ ምክንያት በሚያገኘው ላቅ ያለ ምንዳና ጸጋ ይደሰታል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡

‹‹ጾመኛ ሁለት ደስታዎች አሉት። በሚያፈጥርበት ጊዜ የሚደሰተውና ከጌታው ጋር ሲገናኝ የሚደሰተው ደስታነው።››(አል ቡኻሪ 1805 /ሙስሊም 1151)

3. በጀነት ውስጥ ከጾመኞች በስተቀር ማንም የማይገባበት የሆነ ረያን የሚባል በር አለ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በጀነት ውስጥ ረያን የሚባል በር አለ። የትንሳኤ ቀን ጾመኞች ይገቡበታል። ከነርሱ ሌላ ማንም በርሱ በኩል አይገባም። የት አሉ ጾመኞች? ይባላል። ወዲያውም እነሱ ወደርሱ ይነሳሉ። ከነርሱ ሌላ ማንም በርሱ በኩል አይገባም። እነሱ ገብተው ሲያበቁ ይዘጋል። ማንም በሱ በኩል አይገባም።›› (አል ቡኻሪ 1797/ ሙስሊም 1152)

4. አላህ (ሱ.ወ) የጾምን ምንዳ ወደራሱ አስጠግቶታል። እናም ከፍያውና ምንዳው፣ ከቸሩ፣ ከለጋሱና ከኃያሉ ጌታ ዘንድ የሆነለት ሰው ሊደሰት ይገባል። አላህ ባዘጋጀለትም ሽልማት ይበሰር። አላህ (ሰ.ወ) በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንደበት ሲነግረን፡-

‹‹ፆም ሲቀር ሁሉም የአደም ልጆች ስራ ለራሳቸው ነው፤ እርሱ ግን የኔ ነው ምንዳውን የምከፍለው እኔው ነኝ።›› ይላል። (አል ቡኻሪ 1805 /ሙስሊም 1151)

ጾምን የሚያበላሹ ነገሮች

ጾምን የሚያበላሹ ነገሮች፣ አንድ ጾመኛ ሊከለከላቸውና ሊቆጠባቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

1. መብላትና መጠጣት፡- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ከነህ የቸነው ነጩ ክርም ከጥቁሩ ክር (ከሌሊት ጨለማ) ለናንተ እስከሚገለጽላችሁ ድረስ ብሉ ጠጡም ከዚያም ጾምን እስከ ሌሊቱ ድረስ ሙሉ።›› (አል በቀራ 187) ረስቶ የበላ ወይም የጠጣ ሰው ጾሙ አይበላሽም፤ ወንጀልም የለበትም። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡- ‹‹ጾመኛ መቸኑን ረስቶ የበላ ወይም የጠጣ ሰው ጾሙን ይቀጥል። ያበላውና ያጠጣው አላህ ነው።›› ብለዋል። (አል ቡኻሪ 1831/ሙስሊም 1155)

2. ምግብንና መጠጥን የሚተካ ነገር፡

በሰውነት ውስጥ የተጓደለን የጨውና የምግብ መጠን ለመጠገን የሚወሰዱ ምግብ ነክ የሆኑ መርፌዎችና መድሃኒቶች ጾምን ያፈርሳሉ። ምክንያቱም የምግብና የመጠጥን ቦታ ስለሚተኩ፣ በምግብና መጠጥ ላይ ያለፈው ሕግ ይመለከታቸዋል።

ለህመምተኛ የሚሰጥ ደም፡፡ ምክንያቱም ደም የምግብና የመጠጥ የመጨረሻው መዳረሻ በመሆኑ ነው፡፡ በማንኛውም መልክ ማጨስ፡፡ ጭስን ወደ ሰውነት እያማጉ ማስገባት፣ ሰውነትን በመመረዝ እንዲጠናከር ያደርገዋል፡፡

3. የፍቶት ጠብታ ቢፈስም ባይፈስም፣ የወንዱ ብልት በሴቲቷ ብልት ውስጥ እንዲሰምጥ በማድረግ የተፈፀመ ግብረ ስጋ ግንኙነት

4. በፍላጎትና በምርጫ በመተሻሸት ወይም በእጅ በማባበልና በመሳሰሉት መንገዶች የፍቶት ጠብታን (የዘር ፍሬ ፈሳሽን) ማፍሰስ በእንቅልፍ ልብ የሚከሰት የዘር ፍሬ መፍሰስ ጾምን አያበላሽም፡፡አንድ ሰው ጾምን የሚያበላሹ ነገሮችን እንዳይፈጽም መጠንቀቅና ስሜቱን መቆጣጠር የሚችል ከሆነ ሚስቱን መሳም ይችላል፡፡

5. አውቆ ማስታወክ፡

ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መልኩ ትውከት በራሱ ከወጣ ጾምን አያፈርስም፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-‹‹ትውከት ያሸነፈው ጾመኛ፣ ጾሙን መክፈል አይጠበቅበትም፡፡ በፈቃዱ ያስታወከ ሰው ጾሙን ይክፈል፡፡›› (አል ቲርሚዚ 720 /አቡ ዳውድ 2380)

6. የወር አበባና የወሊድ ደም መፍሰስ፡፡

የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም በቀኑ የመጨረሻ ክፍል ላይም ቢሆን ከፈሰሰ ሴቷ ጾሟ ይበላሻል፡፡ በሌላም በኩል፣ በወር አበባ ደም ላይ ቆይታ ጎሕ ከፈነጠቀ በኋላ ብትጸዳና የዚያን ቀን ብትጾም፣ ጾሟ ትክክል አይሆንም፡፡ ያንን ቀን መጾም የለባትም፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹የወር አበባ ላይ በምትሆንበት ጊዜ አትሰግድም አትጾምም አይደል እንዴ?›› (አል ቡኻሪ 1850)

አንዲት ሴት ከተለመደው የወር አበባና የወሊድ ደም ውጭ በበሽታ ምክንያት ደም የሚፈሳት ከሆነ ከመጾም አትከለከልም፡፡

አላህ እንዳይጾሙ ፍቃድ የሰጣቸው ሰዎች አላህ (ሱ.ወ) ከሰዎች መካከል ለተወሰኑ ሰዎች በረመዳን ወር አለመጾም እንዲችሉ ፍቃድ ሰጥቷል፡፡ ይህንንም ያደረገው ለነርሱ ከማዘን፣ ከማግራትና ከማቅለል አንፃር ነው፡፡ እኚህ ሰዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1.በመጾሙ የሚጎዳ ታማሚ፡-

ለርሱ ማፍጠር ይፈቀድለታል፡፡ከረመዳን በኋላ ሲሻለው ያፈጠረውን ይከፍላል፡፡ .

2. በሽምግልና ወይም ይድናል ተብሎ በማይከጀል በሽታ ምክንያት

መጾም የማይችል ደካማ ማፍጠር ይፈቀድለታል፡፡ ለእያንዳንዱ ቀን አንድ ሚስኪን ያበላል፡፡ ይሽውም፣ በሀገሩ ከሚበላ የምግብ ዓይነት አንድ ኪሎ ተኩል በመስጠት ይሆናል፡፡

3. ተጓዥ መንገደኛ በጉዞው ላይ እያለ ከአራት ቀን ለማይበልጥ ጊዜ ሲያርፍ ማፍጠር ይችላል፡፡ ያንን ጾም የፈታበትን ቀን ከረመዳን በኋላ ሀገሩ ሲመለስ ይከፍላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

‹‹በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት፡፡ አላህ በናንተ ገሩን (ይሻል) በናንተም ችግሩን አይሻም፡፡›› (አል በቀራ 185)

4. የወር አበባና የወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች፡፡ በነኚህ ሁለት ሁኔታዎች ላይ ያሉ ሴቶች መጾም በነሱ ላይ እርም ነው፡፡ መጾማቸው ትክክለኛ አይደለም፡፡ ከረመዳን በኋላ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡ (ገጽ፣ 96 ተመልከት)

«እስልምናን ለክርስቲያኑ»

«እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩን እወቅ»(ሙሐመድ 19)

«ከሁሉ በፊት አምላክ አንድ መሆኑንና እርሱም ሁሉን ነገር የፈጠረና ያዋቀረ ያልነበረውን ነገረ ሁሉ እንዲኖር ያደረገውን አመንኩ» "ነገር ግን አላህ ውለታ ዋለላችሁ፤ ወደ እምነትም መራችሁ" ቁርአን(49፥17)

እምነት የምንለው፡- በአላህና በመልዕክተኞቹ በመላዕክት በመጽሐፍቶቹ በምጽዓት ቀን እንዲሁም ደግም ክፉ ከአላህ ዘንድ ነው ብሎ ማመን ነው።

1, እርሱ አላህ

፧የሰላም ባለቤት ነው «እርሱ አላህ ነው ያ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ ንጉሡ ከጉድለት ሁሉ የጠራው የሰላም ባለቤቱ ጸጥታን ሰጪው ባሮቹን ጠባቂው አሸናፊው ኃያሉ ኩሩው ነው።» (አል-ሐሸር 23)

፧የሩቅ ሚስጥራት ቁልፍ እርሱ ዘንድ ነው «የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም። »(አል-አንዓም 59)

፧እርሱ ቁርዓንን ያወረደ ነው «ቁርዓንንም ለሰዎች በዝግታ ታነብላቸው ዘንድ ከፋፈልነው። ቀስ በቀስም አወረድነው።» (አል-ኢስራእ 106)

፧ለእርሱም ሚስትም ልጅም የለውም «እነሆ የጌታችን ክብር ላቀ ሚስትንም ልጅንም አልያዘም።» (አል-ጂን 3)

፧እርሱ ቅርብ ነው «ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው)፡- እኔ ቅርብ ነኝ። የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ። » (አል-በቀራህ 186)

፧እርሱ ጸጸትን ተቀባይ ነው «ይጸጸቱ ዘንድ ወደ ጸጸት መራቸው። አላህ እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና» (አል-ተውባ 118)

፧እርሱ ሰውን የፈጠረ ነው «አንድ ሆኖ ከፈጠርኩት ሰው ጋር ተወኝ።» (74፡11)

፧እርሱ ዝናም የሚያወርድ ነው «እርሱ ያ ተስፋ ከቆረጡ በኋላ ዝናምን የሚወርድ ነው።» (42፡28)

፧እርሱ መከራን የሚያስወግድ ነው «ያ ችግረኛን በለመነው ጊዜ የሚቀበል መከራንም የሚያስወግድ ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን?» የለም(27፡62)

፧እርሱ ወደ ቀጥተኛ መንገድ መሪ ነው «አላህም እነዚያን ያመኑትን ወደ ቀጥተኛው መንገድ በእርግጥ መሪ ነው።» (22፡54

፧እርሱ የማይመገብ ሲሆን ይመግባል «ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ከሆነው አላህ እርሱ የሚመግብ የማይመገብም ሲሆን ሌላን አምላክ እይዛለሁን? በላቸው . . .»(አል-አንአም 14)

፧እርሱ ማንገላጀት ሆነ እንቅልፍ የለበትም «አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም ህያው ራሱን ቻይ ነው ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም።»(አል-በቀራህ 255)

፧እርሱ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም «አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም»(2፡286)

፧እርሱ መረጋጋትን የሚያሰፍን ነው «አላህ በመልእክተኛው ላይ መረጋጋትን አሰፈነ»(9፡26)

፨እርሱ ጸጋው የማይቆጠር ነው፡- «የአላህን ጸጋዎች ቆጥራችሁ አትዘልቋቸውም»(16፡18)

እኔም የአላህን ሱብሃነሁ ወተአላ ባህሪያት መግለጹን ገታ ላድርገው።

2, መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ)

፨የዓለም መልእክተኛ ናቸው «(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፡- እናንተ ሰዎች ሆይ እኔ ወደ እናንተ ወደ ሁላችሁም የአላህ መልእክተኛ ነኝ»(አል-አእራፍ 158)

፨በትንቢት የታወቁ ናቸው «እነዚያ መጽሐፍን የሰጠናቸው ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል።(አል-አንአም 20)

፨ቁርዓንን ተቀብለዋል «ቁርዓንን ባንተ ላይ እንድትቸገር አላወረድንም»(20፡2)

፨ሁሌም ይታወሳሉ «መወሳትህንም ላንተ ከፍ አድርገንልሃል።»(አል-ኢንሽራህ 4)

፨ሸክሞችን ያራግፋል «ሸክማቸውን ያራግፍላቸዋል፤ የተጫናቸውን ቀንበርም ያወርድላቸዋል።»(7፡157)

፨የዓለማት እዝነት ናቸው «(ሙሐመድ ሆይ) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጂ አልላክንህም» (አንቢያእ 107)

፨ብርሃን ለጋሽ መብራት ናቸው «ወደ አላህም በፈቃዱ ጠሪና አብሪ ብርሃንም (አድርገን ላክንህ)።» (33፡46)

፨መጻፍም ማንበብ የሚችሉ አልነበረም «ከርሱ በፊትም መጽሐፍን የምታነብ በቀኝህም የምትጽፍ አልነበርክም ያን ጊዜ አጥፊዎቹ በእርግጥ በተጠራጠሩ ነበር።» (አል-አንከቡት 48)

፨የነቢያት መደምደሚያ መሆናቸው «ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም ግን የአላህ መልእክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው።» (አል-አህዛብ 40)

፨ስለ ጸባያቸው «አንተ በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ»

፨ነቢዩ እውነተኛ ናቸው «ነቢያች (ሙሐመድ) አልተሳሳተም አልጠመመም።» (አል-ነጅም 2)

፨እጃቸው «ከነቢዩ መዳፍ የለሰለሰ ሐር ወይም ሌላ ጨርቅ ነክቼ አላውቅም።።»

፨ሽታቸው «ከአላህ መልእክተኛ ሽታ ይበልጥ የሚያውድ ሽቶ፤ ሚስክ ወይም አንበር አሸትቼ አላውቅም።» (አል ኹላሰቱ ሲየር ገጽ19-20)

፨ጥርሶቻቸው «ሁለት የፊት ጥርሶቻቸው ፍንጭት ናቸው። ሲናገሩ በነርሱ በኩል ብርሃን የሚያልፍ ይመስላል።»

፨ፊታቸው «ነቢዩ ሲደሰቱ ፊታቸው የጨረቃ ቁራጭ እስኪመስል ድረስ ያበራል።»

፨ፀጉራቸው «በመጀመሪያ አካባቢ ጸጉራቸውን ይለቁ ነበር። በኋላ ላይ ግን መክፈል ጀመሩ።»

፨ቁመታቸው «በጣም ረዥም ወይም አጭር አይደሉም። ቁመታቸው መካከለኛ ነው።

፧አይናቸው «የአይናቸው ጥቁረት የበረታ»

፧ንግግራቸው «ንግግራቸው በስርዓት የተዋቀረ ምጥንና የተሟሏ » ነበር (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም)

ማጣቀሻ

© አል-ቁርዓኑል ከሪም

© አኽላቀ ረሱል

© ረሒቀል መኽቱም

© የምን ሐዘን

© ላለመደናገር ማመሳከር

© የሐመረ ተዋህዶ ቅጥፈት በእስልምና እውነት

By ☞ ousman abdulfeta

11.. ኢትዮጵያችን

የክርስትና አመጣጥ በክርስትያን እይታ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩኅ እና በጣም አዛኝ በሆነው።

የአላህ ሰላምና እዝነት በመጨረሻው ነቢይ ላይ ይሁን። እንዲሁ የሐቅን ጎዳና በተከተሉት ሁሉ ላይ። እንደሚታወቀው ክርስትና ሲነሳ አንድ ላይ የሚወሳው የኢየሱስ (ዐ.ሰ) ስቅለት ነው። ይህ ማለት ክርስትናና ስቅለት የማይነጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ክርስትና በጠላት የወጣ ስያሜ ሲሆን ይህ ስያሜውን አሜን ብለው የተቀበሉት በኢየሱስ ላይ ድንበር ያለፉት አምላኪዎቹ ናቸው።

ሐዋሪያት እምነታቸው እንዲህ ነበር፦ «ሐዋሪያት ፡- እኛ የአላህ ረዳቶች ነን፤ በአላህም አምነናል፤ እኛም ትከክለኛ ታዛዦች መሆናችንን፥ መስክር፥ አሉ።» (አል-ኢምራን 52)

« ወደ_ሐዋርያትም በኔና በመልክተኛዬ እመኑ በማለት ባዘዝኩ ጊዜ (አስታውስ) አመንን፤ እኛም እስላሞች መሆናችንን መስክር አሉ።» (አል-ማዒዳህ 111)

በመሆኑም ሐዋሪያት ሆነ ኢየሱስ የአላህ ሰላም በርሱ ላይ እና ቅን ጎዳና በተከተሉት ሁሉ ላይ ይሁንና መንገዳቸው አንድና ቀጥተኛው የሆነው እስልምና ነው። ይህን ስያሜም ያገኘው ከጠላቶቹ ሳይሆን ከአምላካችን ከጌታ ከአላህ ዘንድ ነው። የአብረሃም የይስሃቅ የያእቆብ አምላክ የሆነው መንገድ ነው እነርሱም የተከተሉት የታዘዙለት።

«እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን፣ ወደ አንተም አወረድን፤ ወደ ኢብራሂምም፣ ወደ ኢስማዒልም፣ ወደ ኢስሐቅም፣ ወደ ያዕቆብም፣ ወደ ነገዶቹም ወደ ዒሳም፣ ወደ አዮብም፣ ወደ ዩኑስም፣ ወደ ሀሩንና ወደ ሱለይማንም አወረድን፤ ለዳዉድም ዘቡርን ሰጠነው።» (አል-ኒሳእ 163)

ወደ ተነሳንበት ነጥብ ስንመለስ ክርስትና ስያሜውን ያገኘው ከጠላቶቻቸው ሲሆን ይህም የሚያስረዳን ኃይማኖቱ መጤና ከጊዚያዊነቱ ጋር የተቆራኘ ነው። እንደ እስልምና ስር መሰረቱ ይዞ የመጣ መንገድ ሳይሆን በሆነ ከፍለ ዘመን ላይ አንድን ክስተት ዋቢ በማድረግ የበቀለ እንክርዳድ መንገድ መሆኑ ልብ ይሏል።

እንደ ክርስትና እምነት ተከታዮች ለክርስትና መመስረት ዋነኛ ተጠያቂ የሚደርጉት የኢየሱስን ስቅለት ጉዳይ ሲሆን።

እንዲህም ሲሉ ይተቻሉ ፡-

«ለምን አላህ በኢየሱስ ቦታ ሌላ ሰው እንዲሰቀል በማድረግ ክርስትና እንዲመሰረት አደረገ» ሲሉ በየጊዜው ጥያቄ ያነሳሉ።

ልብ በሉ ክርስትና የተመሰረተው እንደነርሱ አባባል ከኢየሱስ ስቅለት ከተባለው ጊዜ ጀምሮ ነው ማለት ነው። ይህ ማለት ይህን ሐይማኖት (ክትስትናን) የሰበከ አንድም ነቢይ የለም ኢየሱስም(ዐ.ሰ) እራሱ ክርስትናን አልሰበከም ማለት ነው።ክርስትናን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱም አያውቀውም የክርስትና ሀይማኖት የተመሰረተው ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ ከ300 አመታት በሁዋላ በጳውሎስና በባርናባስ አማካኝነት ነው። ማስረጃችንም እነሆ

25 በርናባስም ጳውሎስን ሊፈልግ ወደ ጠርሴስ መጣ፤

26 ባገኘውም ጊዜ ወደ አንጾኪያ አመጣው። በቤተ ክርስቲያንም አንድ ዓመት ሙሉ ተሰበሰቡ፥ ብዙ ሕዝብንም አስተማሩ፤ ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ #ክርስቲያን_ተባሉ። (የሐዋሪያት ስራ 11:26)

ባይሆንማ እንዲህ አይነት ጥያቄ ባልጠየቁና ባልተወዛገቡ ነበር። «እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት፣ ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤» (አል-ኒሳእ 157)

እነርዚህን ጥያቄዎች አስተውሏቸው፡-

1, ክርስትና የተመሰረተው ከስቅለቱ በኋላ ከሆነ የሰዎች የፈጠራ ኃይማኖት(መንገድ) እንደሆነ አታስተውሉምን?

2, ወደ ያዕቆብና ነገዶቹ እንዲሁም ወደ ሚሳ(ኢየሱስ) በተወረደው ማመን? ወይስ ስቅለቱን ተከትሎ አዲስ ኃይማኖት መፍጠሩ ነው ትክክል?

3, ክርስትና የሚባለው (እንደ እናንተ እምነት) ስቅለቱ ነው ማለት ነው ?

ክርስትና መመስረት የሰዎች ፍላጎትና ሃሳብ እንዲሁ ድርጊት ሲሆን አምላካችን አላህ ይህን ኃይማኖት ከመፈጠር አያግደውም።

ማንኛውም የሰው ልጅ ነጻ ምርጫ እስካለው ድረስ አላህ ትክክለኛውን ጎዳና ካመላከተ በኋላ ማመን መካድ የፈለገውን ፈጥሮ የመከተል ለሰውየው የተተወ ድርሻ ነው። «ቅኑን መንገድ መግለፅ በኛ አለብን።»(ሱረቱል-ለይል 12)

«አስታዉስም: አንተ አስታዋሽ ብቻ ነህና። በእነርሱ ላይ ተቧሚ (አስገዳጅ) አይደለህም።»(ሱረቱል- ጋሺያህ 21-22)

«እውነቱም፥ ከጌታችሁ ነው፤ *የፈቀደም ሰው* وَمَنْ شَاءَ يمን፤ *የፈቀደም ሰው* وَمَنْ شَاءَ ይካድ፣ በላቸው፤» (አል-ካህፍ 29)

የክርስትና መመስረት ተጠያቂው መስራቹና ተከታዩ ነው። የሐዋሪያት እምነት እስልምና እንደነበረና ለአላህ ታዛዦች መሆናቸውን መስክረዋል ይህን ምስክርነታቸው በኢየሱስ ፊት አስረግጠዋል።ኢየሱስ ያስተማረው ይህንኑ ሆኖ ሳለ ሌላውን ተጠያቂ ማድረግ የዋህነት አይሆንምን?

«ከተዉራትም ከኔ በፊት ያለዉን ያረጋገጥሁ ስሆን የዚያንም በናንተ ላይ እርም የተደረገዉን ከፊል ለናንተ እፈቅድ ዘንድ፥ (መጣኋችሁ) ከጌታችሁም በሆነ ታምር መጣሁዋችሁ አላህንም ፍሩ፤ ታዘዙኝም። አላህ ጌታየና ጌታችሁ ነዉ፤ ስለዚህ ተገዙት፤ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነዉ (አላቸዉ)።»(አል-ዒምራን 50-51)

«አልመሲሕም አለ፡- የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ፤ እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ፤ መኖሪያውም እሳት ናት፤ ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም።(አል-ኒሳእ 72)

ያላስተማረውን ያፈነገጠ ትምህርት ከተከተሉ በኋላ ወየውልኝ እከሌ እከሌ ነው ያጠመመኝ ብትል ማንስ ዞር ብሎ ያዳምጥህ መሰለህ?

«አላህም፡- የመርየም ልጅ ሚሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን? በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፤ ጥራት ይገባህ፤ ለኔ_ተገቢዬ_ያልሆነን_ነገር_ማለት_ለኔ_አይገባኝም ፤ ብዬው እንደሆነም በእርግጥ

አውቀኸዋል፤ በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፤ ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም፤ አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና ይላል።» (አል-ማዒዳህ 116)

አሁንም ቢሆን ጊዜ አላችሁ ሳይረፍድ ጥርት ባለ ንስሃ ከተመለሳችሁ ጌታችን አላህ ወንጀላችሁን ምሮ የገነት ጓድ ሊደርጋችሁ በእርግጥ ቻይ ነው።

«እነዚያ ያመኑ እነዚያም ይሁዳውያን የኾኑ፣ ክርስቲያኖችም፣ ሳቢያኖችም (ከእነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ መልካምንም ሥራ የሠራ ለነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው፡፡ በነርሱም ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም፡፡» (አል-በቀራህ 62)

«እነዚያ (ከመደበቅ) የተጸጸቱና (ሥራቸውን) ያሳመሩም (የደበቁትን) የገለጹም ብቻ ሲቀሩ፡፡ እነዚህም በነሱ ላይ (ጸጸታቸውን) እቀበላለሁ፤ እኔም ጸጸትን በጣም ተቀባይ አዛኙ ነኝ፡፡» (አል-በቀራ160)

«እነሆ እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡» (አል-በቀራ 54)

«እላንተ ሰዎች ሆይ! መልክተኛው እውነትን ከጌታችሁ አመጣላችሁ እመኑም ለናንተ የተሻለ (ይሆናል) ብትክዱም አትጎዱትም፤

በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነውና፤ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው።» (አል-ኒሳእ 170)

«የመጽሐፉም ባለቤቶች ባመኑና (ከክሕደትም) በተጠነቀቁ ኖሮ ከእነሱ ኃጢያቶቻቸውን በእርግጥ ባበስንና የመጠቀሚያ ገነቶችንም በእርግጥ ባገባናቸው ነበር።»(አል-ማዒዳህ 65) አላህ የበለጠውን ያውቃል!

~~እስልምናና ክርስትና (ኦርቶዶክስ) በኢትዮጵያ~~

ኢትዮጵያውን ሙስሊሞች ከአረቦች ቀድመን ነው ኢስላምን የተቀበልነው። ከመካ ቀጥሎ መዲና ሳይገባ እስልምና ሐበሻ ነው የገባው። ሁሉም ሙስሊም ሃገራችንን ኢትዮጵያን ይወዳል። ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ደግሞ ከማንም የበለጠ በአገሩ ይኮራል።

እርግጥም ሁሉም ነብያቶች ሙስሊሞች እንደነበሩ የታወቀ ጉዳይ ነው። ሆኖም ሙስሊም ያልሆኑ ቡድኖች ወይም ደግሞ ግለሰቦች ይህን ሃቅ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ እንደሚያስተባብሉት ሃገር ያወቀው ፀሃይ የሞቀው ጉዳይ ነው።

በርግጥ ነብያቶች ሁሉ ሙስሊሞች ነበሩን? አዎ እንዴታ!!! ምክንያቱም ኢስላም የሚለው ፍች ትርጉሙም እራስን ለፈጣሪ ፈቃድ ማስገዛት ማለት ነው በእንግሊዝኛው (submission to the will of God, Allah) ማለት ሲሆን እንግዲህ በዚህ ዩኒቨርስ ላይ ያለ ማንኛውም ፍጡር በአጠቃላይ ለፈጣሪው እንዲገዛ የተፈጠረ ነው፡፡ ሆኖም ግን ለፈጠራቸው ተገዢ የመሆንና ያለመሆን ነጻ ምርጫ ሰዎችም ሆኑ ጋንኤሎች ተሰጥቷቸዋል። በዚህም (free will) ነጻ ምርጫ ተጠቅመው ማመን ወይም ያለማመን / ለፈጠራቸው ታዛዥ መሆን ያለመሆን መብታቸው የተጠበቀ ነው። ስለዚህ ነብያት ደግሞ የፈጣሪያቸውን ፈቃድ ለመፈጸም ከህዝቦች መሃከል በአንዱና ብቸኛ በሆነው ፈጣሪ ተመርጠው ለየወገኖቻቸው ሚላኩ ንጹሃን ናቸው ለዚህም ንጽህናቸውና ከብራቸው ነብይ የሚል አልቅና ማዕረግ ፈጣሪ ችሯቸዋል።

ከአደም ጀምሮ፣ አብርሃም፣ ኢስማኤል፣ ያእቆብ፣ ዮሴፍ ፣ሰለሞን፣ ሙሴ፣ ኢየሱስ፣ ሙሃመድ(ሰዐወ) በሁሉም ላይ የአላህ ሰላምና እዝነት ይውረድና ለፈጣሪያቸው ፈቃድ የተገዙ ነብያት ነበሩ። ለዚህም ነው ለፈጣሪው ፈቃድ ያደረ ሁሉ #ሰለመ ሚባለው ወይም ሙስሊም ሚሆነው።

ለማንኛውም ዛሬ በዚህ ጽሁፌ እስልምና ማለት ምን እንደሆነና የማን ሃይማኖት እንደሆነ ለማስተማር ሳይሆን በተደጋጋሚ በሚቀርቡ የአሉባላታ ወሬዎች ላይ ተንተርሼ መሰረተ ቢስነታቸውን ለማሳየት እሞክራለሁ።

ይኽውም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች አረብ አረብ ይሸታሉ በሚል ተደጋጋሚ መሰረት ቢስ ውንጀላዎችና ወሬዎች የኢትዮጵያውን ሙስሊም ለማንቋሸሽና ብሎም ሃይማኖቱን ለመዝለፍ ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች አንዱን ዛሬ ይመልስ ይሆናል ብዬ ያሰብኩትን ነጥብ እንደሚከተለው ላስቀምጥ እወዳለሁ። በቅድምያ የኢስላምም ይሁን የክርስትና ምንጭ የመሃከለኛው ምስራቅ እንደሆነ ይታወቃል።

ታድያ የነዚህ የአብርሃማዊ እምነቶች በሚል ሚታወቁት (Abrhamic faith) የሶስቱም ሃይማኖትች ማለትም የይሁድ ፣ የክርስትና እንዲሁም የእስልምና ማለት ነው።

ምንጩ አረባዊ ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያ ክርስትያኖች ምነው ዘነጉትሳ?። በተለይም ክርስትናና እስልምና በኢትዮጵያ። ሆኖም ግን አንባብያን እንድትገነዘቡልኝ ምፈልገው አብይ ጉዳይ ቢኖር ከላይ እንደገለፅኩት እስልምና የሁሉም ነብያት ሃይማኖት ነው ብዬ እያልኩ ለምን እዚህ ደግሞ ቅደም ተከተሉን ጠብቄ እስልምና የዛሬ 1431 አመት እንደተጀመረ አድርጌ ማቅረቤ ግጭት እንዳይመስልብኝ። በርግጥም እስልምና የመጀመርያው ሰው ከነበረው አደም ጀምሮ የነበረ ሃይማኖት ሲሆን ነብዩ ሙሃመድም (ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻው ነብይ እንጂ አዲስ ሃይማኖት ይዘው እንዳልመጡ ግልጽ ላደርግ እወዳለሁ።

ምክንያቱም የሰው ልጅ ፈጣሪ አንድ ከሆነ ይህ አንድ ፈጣሪ ደግሞ ለፈጠራቸው አካላት ሁለት ወይም ከዛ በላይ ህግጋቶች ወይም ደግሞ ሃይማኖትቶች አያወርድምና ልክ አንድ ድርጅት እንደሚያዘጋጀው አይነት መመርያ መጽሃፍ (manual, guide)ማለት ነው። መቸም አንድ ራዲዮ የሰራ አካል 2 ማኑዋል እንደማያዘጋጅ ግልጽነው ነው!

For God is not the author of confusion. 1Corinthians 14:33

ስለሆነም በእርግጠኝነት ፈጣሪ ከአንድ መመርያ ወይም መንገድ ውጭ ሌላ መመርያ ሊያስቀምጥ እንደማይችል እሙን ነው።ይህ ሆኖ ሳለ ሞዴሉ በተቀያየረ ቁጥር ግን ይሁን ከግዜው ጋር ተስማሚነት ያላቸው መመርያ መጽሃፍቶቹ መለዋወጣቸው አይቀሬ ነው።

☞ የታሪክ ምሁራን እንደሚሉት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ4ተኛው አመተ ልደት መገባደጃ ላይ እንደሆነ ይነገራል ይህውም በ"ቻሊሶዶን ጉባኤ" ወቅት በተፈጠረው መከፋፈል ተባረው በጊዜው ወደ ኢትዮጵያ በመጡት ቄስ አቡሰላማ እንደሆነ ይታወቃል። እንግዲህ እኚህ ሶሪያዊ ቄስ አቡሰላማ ወደ ኢትዮጵያ ባመጡት የክርስትና ሃይማኖት እንጂ ኢየሱስ ጎንደር ድረስ መጥቶ ባስተማረው ሃይማኖት እያመንን እንዳልሆነ ልብ ልንል ይገባል።

እንግዲህ በዚህ በቻሊስዶንያው ምእላተ ጉባኤ ላይ ከ ኦክቶበር 8 እስከ ኖቬምበር 1 451 ዓ.ል በእየሱስ ፍጡር መሆንና መለኮታዊነት ዙርያ በተመለከተ ባደረጉት ክርክር እየሱስ ፈጣሪም ሰውም ነው ብለው የተስማሙበት ምእላተ ጉባኤ እንደሆነ ይነገራል።ይህ ደግሞ ከ 325 የ"ኒቂያ ጉባኤ" ወዲህ የተደረገ ስብስብ ነው ፡

ይህውም በንጉስ ቆንስታንቲዩ የተመራው የኒቂያ ጉባኤ ክርስትያኖች ኢየሱስ አምላክ አይደለም በሚሉና አይ አምላክም ሰውም ነው በሚሉት የቤተክርስትያን አዋቂዎች መሆኑ ሲሆን ውጤቱም እንደሚታወቀው በኒቂያው ጉባኤ ላይ የስላሴ አስተምህሮትን ቤተክርስትያን በድምጽ ያሳለፈችበት ነበር።

በእርግጥ አቡ ሰላማ በ4ኛው ክ/ዘመን ከሌሎች 8 ቀሳውስት ጋር ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ይነገራል። ይህውም እነዚህ 8 ቀሳውስትና አቡሰላማ ከሶሪያ የተባረሩበት ምክንያት #መመነንን ያበረታታሉ በሚሉ ከሶችም ጭምር ነው።ይህ ደግሞ ዛሬ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጎልቶ ሚታይ ነው ።ምክንያቱም ውርሱ ከሶርያውያንና ግብጻውያን አረቦች በብዛት ይተገብሩት የነበረው ሃይማኖታዊ ሂደት ስለነበር በወቅቱ። ታድያ ይህን ታሪክ በመዘንጋት ይሁን ወይም ሆን ተብሎ ኢስላም ብቻ በአረቦች እንደመጣና (መጤ) ክርስትና ደግሞ ሃገር በቀል እንደሆነ ለማሳየት ሚቃጣቸውም አክራሪዎች አይጠፉም።

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ጀምሮ ጳጳሳት በሙሉ ይመጡ የነበረው ከአሌክሳንድርያ ቤተ ክርስትያን መሆኑንን እንዴት ዘነጉት? የግብጽ አረቦች የኢትዮጵያን ፓትርያርኮች እንደሚሾሙ እንዴት ተረሳቸው? ገና ነጻነቱን ካወጀ 50 አመት ዕድሜ ያለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ከ4 ተኛው ክፍለዘመን ጀምሮ እስከ 20 ኛው ክፍለ ዘመን የነበረን ታሪክ…

ይህን ሁሉ ዘመን ግንኙነት አረብ አረብ ካልሸተተ የቱ ነው አረባዊነት??? በእርገጥ እስልምና በአረብ ስደተኞች ቢጀመርም ቅሉ አረቦች ግን ለየትኛውም ዘመን ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን "ሸህ" ወይም "ሙፍቲ" አልሾሙላቸውም። ታድያ የቱ ነው አረብ አረብ ሚሸተው?

1600 ዓመታት በአረቦች የተመራው ቤተክርስታያን ወይስ 1431 አመታት እራሱን ያስተዳደረው ኢትዮጵያዊው ሙስሊም ?

እኔ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች አረብ አረብ ይላሉ ብዬ አልልም። ሃቁ በእርግጥም በተቃራኒው ነው። ሆኖም ይህን የተዛባ ብዥታ ሰዎች ማስተካከል አለባቸው የሚል እምነት አለኝ። በርግጥ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መጠርያ ስም ወይም ጀለብያ መልበስ አረባዊ ሚያሰኝ ከሆነ ሚኒስከርት ወይም ሌላ የምእራቡ ዓለም አለባበስ ታድያ ለምን አያስወቅስም? ነው ወይንስ በጭፍን ጥላቻ ተነሳስቶ የሙስሊሙን ክብር እንዝና በሃሰት ማጠልሸት?

ሌላው ስምን በተመለከተ ሲሆን በአጭሩ … መሃመድ ትርጉሙም (ምስጉኑ) የሚልን ውብ እና ቆንጆ ስም እያለ ማንም ቢሆን ኢትዮጵያዊነቱን ለማረጋገጥ ሲል ልጁን አሸብር፣ አስጨናቂ፣ አንበርብር፣ ቅጣው ወይም እረገጤ ብሎ ስም የሚሰጥ እንደሌለ ግልጽ ይሁን ወይንስ ታድያ እህቱ ፣ ሚስቱ ወይም እናቱ እራቆቱዋን በየመንገዱ እንድትታይለት የሚፈልግ ያለመኖሩን ያህል በክብር ሂጃብን መልበስና እራስን ማስከበር የተሻለ ለመሆኑ ምን መረጃ ያሻል? ዕንቁ የያዘ ሰው ሁሉ መቸም ከሌሎች መደበቁ አይቀሬ ነው…

ሴቶች ደግሞ ለባሎቻቸው፣ ለወንድሞቻቸው እንቁዎች ሰለሆኑ ጥበቃ ይሻሉ። አንድ የጀርመን ጠበብት ያለውን ላስታውሳቹና ልሰናበት ☞"እውነት እውነት ከመሆኑዋ በፊት በሶስት መንገዶች ታልፋለች መጀመርያ ያጥላሉዋታል ያናንቋታል ከዛም በጉልበት ሊጥሏት ይሞክራሉ በመጨረሻም ያለምንም ሌላ እውነተኛ ደጋፍ ሳያሻት እራሷ ምስክር ትሆናለች!!! ኡተር ሾፐንሃወር

ጀርመናዊ ፍሎሶፈር 1788 1860::

ኦርቶዶክስ ማለት ምን ማለት ነው? አስተምህሮቷስ ምንድነው?

"ፈጣሪ ቃል(እየሱስ) ከፈጠረው ሥጋ ጋር ተዋህዷል: ከሁለት አካል አንድ አካል: ከሁለት ባህሪ አንድ ባህሪ ሆኗል::አምላክ

ሰው ሆነ: ሰውም አምላክ ሆነ:: በተዋህዶ እምነት አምላክ ሰው ሆኖ የሰውነትን ባህርይ ገንዘቡ አደረገ: ሰውም የአምላክነትን ባህርይ ገንዘቡ አደረገ ልክ እንደ ብረትና እሳት::"[እየሱስ ማን ነው ? በመምህር ታሪኩ አበራ: ገጽ15-16: 4ተኛ እትም 2004

ዓ.ል]

በዚህ የቃልና የስጋ ውህደት ትንታኔ መሰረት የኢየሱስ አምላክነትና ሰውነት የባህሪ መወራረስ አድርገዋል: ይህ ማለት ፍጹም ሰው የሚባል እየሱስ የለም! ፍጹም አምላክ የሚባል እየሱስ የለም ማለት ነው! ምክንያቱም አንዱ የአንዱን ባህሪ ስለወረሰ አንዱ የአንዱ ቅይጥ ነው ማለት ነው!

ይህ ከሆነ ደግሞ የአምላክን ባህሪ የወረሰ ሰው ፍጹም አምላክ መሆን ባይችልም ፍጹም ሰው ግን መሆን አይችልም! ምክንያቱም ፍጹም ሰው የማያስኘው የአምላክነት ባህሪ አለውና!:: የሰውን ባህሪ የወረሰ አምላክም ፍጹም አምላክ ነው ሊባል አይችልም ምክንያቱም የሰውነት ባህሪ ወርሷልና!:

ይህ ከሆነ ዘንዳ! እየሱስ በላ ተኛ ሞተ ሲባል ያ የአምላክነት ባህሪ የወረሰውና ከአምላክ ጋር አንድ የሆነው እየሱስ ማለት እንጂ ሰውነቱ ለብቻው ተነጥሎ እየሱስ ይህን ያደረገው በስጋ ወራት ነው ለማለት በሩ ዝግ ነው! በውህደት ወደ አንድ ነገር የመጣ አካል ኋላ ላይ ተነጥሎ ለብቻው ፍጹም ሰው ሆኖ ይህን አደረገ ለማለት ያስቸግራልና!

ብረት እሳት ውስጥ ገብቶ ሲቀልጥ እሳት እንደሚሆነው ከሆነ የቃል የስጋ ውህደት የአምላክነትና የሰውነት ባህሪው

የማይነጣጠሉ የተዋሃዱ ናቸው ማለት ነው! ይህ ከሆነ ደግሞ ሲበላም ሆነ እንቅልፍ ሲተኛ ሰውነቱ ብቻ ሳይሆን አምላክነቱም አብሮት በልቷል አምላክነቱም አብሮት እንቅልፍ ተኝቷል ማለት ነው!

ብረት እሳት ውስጥ ገብቶ ሲቀልጥ እሳቱ ብረት ይሆናል ብረቱ ደግሞ እሳት ይሆናል አንዱ ከአንዱ መነጠል አይቻልም: ቃልም

ስጋ ሆነ ሲባል :አምላክ ሰው ሆነ: ሰውም አምላክ ሆነ እንደማለት ነው። ሰው የአምላክን ባህሪ ወርሶ አምላክ የሰውን ባህሪ ወርሶ በውህደት አንድ አካል የማይነጠል ሆኗል ማለት ነው: ይህ ሲሆን እየሱስ ሞተ ሲባል በአምላክነትና በሰውነት ውህደት የተፈጠረው አንድ ነጠላ እየሱስ ሞተ ማለት እንጂ ሰውነቱ ብቻ ተነጥሎ ሞተ ለማለት ብረት ቀልጦ ከእሳቱ ጋር ፍጹም አንድ እሳት ሆኖ በዛው ሰዓት ብረት ከእሳት ተለየ ብሎ እንደመቃዠት ነው::

ሰውነቱ የአምላክነት ባህሪ ወርሷል አምላክነቱ የሰውነት ባህሪ ወርሷልና ስለዚህ እየሱስ100% ሰው 100% አምላክ ነበር የሚለው የማደናገሪያ አባባል ከየት የመጣ ነ ?

ምንጭ:☞[እየሱስ ማን ነው ? በመምህር ታሪኩ አበራ: ገጽ15-16: 4ተኛ እትም 2004 ዓ.ል] መፅሀፍ የተወሰደ

‘ኢትዮጵያ ወዲህ መጽሃፉ ወዲያ ’ ለምን ይዋሻል ግን?

ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዛብሄር ትዘረጋለች፡፡ (መዝሙር 68፤31)

እንደሚታወቀዉ ያለፉት የኢትዮጵያ ክርስቲያን ነገስታትም ሆኑ የዘመናችን ዘመነኛ ክርስትያኖች ከዚህ ከመዝሙር 68፤31) ጥቅስ በመነሳት ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት፤ፅዮን ነች፤እንዲሁም ምድሪቱ አራሷ ክርስቲያን ነች ምናምን እያሉን ፕሮፖጋንዳቸዉን ሰምተናል። እስኪ ይህች የምትንቋለጻጻሰዋን ሀገሬ ኢትዮጵያ ጥቅሱ እንደማይመለከታት በመረጃና በማስረጃ እንመርምረዉ ። ብሉይ ኪዳን በተጻፈበት በዕብራይስጡ ቋንቋ አትዮጵያ በሚለዉ ምትክ የሚጠቀመዉ ኩሺ በሚለዉ ነዉ። እንደሚታወቀዉ መጽሀፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 10፤6 ላይ እንደሚያስተምረዉ ኩሽ ከኻም ልጆች አንዱ ነበር የኩሽ ስርወ መንግስት ደግሞ የተመሰረተዉ (ከ 727-663 አመተ ዓለም) በኑብያ ሲሆን ዋና ከተማዉን ናፓታ በማድረግ ነበር ።

በ 400 አ.አ ማኒቶ የተባለ የግብጽ ሊቃዉንት በብሉይ ኪዳን ከ ዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ሲተረጉም ኩሽ የሚለዉን ኢትዮጵያ በሚለዉ ተክተው ነበር የተረጎሙት።በኑብያ (የአሁኒቷ ሱዳን) ይኖሩ የነበሩት ህዝቦች ጥቁር ስለነበሩ በግሪክ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ወይንም አቻ ትርጉሙ በፀሀይ ፊታቸዉ ተቃጥሎ የጠቆረ እንደማለት ነዉ። ምንም እንኳን በ1611 በታተመዉ በንጉስ ጀምሱ መጽሀፍ ቅዱስ ከግሪክ ወደ እንግሊዝኛ #ኩሽ የሚለዉን ኢትዮጵያ ብሎ ቢተረጉመዉም አሁን ላይ የሚታተሙ የ መጽሃፍ ቅዱስ ቅጅዎች ላይ ኩሽ፤ኑቢያ ወይንም ሱዳን በሚል እየተረጎሙት ይገኛሉ ። ምሳሌ

▸1978 NEW INTERNATIONAL VERSION (NIV) #Cush will submit herself to God psalm 68;31

▸1970 NEW ENGLISH BIBLE (NEB) let #Nubia stretch out her hand to God psalm 68;31

▸1992 HOLY BIBLE GOOD NEWS EDITION the #Sudanese will raise their hands in prayer to God psalm 68;31

የ“ዘመን መለወጫ” ስህተቶች

ኢትዮጵያ በምትከተለው ክርስቲያናዊው የዘመን አቆጣጠር መሰረት አዲስ አመት ሊገባ የያዝነው አመት እየተጠናቀቀ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ክስተት ተከትሎ የሚፈፀሙ #እምነትን የሚጎዱ በርካታ ጥፋቶች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ:-

1. ቀዳሚው ድግምትና ጥንቆላ ነው።።

በሃገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ነህሴ ሊጠናቀቅ ሲል በየጠንቋዩ ቤት የሚልከሰከሱትና ደጅ ሚጠኑ እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች ናቸው፡ ፡ከዚያም አምስቱ ወይም ስድስቱ_የጳጉሜ ቀናት መንገዶች በድግምት ስራዎች ይሞላሉ።። በነዚህ ቀናት ማልዶ የወጣ ሰው እንዲራመዳቸው ታስቦ በጎረቤት መተላለፊያ እና ህዝብ በሚያዘወትራቸው መንገዶች ላይ ፍየሎች፣ ዶሮዎች፣ ድመቶች፣ ጥንቸሎች ወዘተ ታርደው ይጣላሉ።። በደም የተነከሩ ሳንቲሞች፣ ብሮች፣ ጌጣ-ጌጦች፣ የተለያዩ ቁሳቁሶች እዚህም እዚያም ወድቀው ይታያሉ።። ጥንቆላና ድግምት ደግሞ ከኢስላም የሚያስወጡ ከባባድ ወንጀሎች ናቸው።።

አላህ ሱብሃነው ወተአላ እንዲህ ይላል:

﴿ وَاتَّبَعُوا مَا تَتْلُو الشَّيَاطِينُ عَلَى مُلْكِ سُلَيْمَانَ وَمَا كَفَرَ سُلَيْمَانُ وَلَكِنَّ الشَّيَاطِينَ كَفَرُوا يُعَلِّمُونَ النَّاسَ السِّحْرَ ﴾ البقرة : ١٠٢

“በሱለይማን ዘመነ-መንግስት ሸይጧኖች የሚያነቡትንም (ድግምት) ተከተሉ።። ሱለይማን ግን አልካደም (ድግምተኛ አልነበረምና።።) ግና ሸይጧኖች ሰዎችን ድግምት የሚያስተምሩ ሲሆኑ ካዱ።።” [አልበቀራህ፡ 102]

ነብዩም ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በሀዲሳቸው እንዲህ ብለዋል፡- {አንድ ሰው ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ በሚናገረው ያመነ፣ በሙሐመድ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ላይ በወረደው ቅዱስ ቁርአን ከደ.ል።።} [አስሶሒሐህ፡ 3387]

- ደጋሚዎችና ከነሱ ዘንድ የሚመላለሱ ሰዎች መቼም ቢሆን ስኬት የላቸውም።። ጌታችን እንዲህ ይላል፡- ↪“ድግምተኛም በመጣበት ስፍራ ሁሉ አይቀናውም።።” [ጣሃ፡ 69]

↪- ደጋሚዎች የሰዎችን ገንዘብ በማታለል የሚበዘብዙ መዥገሮች ናቸው።። ገንዘቡን ለነሱ የሚሰጥ አካልም አላህ ፊት ተጠያቂ ነው፡ ፡ ነብዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡- ↪{የአደም ልጅ በቂያማህ ቀን አምስት ነገሮችን ሳይጠየቅ እግሮቹ አይንቀሳቀሱም።። እድሜውን በምን እንዳጠፋው፤ ወጣትነቱን በምን እንደጨረሰው፤ ገንዘቡን ከየት እንዳመጣው፤ እንዲሁም በምን እንዳወጣው፤ ባወቀው ምን እንደሰራ።።} [አስሶሒሐህ፡ 946]

↪- ደጋሚዎች የነገር ቋቶች የማህበራዊ ህይወት ጠንቆች ናቸው።። የተቸገረ ደንበኛቸው መፍትሄ ፈልጎ ሲመጣባቸው በብዛት የቸግሩ መንስኤ የሆነው ወይ ጎረቤቱ፣ ወይ ዘመዱ ወይ ደግሞ የቤተሰቡ አባል እንደሆነ በመጠቆም ሰዎች ውስጣቸው እንዲሻክር አለመተማመን እንዲነግስ ያደርጋሉ።። በድግምቶቹ ምክንያት የጤና መጓደል፣ የትዳር መፍረስ፣ የዝምድና መቆራረጥ፣ የጎረቤቶች በጎሪጥ መተያየት አልፎም ደም የሚያቃባ ግጭት እንዲከሰት ሁሉ ሰበብ ሊሆኑ ይችላሉ።።

- ጠንቋይና ደጋሚ ዘንድ የሚሄድ ሰው የተነገረውን ባያምን እንኳን ከባድ ቅጣት ይከተለዋል።። ነብዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ይላሉ፡-

↪{ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ስለሆነ ነገር የጠየቀው የአርባ ቀን ሶላቱ ተቀባይነት የለውም።።} [ሙስሊም፡ 5957]

2. ሌላኛው የ “ዘመን መለወጫን” ተከትሎ የሚፈፀመው ጥፋት መስከረም አንድን ወይም እንቁጣጣሽን ማክበር ነው።።

አቆጣጠሩ ሀገራዊ እንጂ እምነታዊ መሰረት እንደሌለው ሊያሳምኑ በከንቱ የሚዳክሩ ሰዎች አሉ::ነገሩ እጅጉን የፈጠጠ እውነታ ሆኖ ሳለ በዚህ ላይ የሚሸወድ መኖሩ እጅጉን የሚደንቅ ነው::ብቻ ለማንም እንደማይሰወር ባስብም ለማስታወስ ያክል የዘመን አቆጣጠሩ ወደ ሀገር ውስጥ የገባው በሚሲዮናውያን እና በአሬንታሊስቶች መሆኑ፣ አመቱ ሲፃፍ መጨረሻ ላይ "ዓመተ ምህረት" መባሉ፣ የነብዩ ዒሳን (ሰላም በሳቸው ላይ ይስፈንና) መወለድ መሰረት ያደረገ እንደሆነ መሞገታቸው እንዲሁም ይበልጥ ለማረጋገጥ የ "ዘመን መለወጫ" ወቅት ላይ "እንኳን ከዘመነ ማቲዎስ ወደ ዘመነ ዮሃንስ አደረሳችሁ" ወዘተ ማለታቸው ጥሩ ጠቋሚ ናቸው:: ስለዚህ ከየትኛውም ከአይሁድ፣ ከክርስቲያን እና ከሌሎች እምነቶች ጋር ከሚያመሳስሉ ነገሮች እራስን መቆጠብ ያስፈልጋል፡ ነብዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም "በሰዎች የተመሳሰለ ከነሱው ነው" ይላሉና::

ኢትዮጲያ በየአመቱ የምታከብረው አዲስ አመት (ዘመን መለወጫ) (እንቁጣጣሽ) እኛ ሙስሊሞችን አይመለከትም!

ስለምን ካሉ ምክንያታችንን በትዕግስት ያንብቡ! ሀገራት እራሳቸውን የቻለ የጊዜ ሰሌዳ አላቸው። ለምሳሌ ያህል ↪አውሮፓዊያን፣ ሀገራችን ኢትዮጲያ እንዲሁም ሙስሊሞችና ሙስሊም ሀገራት የሚጠቀሙት ማለት ነው።ሀገራችን የምታከብረው አዲሱ አመት እኛ የሀገሯ ሙስሊሞች የማይመለከተን ዋነኛው ጉዳይ አከባበሩ የክርስትና እምነት ላይ ያንጠለጠለ ነው።

- ↪በመጀመርያ ደረጃ ከስሙ እንኳን ስንነሳ "አመተ ምህረት" ማለት ነብዩ ኢሳ(የአላህ ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁንና) ከተወለዱ ቡኃላ ምህረት ተደርጎልናል ብለው ስለሚያስቡ ስያሜውን አመተ ምህረት ብለው ሰይመውታል። እኛ ሙስሊሞች ደግሞ ይህንን ግጥም አድርገን እንቃወማለን። ምክንያቱም ደግሞ ጌታችንና አምላካችን አላህ ምህረቱ ከዛሬ 2010 አመተ ልደት የጀመረ ሳይሆን፤ የሰው ዘር ከተፈጠረ ጀምሮ ምህረቱ አለ። ወደ ፊትም ይኖራል።
- ↪በሁለተኛ ደረጃ የዘመኑ አጠራር ከዘመነ ዩሀንስ ወደ ዘመነ ማትዩስ እያለ የተለያዩ በመፀሀፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ስያሜዎችን ይጠቀማሉ።
- ↪በሶስተኛ ደረጃ እኛ ሙስሊሞች በአሉ የማይመለከተን ጉዳይ እምነታችን ስለማንኛውም ጉዳይ ምን ማድረግ እንዳለብን የሚያብራራልን መፀሀፍ አለን። ይህም ቁርአንና ሀዲስ ናቸው። ከዚህ ውጭ ባህል ምናምን እያልን እምነታችንን የማያዘን ነገር አንፈፅም። በተለይ ደግሞ ከእምነታችን ተቃራኒ የሆኑ እምነቶች የሚያከብሩትን በአል ማክበርም ይሁን የደስታ መግለጫ ማቅረብ በጥብቅ የተከለከለ ነው። ነገር ግን በሀዘናቸው ወቅት ማስተዛዘን፣ ሲታመሙ መጠየቅ፣ እርዳታ ሲያስፈልጋቸው መርዳት፣ ሰላምታን ማቅረብ፣ በማህበራዊ(ሰርግ፣ ምርቃትና የመሳሰሉት) የደስታ ጊዚያቸው ላይ እንኳን ደስ አላቹ ማለትም ይሁን መሳተፍ አልተከለከልንም።

ስለዚህ የተከበራቹ ሙስሊም ወንድሞቼ! ከሀዲያን ቅር እንዳይላቸው፣ ግንኙነታችን እንዳይሻክር፣ ባህል ምናምን እያልን እምነታችንን የሚቃረን ነገር ከመፍጠር እንታቀብ።

አንዳንድ ሰው ብዙ አመት ሳደርገው የነበርኩት ነገር ነው እንዴት ላቁመው ብለው ይጨናነቃሉ ወላሂ ከልብ ከነየቱ(ካሰቡ) ይቻላል። እኔ የራሴን ተመኩሮ ላካፍላቹ፤ በአል በመጣ ቁጥር 20 ለሚጠጉ ለተለያዩ ጎደኞቼ እደውል ነበር። ደውዬም እንኳን አደረሳቹና መልካም በአል እል ነበር። የአላህ ፍቃድ ሆነና ይህ ተግባር ትክክል እንዳልሆነ ከኡስታዞቼ ሰማው። እንዴት ብዬ ላቁም የምለው ትልቅ የቤት ስራ ሆነብኝ ምክንያቱም ያስለመድኳቸው እነሱም በተራቸው እንካን አደረሰህ ስለሚሉኝ ከነፍስያ ጋር ትግል ጀመርኩ። ከስንት ቀን የትግል ጊዚያት ቡኃላ ከሌሎች እምነቶች ጋር ያለኝን ግንኙነት ጌታዬ ያዘዘኝን ብቻ ልፈፅም ወሰንኩ። በእነሱ ላይ የፈቀደልኝን ነገር አጥብቄ በመያዝ እንዲሁም የከለከለኝን በመከልከል ቀጠልኩ። ይህንን ሳደርግ ውስጤ ላይ አንድ ፍርሀት ነበር እሱም ምን ይሉኝ ይሆን? ይቀየሙኛል? ያገሉኛል? ነገር ግን ከጌታዬ ስለማይበልጥ አደረኩት። ለውሳኔዬም ትልቅ አጋዥ የሆነኝ የዛን የአዛኙን ነብይ ሙህመድ(ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ንግግር ነበር። ይኸውም:-

- ↪" ሰዎች ይደሰቱ አላህ ይቀየም የሚሉ፤ ታላቁ ጌታችን አላህም ጠልቷቸው እነዛ እንዳይቀየሙ ብሎ የሳሱላቸው እንዲጠሉት

ያደርጋል ብለዋል። በተቃራኒው አላህ ይደሰት ሰዎች ቅር ይበላቸው ብሎ የጌታቸውን ትእዛዝ ያከበሩትን አላህ ወዷቸውም ሰዎችም እንዲወዷቸው ያደርጋል።" ወወላሂ፣ ወቢላሂ፣ ወተላሂ ኩራት አደለም በስራም ቦታ ይሁን ጎረቤት ይወዱኛል፣ ያከብሩኛል። ሰዎች የሚያከብሩህና የሚወዱህ የጌታህን ትእዛዝ ችላ ስላልክ አደለም። ለዚህም ነው አንድ ወንድማችን ፂሙ ረዥም ነበርና ስራ ለመቀጠር ብዙ ተቸገረ። እናም የስራ ማጣቱ ምክንያት የፂሙ መርዝም ነው ብሎ እርግፍ አደረገውና ከዚህ በፊት ጠይቋቸው ከነበሩት ውስጥ በድጋሚ ወደ አንዱ መስሪያ ቤት ሲሄድ አንተ የጌታህን ትእዛዝ ለስራ ብለህ ከተውክ ለድርጅታችን እንዴት ታማኝ ልትሆን ትችላለህ ብለው ደና ሰንብት አሉት። የገባው ይገበዋል። ጌታውን አስከፍቶ ፍጡር ማስደሰት ከሁለቱም ያጣ ይሆናል፤ በተቃራኒው ጌታው ያስደሰተ ፉጡሮች ይወዱታል እንጂ አይጠሉትም! ቢጠሉትም የአላህ ወዳጅ ጠላይ ብሎ ለሰከንድም ማሰብ አግባብ አደለም!

12..ሽብርተኛው ማነው?

ቅዱስ ቁርአን 114 ምዕራፎች፣6236 አንቀጾች፣77439 ቃላት ያሉት ሲሆን፣ ‹‹ሰይፍ›› የሚለው ቃልም ሆነ ወይም ዐረብኛ ቋንቋ ውስጥ ካሉት 60 ያህል አቻ ቃላት ውስጥ አንዱ፣አንድም ጊዜ እንኳን ቁርአን ውስጥ አልተጠቀሰም። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ‹‹ሰይፍ›› የሚለው ቃል ከ200 ጊዜ በላይ ተደጋግሞ ተጠቅሷል።

ወደተነሳንበት ርእስ እንመለስና ሽብርተኛ ጽዮናውያን ሰፋሪዎች በፍልስጥኤም ሕዝብ ላይ ከተፈጸሙት የጅምላ ፍጅቶች ውስጥ ጥቂቶቹን ላስቃኛቹ፡-

- እ.አ.አ በ31/12/1948 600 ንጹኃን ሲቪሎች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንዳሉ የተገደሉበት የአልሸይኽ መንደር የጅምላ ፍጅት።
- እ.አ.አ በ11/4/1948 ከመንደሩ ነዋሪዎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በጅምላ የተጨፈጨፉበት የዴር ያሲን መንደር ፍጅት።
- እ.አ.አ በ11/7/1948 በመንደሩ መስጊድ ውስጥ ተሸሽገው የነበሩ 426 ንጹኃን ሲቪሎችን ጽዮናውያን ወራሪዎች መስጊዱን ሰብረው በመግባት የጨፈጨፉበት የአልለድ ፍጅት።
- በ10/1965 በከፈር ቃሲም 94 ሴቶችና ሕጻናት የተጨፈጨፉበት የጅምላ ፍጅት።
- በ18/9/1982 በጦር ወንጀለኛው ጽዮናዊ አሸባሪ በኤርያል ሻሮን ጦር፣በሊባኖሱ የክርስቲያን ፈላንጂስት ሚሊሽያዎች ተባባሪነት የተፈጸመው ዘግናኙ የሰብራና ሻቲላ ጭፍጨፋ። 72 ሰዓታትን በፈጀው በዚህ የዘር ማጥራት ሽብር አብዛኞቻቸው ሴቶች ሕጻናትና በዕድሜ የገፉ ሽማግሌዎች የሆኑ 3500 ፍልስጥኤማውያንና ሊባኖሳውያን በአሳላማዊ ማንነታቸው ምክንያት ብቻ በዘግናኝ ሁኔታ ተጨፍጭፈዋል።
- በ25/4/1994 የተፈጸመው የአልኢብራሂሚ መስጊድ ጭፍጨፋ። አንድ የእስራኤል ጦር ወታደር ከጽዮናውያን ሰፋሪዎች ጋር በመተባበር በፈጸመው የሽብር ጥቃት መስጊዱ ውስጥ በመስገድ ላይ የነበሩ 29 ሰጋጆችና ከመስጊዱ ውጭ የነበሩ 5 ሰዎች ሲገደሉ ከ350 የሚበልጡ ሰጋጆች ደግሞ ቆስለዋል።
- በ1995 በኦክላሆማ ሲቲ በፌዴራል መንግስት ሕንጻ ላይ የተፈጸመውን 168 ሰዎች የተገደሉበትና ሌሎች 500 ሰዎች የቆሰሉበትን ፍንዳታ፤በ7/2011 በኦስሎና በቶያ ደሴት በተመሳሳይ ወቅት የተፈጸመውን፣ከ92 ሰዎች በላይ የሞቱበትንና 90 ሰዎች የቆሰሉበትን ሁለቱን የሽብር ጥቃቶችም በዚህ ላይ መደመር ትችላላችሁ። ሁለቱ ጥቃቶች የተፈጸሙት በለየላቸው አክራሪና ዘረኛ ክርስቲያን አሸባሪዎች ነበር።

በተጨማሪም ሽብርተኝነት ከአንድ ሃይማኖት ወይም ባሕልና ሥልጣኔ ጋር ያለውን ትስስር የምንፈትሽ ከሆነ፣የሚከተሉትን እውነታዎች በቸልታ ማለፍ አንችልም። እነሱም፡-

አሁን ባለንበት ዘመን ውስጥ አንድ ሙስሊም አገር አንድን የምዕራብ አገር ወርሮ አያውቅም። በተቃራኒው ግን ጥንታዊውም ሆነ አዲሱ ዓለም የምዕራባውያን ኃይሎች የወረራና የዘመቻ ሲላማ ሆኖ መኖሩን ታሪክ ይመሰክራል። የአሜሪካ ቀይ ሕንዶች የምዕራባውያንን የሥልጣኔ አርማ በሚያውለበልቡ አውሮፓውያን ወራሪዎች እጅ የጅምላ ጭፍጨፋ የተካሄደባቸው ሲሆን፣የዛ ከፍለ አህጉራቸውን ከመነጠቃቸውም በላይ ቁጥራቸው ከአስር ሚሊዮን ወደ 200 ሺህ አሽቆልቁሏል። ምዕራባውያን ‹‹ሁለቱ የዓለም ጦርነቶች›› ብለው በሰየሟቸውና በተጨባጭ ግን የአውሮፓውያኑ የራሳቸው በሆኑት ሁለት ታላላቅ ጦርነቶች ምክንያት

በዓለማችን ላይ አስከፊ አደጋ ደርሷል። በአንደኛው ጦርነት ወደ ሃያ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች የተገደሉ ሲሆን፣ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ቁስለኛና አካለ ስንኩል ሆነዋል። በሁለተኛው ጦርነት ደግሞ 55 ሚሊየን ያህል ሲገደሉ፣53 ሚሊዮን ሰዎች ቆስለው ሦስት ሚሊዮን የደረሱበት ሳይታወቅ ቀርቷል። የአውሮፓውያን ተዋጊዎች የጎላ ባህሪ የጠላትን ቅስም ለመስበር ሲባል ሲቪሎችን ዒላማ ማድረግ ስለነበረ፣ የጦርነቶቹ አብዛኞቹ ሰለባዎች የቅኝ ተገዥ አገር ሲቪሎች ነበሩ።

እንደዚሁም ደግሞ በንጹሃን ላይ የሚፈጸመውን ጥቃት በመኮነንና ወንጀል መሆኑን በማረጋገጥ መርሕ ላይ ከተስማማን፣በአንጻሩ እነዚህን የሽብር ድርጊቶች የሚፈጽሙትን ወገኖች ወደዚህ የሚገፋፋቸውን ነገርም ችላ ማለት አንችልም። አሜሪካና ምዕራባውያን በሙስሊሞች ላይ ለሚፈጽሙት የማያቋርጥ ጥቃትና ሽብር፣በተለይም በዕራቅ ላይ በጣሉትና በወቅቱ ሁለት ሚሊዮን ሕጻናት እንዲያልቁ ምክንያት ለሆነው ማዕቀብ፣በተጨማሪም በፍልስጥኤም ሕዝብ ላይ በጽዮናውያን ወራሪዎች የሚፈጸመውን ወንጀል በመደገፋቸው ምክንያት የሚሰጥ ምላሽ ነው የሚል ማመካኛ ያቀርባሉ።

ምነው ለሙስሊሙ ሲሆን ትርጉሙ ተቀየረሳ

ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሉዋቸው፡፡ ቢከለከሉም ወሰንን ማለፍ፤ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው)፡፡" (2:193)

Vs

የይሁዳ መልእክት 1፡1-7 ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት #እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆኑብኝ።"

ሙስሊም ያልሆኑ በተለይም ክርስትያን ወገኖቻችን ሱረቱል በቀራ 2:193 ላይ የተገለፀውን በመጥቀስ ኢስላምን ያልተቀበለ ግደል ይላል፣ካልሰለሙ እረዱዋቸው፣ ወዘተ ብሎ ይሰብካል በማለት የዋህ ሰዎች ላይ በእስልምና ላይ ጥላቻን በመፍጠር እስልምና አስፈሪ ገፅታን በማላበስ ህዝቡ ላይ ተፅእኖ ለመፍጠር በየቀኑ በየደቂቃው ይተጋሉ። እውነታው ግን በተቃራኒው ነው አላወቁም እንጂ ከሚመሩበት መፅሀፍ ቅዱስ ይህ እንዳለ አላወቁምና

☞ ‹‹ የተጠራህለትን የዘለዓለም ሕይወት ትቀበል ዘንድ መልካሙን የሃይማኖት ገድል #ተጋደል›› (1ኛ ጢሞ 6፥12)

ጳውሎስም ‹‹ መልካሙን ሀይማኖት ገድል #ተጋድያለሁ፤ ሩጫዬን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖቴንም ጠብቄያለሁ። (2ኛ ጢሞ 4፥7-8)

'አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት" ኤፌ4:5

“መልካሙን የእምነት ገድል #ተጋደል” 1 ጢሞ. 6፥16 »

ወደ ዕብራውያን 11:33 እነርሱ #በእምነት #ተጋደሉ፤ ነገሥታትን ድል ነሡ፤ ጽድቅን አደረጉ፤ ተስፋቸውን አገኙ፤ የአናብስትንም አፍ ዘጉ ።

የይሁዳ መልእክት 1፡1-7 ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ #ሃይማኖት #እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆኑብኝ።"...

ታድያ በክርስትናው አለም እውነትን ለማንገስ ውሸትን ለማጥፋት ለሀይማኖት መጋደል እንደሚያስፈልግ ከላይ በሰፊው በመፅሀፍ ቅዱስ ተገልፆ እያለ በቁርአንም ተመሳሳይ መልእክት በመኖሩ ማለትም ውሸትን በማውደምና ፣ እውነትን ለማንገስ በቻላችሁት መጠን ለሀይማኖት ፣ለእውነት፣ ለሀቅ፣ለፍትህ ተጋደሉ ((ሱረቱል በቀራህ 193) የሚለውን ለምን በመጥፎ ጎኑ መተርጎም አስፈለጋቹ? ከላይ መፅሀፍ ቅዱስን በተረጎማችሁበት አእምሮ ቁርአኑን መተርጎም ለምን ተሳናቹ?

ለማንኛውን የቁርአኑ ተጋደሉ ምን ለማለት ፈልጎ ይሆን? አብረን እንመልከት

ሁከት እስከማይገኝና ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ #ተጋደሉዋቸው፡፡ ቢከለክሉም ወሰንን ማለፍ፤ በበዳዮች ላY እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው)፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 193)፡፡

- ‹‹ ሁከት እስከማይገኝና ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሉዋቸው›› የሚለው የመጨረሻን ግብ የሚገልጽ ነው፡ : የኛ ዓላማ መሆን ያለበት፡ የሰው ዘር እንዲጠፋ፣ ወይም ብሄርተኝነት እንዲስፋፋ ሳይሆን፡ የአላህ ዲን የበላይ እንዲሆን ነው፡፡ የጣኦት አምልኮ ተንኮታኩቶ፡ እውነትም ነግሶ በምድር ላይ እንዲታይ፡ አማኞችም ጌታቸውን የማምለክ ነጻነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ ነው፡፡ ጠላት እንዳይበታተነን ሁሌም በንቃት መስራት ይጠበቅብናል፡፡
- ‹‹ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ›› ማለትም ትርጉሙ ይኸው ነው፡፡ የአላህ ሸሪዓ በምድር ላይ ነግሶ፡ የሰዎች ነጻነት ታውጆ፡ የኩፍር የበላይነት አክትሞ እስኪንኮታኮት ድረስ ማለት ነው፡፡

አንዳንድ ወገኖች፡- ሰዎች ሁሉ እስኪሰለሙ ወይም ሙስሊም እስከሚሆኑ ድረስ ለማለት ነው ይሉናል፡፡ እነሱ እንደሚሉት ከሆነማ፡ - ‹‹ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ›› ከማለት ይልቅ፡ ‹‹ሰዎች ሁሉ ሃይማኖተኛ እስኪሆኑ ድረስ›› አይልም ነበር ታዲያ? ከየት ያመጣችሁት ግንዛቤ ነው? እንደውም ቀጣዩ ቃል ይህን ሃሳብ ያፈርስባችኋል፡፡

- ‹‹ቢከለክሉም›› የሚለው ሁለት ትርጉምን ያቅፋል፡፡

አንደኛ፡- ከዚህ ካሉበት የጣኦት አምልኮ ተከልክለው ኢስላምን በፈቃደኝነት ቢቀበሉ የሚል ሲሆን፡

ሁለተኛው፡- በነበሩበት የክህደት እምነት መዘውተርን ፈልገው፡ ኢስላምን ባይመርጡና ነገር ግን ለሚያስተዳድረው ኢስላማዊ መንግስት ያለባቸውን ‹‹ግብር›› በአግባቡ ቢከፍሉ የሚል ሲሆን፡ ከሁለት አንዱን ቢተገብሩ ውጤቱ ደግሞ፡-

- ‹‹ ወሰንን ማለፍ፤ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው)›› በማለት፡ በነሱ ላይ ወሰን ማለፍን ይከለክላል፡፡ (ተፍሲር ቁርጡቢይ፡ ጀሚዑል አሕካም)፡፡

እንደሰዎቹ ግንዛቤ፡ ሙስሊም እስኪሆኑ ድረስ ከተባለማ፡ ካልሰለሙ ግደሏቸው እንጂ፡ ወሰን አትለፉባቸው እንዴት ይባላል?

ስለዚህ ‹‹ሃይማኖትም ለአላህ እስኪሆን ድረስ›› ማለት፡- ሰዎች ያለ ፈቃዳቸው አምነው እስኪቀበሉ ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን መልእክቱ፡- ፈቅደውና ወደው ኢስላምን እስኪቀበሉ፡ ያ ካልሆነም ለኢስላማዊው መንግስት የሚጣልባቸውን ግብር እስኪከፍሉ ድረስ ነው የሚለውን ያቀፈ ነው፡፡ ወንድምና እህቶች ከቁጥር 190-193 ያለውን የቅዱስ ቁርኣን አንቀጽ በመጠኑም ቢሆን እንዲህ ከተረዳነው፡ ታዲያ የታለ ሰዎች እስኪሰልሙ ድረስ ግደሏቸው የሚለው? የታለ ከመሬት ተነስታቹ ሰው አጥፉ የሚለው? መልሱን ለህሊና፡፡

‹‹ ከእግዚአብሔር በቀር ለአንዳች አምላክ የሚሠዋ ፈጽሞ ይጥፋ። ›› (ኦሪት ዘጸአት ምዕ 22፡20)፡፡

1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

16፥13 ንቁ፥ በሃይማኖት ቁሙ፥ ጎልምሱ ጠንክሩ።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4፥5 አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤

ወደ ቆላስይስ ሰዎች 2፥7 ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታነጹ፥ እንደ ተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ፥ ምስጋናም ይብዛላችሁ።

ታድያ በክርስትናው አለም እውነትን ለማንገስ ውሸትን ለማጥፋት ለሀይማኖት መጋደል እንደሚያስፈልግ ከላይ በሰፊው በመፅሀፍ ቅዱስ ተገልፆ እያለ በቁርአንም ተመሳሳይ መልእክት በመኖሩ ማለትም ውሸትን በማውደምና ፣ እውነትን ለማንገስ በቻላችሁት መጠን ለሀይማኖት ፣ለእውነት፣ ለሀቅ፣ለፍትህ ተጋደሉ ((ሱረቱል በቀራህ 193) የሚለውን ለምን በመጥፎ ጎኑ መተርጎም አስፈለጋቹ?

ከላይ መፅሀፍ ቅዱስን በተረጎማችሁበት አእምሮ ቁርአኑን መተርጎምስ ለምን ተሳናቹ? አይን የራሱን ጉድፍ ሳያይ የሰውን ጉድፍ ያያል ነው ነገሩ

☞"መልካም ለማሰብ ያልታደለ አእምሮ ለተንኮል ተወዳዳሪ የለውምና"

ይህንን ያውቃሉ

የአውሮፖ ክርስቲያኖች ምንያህል ሰዎችን እንደጨፈጨፉ???? ☞ መቼም ሽብር አይባልም የሰው ደም ጠጥተው።

1. በ S.America በ17th ዘመን ስፔንና_ፖርቹጋል የገደሉት ብዛት 56 ሚሊየን ሰው ጨፍጭፈዋል።

2. Red Indians ከ150 አመት በፊት 89 ሚሊየን ሰው ጨፍጭፈዋል።

☞ In Africa

3. ባለፉት 400 ዓመታት 180 ሚሊየን ሰዎችን ጨፍጭፈዋል።

4. S.Africa 39 ሚሊየን ሰዎችን ጨፍጭፈዋል።

☞In Austeralia

5. አቦርጂና የሚባሉ ጎሳዎችን 16 ሚሊየን ሰዎችን ጨፍጭፈዋል

☞In Asia

6.ታላቋ ቢሪታንያ ህንድን በቅኝ አገዛዝ ጊዜ እስከ 50 ሚሊየን ሰዎችን ጨፍጭፈዋል። በአጠቃላይ በኤሲያ ብቻ እስከ 86 ሚሊየን ሰዎች ተጨፍጭፈዋል።

☞አጠቃላይ ስትደምሩት ከ450 ሚሊየን ሰዎች በላይ በአውሮፖ ክርስቲያኖች #ተገለዋል ።

☞እዚህ ጋር ልብ በሉ #በኢራቅ_በፍልስጤም_በአፍጋን የተጨፈጨፉትንና እየተጨፈጨፉ ያሉትን አልቆጠርንም። አይገርምም ግን በሚዲያ አንድም ቀን ይሆን ሁሉ ሰው ቁርጥም አርግተው የበሉ ሰዎች #አሸባሪ ሲባሉ ሰምተን አናቅም

☞ታዲያ ምኑ ጋር ነው ሰባዊ መብት፡ ወይስ ነጭ ብቻ ሲሞት ነው ሰባዊ መብት የሚባለው፡ ነጭ ጨፍጫፊ፣ሴትን ደፊሪ ሲሆን ሰባዊ መብቱ ነው ይሉለታል።

ሰዎች ስለ isis ያወራሉ isis ግን አብዛኛውን እየገደለ ያለው ሙስሊሞችን ነው ታዲያ isis ሙሉ ለሙሉ ሙስሊሞች መሆናቸው ምን ያህል ታዓማኒነት አለው።

☞ሚዲያ ባለፋት 20 አመታት ወዲህ #ለኢስላም ጥቁር ጥለሸት እየቀባ ይገኛል፡ #ሚዲያውሰዎች ስለ ኢስላም መጥፍ አመለካከት እንዲይዙና ሙስሊሞችን በጥላቻ መንፈስ እንዲመለከት ያደርጋል፡ ሚዲያው ኢስላም ላይ ትልቅ የማጠልሸት ዘመቻውን ከፍቷል። ሚዲያው በእኔ አስተሳሰብ ቀኑን_ጭለማ #ጭለማውን ደግሞ ቀን እያደረገ የሚያቀርብ የውሸት ድርጅት ነው

☞ግን ይሄ ሁሉ ውሸትና እውነት ተደብቆ አይቀርም፡ የአውሮፖ ክርስቲያኖችና አይሁድ በሙስሊሞችና በሰው ዘር ላይ የሚረጩት መርዝና_ጥላቻ ነግሶ አይቀርም፡ እንዲሁም ምድርን በፈሳድ ሞልተዋት አለትቀርም። አንድቀን እውነት በውሸት ላይ መንገሱ አይቀርም፡ ሙስሊሞችም በክርስቲያንና በአይሁድ ላይ መንገሳቸው አይቀርም!!! ንግግሬን በቁርዓን እቋጫለው

♥በልም እውነት መጣ ውሸትም ተወገደ እነሆ ውሸት ተወጋጅ ነውና ♥ ሱራ ኢስራ 17:81

13.ወንጌሎችን ማን ፃፋቸው?

ምርጫውንስ ማን አካሄደው?

በአንድ ወቅት ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ወንጌሎች እንደነበሩና ከነኚህ ውስጥ ቤተክርስቲያን አራቱን ማለትም የማቴዎስን፡የማርቆስ፡ የሉቃስንና የዮሐንስን ወንጌሎች ብቻ እንደመረጠች ክርስትና ይነገራል፡፡ቀሪዎቹ ወንጌሎች እንዲቃጠሉ ወይም እንዲጠፉና እንዲወድሙ ሌላው ደግሞ እንዲደበቁ ተደርገዋል፡፡

ኢስላም ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን አንድ ነጠላ የቅዱስ ቁርአን ቅጂ ብቻ መኖሩንና ተመሳሳይ የማማረጥ ሂደት አለመደረጉን ወይም አለማስፈለጉን ይናገራል፡፡

- ለመሆኑ ቤተክርስቲያን ምርጫውን በምን መስረት ላይ ተመርኩዛ ነው ያካሀደችው? ለምንስ እነኛ አራት ወንጌሎች ብቻ በተለይ ተመረጡ?
- ለምን ሥስት ወይም አምስት ወይም ደግሞ አስር ወንጌሎች አልተመረጡም???
- የተቀሩት ወንጌሎችስ ለምን አልተመረጡም?
- የእነ የቶማስ ወንጌል፣የበርናባስ ወንጌል፣ የፊሊፕ ወንጌል ወዘተ… ለምን አልተመረጡም?ወንጌሎችን የመምረጥና የማስወገድ መብት ያለው ማነው?
- ያን መብትስ ማን ሰጠው?
- ወንጌሎች የእግዚአብሄር ቃል ከሆነ ዘንዳ ሌሎቻቸው መወገድ የሚኖርባቸው ለምን ይሆን?

①) የሉቃስ ወንጌል :-

ሉቃስ በጭራሽ የኢየሱስ ሃዋርያ አይደለም ። እየሱስን ፊጽሞ በአይኑ አላየውም ። ሲናገሩም አዳምጦዋቸው አያውቅም ። ሉቃስ የእየሱስ ደቀመዝሙር ደቀመዝሙር እንኳዋ አይደለም ።

ስለ ሉቃስ ወንጌል የክርስቲያን ምሁራን እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል:-

☞"ምንአልባትም የሉቃስ ወንጌል የተጻፈው በ60 ዓ.ም ገደማ ሳይሆን አይቀርም።."…ምሁራን :-(ቲም ፌሎስ፣የአዲስ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ፣)

ሉቃስ የዚህ ወንጌል ጸሃፊ መሆኑን መጠራጠር የጀመሩት ባለፉት 100 ዓመታት ውስጥ ብቻ ነው። በመቀጠልም የክርስቲያን ምሁራን እንዲህይላሉ:-

☞"ሉቃስ አይሁድ አልነበረም፤ አህዛብ ነበር። የት ተወልዶ እንዳደገም አናውቅም።"

ምንጭ:-(ቲም ፌሎስ፣የአዲስ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ፣ በትምህርተ መለኮተ)

ሉቃስ በተራው ጭራሽ የእየሱስ ሃዋርያ ያልነበረ የጳውሎስ ደቀመዝሙር ነው። እንኳን ሉቃስ ፃውሎስም ራሱ ኢየሱስን በአይኑ አይቶተረ አያውቅም። እየሱስን ፈጽሞ ያላየና ጭራሽ ከሳቸው ያልሰማ እስከሆነ ድረስ የሉቃስን ዘገባ እንዴት መቀበል እንችላለን ? የሶስተኛ ደረጃ ዘገባዎች እስከሆኑ ድረስ የርሱ ዘገባዎች ምን አይነት የትክክለኛነት ዋጋ ይኖራቸዋል?

ሉቃስ ወንጌሉን የጀመረው እንዲህ በማለት ነበር፡-

«የከበርክ ቴዎፍሎስ ሆይ፣ ከመጀመሪያ በአይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፣ በኛ ዘንድ ስለተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለሞከሩ እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ፡፡» (ሉቃስ 1:1-4)

ከሉቃስ አባባል እንደምንረዳው፡-

በርሱ ዘመን በርካታ ሰዎች የየራሳቸውን ወንጌል ይጽፉ ነበር፡፡ በክርስትና የመጀመሪያ ከፍለ ዘመን ወንጌሎች እንደ አሸን የፈሉበት ሁኔታ ነበር፡፡

ሉቃስ 1:1-4 “……ብዙዎች ታሪኩን የተቻላቸውን ያህል ጽፈውት ይገኛል……”ለመሆኑ ብዙዎች ከሆነ የጻፉት በግል ጥንቃቄ የተጻፈውን የሉቃስ ወንጌል ለአምላክ ቃል ማእረግነት ለመብቃት ምን መመዘኛ ተቀምጦ ነው ከብዙዎቹ በተለየ መልኩ የአምላክ ቃል ለመሆን የበቃው? እነዛ ብዙዎች የተባሉት መፅሐፍትስ ለምን በመፅሐፍ ቅዱስ አልተካተቱም? ምርጫውንስ ማን አካሄደው?

ሉቃስ ጽሑፉን የጻፈው ‹የጌታ ቃል› ብሎ ሳይሆን ለባልንጀራው የግል ደብዳቤ ነው፡፡ ሉቃስ የፃፈው ለባለንጀራው ነው እንጂ ለህዝበ ክርስትያን አደለም!

ብዙህ የዋህ ክርስትያን እንደሚያስበው በመንፈስ ተመርቶ ሳይሆን ለጓደኛው የፃፈው ነው። ምንም እንኳ መጽሐፍ -ቅዱስን ቅዱሳን ሰዎች በእግዛብሔር መንፈስ ተነድተው ጻፉት ቢባልም ጸሐፊዎቹ ግን በግል ተነሳሽነት እንደጻፉት ከመግለጻቸውም በተጨማሪ ጸሐፊያቸው የማይታወቅ መጽሐፍትም በዚህ የአምላክ ቃል ነው በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ።

እንግዲህ ከጥቅሱ መረዳት የምንችለው ሉቃስ ወንጌሉን የጻፈው በእግዚአብሔር መንፈስ ቀረጹስ ተነድቶ ሳይሆን ሁኔታዎች እንዲጽፍ አነሳስተውት ከመሆኑ በላይ ሲጽፍ የተቻለውን ያህል ቅደም ተከተል ላለማዛባት ጥንቃቄ ማድረጉን ነው።

የጻፈውም ‹መልካም ሆኖ ታየኝ› በማለት በግል ተነሳሽነት ሲሆን ሁሉንም ነገር ከመጀመሪያው ጀምሮ በመከታተል በግል ጥረቱ እንጅ በመንፈስ ተሞልቶ አይደለም፡፡

«የከበርክ ቴዎፍሎስ ሆይ፣ ከመጀመሪያ በአይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፣ …. እዚህ ጋር ትኩረት ሰጥተን ብናነበው ሉቃስ እየፃፈ ያለው ከሌላ ሰው የተተላለፈለትን ታሪክ ነው። ይህ ደግሞ ተአማኒነቱ የወረደ ነው ማለት ነው።

ሉቃስ ደብዳቤው ከዘመናት በኋላ ወንጌል ይሆናል ብሎ ፈጽሞ አላሰበም፡፡ ለጓደኛው እርግጡን ያውቅ ዘንድ ሲል ነው የጻፈለት፡

መጽሀፍ ቅዱስ እራሱ እንደሚበረዘ ፣ እንደሚከለስ በራሱ አንደበት እንዲህ ሲል አረጋግጧል።

☞እናንተስ። ጥበበኞች ነን የእግዚአብሔርም ሕግ ከእኛ ጋር ነው እንዴት ትላላችሁ ? እነሆ፥ የጸሐፊ ብርዕ ሐሰተኛ ነው በሐሰትም አድርጎአል ። (ትንቢተ ኤርምያስ 8:8)

☞ ከሞትሁ በኋላ ፈጽማችሁ እንድትረከሱ ፥ ካዘዝኋችሁም መንገድ ፈቀቅ እንድትሉ አውቃለሁና። በእጃችሁም ሥራ ታስቈጡት ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ስላደረጋችሁ በኋለኛው ዘመን ክፉ ነገር ያገኛችኋል። (ዘዳግም 31:29) ኦሪት ዘዳግም 4: 2 እግዚአብሄር እንዲህ ይላል 2፤ እኔ ያዘዝኋችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትጠብቃላችሁ እንጂ ባዘዝኋችሁ ቃል ላይ አትጨምሩም፥ ከእርሱም አታጎድሉም።

☞የሠራዊትን ጌታ የአምላካችንን የእግዚአብሔርን "የሕያውን አምላክ ቃል ለውጣችኋልና" (ኤርምያስ 23፥36)

በቅዱስ፣ቁርአን 2:77-79 ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል :-

Then woe to those who write the Book with their own hands, and then say: 'This is from Allah,' to traffic with it for a miserable price! "ለእነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት ይህ ከአላህ ዘንድ ነው ለሚሉ ወዮላቸው፤.... " ይለናል። (ቁርአን 2:77-79)

ስለዚህ እህት ወንድሞች በመፅሀፍ ቅዱስ እንደነ ጳውሎስ፣እነ ሉቃስ፣እነ ማቴዎስ፣እነ ማርቆስ ፣ እና ዮሐንስ ባሉ ሰዎች በራሳቸው ፍቃድ የአምላክን ቃል እንደሚለውጠና እንደሚቀይሩ ቅዱስ ቁርአንም መፅሀፍ ቅዱስም አስቀድመው ተናግረው ነበር።

②)የማርቆስ ወንጌል ማን ጻፈው?:-

ማርቆስ የ ኢየሱስ ሃዋርያ(ደቀመዝሙር) አይደለም ። ማርቆስ የጴጥሮስ ደቀ መዝሙር ነው ። ስለሆነም የማርቆስ ወንጌል ከኢየሱስ የተላለፈ የመጀመርያው ቀጥተኛ ትረካ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም ።

የክርስቲያን ምሁራን ስለ ማርቆስ ወንጌል እንዲህ ይሉናል:- "ከሌሎች ጋር ሲናጻጸር ስለዚህኛው ወንጌል ጸሃፊ ብዙ የሚታወቅ ነገር የለም። መጽሃፉም ቢሆን በየትኛውም ስፍራ ስሙን አይጠቅስም፤የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚገልጸው ጸሃፊው የክርስቲያን ቤተሰብ አባል የሆነ ዮሀንስ ማርቆስ መሆኑን እና የጳውሎስ፣ የበርናባስና ምናልባትም የጴጥሮስ ረዳትና ተማሪ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። ("ምንጭ:-ሜሪል ሲ ቴኒ ፣የአዲስ ኪዳን ቅኝት ገጽ 236።)

☞ማርቆስ እየሱስ የሰሩትን አላየም።

☞የተናገሩትንም በጆሮው አልሰማም።

ስለዚህም ማርቆስ ስለ እየሱስ ያቀረበውን ዘገባ እውነተኛነት ማንም ሰው ማረጋገጥ አይችልም። ስለ ኢየሱስ በመዘገብ ረገድ ከሃዋርያቱ ተማሪዎች ይልቅ የእየሱስ ቀጥተኛ ተማሪዎች የነበሩት ሃዋርያት አስተማማኝ ዘጋቢዎች ናቸው። ማርቆስ ግን የእየሱስ ደቀመዝሙር ደቀመዝሙር ነው ።

እኛ እንደ ሙስሊምነታችን ለእየሱስ የአላህ ሰላም በሱ ላይ ይሁንና ኢንጂል በነሱ አጠራር ወንጌል እንደተሰጠው አናምናለን ነገር ግን ይህን ስንል አሁን እነሱ እጅ ያለው ወንጌል ማለታችን እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል ። ለእየሱስ እንደተሰጣው አናምናለን እንጂ መጽሐፉን እንድንከተለው አልታዘዝንም ምክንያቱም የሰው እጅ ገብቶበት ተበርዟልና።

የማርቆስ ወንጌል በ68 ዓመተ ልደት አከባቢ ማለትም እየሱስ ካረገ ከ35 ዓመታት በሃላ እንደተጻፈ ይገመታል።

ከዚህም የምንረዳው ይህ ወንጌል እየሱስ በሕይወት ሳለ አልተጻፉም ። እየሱስ ካረገ ከበርካታ አስርት አመታ በኋላ የተጻፈ

ነው። እግረ መንገዳችንን የማርቆስ ወንጌልን ካነሳን አይቀር ሁሌም ለክርስትያኖች አንድ የምናነሳላቸው ጥያቄ አለ። ክርስትያኖች እኛ አማኞች ነን ሲሉ ሁሌም እንሰማለን። እኛም ቀለል አድርገን የምናነሳው ጥያቄ በማርቆስ ወንጌል አማኝ ተከታዩን ተዓምር ማድረግ እንደማይሳነው ይነግረናል።

ማርቆስ 16:17 -18

17 ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥

18 የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።

- የኛ ጥያቄ አማኝ ነን ለሚሉ ክርስትያን ወገኖች አማኝ ይህን ማድረግ ይችላልና አዲስ ቋንቋ ተናገሩልን ስንላቸው "ሳንታ ሳንታ ዋና" ይሉንና ሌላ ቃል ይቀጥላሉ ብለን ስንጠብቃቸው ዝም ይላሉ። እሺ ይሁን እንልና አማኝ የሚገድልን ነገር ቢጠጣ አይገድለውም ተብሏልና ሃላፊነቱን ወስደክ ይህችን መርዝ ትጠጣታለክ ወይ ብለን መርዝ ብንሰጠው። "ማን ሞኝ አለ" የማይተናነስ መልስ ይሰጡናል። ይህ የሚያሳየን እኚህ አማኝ ነን ብለው የሚሉት ሲያምኑ የማርቆስ ወንጌልን ሳያካትት ነው የሚያምኑት ማለት ነው። ይህስ ጥቅስ እውነት የእየሱስ አስተምህሮ ነውን? አስተምህሮስ ከሆነ ክርስትያኖች ለመተግበር ለምን ይሸሻሉ? ኢየሱስስ እንደዚህ ለሰው ልጅረ አደገኛና ጎጂ የሆነ ነገር ያስተምራልን? በጭራሽ! ሲቀጥል በየትኛው ሃይማኖትስ ነው እንደዚህ ሂወትን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ነገርን አድርጉ ብሎ የሚያዘው?

③)የማትዮስ ወንጌል ማን ጻፈው?:-

የማትዮስ ወንጌል ከ95-112 ዓ.ል ማለትም ከእየሱስ እርገት ከ60-80 ዓመታት ባሉት ጊዜያት ውስጥ እንደተጻፉ በምሁራን ተገምቷል።።ማቲዮስ ወንጌሉን የጀመረው ስለ እየሱስ ትውልድ በመተረክ ሲሆን ‹ይህ ጽሑፍ ከአምላክ በራእይ ተገለጸልኝ› የሚል መልእክት አላሰፈረም፡- «የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ፣ የእየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ። አብርሃም ኢስሐቅን ወለደ፤ ኢስሐቅም ያእቁብን ወለደ . . . » (ማቲዮስ ም 1 ቁ 1-8)

የጸሐፊው ማንነት አይታወቅም፡-

የክርስትና ሃይማኖት ምሁራን ስለ ማቲዎስ ወንጌል የሚከተለውን ጽፈዋል:-

☞"ወንጌሉን የጻፈው ማቴዎስ ነው" ያሉት የቀደሙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ናቸው እንጂ የጸሃፊው ስም አልተጻፈበትም።መች እንደተጻፈ ደግሞ አልታወቀም። ቲቶ(ጥጦስ)በሚባል በሮማ መንግስት የጦር መሪ እጅ ኢየሩሳሌም የፈረሰችው በ70 ዓ.ም ሲሆን ወንጌሉ ከዚያ በፊት ወይም ከዚያ በኋላ ተጽፎ እንደሆን መምህራን አልተስማሙበትም። በ 60 እና 80 ዓ.ም መካከል እንደተጻፈ ይገመታል።

ምንጭ:- (የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፤የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር፤ገጽ 41)

ብዙ ክርስቲያኖች የማቲዎስ ወንጌልን "ማቲዎስ" እንደጻፈው ያስበሉ ይህን ይበሉ እንጂ ማቲዎስ ይህንን ወንጌል በፍጹም አልጻፈውም!!

የማቲዎስ ወንጌልን በ "ማቲዎስ"ተጻፈ የሚባለው አባባል ከ እውነት በጣም የራቀ ነው። ምንም አይነት መረጃ የለም። ያሉት መረጃዎች በሙሉ የሚያመላክቱት ይህንን ወንጌል በፍፁም "ማቲዎስ" የተባለው ግለሰብ አለመጻፉ ነው። መጽሃፍ ቅዱስ አስከ አሁን ደቂቃ ድርስ ማን እንደጻፈው በ ትክክል የሚታውቀ ነገር የለም።

እኛ ሁልጊዜም በመረጃ ነውና የምንናገረው መርጃዎቻችንን አንድ በ አንድ እንያቸው:

1. ማስረጃ ከራሱ ባይብል :-

"በማቲዎስ" ተጻፈ በታባለው ወንጌላ ላይ ይህንን እናገኛለን ።

"ኢየሱስም ከዚያ አልፎ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ ማቴዎስ የሚባል አንድ ሰው አየና። ተከተለኝ አለው። ተነሥቶም ተከተለው። በቤቱም በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፥ እነሆ፥ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች መጥተው ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብረው ተቀመጡ"። (ማቴዎስ ወንጌል 9:9-10)

እንግዲህ ይታያቹህ !ይህንን ወንጌል ማቲዎስ ጻፈው ተብሎ ማቲዎስ ግን እንደሶስተኛ ወግን ሲጠቀስ እናነባልን።

ይህንን ወንጌል እውነት ማቲዎስ ቢፅፈው ኖሮ ማለት የነበረበት

☞ "ተቀምጦ" ሳይሆን "ተቀምጬ "፤

☞ "አንድ ሰው አየና" ሰይሆን "እኔን አየና"፤"

☞ አለው" ሳይሆን" አለኝ" ወዘተ… መሆን ነበርበት። ነገር ግን ይህንን ወንጌል ማቲዎስ ስላልጻፈው ማቲዎስ እንደሶስተኛ ወገን መጠራቱ የግድ ሆኗል።

2. ማስረጃ ከክርስቲያን ሙሁራን:–

የክርስቲያን ሙሁራን "ማቲዎስ ወንጌል "በተመለከተ እንዲህ በማለት ጽፈዋል። <<ከስሙ እና ከሚሰራው ስራው በቀር ስለዚህ ሰው በውል የታወቀ ነገር የለም። ይህ ሰው በሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ ውስጥ ከሐዋሪያት የስም ዝርዝር ውስጥ ከመጠቀሱ በስተቀር

(የ ሐዋ ስራ1:13) ታሪኩን በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በግልጽ አናገኘውም። በአፈታሪክ ጽሑፎች ውስጥ ግን የተባሉ ነገሮች መኖራቸው ልብ ይሏል። በወንጌሉ ውስጥ ማቲዎስ ጸሐፊው እንደሆነ በግልጽ አልተነገርም።>>

ምንጭ: (ሜሪል ሲ .ቴኒ፤የ አዲስ ኪዳን ቅኝት ገጽ 217)

ክርስቲያን ሙሁራን እንዲህም ብለው ጽፈዋል:— “የማቲዎስ ወንጌል :”ወንጌሉን የጻፈው ማቲዎስ ነው>” ያሉት የቀደሙ የቤትክርስቲያን አባቶች ናቸው እንጂ የጸሃፊው ስም አልተጻፈበትም።መች እንደተጻፈ ደግሞ አልተወቀም።ቲቶ (ጥጦስ)በሚባል በሮም መንግስት የጦር እጅ ኢየሩሳሌም የፈረሰችው በ 70 ዓም ሲሆን ወንጌሉ ከዚያ በፊት ወይም ከዚያ በኃላ ተጽፎ እንደሆነ መምህራን አልተስማሙበትም። በ60 ዓም እና 80 ዓም መካከል ሳይጻፍ አይቀርም ይባላል። (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፤ የኢትዮጲያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ገጽ 41) የመጨረሻው ወንጌል የሆነው የዩሐንስ ወንጌል ደግሞ ከ100-125 ዓ.ል ማለትም እየሱስ ካረጉ ከ70-90 ባሉት አመታት ውስጥ መጻፉ ተገምቷል።።

④)የዮሃንስ ወንጌል ማን ጻፈው?

ወንጌላዊውን ዮሃንስ በተመለከተ ምሁራን ወንጌልን የጻፈው ዮሃንስ የ እየሱስ ደቀመዝሙር የነበረው ዮሃንስ አይደለም ይላሉ ። ተንታኞች እንደሚናገሩት የዮሃንስ ወንጌል ይዘት እና የቃላት አጠቃቀሙ ሲታይ በእየሱስ ሃዋርያው ዮሃንስ የተጻፈ ሊሆን አይችልም ። የሆነ ሰው ጽሮት የበለጠ ተአማኒነት ለማሰጠት ከሃዋርያው ዮሃንስ ጋር አያይዞታል ።

ወንጌሉ የተጻፈው ከ100-125 ዓ.ል ማለትም እየሱስ ካረጉ ከ70-90 ባሉት አመታት ውስጥ መጻፉ ተገምቷል።።ኢየሱስ ሲሰወር ዮሃንስ እድሜው ሃያ(20) አመት ብቻ ነበር ። ቢባል ወንጌሉ በተጻፈበት ጊዜ እድሜው በትንሹ ሰማንያ አራት አመት ነው ።

ታድያ ሃዋርያው ዮሃንስ ወንጌሉን ለመጻፍ እድሜው 84 አመት እስኪሆን ድረስ መቆየት ለምን አስፈለገው ? ስራውን ለመጀመር 64 አመት ሙሉ ምን አስጠበቀው ፤ ይህ የዩሃንስ ወንጌል በሃዋርያው ዮሃንስ አልተጻፈም የሚለውን ማጠቃለያ ያረጋግጣል ።

አዶልፍ ሐርናክ የታዋቂውን የክርስትያን ታሪክ ተመራማሪ የዴቪድ እስትረውስን የምርምር ስራ በመጥቀስ ጸሐፊው ‹የአራተኛውን ወንጌል ብቻ ሳይሆን የመጀመሪያዎቹን ሦስት ወንጌሎችም ታሪካዊ ተአማኒነት ውድቅ አድርገውታል› ሲል ጽፏል።። (What is Christianity, Adolf harnack p 20 (ምንጭ-እየሱስ የኢስላም ነቢይ ገጽ 12-13)

የሀይማኖት ምሁራን ስለ ዮሐንስ ምን አሉ?

ስለ ዮሀንስ ወንጌል በክርስቲያን ምሁራን ከተጻፉት ውስጥ የሚከተለውን በስሱ እንመልከት:-“በዮሀንስ ወንጌልና በሌሎች ሶስት ወንጌላት መካከል በግልጽ የሚታይ ልዩነት በመኖሩ የወንጌሉ ተአማኒነት አጠያያቂ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል። ይህ ወንጌል የተጻፈው በዘብዴዎስ ልጅ በዮሀንስ እንደሆነ ይታመናል በመጀመርያው ምዕተ አመት አካባቢ ስለ ነበረችው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚታወቀው በጣም በጥቂቱ በመሆኑ፤የዚህን ወንጌል አወቃቀር አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ እጅግ አስቸጋሪ ሆኗል።”

(*ምንጭ*-ሜሪል ሲ ቴኒ፣የአዲስ ኪዳን ቅኝት፣አሳታሚ የኢትዮጵያ ቃለ ህይወት)

“ከአራቱ ወንጌሎች የትኞቹም ስለጸሃፊው ማንነት የሚናገሩት ነገር እንደሌለ ቀደም ብለን ተመልክተናል።ነገር ግን ይህ መጽሃፍ ከተጻፈ በ ኋላ ብዙም ሳይቆይ “የ ዮሃንስ ወንጌል የሚል ስያሜ ተሰጠው። በዚህ መንገድ አንባቢያን ጸሀፊው ማን እንደሆነ ሊያውቁ ይችላሉ።

ከጥንት ጊዜ አንስቶ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የዘብዴዎስ ልጅ የሆነው ዮሀንስ አራተኛውን ወንጌል እንደጻፈ ያምኑ ነበር።..ዛሬ ግን ብዙ ወንጌላውያን የሆኑ ምሁራን ይህንን ወንጌል ዮሀንስ እንደጻፈው ይጠራጠራሉ።”

(ምንጭ:-ቲም ፌሎስ የአዲስ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያና ፣በትምህርተ መለኮተ ማስፋፊያ(ትመማ) መልክ የተዘጋጀ 1ኛ መጽሃፍ ጽሁፍ፣ገጽ 440-444።)

የሐገራችን የክርስትና ሐይማኖት አዋቂዎችም በእጃቸው የሚገኘው መጽሐፍ ‹ቅዱስ› መቼና ማን እንደጻፈው ከግምት የዘለለ ሐሳብ እንደሌላቸው እየተሸኮረመሙ ቢሆንም ተናዘዋል፡፡ ተከታዮቹን ምስክርነቶች ለአብነት ያህል እንመልከት፡-

‹ምሁራን ሉቃስ የዚህ ወንጌል ጸሐፊ መሆኑን መጠራጠር የጀመሩት ባለፉት መቶ አመታት ውስጥ ብቻ ነው፡፡… እንደ ሌሎች የመጽሐፍ ‹ቅዱስ› ባለታሪኮች ሁሉ ስለ ሉቃስም ያለን መረጃ የተወሰነ ነው፡፡›

(ምንጭ:ቲሞፎሎስ፣ የአዲስ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ፣ በትምህርተ መለኮት ማስፋፊያ (ትመማ) መልክ የተዘጋጀ፣ ሁለተኛ መጽሐፍ ጽሑፍ፣ ገጽ 336)

‹ዛሬ ግን ብዙ ወንጌላውያን የሆኑ ምሁራን ይህንን ወንጌል ዮሐንስ እንደጻፈው ይጠራጠራሉ፡፡›ቲሞፎሎስ፣ የአዲስ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ፣ በትምህርተ መለኮት ማስፋፊያ (ትመማ) መልክ የተዘጋጀ፣ አንደኛ መጽሐፍ ጽሑፍ፣ ገጽ 440

ከኒቃያ ጉባኤ በፊት ከ270 ያላነሱ የተለያዩ የወንጌል አይነቶች እንደነበሩ የታሪክ ጸሐፍት ይገልጻሉ፡፡ በተለይም የእየሱስን አምላክነት በማይቀበሉ አሐዳውያን ክርስትያኖች እጅግ ጠቃሚ የታሪክና የስነ መለኮት ምንጮች ነበሩ፡፡ጣኦት አምላኪው የወቅቱ የሮም ገዥ በጠራው ጉባኤ ላይ ግልጽ ባልሆነ መስፈርት አሁን በክርስትያኖች እጅ የሚገኙት የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ተመርጠው ሌሎች እንዲቃጠሉና እንዲወገዱ፣ ደብዛቸው እንዲጠፋ ተደረገ፡፡

በእርግጥ ሂደቱ የአጼውን ድጋፍ ለማግኘት ሲባል ንጹሑን የእየሱስ አስተምህሮ ከሮማውያን የጣኣት አምልኮ ጋር በማዳበል አዲስ አይነት ሐይማኖት የመፍጠር ሽፍጥ የተፈጸመበት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ በመሆኑም የሮማ የሦስት አማልክት ጽንሰ ሐሳብ ከክርስትና ትምህርት ጋር ተቀላቅሏል፡፡ የክርስትና ማእከል ከእየሩሳሌም ወደ ሮማ ተዛውሯል፡፡ በሮማዎች የጣኣት አምልኮ ባሕል የጸሐይ ቀን (Sunday) የክርስትያኖች ሰንበት እንዲሆን ተወስኗል፡፡

በክርስትና ላይ እንዲህ አይነት «ማስተካከያዎችን» ያደረጉ ወገኖች የክርስትናን መለኮታዊ ባህሪ ቢያጠፉም ያፄውን ድጋፍ ግን አግኝተዋል፡፡ ይህም ሆነና በርሱ ጉልበት በመታገዝ ተቀናቃኞቻቸውን አሐዳውያንን እያሳደዱ በመጨፍጨፍ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስትያንን የማይገሰስ ስልጣን መመስረት ችለዋል፡፡

አጠር ባለ አነጋገር ያሉን በእጅጉ አጠራጣሪ የሆኑ አራት ወንጌሎች ናቸው;;ከዚህ እንደምንረዳው ሦስቱም ወንጌሎች እየሱስ በሕይወት ሳለ አልተጻፉም፡፡ እርሱ ካረገ ከበርካታ አስርት አመታት በኋላ የተጻፉ ናቸው፡፡ ሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎችም እስከ 150 ዓ.ል ባለው ጊዜ ውስጥ እንደተዋቀሩ ይገመታል፡፡(F.C Grant The Gosples: Their origine and Their Growth, Faber and faber, 24 russel square, Lendon 1957, p 20-21.)

N.B ወንጌል (ኢንጅል) አላህ ለነቢዩ ኢሣ (ለእየሱስ) ያወረደላቸው መጽሐፍ ሲሆን የአዲስ ኪዳንን የተለያዩ ክፍሎች ወንጌላት ብሎ መጥራት አግባብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እየሱስ የሰበከው ትክክለኛ ወንጌል በጽሑፍ አልተላለፈም፡፡ አራቱ ወንጌላት የሚባሉትና ሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ከእየሱስ ሞት በኋላ የተጻፉ ከመሆናቸውም በላይ ከእየሱስ ኦሪጅናል ትምህርት ጋር የሚቃረኑ ናቸው፡፡)

ማጠቃለያ

ከላይ በቀርብነው መረጃ መሰረት ባይብልን ጠቅለል ስናደርገው እንዲህ ብለን ለመወስን እንገደዳለን።

1 ወንጌሎቹ የተጻፉት በማይታወቁ ሰዎች ነው።

2 መጽሀፍ ቅዱስን የጻፉት ሰዎች ቁጥር አይታወቅም።

3 የመጽሀፍ ቅዱስ ታሪኮች የተጻፉበት ቦታ አይታወቅም።

4 መጽሀፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቀን አይታወቅም።

በመጨረሻም አላህ ሱወ ለተለያዩ ጥቅማጥቅሞች ሲሉ የ አምላክ ቃል ያልሆነውን የ አምላክ ቃል ነው ለሚሉ አሳማሚ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው እንዲህ በማለት ያሳስባል።"ለነዚያም መጽሃፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት ይህ ከ አላህ ዘንድ ነው ለሚሉ ወዮላቸው ለነርሱም ከዚያ ከሚያፈሩት (ኃጥጢአት) ው አዮላቸው።""(ቁራአን 2:79)

ኦርጂናል የኢየሱስ(አሰ) ወንጌል (ኢንጂል) የት ነው ሚገኘው?

የኢየሱስ ክርስቶስ(ዐሰ) ከፈጣሪ ዘንዳ ተፅፎ የተሰጠውና ሀዋሪያቱን እየዞረ ያስተማረበት ወንጌል(ኢንጂል) የት ነው ሚገኘው?

እኛ እየጠየቅን ያለነው እየሱስ ክርስቶስ(ዐሰ) ከማስተማሩ በፊት ስለ ውልደቱ እና ተልእኮውን ከጨረሰ በኃላ ስለ እርገቱ የሚያወሩት የአራቱ ወንጌላት ክፍሎች ወንጌል ሳይሆኑ በኢየሱስ ወንጌል ላይ የተጨመሩ የታሪክ መዝገብ ወይም የትውልድ መጽሐፍ ናቸዉ።እናም ግን ልንጠይቃቹ ምንፈልገው ነገር እየሱስ(ዐሰ) በነበረበት ጊዜ የነበረዉ ወንጌል ወይም የኢየሱስ ወንጌል(ኢንጂል) የት ጠፉ ነዉ? የትስ ገባ?

ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና። ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ። (ማርቆስ 1:14)

ማቴዎስ 9:35 ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ፥ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር።

ይህም ወንጌል ለኢየሱስ (ዐሰ) ከአምላኩ የተሰጠው መልዕክት እንደሆነ ኢየሱስ በአንደበቱ ተናግሯል፡-የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፥ (ዮሐ.17:8)

ዮሐ.12:49 እኔ ከራሴ አልተናገርሁምና፤ ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ። ተመልከቱ እንግዲህ ኢየሱስ ወንጌሉ ከፈጣሪ ዘንዳ ተሰጠኝ እያለ ነው። የኛም ጥያቄ እዚህ ጋር ነው ለኢየሱስ ከአምላኩ ዘንዳ የተሰጠው ትዕዛዝ (ወንጌል)ና ሀዋሪያቱን አስተምሮ ያለፈበት አርጂናሉ ወንጌል የት ይገኛል? እስኪ አምጡና አሳዩን። የነ ማቲዎስ፣ሉቃስ ወዘተ ወንጌል ኢየሱስ ካረገ በሁዋላ በስሚ ስሚ የተፃፉ ናቸው እንጂ እንደ ኢየሱስ ከፈጣሪ አልወረደላቸውምና።

ስለ ኢየሱስ ውልደት፣ ዕድገትና ዕርገት የሚያወሩት የአራቱ ወንጌላት ክፍሎች ወንጌል ሳይሆን የታሪክ መዝገብ ነው የሚባሉት፡-

ማቴዎስ 1፥1 የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ።የትውልድ መጽሐፍ የኢየሱስ ወንጌል ሊባል አይችልም። የጠፋው የኢየሱስ ወንጌል የሚጀምረው ከማስተማሩ ነው፡-

ማርቆስ ወንጌል 1.1-3 የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ። እነሆ፥ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ በነቢዩ በኢሳይያስ እንደ ተጻፈ፥

ማርቆስ 1:14 ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና። ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ። ይህ የኢየሱስ ወንጌል የት ነው ያለው?

በአንድ ወቅት ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ወንጌሎች እንደነበሩና ከነኚህ ውስጥ ቤተክርስቲያን አራቱን ማለትም የማቴዎስን፡የማርቆስ፡ የሉቃስንና የዮሐንስን ወንጌሎች ብቻ እንደመረጠች ክርስትና ይነገራል፡፡ቀሪዎቹ ወንጌሎች እንዲቃጠሉ ወይም እንዲጠፉና እንዲወድሙ ሌላው ደግሞ እንዲደበቁ ተደርገዋል፡፡

ኢስላም ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን አንድ ነጠላ የቅዱስ ቁርአን ቅጂ ብቻ መኖሩንና ተመሳሳይ የማማረጥ ሂደት አለመደረጉን ወይም አለማስፈለጉን ይናገራል፡፡

ለመሆኑ ቤተክርስቲያን ምርጫውን በምን መሰረት ላይ ተመርኩዛ ነው ያካሀደችው? ለምንስ እነኛ አራት ወንጌሎች ብቻ በተለይ ተመረጡ? #ለምን ሥስት ወይም አምስት ወይም ደግሞ አስር ወንጌሎች አልተመረጡም???

የተቀሩት ወንጌሎችስ ለምን አልተመረጡም? የእነ የቶማስ ወንጌል፣የበርናባስ ወንጌል፣ የፊሊፕ ወንጌል ወዘተ… ለምን አልተመረጡም?ወንጌሎችን የመምረጥና የማስወገድ መብት ያለው ማነው?

ያን መብትስ ማን ሰጠው? #ወንጌሎች የእግዚአብሄር ቃል ከሆነ ዘንዳ ሌሎቻቸው መወገድ የሚኖርባቸው ለምን ይሆን?

በ 397 AD በካርቴጅ ጉባኤ የቶማስ ወንጌል፣ የይሁዳ ወንጌል፣ የጴጥሮስ ወንጌል፣ የያዕቆብ ወንጌል፣ የበርናባስ ወንጌል፣ የፊሊጶስ ወንጌል፣ የበርተሎሞዎስ ወንጌል፣ የመቅደላዊት ማርያም ወንጌል የተባሉትን አስወጥተው የማቴዎስ ወንጌል፣ የማርቆስ ወንጌል፣ የሉቃስ ወንጌልና የዮሃንስ ወንጌል ብቻ የቀኖና ወንጌሎች ብለው ሌሎችን አፖክራፋ ማለትም ድብቅ ወንጌሎች ብለው ቀነሷቸው፣ ታዲያ በኢየሱስ ወንጌል ላይ እንዲህ መጨመርና መቀነስ እንደተካሄደበት ምሁራኖቻሁ ሳይቀሩ የጻፉትን ነገር እኛ ሙስሊሞች የኢየሱስ ወንጌል ተበርዟል ብንል ቀጠፍን ወይስ አጋፈጥን? ያገሬ ሰው ያልተጠረጠረ ተመነጠረ የተጠረጠረ አስመነጠረ ይሉ የለ?
ዋቢ መጽሃፍትን ይመልከቱ፡-

1. Lost Scriptures: Books that Did Not aMake It into the New Testament. Oxford University Press, USA. 2003

2. The New Testament and Other Early Christian Writings: A Reader. Oxford University Press, USA. 2003

14.የቁርዓን አወራረድ

ቁርኣንን ማን አወረደ ? አላህ ወይስ ጂብሪል ?

A. አላህ፦

25፥1 *ያ ፉርቃንን በባሪያው ላይ ለዓለማት አስጠንቃቂ ይኾን ዘንድ ያወረደው ከብርና ጥራት ተገባው*:: نَزَّلَ الَّذِي تَبَارَكَ نَذِيرًا لِّلْعَالَمِينَ لِيَكُونَ عَبْدِهِ عَلَىٰ الْفُرْقَانَ

B. ጂብሪል፦

2፥97 ለጂብሪል ጠላት የኾነ ሰው በቁጭት ይሙት በላቸው:: *እርሱ ቁርኣኑን ከበፊቱ ለነበሩት አረጋጋጭ ለምእመናን መሪና ብስራት ሲኾን በአላህ ፈቃድ በልብህ ላይ አውርዶታልና*:: بَيْنَ لِّمَا مُصَدِّقًا اللَّهِ بِإِذْنِ قَلْبِكَ عَلَىٰ نَزَّلَهُ فَإِنَّهُ لِّجِبْرِيلَ عَدُوًّا كَانَ مَن قُلْ لِلْمُؤْمِنِينَ وَبُشْرَىٰ وَهُدًى يَدَيْهِ

መልስ

ቁርኣንን ወደ ነብያችን"ﷺ" ያወረደው አምላካችን አላህ ነው፤ እራሱ አላህ፦ "በባሪያችንም ላይ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾኑ ከብጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ" በማለት ይናገራል፦

2፥23 *በባሪያችንም ላይ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾኑ ከብጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ*:: እውነተኞችም እንደኾናችሁ ከአላህ ሌላ መስካሪዎቻችሁን ጥሩ:: مِّن شُهَدَاءَكُم وَادْعُوا مِّثْلِهِ مِّن بِسُورَةٍ فَأْتُوا عَبْدِنَا عَلَىٰ نَزَّلْنَا مِّمَّا رَيْبٍ فِي كُنتُمْ وَإِن صَادِقِينَ كُنتُمْ إِن اللَّهِ دُونِ

25፥1 *ያ ፉርቃንን በባሪያው ላይ ለዓለማት አስጠንቃቂ ይኾን ዘንድ ያወረደው ከብርና ጥራት ተገባው*:: نَزَّلَ الَّذِي تَبَارَكَ نَذِيرًا لِّلْعَالَمِينَ لِيَكُونَ عَبْدِهِ عَلَىٰ الْفُرْقَانَ

አላህ ወደ ነብያት ወሕይ የሚያወርድበት መንገድ ሦስት ናቸው፤ እነርሱም፦ በራዕይ፣ ወይም "ከግርዶ ወዲያ"፣ ወይም "መልከተኛን መልአክን" የሚልክ እና በፈቃዱ የሚሻውን ያወርዳል፦

42:51 ለሰው" አላህ *"በራእይ"፣ ወይም "ከግርዶ ወዲያ"፣ ወይም "መልከተኛን መልአክን" የሚልክ እና በፈቃዱ የሚሻውን "የሚያወርድለት" ቢሆን እንጅ በገሃድ "ሊያናግረው" ተገቢው አይደለም*፤ እርሱ የበላይ ጥበበኛ ነውና። وَمَا كَانَ لِبَشَرٍ أَن يُكَلِّمَهُ ۚ يَشَاءُ مَا بِإِذْنِهِ فَيُوحِيَ رَسُولًا يُرْسِلَ أَوْ حِجَابٍ وَرَاءِ مِن أَوْ وَحْيًا إِلَّا ٱللَّهُ حَكِيمٌ عَلِيٌّ إِنَّهُ

68/*9-+

እዚህ አንቀጽ ላይ "ረሱል" ለ رَسُول የሚለው ቃል "ተላላኪ" ማለት ሲሆን "መለከ" مَلَك ማለትም "መልአክ" የሚለው ቃል ተለዋዋጭ"inter-change" ሆኖ የመጣ ነው፤ ይህም የወህይ መልአክ ጂብሪል"አ.ሰ." ነው፤ አላህ በሦስተኛው መንገድ ነው ቁርኣን ለነብያችን"ﷺ" ያወረደው፤ "መልአክን የሚልክ እና በፈቃዱ የሚሻውን የሚያወርድለት ቢሆን እንጅ" የሚለው ይሰመርበት፤ ጂብሪልም መልአክ እንደመሆኑ መጠን ከአላህ ወደ ነብያችን"ﷺ" ቀልብ ቁርኣንን በአላህ ፈቃድ አውርዶታል፦

2፥97 ለጂብሪል ጠላት የኾነ ሰው በቁጭት ይሙት በላቸው፡፡ *እርሱ ቁርኣኑን ከበፊቱ ለነበሩት አረጋጋጭ ለምእመናን መሪና ብስራት ሲኾን በአላህ ፈቃድ በልብህ ላይ አውርዶታልና*፡፡ بَيْنَ لِّمَا مُصَدِّقًا اللَّهِ بِإِذْنِ قَلْبِكَ عَلَىٰ نَزَّلَهُ فَإِنَّهُ لِّجِبْرِيلَ عَدُوًّا كَانَ مَن قُلْ لِلْمُؤْمِنِينَ وَبُشْرَىٰ وَهُدًى يَدَيْهِ

"በአላህ ፈቃድ በልብህ ላይ አውርዶታልና" የሚለው ሃይለ-ቃል እና "መልክተኛን መልአክን የሚልክ እና በፈቃዱ የሚሻውን የሚያወርድለት ቢሆን እንጅ" የሚለው ሃይለ-ቃል ይሰመርበት፤ ጅብሪል ተልኮ የመጣ መልአክ ነውና ከራሱ አመንጭቶ አይደለም ያወረደው፤ ከዛ ይልቅ ባይሆን ጅብሪል እራሱ የዙፋኑ ባለቤት በሆነው በአላህ ዘንድ የአላህ ባለሟል ነው፤ የአላህ ታማኝ መልእክተኛ ነው፡-

81፥20 የጎይል ባለቤት በዙፋኑ ባለቤት ዘንድ *ባለሟል* የኾነ፡፡ مَكِينٍ ذِى عِندَ قُوَّةٍ ذِى ٱلْعَرْشِ

81፥21 በዚያ ስፍራ ትእዛዙ ተሰሚ፤ *ታማኝ የኾነ ነው*፡፡ أَمِينٍ ثَمَّ مُّطَاعٍ

ጂብሪል "ባለሟል" እና "ታማኝ" መባሉ በራሱ ላኪ እንዳለው ያሳያል፤ ላኪው አላህ፣ ተላኪው ጂብሪል፣ መልእክቱ ቁርአን ነው፤ ጂብሪል ታማኙ መንፈስ ሆኖ ከአላህ ዘንድ ቁርአንን አውርዶታል፡-

26፥193 እርሱን *ታማኙ መንፈስ* አወረደው፤ الْأَمِينُ الرُّوحُ بِهِ نَزَلَ

16፥102 እነዚያን ያመኑትን ለማረጋጋት ሙስሊሞቹንም ለመምራትና ለማብሰር *ቁርአንን ቅዱሱ መንፈስ እውነተኛ ሲኾን ከጌታህ አወረደው* በላቸው፡፡ لِلْمُسْلِمِينَ وَبُشْرَىٰ وَهُدًى آمَنُوا الَّذِينَ لِيُثَبِّتَ بِالْحَقِّ رَّبِّكَ مِن الْقُدُسِ رُوحُ نَزَّلَهُ قُلْ

"ረቢከ" رَّبِّكَ ማለትም "ጌታህ" ከሚለው ቃል መነሻ ቅጥያ ላይ "ሚን" مِن ማለትም "ከ" የሚል መስተዋድድ አለ፤ ይህ የሚያሳየው ታማኙ መንፈስ ከነቢያችን"ﷺ" ጌታ ከአላህ በታማኝነት ቁርአንን እንዳወረደው ነው፤ ስለዚህ ነው አላህ ስለ ጂብሪል ሲናገር፡- "ወደ ባሪያውም አላህ ያወረደውን አወረደ" ብሎ ያለው፡-

53፥10 *ወደ ባሪያውም አላህ ያወረደውን አወረደ*፡፡ أَوْحَىٰ مَا عَبْدِهِ إِلَىٰ فَأَوْحَىٰ

ምን ትፈልጋለህ? አላህ ወደ ባሪያው ያወረደውን ቁርአንን ጂብሪል አወረደው። ቁርአንን አያስተነትኑምን ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ በእርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር፡-

4፥82 *ቁርአንን አያስተነትኑምን ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር*፡፡ ۚ ٱلْقُرْءَانَ يَتَدَبَّرُونَ أَفَلَا كَثِيرًا ٱخْتِلَٰفًا فِيهِ لَوَجَدُوا۟ ٱللَّهِ غَيْرِ عِندِ مِنْ كَانَ وَلَوْ

ቁርአን እንዴት ተጻፈ?

በአቡ ሀይደር

በአላህ ሥም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ከብርና ምሥጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2) የአላህ ውዳሴና ሰላም የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለኾኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ታሀ 47)።

1ኛ/ ቅዱስ ቁርአን የአላህ ቃል ነው። ቃሉም ሆነ መልእክቱ የአላህ ብቻ ነው። በቁርአን ውስጥ የመላእክት፣ የነቢያት፣ የጻሐፊዎች፣ የኢጋንንት ቃልና ሀሳብ አልሰፈረም አይሰፍርምም። በቁርአን ውስጥ ተናጋሪው ጌታ አላህ ብቻ ነው። ስለ ነቢያት የሚተርክልን፣ ስለ መላእክት የሚያወሳልን፣ ይህን አድርጉ ያንን ደግሞ አትቅረቡ! በማለት የሚያናግረን እሱ ጌታ አላህ ብቻ ነው። አንድ ሙስሊም ቁርአንን ከፍቶ አነበበ ማለት፣ ጌታ አላህን አናገረው ማለት ነው። ምክንያቱም በውስጡ የሰፈረው ቃል በጠቅላላ ተናጋሪው አላህ በመኾኑ ማለት ነው። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" يَعْلَمُونَ لَا قَوْمٌ بِأَنَّهُمْ ذَلِكَ مَأْمَنَهُ أَبْلِغْهُ ثُمَّ اللَّهِ كَلَامَ يَسْمَعَ حَتَّى فَأَجِرْهُ اسْتَجَارَكَ الْمُشْرِكِينَ مِنَ أَحَدٌ وَإِنْ " التوبة سورة 6

"ከአጋሪዎችም አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅ #የአላህን_ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው። ከዚያም ወደ መጠበቂያው ስፍራ አድርሰው። ይህ እነሱ የማያውቁ ሕዝቦች በመኾናቸው ነው።" (ሱረቱ-ተውባህ 9፡6)።

2ኛ/ ቅዱስ ቁርአን ከጌታ አላህ ዘንድ ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም) ልብ የወረደው በመልአኩ ጂብሪል (ዐለይሂ-ሰላም) በኩል ነው። እንደሚታወቀው ወሕይ (መለኮታዊ ራእይ) ከጌታ አላህ ወደ ነቢያት ሲተላለፍ፣ በሶስት መንገዶች ነው (ሱረቱ-ሹራ 42፡51)። የመጀመሪያው፡- በራእይ ወይም በህልም አማካኝነት ለነቢይነት ወደተመረጠው ግለሰብ ይወርዳል። ልክ ነቢ ኢብራሂም (ዐለይሂ-ሰላም) ልጁን ኢስማዒልን እንዲያርድ ከአላህ በኩል በህልሙ ትእዛዝ እንደመጣለት ማለት ነው (ሱረቱ-ሷፍፋት 37፡101-112)።

በሌላኛው መንገድ ደግሞ፡- ቀጥታ የአላህ ቃል ያለ መልአክ ጣልቃ-ገብነት ወደ ተመረጠው ነቢይ በመድረስ፣ ያ ነቢይ የአላህን ቃል በጆሮው እያዳመጠ ትእዛዛትን ይቀበላል። ልክ ሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም) በሲናእ ተራራ ላይ ለዐርባ ቀናት ያህል የጌታውን ቃል እንደሰማውና፣ ጌታው አላህም እሱን እንዳናገረው ማለት ነው (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡164፣ ሱረቱል አዕራፍ 7፡143)።

በሶስተኛው መንገድ ደግሞ፡- በጌታ አላህ እና ለነቢይነት በተመረጠው ግለሰብ መካከል፣ መልአክ ይመረጥና፣ ያ መልአክ (ጂብሪል) ከአላህ ራእይን እየተቀበለ፣ አድርስ ወደተባለው ነቢይ ዘንድ ሄዶ የአላህን ቃል ያለ-ምንም ጭመራና ቅነሳ ያስተላልፋል ማለት ነው (ሱረቱ-ነሕል 16፡2)። ቅዱስ ቁርአን ወደ ረሱላችን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ልብ የተወረደው፣ በዚህ በሶስተኛው መንገድ በመልአኩ ጂብሪል (ዐለይሂ-ሰላም) በኩል ነው። ቀጣዮች ቁርአናዊ አንቀጾች ይህንን ሀሳብ ይበልጥ ያብራራሉ፡-

"ለጂብሪል ጠላት የኾነ ሰው (በቁጭት ይሙት) በላቸው፡፡ እርሱ (ቁርኣኑን) ከበፊቱ ለነበሩት (መጻሕፍት) አረጋጋጭ ለምእመናን መሪና ብስራት ሲኾን በአላህ ፈቃድ በልብህ ላይ አውርዶታልና፡፡" (ሱረቱል-በቀራህ 2፡97)፡፡

"እነዚያን ያመኑትን ለማረጋጋት ሙስሊሞቹንም ለመምራትና ለማብሰር (ቁርኣንን) ቅዱሱ መንፈስ (ጂብሪል) እውነተኛ ሲኾን ከጌታህ አወረደው በላቸው፡፡" (ሱረቱ-ነሕል 16፡102)፡፡

"እርሱም (ቁርኣን) በእርግጥ ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው፡፡ እርሱን ታማኙ መንፈስ (ጂብሪል) አወረደው፤ ከአስፈራሪዎቹ (ነቢያት) ትኾን ዘንድ በልብህ ላይ (አወረደው)፡፡" (ሱረቱ-ሹዓራእ 26፡192-194)፡፡

3ኛ/ ቅዱስ ቁርኣን ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ልብ የወረደው በዐረብኛ ቋንቋ ነው፡፡ ማንኛውም ነቢይና መልክተኛ ራእይ የሚወርድለት፡ የተላከበት ማኅበረሰብ (ሕዝቦቹ) በሚረዱትና በሚገባቸው ቋንቋ ነው (ሱረቱ-ኢብራሂም 14፡4)፡፡ ነቢያችን (ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም) የተላኩት ለመላው የዓለም ሕዝብ ቢሆንም፡ የዳዕዋው ጅማሬ ከገዛ ሀገራቸው ስለሆነ የሚነሳው፡ መለኮታዊው ራእይ በዐረብኛ ቋንቋ ሆነ ማለት ነው፡፡ ከአንድ አካባቢ የተነሳ ወንዝ፡ ሌላ ስፍራ ሄዶ የሚያገለግለው፡ ቅድሚያ አካባቢውን ካዳረሰ በኋላ ነውና፡ የቁርኣንም መልክት ለመላው የሰው ልጆች ይዳረስ ዘንድ፡ በየጊዜው አላህ በሚያስነሳቸው የኢስላም ሊቃውንት ሰበብ፡ የቁርኣን መልእክት በየሀገሩ ቋንቋ እየተተረጎመ ተሰራጨ ማለት ነው፡፡ ቅዱስ ቁርኣን በዐረብኛ ቋንቋ ለመውረዱ ቀጣዮቹ ቁርኣናዊ አንቀጾች እንዲህ ይናገራሉ፡-

"እኛ (ፍቹን) ታውቁ ዘንድ ዐረብኛ ቁርኣን ሲሆን በእርግጥ አወረድነው፡፡" (ሱረቱ ዩሱፍ 12፡2)፡፡

"እንደዚሁም ዐረብኛ ቁርኣን ኾኖ አወረድነው፡፡ አላህንም ይፈሩ ዘንድ ወይም ለእነሱ ግሣጼን ያድስላቸው ዘንድ ከዛቻ ደጋግመን በውስጡ ገለጽን፡፡" (ሱረቱ ጣሀ 20፡113)፡፡

"በዚህም ቁርኣን ውስጥ ለሰዎች ይገሠጹ ዘንድ ከየምሳሌው ሁሉ በእርግጥ አብራራን፡፡ መዛባት የሌለበት ዐረብኛ ቁርኣን ሲኾን (አብራራነው)፡፡ ሊጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡" (ሱረቱ-ዙመር 39፡27-28)፡፡

በተጨማሪም፡- (ሱረቱ-ረዕድ13፡37፣ ሱረቱ ፉሲለት 41፡3፣ ሱረቱ-ሹራ 42፡7፣ ሱረቱ-ዙኽሩፍ 43፡3 ይመልከቱ)፡፡

4ኛ/ ቅዱስ ቁርኣን ከጌታ አላህ ዘንድ ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ልብ ሲወርድ በጠቅላላ አንድ ጊዜ አልወረደም፡፡ 23 ዓመታትን በፈጀ ዘመን ውስጥ፡ እንደ አስፈላጊነቱ በሱራዎችና በአንቀጾች ተከፋፍሎ ነው ቀስ በቀስ የወረደው፡፡ በወቅቱ የነበሩ ሰዎች ስለ አንድ የእምነት ጉዳይ ሲጠይቁ ለዚያ ምላሽ ይኾን ዘንድ፣ወይንም አንድን ነገር ይሠሩትና ይፈጽሙት ዘንድ ህግ መደንገግ ሲያስልግ፣ ወይንም አንድን ነገር ይርቁትና ይጠነቀቁት ዘንድ ገደብ ማበጀት ሲያስፈልግ አንድ ሙሉ የቁርኣን ሱራ፡ ወይንም የተወሰኑ አያቶች (አናቅጽ) በጉዳይ ላይ በመመርኮዝ ይወርዳል ማለት ነው፡፡

ለምሣሌ፡- የአላህን ባሕሪያት እንዲሁም ፍጹማዊ አንድነቱን የሚናገረውን የቁርኣንን ከፍል ሱረቱል ኢኽላስን ብንወስድ፣ ይህ ሱራ የወረደበት ሰበብ፡- በወቅቱ የነበሩ ዐረብ ጣኦታውያን (ሙሽሪኩል ዐረብ) ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም) ዘንድ በመምጣት፡- ይህ እኔን መልክተኛ አድርጎ ልኮኛል በማለት፣ የምታመልከውና የምትሰብከውን ጌታ ምንነት ግለጽልን! ብለው በጠየቁ ጊዜ፣ ሱራው ለጥያቄአቸው ምላሽ ኾኖ ወረደ ማለት ነው፡፡ ለዚህም ነው ‹‹ቁል›› የሚል ትእዛዛዊ ግሥን በአንቀጹ መጀመሪያ ላይ ያስቀደመው፡፡

ሌላ ምሣሌ፡- 109ኛውን ሱራ "ሱረቱል ካፊሩንን" እንውሰድ፡፡ ጣኦታውያን የነቢዩ ሙሐመድን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሃይማኖታዊ ስብከት በኃይል ማስቆም ሲያቅታቸው፣ ወደሳቸው ዘንድ በመምጣት፡- በቃ አንድ አመት የኛን (የሀሰት) አማልክት ከኛ ጋር አምልክ፣ በቀጣዩ አመት ደግሞ፣ እኛ የአንተን (እውነተኛ) አምላክ እናምልክ! ብለው ሀሳብ አቀረቡ፡፡ በምላሹም፡- እናንተ ከሀዲያን ሆይ! እኔ እናንተ የምትገዟቸውን የሃሰት አማልክት አልገዛም! ብለህ ነገራቸው የሚል "ሱረቱል ካፊሩን" የተሰኘው መለኮታዊ ቃል፣ ሙሉ ሱራው ወረደ ማለት ነው፡፡ (ተፍ

ሲር ሐዳሊቁ-ሩሒ ወር-ረይሓን፣ ሸይኽ ሙሐመዱል-አሚን ኢብኑ ዐብዲላህ አል-ሀረሪይ)፡፡

ቅዱስ ቁርኣን በቀስታ እየተከፋፈለ ለመውረዱ ማሥረጃ ካስፈለገ፣ ቀጣዮቹን አንቀጾች እናስተውላቸው፡-

"ከርሱ በፊት ያሉትን መጻሕፍት የሚያረጋግጥ ሲኾን መጽሐፉን (ቁርኣንን) ባንተ ላይ #ከፋፍሎ በእውነት አወረደ፡፡ ተውራትንና ኢንጂልንም አውርዷል፡፡" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡2)፡፡

"ቁርኣንንም በሰዎች ላይ በዝግታ ላይ ኾነህ ታነበው ዘንድ #ከፋፈልነው፡፡ #ቀስ_በቀስ ማውረድንም አወረድነው፡፡" (ሱረቱል ኢስራእ 17፡106)፡፡

"እነዚያ የካዱትም «ቁርኣን በእርሱ ላይ ለምን በጠቅላላ አንድ ጊዜ አልተወረደም» አሉ፡፡ እንደዚሁ በእርሱ ልብህን ልናረጋ (ከፋፍለን አወረድነው)፡፡ ቀስ በቀስ #መለያየትንም ለየነው፡፡" (ሱረቱል ፉርቃን 25፡32)፡፡

5ኛ/ ቅዱስ ቁርኣን ከጌታ አላህ ዘንድ ወደ ነቢያችን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ልብ ሲወርድ፣ በልቦናም ሆነ በጽሑፍ ደረጃ ተጠብቆ እንዲቆይ ጌታ አላህ ቃል ገብቶለታል፡፡ ቁርኣኑን የመጠበቅ ኃላፊነትን ለሳቸው ወይንም ለሶሓቦቹ አልሰጠም፡፡ እሳቸው የወረደላቸውን የአላህ ቃል ለሕዝቦቻቸው በቃልም ሆነ በተግባር በማብራራት እንዲያደርሱ ሲታዘዙ፣ እነሱ ሶሓቦቹ (ረዲየላሁ ዐንሁም) ደግሞ፣ በደረሳቸው የአላህ ቃል መሠረት፣ ቃሉን እንዲያነቡና እንዲሰሩበት ታዝዘዋል፡፡ ቃሉን ለመጠበቅ ኃላፊነቱን ግን አላህ ወስዶታል፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

"እኛ ቁርአንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡" (ሱረቱል ሒጅር 15፡9)፡፡

መልአኩ ጂብሪል (ዐለይሂ-ሰላም) ከአላህ ዘንድ የተሰጠውን የቁርአን ክፍል ወደሳቸው ዘንድ በመምጣት በሚያነብላቸው ወቅት፡ እሳቸውም ይጠፋብኛል በሚል ስጋት፡ ወዲው ከመልአኩ አንዲትን ቃል እንደሰሙ፡ ወሕዩ ከማለቁ በፊት፡ የሰሙትን ነገር በመደጋጋም ለመሐፈዝ ፡ምላሳቸውን በፍጥነት ያንቀሳቅሱ ነበር፡፡ ጌታ አላህም፡- ይህን ቁርአን እንዳይጠፋና እንዳትረሳው በማድረግ (የተሻሩ የህግ አንቀጾች ሲቀሩ) ባንተ ልብ ላይ ሰብስቦ ማስቀመጡ የኔ ድርሻ ነውና፡ በቁርአን ንባብ ላይ አትቸኩል፡፡ የመጣልህ መልእክትም እስኪጠናቀቅ ድረስ አዳምጠው፡፡ ከዛም ባንተ ልብ ላይ የተጠበቀ ሆኖ አቆየዋለሁ አላቸው፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

"በእርሱ (በቁርአን ንባብ) ልትቸኩል ምላስህን በእርሱ አታላውስ፡፡ (በልብህ ውስጥ) መሰብሰቡና ማንበቡ በእኛ ላይ ነውና፡፡ ባነበብነውም ጊዜ (ካለቀ በኋላ) ንባቡን ተከተል፡፡ ከዚያም ማብራራቱ በእኛ ላይ ነው፡፡" (ሱረቱል ቂያማህ 75፡16-18)፡፡

"እውነተኛው ንጉስ አላህም (ከሓዲዎች ከሚሉት) ላቀ፡፡ ወደ አንተ መወረዱም ከመፈጸሙ በፊት በማንበብ አትቸኩል፡፡ «ጌታዬ ሆይ! ዕውቀትንም ጨምርልኝ» በል፡፡" (ሱረቱ ጣሀ 20፡114)፡፡

6ኛ/ ቅዱስ ቁርአን፡ በነቢያችን እና በሶሓቦች ልቦና ብቻ ሳይኾን የተቀመጠው፡ በጽሑፍም ተዘጋጅቶ ይቀመጥ ነበር፡፡ የአላህ መልክተኛ ነቢያችን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) በእጃቸው መጽሐፍም ሆነ በመጽሐፍ ላይ ያለን ነገር ማንበብ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ከአላህ ዘንድ አንድ የቁርአን ሱራ ወይንም የተወሰነ አንቀጽ በሚወርድላቸው ጊዜ፡ ከሶሓቦቻቸው አንደኛቸውን በመጥራት፡ ይህንን አንቀጽ እንዲህ በሚባለው ሱራ ውስጥ፣ እንዲህ ተብሎ ከሚጠራው ሱራ ቀጥሎ አስቀምጡት (ጻፉት) በማለት ያዙ ነበር፡፡ ቀጣዩ ሐዲሥ ይህንን እውነታ እንዲህ ያብራራዋል፡-

فَيَقُولُ لَهُ يَكْتُبُ مَنْ بَعْضَ دَعَا الشَّيْءُ عَلَيْهِ أُنْزِلَ إِذَا وَسَلَّمَ عَلَيْهِ اللَّهُ صَلَّى اللَّهِ رَسُولُ كَانَ :-عنه الله رضي- عفان بن عثمان وروى وَإِذَا وَكَذَا كَذَا فِيهَا يُذْكَرُ الَّتِي السُّورَةِ فِي الْآيَاتِ هَذِهِ ضَعُوا قَالَ الْآيَاتُ عَلَيْهِ أُنْزِلَتْ وَإِذَا وَكَذَا كَذَا فِيهَا يُذْكَرُ الَّتِي السُّورَةِ فِي هَذِهِ ضَعُوا قَالَ الْآيَةُ عَلَيْهِ أُنْزِلَتْ. كَذَا فِيهَا يُذْكَرُ الَّتِي السُّورَةِ فِي الْآيَةَ هَذِهِ ضَعُوا (حجر ابن الحافظ وحسنه والحاكم، أحمد رواه).

ዑሥማን ኢብኑ ዐፋን (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዲህ ይላል፡- "የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) አንዳች የቁርአን ክፍል በሚወርድላቸው ጊዜ፡ ከጸሐፊዎቹ አንዱን በመጥራት፡- ‹‹ይህንን አንቀጽ እንዲህ ተብሎ በሚጠራው ሱራ ውስጥ አስቀምጡት››፡፡ አሁንም በድጋሚ የተወሰኑ የቁርአን አንቀጾች ሲወርድላቸው፡ ‹‹እነዚህን አንቀጾች እንዲህ ተብሎ በሚጠራው ሱራ ውስጥ አስቀምጡት›› ይሉ ነበር" (ሙስነድ ኢማሙ አሕመድ 499፣ ሐኪም አል-ሙስተድረክ 2875፣ 3272)፡፡

7ኛ/ ቅዱስ ቁርአንን በአላህ ነቢይ ትእዛዝ የሚጽፉ የነበሩ የተወሰኑ ሶሓባዎች ነበሩ፡፤ እነዚህ ሶሓባዎች ‹‹ኩትታቡል-ወሕይ›› በመባል ይታወቃሉ፡፡ ዋና ዋናዎቹም፡- ሁለቱ ኹለፋኦች (ዑሥማን፣ ዐሊይ)፣ ዘይድ ኢብኑ-ሣቢት፣ ኡበይ ኢብኑ-ከዕብ፣ አርቀም ኢብኑ-አቢ አል-አርቀም፣ ሙዓዊህ ኢብኒ አቢ-ሱፍያን፣ ኻሊድ ኢብኑል-ወሊድ፣ ረዲየላሁ ዐንሁም ናቸው፡፡ ሌሎችም አሉ፡፡

እነዚህ የቁርአን ጸሐፍት፡ ወቅቱ በፈቀደላቸው የጽሕፈት መገልገያ መሳሪያዎች፡- የዘንባባ ዛፍ ቅርፊት፣ ስስ ድንጋይ፣ የቆዳ ቁራጭ፣ ካርቶን፣ በግመል ላይ በሚቀመጠው ኮርቻ፣ የግመል/ የፍየል ሰፋፊ አጥንት ላይ ይጽፉ ነበር፡፡ ከዛም ለራሳቸው ኮፒ ጽፎ በማስቀረት፡ የጻፉትን በአላህ መልከተኛ ቤት ያኖሩት ነበር፡፡

ዘይድ ኢብኑ-ሣቢት (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዲህ ይላል፡- "ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ዘንድ እያለን፡ ቁርአንን በዛፍ ቅርፊት ወይም በቆዳ ላይ እንጽፍ ነበር" (ቲርሚዚይ 4335)፡፡

ይህ በረሱል ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ዘመን፡ በልብ ተሐፍዞ፡ በዘመኑ የጽሕፈት መገልገያ መሳሪያዎች ላይ ተጽፎ የነበረው ቁርአን፡ ወደ አንድ መጽሐፍ የመሰብሰቡ ሂደት ደግሞ፡ መቼ እና እንዴት እንደነበር በአላህ ፈቃድ እንመለከተዋለን ኢንሻአላህ፡፡

ቁርአን እንዴት ተሰበሰበ?

ዛሬ የምንመለከተው ፡- ይህ የአላህ ቃል የኾነው ቁርአን እንዴት ተሰብስቦ አንድ መጽሐፍ እንደኾነ፡ እሱም በማን ጊዜ እንደተሰበሰበ እና ለዚህም ምክንያቱ ምን እንደነበር እንመለከታለን ኢንሻአላህ፡፡ መልካም ንባብ፡-

1ኛ/ ቅዱስ ቁርአን በነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሕይወት ዘመን፡ ከአላህ ዘንድ ወደሳቸው ልብ ወርዶ፣ በሳቸውና በተወሰኑ ሶሓቦች ልብ በቃል የተያዘ ኾኖ፣ እንዲሁም በጽሑፍ ተገልብጦ የተጠናቀቀ ቢኾንም፡ ያ በልብ የተያዘውና በእጅ የተጻፈው ቁርአን ተሰብስቦ አንድ መጽሐፍ ኾኖ አልተዘጋጀም ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያቱ፡-

ሀ/ የወሕይ አለመቋረጥ (አለመጠናቀቅ)፡- የአላህ መልከተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ከአላህ ዘንድ በመልአኩ ጂብሪል (ዐለይሂ ሰለም) አማካኝነት ይወርድላቸው የነበረውን ቁርአን በየጊዜው ይጠባበቁ ነበር፡፡ ከቁርአን ሱራዎች የአንዱ ሱራ የተወሰነ አንቀጽ ይወርድላቸውና፡ ይህ የቁርአን ሱራ ክፍል ሙሉ በሙሉ ወርዶ ከመጠናቀቁ በፊት፡ በቀጣዩ ደግሞ የሌላ ሱራ ክፍል የኾነው የተወሰነ የቁርአን አንቀጽ ይወርዳል፡፡ በመቀጠልም መጀመሪያ ላይ ወርዶ የነበረው ቀሪው የቁርአን ሱራ ክፍል ይወርድና ሱራው ይጠናቀቃል፡፡ ከዚያም የሌላ ሱራ አናቅጽ ወይንም ሙሉ ሱራ ይወርዳል፡፡ ቁርአን የተሟላ ኾኖ እስኪጠናቀቅ ድረስ በዚህ መልኩ ነበር የወረደው፡፡ ይህ ደግሞ ቁርአን ሰብስቦ በሱራዎቹ ቅደም ተከተል መሠረት ለመሰብሰብ አይመችም ነበር ማለት ነው፡፡ (ሙጀዝ ዑሉሚል-ቁርአን 159፣ ዘርከሺይ፡ አል-ቡርሀን ፊ ዑሉሚል ቁርአን 1/262)፡፡

ለ/ የአወራረዱ ቅደም ተከተል፡- የቅዱስ ቁርአን የሱራዎቹና የአንቀጾቹ አቀማመጥና ቅደም ተከተል፡ በአወራረዱ መሠረት አልነበረም፡፡ አንዳንድ የቁርአን ሱራዎች በአወራረድ ቅደም ተከተል መጀመሪያ አካባቢ ላይ የወረዱ ኾነው፡ በቁርአን ላይ ሲቀመጡ ግን ወደ መጨረሻ ላይ ይኾናል ተራቸው፡፡ ለምሣሌ፡- 96ኛው ሱራ ‹‹ሱረቱል-ዐለቅ›› ከ1-5 ያለው አንቀጽ፡ ከቁርአን ክፍል ለመጀመሪያ ጊዜ የወረደ ነው፡፡ ዛሬ ግን በቁርአን ውስጥ አቀማመጡ ከ95 ሱራዎች በኋላ 96ኛ ረድፍ ላይ ነው የሚገኘው፡፡ እንዲሁም 2ኛውን ሱራ ‹‹ሱረቱል-በቀራህን›› ብንመለከተው፡ በመዲና ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ከወረዱት ሱራዎች ነው፡፡ ግን በቁርአን ውስጥ መጀመሪያዎቹ ተርታ ከፋቲሓ ቀጥሎ በ2ኛ ምእራፍ ላይ ነው የተቀመጠው፡፡ ቁርአን እንደ አወራረዱ ቅደም ተከተል ቢኾን ኖሮ የተጻፈው፡ የምእራፎቹ ቅደም ተከተል፡ ቀድሞውኑ በለውኽል መሕፉዝ (በተጠበቀው ሰሌዳ) ከተቀመጠው ጋር የተቃረን ነበር የሚኾነው፡፡ በዚህም ሰበብ ቁርአንን እሳቸው በሕይወት እያሉ፡ ለውኽል-መሕፉዝ ላይ ባለው አቀማመጥ ቅደም ተከተል መሠረት መሰብሰቡ አልተመቸም ማለት ነው፡፡ (ዶክተር. ጀማል ሙስጣፋ ዐብዲል-ሓሚድ፡ ጀምዑል ቁርአን በይነል ሓቃኢቂ-ሣቢተቲ ወሸ-ሹቡሓት አል-ሃቢጠህ 43)፡፡

ሐ/ የመልክተኛው ቆይታ ማጠር፡- ረሱል (ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም) ቁርአን በሳቸው ላይ ተጠናቅቆ ከወረደ በኋላ፡ በሕይወት የቆዩት ለጥቂት ቀናት ነው፡፡ አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፡ ከቁርአን ለመጨረሻ ጊዜ የወረደው በሱረቱል በቀራህ አንቀጽ 281ኛው ላይ የሚገኘው የቁርአን አንቀጽ ነው፡፡ ከዚህ የቁርአን አንቀጽ መውረድና የወሕይ መጠናቀቅ በኋላ በሕይወት የቆዩት ለዘጠኝ ቀናት ያህል ነው፡፡ በነዚህ ቀናት ውስጥ ደግሞ ሙሉውን ቁርአን በአንድ መጽሐፍ ለመሰብሰብ በቂ ጊዜ አልነበረም፡፡

መ/ የሚያነሳሳ ምክንያት አለመኖሩ፡- ሙስሊሞች (ሶሓቦች ረዲየላሁ ዐንሁም) በነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ዘመን፡ በሰላምና በመልካም ሁኔታ ላይ ነበሩ፡፡ ቁርአንን በቃላቸው የሚያነቡ ብዙ ሶሓቦችም ነበሩ፡፡ በኽሊፋው አቡ-በክር ሲዲቅ (ረዲየላሁ ዐንሁ) የኺላፋነት ዘመን እንደነበረው አይነት ፊትናም ይፈጠራል የሚል ስጋት አልነበረም፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ መልክተኛው ራሳቸው በመሐከላቸው በሕይወት ስላሉ፡ ቁርአንን ለመሰብሰብና በአንድ መጽሐፍ ለማድረግ የሚያነሳሳ ነገር አልተፈጠረም ነበር፡፡

2ኛ/ ቅዱስ ቁርአን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰበሰበው፡ ከነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሞት ሁለት አመት በኋላ፡ በአቡ በክር አስ-ሲዲቅ ረዲየላሁ ዐንሁ ዘመነ ንግሥና ጊዜ ነው፡፡ አቡ በክር አስ-ሲዲቅ (ረዲየላሁ ዐንሁ) ኽሊፋ በነበረበት ጊዜ፡ ኢስላምን በመልክተኛው የሕይወት ዘመን የተቀበሉ የተወሰኑ የዐረብ ጎሳዎች፡ ከሳቸው ሞት በኋላ ወደነበሩበት ክህደት ተመለሱ፡፡ ዘካንም ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ኽሊፋው አቡ በክርም (ረዲየላሁ ዐንሁ)፡ እነዚህን ሙርተዶች ለመዋጋት ቦኻሊድ ኢብኑል-ወሊድ (ረዲየላሁ ዐንሁ) የሚመራ ጦርን አዘጋጀ፡፡ ጦርነቱም የሀሰተኛው ነቢይ ነኝ ባይ ሙሰይለመቱል-ከዛብ ሕዝቦች መንደር የሚገኘው ‹‹የማማህ›› በተሰኘው ስፍራ ነበር፡፡ ይህም በሂጅራ አቆጣጠር በአሥራ ሁለተኛው አመት ነበር፡፡ ጦርነቱም እጅግ የተቀጣጠለና የተፋፋመ ነበር፡፡ በመጨረሻም ሀሰተኛው ነቢይ ሙሰይለማህ ተገደለ፡፡ ህዝቦቹም ተሸነፉ፡፡ ከነሱ ውስጥም ከሞት የተረፉት ኢስላምን ተቀበሉ፡፡ ከሙስሊሞቹ በኩል ከአምስት መቶ እስከ ሰባት መቶ የሚደርሱት ሰማእት (ሸሂድ) ሆነዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ሰባ ያህሉ ቁርአንን በቃላቸው ያጠኑ ነበሩ፡፡

የነዚህ የሰባዎቹ ቁርአን ሐፊዞችና ቁርራኦች መገደል በሁለተኛው ኸሊፋ ዑመር ኢብኑል-ኸጣብ (ረዲየላሁ ዐንሁ) ልብ ላይ ስጋትን አሳደረ፡፡ የሐፊዞቹ ሰማእት መሆን፡ የተወሰነ የቁርአን ክፍል በዚያው አብሮ ሊጠፋ ይችላል በሚል ስጋት፡ ወደ ኸሊፋው አቡ በክር (ረዲየላሁ ዐንሁ) ዘንድ በመምጣት፡ ቁርአን በአንድ መጽሐፍ መልክ እንዲሰበሰብ ሀሳብ አቀረበ፡፡ ሙሉ ዘገባውን ከሶሒሕ አል-ቡኻሪይ ላይ እንዲህ ቀርቧል፡-

ዘይድ ኢብኑ-ሣቢት (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዲህ ይላል፡- "አቡ በክር ሲድዲቅ (ረዲየላሁ ዐንሁ) በየማማህ ሰማእት ከሆኑት ሶሓቦች በኋላ ወደኔ እንዲህ የሚል መልክትን ላከ፡፡ (ዘይድ ኢብኑ-ሣቢት ሆይ!) ዑመር ኢብኑል-ኸጣብ እኔ ዘንድ መጣና፡- ‹‹በሶሓቦቹ ላይ ግድያው ተፋፍሟል፡፡ በሶሓቦቹ ላይ ከዚህ የበለጠ ግድያው እየበዛ ይሄድና በዚያውም በቃላቸው ያጠኑት ቁርአን፡ አብዛኛው ክፍል አብሯቸው ሊጠፋ ይችላል የሚል ስጋት አለኝና፡ ቁርአንን በአንድ መጽሐፍ እንዲሰበሰብ ብታዝበት መልካም ነው አለኝ፡፡ እኔም፡- እንዴ

ት መልክተኛው ያልሰሩትን ሥራ ትሰራለህ? ስለው፡ ዑመርም፡- ወላሂ ይህ ሥራ መልካም ነው! መልክተኛውን መቃወም አይደለም! በማለት እኔን ከመወትወት አልተወገደም፡፡ በመጨረሻም አላህ ልቤን አሰፋልኝና ዑመር የተመከተውን ነገር እውነታነት እንደመለከት አደረገኝ፡፡ እናም ዘይድ ሆይ! ‹‹አንተ ገና ለጋ ወጣት ነህ፡፡ በዲንህም የማንጠራጠርህ ጥሩ አዕምሮ ያለህ ነህ፡፡ ለረሱላችን (ዐለይሂ-ሶላቱ ወስ-ሰላም) በሕይወት እያሉ ወሕይን (ቁርአንን) ከሚጽፉትም የቁርአን ጸሐፍት አንዱ ነህ፡፡ ስለዚህ አሁንም ቁርአንን በቃል ካጠኑት ሰዎች ጋር በማመሳከር፡ የተጻፉትን በመሰብሰብ በአንድ መጽሐፍ ሰብስበው›› አለኝ፡፡ በጌታዬ ይሁንብኝ! እኔ ግን ከተራራዎች መሐል አንዱን ከቦታው ንቀለው! ብለው ቢያዙኝ ኖሮ፡ ቁርአንን ሰብስበው ብለው ካዘዙኝ ትእዛዝ የበለጠ አይከብድብኝም ነበር፡፡ ስለኾነም እንዲህ አልኳቸው፡- ‹‹እንዴት የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም) ያልሰሩትን ነገር ትሠራላችሁ?›› አቡ በክርም (ረዲየላሁ ዐንሁ)፡- ‹‹ወላሂ! ይህ መልካም ሥራ ነው! ብሎ በመማል፡ በሥራው ላይ እንድሳተፍ ከመወትወት አልተወገደም፡፡ በመጨረሻም ለአቡ በክርና ለዑመር ልባቸውን ያሰፋው አላህ፡ እኔም ሥራው መልካም ኾኖ እንዲታየኝ ልቤን አሰፋልኝ፡፡ ከዚያም ቁርአንን በመከታተል፡ በአማኞች ልቦና በቃል የሚያነቡትን ተጽፎ ከተቀመጡት ጋር እያመሳከርኩ ቁርአንን ሰበሰብኩት" (ቡኻሪይ 4679, 4986, 6768)::

3ኛ/ ይህ ቅዱስ ቁርአንን በአንድ መጽሐፍ የመሰብሰቡ ሥራ የተጠናቀቀው በአሥራ አምስት ወራት ውስጥ ነው፡፡ በሂጅራ አቆጣጠር በአሥራ ሁለተኛው አመት ጅማሬ ላይ ከየማማው ጦርነት በኋላ ተጀመረ፡፡ ለአሥራ አምስት ወራት የቆየ ኾነ፡፡ በአሥራ ሶስተኛው ዓመተ ሂጅራህ በስድስተኛው ወር ላይ ደግሞ (ከቁርአኑ ተሰብስቦ መጠናቀቅ የተወሰነ ቆይታ በኋላ) አቡ በክር ሲዲቅ (ረዲየላሁ ዐንሁ) ምድራዊ ቆይታቸውን በማጠናቀቅ ሞቱ ማለት ነው፡፡

ምንጭ፡- ዶክተር. ዓሊይ ኢብኑ ሱለይማን አል-ዑበይድ፡ جمع القرأن الكريم وكتابة حفظا

"የቁርአን ተአምራቶች"

ካለዲኔ ፈዝቡከ ለምኔ

በቁርአን ውስጥ ከሚገኙ የተአምራት መገለጫዎች

1. የመጀመሪያ መገለጫ፡-

የቁርአን ያማረ ቅንብሩ፣የቃላት አሰካኩ፣ የተሳካና ልብ የሚማርክ መልእክቱ፣ የማብራራት ምጥቀቱና የአረቦችን የቋንቋ ከህሎት ሰንጥቆ ያለፈ ያገላለፅ ኃይሉ፣ ከጥበበኛውና ከምስጉኑ (አምላክ) የወረደ፣ አንቀፆቹ በጥበብ የተቀመሩ፣ቃላቶቹ በሚገባ የተብራሩ፣ ያገላለፅ ምጥቀቱ አእምሮን የዘለለ፣ የቋንቋ ፍሰቱ ንግግርን ሁሉ ያስናቀ መሆኑ ።

2. የሁለተኛው መገለጫ

አስገራሚ ሰርአታዊ ቅንብሩ፣ እንግዳ የሆነና ከአረቦች የንግግር ዘይቤ እንዲሁም የቋንቋ ህግጋትና ሥርአት የተለየ መሆኑ ፣ቁርአን የመጣበት የአነጋገር ስልት ፣የአንቀፆቹ አከፋፈልና የመቆሚያ ቦታ ስኬት ፣ የቃላቶቹ መጣጣምና የመለያ ክፍፍላቸው ጥምረት፣ ከርሱ በፊትም ሆነ ከርሱ በኋላ ተወዳዳሪ የማይገኝለት መሆኑ፣ አንድም ሰው በከፊል እንኳን የርሱን ተመሳሳይ ማምጣት አለመቻሉ ። ለዚህ ነው (ቁርአንን) በጥላቻው ቁንጮ ደርሶ የነበረው ኡትባ ብኑ ረቢዓ ቁርአንን በሰማ ጊዜ እንዲህ ያለው፡- ‘’ሰዎች ሆይ እኔ አንድን ነገር በእርግጥ ሳላውቀው ፣ ሳላነበውና ሳልናገረው እንደማልተወው ታውቃላቸሁ። በአላህ እምላለሁ እርሱን የሚመስል ሰምቶ የማላውቀውን ንግግር በእርግጥ ሰማሁ። እርሱ ግጥምም አይደለም፣ ድግምትም አይደለም፣ጥንቆላም አይደለም።’’

3. ሦስተኛው መገለጫ

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ሆነው ሳለ ቁርአን ከህይወት መፈጠር ጀምሮ በርሳቸው ላይ እስከ ወረደበት ጊዜ ድረስ ቀድመው የተከሰቱ ነገሮችን መዘገቡ አንዱ ተአምር ነው።ቁርአን የነቢያቶችና የህዝቦቻቸውን ታሪክና በዘመኑ የጠፉ ህዝቦችን ሁኔታ ዘግቧል። ከመጽሐፉ ባለቤቶች ለቀረቡ ዋሻ ውስጥ (ሦስት መቶ ዘጠኝ አመት) ሲኖሩ ስለነበሩ ህዝቦች፣ ስለ ሙሳና ኸድር (ሰላም በእነርሱ ላይ ይውረድና)፣ ስለ ዙል-ቀርነይን ሁኔታና ስለሌሎችም ፈታኝ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል።

4. አራተኛው መገለጫ

በወህይ (በጅብሪል አማካኝነት ከአላህ በቀጥታ ለነብዩ ሙሐመድ የሚወርድ መልእክት) ካልሆነ በስተቀር በወቅቱ ሊታወቁ የማይችሉ ወደፊት የሚከሰቱ ክስተቶችን መዘገቡ ሌላው ተአምር ነው።ቁርአን እንደሚፈፀሙ የተናገራቸው እነዚህ ክስተቶች ከንግግሩ አንድም ነገር ሳይቀር የተፈፀሙ አሉ፡፡ ከነዚህ መካከል በሱረቱል ፈትህ ቁጥር 27 ላይ ‘’አላህ ለመልእክተኛው ሕልሙን አውነተኛ ሲሆን አላህ የሻ እንደሆነ ጸጥተኞች ሆናችሁ ራሶቻችሁን ላጭታችሁ አሳጥራችሁም የማትፈሩ ስትሆኑ የተከበረውን

መስጊድ በእርግጥ ትገባላችሁ…'' ያለውንና በሱረቱል-ሩም ቁጥር 2-3 ''ሩም ተሸነፈች፤ በጣም ቅርብ በሆነችው ምድር። እነርሱም ከመሸነፋቸው በኋላ በእርግጥ ያሸንፋሉ፤ በጥቂት ዓመታት ውስጥ (ያሸንፋሉ)…'' ያለውን መጥቀስ ይቻላል።

5. አምስተኛው መገለጫ

እርሱነቱ ዘውታሪ፣ ተአምሩ ዘላለማዊ፣ የአመታት መቀያየር ምንም የማይበግረው፣ እስከ ዕለተ-ቂያማ ድረስ የዘመን መለዋወጥ ክብሩን የማይቀንሰው መሆኑ ሌላ ተአምር ነው። ቁርአን ዘውታሪና ዘላለማዊ ከመሆኑ ጋር አላህ (ሱ.ወ.) ሊጠብቀው ቃል ገብቶለታል፡-

" إنا نحن نزلنا الذكر وإنا له لحافظون (الحجر 9)

''ቁርአንን እኛው አወረድነው፣ እኛም ለርሱ ጠባቂዎቹ ነን'' (አል-ሂጅር 9)

" لا يَأْتِيهِ البَاطِلُ مِن بَيْنِ يَدَيْهِ ولا مِنْ خَلْ تَنزِيلٌ مِّنْ حَكِيمٍ حَمِيدٍ (فصلت 42)

'' ከኋላውም ከፊቱም ውሸት አይመጣበትም ጥበበኛ ምስጉን ከሆነው ጌታ የተወረደ ነው'' (አል-ፉሲለት 42)

6. ስድስተኛው መገለጫ

ባጠቃላይ አረቦችም ሆነ በተለይም ደግሞ ነብዩ ሙሐመድ ከነብይነታቸው በስተፊት በዘመኑ የማያውቁት፣ በዚያን ጊዜ አሉ የሚባሉ ሊቃውንቶች ያልደረሱበት፣በወቅቱ ከነበሩት ጽሁፎቻቸው ያልተጻፈ ትምህርትና ዕውቀትን ቁርአን ሰብስቦ የያዘ መሆኑ ሌላኛው ተአምር ነው። አላህ እንዲህ በማለት እውነትን ተናገረ፡-

" ولَقَدْ ضَرَبْنَا لِلنَّاسِ فِي هَذَا القُرْآنِ مِن كُلّ مَثَلٍ لَّعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ (الزمر 27)

''በዚህም ቁርአን ውስጥ ለሰዎች ይገሠጹ ዘንድ ከየምሳሌው ሁሉ በእርግጥ አብራራን'' (አል-ዙመር 27)

7. ሰባተኛው መገለጫ

የቁርአን ሳይንሳዊ ተአምራት፡-ቁርአንን ለሚያነብና በሰው ልጅና በዩኒቨርስ አንዲሁም በሌሎች የሳይንስ ጥናት ዘርፎች ግንዛቤ ያለው ሰው የሚረዳው ነገር ቢኖር በሰው ልጅ አእምሮ ለተገኙ ማንኛውም አይነት ሳይንሳዊ እውነታዎች በሙሉ በምልክታ ወይንም በቀጥተኛ መልኩ በቁርአን ውስጥ የተጠቀሰ መነሻ እንዳላቸው ነው። (ሳይንሳዊ ተአምሮች በተከበረው ቁርአን ውስጥ፤ ሸህ ዘንዳኒና ዶክተር ዘግሉል አል-ነጃር የተወሰደ) ይህ የቁርአን ባህሪ መቆሚያ የሌለው ነው። የሰው ልጅ የሳይንሳዊ ዕውቀቱ

እየሰፋ በሄደ ቁጥር የቁርአን ተአምራዊነት፣አስደናቂነትና ታላቅነቱ ለሳይንቲስቶች የበለጠ ግልፅ እየሆነ ይመጣል። አላህ እንዲህ በማለት እውነትን ተናገረ፡-

" سَنُرِيهِمْ آيَاتِنَا فِي الآفَاقِ وفِي أَنفُسِهِمْ حَتَّى يَتَبَيَّنَ لَهُمْ أَنَّهُ الحَقُّ أَوَ لَمْ يَكْفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُ عَلَى كُلّ شَيْءٍ شَهِيدٌ (فصلت 53)

‘’እርሱም (ቁርአን) እውነት መሆኑን ለነርሱ እስከሚገለፅላቸው ድረስ በአፅናፍቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተአምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን።ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ አይበቃችሁምን?’’ (ፉሲለት 53)

8. ስምንተኛው መገለጫ

ቁርአን እርሱን የሚያዳምጡ ሰዎችን ልብ በአስገራሚ ሁኔታ የመማረክ ሀይሉና በሚያነቡት ሰዎች ላይ የሚፈጥረው ከባድና ብርቱ ተፅኖ ሌላኛው የተአምር መገለጫ ነው። ቁርአን በአስተባባዮች ላይ የሚያሳድረው ጫና በጣም ከባድና አደገኛ ነው።። ከዚህም የተነሳ (አስተባባዮች) ለራሳቸው፣ለሴቶቻቸውና ለልጆቻቸውም ጭምር ቁርአንን ማዳመጥ ከሚፈጥርባቸው ተፅኖ በመፍራት እንዲህ ይሉ እንደነበር በሱረቱል-ፉሲለት ቁጥር 26 ተገልጿል፡-‘’ “ لَا تَسْمَعُوا لِهَٰذَا الْقُرْآنِ

وَالْغَوْا فِيهِ لَعَلَّكُمْ تَغْلِبُونَ ”

“ይህንን ቁርአን አትስሙ ታሸንፉም ዘንድ በርሱ ውስጥ (ሲነበብ) ተንጫጩ” የአማኞችን ሁኔታ ስንመለከት የቁርአን ድንቅ ማራኪነት፣ በነፍሶቻቸው ላይ የሚያሳድረው ብርቱ ተፅኖና እንዲሁም በልቦቻቸው ላይ የሚፈጥረው ልዩ የክብር ስሜት ይህንን መለኮታዊ መጽሐፍ እንዲናፍቁት፣ ሌሎች ስነ-ጽሑፎችንም ሆነ ንግግሮች እንዲርቁና ከምንጭ አጠገብ እንደበቀለ ቡቃያ ልባቸውን የሚያረጥቡበት የህይወታቸው አካል አድርገውት እንዲኖሩ አስችሏቸዋል። ለመሆኑ ለዚህ ሁሉ ምስጢሩ ምንዲን ነው? በሙእሚኖች ደም ውስጥ የተሰራጨው ይህ አዲስ ሩህ ምን ይሆን? የሙስሊሞችን ነፍስ በበላይነት የማረከው ይህ ተአምር ምን ይሆን? እርሱ በርግጥ አላህ (ሱ.ወ.) ይህንን የማድረግ ሀይል የቸረው የራሱ የአላህ (ሱ.ወ) መጽሐፍ (ቁርአን) ነው። አላህ (ሱ.ወ.) ስለ ቁርአን በሱራ-አልዙመር እንዲህ ብሏል፡-

” اللَّهُ نَزَّلَ أَحْسَنَ الحَدِيثِ كِتَابًا مُتَشَابِهًا مَثَانِى تَقْشَعِرُّ مِنْهُ جُلُودُ الذِينَ يَخْشَوْنَ رَبَّهُمْ ثُمَّ تَلِينُ جُلُودُهُمْ وقُلُوبُهُمْ إِلَى ذِكْرِ اللَّهِ ” (الزمر 23)

“አላህ ከዜና ሁሉ መልካምን ተመሳሳይ ተደጋጋሚ የኾነን መጽሐፍ አወረደ፤ ከርሱ (ግሣጼ) የነዚያ ጌታቸውን የሚፈሩት ሰዎች

ቆዳዎች ይኮማተራሉ፤ ከዚያም ቆዳዎቻቸውና ልቦቻቸው ወደ አላህ (ተስፋ) ማስታዎስ ይለዝባሉ… “ በሱራ-አልሀሽር አንቀፅ 21 ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

” لَوْ أَنزَلْنَا هَذَا الْقُرْآنَ عَلَى جَبَلٍ لَرَأَيْتَهُ خَاشِعًا مُتَصَدِّعًا مِّنْ خَشْيَةِ اللَّهِ ” (الحشر 21)

“ይህንን ቁርአን በተራራ ላይ ባወረድነው ኖሮ ከአላህ ፍራቻ (የተነሳ) ተዋራጅ፣ ተሰንጣቂ ኾኖ ባየኸው

ነበር…”።

‹‹ሙሰዲቅ›› እና ‹‹ሙሀይሚን››

በአቡ ሀይደር

በአላህ ሥም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2)፡፡ የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡

የሰማይና የምድር ጌታ የሆነው አምላካችን አላህ ሰዎችን በዚህ ምድር ላይ ሲፈጥራቸው ለትልቅ ዓላማ ያውም እሱን በብቸኝነት እንዲያመልኩት ነው (አል-ዛሪያት 51:56-58):: በዚህ ዓላማ ሁሉም ይስማማል፡፡ ግን የሚነሳው ጥያቄ፡- ታዲያ ይህን ጌታ እንዴት እናምልከው? እኛ በምንፈልገው መንገድ ወይስ እሱ በሚፈልገው መንገድ? የሚል ይሆናል፡፡ ለዚህም ሁላችንም በመስማማት የምንሰጠው መልስ፡- እሱ በሚፈልገው መንገድ የሚለውን ነው፡፡ ይህም ሌላ ጥያቄ ያስነሳና፡- ታዲያ አላህ ከኛ የሚፈልገው የአምልኮ ዓይነት የትኛው ነው? የሚጠላውስ? ያስብላል፡፡ እሱ የሚወደውና የሚጠላው የአምልኮ ዓይነት ምን ምን እንደሆነ በቀጥታ በግልጽ እንዳይነግረን ሰው የሱን ቃል ሰምቶ በህይወት መኖር አይችልም፡፡ ወይም መላእክትን እንዳይልክልን፡ መላእክትና ሰው ፈጽሞ የባሕሪ ግንኙነት የላቸውም፡፡ ስለዚህ አላህ እኛን የመፍጠሩን ዓላማ በዝርዝር ለመግለጽ፡ ከራሳችን ከሰዎች መካከል ሰዎችን መርጦ፡ የመረጣቸውን ሰዎች ነብይና መልክተኛ አድርጎ ወደኛ ላከልን፡፡ በላካቸው መልክተኞች በኩል ደግሞ ቃሉን በማስተላለፍ እኛን የመፍጠሩን ዓላማ ገለጸልን፡፡ እነዚህም በነቢያት በኩል የተሰጡ የአምላክ ቃላት በብእር ተከትበው ሲጠረዙ “መለኮታዊ መጽሐፍት” ይሰኛሉ፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

“መልክተኞቻችንን በግልፅ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ መጽሐፎችንና ሚዛንን ወደነርሱ አወረድን…” (ሱረቱል ሐዲድ 57፡25)፡፡

ቅዱስ ቁርአን እነዚህን ቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍት አረጋጋጭ "ሙሰዲቅ" ነው፡፡ በዛው መልኩም ተቆጣጣሪ "ሙህይሚን" ነው፡ ፡ አረጋጋጭ ማለት፡- እነዚህ ቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍት ከአላህ ዘንድ የወረዱ፡ በወቅቱ ለነበሩት ነቢያት የተሰጡ፡ የአላህ ቃልና የሕይወት መመሪያን ያካተቱ አምላካዊ ቃል እንደሆኑ መመሥከርና ማረጋገጫ መስጠት ማለት ነው፡፡ ተቆጣጣሪ ማለት ደግሞ፡- እነዚህ መለኮታዊ መጽሐፍት ወደ ምድር ወርደው ማገልገል ከጀመሩ በኋላ፡ በጊዜ ቆይታ ምክንያት በመጽሐፎቹ ላይ የተደረገ ጣልቃ ገብነት መኖሩን፣ የሰው ሀሳብ የተካተተባቸው መኾኑን በመግለጽ፡ እውነት በሀሰት ተደብቃ እንዳትቀር ትክክለኛውን እውነት በመመሥከር የቀደመውን መቆጣጠር ማለት ነው፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

“ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በውነት አወረድን…” (ሱረቱል-ማኢዳህ 5፡48)፡፡

ከዚህ አንቀጽ ሶስት ነገራትን እንገነዘባለን፡፡ እሱም፤-

1/ ቅዱስ ቁርአን በነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ልብ ላይ የተወረደ፡ ፍጹም እውነት የኾነ አምላካዊ ቃል መኾኑን፣

2/ ይህ ቅዱስ ቁርአን፡ ከሱ በፊትም ሌሎች አምላካዊ መጽሐፍቶች ከአላህ ዘንድ ወደ ነቢያቱ እንደተወረዱ በመመሥከር እንደሚያረጋግጥና፣

3/ ቁርአን እነዚሁኑ ቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍት፡ የበላይ ተቆጣጣሪያቸው በመሆን፡ የሰው እጅ የገባበትን ሐሳብ በማስተካከል ትክክለኛውን ነገር በማስተማር እና እውነታው ተደብቆ እንዳይቀር ቁጥጥር በማድረግ ተጠባባቂ መኾኑን እንረዳለን፡፡

አንዳንድ ወገኖች የቅዱስ ቁርአንን አረጋጋጭነት ለመጽሐፍ ቅዱሳቸው እውነተኛነት ምሥክር ሊያደርጉት ይሞክራሉ፡፡ ቁርአን የመሠከረለትን መጽሐፍ ቅዱሳችንን እንዴት እናንተ ተበረዘ፡ ተደለዘ በማለት ትቃወማላችሁ? በማለትም ጥያቄን ያቀርባሉ፡፡ ለዚህ ጥያቄያቸው መጠነኛ ምላሽን ከዚህ በታች እናቀርባለን፡፡

ሀ/ ቅዱስ ቁርአን ከሱ በፊት የነበሩትን ቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍት እንደሚያረጋግጥ የተናገረውን ክፍል በርግጥም ትክክል ነው ብላችሁ ታምኑበታላችሁን? አዎ! ከኾነ ምላሻችሁ፡ በቁርአንም እውነተኛነት አምናችኋል ማለት ነው፡፡ አይ! አናምንበትም ካላችሁ ደግሞ፡ እንግዲያውስ ከውስጡ ጥቅስን መዝዛችሁ በማውጣት፡ ያ ጥቅስ የናንተን መጽሐፍ እንደሚያከብረው ለመግለጽ መሞከሩ ለምን አስፈለጋችሁ? የማታምኑበትን ጥቅስ ለማስረጃነት መገልገላችሁ ምን ትርጉም አለው?

አንድ ሙስሊም መጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሶ ‹‹ኢየሱስ ነቢይ ነው!›› የሚል ጥቅስ ቢያሳያቸሁ፡ እሱ ነቢይ መኾኑን ስላመነበትና እናንተም ነቢይ ነው ብላችሁ በማመን እምነታችሁን እንድታስተካክሉ ካለው ቅን ፍላጎት ስለመነጨ ነው፡፡ ወይንም የኾነ የመጽሐፉን ክፍል በመጥቀስ፡ ይህ ስህተት ነው ብሎ የሚቃወመው፡ የጠቀሰው ክፍል ተሳስቷል ብሎ ስላመነ ነው፡፡ እናንተ ግን ለመጽሐፋችሁ እውነተኝነት የቁርአንን ምሥክር የምትጠቀሙት በቁርአኑ ምሥክርነት አምናችሁ ነውን ወይስ ምን ፈልጋችሁ? ጥያቄ ዓላማ ከሌለው ጊዜ መግደል ብቻ ይኾናልና፡፡

ለ/ ቅዱስ ቁርአን ማረጋገጫነቱን የሚሰጠው ጥቅላዊና ዝርዝር በኾነ መልኩ ነው፡፡ ለምሣሌ፡- ‹‹ከሱ በፊት የወረዱትን መጽሐፍት የሚያረጋግጥ›› በማለት፡ በብዙ የቁርአን ክፍሎች ላይ ይናገራል፡፡ እነዚህ ቀደምት መጽሐፍት በመባል ጥቅላዊ በኾነ መልኩ በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱት ‹መጽሐፍ ቅዱስ› ለመኾኑ ምን ማረጋገጫ መስጠት ትችላላችሁ? ምክንያቱም ቃሉ ላይ ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ›› የሚል እተጻፈምና፡፡

አንዳንድ ስፍራ ላይ ደግሞ ‹ተውራት› ‹ዘቡር› ‹ኢንጂል› በማለት ሥም በመጥቀስ ለመጽሐፎቹ ምሥክርነትን ይሰጣል፡፡ ግን ተውራት ማለት ኦሪት፣ ዘቡር ማለት መዝሙር፣ ኢንጂል ማለት ወንጌል ነው ብሎ ማን ተረጎመላችሁና ነው፡ ይህን ማረጋገጫነት ለመጽሐፋችሁ የምትገለገሉበት?

ምክንያቱም፡- መጽሐፍ ቅዱስ ማለት በናንተ ገለጻ፡ ከእግዚአብሄር ዘንድ ለነቢያቱ የተሰጠ የራሱ የእግዚአብሄር ቃል ሳይኾን፡ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በነቢያትና ሐዋሪያት የተጻፈ መጽሐፍ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈሩት ቃሎች በጠቅላላ እግዚአብሄር የተናገራቸው ናቸው ብላችሁ እናንተም አታምኑም፡፡ አብዛኞቹ የመጽሐፉ ክፍሎች ደግሞ የታሪክ መጽሐፍት ናቸው፡፡ የነገስታትን ታሪክ በሰፊው ይዘዋል፡፡ የአላህ ቃል የኾነው ቁርአን ደግሞ ምሥክርነትን የሚሰጠው፡ አላህ ስላወረደውና ለሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም) በመለኮታዊ እጁ ጽፎ ስለሰጠው ስለ ቃሉ ስለ ተውራት እንጂ፡ በሙሴና በእያሱ ስለተጻፈው፡ የሙሴን የሕይት ታሪክ ስላቀፈው፡ እንዲሁም ልደቱንና አሟሟቱን ስለሚተርከው የኦሪት መጽሐፍ አይደለም፡፡

ቅዱስ ቁርአን ምሥክርነቱን የሚሰጠው፡ አላህ ስላወረደውና ለዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ስለሰጠው፡ የራሱ መለኮታዊ ቃል ስለኾነው ኢንጂል እንጂ፡ እነ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ እና ዮሀንስ ስለጻፉት ወንጌል አይደለም፡፡ አላህ ኢንጂልን ለዒሳ ሰጠሁት አለ እንጂ፡

ለነዚህ ወንጌላውያን ሰጠኋቸው አላለም፡፡ ከዚህ በመነሳት ቅዱስ ቁርአን ቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍትን ‹‹አረጋጋጭ›› ነው ሲባል እናንተ የተረዳችሁበት መንገድ ፍጹም ስህተት እንደኾነ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስህተቱን ለማረም ከፈለጋችሁ ግን በቀላሉ፡-

• ቁርአን ተውራት የሚባልን መጽሐፍ አላህ ለሙሳ ዐለይሂ-ሰላም እንደሰጠው፡ ለእስራኤላውያኖችም የሕይወት መተዳደሪያ እንዲሆን የሰጣቸው የህግ መጽሐፍ መኾኑን ይመሠክራል፡፡ (ሱረቱ አለ-ዒምራን 3፡93 አል-ማኢዳህ 43-44)

• ቁርአን ዘቡር የሚባልን መጽሐፍ፡ አላህ ለዳዉድ ዐለይሂ-ሰላም እንደሰጠው፡ በዚህ መለኮታዊ መጽሐፍ መሠረትም አላህን በመዘከር፣ በማወደስና በማውሳት፡ የጌታውን ክብር ከፍ የሚያደርግበት የአምልኮ መጽሐፍ እንደኾነ ይመሠክራል ማለት ነው፡፡ (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡163፣ አል-ኢስራእ 17፡55)፡፡

• ቁርአን ኢንጂል የሚባል መጽሐፍን፡ አላህ ለዒሳ ዐለይሂ ሰላም እንደሰጠው፡ በዚህ መለኮታዊ መጽሐፍም እስራኤላውያንን የሚያስተዳድርበት መመሪያን እንዳቀፈ ይመሠክራል፡፡ (ሱረቱል ማኢዳህ 5፡46፣ አል-ሐዲድ 57፡27)፡፡

• ቁርአን ሌሎች በሥም ያልተጠቀሱ መለኮታዊ መጽሐፍት መኖራቸውን በመጥቀስ፡ አላህ ለነቢያቱ እንደሰጠ ጥቅላዊ በኾነ መልኩ በመግለጽ ለመጽሐፍቶቹ ምሥክርነትን ይሰጣል፡፡ (ሱረቱል በቀራህ 2፡136፣ አል-በቀራህ 2፡285፣ አሊ-ዒምራን 3፡84)፡፡

• ቁርአን እነዚህ መለኮታዊ መጽሐፍቶች የሰው እጅ እንደገባባቸው፡ ቃላት ከውስጣቸው እየወጣ በሌላ እየተተካ መለወጣቸውን ይመሠክራል፡፡ (ሱረቱል በቀራህ 2፡75፣ አል-በቀራህ 2፡79፣ አን-ኒሳእ 4፡46፣ አል-ማኢዳህ 5፡41)፡፡

ሐ/ ቅዱስ ቁርአን ከአንድ ሙስሊም የሚፈልገው እምነት፡- አላህ ባሮቹን በከንቱ እንዳልተዋቸውና በየዘመናቱ ህግና መመሪያን በነቢያቱ በኩል በመላክ መለኮታዊ መጽሐፍትን እንደሰጣቸው አምኖ መቀበሉን ነው፡፡ ደግሞም እነዚህ ቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍት የተሰጡት፡ በወቅቱ ለነበሩት ነቢያት በመኾኑ፡ መልእክታቸው በዘመንና በቦታ የተገደበ እንደኾነ ማመኑን ነው፡፡ ዘመንም ኾነ ስፍራ ሳይገድበው፡ በየትኛውም ዘመንና ቦታ ለሚኖር የዓለም ሕዝብ መለኮታዊ መመሪያ ኾኖ የወረደው ቅዱስ ቁርአን ብቻ ነው፡፡ (አል-አንዓም 6፡90፣ አል-ፉርቃን 25፡1፣ አል-አንቢእ 21፡107)፡፡ በቁርአን መውረድ ሰበብ፡ የቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍት ህግጋት ተሻረ፡፡ ትምሕርታቸውም በቁርአን ተተካ፡፡ ከዚህ ቁርአን መውረድ በኋላ፡ የሚመጣ ማንኛውም ሰው በቁርአን አምኖ፡ በቁርአን ህግ ሕይወቱን ከመምራት ውጭ ሌላ ምንም መዳኛ የለውም፡፡ ቁርአን የመጨረሻው መለኮታዊ መጽሐፍ፣ ነቢዩ ሙሐመድም ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም የመጨረሻው ነቢይ ናቸውና (አል-አሕዛብ 33፡40)፡፡

መ/ ቅዱስ ቁርአን ስለ ተውራትና ኢንጂል የሰጠውን ምሥክርነት ለመጽሐፍ ቅዱስ መገልገል የሚፈልጉ ወገኖችን አንድ ጥያቄ እንጠይቃቸው፡፡ እሱም፡- ቁርአን ተውራትንና ኢንጂልን ከአላህ ዘንድ የወረዱ መለኮታዊ መጽሐፍ መኾናቸውን ማረጋገጡ፡ ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኝነት የተሰጠ ምሥክር አድርጋችሁ ከወሰዳችሁት፡ ይኸው ቁርአን ተውራትና ኢንጂል ስለ ነቢዩ ሙሐመድ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ወደፊት ነቢይ ኾኖ መነሳት ትንቢትን በውስጣቸው እንዳቀፉ ይነግረናል (ሱረቱል አዕራፍ 7፡157)፡፡ ተውራትና ኢንጂል ማለት ደግሞ፡ ዛሬ በናንተ እጅ የሚገኘው መጽሐፍ ማለት ከኾነ፡ እንግዲያውስ ከመጽሐፋችሁ ውስጥ ስለ ነቢዩ ሙሐመድ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የተነገረውን ትንቢት አውጥታችሁ ልታሳዩን ትችላላችሁን? በማለት እንጠይቃችኋለን፡፡ የናንተም መልስ፡- በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የሳቸው ነቢይነት አልተጠቀሰም! የሚል ከኾነ፡ እንግዲያውስ ቁርአን የመሰከረለት ተውራትና ኢንጂል፡ ዛሬ ተበርዞና ተከልሶ በእጃችሁ የሚገኘው መጽሐፍ ሳይኾን፡ ገና በመጀመሪያ ይዘቱ፡ ከአላህ ዘንድ ፍጹም እውነት ኾኖ ሲወርድ የነበረውን ማንነቱን ነው ማለት ነው በማለት የመጽሐፉን መበረዝ ማስረዳት ይቻላል፡፡

“በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማኢልና ወደ ኢስሀቅም ወደ ያእቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ኢሳ በተሰጡት በዘያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል #የማንለይ_ስንሆን_አመንን እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ፡፡” (ሱረቱል-በቀራህ 2፡136)፡፡

“መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምስራቅና ምእራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን በመላእክትም በመጽሐፍትም በነቢያትም ያመነ ሰው ገንዘቡንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች ለምስኪኖችም ለመንገደኞችም ለለማኞችም … የሰጠ ነው…” (ሱረቱል-በቀራህ 2፡177)፡፡

“መልክተኛው ከጌታው ወደርሱ በተወረደው አመነ ምእምኖቹም (እንደዚሁ) ሁሉም በአላህ በመላእክቱም በመጽሐፍቱም በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ #በአንድም_መካከል_አንለይም (የሚሉ ሲሆኑ) አመኑ ሰማን፣ ታዘዝንም፣ ጌታችን ሆይ! ምህረትህን (እንሻለን) መመለሻም ወደ አንተ ብቻ ነው አሉም፡፡” (ሱረቱል-በቀራህ 2፡285)፡፡

“በአላህ አመንን በኛ ላይ በተወረደውም (በቁርአን) በኢብራሂምና በኢስማኤልም በኢስሀቅም በያእቁብም በነገዶችም ላይ በተወረደው ለሙሳና ለኢሳም ለነቢያትም ሁሉ ከጌታቸው በተሰጠው (አመንን) #ከነርሱ_መካከል_አንድንም_አንለይም እኛ ለርሱ ታዛዦች ነን በል፡፡” (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡84፡፡

15.የነቢያት ማንነትና አስተምህሮአቸው

ክፍል አንድ

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2)። የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)።

መግቢያ፦

በነቢያትና ሩሱሎች ማመን ከስድስቱ የኢማን ማእዘናት (አርካኑል ኢማን) መካከል እራሱን የቻለ አንድ ማእዘን ነው። ማንኛውም ሰው የነቢያትንና የሩሱሎችን ነቢይነት አምኖ ካልተቀበለ ትክክለኛ አማኝ ሊባል አይችልም። የሚመደበውም ከከሀዲዎች ጎራ ነው። ምክንያቱም፦

- ነቢያትን የነቢይነት ማእረግ ሰጥቶ ወደ ሕዝባቸው የሚልካቸው ፈጣሪ አምላክ የሆነው አላህ በመሆኑ፡ እነሱን አለመቀበልና በነሱ አለማመን፡ የላካቸውን አላህ አለማክበርና በሱም አምላክነት አለማመን ማለት ነውና። መልክተኞችን የሚንቅና የማያከብር ሰው፡ ለላኪው ጥሩ ግምትና መልካም አስተሳሰብ የሌለው ብቻ ነው። አላህን አክብሮ አለመገኘት ደግሞ ትልቅ ክህደት ነው።

- ነቢያት ሰዎችን ከጌታ አላህ ጋር የሚያስተዋውቁ፡ እሱ ያዘዘውንና የከለከለውን ነገር ያላንዳች ጭማሬና ቅነሳ በአግባቡ በማድረስ፡ በቃል በማብራራትና በተግባርም ሰርቶ በማሳየት መልካም አርአያ በመሆን፡ በአላህና በባሪያው መሀል ያሉ አገናኝ ድልድይ ናቸው። ትክክለኛ እምነትና ክህደት የሚታወቀውም በነዚሁ ነቢያት ባስተማሩት የእምነትና የህግ ሚዛን በመሆኑ፡ የነቢያትን መልክት አለመቀል ግለሰቡን ከአማኞች ጎራ አውጥቶ ወደ ከሀዲያን ቡድን ይጨምረዋል ማለት ነው። ይህ በመሆኑም ስለነቢያት ማንነትና አስተምህሮ የተወሰኑ መሰረታዊ ነገራትን መማር ይገባናል ማለት ነው።

የታሪኩ ባለቤት፦

ስለ ነቢያት ማንነት መማርና መናገር ስንጀምር፡ እንዲህ የሚል አንድ ፍትሐዊ ጥያቄ ሊቀርብልን ይችላል፦ በነቢያት ዘመን በህይወት ነበራችሁን? ካልነበራችሁስ የነቢያትን ታሪክ የምትናገሩት ከምን ምንጭ ተነስታችሁ ነው? የሚል። የኛ ምላሽም፦ ስለ ነቢያት በልበ-ሙሉነት የምንናገረው ዓለማትን ከመፍጠሩ በፊት የነበረውና የነቢያት አምላክ የሆነው ሕያው አምላክ አላህ በመለኮታዊ ቃሉ "ቅዱስ ቁርአን" እና በነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) አንደበት በ"ሐዲሥ" ላይ ስለነገረን ነው። ከጌታ አላህ ይልቅ እውነት ተናጋሪ ፈጽሞ የለም ሊኖርም አይችልም። ከነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) በኋላም እውነትን ነጋሪና መካሪም አይታሰብም። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል-

" حَدِيثًا اللَّهِ مِنَ أَصْدَقُ وَمَنْ فِيهِ رَيْبَ لَا الْقِيَامَةِ يَوْمِ إِلَى لَيَجْمَعَنَّكُمْ هُوَ إِلَّا إِلَهَ لَا اللَّهُ " النساء سورة 87

"አላህ ከርሱ በስተቀር አምላክ የለም፤ ወደ ትንሣኤ ቀን በርሱ ጥርጥር የሌለበት ሲሆን፣ በእርግጥ ይሰበስባችኋል። *በንግግርም ከአላህ ይበልጥ እውነተኛ ማነው?*" (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡87)።

" قِيلًا اللَّهِ مِنَ أَصْدَقُ وَمَنْ حَقًّا اللَّهِ وَعْدَ أَبَدًا فِيهَا خَالِدِينَ الْأَنْهَارُ تَحْتِهَا مِنْ تَجْرِي جَنَّاتٍ سَنُدْخِلُهُمْ الصَّالِحَاتِ وَعَمِلُوا آمَنُوا وَالَّذِينَ " النساء سورة 122

"እነዚያም ያመኑና በጎ ስራዎችን የሠሩ፣ በስራቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች ዘላለም በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲሆኑ እናገባዋቸዋለን፤ አላህ እውነተኛን ተስፋ ሰጣቸው። *በንገገርም ከአላህ ይበልጥ እውነተኛ ማን ነው?*" (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡122)።

ይህ በመሆኑም፡ የአላህ ቃል የሆነው ቅዱስ ቁርአን ስለ ነቢያት መሰረታዊ ነገራትን በመተረክ ቁም-ነገር ያስጨበጠናል ማለት ነው።

" الْغَافِلِينَ لَمِنَ قَبْلِهِ مِنْ كُنْتَ وَإِنْ الْقُرْآنَ هَذَا إِلَيْكَ أَوْحَيْنَا بِمَا الْقَصَصِ أَحْسَنَ عَلَيْكَ نَقُصُّ نَحْنُ " يوسف سورة 3

“እኛ ይህንን ቁርአን ወደ አንተ በማውረዳችን በጣም መልካም ዜናዎችን በአንተ ላይ እንተርክልሀለን እነሆ ከርሱ በፊት (ካለፉት ህዝቦች ታሪክ) በእርግጥ ከዘንጊዎቹ ነበርክ” (ሱረቱ ዩሱፍ 12፡3)።

" يُؤْمِنُونَ لِقَوْمٍ بِالْحَقِّ وَفِرْعَوْنَ مُوسَى نَبَإِ مِنْ عَلَيْكَ نَتْلُو * الْمُبِينِ الْكِتَابِ آيَاتُ تِلْكَ * طسم " القصص سورة 3-1

“ጣ.ሲ.ን ሚም ይህች ገላጭ ከሆነው መጽሐፍ አንቀጽ ናት ከሙሳና ከፈርአን ዜና እውነተኞች ስንሆን ለሚያምኑ ህዝቦች ባንተ ላይ እናነባለን” (ሱረቱል-ቀሶስ 28፡1-3)።

" ذِكْرًا لَدُنَّا مِنْ آتَيْنَاكَ وَقَدْ سَبَقَ قَدْ مَا أَنْبَاءِ مِنْ عَلَيْكَ نَقُصُّ كَذَلِكَ " طه سورة 99

“እንደዚሁ በእርግጥ ካለፉት ወሬዎች በአንተ ላይ እንተርካለን ከኛም ዘንድ ቁርአንን በእርግጥ ሰጠንህ” (ሱረቱ ጣሀ 20፡99)።

ነቢይነት የአላህ መለኮታዊ ምርጫ እንጂ የሥራ ውጤት አይደለም፡-

ሌላው ልናውቅ የሚገባን ነገር፡ ነቢይነት በዘር፣ በቋንቋ፣ በጉልበትና በሕዝብ ምርጫ የሚከናወን አይደለም። ነቢይነት የአላህ ፈቃድ ብቻ የታከለበት አምላካዊ ምርጫ ነው። ሕዝቦች ባሕሪውን ስለወደዱለት ነቢይ የሚሆን፡ ስለጠሉት ደግሞ ከምርጫው የሚቀር የለም። አላህ በራሱ መለኮታዊ ዕውቀትና ፍጹማዊ ጥበቡ የሚፈልገውን ለነቢይነት ይመርጣል። ያ የተመረጠው ነቢይ እንኳ፡ ‹ቆይ እስኪ ላስብበት› የሚል ዕድል የለውም። በአላህ መለኮታዊ አሰራር ውስጥ፡ ፍጥረታዊ ሀሳብ ድርሻ የለውምና። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" الْفَضْلِ ذُو وَاللَّهُ يَشَاءُ مَنْ بِرَحْمَتِهِ يَخْتَصُّ وَاللَّهُ رَبِّكُمْ مِنْ خَيْرٍ مِنْ عَلَيْكُمْ يُنَزَّلَ أَنْ الْمُشْرِكِينَ وَلَا الْكِتَابِ أَهْلِ مِنْ كَفَرُوا الَّذِينَ يَوَدُّ مَا الْعَظِيمِ " البقرة سورة 105

“እነዚያ ከመጽሐፍ ባለቤቶችና ከአጋሪዎቹም የካዱት በናንተ ላይ ከጌታችሁ የሆነ መልካም ነገር መወረዱን አይወዱም አላህም በችሮታው (በነቢይነት) *የሚሻውን ይመርጣል* አላህም የተላቀ ችሮታ ባለቤት ነው” (ሱረቱል-በቀራህ 2፡105)።

" الْعَظِيمِ الْفَضْلِ ذُو وَاللَّهُ يَشَاءُ مَنْ بِرَحْمَتِهِ يَخْتَصُّ " عمران آل سورة 74

“በችሮታው (በነቢይነት) *የሚሻውን ይመርጣል* አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው” (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡74)።

" بَصِيرٌ سَمِيعٌ اللَّهَ إِنَّ النَّاسِ وَمِنَ رُسُلًا الْمَلَائِكَةِ مِنَ يَصْطَفِي اللَّهُ " الحج سورة 75

“አላህ ከመላእክት ውስጥ መለክተኞችን ይመርጣል ከሰዎችም (እንደዚሁ) አላህ ሰሚ ተመልካች ነው” (ሱረቱል-ሐጅ 22፡75)።

ክፍል ሁለት

“ነቢይ” እና “ረሱል” ቋንቋዊና ሃይማኖታዊ ፍቺው

ነቢይ የሚለው ቃል “ነበአ” ከሚለው የዐረብኛ ስርወ ግንድ የመጣ ቃል ነው። የቃሉም ፍቺ፡- ጥቅም ያለውን ወሬ ማውራት የሚል ትርጉም አለው። ለምሳሌ ጌታ አላህ እንዲህ ይላል፡-

" الْعَظِيمِ الْنَّبَإِ عَنِ * يَتَسَاءَلُونَ عَمَّ " النبأ سورة 2-1

“ከምን ነገር ይጠያየቃሉ? ከታላቁ ዜና (ከቁርአን) ይጠያየቃሉ” (ሱረቱ-ነበእ 78፡1-2)።

እዚህ ላይ “ዜና” ለሚለው የአማርኛ ትርጉም የዐረብኛው ቁርአን ያስቀመጠው ቃል “ነበእ” የሚለውን ነው። ከዚህ አንጻር ነቢይ ማለት ቋንቋዊ ትርጉሙ ከአላህ ዘንድ የሚመጣለትን ዜና (ትንቢት፣ ትእዛዝ) የሚያወራ የሚናገር ይሆናል ማለት ነው።

" الْخَبِيرُ الْعَلِيمُ نَبَّأَنِيَ قَالَ هَذَا وَإِذْ أَسَرَّ النَّبِيُّ إِلَى بَعْضِ أَزْوَاجِهِ حَدِيثًا فَلَمَّا نَبَّأَتْ بِهِ وَأَظْهَرَهُ اللَّهُ عَلَيْهِ عَرَّفَ بَعْضَهُ وَأَعْرَضَ عَنْ بَعْضٍ فَلَمَّا نَبَّأَهَا بِهِ قَالَتْ مَنْ أَنْبَأَكَ " التحريم سورة 3

"ነቢዩ ከሚስቶቹ ወደ አንዷ ወሬን በመሠጠረ ጊዜ (አስታውስ) እርሱንም በነገረችና አላህ እርሱን (ማውራትዋን) ባሳወቀው ጊዜ ከፊሉን አስታወቀ ከፊሉንም ተወ፤ በርሱም ባወራት ጊዜ ይህን ማን ነገረህ? አለች፤ ዐዋቂው ውስጠ አዋቂው ነገረኝ አላት፤" (ሱረቱ-ተሕሪም 66፡3)።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ‹‹ዐዋቂው ውስጠ አዋቂው ነገረኝ አላት›› ለሚለው ኃይለ-ቃል በዐረብኛ የተቀመጠው ‹‹ነበበኢ›› የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም ነቢይ ነቢይ የተሰኘው ከአላህ ዘንድ መልእክት የሚመጣለት በመሆኑ ነው፡፡

እንዲሁም ደግሞ ነቢይ የሚለው ቃል “ነበወህ” ከሚለውም የዐረብኛ ግስ የመጣ ነው ተብሏል፡፡ ይህ ማለት፡- ከፍ የተደረገ ስፍራ፣ ነገር እና ቦታ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ከዚህ አንጻር ነቢይ በዚህ የተሰየመው ከተቀሩት (ነቢይ ካልሆኑት) ሰዎች አላህ ዘንድ ያለው ስፍራና ክብሩ ከፍ ያለ ስለሆነ ነው፡፡ (ሱረቱ መርየም 19፡57)፡፡

ረሱል የሚለው ቃል ደግሞ ቋንቋዊ ትርጉሙ፡- መልእክትን አድራሽ ተላላኪ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ሩሱሎች (መልክተኞች) በዚህ ስያሜ የተጠሩት ከአላህ ዘንድ የተቀበሉትን መልእክት፡ መልእክቱ ላልደረሳቸው ህዝቦች እንዲያደርሱ ስለሚላኩ ነው፡፡ ይህ ቋንቋዊ ትርጉማቸው ነው፡፡ (አር-ሩሱሉ ወር-ሪሳላህ፡ ዶክተር ሱለይማን አል-አሽቀር)፡፡

ሃይማኖታዊ ትርጉማቸው ደግሞ፡- ነቢይ ማለት አላህ ምእምናኖችን የሚያዝበትንና ለራሱ የሚተገብርበትን ነገር የሚያወርድለት ሲሆን፡ ረሱል ደግሞ መልክቱ ወዳልደረሳቸው ከሓዲያን ህዝቦች እንዲያደርስ ከአላህ ዘንድ ወሕይ (ራእይ) የወረደለት ማለት ነው፡፡ ወሕዩ በአዲስ ሸሪዓህ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡

በመሐከላቸው ያለው ልዩነት፡-

ቅድሚያ ማወቅና መረዳት ያለብን ነገር ቢኖር፡ በነቢይና በረሱል መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅም ሆነ አለማወቅ በአንድ ሙስሊም እምነት ውስጥ ምንም የሚያመጣው ለውጥ አለመኖሩን ነው፡፡ ጉዳዩ ተጨማሪ ዕውቀት የማግኘትና ያለማግኘት ከመሆን በዘለለ መልኩ፡ እምነት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ የለውም፡፡ በአምልኮ ላይም የሚፈጥረው ክፍተት የለም፡፡ ምክንያቱም፡-

አንድ ሙስሊም፡- ነቢይነትም ሆነ ረሱልነት የአላህ መለኮታዊ ምርጫ እንጂ የሰዎች የስራ ውጤትና ልፋት አለመሆኑን ካመነ፣ ነቢያትም ሆኑ ሩሱሎች ከአላህ ዘንድ መለኮታዊ ራእይ (ወሕይ) የሚወረድላቸው እንጂ ፈላስፋ ወይም ልብ-ወለድ ተናጋሪ አለመሆናቸውን ከተቀበለ፣ ነቢያትም ሆኑ ሩሱሎች አላማቸው ሰዎችን ከአላህ ጋር በማስተዋወቅ ከጨለማ ወደ ብርሐን መንገድ ሰበብ ሁኖ በማውጣት የጀነትን መንገድ ማመላከት እንደሆነ ከተረዳ፣ ነቢያትም ሆኑ ሩሱሎች በዚህ ተልእኮአቸው የጌታቸውን ውዴታና እሱ ዘንድ ያለውን አምላካዊ ስጦታ እንጂ፡ ምድራዊ ደሞዝና ስልጣን ፈላጊዎች አለመሆናቸውን በአግባቡ ከተገነዘበ፣ ነቢያትም ሆኑ ሩሱሎች ከሰዎች መካከል የተመረጡ ሰዎች እንጂ፡ ከመልአክ ወይም ከጂንኒ ወገን እንዳልሆኑ ካስተዋለ ለአማኝነቱ ይህ በቂው ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በነቢይ እና ረሱል መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ ደፋ ቀና ማለቱ ወይም አለማለቱ ተጨማሪ ዕውቀት ከማግኘት ወይም ከማጣት ውጪ በእምነቱ ላይ የሚያደርሰው ምንም ጉድለት የለውም፡፡

የአላህ ቃል የሆነው ቅዱስ ቁርአን እንዲሁም የነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ንግገር የሆነው ሐዲሥ፡ በነቢይ እና በረሱል መካከል ልዩነት መኖሩን የሚጠቁሙ የቃላት አገላለጾችን በውስጣቸው ይያዙ እንጂ፡ ልዩነቱ ይህ ነው የሚል ቀጥሏይ (ፍጹማዊ) የሆነ ማስረጃን አናገኝም፡፡ የኢስላም ሊቃውንትም በጉዳዩ ላይ የተለያየ እይታ ነው ያላቸው፡፡ ከፊሎቹም ከዚህ በመነሳት፡- በነቢይ እና በረሱል መካከል ምንም ልዩነት የለም፡፡ ማንኛውም ነቢይ ረሱል ነው፡ ማንኛውም ረሱል ነቢይ ነው! የሚል ድምዳሜ ሰጥተዋል፡፡

ክፍል ሶስት

በ “ነቢይ” እና “ረሱል” መካከል ያለው ልዩነት፡-

የተወሰኑ ወንድምና እህቶች ባቀረቡት ሀሳብ መሰረት፡ የኢስላም ሊቃውንት (ዑለማእ) ዘንድ በ ነቢይ እና በ ረሱል መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት እንደሚያስቀምጡት በመጠኑ ለማቅረብ እሞክራለሁ ኢንሻአላህ፡፡

ባለፈው በክፍል ሁለት ያነሳሁትን ሀሳብ ዛሬም እደግመዋለሁ፡፡ በነቢይና በረሱል መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅም ሆነ አለማወቅ በአንድ ሙስሊም እምነት ውስጥ ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ ጉዳዩ ተጨማሪ ዕውቀት የማግኘትና ያለማግኘት ከመሆን በዘለለ መልኩ፡ እምነት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ የለውም፡፡ በአምልኮ ላይም የሚፈጥረው ክፍተት የለም፡፡ ምክንያቱም፡-

አንድ ሙስሊም፡- ነቢይነትም ሆነ ረሱልነት የአላህ መለኮታዊ ምርጫ እንጂ የሰዎች የስራ ውጤትና ልፋት አለመሆኑን ካመነ፣ ነቢያትም ሆኑ ሩሱሎች ከአላህ ዘንድ መለኮታዊ ራእይ (ወሕይ) የሚወረድላቸው እንጂ ፈላስፋ ወይም ልብ-ወለድ ተናጋሪ አለመሆናቸውን ከተቀበለ፣ ነቢያትም ሆኑ ሩሱሎች አላማቸው ሰዎችን ከአላህ ጋር በማስተዋወቅ ከጨለማ ወደ ብርሐን መንገድ ሰበብ ሁኖ በማውጣት የጀነትን መንገድ ማመላከት እንደሆነ ከተረዳ፣ ነቢያትም ሆኑ ሩሱሎች በዚህ ተልእኮአቸው የጌታቸውን ውዴታና እሱ ዘንድ ያለውን አምላካዊ ስጦታ እንጂ፡ ምድራዊ ደሞዝና ስልጣን ፈላጊዎች አለመሆናቸውን በአግባቡ ከተገነዘበ፣ ነቢያትም ሆኑ ሩሱሎች ከሰዎች መካከል የተመረጡ ሰዎች እንጂ፡ ከመልአክ ወይም ከጂንኒ ወገን እንዳልሆኑ ካስተዋለ ለአማኝነቱ ይህ በቂው ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በነቢይ እና ረሱል መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ ደፋ ቀና ማለቱ ወይም አለማለቱ ተጨማሪ ዕውቀት ከማግኘት ወይም ከማጣት ውጪ በእምነቱ ላይ የሚያደርሰው ምንም ጉድለት የለውም፡፡

የአላህ ቃል የሆነው ቅዱስ ቁርአን እንዲሁም የነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ንግገር የሆነው ሐዲሥ፡ በነቢይ እና በረሱል መካከል ልዩነት መኖሩን የሚጠቁሙ የቃላት አገላለጾችን በውስጣቸው ይያዙ እንጂ፡ ልዩነቱ ይህ ነው የሚል ቀጥዒይ (ፍጹማዊ) የሆነ ማስረጃን አናገኝባቸውም፡፡ የኢስላም ሊቃውንትም በጉዳዩ ላይ የተለያየ እይታ ነው ያላቸው፡፡ ከፊሎቹም ከዚህ በመነሳት፡- በነቢይ እና በረሱል መካከል ምንም ልዩነት የለም፡፡ ማንኛውም ነቢይ ረሱል ነው፡ ማንኛውም ረሱል ነቢይ ነው! የሚል ድምዳሜ ሰጥተዋል፡፡ አብዝኃኞቹ ሊቃውንት ግን ልዩነት እንዳለ አበክረው ገልጸዋል፡፡ ልዩነቱ ምንድነው? በሚለው ላይ ግን የጋራ አቋም የላቸውም፡፡ እናንተ እነዚህ ሊቃውንት ያቀረቡትን በነቢይ እና በረሱል መካከል ያለውን የመለያ ሀሳብ ማወቁ ይጠቅመናል ካላችሁ ቀጥሎ ያለውን በጥሞና ያንብቡ፡፡ መልካም ንባብ፡፡

ሀ/ መልእክትን ከማድረስ አንጻር፡-

ከአላህ ዘንድ መልእክት የሚመጣለት ሆኖ፡ መልእክቱን ራሱ እንዲተገብረው እንጂ ለሌሎች እንዲያደርስ የማይታዘዝ ከሆነ ነቢይ ይባላል፡፡ ይህንኑ የመጣለትን መልእክት ለሌሎች እንዲያደርስ ከታዘዘ ግን ረሱል ተብሎ ይጠራል የሚል ነው፡፡ (ሸርሑል ዐቂደቲ-ጠሓዊየህ 158)፡፡

ከዚህ ሀሳብ በመነሳት፡- ማንኛውም ረሱል ነቢይ መሆን ሲችል፡ ነቢይ ግን ረሱል አይሆንም የሚለውን ሀሳብ መያዝ ይቻላል ማለት ነው፡፡ ለዛ ነቢይ የመጣለት ነገር ረሱሉም መጥቶለታልና፡፡

ለ/ ከወሕይ (ራእይ) አመጣጥ አንጻር፡-

ከአላህ ዘንድ የሚመጣው መለኮታዊ ራእይ (ወሕይ) በመልአክ በኩል ከሆነ፡ ይህ ወሕይ የመጣለት አካል ረሱል ተብሎ ሲጠራ፡ ወሕዩ የመጣለት (የተገለጠለት) ግን በመልአክ በኩል ሳይሆን በህልሙ ወይንም በንቃተ-ህሊናው ሳለ በልቦናው በማስቀመጥ ከሆነ ግን ነቢይ ተብሎ ይጠራል የሚል ነው፡፡ (ተፍሲር አል-ኢማሙል ቁርጡቢይ፡ አል-ጃሚዑ ሊአሕካሚል ቁርኣን 12/75)፡፡

ሐ/ ከመጽሐፍ መውረድ አንጻር፡-

ለነቢይነቱ ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ ከሚሰጠው ተአምራት በተጨማሪ፡ ከአላህ ዘንድ መለኮታዊ መጽሐፍ የሚወርድለት ከሆነ ረሱል ተብሎ ይጠራል፡፡ መለኮታዊ መጽሐፍ ሳይወርድለት ከሱ በፊት የቀደመውን የረሱሉን መንገድ በማደስ ወደሱ ጥሪ የሚያደርግ ከሆነ ደግሞ ነቢይ ይባላል የሚል ነው፡፡ (አል-ኢማሙ ነሰፊይ፡ መዳሪኩ-ተንዚል 3/108)፡፡

መ/ አዲስ ሸሪዓህ ይዞ ከመምጣት አንጻር፡-

ከአላህ ዘንድ አዲስ ሸሪዓህ (ህግጋት) የሚመጣለት ከሆነ ረሱል ተብሎ ይጠራል፡፡ አዲስ ሸሪዓህ የማይመጣለት ሆኖ የቀደመውን ረሱል ሸሪዓህ የሚከተልና አማኞቹንም የሚያስተምር ከሆነ ነቢይ ይሆናል ነው፡፡ (ዶክተር. ዑመር ሱለይማን አል-አሸቀር፡ አር-ሩሱሉ ወር-ሪሳላት 15)፡፡

ከላይ የምናነባቸው ሀሳቦች የሃይማኖቱ ሊቃውንት እይታና ድምዳሜ ነው፡፡ ፍጹማዊ እንከን አልባነት የአላህና የመልክተኛው ቃል ብቻ በመሆኑ፡ የእነዚህ ሊቃውንት ሀሳብም፡ በሌሎች ሊቃውንት ዘንድ ትችት ገጥሞታል፡፡ ይህ ማለት በሩ አሁንም ለምርምር ክፍት ነው ማለት ነው፡፡

• ነቢይ ለራሱ እንጂ ለሌሎች እንዲያደርስ አልተላከም የሚለውን ሀሳብ፡ አላህ ረሱልን ብቻ ሳይሆን ነቢይንም እንደላከ የሚያሳዩ ማስረጃዎችን በመጥቀስ ሊቃንት (ዑለማእ) ሀሳቡን ውድቅ አድርገዋል፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" عَلِيمٌ وَاللَّهُ آيَاتِهِ اللَّهُ يُحْكِمُ ثُمَّ الشَّيْطَانُ يُلْقِي مَا اللَّهُ فَيَنْسَخُ أُمْنِيَّتِهِ فِي الشَّيْطَانُ أَلْقَى تَمَنَّى إِذَا إِلَّا نَبِيٍّ وَلَا رَسُولٍ مِنْ قَبْلِكَ مِنْ أَرْسَلْنَا وَمَا حَكِيمٌ " الحج سورة 52

"ከመልክተኛና ከነቢይም ከአንተ በፊት አንድንም አልላክንም፣ ባነበበ (ና ዝም ባለ) ጊዜ፣ ሰይጣን በንባቡ ላይ (ማጥመሚያን ቃል) የሚጥል ቢሆን እንጂ፤ ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል፤ ከዚያም አላህ አንቀጾቹን ያጠነክራል አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው።" (ሱረቱል ሐጅ 22፡52)፡፡

በዚህ አንቀጽ ውስጥ፡- ከአላህ ዘንድ የሚላክ ማንኛውም ነቢይም ሆነ ረሱል፡ ከአላህ የወረደለትን መለኮታዊ ቃል አንብቦ በጨረሰ ጊዜ ሰይጣን የማጥመሚያ ቃልን በንባቡ ላይ ለመጨመር እንደሚሞክርና፡ ሙከራው ሳይሳካለት አላህ ድርጊቱን ወዲያው በማክሸፍ የሱን ቃላቶች እንደሚያጠናክር ሲነግረን፡ እግረ-መንገዱም ነቢይም የሚላክ መሆኑን እንረዳለን ማለት ነው፡፡

በተጨማሪም፡- ነቢይ የወረደለትን ራእይ (ወሕይ) ለሰዎች አለማድረስ፡ የአላህን መልክት መደበቅ ይባላል፡፡ አላህ ደግሞ የሱ መልክት እንዲደበቅና በአንድ ነቢይ ልብ ውስጥ የተቀበረ ሆኖ እንዲቀርና ከዛው ነቢይ መሞት ጋር አብሮ እንዲሞት አላወረደም፡፡ (አር-ሩሱሉ ወር-ሪሳላት 14-15)፡፡

• መልአክ የሚመጣው ለረሱል ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ነቢይ ብቻ ከሆነ ግን በህልም ወይም በኢልሃም (በንቃተ ህሊናው እያለ በልቦናው ማስቀመጥ፣ ማሳወቅ) ነው የሚመጣለት የሚለውም ትችት ገጥሞታል፡፡ (ኢማም አል-ማወርዲይ፡ አዕላሙ-ኑቡዋህ 33)፡፡

ጉዳዩ በራሱ ማስረጃ የሌለው ከመሆኑ ጋር፡ በተጨማሪም በአንድ ሐዲሥ ላይ እንደተዘገበው፡- አይሁዶች ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ዘንድ በመምጣት፡- ‹‹ማንኛውም ነቢይ ከመልአክ በኩል ወዳጅና ረዳት ይኖረዋል፡፡ ያንተ ወዳጅህና ረዳትህ ማነው?›› ብለው በጠየቋቸው ጊዜ፡ የነቢዩም ምላሽ፡- ‹‹መልአኩ ጂብሪል ነው!›› የሚል ነበር፡፡ እነሱም፡- ‹‹ይህ በቅጣትና በጦርነት ጊዜ የሚወርደው መልአክ ነው እንዴ! እሱማ ዋና ጠላታችን ነው፡፡ በዝናብና በእጽዋት ላይ ኃላፊነት የተሰጠው መልአኩ ሚካኢል ቢሆን ኖሮ በተከተልንህ ነበር›› አሉ፡፡ ጌታ አላህም ‹‹ለጂብሪል (ለጉብርኤል) ጠላት የኾነ ሰው (በቁጭት ይሙት) በላቸው፡፡ እርሱ (ቁርኣኑን) ከበፊቱ ለነበሩት (መጻሕፍት) አረጋጋጭ ለምእመናን መሪና ብስራት ሲኾን በአላህ ፈቃድ በልብህ ላይ አውርዶታልና፡፡›› (አል-በቀራህ 2፡97)፡፡ የሚለውን መለኮታዊ ቃሉን በሳቸው ላይ አወረደው፡፡ (ሙስነድ ኢማሙ አሕመድ 2483)፡፡

በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ነቢያት በጠቅላላ ከመልአክ በኩል ወዳጅ እንደሚኖራቸው የሚያሳይ ሀሳብ አልለ፡፡ በወቅቱ አይሁዶች የተናገሩት ስህተት ቢሆን ኖሮ፡ የአላህ መልክተኛም ከምላሻቸው በፊት የነሱን የተሳሳተ አመለካከት ባስተካከሉ ነበር፡፡

• አዲስ ሸሪዓህ ይዞ የሚመጣ ከሆነ ረሱል ይሰኛል፡፤ የቀደመውን ሸሪዓህ ይዞ የሚከተል ከሆነ ግን ነቢይ ብቻ ይሆናል የሚለውም ብዙ የሚያስኬድ አይደለም፡፡ ነቢዩላህ ዳዉድና ልጁ ሱለይማን (ዐለይሂማ-ሰላም) ረሱል እንደነበሩ የታወቀ ነው፡፡ ሆኖም ሁለቱም ይከተሉና ይመሩበት የነበረው የሙሳን (ዐለይሂ-ሰላም) ሸሪዓህ፡ የተውራትን ህግ ነበር እንጂ አዲስ ሸሪዓህ አልመጣላቸውም፡፡ (ኢብኑ ተይሚይያህ፡ አን-ኑቡዋት 184)፡፡

የተሻለው አማራጭ፡-

በነቢይና በረሱል መካከል ያለው ልዩነት፡- ረሱል የሚላከው መልክቱን ለተቀበሉት አማኞችም ላልተቀበሉት ከሀዲያንም ጭምር ነው፡፡ መልእክቱ በአዲስ ሸሪዓህ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ ነቢይ ግን የቀደመው ረሱል አስተላልፎት የሄደውን መልእክት፡ እርሱ ለአማኞች እንዲያደርስና እንዲያድሰው ይላካል እንጂ፡ ልክ እንደ ረሱሉ መልክቱን ላልደረሳቸውና ለሚቃወሙ ህዝቦች የማድረስ ግዳጅ የለበትም የሚለው ነው፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡ (ኢብኑ ተይሚይያህ፡ አን-ኑቡዋት 184)፡፡

ይህ ሀሳብ ከመጀመሪያዎቹ የሚለየው፡-

1/ ነቢይ ለራሱ እንጂ ለማንም አልተላከም የሚለውን በመቃወም፡ ለአማኞች ግን በቀደመው የረሱል መንገድና ሸሪዓህ መሰረት መላኩን ያጸድቃል፡፡

2/ ረሱል አዲስ ሸሪዓህ ይመጣለት ዘንድ ግድ ነው የሚለውን መስፈርት በመቃወም፡ አዲስ ሸሪዓህ ሊመጣለትም ወይንም የቀደመውን የረሱልን ሸሪዓህ ሊከተል ይችላል በማለት፡ ዳዉድንና ሱለይማንን በምሣሌነት ጠቅሶ በሩን ክፍት ያደርገዋል፡፡

3/ ለነቢይ መልአክ አይመጣም፡፡ መልአክ የሚገለጠው ለረሱል ብቻ ነው የሚለውን ማስረጃ የሌለውን ሀሳብም አይቀበልም፡፡

ማጠቃለያ ፦

ከሁሉም የሊቃውንት ሀሳብ የምንወስደው የጋራ ስምምነት፡- ረሱልነት (መልክተኝነት) ከነቢይነት የነላ እና ከፍ ያለ ደረጃ መሆኑን፣ እንዲሁም ማንኛውም ረሱል ነቢይነትንም እንደሚላበስ ነው፡፡ ስለዚህ ‹‹ፈኩልሉ ረሱሉን ነቢይ፡ ወለይሰ ኩልሉ ነቢይዩን ረሱል›› (ማንኛውም ረሱል ነቢይ ሲሆን፡ ነቢይ ሁሉ ግን ረሱል አይደለም) የሚለው ሀሳብ ትክክል ይሆናል ማለት ነው፡፡

በሂሳብ ህግ መሰረት፡- all equilateral triangles are also isosceles. But all isosceles triangles are not equilateral. የሚል መርሕ አለ፡፡ ሶስቱም ጎንኖቹ እኩል (60 ዲግሪ) የሆነው equilateral triangle ይባላል፡፡ ሁለቱ ጎንኖቹ ብቻ እኩል የሆኑት ደግሞ isosceles triangle ተብሎ ይጥራል፡፡ ሶስቱም ጎንቹ እኩል በሆነው equilateral triangle ውስጥ ሁለት ጎንኖቹ እኩል በመሆናቸው isosceles triangle የሚለውንም አብሮ ያቅፋል ማለት ነው፡፡ ባለ ሁለት እኩል ጎንኖቹ ግን በሶስተኛው እኩል አለመሆን ምክንያት equilateral triangle የተባለውን ሊያቅፍ አይችልም፡፡

በረሱልነት ውስጥ ነቢይነት በመኖሩ፡ ማንኛውም ረሱል የተባለ ሁሉ ነቢይም ተብሎ ይጠራል፡፡ በነቢይነቱ ብቻ የሚታወቀው ግን ረሱል ተብሎ በኢጥላቅ (በስድ) አይጠራም፡፡ ይህ የቀጥታ ስያሜ የአላህን መልእክት ወደ ከሀዲያን እንዲያደርስ ለተላከው ብቻ የሚሰጥ ነው ማለት ነው፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

" عَلِيمًا شَيْءٍ بِكُلِّ اللَّهُ وَكَانَ النَّبِيِّينَ وَخَاتَمَ اللَّهِ رَسُولَ وَلَكِنْ رِجَالِكُمْ مِنْ أَحَدٍ أَبَا مُحَمَّدٌ كَانَ مَا " الأحزاب سورة 40

"ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድንም ሰው አባት አይደለም፤ ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፤ አላህም በነገሩ ሁላ ዐዋቂ ነው።" (ሱረቱል አሕዛብ 33፡40)፡፡

" نَبِيًّا رَسُولًا وَكَانَ مُخْلَصًا كَانَ إِنَّهُ مُوسَى الْكِتَابِ فِي وَاذْكُرْ " مريم سورة 51

"በመጽሐፉ ዉስጥ ሙሳንም አዉሳ፤ እርሱ ምርጥ ነበርና መልክተኛ ነቢይም ነበር።" (ሱረቱ መርየም 19፡51)፡፡

" نَبِيًّا رَسُولًا وَكَانَ الْوَعْدِ صَادِقَ كَانَ إِنَّهُ إِسْمَاعِيلَ الْكِتَابِ فِي وَاذْكُرْ " مريم سورة 54

"በመጽሐፉ ኢስማዒልንም አዉሳ፤ እርሱ ቀጠሮን አክባሪ ነበረና፤ መልክተኛ ነቢይም ነበር።" (ሱረቱ መርየም 19፡54)፡፡

ሐቅን ከገጠምኩ ከአላህ ተውፊቅ ሲሆን፡ ስህተቱ ግን የነፍሲያዬና የሸይጧን ጉትጎታ ነው፡፡ አላህና መልክተኛው ከኔ ስህተት የጸዱ ናቸው፡፡

«የነብያት ደረጃዎች በመፅሀፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁርአን»

▶1 ሰካራም ነብይ ኖህ ኦሪትዘፍ 9:20_25

▶2 ዝሙተኛ እና ነብይ ነፍሰ ገዳይ ነብይ ሳምሶን (መፅሀፈ መሳፍንት 14_19:20)

▶3 ጣኦት አምላኪ ነብይያቶች ሰለሞንና አሮን (መፅሀፈነገስት 11:1_13) & አዘፅአት 32 2_24

▸4 ልጆቻቸውን ዝሙት የሰሩ ነብይቶች ዳዊትና ያእቆብ (ኦዘፍጥረት 38:15_24)

▸5:ነፍሰ ገዳይ ነብይቶች ሳምሶንና ዳዊት (መፅሀፈ መሳፍንት 14:19_20)

▸6 በራሱ ልጆች ላይ ዝሙት የፈፀመ ነብይ ሎጥ (ኦሪት ዘፍጥረት 19:30_38)

▸7 በልጁ ሚስት ላይ ዝሙት የፈፀመ ነብይ ይሁዳ (ኦዘፍጥረት 38:15_24)

▸8 በጎረቤት ሚስት ላይ ዝሙት የፈፀመ ነብይ ዳዊት (2ኛ መፅሀፈ ሳሙኤል 11:2_27)

▸9 በጉልበቱ ሌላ ሚስት የቀማ ነብይ ዳዊት (2ኛ መፅሀፈ ሳሙኤል 12 10_11)▸ http://wp.me/P3Aleh-2I

▸10 ዘፋኝና ስሜት ቀስቃሽ ግጥሞች ገጣሚ ነብየደ ሰለሞን (መሀልየ መሀልየ 7: 3_8) & መሀልየ 8:8_9

▸11 ወደ ዝሙት የሚያዝ ነብይ ይሁዳ (ኦሪት ዘፍጥረት 38:8)

▸12 ለጥሎሽ ሲል 200 ፍልስጤማውያን የገደለ ነብይ ዳዊት (መፅሀፈ ሳሙኤል 18:24_27)

▸14 እብድ ለመምሰል ላህጩን ያዝረከረከና የደነሰ ነብይ ዳዊት (2 መፅሀፈ ሳሙኤል6:5_21)

▸15 ሰባት መቶ ሚስቶች ና ሶስት መቶ እቁባቶች የነበሩት ነብይ ሰለሞን

▸16 የነብይ ልጅ የአባቱን እቁባት ጋር ዝሙት አረገ(ፈፀመ) (ኦሪዘፍጥረት 35;22)

ከላይ እንዳየቸሁት በፈጣሪ ዘንድ የተከበሩ ነብያቶች ማንም ተራ ሰው የማይሰራውን ወንጀል ነብያቶች ሰሩ ይላል በአገራችን እንኳን ከስንት አንድ ሲከሰት ስንሰማ የምንደነግጠው የቤተሰብ ዝሙት በጥቂቱ በአስራ አንድ ቦታ በመፅሀፍ ቅዱስ ተጠቅሱያል እውነት መፅሀፍ ቅዱስ የአምላክ ቃል ነው እሄን ቅዱስ መፅሀፍ ተብሎ እያነበበ ያደገ ወጣት እህቱን ወይም ቤተሰቡን ዝሙት ለመስራት ድፍረት ያጣል ብሎ መገመት ይከብዳል።አውሮፓውያኖች የቤተሰብ ዝሙት ባህል ያደረጉት የመፅሀፍ ቅዱስ ውጤት ይሆን?

በነብያቶች ላይ የተደረገው አስፀያፊ ውንጀላዎች ቅጥፈቶች እንዲህ በማለት አላህ ሱ:ወ በተከበረ ቃሉ እንዲህ በማለት ቅጥፈቶችንን ተከላክሎላቸዋል አላህ ሱ፣ወ ፍፁም ጥራት ይገባው"

83.ይህችም ማስረጃችን ናት፡፡ ለኢብራሂም በሕዝቦቹ ላይ (አስረጅ እንድትኾን) ሰጠናት፡፡ የምንሻውን ሰው በደረጃዎች ከፍ እናደርጋለን፡፡ ጌታህ ጥበበኛ ዐዋቂ ነውና፡፡

84.ለርሱም ኢስሐቅን (የልጅ ልጁን) ያዕቁብንም ሰጠነው፡፡ ሁሉንም መራን፡፡ ኑሕንም በፊት መራን፡፡ ከዘሮቹም ዳውድን፣ ሱለይማንንም፣ አዩብንም፣ ዩሱፍንም፣ ሙሳንም፣ ሃሩንንም (መራን)፡፡ እንደዚሁም በጎ ሰሪዎችን እንመነዳለን፡፡

85.ዘከሪያንም፣ የሕያንም፣ ዒሳንም፣ ኢልያስንም (መራን)፡፡ ሁሉም ከመልካሞቹ ናቸው፡፡

86.ኢስማዒልንም፣ አልየሰዕንም፣ ዩኑስንም፣ ሉጥንም (መራን)፡፡ ሁሉንም በዓለማት ላይ አበለጥናቸውም፡፡87.ከአባቶቻቸውም፣ ከዘሮቻቸውም፣ ከወንድሞቻቸውም (መራን)፡፡ መረጥናቸውም፤ ወደ ቀጥታውም መንገድ መራናቸው፡፡

ቁርአን ሱረቱ አል_አንአም 84_88

*** በኦሪት ዘፍጥረት 19:31-35) ውስጥ ሉጥን በተመለከተ አስጸያፊ መልእክቶች ሰፍረዋል፡፡ ሉጥ አስካሪ መጠጥ ጠጥተው መስከራቸው፣ ከዚያም ከሴት ልጃቸው ጋር መዘሞታቸው፣ እርሷም ማርገዟና ዝሪያቸው በርሷ በኩል መቀጠሉ ተጠቅሷል፡፡ እስኪ አስቡት! አላህ የሶዶምን ከተማ የገለበጠውና ሕዝቡን ያጠፋው የሶዶም ሕዝብ የኂህን ንጹህ ነብይ ቃል ባለመስማቱ፣ በርሳቸው እና በትምርታቸው በመሳለቁ ነበር፡፡ ወደ ንጽህና ያደረጉትን ጥሪ ባለመቀበሉ በጅምላ ቀጣው፡፡ የኢብራሂም የወንድም ልጅ የሆኑትን የሉጥን ንጽህና ለመመስከር ከጠፉ ከተሞች ቅሪቶች ውጭ ሌላ ምስክር ባይኖር እንኳ በቂ ምስክር አይደለምን? እንዲህ ዓይነት አስጸያፊ መልእክቶችን የያዘን መጽሐፍ መለኮታዊ ብለን ልንቀበለው እንችላለን?

*** ኦሪት ዘፍጥረት ምእራፍ 38 ላይ የየእቁብ ልጅ የሁዛ -ምን አልባትም ነብይ ሊሆን ይችላል- ከልጁ ሚስት ጋር ዝሙት መፈጸሙ ተጠቅሷል፡፡ የበኑ ኢስራኤል ነብያት ዝርያ ለምሳሌ (ዳውድና ሱለይማን) የተገኙት ከዚህ የዝሙት የዘር ግንድ መሆኑም ተጠቅሷል፡፡

ይህ ዘገባ ሐሰት መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ምንም ዓይነት መሠረት የሌለው ቅጥፈት ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንደሚሉት፡- ‹‹ከአደም አንስቶ የርሳቸው የዘር ግንድ በጋብቻ ላይ ብቻ የተመሰረተ እና የተገኘ ነው፡፡›› (ደላኢሉ ኑቡዋ በይሐቂ 1/173-175)

በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ነብያት የአንድ አባት ልጆች ናቸው፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) አያት ቅድመ አያት ውስጥ አንድም የዝሙት ልጅ ከሌለ ይህ ባህሪ በሌሎች ነብያትም ላይ የሚሰራ ነው፡፡ እርሳቸው የኢብራሂም የልጅ ልጅ አይደሉምን? የሁዛም እንደዚሁ የኢብራሂም የልጅ ልጅ ነው፡፡ በነብያት ቤት ውስጥ ዝሙት ሊከሰት አይችልም፡፡

*** በመጽሐፈ ነገስት ምእራፍ 11፣ ውስጥ ሱለይማን በእድሚያቸው መጨረሻ ላይ እንደካዱና ጣኦት ማምለክ እንደጀመሩ ይገልጻል፡፡ በዚህም ሆነ በመጭው ዓለም ታላቅ ደረጃ ለግሶ አላህ የመረጠው ነብይ ክህደት ይፍጽማል ተብሎ እንዴት ይታሰባል?
=ሱለይማን አላህን በጽኑ አምላኪና አመስጋኝ ነብይ እንደሆኑ በቁርአን ተጠቅሷል፡፡ ለነብይ ተገቢው ባህሪ ይህ አመስጋኝነት ነው፡

=ቁርአን ዒሳን፡- ‹‹አላህ ወደ መርየም ያኖረው መንፈሱና ቃሉ›› ሲል ይገልጻቸዋል፡፡ (አል ኒሣእ 171)

= ኢብራሂም የአላህ ምርጥ ወዳጅ፣(አልኒሣእ 125)

= ሙሳ አላህ ያናገራቸው፣ (አልኒሣእ 114) መሆናቸውንም ተናግሯል፡፡

= የዳውድን ቤተሰብም፡- ‹‹የዳውድ ቤተሰቦች ሆይ፣ አመስጋኞች ስትሆኑ ስሩ›› ሲል አናግሯቸዋል፡፡ (ሰበእ 13) አላህ ነብያቱን የሚገልጽባቸው ባህሪያት እነዚህ ናቸው፡፡http://wp.me/P3Aleh-2I

*** ብሉይ ኪዳን ስለ ነቢዩላህ ዳውድ ሲተርክ አርያ የተባለውን ሰው ሚስት እንደተመኙና ሆነ ብለው እርሱን በማስገደል ሚስቱን እንደቀሙት ይተርካል፡፡ ሳሙኤል 2ኛ 11፡2-4)

ይህ እኩይ ባህሪ ለነቢይ ቀርቶ ለተራ ሰው፣ በእውን ቀርቶ በሕልም እንኳ የሚያስጸይፍ ነው፡፡ አላህ ዳውድን በተመለከተ ‹‹ምን ያምር አገልጋይ፡፡ እርሱ ወደ አምላኩ ተመላሽ ነው፡፡›› ብሏል፡፡ (ሱረቱ ሷድ 30)

^* የነብያትን ስም እንዲህ የሚያጠፋና የሚያረክስ መጽሐፍ እንዴት ከአላህ የተገኘ ሊሆን ይችላል? ይህ ታሪክ ይከሰታል ብሎ ማሰብ የነብይነትን ደረጃ አለማወቅ ነው፡፡ ነቢ ዳውድ አላህን አዘውትረው የሚያመልኩና አልቃሽ ነብይ ነበሩ፡፡ ከርሳቸው ጋር የተቀመጡ ሁሉ የርሳቸው ለቅሶ ተጋብቶበት ያለቅሳል፡፡ ወደ አላህ በንስሐ መመለስን ያበዛሉ፡፡ ፊታቸውን ከአምላካቸው ለቅጽበት እንኳ አላዞሩም፡፡

የሕይወታቸው ዋነኛ መርህ ዑቡዲያ ነበር፡፡ አላህን ዘወትር ማምለክ፡፡(ሷድ 17) የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) የነቢይ ዳውድን ኢባዳ ሲያወድሱ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከአላህ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጁ ሶላት የዳውድ ሶላት ነው፡፡ ከላህ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጁ ጾም የዳውድ ጾም ነው፡፡ የሌሊቱን ግማሽ ይተኙና ሲሶውን ይቆማሉ፡፡ 1/6ኛውንም ይተኛሉ፡፡ 1 ቀን ይጾማሉ፣ አንድ ቀን ያፈጥራሉ፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

ነቢይ ዳውድ ንጉስ ነበሩ፡፡ የመንግስት ሃብት በአጠቃላይ በእርሳቸው እጅ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን ያን ሃብትና ንብረት ለግላቸው ለመጠቀም፣ ሌላው ቀርቶ በርሱ አንዲት ቁራሽ ምግብ እንኳን ለመግዛት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የሚቀልቡት የእጅ ሙያቸውን ተጠቅመው በሚያገኙት የግል ገቢ ነበር፡፡ አንዲት ቁራሽ እንኳ ያለ አግባብ ለመውሰድ ባልፈቀዱት፣ የሕይወት መርሃቸው እና ልዩ ባህሪያቸው አላህን ማገልገል በሆኑት በዚህ ነብይ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ያንን አጸያፊ ቅጥፈት ይደርትባቸዋል፡፡ እጅግ ብጹእ እና ንጹህ ከመሆናቸው አኳያ ይህ ቅጥፈት በተግባር ቀርቶ በሐሳብ እንኳ ለቅጽበት ሊታወሳቸው ፈጽሞ የሚችል አይደለም፡፡

**** በብሉይ ኪዳን (ዘፍጥረት 32፡22-28) ውስጥ አእምሮ ሊቀበለው የማይችል ሌላም አስገራሚ ነገር እናገኛለን፡፡ እርሱም እስራኤል (ያእቁብ) ከአምላክ ጋር ታግለው ማሸነፋቸው ነው፡፡ እናም የምእራቡ አለም ቁሳዊ ፍልስፍና ወሰንን ሁሉ ጥሶ አምላክን የሰው ቅርጽ በማስያዝ ከነብዩ ጋር እንዲታገል አድርጎታል፡፡ ሐምዛ ከመስለማቸው በፊት ለነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) የተናገሩት ተከታዩ ቃል ለነዚህ ወገኖች ጥሩ ምላሽ ይዟል፡-

‹‹የወንድሜ ልጅ ሙሐመድ ወይ፣ ሌሊት በበረሃ በምዘዋወር ጊዜ አላህ በግንብ ውስጥ ተወስኖ ከመቀመጥ በላይ መሆኑን እረዳለሁ፡ ፡››

ስለዚህም ክርስትያኖችና አይሁዶች የአምላክ ቃል ነው ብለው የሚያስቡት መጽሐፍ በዘመነ መሐይምነት ወደነበሩት ሐምዛ የሕሊና ደረጃ እንኳ ከፍ ሊል አልቻለም፡፡ ታዲያ በእንዲህ አይነት ብክለቶች የተሞላውን ይህን መጽሐፍ የአምላክ ቃል ነው ብሎ እንዴት ማሰብ ይቻላል?

ይህ መጽሐፍ ስለ ነቢያት የሚናገረው ሊታመን ይችላልን? በፍጹም አይታመንም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አላህንና ነቢያቱን አስመልክቶ በቅጥፈትና በጥመት የተሞላ ነው፡፡ ብሉይ ኪዳን የጥመት ምንጮች ናቸው፡፡

^ ቁርአን በነብያት ዙሪያ ለተደረቱ ቅጥፈቶች ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፡፡ ምክንያቱም ነብያትን ሙሉ በሙሉ እንድንከተል ያዘናልና፡፡ በቁርአን ትምህርት መሠረት ነብያት ስብእናቸው የተሟላ፣ የቅን ጎዳና መሪዎች፣ በሁሉም ጉዳዮች ሊከተሏቸው እና

ሊታዘዟቸው የሚገቡ ታላላቅ መምህራን ናቸው:: ሁሉም ነብያት የአላህን ውዴታ የሚያየንጸባርቁልን መስታወቶች ናቸው:: ከነዚህ መስታወቶች ላይ አንዲት እንኳ የአቧራ ቅንጣት አይገኝም:: የተከበረው ቁርአን ይህንን እውነታ እጅግ ውብና ግልጽ በሆነ መልኩ አስቀምጦታል::ቁርአን ውስጥ የተጠቀሱ የአንዳንድ ነብያትን ድርጊቶች በስህተት በመረዳት ነብያት ሐጢአት ሊፈጽሙ እንደሚችሉ የሚያስቡ ወገኖችን እናገኛለን:: የስህተታቸው ምንጭ መልእክቶችን በወጉ አለመረዳት ሲሆን ጥቂት ቢያስተነትኑ የአስተሳሰባቸውን ግድፈት መረዳትና እንደብዙሐን ዓሊሞች ለነብያት ተገቢውን ክብር መስጠት በቻሉ ነበር::

" سَبِيلاً وَسَاءَ فَاحِشَةً كَانَ إِنَّهُ الزِّنَى تَقْرَبُوا وَلاَ " (الإسراء:32)

☞"ዝሙትን አትቅረቡ ። እርሱ በርግጥ መጥፎ ስራ ነው ። መንገድነቱም ከፋ" አል ኢስራእ 32

☞#ዝሙተኛው #ዝሙተኛይቱን #ወይም #አጋሪይቱን #እንጂ #አያገባም:: #ዝሙተኛይቱንም #ዝሙተኛ #ወይም #አጋሪ #እንጂ #አያገባትም:: ይህም በምእምናን ላይ ተከልክሏል::(24:2)

ٱلْمُؤْمِنِينَ عَلَى ذَٰلِكَ وَحُرِّمَ ۚ مُشْرِكٌ أَوْ زَانٍ إِلَّا يَنكِحُهَآ لَا وَٱلزَّانِيَةُ مُشْرِكَةٌ أَوْ زَانِيَةً إِلَّا يَنكِحُ لَا ٱلزَّانِى An-Nur 24:26

كَرِيمٌ وَرِزْقٌ مَّغْفِرَةٌ لَهُم يَقُولُونَ ۖ مِمَّا مُبَرَّءُونَ أُوْلَٰٓئِكَ لِلطَّيِّبَٰتِ وَٱلطَّيِّبُونَ لِلطَّيِّبِينَ وَٱلطَّيِّبَٰتُ لِلْخَبِيثَٰتِ ۖ وَٱلْخَبِيثُونَ لِلْخَبِيثِينَ ٱلْخَبِيثَٰتُ

☞መጥፎዎቹ ሴቶች ለመጥፎዎች ወንዶች መጥፎዎቹ ወንዶችም ለመጥፎዎቹ ሴቶች የተገቡ ናቸው:: ጥሩዎቹ ሴቶችም ለጥሩዎቹ ወንዶች ጥሩዎቹ ወንዶችም ለጥሩዎቹ ሴቶች የሚገቡ ናቸው:: እነዚያ (መጥፎዎቹ) ከሚሉት ነገር ንጹሕ የተደረጉ ናቸው:: ለእነርሱ ምህረትና መልካም ሲሳይ አላቸው:: (ሱረቱል አል ኑር 26)

16.ነብዩ ሙሃመድ(ሶ.ዐ.ወ)

wincdaaw-ኢትዮ ኢስላማዊ ዳዕዋ

ነቢዩ ሙሐመድ(ሰዐወ) በመፅሀፍ ቅዱስ

*** ከወንድሞቻቸው መካከል እንዳንተ ያለ ነብይ አስነሳላቸዋለሁ ***

ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መለስ ስንል ስለ ነብዩ መምጣት ትንቢት መነገሩን ቁርዓን ባመላከትን መሰረት ማረጋገጥ እንችላለን፡-

መጽሐፍ ቅዱስ :- «ከወንድሞቻቸው መካከል እንዳንተ ያለ ነብይ አስነሳላቸዋለሁ፤ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜ የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ...» ኦሪት ዘዳግም 18፡18-22

ክርስቲያኖች ይህ ትንቢት የተነገረው ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚል እምነት አላቸው፤ መቼም በጥቅሱ ውስጥ ኢየሱስ /ዐ.ሰ/ ወደፊት ይመጣል ወይም ነብዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ይመጣሉ የሚል የትንቢት ቃል የለም፡፡ ነገር ግን ስለዚህ ነብይ አነሳስና ባህሪ በትንቢቱ ቃል ውስጥ ስለተጠቀሰ እነዚህን ነገሮች እንደ መስፈርት ተመልክተን ያንን መስፈርት ሊያሟላ የሚችለውን መለየት የኛ ፋንታ ይሆናል፡፡ በትንቢቱ ውስጥ የተነገሩት መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. «ከወንድሞቻቸው መካከል»፡- ያ የሚነሳው ነብይ ከሙሴ ወንድሞች መካከል መሆን አለበት፡፡

ለ. «እንደ አንተ ያለ ነብይ»፡- እንደ ሙሴ ያለ ነብይ ማነው?

ሐ. «አስነሳላቸዋለሁ»፡- ያ የሚመጣው ነብይ ወደፊት የሚመጣ ነብይ መሆን አለበት፡፡

መ. «ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ»፡- ያ የሚነሳው ነብይ የአምላክ ቃል በአንደበቱ እየተደረገለት የሚናገር መሆን አለበት፡፡

ሠ. «ያዘዝሁትን ቃል ሁሉ ይነግራችኋል»፡- የታዘዘውን ቃል ሙሉ በሙሉ አንድ ሳያስቀር ማስተላለፍ አለበት፡፡

ረ. «በስሜም የሚናገረውን»፡- ያ የሚነሳው ነብይ ንግግሩ ሁሉ በአምላክ ስም የተጀመረ መሆን አለበት፡፡

ሀ. «ከወንድሞቻቸው መካከል» ይህ ትንቢት ሲነገር አስራ ሁለቱም የእስራኤል ነገዶች ከሙሳ /ሙሴ/ ጋር ነበሩ፡፡ ይህ ይነሳል የተባለው ነብይ ከእነሱ መካከል የሚነሳ ቢሆን ኖሮ የትንቢቱ ቃል «ከእናንተ መካከል» ማለቱ በተገባው ነበር፡፡ ትንቢቱ ግን «ከወንድሞቻቸው መካከል» በማለት የሚነሳው ነብይ ከእስራኤላውያን ወንድሞች መሆኑን ገልጿል፡፡ አሁን የሚነሳው ጥያቄ እነዚህ የእስራኤላውያን ነገድ ወንድሞች የተባሉት እነማን ናቸው? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

መ.ቅ፡- «የእግዚአብሔር መልዓክም አላት “እነሆ አንቺ ጸንሰሻል ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም እስማኤል ብለሽ ትጠሪዋለሽ፤ እግዚአብሔር መቸገርሽን ሰምቷልና፡፡ እርሱም የበዳን አህያን የሚመስል ሰው ይሆናል፤ እጁ በሁሉም ላይ ይሆናል የሁሉም እጅ ደግሞ በእርሱ ላይ ይሆናል፤ እርሱም በወንድሞቹ ሁሉ ፊት ይኖራል”፡፡» ኦሪት ዘፍጥረት 16፡11-12

እስራኤላውያን ከአባታቸው ከያዕቆብ የተገኙና የዘር ግንዳቸውም ከኢስሐቅ በኩል የመጣ መሆኑ ግልጽ ከሆነ፤ እስማኤልና ኢስሐቅም ወንድማማቾች ስለሆኑ የሁለቱ ዘሮች ወንድማማቾች ለመሆን የሚያግዳቸው አንዳችም ነገር የለም፡፡ ስለዚህ የትንቢቱ ቃል «ከወንድሞቻቸው መካከል» ማለቱ ከአረቦች መካከል መሆኑን ያመላክታል፡፡ ከሙሴ በኋላ ከአረብ ምድር የተነሱት ብቸኛውና ታላቁ ነብይ ደግሞ ነብዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ብቻ ናቸው ይህንን አስመልክቶ ቁርዓን እንዲህ ይላል፡-

ቅ.ቁርዓን፡- «እርሱ ያ በመሃይሞቹ ውስጥ አንቀጾቹን (ቁርዓንን) በነርሱ ላይ የሚያነብላቸው (ከሚጋራት) የሚያጠራቸውም መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸው የኾነን መልክተኛ (ሙሐመድን) ከነርሱ ውስጥ የላከ ነው፤ እነርሱም ከርሱ በፊት በግልጽ ስህተት ውስጥ ናቸው፡፡» አል-ጁመዓህ 62፡2

ለ. «እንደ አንተ ያለ ነብይ» ሲል ኢየሱስን ወይም ኢያሱን ነው ብንል ሁለቱም ከእስራኤላውያን ናቸውና ትንቢቱ እነሱ መሆናቸውን አያመላክትም፤ ምክንያቱም ከእስራኤላውያን ሙሴን የሚመስል ነብይ እንደማይነሳ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ አስቀምጧል፡-

መ.ቅ፡- «እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነብይ ከዚያ ወዲህ በእስራኤል ዘንድ አልተነሳም፤...» ኦሪት ዘዳግም 34፡10-11

«እንደ አንተ ያለ ነብይ አስነሳለሁ» የሚለው የትንቢቱ ቃል ደግሞ መፈጸም ስላለበት ያ የሚነሳው ነብይ ከሌላ ምድር ተነስቷል፡፡ ነገር ግን ይህን ትንቢት ለኢያሱ ነው ለሚሉት ግልጽ ማድረግ የምንፈልገው በሙሴና በኢያሱ መካከል ምንም ዓይነት መመሳሰል የለም፡፡ ምክንያቱም ሙሴ የመጽሐፍ (የተውራት) ሕግ ባለቤት ሲሆን፤ ኢያሱ ግን እንደዚያ አልነበረም እንዲያውም የሱ ተከታይ ነበረ፡፡ በአጠቃላይ ግልጽ ለማድረግ ሙሴን የሚመስል ነብይ ማነው? ለኢየሱስ ወይም ለሙሐመድ /ሰላም በሁለቱም ላይ ይሁን/ ለማን ነው የሚገባው የሚለውን ስናነጻጽር፡-

1. እንደ ክርስቲያኖች እምነት ኢየሱስ ስለ ዓለም ኃጢዓት ሞቷል፡፡ ሙሴና ሙሐመድ ግን ስለ ዓለም ኃጢአት አልሞቱም፡፡

2. አሁንም እንደ ክርስቲያኖች እምነት ኢየሱስ አምላክ ነው፡፡ ሙሴና ሙሐመድ ግን አምላክ አይደሉም፡፡

3. አወላለዳቸውን ያየን እንደሆነ ሙሴና ሙሐመድ ከእናትና ከአባት ሲሆን ኢየሱስ ግን ተአምራዊ በሆነ አፈጣጠር ከእናት ብቻ ነበር፡፡

4. የቤተሰብ ሁኔታ ሙሴና ሙሐመድ ያገቡና የወለዱ ሲሆኑ ኢየሱስ ግን ሚስትም ልጅም አልነበረውም፡፡

5. የሥራ ድርሻቸው ሙሴና ሙሐመድ ነብይና አስተዳዳሪ ሲሆኑ ኢየሱስ ግን ነብይ ብቻ ነበር፡፡

6. በጎልማሳነታቸው ተገደው ስለመሰደዳቸው ሙሴ ወደ ሜዲያን ተሰደዋል ሙሐመድም ወደ መዲና ተሰደዋል፡፡ ኢየሱስ ግን በጎልማሳነቱ ከእስራኤል አልወጣም፡፡

7. ከፈጣሪ የወረደላቸውን መልዕክት በጽሑፍ ማስቀመጣቸው ሙሴ በሕይወት እያለ ኦሪትን /ተውራትን/ በጽሑፍ አስቀምጠዋል፡፡ ሙሐመድ በሕይወት እያሉ ቁርዓንን አስቀምጠዋል፡፡ ኢየሱስ ግን ካረገ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው ወንጌል በጸሐፍያን የተጻፈው፡፡

8. የትምህርታቸው ባህሪይ ሙሴና ሙሐመድ መንፈሳዊና ሕግ-ነክ ሲሆን፤ ኢየሱስ ግን ይበልጡን መንፈሳዊ ነበር፡፡

9. አመራራቸው በሕዝብ ዘንድ የነበራቸው ተቀባይነት ሙሴና ሙሐመድ በመጀመሪያ ተቀባይነት አላገኙም ነበር በኋላ ግን ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡ ኢየሱስ ግን በአብዛኛው እስራኤላውያን ዘንድ ተቀባይነት አላገኙም ነበር፡፡

በአጠቃላይ በጣም ብዙ አለመመሳሰልን በሙሴና በኢየሱስ መካከል እናገኛለን፡፡ ነገር ግን ነብዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ለዚህም ነው ኢየሱስ ከእስራኤሎች ነብይ እንደማይነሳ በግልጽ የተናገረው፡-

መ.ቅዱ፡- «አላችኋለሁ የእግዚአብሔር መንግስት ከእናንተ ትወሰዳለች ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች፡፡» የማቴዎስ ወንጌል 21፡43

ይህ የሚያመለክተው የነብይነት ማዕረግ ከእስራኤላውያን እንደሚነጠቅና ለሌላ ሕዝብ እንደሚሰጥ ያመለክታል፡፡ ስለዚህም ከአረቦች ሙሴን የሚመስል ነብይ እንደተላከ ቁርዓን ገልጾልናል፡-

ቅ.ቁረዓን ፡- «እኛ በናንተ ላይ መስካሪ መልክተኛን ወደናንተ ላክን ወደ ፈርዖን መልክተኛን እንደላክን፡፡»

አል-ሙዘሚል 73፡15

ሐ. «አስነሳላቸዋለሁ» አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህ ትንቢት የተነገረው ለኢያሱ ነው ሲሉ ይደመጣል፡፡ የትንቢቱ ቃል ግን «አስነሳላቸዋለሁ» ነው የሚለውና ይህም ወደፊት ለሚከሰት ድርጊት ነው የሚናገረው ኢያሱ ግን ይህ ትንቢት በተነገረበት ጊዜ በዘመኑ ነበር፡፡ ስለዚህ ትንቢቱ ለኢያሱ ነው ብለን መናገር አንችልም፡፡

መ. «ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ» ያ የሚነሳው ነብይ መለኮታዊ ራዕይ እየተገለጸለት እንጂ ከራሱ /ከልብ ወለድ/ አይናገርም፡፡ ይህን አስመልክቶ ቁርዓን ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

ቅ.ቁ፡- «ነብያችሁ (ሙሐመድ) አልተሳሳተም፤ አልጠመመም፡፡ ከልብ ወለድም አይናገርም፡፡ እርሱ (ንግግሩ) የሚወርድ ራዕይ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡» አል-ነጅም 53፡2-4

ስለዚህ የአምላክን ቃል በአንደበታቸው እየተደረገላቸው ነበር የሚናገሩት፡፡

ለምሳሌ ያህል፡- ቅ.ቁ፡- « በል "እርሱ አላህ አንድ ነው፡፡ አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው፡፡ አልወለደም አልተወለደም፡፡ ለርሱም አንድም ብጤ የለውም"፡፡» አል-ኢኽላስ 112፡1-4

ይህ የቁርዓን ጥቅስ የወረደበት ምክንያት ሙሽሪኮች /አጋሪዎች/ ወደ ነብዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ መጡና "እኛ በካዕባ ዙርያ 360 ጣዖቶች እናመልካለን አንተ የምታመልከውን አምላክ ባሕሪ ግለጽልን" አሏቸው፡፡

በዚህን ጊዜ ይህ የቁርዓን አንቀጽ ወረደ፡፡ አላህ አንድ መሆኑን እንዲናገሩ «በል» በሚለው ትዕዛዝ ታዘዙ፡፡ ነብዩ ግን ለእነዚህ ሕዝቦች «አላህ አንድ ነው» አላሏቸውም፡፡ እሳቸው ያሉት «በል "አላህ አንድ ነው"» በማለት ነበር፡፡ «በል» የሚለው ቃል ከአላህ ዘንድ ወደ ነብዩ ሲመጣ በትዕዛዝ መልክ ነበር፡፡ ከነብዩ አንደበት ሲሰማ ደግሞ ማንን ለማዘዝ ነው? የሚል ጥያቄ ይነሳል፡፡ መልሱም

እሳቸው ማዘዛቸው ሳይሆን ቁርዓኑን ከላይ እንደ ወረደ ማለት «የአላህን ቃል» በወረደበት መልኩ ለሕዝባቸው ማስተላለፍ ስለነበረባቸው ነው።።

ሠ. «ያዘዝሁትን ቃል ሁሉ ይነግራችኋል» ያ የሚነሳው ነብይ ከአምላክ ዘንድ የታዘዘውን ቃል አንድም ሳያስቀር ማድረስ አለበት።። ይህንን አስመልክቶ ቁርዓን እንዲህ ይላል፡-

ቅ.ቁ፡- «አንተ መልክተኛ ሆይ! ከጌታህ ወዳንተ የተወረደውን አድርስ፤ ባትሰራም (ጥቂትንም ብታስቀር) መልክቱን አላደረስክም ፤ (አድርስ) አላህም ከሰዎች ይጠብቅሃል፤ አላህ ከሃዲዎችን ሕዝቦች አያቀናምና።።» አል-ማኢዳህ 5፡67

ነብዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ በሃዲሳቸው ከአላህ የታዘዙትን ምንም ሳያስቀሩ ማድረሳቸውን ከሐጅተል ወዳዕ /የመሰናበቻ ሐጅ/ ሲመለሱ ባልደረቦቻቸውን አስመስክረዋል።። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መለስ ስንል እውን ኢየሱስ ከአምላክ ዘንድ የታዘዘውን ቃል በሙሉ አድርሷልን? ካላደረሰስ ለምን? እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መልዕክቱን ሙሉ በሙሉ እንዳላደረሰ እንረዳለን።።

መ.ቅ፡- «የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም።።»

የዮሐንስ ወንጌል 16፡12

ረ. «በስሜም የሚናገረውን» የቅዱስ ቁርዓንን 113 ምዕራፎች ብንመለከታቸው የሚጀምሩት በአላህ ስም ነው።። ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በሳቸው ዘመን ይኖሩ ለነበሩት አምስት ንጉሶችም ኢስላምን እንዲቀበሉ መልክተኛ በላኩ ጊዜ በደብዳቤአቸው ላይ ሲጀምሩ በአላህ ሥም ነበር የጀመሩት።። እንዲሁም የሳቸው ተከታይ የሆኑ ሙስሊም ሕብረተሰብ አንድን የተቀደሰ ሥራ ሲጀምሩ «በአላህ ሥም እጅግ በጣም ሩኅሩኅ በጣም አዛኝ በኾነው» ብለው ነው የሚጀምሩት።።

መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ግን ብንመለከት በአምላክ ሥም የተጀመሩ አንድም ምዕራፍ አናገኝም።። የኢየሱስ ወንጌል ማቴዎስ እንደፃፈው፣ የኢየሱስ ወንጌል ማርቆስ እነደፃፈው፣ የኢየሱስ ወንጌል ሉቃስ እንደፃፈው፣ የኢየሱስ ወንጌል ዮሐንስ እንደፃፈው እየተባለ ተፃፈ እንጂ በአምላክ ሥም ተጀምሮ አልተፃፈም።። እንዲሁም አንድን ሥራ ሲጀምሩ በአንዳንድ የክርስትና እምነት ተከታዮች «በስመ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ» በማለት ነው የሚጀምሩት፤ ሌሎቹም «በኢየሱስም ሥም» በማለት ነው የሚጀምሩት እንጂ በአምላክ ሥም አይደለም።።

መደምደሚያ

☞"ይህ የሚቆየው የፈጣሪ መልዕክተኛ የሆነው ስሙም #ሙሐመድ እስኪመጣ ድረስ ብቻ ነው፣እርሱ ሲመጣም በፈጣሪ ሕግ ለሚያምኑ ሁሉ ይህን ሽንገላ ይገልጣል"። (በርናባስ ወንጌል ምዕራፍ 220 ቁጥር 16) በርናባስ ከኢየሱስ(ዐሰ) አንደበት የሰማውን እንዲህ ፅፎታል።

►…..በዚያም ወቅት አምላክ እኔን ከምድር ላይ ይወስደኝና እኔን አሳልፎ የሸጠውን ከሐዲ መልኩን በመቀየር እኔን እንዲመስል ያደርገዋል፣ሰዎችም እኔ የተገደልኩ ይመስላቸዋል ። እርሱ ይህን የውርደት ሞት ከሞተ በኋላም ከብሬን ተነፍጌ ለረዥም ዘመን በአለም እኖራለው ነገር ግን ቅዱሱ የአምላክ መልዕክተኛ ሙሐመድ በሚመጣ ጊዜ ይሄ ውርደት ከእኔ ይወገዳል። (የበርናባስ ወንጌል ምዕ 112 ቁጥር 13-16)

የበርናባስ ወንጌል እና ነብዩ ሙሀመድ(ሰ.ዐ.ወ) - http://wp.me/P3Aleh-8h

❤ይህ ትንቢት ለማን የተነገረ ትንቢት ነው?❤

'ይሕን ጥያቄ መልሱልን እስኪ ክርስትያን ወገኖቻችን እየሱስ ክርስቶስ መፃፍና ማንበብ ይችላልን ? ወይስ አይችልም?

መልሱ ቀላል ስለሆነ እኛው እንመልሰውና አዎ ኢየሱስ መፃፍም ሆነ ማንበብም ይችላል ትሉናላቹ።ታድያ ይሄ ወደፊት የሚመጣው የማይፅፍና የማያነበው ነቢይ ኢየሱስ ካልሆነ ማነው?

እኛ ሙስሊሞች ነብዩ MOHAMMED (ሰዐወ) ማንበብም ሆነ መፃፍ አይችሉም ብለን እናምናለን ስለዚህ ይህ ትንቢት ፍፃሜውን ያገኘው በነቢዩ ሙሐመድ(ሰዐወ) አማካኝነት ነው።

እየሱስ ማንበብና መፃፍ ከቻለና ነብዩ መሐመድ (pbuh) ማንበብና መፃፍ ካልቻሉ ይሔ ትንቢት የተነገረው ለማን ነው ?

"የማይጽፍ እና የማያነብ"ነቢይ ሙሀመድ(ሰአወ) ናቸው።

አምላካችን አላህ በመልአኩ ጂብሪል ወደ ነብያችም"ﷺ" ልብ "ኢቅራ"(አምብብ) የሚል ትእዛዝ አውርዷል፡-96:1 #አንብብ በዚያ ሁሉን በፈጠረው ጌታህ ስም። አምላካችም አላህ ነብያችን"ﷺ" በወረቀት ላይ መጻፍ እንደማይችሉ እና በወረቀት በተጻፈ መጽሐፍ ላይ ያለን ቃል ማንበብ እንደማይችሉ አስረግጦ ነግሮናል፡- ለእነዚያ ያንን እነርሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍ እና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለኾኑት በእርግጥ እጽፍለታለሁ፡፡ (7፥157)

በላቸው፡- «እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደ እናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ፤ እርሱም ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና ለእርሱ ብቻ የኾነ ነው፤ እርሱ እንጂ ሌላ አምላክ የለም፡፡ ሕያው ያደርጋል፡፡ ይገድላልም፤ በአላህ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የማይጽፍ እና የማያነብ ነቢይ በኾነው መልክተኛው እመኑ፡፡ ቅንንም መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት፡፡(7:158) ከእርሱ በፊትም መጽሐፍን #የምታነብ በቀኝህም #የምትጽፈው አልነበርክም፡፡ ያን ጊዜ አጥፊዎቹ በእርግጥ በተጠራጠሩ ነበር፡፡ (29:48)

መፅሀፍ ቅዱስ ላይ ደግሞ ወደፊት የሚመጣው ነቢይ ማንበብም ሆነ መፃፍ እንደማይችል እንዲህ ይገልፅልናል

☞"ደግሞም መፅሐፉን ማንበብን ለማያውቅ ይሕን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ ማንበብ አላውቅም ይላቸዋል (ኢሳያስ29:12) VS መልኣኩ ጅብሪል (አሰ) ለነቢዩ ሙሀመድ(ሰአወ)አንብብ ሲላቸው ማንበብ አልችልም ያሉበት ንግግር በሐዲስ ተዘግቧል፡-

ሰሂህል ቡሃሪ ቅጽ 1 መጽሐፍ 1 ቁጥር 3:

بُدِئَ مَا أَوَّلُ قَالَتْ أَنَّهَا الْمُؤْمِنِينَ، أُمِّ عَائِشَةَ عَنْ الزُّبَيْرِ، بْنِ عُرْوَةَ عَنْ شِهَابٍ، ابْنِ عَنِ عُقَيْلٍ، عَنْ اللَّيْثُ، حَدَّثَنَا قَالَ بُكَيْرٍ، بْنُ يَحْيَى حَدَّثَنَا إِلَيْهِ حُبِّبَ ثُمَّ الصُّبْحِ، فَلَقِ مِثْلَ جَاءَتْ إِلاَّ رُؤْيَا يَرَى لاَ فَكَانَ النَّوْمِ، فِي الصَّالِحَةُ الرُّؤْيَا الْوَحْيِ مِنَ وسلم عليه الله صلى اللَّهِ رَسُولُ بِهِ إِلَى يَرْجِعُ ثُمَّ لِذَلِكَ، وَيَتَزَوَّدُ أَهْلِهِ، إِلَى يَنْزِعَ أَنْ قَبْلَ الْعَدَدِ ذَوَاتِ اللَّيَالِيَ ـ التَّعَبُّدُ وَهُوَ ـ فِيهِ فَيَتَحَنَّثُ حِرَاءٍ بِغَارِ يَخْلُو وَكَانَ الْخَلاَءُ، حَتَّى فَغَطَّنِي فَأَخَذَنِي ” قَالَ .“ بِقَارِئٍ أَنَا مَا ” قَالَ .اقْرَأْ فَقَالَ الْمَلَكُ فَجَاءَهُ حِرَاءٍ، غَارِ فِي وَهُوَ الْحَقُّ جَاءَهُ حَتَّى لِمِثْلِهَا، فَيَتَزَوَّدُ خَدِيجَةَ،

أَنَا مَا فَقُلْتُ .اقْرَأْ فَقَالَ أَرْسَلَنِي ثُمَّ الْجَهْدَ، مِنِّي بَلَغَ حَتَّى الثَّانِيَةَ فَغَطَّنِي فَأَخَذَنِي .بِقَارِئٍ أَنَا مَا قُلْتُ .اقْرَأْ فَقَالَ أَرْسَلَنِي ثُمَّ الْجَهْدَ، مِنِّي بَلَغَ
{الأَكْرَمُ وَرَبُّكَ اقْرَأْ * عَلَقٍ مِنْ الإِنْسَانَ خَلَقَ * خَلَقَ الَّذِي رَبِّكَ بِاسْمِ اقْرَأْ} فَقَالَ أَرْسَلَنِي ثُمَّ الثَّالِثَةَ، فَغَطَّنِي فَأَخَذَنِي .بِقَارِئٍ

አይሻ እንደተረከችው “ነቢዩ በመቀጠል እንዲህ ላሉ፦ መልኣኩ ያዘኝና ላቅም እስኪያንሰኝ ድረስም ተጫነኝ። ከዚያም ለቀቀኝና እንዳነብ ጠየቀኝ እኔም ማንበብ ላላውቅም ላልኩት: ከዚያ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ላቅም እስኪያንሰኝ ድረስ ያዘኝ: ከዚያ ለቀቀኝና እንደገና እንዳነብ ጠየቀኝ እኔም እንደገና ማንበብ ላላውቅም ላልኩት: ከዚያም በኋላ ለሶስተኛ ጊዜ ያዘኝና ተጫነኝ ከዚያ ለቀቀኝና ” አንብብ በዚያ ሁሉን በፈጠረው ጌታህ ስም። ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው። አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን” አለኝ:”አንብብ የሚላቸው ቁርአንን ነው፤ ነብያችም"ﷺ" ሲያነቡት የነበረው ግን በቃል ለሚነበበው መነባነብ ነው፤ ምክንያቱ አላህ፦ "ባነበብነውም ጊዜ ካለቀ በኋላ ንባቡን ተከተል" የሚል ሀይለ-ቃል ይጠቀማል፦ባነበብነውም ጊዜ ካለቀ በኋላ ንባቡን ተከተል።(75:18)

አምላካችን አላህ(ሱወ) በመልኣኩ ጂብሪል አማካኝነት ወደ ነብያችም"ﷺ" ሲያነብ ያንን ንባብ ነብያችን"ﷺ" የሚከተሉት መነባነብ ስለሆነ ነው፤ በተጨማሪም ቀስ በቀስ በልባቸው መውረዱ ነው፤ ይህ የወረደው ተንዚል ለሰዎች ካነበቡ በኃላ ነው 40 የሚያክሉ ፀሐፊዎቻቸው የሚፅፉት፤ ልብ አድርጉ ቁርአን ከመጻፉ በፊት ለሰዎች በቃል ማንበባቸው በራሱ አንብብ የተባሉት መጽሐፍ በልባቸው ላይ የሚወርድ ግህደተ-መለኮት እንጂ ወረቀት አለመሆኑን ፍትንውና ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፦

- ቁርአንንም በሰዎች ላይ ሆነህ ,ታነበው ዘንድ ,ከፋፈልነው፤ ቀስ በቀስ ,ማውረድንም አወረድነው።(17:106)
- እኛ ,መጽሐፉን በእነሱ ላይ ,የሚነበብ ሆኖ ,በአንተ ላይ ,ማውረዳችን አይበቃቸውምን?(29:51)
- ከመጽሐፉ ወደ አንተ ,የተወረደውን ,አንብብ፤ (29:45)❤
- ከጌታህም ,መጽሐፍ ወደ አንተ ,የተወረደውን ,አንብብ፤(18:27)

እየሱስ ማንበብና መፃፍ ከቻለና ነብዩ መሐመድ (pbuh) ማንበብና መፃፍ ካልቻሉ ይሔ ትንቢት የተነገረው ለማን ነው?

ነቢዩ ሙሀመድ(ሰዐወ) አኢሻን በልጅነቷ ለምን ነበር ያገቧት? ምክንያታቸውስ ምን ነበር?

ወደ ምላሹ ከመግባታችን በፊት አንድ ቀላል ጥያቄ እንጠይቃቹ ። የኢየሱስ እናት ድንግል ማርያም የሴፍ ሲያጫት ስንት ዓመቷ ነበር? እርሱ ዘጠና (90) አመቱ እርሷ ደግሞ አስራ ሁለት (12) አመቷ ነበር! እንደ 1913ቱ እትም የካቶሊክ ኢንሳይክሎፒዲያ/ Catholic Encyclopedia መሰረት።

ኢብኑ ሰዐድ በጦበቃት ላይ እንደዘገቡት አዒሻ ለነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከመታጨቷ በፊት ጁበይር ኢብኑ ሙጥኢም ለሚባል ሰው ታጭታ ነበር:: በሃይማኖት መለያየት ምክንያት ጋብቻው ተሰርዟል:: ይህ የሚያሳየው በነበረው ሁኔታ አዒሻ ለጋብቻ ደርሳ እንደነበር ነው::

እንደሚታወቀው በሞቃታማ አካባቢዎች /ምሳሌ ዐረቢያ በረሃ/ ሴቶች ቶሎ ለአቅመ ሐዋን ይደርሳሉ:: ቶሎም ያገባሉ፣ አ ንዲሁም ቶሎ የልጅ እናት ይሆናሉ:: ይህ እኛ የምንለው ሳይሆን በተጨባጭ የተረጋገጠ እውነታ ነው:: “Woman” የተሰኘው መጽሐፍ “The average temperature of the country of province, is considered the chief factor here, not only with regard to menstruation but as regards of the whoe of sexual development at puberty.’’ (Herman H. ploss, Max Bartels & Paw Bartels, Woman, volume I, lord & Bransby, 1988, page 563)

“የአንድ ሀገር ወይንም አውራጃ አማካይ የሙቀት መጠን እዝያ ላይ ዋናው ምክንያት ነው ለሴቶቹ ቶሎ አካላዊና አእምሮዋዊ መድረስ፡፡ይህ የወር አበባን ብቻ አስመልክቶ ሳይሆን መላውን በአቅመ ሔዋን የሚከሰተውን የፆታዊ አካላዊ ለውጥን ጨምሮ ነው፡፡ ’’

በኢስላማዊ መዛግብት እንደሰፈረው ትንሹ ሴት ለልጅ የወር አበባ የምታየበት እድሜ ዘጠኝ መሆኑ እንዲህ ተዘግቧል፡-

ትንሹ ሴት ልጅ የወር አበባ የምታይበት እድሜ #ዘጠኝ ዓመት ነው፡፡”አልካፊ ፊ ፊቅህ ኢብነ ሀንበል፣ ጥራዝ 1፣ ገጽ 74፣

ሸርህ አል – ዑምዳ፣ ጥራዝ 1፣ ገጽ 480/

እነ ሐመረ ተዋህዶ “ጥቃት ተፈፀመባት” የሚሏት አሚሻ ሴት አገልጋይ ዘጠኝ ዓመት ከሞላት እንደ ትልቅ ሴት ትቆጠራለች በ9 አመቷ የወር አበባ ታያለች፣ሰውነቷ ቶሎ ይደነድናል፣ እንዲሁም ለአካለ መጠን(ለጋብቻ) ትደርሳለች ብላለች፡፡

እንዲህም ተዘግቧል፡-

“አሚሻ እንዳለችው ሴት አገልጋይ /ባሪያ/ ዘጠኝ ዓመት ከሞላት እርሷ ሴት /የደረሰች ነች፡፡ “/ሱነኑል በይሀቂ አልኩብራ፣ አልካፊ ፊ ፊቅህ ኢብነ ሀንበል ጥራዝ 3፣ ገጽ 27፣ ዐውነል ማዕቡድ፣ ጥራዝ 6፣ ገጽ 83/

ስለዚህ ሁሉም ስፍራ ያሉ ሴቶች በተመሳሳይ ጊዜ የወር አበባ እንደማይመጣባቸው መታወቅ አለበት፡፡ሞቃታማ አካባቢ ያሉ ሴቶች ቶሎ የወር አበባ ያያዩ፡፡ ለምሳሌ በሱነኑል በይሀቂ አል-ኩብራ ጥራዝ 7፣ ገጽ 421 ላይ በአስር ዓመት እድሜው ስለወለደች ሴት ተዘግቧል፡፡በዚሁ የሐዲስ መጽሐፍ ላይም በዘጠኝ ዓመቷ ስላረገዘች ሴትም ተዘግቧል፡፡የኢየሱስ እናት የሆነችው ማሪያም በ12 አመቷ አናፂው ዮሴፍ እጮኛዋ እንደነበረና እንዳገባት ኢንሳይክሎፒድያ ብሪታኒካ ዘግቦታል። አሚሻም በዘጠኝ ዓመቷ ለአቅመ ሔዋን መድረሳም እንዲህ ተዘግቧል፡-

“አሚሻ በእርግጥ ዘጠኝ ዓመት ሳለች ደረሰች /ለአቅመ ሔዋን/” ቱሕፈቱል አህወዚ፣ ጥራዝ 4፣ ገጽ 208/

በነበረው ማህበረሰብ ውስጥ አሚሻ /ረ.ዐ/ በዘጠኝ ዓመቷ ለአቅመ ሄዋን ከደረሰች ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ቢያገቧት ምንድ ነው ችግሩ?

ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከፈፀሟቸው ጋብቻዎች ጀርባ ሁሉ አስተምህሮት አለ፡፡ ለምሳሌ በዘመነ ጃሂሊያ /መሃይማን/ ጋብቻን በሸዋል ወር ውስጥ መፈፀም መጥፎ ድርጊት ተደርጉ ይጠላ ነበር፡፡ይህን ኃላ ቀር ልማድ ለማስቀረት ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከአሚሻ ጋር በሸዋል ወር ውስጥ ጋብገፐ በመፈፀም ኃላ ቀሩ ባህል እንዲቀር አርአያ ሆኑ፡፡ አሚሻ ራሷ በሸዋል ወር ውስጥ እንዳገቧት እንዲህ ትገልፃለች፡-

ከዑርዋ እንደተላለፈው አሚሻ እንዲህ ብላለች፡-

“የአላህ መልዕክተኛ ያገቡኝ በሸዋል ወር ነው፡፡ ወደ ቤት ያስገቡኝም /ዱኩል/ በሸዋል ወር ነው፡፡

“ሱነኑ ነሳኢ አል-ኩብራ፣ ጥራዝ 3፣ ገጽ 274፣ ሰሒህ ሙስሊም፣ ጥራዝ 2 ገጽ 1039/ አሚሻ /ረ.ዐ/

“የአላህ መልዕክተኛ በሸዋል ወር ነው ያገቡኝ” ብላለች፡፡ ኢማሙ ነወዊ ይህን አስመልክተው አሚሻ በዚህ አነጋገሯ ልትገልጻው የፈለገችው በመሃይምነት /ጃሂሊያ/ ጊዜ በሸዋል ውስጥ ኒካህም ሆነ ጋብቻ ይጠላ ስለነበር ነው፡፡ በዚህ አነጋገሯ ይህንን መጻሪያን ለማሳየት ነው፡፡ ”/አል–ዲባጅ አል ሙስሊም፣ ጥራዝ 4፣ ገጽ 28/ በቀድሞ ዘመቻ ጋብቻ የሚፈጸመው ሴት ልጅ የወር አበባ እንዳየች ወዲያው ነበር ባል የምታገባ የነበረው፡፡

ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ እንዲህ ይላል፡፡

“ለጋብቻ ትንሹ የእድሜ ገደብ፣ በፊት 12 ዓመት አልያም ከዚያም ያነሰ የነበረው ሲሻሻልና ከፍ ሲል ቆይቶ በአብዛኛው ሀገሮች አሁን በ15 እና በ21 ዕድሜ መካከል ሆኗል። “‘’Marriage’’ Britannical Tudent Library.

2008. Encyclopedia Britannica 2006 Ultimate Reference Suite DVD 6 oct.2008)

ነቢዩ ሙሃመድ(ሰዐወ) የማደጎ ልጃቸው የነበረውን የዘይድ ኢብን ሃሪስ ሚስት ለምን አገቧት?

☞ዐረቦች ከኢስላም በፊት ሲሰሩት ከነበሩት አፍራሽ ባህሎች አንዱን ለአብነት እናቅርብ።

ይኸውም አንድ ሰው ከአብራኩ ያልወጣን ልጅ ‹‹አንተ ልጄ ነህ፤ እወርስሃለሁ ትወርሰኛለህ›› በማለት ይዋዋላል። የማደጎ ልጅ ያደርገዋል። ለቤተሰቡና ለአከባቢው ሰው በማሳደግ ይጅምራል።ይህም የማደጎ ልጅ ከአብራኩ ከተወለዱ ልጆች ጋር እኩል መብት ይሰጠዋል። ይኸውም አሳዳጊው (አባት ተብዬው) ቢሞት ይወርሰዋል፤ እርሱም ከአሳዳጊው ይወርሳል።

የአሳዳጊውን ልጅ እንዲያገባ አይፈቀድለትም። አሳዳጊውም የማደጎ ልጁን ሴት ልጅም ሆነ እርሱ የፈታትን ሴት ማግባት እርም ይሆንበታል።የማደጎ ልጅ ወላጅ አባት ስምም በአሳዳጊው ይተካ።

ይህ ባል በግርድፉ ስናየው መጥፎ ላይመስለን ይችላል። በእርግጥ ማንም ግለሰብ አሳዳጊ የሌላቸውን ልጆች ሆነ የሌላ ሰው ልጅ በራስ ተነሳሽነት ቢያሳድግና ለደረጃ ቢያበቃ ኢስላም አይከለክልም፣አይቃወምም።ነገር ግን ህጋዊ ልጅ ያልሆነውን ሰው ልጄ ነው በማለት የአባቱን ስም ቀይሮ የሥጋዊ ልጁ ካልሆነ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ማህበራዊ ግኑኝነት ጋር ማስተሳሰር ቁርአን አይቀበለውም።

ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ግኑኝነት ስንል የማደጎ ልጅ እንዲወርስና በአሳዳጊውም እንዲወረስ ማድረግና ከጋብቻ ጋር የሚገናኙ ጉዳዮችን ለመጠቆም ነው።የማደጎ አሳዳጊውን መውረስ ወይም መወረስ እንዲሁም እንደ ስጋ ዘመድ ተቆጥሮ የተለያዩ የጋብቻ ማነቆዎች መፈጠራቸው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ውዝግብና ማህበራዊ ቀውስ ፈጥሮ ነበር።

↘1ኛ) ለምሳሌ አሳዳጊ ሲሞት የስጋ ልጆች ውርስ በሚቀርብበት ወቅት የማደጎ ልጅም ወራሽ ነኝ ብሎ ስለሚቀርብ ሽኩቻ መፍጠሩ እሙን ነው።

↘2ኛ) የማደጎ ልጅ በሚሞትበት ጊዜ አሳዳጊ ወራሽ ነኝ በማለት ሲመጣ የማደጎ ልጅ ሚስት የስጋ ወላጅ፤ ልጆችና ሌሎችም ለውርስ ይቀርባሉ።ግና የማደጎ ልጅ ባህል ሚስት ባሏን እና ልጇና ልጅም አባቱን ወዘተ….እዳይወርስ ያግዳዋል። አልያም ሊያገኙ የሚገባቸውን ትክክለኛ ድርሻ ይነፈጋሉ።

↘3ኛ) የማደጎ ልጅ በስጋ አባቱ ስም መጠራት ሲገባው የወላጅ አባቱ ስም ተቀይሮ በአሳዳጊው ስም መጠራት የአባትነትን ተፈጥሮአዊ ፀጋና ማንነት እንደመፋቅ ይቆጠራል።

የማደጎ ልጅ ሲባል በአገራችን እንደሚታወቀው ከመንገድ ዳር ወይም ከተስፋ ተቋማት ወይም ከድሃ ቤተ ዘመዶች ተቀብለን ልጇ ነህ ወላጅህ ነኝ ትወርሰኛለህ፣ እወርስሃለሁ በማለት ቃል የምንገባቸውን ሰዎችና በዚህ መስክ የምናሳድጋቸውን ልጆች ብቻ ሳይሆን

የሚመለከተው በቂ መጠለያ ቤተሰብና መተዳደሪያ ያላቸውን ልጆችንም እንደ ስጋ ልጅ መቁጠርን የሚጠቁም መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡

↘4ኛ) እንደ አሳዳጊ የማደጎ ልጁን ልጆቹንም ሆነ የቀድሞ ሚስት (የተፈታቸውን) እንዲያገባ ቅርብ ዘመድ (እህት አክስት) የዐረቦች ባህል አይፈቅድም ነበር፡፡

☞ በመሆኑም በማህበረሰቡ የጋብቻ ህይወት ላይ ነቀርሳ ሆኖ ቆይቷል፡፡ስለዚህ ተመሳሳይ ችግሮችን ለመፍታትና ኢስላም ከማህይማን የተወረሱ ጎጂ ባህሎችን ለመፍታትና ኢስላም ከመሐይማን የተወረሱ ጎጂ ባህሎችን ለማጥፋ ሲል አስደናቂ ፀረ-ጎጂ ባህል እርምጃ ወስዷል፡፡

☞ጥበበኛው አላህ(ሱ.ወ) ከላይ የተጠቀሰውን ጎጂ የሕይወት ገጠመኝ መዋጋት ፍላጎቱ ነበርና ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የነብይነት ማዕረግ ከማግኘታቸው በፊት ከላይ በጠቀስነው የዐረቦች ባህላዊ ህይወት ውስጥ እንዲያልፉ አደረገ፡፡

↘ይኸውም ዘይድ ኢብን ሃሪሳን የማደጎ ልጅነት እውቅና ሰጡት፡፡በምን አይነት ሁኔታ ነብዩ(ሰዐወ) ዘይድን ልጃቸው ሊያደርጉት እንደበቁ የታሪክ ሰዎችና የቁርአን ተንታኞች በሰፊው የገለጹት ጣፋጭ ታሪክ አለ፡፡ለጊዜው ወደ ታሪኩ አንገባም፡፡ እዚህ ላይ ትኩረት መስጠት የምንሻው ራሳቸው ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ዘይድ ኢብን ሀሪስን(ልጅ) አድርገው መያዛቸውንና የዚህ ልጅ ስምም ዘይድ ኢብን ሀሪስ መባሉ ቀርቶ ዘይድ ኢብኑ ሙሐመድ እየተባለ መጠራቱ ነው፡፡

አብደላ ኢብን ዑመር (ረ.ዐ) የተባለው የነብዩ አስሃባ(ባልደረባ) እንዲህ ይገልጸዋል፡-

☞‹‹ዘይድ ኢብ ሀሪስን ዘይድ ኢብን ሙሐመድ ብለን ነበር የምንጠራው፡፡ የኋላ ኋላ ግን አላህ (ሱ.ወ) ፡- (ሱረቱ አል-አህዛብ 5) አንቀጽ ሲያወርድ ነብዩ‹‹አንተ ዘይድ ከእግዲህ ዘይድ ኢብን ሀሪስ ኢብን ሹረይሂል ተብለህ ነው የምትጠራው፡፡››አሉት፡፡

☞ እኛም በዚሁ (በመጀመሪያው) ስሙ እንጠራው ጀመርን ፡፡(ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ዘይነብ ቢንት ጃህሽ አል-አሰዲይ በመባል የምትታወቀውን የአክስታቸውን ልጅ ለዘይድ ድረውለት ነበር፡፡ ለተወሰኑ ጊዜያት ዘይድና ዘይነብ አብረው መኖር ቢችሉም በመሃከላቸው ያለው ግኑኝነት ከቀን ወደ ቀን እየሻከረ መጥቶ ለፍች ተዳረሱ፡፡

የውዝግቡ ምንጭ ዘይነብ ከሉዕላን ቤተሰብ የተወለደችና በዘር ሐረጓና በዕውቀቷ የምትኩራራ ስለነበረች ትላንትና ባሪያ የነበረውን ዘይድ አቻዬ ነው የሚል እምነት አልነበራትም፡፡በመጨረሻም ዘይድ አሰናበታት፡፡ የኋላ ኋላ አላህ (ሱ.ወ) የማደጎ ልጅ ሥርዓትን በኢስላማዊ ባል መተካተ መለኮታዊ እቅዱ ሆነና የነብዩ ሙሐመድን(ሰ.ዐ.ወ) የማደጎ ልጃቸው(ዘይድ) የፈታትን ሴት ማለትም ዘይነብ ቢንት ጀህሽን እንዲያገቡ #በቁርአን_ታዘዙ ፡፡

ነገር ግን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) መናፍቃንን እና የሐሜተኞችን ምላስ በመፍራት ዘይነብን የትዳር ጓደኛቸው ለማድረግ እያንገራገሩ ባሉበት ወቅት በቅዱስ ቁርዓን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መልአኩ ጅብሪል ይዞ ከተፍ አለ፡፡

“……አላህን ልትፈራው ይልቅ የተገባው ሲሆን፤ ሰዎችን የምትፈራ ሆንክ…….ዘይድም ከርሷ ጉዳይን በፈጸመ ጊዜ ፍላጎቱን አርክቶ በፈታትና ዒዳዋን በጨረሰች ጊዜ) በምዕመናኖች ላይ ልጅ አድርገው ባስጠጋቸው (ሰዎች) ሚስቶች፤ ከነርሱ ጉዳይን በፈጸሙ ጊዜ (በማግባት) ችግር እንዳይኖሩባቸው፤ እርሷን አጋባንህ፤ የአላህም ትእዛዝ ተፈጻሚ ነው።።›› (ሱረቱ አል-አህዛብ 33፡ 37)

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ዘይነብን ከቤታቸው አስገቡ። የማደጎ ልጅ ጥንታዊ ወግም በነብዩ አርዓያነት ተሸረ።

وَكَانَ اللَّهُ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمًا ۗ مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَا أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ اللَّهِ وَخَاتَمَ النَّبِيِّينَ [٣٣ : ٤٠]

“ሙሐመድ፤ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም ፤ ግን የአላህ መልእክተኛና የነብያት መደምደሚያ ነው፤ አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው።።”(ሱረቱ አል-አህዛብ 40)

ከላይ የጠቀስነው ታሪክ የምንረዳው ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ)› ዘይነብን ያገቡት በራሳቸው ፍላጎት ሳይሆን ☞#በአላህ_ትእዛዝ

መሆኑን እና ጋብቻው የተፈጸመውም ለከፍተኛ ዓላማ መሆኑ ነው ።።አላህም ነብዩን ይህችን ሴት እንዲያገቡ ያስገደደበት ምክኒያት በምዕመናኖች ላይ ማህበራዊ ችግር እንዳይፈጥር መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል።

ዓኢሻ(ረ.ዐ) የተባለችው የነብዩ ባለቤትም የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከአምላክ የሚተላለፍላቸውን መልእክት የሚሸሽጉ ቢሆን ኖሮ ይህን አንቀጽ ሳይነግሩን ይቀሩ ነበር በማለት ዘይነብ ጋር በመጋባት የአከባቢውን ባህል መዋጋ ለነብዩ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደነበር ጠቁማለች።

ኢማም አል-ቡኻሪ እንደዘገቡትም ዘይነብ(ረ.ዐ) የተቀሩትን የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሴቶች(ሚስቶች ‹‹እናንተ በወላጆቻችሁ አማካኝነት ነብዩ ጋር ስትዳሩ እኔን ግን የዳሩኝ ወላጆቼ ሳይሆኑ ከሰባት ሰማያት በላይ ያለው አላህ(ሱ.ወ) ነው።።›› በማለት ትፎክርባቸው ነበር።

በጥቅሉ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ዘይነብን ያገቡት የዐረቦችን ባህል ለመቃወም፤ ሸሪዓ (ህገ-ኢስላም) ለመመስረት መሆኑን ነው።። አላህም እነሆ ምን አይነት ጥበብ በዚህ ረገድ እንደተጠቀመ መመልከት እንችላለን።።የሰው ልጅ ያለው እውቀትም የአላህን ፍላጎት ጥበብ ሙሉ በሙሉ ሊደርስበት አይችልም። ለዚህም ነው የተከበረው ቁርአን ፡-

وَمَا أُوتِيتُم مِّنَ الْعِلْمِ إِلَّا قَلِيلًا [١٧ : ٨٥]

“ከዕውቀት ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም ፤በላቸው”(ሱረቱ አል- ኢስራእ 17፡85) ሲል ያሳሰበው።

መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ!!

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2)። የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)።

" الْمُمْتَرِينَ مِنَ تَكُونَنَّ فَلَا رَبِّكَ مِنْ الْحَقُّ جَاءَكَ لَقَدْ قَبْلِكَ مِنْ الْكِتَابَ يَقْرَءُونَ الَّذِينَ فَاسْأَلِ إِلَيْكَ أَنْزَلْنَا مِمَّا شَكٍّ فِي كُنْتَ فَإِنْ " سورة يونس 94

"ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ። እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሃል። ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን።" (ሱረቱ ዩኑስ 10፡94)።

የዚህን አንቀጽ መልእክት በአግባቡ ለመረዳት ወገኖቻችን አልታደሉም። በተሳሳተ መንገድ ተረድተው መልክቱን ለነሱ ሊያደርጓትም ቋመጡ። በድፍረትም እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፦ በዚህ አንቀጽ መሠረት ቅዱስ ቁርአን ለሙስሊሞች፡ በእምነታቸው ጥርጥር ከገባባቸው መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ዘንድ ሄደው በመጠየቅ እውነቱን መረዳት እንደሚችሉ መጠቆሙን እንረዳለን!!፡

ውይ ስታሳዝኑ.... እኔ የምለው፦ እንደው ትክክለኛ ትርጉሙንና መልእክቱን ከማየታችን በፊት፡ እናንተ እንዳላችሁት

የ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ›› አንባቢዎችን እንድንጠይቅ ከሆነ ቁርኣኑ የሚገፋፋን፡ ለምን ከናንተ በፊት የነበሩትን አይሁዶቹን አንጠይቅም? ለምን ወደናንተ መምጣት አስፈለገ? ወይስ ቅድሚያ ወደናንተ እንድንመጣ ፈልጋችሁ ነውን?

ደግሞስ እናንተን ነው ቢባል እንኳ ማንን ነው የምንጠይቀው? ካቶሊክን?፣ ኦርቶዶክስን?፣ ፕሮቴስታንትን?፣ ኢየሱስ ብቻ (only jesus) የሚሉትን?፣ የይሆዋ ምስክሮችን (Jihovah witness)?.....? እኮ ማንን? እንጠይቃችሁ ዘንድ ንገሩና! በስም ከፋፍለን የጠራናችሁ፡ በመሐከላችሁ የእምነት ልዩነት መኖሩ የታወቀ ስለሆነ ነው። ደግሞስ በየትኛው ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ›› መሰረት ላይ ሆናችሁ ነው የምትጠየቁት? 66ቱ ወይስ 73ቱ ? ወይንስ 81ዱ ? ደግሞስ የየትኛው ዓመት እትም? ምረጡልና!!

ወደ ሐቁ ስንመጣ ግን የቅዱስ ቁርኣኑ መልእክት በፍጹም ይህን አያረጋግጥም። እነሱ የተረዱትን ሀሳብ የሚገልጽ ነገር በቅርቡም ሆነ በሩቁ በቃሉ ውስጥ አይገኝም። እንዴት? የሚሉ ከሆነና፡ ቀጥተኛ ትርጉሙን መረዳት የሚሹ ከሆነ ማብራሪያውን ከልብ ይከታተሉ። እውነቱንም ለመረዳት አላህ ያግዘን። ልባችንንም ያስፋልን።

1ኛ. ጥቅላዊ ማብራሪያ፦

የአንቀጹ መልእክት፦ የነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነቢይነትና ወደሳቸው የሚወርድላቸው መለኮታዊ ራእይ (ቅዱስ ቁርኣን) ከአላህ ዘንድ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የሌለበት መሆኑን እና፡ በዚህ ጉዳይም ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንደማይጠራጠሩና፡ ‹‹ቢጠራጠሩ እንኳ›› ከሳቸው በፊት የነበሩትን የቀደምት መለኮታዊ መጽሐፍት ሊቃውንቶችን በመጠየቅ እውነተኝነታቸውን ማረጋገጥ እንደሚችሉ ነው። ምክንያቱም፦ የሳቸው ነቢይነትም ሆነ፡ የቅዱስ ቁርኣን አምላካዊ ቃልነት በመጽሐፎቹ አርጂናል ቅጂ ላይ እንደተጠቀሰ ሊቃውንቶቹ ያውቃሉና!!። ስለዚህም ‹‹እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በርግጥ መጥቶልሀል። በመሆኑም ከተጠራጣሪዎች አትሁን!›› በማለት፡ እቅጩን በመንገር ጉዳዩን ይደመድመዋል። አለቀ ደቀቀ። እውነቱ ያለው እዚሁ ነው። እዛ እውነት አለና ሂደህ ጠይቅ! የሚል ቃልም ሆነ ፊደል ማግኘት አይቻልም። ሊቃውንቶቹን ጠይቅ! የተባለው፡ እነሱን

እንኳ ብትጠይቃቸው አንተን በሚገባ ያውቁሀል። ነቢይነትህንም ሆነ የሚወርድልህ ራእይ ከአላህ ዘንድ መሆኑን ይመሰክራሉ ነው፡ ፡ ይኸው የጌታ አላህ ምስክርነት፡-

"እነዚያ መጽሐፍን የሰጠናቸው ወንዶች ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል። ከነሱም የተለዩ ክፍሎች እነርሱ የሚያወቁ ሲኾኑ እውነቱን በእርግጥ ይደብቃሉ።" (ሱረቱል በቀራህ 2፡146)።

"እነዚያ መጽሐፍን የሰጠናቸው ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል። እነዚያ ከእነርሱ ውስጥ ነፍሶቻቸውን ያከሰሩት እነርሱ አያምኑም።" (ሱረቱል አንዓም 6፡20)።

ይህ ነው እውነታው! ከዛ ውጪማ እውነቱን ለማወቅ ከፈለግህ፡ እነሱን ሄደህ ጠይቅ ለማለት ከሆነ፡ በዚያው አንቀጽ ውስጥ ‹‹እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሃል›› በማለት አስረግጦ መናገር ለምን አስፈለገው? የቃሉ መልእክት ግን፡- እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ብትጠይቃቸው የአንተን ነቢይነትም ሆነ የሚወርድልህን ራእይ (ቅዱስ ቁርኣን) ከአላህ ዘንድ የመጣ መሆኑን ይናገራሉ ነው። ደግሞም ሊቃውንቶቹ ለሐቅ ያደሩ፡ እውነቱ ሲነገራቸው አምነው የተቀበሉ፡ እንደ ዐብዱላህ ኢብኑ ሰላም (ረዲየላሁ ዐንሁ)፣ እንደ ዐብዱላህ ኢብኑ-ዐምር ኢብኑል-ዓስ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) አይነቶቹን እንጂ፡ ለምድራዊ ጥቅማቸው ሲሉ እውነቱን በሀሰት የለወጡ፡ የመጽሐፉን ትክክለኛ መልእክት የደበቁና፡ በመጽሐፉ ላይ እጃቸውን ያስገቡትን አይደለም። እነዚህን ክፍሎችማ ሄዶ መጠየቅ ለጥመት እንጂ ለምሪት እንደማይጠቅም በሌላ አንቀጽ እንዲህ ይገልጸዋል፡-

"ከመጽሐፉ ባለቤቶች የሆኑ ጭፍሮች ነፍሶቻቸዉን እንጂ የማያሳስቱ ሲሆኑ ሊያሳስቱዋችሁ ተመኙ ግን አያውቁም" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡69)።

2ኛ. ዝርዝር ማብራሪያ፡-

መልእክቱ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆንና፡ በአንቀጹ ላይም ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት፡ ወገኖቻችን ካሰቡትና ከቋመጡለት ነገር ጋር ምንም ግኙኝነት እንደሌለው ለማወቅ ይረዳ ዘንድ፡ በኃይለ ቃል እየከፈልን እንመልከተው።

1ኛ. ‹‹ወደ አንተም ካወረድነው›› በሚለው ኃይለ ቃል ውስጥ፡ ከጌታ አላህ ዘንድ ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የወረደ መለኮታዊ ራእይ መኖሩን በቀላሉ እንረዳለን። ይህም ራእይ ‹‹ቅዱስ ቁርኣን›› ነው።

"እኛ ቁርአንን ባንተ ላይ ማውረድን እኛው አወረድነው።" (ሱረቱ-ደህር (ኢንሳን) 76፡23)። ከዛም ይቀጥልና፡-

2ኛ. ‹‹በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን›› በማለት ደግሞ አንድን ነገር እንዲያደርጉ ማረጋገጫ ይሰጣል። ማረጋገጫው ምንድነው? የሚለውን ኋላ ላይ እንመለስበታለን። ‹‹በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን›› ማለት ግን፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) መጠራጠራቸውን የሚያመላክት አይደለም። ምክንያቱም ቃሉ የሚናገረው ‹‹በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን›› እያለ እንጂ፡ ‹‹በመጠራጠር ውስጥ ነህና›› እያለ አይደለም።

‹ብትሆን› (if) የሚለው ቃል Conditional sentence ነው። ሊከሰትም ላይከሰትም የሚችል፡ በሁኔታዎች የሚወሰን አያያዥ (conjunction) የሆነ ቃል ነው።

አጠቃላይ ሀሳቡ፡- ወደ ‹‹አንተ ካወረድነው መጽሐፍ (መለኮታዊ ራእይ) ብትጠራጠር እንኳ›› ለማለት ነው። ታዲያ ምን ይሁን? ከተባለም፡-

3ኛ. ‹‹እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ›› በማለት ማረጋገጫ ይሰጠናል። የመጽሐፉን አንባቢዎች ጠይቅ የሚለው ሀሳብ የሚያያዘው፡ ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን ከሚለው የቁርኣኑ ቃል ጋር እንጂ፡ እውነትን

ከፈለግህ ከሚል የፈጠራ ወሬ ጋር አይደለም፡፡ ታዲያ ከየት አምጥታችሁ ነው፡ እውነቱን ከፈለጋችሁ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነቡትን ጠይቁ! ይላል ቁርኣናችሁ የምትሉን?

ከላይ በጥቅላዊ ማብራሪያው ላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት፡ የመጽሐፍቱን ሊቃውንቶች ብትጠይቃቸው እንኳ፡ በመጽሐፉ ውስጥ በኦርጂናል ይዘቱ የአንተ ነቢይነት እንደተነገረ ያውቃሉ፡ እነሱም ይመሰክራሉ እያለ ነው፡፡

ወገኖቻችን! ‹‹ከአንተ በፊት›› የሚለው ኃይለ ቃል የናንተን ምኞት ከንቱ አያስቀረውምን? ቅዱስ ቁርኣን እየተናገረ ያለው፡- ‹‹ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ›› በማለት እንጂ፡ ከአንተ በኋላ የሚመጡትን ጠይቅ አላለም፡፡ አሁንስ ገባችሁ?

4ኛ. ‹‹እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሃል ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን›› በማለት አንቀጹ በሚያምር አገላለጽ ተደመደመ፡፡ አላህ አከበር! ወደሳቸው ይወርድ የነበረው መለኮታዊ ራእይ፡- እውነቱ እኔው ራሴ ነኝ! ካለ፡ ሌላ እውነት ፍለጋ እንዴት ይኬዳል? ስለዚህ እውነቱ እዚሁ ቁርኣን ውስጥ ነው ያለው፡፡ ‹‹ብትጠራጠር እንኳ እነሱን ጠይቅ›› ማለቱ፡ እውነትን ፍለጋ ወደነሱ ሂድ! ከማለት ጋር ምንም ግኑኝነት የለውም፡፡ ግኑኝነቱ፡ እነሱም ቢሆኑ ብትጠይቃቸው የአንተን ነቢይነት በሚገባ ስለሚያውቁ ይነግሩሀል ነው፡፡

5ኛ. የአላህ ነቢይም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ይህ አንቀጽ በወረደላቸው ግዜ፡ የመጽሐፉን ሰዎች ሄደው አልጠየቁም፡፡ ባይሆን በተቃራኒው እንዲህ ነበር ያሉት፡-

‹‹ላ አሹክኩ ወላ አስአል›› ‹አልጠራጠርም አልጠይቅምም›፡፡ (ተፍሲሩ-ጠበሪይ፡ ጀሚዑል በያን ሱረቱ ዩኑስ 94 ቁጥር 17893-17894)፡፡

እኛም የነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ተከታይ የሆንን ሙስሊሞች፡ እሳቸውን በመከተል አንጠይቅምም ደግሞም አንጠራጠርምም፡፡

6ኛ. ኢማሙል ቡኻሪይ በዘገቡት ሶሒሕ ሐዲሥ ላይ ደግሞ፡ እንዲህ የሚል ግሳጼ ተቀምጧል፡-

اللهُ صَلَّى نَبِيِّهِ عَلَى أُنْزِلَ الَّذِي وَكِتَابُكُمُ الكِتَابِ، أَهْلَ تَسْأَلُونَ كَيْفَ المُسْلِمِينَ، مَعْشَرَ يَا " :قَالَ عَنْهُمَا، اللَّهُ رَضِيَ عَبَّاسٍ بْنِ اللَّهِ عَبْدِ عَنْ مِنْ هُوَ :فَقَالُوا الكِتَابَ، بِأَيْدِيهِمُ وَغَيَّرُوا اللَّهُ كَتَبَ مَا بَدَّلُوا الكِتَابِ أَهْلَ أَنَّ اللَّهُ حَدَّثَكُمُ وَقَدْ يُسْبَ، لَمْ تَقْرَءُونَهُ بِاللَّهِ، الأَخْبَارِ أَحْدَثُ وَسَلَّمَ عَلَيْهِ أُنْزِلَ الَّذِي عَنِ يَسْأَلُكُمْ قَطُّ رَجُلًا مِنْهُمْ رَأَيْنَا مَا وَاللَّهِ وَلاَ مُسَاءَلَتِهِمْ، عَنْ العِلْمِ مِنَ جَاءَكُمْ مَا يَنْهَاكُمْ أَفَلاَ قَلِيلًا، ثَمَنًا بِهِ لِيَشْتَرُوا اللَّهِ عِنْدِ عَلَيْكُمْ " رواه البخاري 2685.7522.7523

ዐብዱላህ ኢብኑ-ዐባስ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) እንዲህ ይላል፡- "እናንተ ሙስሊሞች ሆይ! በነቢዩ ላይ የተወረደላችሁ መጽሐፍ (ቁርኣን) ከአላህ ዘንድ የመጣ አዲስ (ያላረጀ) ሆኖ ሳለ፡ እናንተም ያልተበረዘና የሰው እጅ ያልገባበት ሆኖ እያነበባችሁት፡ የመጽሐፉን ሰዎች (አይሁዶችና ክርስቲያኖች) እንዴት ትጠይቃላችሁ? አላህም (በቁርኣኑ) የመጽሐፉ ሰዎች መጽሐፉን በእጃቸው እንደበረዙትና እንደቀየሩት፣ ከዛም የተበረዘውን ጥቂትን ምድራዊ ዋጋ ለመሸመት፡ ይህ ከአላህ ዘንድ የመጣ ነው እንዳሉ ነግሯቹኋል፡፡ እንግዲያውስ ወደናንተ የመጣላችሁ ዕውቀት እነሱን ከመጠየቅ አይከለክላችሁምን? በአላህ ይሁንባኝ! ከነሱ ውስጥ አንድም ሰው ወደናንተ ስለወረደው ሲጠይቁአችሁ በፍጹም አላየንም (ታዲያ እናንተ እነሱን እንዴት ትጠይቃላችሁ?)" (ቡኻሪይ 2685፣ 7522፣ 7523)፡፡

አዎ! ልንጠይቃቸውም አይገባም! ትክክለኛው ሀሳብ ይህ ነው ወላሁ አዕለም፡፡

"ጌታህ በመካከላቸው በትክክል ፍርዱ ይፈርዳል፤ እርሱም አሸናፊው ዐዋቂው ነው። በአላህም ላይ ተጠጋ፤ አንተ ግልጽ በሆነው እውነት ላይ ነህና።" (ሱረቱ-ነምል 27፡79)፡፡

የውሻው ተረት ተረት

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2)፡፡ የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡

ክቡራን ወንድሞቼና እህቶቼ! አሰላሙ ዐለይኩም ወራሕመቱላሂ ወበረካቱሁ፡፡

ከአንድ እህቴ በኩል የቀረበልኝ ሀሳብ ስለሆነ እንጂ መልስ ለመስጠት ብዙም አስቤበት አላውቅም ነበር፡፡ ይሄን ያህልም ሰዎች ለጉዳዩ ቦታ ይሰጡታል ብዬ አላሰብኩም ነበር፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ነው፡- ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) በወቅቱ የነበሩ ሰዎችን እሳቸው ነቢይ እንደሆኑ ለማሳመን፡ ከአፈር ውስጥ ወተት ፈለቀልኝ የሚልን ሀሳብ በልባቸው ይዘው ወተትን በአፈር ውስጥ ይቀብሩታል፡፡ ከዛም ወደ ህዝባቸው ዘንድ በመሄድ ‹‹እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ትክክለኛ ነቢይ ለመሆኔ ማስረጃ ከፈለጋችሁ፡ ይሽው ከአፈር ውስጥ በተአምር ወተት ሳፈልቅ ኑ ተመልከቱ! በማለት ሰዎቹን ወደ ስፍራው ይዘው ይጓዛሉ፡፡ ውሻ ደግሞ ከሩቅ የማሽተት ተሰጥኦ አለውና በስፍራው ሲደርሱ ውሻው አፈሩን በእግሮቹ ጣት በመታገዝ እየቆፈረው ወተቱን ቀድሞ በማሳየት አጋለጣቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ነው ውሻ በኢስላም የተጠላው የሚል ነው፡፡

ይህንን የወገኖቻችንን ከስ ድሮ ነበር እንደ ተረት የምሰማው፡፡ ዛሬም ያ ያልበሰለ ጭንቅላት ድጋሚ ያነሳዋል ብዬ አላሰብኩም ነበር፡ ፡ መብሰሉ ላይቀር ነገር የሰው ከሰል ይጨርሳል ይባላልና ለማንኛውም ጥቂት ነገር እኔም ላክልበት፡-

1ኛ/ እውነት አፈሩ ውስጥ ወተት ከተቀበረ በምን አይነት መልኩ ነው ተመልሶ ሊፈልቅ የሚችለው ? አፈሩ አይመጠውም እንዴ? ወይስ በወቅቱ የነበረው የምድር አፈር ፈሳሽ ነገርን መምጠጥ አይችልም ነበር? እንዴት ሆኖ ሊፈልቅ ይችላል?

2ኛ/ አይ በእቃ (ጀሪካንና መሰሎቹ) ላይ ተቀምጦ ነው ከተባለም፡ ታዲያ ምኑ ላይ ነው ተአምሩ ? በጀሪካንም ሆነ በማንኛውም ፈሳሽ መያዢያ እቃ ውስጥ ወተት አኑሮ መቅበር ማንም ሰው የሚችለው ተግባር አይደለምን? ወይስ ከጀሪካኑ ስር ወደ ውጭ መፍለቅ ጀመረ ሊባል ነው?

3ኛ/ ደግሞስ አንድ ነቢይ ነኝ የሚል ሰው ከአፈር ወተት አፈልቃለሁ ብሎ ለህዝቦቹ ከተናገረ፡ እዛው እነሱ ያሉበት ስፍራ ላይ ተአምሩን ያሳያል እንጂ፡ ኑ ብሎ ወደሆነ ስፍራ እንዴት ሊወስዳቸው ይችላል ? ይህ ለነሱ የሚጠቁመው ነገር አይኖርምን? የነቢይ ተአምር ከአምላኩ ጋር እንጂ ከተወሰነ የመሬት ስፍራ ጋር አይደለም የሚያያዘው፡፡ ህዝቡስ እንዴት ተንትቶ ሊሄድ ቻለ? ለምንስ ያ ቦታ ብቻ ተመረጠ?

4ኛ/ በጣም የሚገርመው ደግሞ ውሻው ነው፡፡ እንደተባለው በስፍራው ላይ ውሻው ቀድሞ ከተገኘና ይህንን ነገር በማጋለጥ የበኩሉን ከተወጣ፡ ታዲያ በወቅቱ የነበሩ ሰዎች እንዴት በሳቸው ነቢይነት ሊያምኑ ቻሉ ? ወይስ ውሻውን ከማየት ተጋርደው ነበር? እውነት ወገኖቻችን አስተሳሰባቸው የጤና ነውን? ስብሓነላህ፡፡ በጥላቻ የሰከረ ልብ ምን ያህል የአእምሮን አስተሳሰብ እንደሚገድል ተመልከቱ እንግዲህ፡፡ ለካ ጭንቅላት ለምን ይጠቅማል? ሲባል፡ ኮፊያ ለማስቀመጥ በማለት መልስ የሰጠው ልጄ ‹‹ሀይደር›› እውነቱን ነበር!! ሰው በአእምሮው ካላሰበበትና ነገሮችን ካላመዛዘነበት ምኑን ከእንሰሳ ተለየ? እንግዲውስ ውሻ በኢስላም ለምን ተጠላ? ወደሚለው ጥያቄ በቀጥታ እንግባ፡-

ሀ/ ቅድሚያ ከላይ የቀረበው የካፊሮች ክስ፡ ፍፁም ከእውነታ የራቀ፡ ለህጻናት እንኳ እንደ ተረት ሊነገር የማይገባው ርካሽ አስተሳሰብ ነው፡፡ ከምን እየቀጣጠፉ እንደሚያቀርቡላቸው ሳስበው ይገርመኛል፡፡ ከዛ በላይ ደግሞ የነሱ አሜን ብሎ መቀበልና ጭራሽ እኛው ዘንድ ቀርበው ይህን ሀሳብ ለውይይት ማቅረባቸው ምን ያህል (brainwash) እንደተደረጉ አመላካች ነው፡፡ አላህ በእዝነቱ ይድረስላቸው፡፡

ለ/ ውሻ በኢስላም የተጠላ ነው የሚል አንድም ሃይማኖታዊ ማስረጃ፡ ከቅዱስ ቁርአንም ሆነ ከሐዲሥ ማቅረብ አይችሉም፡፡ ይህም ተራ አሉባልታ ነው፡፡ ኢስላም ውሻን መጥላትን ሳይሆን እያስተማረ ያለው፡ ውሻን ማሳደግን በምን አይነት መልኩ መሆን እንዳለበት በመግለጽና ገደብ በማበጀት ብቻ ነው፡፡ የተፈቀደውም፡-

1/ ለአደን ስራ፡-

ውሻን በማሰልጠን በኢስላም ለመብልነት የተፈቀዱ የእንሰሳት አይነቶችን አድኖ ቢይዝልን እንሰሳው ሐላል ይሆናል፡፡ ስለዚህ ውሻን ለአደን ተግባር መያዝ ይቻላል፡፡ ማስረጃውም ቀጥሎ የሚቀርበው የአላህ ቃልና የመልክተኛው ሐዲሥ ነው፡-

" وَاذْكُرُوا عَلَيْكُمْ أَمْسَكْنَ مِمَّا فَكُلُوا اللَّهُ عَلَّمَكُمُ مِمَّا تُعَلِّمُونَهُنَّ مُكَلِّبِينَ الْجَوَارِحِ مِنَ عَلَّمْتُمْ وَمَا الطَّيِّبَاتُ لَكُمُ أُحِلَّ قُلْ لَهُمْ أُحِلَّ مَاذَا يَسْأَلُونَكَ " الْحِسَابِ سَرِيعُ اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ وَاتَّقُوا عَلَيْهِ اللَّهِ اسْمَ المائدة سورة 4

"ለነርሱ ምን እንደተፈቀደላቸው ይጠይቁሃል፤ በላቸው፡- ለናንተ መልካሞች ሁሉና እነዛ ከአዳኞች አሰልጣኞች ሆናችሁ ያስተማራችኋቸው (ያደኑት) ተፈቀደላችሁ፤ አላህ ካስተማራችሁ ዕውቀት ታስተምሩዋቸዋላችሁ፤ ለናንተም ከያዙላችሁ ነገር ብሉ በርሱም ላይ የአላህን ስም አውሱ አላህንም ፍሩ፤ አላህ ምርመራው ፈጣን ነውና።" (ሱረቱል ማኢዳህ 5፡4)፡፡

በዚህ ትርጉም ውስጥ ‹‹ከአዳኞች›› ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱና ዋነኛው ውሻ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ውሻን ለአደን ተግባር መጠቀም ይቻላል፡፡

تَأْكُلْ، فَلاَ أَكَلَ وَإِنْ فَكُلْ، وَقَتَلَ فَأَمْسَكَ وَسَمَّيْتَ كَلْبَكَ أَرْسَلْتَ إِذَا :قَالَ وَسَلَّمَ عَلَيْهِ اللهُ صَلَّى النَّبِيِّ عَنِ عَنْهُ، اللَّهُ رَضِيَ حَاتِمٍ بْنِ عَدِيِّ عَنْ قَتَلَ أَيُّهَا تَدْرِي لاَ فَإِنَّكَ تَأْكُلْ، فَلاَ وَقَتَلْنَ فَأَمْسَكْنَ عَلَيْهَا، اللَّهِ اسْمُ يُذْكَرِ لَمْ كِلاَبًا، خَالَطَ وَإِذَا نَفْسِهِ، عَلَى أَمْسَكَ فَإِنَّمَا... البخاري رواه 5081. ومسلم 5484

ዐዲይ ኢብኑ አቢ ሓቲም (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደነገረን የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "ቢስሚላህ በማለት ለአደን (ያሰለጠንከውን) ውሻህን ብትልከና አድኖ ቢገድለው አንተም ከአደኑ ብላ፡፡ ውሻው ያደነውን መብላት ከጀመረ ግን አትብላ፡፡ እሱ ለራሱ ነው ያደነውና፡፡ ሌሎች የአላህ ስም ሳይወሳባቸው የተላኩ ውሾችን ከተቀላቀለና እነሱ አድነው የገደሉትን ካገኘህ አትብላ፡፡ የትኛው ውሻ እንደገደለው አታውቅምና…" (ቡኻሪይ 5484፣ 5081)፡፡

በቁርአኑም ሆነ በሐዲሡ መሰረት ለአደን የምንጠቀመው ውሻ ላይ ሁለት ነገር ማሟላት ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ ማሰልጠንና ቢስሚላህ ብሎ መላክ፡፡

2/ ለጥበቃ፡-

ሌላው ውሻን ማሳደግ የሚቻልበት መንገድ ከጥበቃ ጋር በተገናኘ ነው፡፡ ጥበቃ ሲባል ደግሞ፡-

ሀ/ የጓሮ አዝመራን

ለ/ ለቤት እንሰሳዎች

ለ/ መኖሪያ ቤትን፡-

كُلَّ أَجْرِهِ مِنْ انْتُقِصَ زَرْعٍ أَوْ صَيْدٍ أَوْ مَاشِيَةٍ كَلْبَ إِلاَّ كَلْباً اتَّخَذَ مَنِ :قال وسلم عليه الله صلى نَّبِيَّ ال أنَّ عنه الله رضي هريرة أبي عن قِيرَاطٌ يَوْمٍ. رواه مسلم 4111.

አቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደነገረን የአላህ ነቢይ (ዐለይሂ-ሶላቱ ወስ-ሰላም) እንዲህ አሉ፦ "ለበግ/ፍየል እረኝነት ወይንም ለአደን ወይንም ለአዝመራ ጥበቃ እንጂ፡ (ከዛ ውጪ ላላ ነገር) ውሻን የያዘ ሰው በየቀኑ ከአጅሩ ላይ ይቀነስበታል" (ሙስሊም 4111)።

ለአደንና ለእረኝነት ውሻን ማሳደጉ የተፈቀደ ከሆነ፡ ለቤት ጥበቃ ደግሞ ከዛም በበለጠ መልኩ የሚፈቀድ መሆኑን ቂያስ በማድረግ ኢማሙ ነወዊይ ረሒመሁላህ (ሸርሑ ሶሒሕ ሙስሊም 10/340) ላይ ገልጸዋል። እንዲሁም ሸይኽ ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አል-ዑሠይሚን (ረሒመሁላህ) ይህን ሀሳብ ደግፈዋል (አል-ኢስላሙ ሱአሉን ወጀዋብ ቁ. 69777)።

ከዚህ ውጪ ዝምብሎ ውሻን ማሳደግ አልተፈቀደም። ምእራባዊያን የኛ ምሣሌ አይደሉም፤ ሊሆኑም አይችሉም። ከአላህ መልከተኛ ፍኖትና መንገድ ያፈነገጡ ሰዎች በመሆናቸው ፍጻሜያቸው ከውሻቸው የባሰ ሆኗል።ሲጀመር ውሻን እንደ ኖርማል በቤት ውስጥ ማሳደግ ጀመሩ።ቀጥሎም የትም ስፍራ የጉዞ ጓደኛቸው አደረጉት።

ቀጠለና ደግሞ በቤት ውስጥ አብሮ አዳሪ በመሆን አብሯቸው መኖር ጀመረ። የሚቾቹንም ንብረት በኑዛዜ የውርስ ተካፋያቸው ሆነ፡ ፡ በመጨረሻም የትዳር አጋር ሆኖ አንሶላ መጋፈፍ ጀመረ። ያለምንም እፍረት ሰርግ ሰርገውና ድግስ አዘጋጅተው ውሻን የትዳር አጋሬ ነው ብሎ ማግባት መሰልጠን ወይስ መሰይጠን? እነዚህ ናቸው ለኛ አርአያ የሚሆኑት? አልሐምዱ ሊላህ ዓላ ኒዕመቲል ኢስላም።

17.ተመልሷል

የጠበቀ ሚስማርን በጣት መንቀል አይቻልም!!

ምስጋና የዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ የተገባ ነው፡፡ የአላህ ውዳሴና ሰላም፡ የሰላም አለቃና መምህር ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ ይሁን፡፡ ድልና የበላይነት ሐቅን ለማንገስና ሀሰትን ለማርከስ፡ በደልን አጥፍቶ ፍትህን ለማስፈን ዕውቀታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ህይወታቸውን መስዋእት በማድረግ ለሚታገሉት ይሁን፡፡

ከቡራን ወንድሞቼና እህቶቼ! ዛሬም እንደተለመደው የማስቃኛችሁ ነገር ቢኖር፡ ኢስላም ለሃይማኖትህ ስትል መዋሸትን ይፈቅዳል! የሚለውን የካፊሮችን ከንቱ ክስ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ምንም የራሳቸው ዕውቀትና ተሞኩሮ የሌላቸው፡ እንደ ገደል-ማሚቱ የተነገራቸውን ብቻ የሚያስተጋቡ፡ የጉዳዩን እውነተኝነት ከማጣራት ይልቅ በጥላቻ ስሜት ወሬውን ማሰራጨት የሚወዱ ናቸው፡፡ እስኪ ኢስላም ለሃይማኖትህ ስትል ዋሽ! ብሎ የፈቀደበትን ማስረጃ አሳዩን ስንላቸው ከሼህ ጎግል ያገኙትን ይህን ሐዲሥ አቅርበዋል፡ ፡ የሚገርመው ቡኻሪና ሙስሊም እያሉ ቁጥር መለጠፍ እንጂ ሐዲሡን አስቀምጡት ሲባሉ ማምጣት አይችሉም፡፡ ቁጥሩንስ ቢሆን የተነገራቸው እንጂ መች ያገኙት ሆነና፡፡ ለማንኛውም ሐዲሡን ላስቀምጥላችሁና ለሃይማኖትህ ስትል ዋሽ! የሚለውን ከንቱ የጠላት ክስን በአላህ ፈቃድ መና እናስቀረው ኢንሻአላህ-

ኡሙ ኩልሱም ቢንት-ዑቅባህ (ረዲየላሁ ዐንሃ) የአላህ መልከተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ሲሉ ሰማች፡- "በሰዎች መሀከል ላማስታረቅና ለማስማማት ብሎ መልካም ንግግርን የሚያስተላልፍና ጥሩውን የሚናገር ሰው ውሸታም አይባልም" ኢብኑ ሺሀብም፡- ‹‹ሰዎች ከሚናገሩት ውስጥ በጦርነት ጊዜ፣ በሰዎች መሐል እርቅ ለመፍጠር እና ባል ሚስቱን ለማዝናናት፡ እንዲሁም ሚስት ባሏን ለማዝናናት ሲባል እንጂ ውሸት ሲፈቀድ አልሰማሁ›› አለ፡፡ (ሙስሊም 6799፣ አሕመድ 28032)፡፡

የሐዲሡን መልእክት ወደ ውስጥ ገብተን እንደተለመደው መጠነኛ ማብራሪያ ከመስጠታችን በፊት ጥቂት ስለ ውሸት ንግግር ኢስላም የሚያስተምረውን እንመልከት፡-

ውሸት በኢስላም ውስጥ ምንም አይነት ስፍራ የሌለው ውዳቂና ርካሽ ተግባር መሆኑን ለመረዳት ቀጥሎ ያሉትን መንደርደሪያ ነጥቦች ለናሙና ያህል እንመልከታቸው፡-

1ኛ. ከጌታችን አላህ መለኮታዊ ስሞች ውስጥ አንዱ "አል-ሐቅ" የሚለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ትርጉሙ፡- ፍጹም እውነት የሚል ነው፡ ፡ አላህ መኖሩ የተረጋገጠ በፍጹም እውነትና በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ‹አል-ሐቅ› ተብሎ ይጠራል (አል-ሐጅ 22፡6)፡፡ ደግሞም ንግግሩ እውነት ብቻ የሆነ ጌታ ስለሆነ አሁንም ‹አል-ሐቅ› ይባላል (አን-ኒሳእ 4፡87.122)፡፡ በተጨማሪም ለባሪያዎቹም እውነተኛና ታማኝ ጌታ ስለሆነ ‹አል-ሐቅ› ይሰኛል (ዩኑስ 10፡32)፡፡ ለባሮቹ የገባላቸውን ቃል-ኪዳን ስለማያፈርስ ቃሉንም ስለሚጠብቅ (ኢብራሂም 14፡47) "አል-ሐቅ" የሚባል አምላክ ነው፡፡ ታዲያ ባሕሪውና ማንነቱ በዚህ መልኩ የተገለጸው ይህ እውነተኛ አምላክ እንዴት ውሸትን ይፈቅዳል ተብሎ ይታሰባል? (ሱበሐነሁ ወተዓላ ዐምማ የሲፉሁ ዘሊሙን ዑሉወን ከቢራ)፡፡

"…አላህም እውነቱን ይናገራል፤ እርሱም ትክክለኛዉን መንገድ ይመራል" (ሱረቱል አሕዛብ 33፡4)፡፡

2ኛ. ጌታችን አላህ በቅዱስ ቁርኣኑ ያዘዘን በንግግራችንም ሆነ በተግባራችን ከእውነተኞች ጋር እንድንሆን ነው፡-

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤ ከዉነተኞቹም ጋር ሁኑ።" (ሱረቱ-ተውባህ 9:119)፡፡

"ሰው ሁሉ በእርግጥ በከሳራ ውስጥ ነው። እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሠሩት፣ በውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገሥም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ።" (ሱረቱል ዐስር 103:2-3)፡፡

3ኛ. ውሸተኞች በተለይም በአላህና በአንቀጾቹ ላይ ሀሰትን የሚቀጥፉ አላህ ዘንድ እጅግ የተጠሉ መሆናቸው በቅዱስ ቁርአን ውስጥ በተደጋጋሚ ተገልጾአል፡፡ ለአብነት ያህል፡-

"በአላህም ላይ ውሸትን ከቀጣጠፈ ወይም በአንቀጾቹ ካስተባበለ ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? እነሆ በደለኞች አይድኑም" (ሱረቱል አንዓም 6:24)፡፡

"በአላህም ላይ እብለትን ከቀጣጠፈ ወይም ወደርሱ ምንም ያልተወረደለት ሲኾን «ወደኔ ተወረደልኝ» ካለና፡- «አላህም ያወረደውን ብጤ በእርግጥ አወርዳለሁ» ካለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው?..." (ሱረቱል አንዓም 6:93)፡፡

"...ሰዎችንም ያለ ዕውቀት ሊያጠም በአላህ ላይ ውሸትንም ከቀጠፈ ሰው ይበልጥ በደለኛ ማን ነው አላህ በደለኞችን ሕዝቦች (ቅኑን መንገድ) አይመራም፡፡»" (ሱረቱል አንዓም 6:144)፡፡

"በአላህ ላይም ውሸትን ከቀጣጠፈ ሰው ወይም እውነቱ በመጣለት ጊዜ ከአስዋሸ ይበልጥ በዳይ ማነው? በገሀነም ውስጥ ለከሐዲዎች መኖሪያ የለምን?" (ሱረቱል ዐንከቡት 29:68)፡፡

እነዚህ አናቅጾች በአንድ ድምጽ የሚያስተጋቡት በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጥፉ ሰዎች አላህ ዘንድ ምን ያህል እንደተጠሉና በደላቸውም እጅግ የከፋ መሆኑን ነው፡፡ ታዲያ ለባሪያዎቹ ውሸትን ይፈቅዳል ብለን ማሰብ እንችላለን?

4ኛ. በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጥፉ ሰዎች ፈጽሞ እንደማይድኑና ለጥፋት የተወሰኑ ሰዎች መሆናቸውን ጌታችን በቃሉ ይነግረናል፡-

"«እነዚያ በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጣጥፉ ፈጽሞ #አይድኑም፤» በላቸው፡፡" (ሱረቱ ዩኑስ 10:69)፡፡

"በአላህም ላይ ውሸትን ልትቀጣጥፉ፣ ምላሶቻችሁ በሚመጥኑት ውሸት፥ ይህ የተፈቀደ ነው፤ ይህም እርም ነው፣ አትበሉ፤ እነዚያ በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጣጥፉ፣ #አይድኑም።" (ሱረቱ-ነሕል 16:116)፡፡

"በትንሣኤ ቀንም፣ እነዚያን በአላህ ላይ የዋሹትን፣ ፊቶቻቸው የጠቆሩ ሆነው ታያቸዋለህ፤ በገሀነም ውስጥ ለትዕቢተኞች መኖሪያ የለምን?" (ሱረቱ-ዙመር 39:60)፡፡

5ኛ. እንዲሁም በነቢያችን ላይ ያላሉትን ብለዋል በማለት እያወቀ የሚዋሸባቸው ሰው ነጌ የሚጠበቀውን አስፈሪ ቅጣት እንዲህ ሲሉ መልከተኛው ገልጸውታል፡-

"በኔ ላይ መዋሸት በአንዳቹ ላይ እንደመዋሸት አይደለም፡፡ በኔ ላይ የዋሸ ሰው መቀመጫውን ከእሳት ያድርግ" (ሙስሊም)፡፡

6ኛ. ውሸት እጅግ የተጠላ መሆኑን ለመግለጽ ሌላው መንገድ ውሸትን ራቁት ብሎ ቅዱስ ቁርኣን ማስጠንቀቁ ነው፡፡ እንደውም ከጣኦት አምልኮ ጋር አቆራኝቶ ነው አላህ ያስጠነቀቀን፡-

"...ከጣዖታት ርከሰት ተጠንቀቁ፤ የሀሰትንም ቃል ራቁ።" (ሱረቱል ሐጅ 22:30)፡፡

በሐዲሥ ላይም የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል፡- "እጅግ በጣም የከበደ ኃጢአትን ልንገራችሁን? ሲሉ፡ ሶሐቦችም፡- ‹‹እንዴታ ይንገሩን እንጂ!›› አሉ፡፡ እሳቸውም፡- ‹‹በአላህ ማጋራት፣ ወላጆችን መጨቆን›› አሉ፡፡ ተደግፈው ነበርና ቁጭ ብለው፡- ‹‹አዋጅ! የሐሰት ቃል፣ የውሸት ምስክርነትም፣ አዋጅ! የሐሰት ቃል፣ የውሸት ምስክርነትም›› አሉ፡፡" (ቡኻሪይ)፡፡

ዐብዱላህ ኢብኑ-መስዑድ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደነገረን የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል፡- "...ውሸትን ተጠንቀቁ፡ ውሸት ወደ ጥመት ይመራል፡ ጥመት ደግሞ ወደ እሳት ይወስዳል" (ቡኻሪና ሙስሊም)፡፡

7ኛ. ሌላው ኢስላም የውሸትን አስከፊነት የገለጸበት መንገድ፡- ሀሰትን መናገር የሙናፊቅ ባሕሪ ነው ብሎ ማስተማሩ ነው፡-

አቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደነገረን የአላህ መልክተኛ(ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል፡- "የሙናፊቅ ምልክት ሶስት ናቸው፡- ሲናገር ይዋሻል፣ ቀጠሮ ያፈርሳል፣ ሲታመን ይከዳል" (ቡኻሪና ሙስሊም)፡፡

8ኛ. ነጌ የቂያም ቀንም ጠቃሚነቱ በእምነታቸውና በስራቸው እውነተኛ ለሆኑ ለአላህ ባሮች ብቻ እንደሆነ ቅዱስ ቁርአን ያስተምራል :-

"አላህ ይላል :- ይህ እውነተኞችን እውነታቸው የሚጠቅምበት ቀን ነው፤ ለነርሱ በሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው በውስጣቸው ሁልጊዜ ዘውታሪዎች ሲሆኑ የሚኖሩባቸው ገነቶች አሉዋቸው፤ አላህ ከነሱ ወደደ፤ እነርሱም ከርሱ ወደዱ፤ ይህ ታላቅ ዕድል ነው።" (ሱረቱል ማኢዳህ 5:119)፡፡

"አላህም እውነተኞችን በውነተኛነታቸው ሊመነዳ፣ መናፍቃንንም ቢሻ ሊቀጣ፣ ወይም (ቢመለሱ) በነሱ ላይ ጸጸታቸውን ሊቀበል፣ (ይህን አደረገ)፤ አላህ መሐሪ አዛኝ ነውና።" (ሱረቱል አሕዛብ 33:24)፡፡

9ኛ. እጅግ በጣም የሚገርመው ደግሞ ኢስላም ውሸትን ለቀልድና ሰውን ለማሳቅ ብሎ እንኳ አለመፍቀዱ ነው፡-

የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል፡- "ወየውለት! ለዚያ ሲናገር ሰዎችን ለማሳቅ ብሎ ለሚዋሽ ሰው፡ ወየውለት! ወየውለት!" (አቡ-ዳዉድ 4992፣ አሕመድ 20055)፡፡

አቢ ኡማማህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደነገረን የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል፡- "በጀነት ውስጥ ላለው መሐከለኛ ቤት ውሸትን ለቀልድም እንኳ ቢሆን ለተወ ሰው ተሚጋች ነኝ" (ሶሒሑ ተርጊብ-ወተርሂብ 6/3)፡፡

10ኛ. የታላቁ ሮም ንጉስ የነበረው ሒረቅል አባ ሱፍያንን (ረዲየላሁ ዐንሁ) ነቢያችሁ በምን ያዛችኋል? ብሎ በጠየቀው ጊዜ እንዲህ ብሎ መለሰለት፡- "አላህን ብቻውን ተገዙት፡ በርሱም ምንንም አታጋሩ፣ አባቶቻችሁ የሚሉትን ነገር ተዉ፣ ሶላት እንድንሰግድ፣ እውነትን እንድንናገር፣ ዝምድናን እንድንቀጥል ያዘናል" (ቡኻሪይ)፡፡ ታዲያ ከዚህ ሁሉ በኋላ ኢስላም ለሃይማኖትህ ስትል ውሸትን መናገር ይፈቅዳል ብሎ ወሬ ማናፈስ የጤና ነውን?

ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ እንግዲያውስ ከላይ መግቢያ ላይ እንደ ርእስ የተጠቀሰው ሐዲሥ መልእክቱ ምንድነው? የሚል ጥያቄ ስለሚነሳ እስኪ ወደሱ እንመለስ፡-

ሀ. በሰዎች መሐል እርቅ ለመፍጠር፡-

ሰዎች ተጣልተው እርቅ ለመፍጠር የሚፈልግ ሸማግሌ እውነቱን ተናግሮ የጥሉን ግድግዳ ማፍረስ የማይችል ቢሆንና ሌላ አማራጭ ቢጠፋበት፡ ሰላሙን ለማውረድ አስቦ የአንደኛውን ጥፋት መግለጹ የባሰ ጥሉን እንደሚያባብሰው ከተረዳ፡ ዋሽቶ ቢያስታርቃቸው እንደ ኃጢአተኛ አይቆጠርም፡፡ ምክንያቱም ዓላማው የግል ጥቅሙን ለማስጠበቅ፣ ተወዳጅነትን ለማትረፍና ምድራዊ ጥቅሙን ለማግኘት ሳይሆን በሰዎች መሐል እርቅ ለማውረድ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በተጨባጩ ዓለም ላይ የምናየውና የምንኖረው እውነት ነው፡ ባልና ሚስት ተጣልተው ትዳሩ ሊፈርስ ቢቃረብና ጉዳዩን የተረዳ ሸማግሌ የእንዳቸውን ነውር ደብቆ ዋሽቶ ቢያስታርቃቸው ጥፋቱ ምኑ ላይ ነው? ወይስ እውነቱን አውጥቶ ያፍረጥርጠውና ትዳሩም ይፍረስ፡ ቤተሰቡም ይበተን?

ጉዳዩን የበለጠ ለመረዳት ምሣሌን እንመልከት፡-

ምሣሌ አንድ፡- አንድ ተበዳይ የሆነ ሰው ከበዳዩ ለማምለጥ እየሮጠ ወደ አንድ ግቢ ሲሸሸግ በአይንህ ተመልክተኸዋል፡፡ በዳዩ ሰው ወዳንተ መጥቶ፡- አሁን በዚህ ጋ የሮጠውን ልጅ አይተኸዋል? የት ነው የተሸሸገው? ብሎ ቢጠይቅህ ምን ብለህ ትመልሳለህ? አሁን አንተ ሁለት አጣብቂኝ ነገር ውስጥ ገብተሀል፡፡

1ኛ. አላየሁም ብለህ መዋሸት

2ኛ. አይቼዋለሁ ብለህ የተደበቀበትን ቦታ ማሳየትና ልጁን ማስገደል ወይም ማስመታት

ታዲያ ውሸት ኃጢአት ነው ብለህ ልጁ የተደበቀበትን ቦታ አሳይተህ ማስገደሉ ፍትህ ነው? አእምሮህስ ይቀበለዋል? ወይንስ የተደበቀውን ሰው እንዳላየህ ገልጸህ ልጁን ማዳን? በተለይ ሊገደል የሚፈለገው ሰው የቤተሰብህ አካል ቢሆን ምን ልታደርግ እንደምትችል አስብ፡፡ ‹‹አሸፃ-ደረረይን›› ከሁለት ጉዳቶች፡ ጉዳቱ የተሻለውን መርጦ መጠቀም አግባብነት ያለው ድርጊት ነው፡፡

ምሣሌ ሁለት፡- የህክምና ባለሙያ ነህ እንበል፡፡ አንድን በሽተኛ እያከምኸው ሳለ፡ ህመሙ በጣም እንዳገረሸበትና በከፋ አደጋ ላይ እንዳለ ታውቃለህ፡፡ ይህን ሁኔታ ለበሽተኛው ብትነግረው፡ ምናልባትም መቋቋም አቅቶት የባሰ ህመሙ አገርሽቶበት ይሞታል ብለህ ትሰጋለህ፡፡ እናም ይህ ህመምተኛ፡- ዶክተር! አሁን እንዴት ነኝ? በምን ሁኔታ ላይ ነው የምገኘው? የጤናዬስ ነገር ያስፈራልን? ቢልህስ ያንተ ምላሽ ምንድነው የሚሆነው? ግልጽ ነው፡፡ እሱን ለማጽናናት የተስፋ ቃል እንጂ፡ በጣም አደጋ ላይ ነህ አትለውም፡፡ ይህን ማለትህ በበሽታው ላይ ሌላ በሽታ ማምጣት ነው፡፡

ለ. ባለቤቱን ለማስደሰት፡-

በትዳር ዓለም በባልና ሚስት መሐል የፍቅር ጨዋታዎች መኖራቸው እሙን ነው፡፡ ታዲያ ባል የባለቤቱን ፍቅር ለመጨመርና በመሐከላቸው መዋደድ እንዲኖር ውሸትን ያዘሉ የጨዋታ ቃላቶች መጠቀም ተፈቅዶለታል፡፡ አንቺ ከዓለማት ሴቶች ሁሉ በላይ ለኔ ውድ ነሽ! እና የመሳሰሉትን፡፡ ምናልባት ምንም ሚስቱን ቢወዳትም፡ እሷ የዚያን ያህል የተወደደች ላትሆን ትችላለች፡፡ በውስጥዋ ደስታን ለመዝራትና ፍቅሩን ለማጠንከር ግን መጠቀም ይችላል፡፡ አንድ ምሣሌ እንመልከት፡-

ባለቤትህ አንተ ቤት ስትገባ እንድትበላና እንድትደሰት ቀኑን ሙሉ ምግብ ሰርታ ለፍታ አዘጋጅታ ጠበቀችህ፡፡ አንተም ወደ ቤት በገባህ ጊዜ የተዘጋጀህልን ምግብ መብላት ጀመርክ፡፡ ግን ምግቡ ላይ ጥፍጥና አላገኘህበትም፡፡ እናም ላንተ ብላ የለፋችው ባለቤትህ ወዳንተ በመምጣት፡ በፍቅር ቋንቋ፡- እንዴት ነው ምግቡ? ብትልህ፡ ምንም አይጣፍጥም! ነው ያንተ መልስ፡ ወይስ መስተካከል ያለበትን ሌላ ቀን እነግራታለሁ ብለህ ለዛሬ ሞራሏን ላለመንካት፡- በጣም አሪፍ ነው የሰራሽው ምግብ፡ ይጣፍጣል ውዴ ባለቤቴ! ነው የምትላት?

ሐ. በጦርነት ጊዜ፡-

ለወረራ የመጣን የጠላት ጦር በማዘናጋትና በማሳሳት ጥቃት ለመፈጸም በፍጥጫው ሌላ አቅጣጫ እንዳለን አድርጎ ማታለል የተፈቀደ ተግባር ነው፡፡ ካልሆነም የት እንዳለህ፡ የጦር ሰራዊቶችህን ብዛትና ቁጥር፡ የታጠቃቸውን የመሳሪያ አይነት፡ ጦርነቱ መቼ እንደሚጀመር ከጠየቁህ እውነቱን ግለጽላቸውና መጥተው ይጨርሱት፡፡

ወንድምና እህቶች ከላይ እንዳነበብነው ኢስላም ውሸትን ምን ያህል እንዳወገዘና የተጠላ ተግባር እንደሆነ በሰፊው ተመልክተናል፡፡ ውሸተኞችም የማይድኑ መሆኑን አንብበናል፡፡ ለሶስት ምክንያቶች ግን ፡ እሱም ለማኅበረሰቡ ጥቅምና ግልጋሎት ሲባል እንጂ ለግል ጥቅም ታስቦ ባልሆነበት ቦታ ላይ መዋሸት መቻሉን አይተናል፡፡ የኢስላም ጠላቶች ግን፡ አንድም የተሟላ ዲን ስለሌላቸው ፡ ሌላም በጥላቻና መጎይምነት ስሜት በመነሳት እነዚህን ሶስቱን ነጥቦች ብቻ አጉልተውና አጋነው፡- ኢስላም ለሃይማኖትህ ስትል ዋሽ! ብሏል በማለት የሌለውን ሊያሳዩን ይሞክራሉ፡፡ ጭራሹኑ ለሃይማኖትህ ስትል መዋሸት በኢስላም ይቻላል ይላሉ፡፡ ይህ ትልቅ ቅጥፈት ነው፡፡ እኔ ለሃይማኖቴና ለጌታዬ አላህ ክብር ስል እንድዋሽ አልተፈቀደልኝም፡፡ ይልቁኑ ይህ ያለው በናንተ መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡ መጽሐፋችሁ እንዲህ ይላል፡-

‹‹በእኔ ውሸት ግን የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ከላቀ ስለምን በእኔ ደግሞ እንደ ኃጢአተኛ ገና ይፈርድብኛል? ስለ ምንስ መልካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም? እንዲሁ ይሰድቡናልና አንዳንዱም እንዲሁ እንድንል ይናገራሉና። የእነርሱም ፍርድ ቅን ነው። ›› (ወደ ሮሜ ሰዎች 3፡7-8)።

ወገኖቻችን ሆይ! ከፍጡራን አምልኮ ወጥታችሁ አንዱንና እውነተኛውን አምላክ አላህን ታመልኩና ትገዙ ዘንድ ወደ ኢስላም ጥሪ እናደርግላችኋለን። ከኢስላም ውጪ ምንም የጀነት መንገድ የለምና፡-

"የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በኛና በናንተ መካከል ትክክል ወደሆነች ቃል ኑ፤ (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጐ ላይይዝ ነዉ፤ በላቸዉ። እምቢ ቢሉም ፡- እኛ ሙስሊሞች መሆናችንን መስክሩ በሏቸው" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡64)።

"ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።" (ሱረቱል ፋቲሓ 1፡6)።

ወላሁ አዕለም

በህይወት ያለው ከሞተው አይበልጥም!!

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና የዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ውዳሴና ሰላም፡ የሰላም አለቃና መምህር ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ ይሁን። ድልና የበላይነት ሐቅን ለማንገስና ሀሰትን ለማርከስ፡ በደልን አጥፎ ፍትህን ለማስፈን ዕውቀታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ህይወታቸውን መስዋእት በማድረግ ለሚታገሉት ይሁን።

የማያጠግብ እንጀራ ባይበላ ይቅር! እንዲሉ ሆነና፡ እንኳን በአላህ አንድነት ላይ እምነቱን ላጸናው ሙስሊም ይቅርና ከሃይማኖት እሳቤ ገለልተኛ ሆኖ በንጹህ ህሊናው የሚያስብን ሰው ማሳመን የሚችል የወረደ አስተሳሰብ ነው።

እሱም፡- የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ሙስሊሞች እንደምትሉት ካልሞተና አላህ ወደራሱ ከወሰደው፡ በዛው ተቃራኒ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ከሞቱና ከተቀበሩ፡ በርግጥም ዒሳ በደረጃ ይበልጣቸዋል ማለት ነው!!። እንደገናም እሱ የአላህ ልጅ መሆን አለበት ማለት ነው! የሚል ነው። ለዚህ የተሳሳተ አስተሳሰብ እርምትን ለሚሻ ሰው በአላህ ፈቃድ መጠነኛ ምላሽን እንካችሁ ብያለሁ። ወማ ተውፊቂ ኢልላ ቢላህ (የመልካም ነገር ሁሉ ገጠመኝ ከአላህ እንጂ ከማንም አይደለም)።

1ኛ/ አላህ (ሱብሐነሁ ወተዓላ) ሞትና ህይወትን የፈጠረ አምላክ ነው። ህይወት የመልካም ስራ ውጤት እንዳልሆነው ሁላ፡ ሞትም የኃጢአት ውጤት አይደለም። ሰው ቀድሞውኑ በዚህ ምድር ላይ ሲፈጠር በአምላካዊ ህግጋቶች (ይህን ፈጽም፡ ያን ደግሞ አትቅረብ በሚሉት) ሊፈተን እንጂ፡ ለዘለዓለም እንዲኖር አይደለም። ዘላለማዊነትን (በጀነት ወይም በጀሀነም) የሚረከብበት ዓለም የውሙል ቂያም (የትንሳኤው ዕለት) ነው። በዚህም ሰበብ በምድራዊ ቆይታው ከአምላኩ ከአላህ ዘንድ ህይወትን ብቻ ሳይሆን ሞትንም ጭምር ተቀብሎ ነው የመጣው። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" الْغَفُورُ الْعَزِيزُ وَهُوَ عَمَلًا أَحْسَنُ أَيُّكُمْ لِيَبْلُوَكُمْ وَالْحَيَاةَ الْمَوْتَ خَلَقَ الَّذِي " الملك سورة 2

"ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መሆኑን ሊሞክራችሁ፣ ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው፤ እርሱም አሸናፊው መሐሪው ነው።" (ሱረቱል ሙልክ 67፡2)።

2ኛ/ ማንም ሰው ምድራዊ ተልእኮውን ከፈጸመ በኋላ ከአላህ ዘንድ የተወሰነለት ምድራዊ ቆይታ ሲጠናቀቅ (አጀሉ ሲደርስ) መሞቱ አይቀሬ ነው። ከሞት ሊያመልጥ የሚችል አንድም ነፍስ የለም። በዚህ ምድር ላይ ሁሉም ከሞት በታች ነውና። የአላህ ቃል ይህንን እውነት እንዲህ ያነላዋል፡-

" الْغُرُور مَتَاعُ إِلَّا الدُّنْيَا الْحَيَاةُ وَمَا فَازَ فَقَدْ الْجَنَّةَ وَأُدْخِلَ النَّار عَنِ زُحْزِحَ فَمَنْ الْقِيَامَةِ يَوْمَ أُجُورَكُمْ تُوَفَّوْنَ وَإِنَّمَا الْمَوْتِ ذَائِقَةُ نَفْسٍ كُلُّ " عمران آل سورة 185

"ነፍስ ሁሉ ሞትን ቀማሽ ናት፤ ምንዳዎቻችሁንም የምትሞሉት (የምትሰጥሙት) በትንሣኤ ቀን ብቻ ነዉ። ከእሳትም የተራቀና ገነትን የተገባ (እንዲገባ የተደረገ) ሰዉ፣ በእርግጥ ምኞቱን አገኘ ቅርቢቱም ሕይወት የመታለያ መሣሪያ እንጅ ሌላ አይደለችም።" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡185)።

" تُرْجَعُونَ وَإِلَيْنَا فِتْنَةً وَالْخَيْرِ بِالشَّرِّ وَنَبْلُوكُمْ الْمَوْتِ ذَائِقَةُ نَفْسٍ كُلُّ " الأنبياء سورة 35

"ነፍስ ሁሉ ሞትን ቀማሽ ናት፤ ለመፈተንም በክፉም በበጎም እንሞክራችኋለን፤ ወደኛም ትመለሳላችሁ።" (ሱረቱል አንቢያእ 21፡ 35)።

" يَسْتَقْدِمُونَ وَلَا سَاعَةً يَسْتَأْخِرُونَ لَا أَجَلُهُمْ جَاءَ فَإِذَا مُسَمًّى أَجَلٍ إِلَى يُؤَخِّرُهُمْ وَلَكِنْ دَابَّةٍ مِنْ عَلَيْهَا تَرَكَ مَا بِظُلْمِهِمْ النَّاسَ اللَّهُ يُؤَاخِذُ وَلَوْ " النحل سورة 61

"አላህም ሰዎችን በበደላቸው በያዛቸው ኖሮ፣ በርሷ (በምድር) ላይ ከተንቀሳቃሽ ምንንም ባልተወ ነበር፤ ግን እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ያቆያቸዋል፤ ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት አንዲትን ሰዓት አይቆዩም፤ አይቀደሙምም።" (ሱረቱ-ነሕል 16፡61)።

ከነዚህ አንቀጾች በግልጽ የምንረዳው፡- ህይወታችንና ሞታችን ያለው በአላህ ዘንድ ብቻ ነው። እሱ የሻውን ነፍስ የፈለገው ያህል ጊዜ ያቆየዋል። ሲፈልግ ሩሑን (መንፈሱን) ከውስጡ እንዲወጣ በማዘዝ ይገድለዋል። ያለ አላህ ፈቃድና ኃይል የተፈጠረና ህያው የሆነ ነፍስ እንደሌለ ሁሉ፡ ያለሱ ፈቃድም የምትሞት አንዲትም ነፍስ የለችም። ቅዱስ ቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

" مُؤَجَّلًا كِتَابًا اللَّهِ بِإِذْنِ إِلَّا تَمُوتَ أَنْ لِنَفْسٍ كَانَ وَمَا..." عمران آل سورة 145

"ለማንኛይቱም ነፍስ በአላህ ፍርድ ቢሆን እንጅ ልትሞት አይገባትም፤ (ጊዜዉም) ተወስኖ ተጽፏል..." (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡ 145)።

3ኛ/ የመርየም ልጅ ዒሳም (ዐለይሂ-ሰላም) ቢሆን ሟች ነው። ከሞት ሊያመልጥና ሊተርፍ አይችልም። ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) አልሞተም ማለት አይሞትም ማለት አይደለም። ወደፊት ቂያማ ከመቆሙ በፊት በመቃረቢያው ላይ ወደዚህ ምድር ይወርዳል። ተልእኮውንም ከፈጸመ በኋላ ሰብአዊ ፍጡር ነውና ይሞታል። ይህንን እውነታ በራሱም አንደበት እንደተናገረ ጌታችን በቃሉ እንዲህ ይነግረናል፡-

" حَيًّا أُبْعَثُ وَيَوْمَ أَمُوتُ وَيَوْمَ وُلِدْتُ يَوْمَ عَلَيَّ وَالسَّلَامُ " مريم سورة 33

"ሰላምም በኔ ላይ ነው፣ በተወለድሁ ቀን፣ በምሞተበትም ቀን፣ ሕያው ሆኜ በምቀሰቀስበትም ቀን" (ሱረቱ መርየም 19፡33)።

በደንብ አስተውሉ! ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) መወለዱን ለመግለጽ ‹በተወለድሁ ቀን› አለ እንጂ፡ ‹በምወለድበት ቀን› አላለም። ተወልዷልና። ሟች መሆኑን ለመግለጽ ግን ‹በምሞትበት ቀን› አለ። አልሞተምና ‹በሞትሁበት ቀን› ብሎ እንደ ውልደቱ ድርጊቱን ታላፊ ጊዜ አድርጎ አልተጠቀመም። ስለዚህ ወደፊት ይመጣል ይሞታል ይቀሰቀሳልም!!

4ኛ/ ወደ ገደለው እንግባና፡- ታዲያ የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) እስካሁን ድረስ አልሞተምና፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) በመሞታቸው ከሳቸው ይበልጣል ስንል፡ ቀጣዩን ጥያቄ በአግባቡ መልስ ልንሰጥበት ይገባል፡-

ዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) እስካሁን በህይወት የቆየው በራሱ ፈቃድ ነውን? ደግሞስ በህይወት እንዲቆይ ያደረገው የተለየ መልካም ስራ ኖሮት ነውን? በዛው ተቃራኒ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) በ63 ዓመታቸው የሞቱትና እስካሁን በህይወት ያልቆዩት ታጢአታቸው በመብዛቱ ሰበብ ነውን ?

ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው ምላሽ፡- በፍጹም! የሚል ነው። ምክንያቱም በመግቢያችን ላይ እንዳየነው ሞትና ህይወት ከአላህ ዘንድ ለባሮቹ የሚለገስ መለኮታዊ ውሳኔ እንጂ፡ የጽድቅና የታጢአት ውጤት አይደለም። የዒሳ (ዐለይሂ-ሰላም) እስካሁን በህይወት መቆየት የጌታው ፈቃድና ዓላማ እንጂ ሌላ አይደለም። የሳቸውም መሞት መለኮታዊ ፍርድ እንጂ ሌላ አይደለም። በመሆኑም የመለኪያው መስፈርት እጅግ የተሳሳተ ነው!!

5ኛ/ እኛ ሙስሊሞች ከጌታ አላህ ዘንድ የታዘዝነው በነቢያት መካከል ምንም አይነት የእምነት ልዩነት ሳናደርግ (በአንዱ አምኖ በሌላው መካድ ሳይኖር) በሁሉም ነቢይነት እንድናምን እንጂ፡ ሰዋዊ መለኪያዎችን እያስቀመጥን አንዱን ከሌላው እንድናወዳድር አይደለም። ይህ አካሄድ ኋላ ላይ አንዱን ነቢይ ከፍ ለማድረግ ሲባል የሌላውን ነቢይ ክብር በመንካት ከአላህ ጋር ወደ መጣላት ያደርሰናል። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" النَّبِيُّونَ أُوتِيَ وَمَا وَعِيسَى مُوسَى أُوتِيَ وَمَا وَالْأَسْبَاطِ وَيَعْقُوبَ وَإِسْحَاقَ وَإِسْمَاعِيلَ إِبْرَاهِيمَ إِلَى أُنْزِلَ وَمَا إِلَيْنَا أُنْزِلَ وَمَا بِاللَّهِ آمَنَّا قُولُوا مُسْلِمُونَ لَهُ وَنَحْنُ مِنْهُمْ أَحَدٍ بَيْنَ نُفَرِّقُ لَا رَبِّهِمْ مِنْ البقرة سورة " 136

"«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል #የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን» በሉ።" (ሱረቱል በቀራህ 2፡136)።

" وَأَطَعْنَا سَمِعْنَا وَقَالُوا رُسُلِهِ مِنْ أَحَدٍ بَيْنَ نُفَرِّقُ لَا وَرُسُلِهِ وَكُتُبِهِ وَمَلَائِكَتِهِ بِاللَّهِ آمَنَ كُلٌّ وَالْمُؤْمِنُونَ رَبِّهِ مِنْ إِلَيْهِ أُنْزِلَ بِمَا الرَّسُولُ آمَنَ الْمَصِيرُ وَإِلَيْكَ رَبَّنَا غُفْرَانَكَ البقرة سورة " 285

"መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ። ምእምኖቹም (እንደዚሁ)። ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ «በአንድም መካከል #አንለይም» (የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ። «ሰማን፤ ታዘዝንም። ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን)። መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው» አሉም፡።" (ሱረቱል በቀራህ 2፡285)።

" مِنْ وَالنَّبِيُّونَ وَعِيسَى مُوسَى أُوتِيَ وَمَا وَالْأَسْبَاطِ وَيَعْقُوبَ وَإِسْحَاقَ وَإِسْمَاعِيلَ إِبْرَاهِيمَ عَلَى أُنْزِلَ وَمَا عَلَيْنَا أُنْزِلَ وَمَا بِاللَّهِ آمَنَّا قُلْ مُسْلِمُونَ لَهُ وَنَحْنُ مِنْهُمْ أَحَدٍ بَيْنَ نُفَرِّقُ لَا رَبِّهِمْ عمران آل سورة " 84

"በአላህ አመንን፤ በኛ ላይ በተወረደዉም፥ (በቁርአን) በኢብራሂምና በኢስማዒልም፣ በኢስሐቅም በያዕቆብም፣ በነገዶችም ላይ በተወረደዉ፤ ለሙሳና ለዒሳም፣ ለነቢያትም ሁሉ ከጌታቸዉ በተሰጠዉ (አመንን)፤ ከነርሱ መካከል አንዱንም #አንለይም፤ እኛ ለርሱ ታዛዦች ነን፣ በል።" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3፡84)።

6ኛ/ በመጨረሻም ለወገኖቻችን የምናቀርበው ጥያቄ፡- አንድ ነቢይ ለረጅም ዘመናት በህይወት መቆየቱ፡ ረጅም ዘመን ሳይኖር ከሞተው ሌላ ነቢይ በደረጃ የሚያስበልጠው ከሆነ፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ አስተምህሮ መሰረት ሄኖክና ኤልያስ ከነቢያት ሁሉ ይበልጣሉ ማለት ነውን ?

በእናንተ ዘንድ እንደሚታወቀው ሙሴ/ሙሳ (ዐለይሂ-ሰላም) ሊቀ-ነቢያት ነው፡፡ ሌሎችም አበይት/ዋና ነቢያት የሚባሉ አሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ምድራዊ ተልእኮአቸውን ሲፈጽሙ ሞተዋል፡፡ በክብር ተቀብረዋል፡፡ ሄኖክ/ኢድሪስ (ዐለይሂ-ሰላም) ግን መጽሓፋችሁ እንደሚናገረው በእምነት አምላኩን በማስደሰቱ ሞትን እንዳያይ ተወስዷል፡-

‹‹ሄኖክ ሞትን እንዳያይ በእምነት ተወሰደ፥ እግዚአብሔርም ስለ ወሰደው አልተገኘም። ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና፤›› (ዕብራዊያን፡ 11፡3)።

ነቢዩ ኤልያስም/ኢልያስ (ዐለይሂ-ሰላም) ቢሆን በአውሎ ነፋስ አማካኝነት ወደ ሰማይ እንደተወሰደ መጽሐፉ ይናገራል፡፡ ተመልሶ መምጣቱንና መሞቱን አይገልጽም፡- ‹‹ሲሄዱም፡- እያዘገሙም ሲጫወቱ፥ እነሆ፥ የእሳት ሰረገላና የእሳት ፈረሶች በመካከላቸው ገብተው ከፈሉአቸው፤ ኤልያስም በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ወጣ።›› (2ኛ ነገስት 2፡11)።

በዚህ ምክንያት እነዚህ ሞትን ያላዩ ነቢያት፡ ከሞቱት (አብረሃም፣ ሙሴ፣ ኢሳይያስ፣ ኤርሚያስ፣ ዳንኤል፣ ህዝቅኤል…) በክብርና በደረጃ ይበልጣሉ ማለት ነውን? ወይስ መመዘኛው የሚያገለግለው ለነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሲሆን ብቻ ነው? አላህ ወደ ሐቁ ጎዳና ይምራችሁ፡፡ እኛንም በእምነታችን ጽናት ይስጠን፡፡

“”የማያዳግም ምላሽ ለህዝበ ክርስትያን””

ክርስትያኖች በገሊላ ናዝሬት ተወልዶ ያደገው ፍጡር እየሱስን ,ፈጣሪ ለማድረግ የማይፈነቅሉት ድንጋይ,የማይቆፍሩት ጉድጓድ የለም። ክርስትያኖች ለእየሱስ አምላክነት ማስረጃ ይሆናሉ ብለው ለሚያቀርብዋቸው ጥቅሶች የተዘጋጀ የማያዳግም ምላሽ በአላህ ፈቃድ እንመለከተዋለን።ቀጥታ ወደ ጥቅሶች ልግባ 1•”እኔና አብ አንድ ነን”(ዮሐንስ ወንጌል 10:30)

እየሱስ ክርስቶስ በዚህ ጥቅስ ላይ እኔና አብ 1 ነን ሲል አንድነቱ የአላማ አንድነት እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም። እንደ ባይብል አስተምህሮት እግዚአብሄር አብና እግዚአብሄር ወልድ 1 አይደሉም,1 ሊሆኑም አይችሉም።

ይህንን እውነታ ማስረጃን አስደግፈን እንመልከተው።

1/“ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ,የሴትም ራስ ወንድ,የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ እወዳለሁ”(1ኛ ቆሮንቶስ 11:3)

የኛ ጥያቄ: የክርስቶስ ራስ እግዚአብሄር ከሆነ እንዴት 1 ናቸው ማለት ይቻላል?

2/“ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ, እኔም አብን እለምናለሁ (የየሐንስ ወንጌል 14:15)

የኛ ጥያቄ: ለማኙ ኢየሱስ ከሆነ ,ተለማኙ ኣብ ከሆነ ለማኝና ተለማኝ እንዴት እኩል ናቸው ማለት እንችላለን?

3/“የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከኔ ኣብ ይበልጣልና (የዮሐንስ ወንጌል 14:28)

የኛ ጥያቄ: ኣብ እንደሚበልጠው በግልፅ እየተናገረ እንዴት 1 ናቸው ትሉናላችሁ?

4/“ኢየሱስም ስለምን ቸር ትለኛለህ, ከኣንዱ ከእግዚኣብሄር በቀር ቸር ማንም የለም”(የዮሐንስ ወንጌል 10:18)

የኛ ጥያቄ: እግዚኣብሄር ቸር ከሆነ, እየሱስ ደግሞ ቸር ኣለመሆኑን ከተናገረ, እንዴት 1 ናቸው ትሉናላችሁ?

5/” ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰኣት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከኣባት በቀር የሚያውቅ የለም” (ማርቆስ ወንጌል 13:32) ማቴዎስ 24:36 ላይም ተደግሞዋል።

የኛ ጥያቄ: የትንሳኤ ቀን እውቀት ያለው ኣብ ብቻ ከሆነ, እውቀቱ ያለው ኣብ እውቀቱ ከሌለው ኢየሱስ ጋር እንዴት እኩል ይሆናሉ?

6/“የሰጠኝ ኣባቴ ከሁሉ ይበልጣል” (የዮሐንስ ወንጌል 10:29)

የኛ ጥያቄ: ሰጪው ኣብ ከሁሉም የሚበልጥ ከሆነ ኣንድነታቸው የቱ ጋ ነው? ይሄን ሁሉ ማስረጃ ቀርቦላቸው ሓቁን ለመቀበል ዝግጁ ካልሆኑ ኣሁን ያለን ኣማራጭ ጥያቄ በመጠየቅ የተሳሳተ እምነታቸውን ውድቅ ማድረግ ነው።

1/እንደ ክርስትያኖች እምነት እግዚኣብሄር ኣብ,እግዚኣብሄር ወልድናእግዚኣብሄር መንፈስ ቅዱስ 1 ናቸው።

የኛ ጥያቄ : እየሱስ እኔና ኣብ 1 ነን እንዳለው ሁሉ “እኔና መንፈስ ቅዱስ 1 ነን ያለበት 1 ጥቅስ ኣሳዩን”???

2/” ሁሉም ኣንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ኪቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ ኣልለምንም፤ ኣንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ ኣንተ፥ኣባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በኣንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ ኣንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ። እኛም ኣንድ እንደ ሆንን ኣንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ ኣንተም በእኔ ስትሆን፥ በኣንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤እንዲሁም ዓለም ኣንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል (ዮሐንስ 17:20—23)

በዚህ ጥቅስ ላይ እየሱስ ሲናገር

“እኛም ኣንድ እንደሆን ኣንድ ይሆኑ ዘንድ” ሲል ኣንድ የሚለው ቃል “ፈጣሪ ወይም ኣምላክ” ለማለት ተፈልጎ ከሆነ

የእየሱስ ንግግር “እኛ ፈጣሪ እንደሆን ፈጣሪ ይሆኑ ዘንድ ማለቱ ነውን”???? እንዲህ ከሆነ መልእክቱ ,የምታመልኩት 15 ኣምላክ ነው ማለት ነው።

እግዚኣብሄር ኣብ + እግዚኣብሄር ወልድ + እግዚኣብሄር መንፈስ ቅዱስ + 12 ደቀመዝሙር=15 ኣምላክ

ሌላው ክርስቲያኖች ኢየሱስን ጌታ ኣምላክ ነው ለማለት የሚጠቀሙበት ጥቅስ“እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን”

(ዮሐንስ ወንጌል 13:14) እየሱስ በዚህ ጥቅስ ላይ “እኔ ጌታና መምህር ስሆን” ብሎ መናገሩ ለኣምላክነቱ ማስረጃ ሊሆን ኣይችልም።

ጌታ የሚለው ቃል እዚህ ላይ እሚያመላክተው የክብር መገለጫ ቃል እንደሆነ እንጂ, ኣምላክ ወይም ፈጣሪ የሚል ትርጉም እንዳለው ኣይደለም። እየሱስ ክርስቶስ እኔ ጌታና መምህር ስሆን ሲል የጌትነት መኣርግ የሰጠው ማነው???ለእየሱስ ክርስቶስ የጌትነት መኣርግ የሰጠው እግዚኣብሄር ነው።

“እናንተ የሰቀላችሁትን እየሱስን እግዚአብሄር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ (የሐዋሪያት ሥራ 2:36)

ታዲያ ለእየሱስ “ጌታ” የሚል መአርግ የሰጠው እግዚአብሄር ከሆነ,እየሱስ ደግሞ ከእግዚአብሄር የተሰጠውን መአርግ ለመግለፅ “እኔ ጌታና መምህር ስሆን” ብሎ ቢናገር, እየሱስ ኣምላክ ነው ለማለት እንዴት ያስደፍራል??? ጌታ የሚለው ቃል በባይብል ውስጥ ኢየሱስ ብቻ አልነበረም ሲጠራበት የነበረው። ይልቁንም የክብርና የመአርግ መገለጫ ቃል እንደሆነ በማስረጃ እንመልከተው።

1/“እርስዋም ጌታዬ ሆይ ጠጣ ኣለችው”(ኦሪት ዘፍጥረት 24:18)

2/“ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሎኣል”(ኦሪት ዘፍጥረት 18:12) ሳራ ኣብራሃምን “ጌታዬ” ብላ ስትጠራው “ኣምላኬ ወይም ፈጣሪየ” ለማለትነውን??? ብለን ማንኛውም ክርስትያን ብንጠይቅ “ኣዎ” ብሎ ለመመለስ የሚደፍር 1 ሰው ኣናገኝም።

3/” ጌታዬ ሙሴ ሆይ ከልከላቸው ኣለው”(ኦሪት ዘህልቁ 11:28) በዚህ ጥቅስ ላይም ሙሴን ጌታዬ ብሎ ሲጠራው,ለሙሴ ያለውን ክብር እየገለፀ እንጂ ,ሙሴ ኣምለኩ ወይም ፈጣሪው ሆኖ ኣይደለም። ስለዚህ “እየሱስ እኔ ጌታና መምህር ስሆን” ብሎ መናገሩ ለኣምላክነቱ ወይም ፈጣሪ ለመሆኑ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ ይቅርና መረጃ እንኳን ሊሆናቸው ኣይችልም።

4/“እኔን ያየ ኣብን ኣይቷል”(ዩሐንስ ወንጌል 14:9) እየሱስ ክርስቶስ እኔን ያየ ኣብን ኣይቷል ሲል ለኛ የሚሰጠን ኣስተምህሮት

እየሱስን ኣብ ሁለትና የተለያዩ መሆናቸውን ነው። የሚገርመው ነገር ይህ ጥቅስ ከሌሎች የባይብል ጥቅሶች መጋጨቱ ነው።

/”መቼም ቢሆን እግዚአብሄርን ያየው ኣንድስ እንኳ የለም”(ዩሐንስ ወንጌል 1:18)

ይህ ጥቅስ እግዚአብሄርን ያየ ማንም የለም ካለን “እየሱስን ያየ ኣብን ኣይቷል”ማለት እንዴት ይቻላል???

“የላከኝ ኣብም እርሱ ስለኔ መስክሮዋል ድምፁን ከቶ ኣልሰማችሁም መልኩንም ኣላያችሁም”(ዩሐንስ ወንጌል 5:37)

በዚህ ጥቅስ ኣብን እንዳላዩት እየሱስ በግልፅ እየተናገረ “እየሱስን ያየ ኣብን ኣይቷል”ማለት ማስረጃ የሌለው ሃሳብ ከመሆን ኣይዘልም።

የእምዬን ወደ አብዬ!

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2)። የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)።

" قَدْ * حَلِيمٌ غَفُورٌ وَاللَّهُ عَنْهَا اللَّهُ عَفَا لَكُمْ تُبْدَ الْقُرْآنُ يُنَزَّلُ حِينَ عَنْهَا تَسْأَلُوا وَإِنْ تَسُؤْكُمْ لَكُمْ تُبْدَ إِنْ أَشْيَاءَ عَنْ تَسْأَلُوا لَا آمَنُوا الَّذِينَ أَيُّهَا يَا
كَافِرِينَ بِهَا أَصْبَحُوا ثُمَّ قَبْلِكُمْ مِنْ قَوْمٌ سَأَلَهَا " المائدة سورة 102-101

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ለእናንተ ቢገለጹ ከሚያስከፏችሁ ነገሮች አትጠይቁ። ቁርአንም በሚወርድበት ጊዜ ከእርሷ ብትጠይቁ ለናንተ ትገለጻለች፤ ከእርሷ አላህ ይቅርታ አደረገ። አላህም መሓሪ ታጋሽ ነው። ከናንተም በፊት ሕዝቦች በእርግጥ ጠየቋት። ከዚያም በእርሷ (ምክንያት) ከሓዲዎች ኾኑ።" (ሱረቱል ማኢዳህ 5፡101-102)።

በዚህ አንቀጽ ላይ ከካፊሮች በኩል የቀረበ አንድ ጥያቄ አልለ፡፡ እሱም፡- ‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ለእናንተ ቢገለጹ ከሚያስከፏችሁ ነገሮች አትጠይቁ›› የሚለውን ቆንጥሮ በማውጣት፡- ኢስላም ከተከታዮቹ ጥያቄን ማስተናገድ አይፈልግም፡፡ አማኞቹ ያለ-ምንም ጥያቄ ዝም ብለው እንዲከተሉ ስለሚፈልግ ‹‹አትጠይቁ!›› በማለት ከልክሏል! ይሉናል፡፡ የጳውሎስን እከክ በጀማል ላይ ልክክ! ይሏችኋል እንዲህ ነው፡፡ እኛም ለዚህ ጥያቄ መሳይ ተቃውሞ የሚኖረን ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡ ወማ ተውፊቂ ኢልላ ቢልላህ፡-

ጥቅላዊ ምላሽ፡-

የቅዱስ ቁርኣኑ አንቀጽ ለማስተላለፍ የፈለገው ነገር፡ ሰዎች መሰረታዊ ያልኾነ፡ ከሕይወታቸው ጋር ተዛማጅነት የሌለው፡ ማወቁ የማይጠቅምና አለማወቁ የማይጎዳን ነገር እያነሱ በመጠየቅ ነቢያቸውን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዳያስቸግሩ የሚገስጽ ነው፡፡ እንዲሁም ከተአምራት ጋር በተያያዘ አንዳንድ ነገራት ይፈጸሙላቸው ዘንድ ጥያቄን ከማብዛት ይልቅ የታዘዙትን ለመፈጸም ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው ለመምከር ነው፡፡ ያ ሳይኾን ቀርቶ፡ እነሱ የጠየቁት ተአምር ቢፈጸምላቸውና ኋላም ሳያምኑ ቢቀሩ ከዓለማት ማንም ያልተቀጣውን ቅጣት እንደሚቀጡ በማወቅ አርፈው ይቀመጡ ዘንድ ለመርዳት ነው፡፡ በተጨማሪም ሸሪዓው ግዳጅ (ዋጂብ) ነው ብሎ ሳይደነግግ በዝምታ ያለፋቸውን ነገራት፡ እነሱም ዝም ብለው ማለፍ ሲገባቸው፡ ጥያቄ እያበዙ በራሳቸው ላይ ተጨማሪ ግዳጆችን እንዳያስደነግጉና ኋላም ግዳጁን ለመወጣት እንዳይቸገሩ ለመርዳት ነው አትጠይቁ! የተባሉት፡፡ ከዚህ ውጭ ሃይማኖትን በተመለከተ ‹‹አትጠይቁ!›› የሚል ነገር ቃሉ ላይ አልተጻፈም፡፡

ዝርዝር ምላሽ፡-

1ኛ/ ኢስላም የዕውቀት ሃይማኖት ነው፡፡ እንደውም ሃይማኖቱ ከእምነት በፊት ዕውቀትን በማስቀደሙ ከወገኖቻችን ሃይማኖት አንዱ መለያው ነው፡፡ የሃይማኖቱ የመጀመሪያ መርሕ ‹‹ዕወቅ›› እንጂ ‹‹እመን›› አይደለም፡፡ ዕውቀት እራሱ ወደ እምነት ይጠራሀልና ቅድሚያ ለዕውቀት ስጥ ነው፡፡ ያላወቀ ሰው አመንኩ ቢል እንኳ፡ ስላመነው ነገር ሌሎችን ማስረዳት አይችልም፡፡ ጥያቄ ቢቀርብለት መመለስ አይችልም፡፡ ያወቀ ሰው ግን ባያምንበት እንኳ ስለ ጉዳዩ መናገር ይችላል፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" وَمَثْوَاكُمْ مُتَقَلَّبَكُمْ يَعْلَمُ وَاللَّهُ وَالْمُؤْمِنَاتِ وَلِلْمُؤْمِنِينَ لِذَنْبِكَ وَاسْتَغْفِرْ اللَّهُ إِلَّا إِلَهَ لَا أَنَّهُ فَاعْلَمْ " محمد سورة 19

"እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም ዕወቅ፡፡ ስለ ስህተትህም ለምእመናንም ምሕረትን ለምን፡፡ አላህም መዘዋወሪያችሁን፣ መርጊያችሁንም ያውቃል፡፡" (ሱረቱ ሙሐመድ 47፡19)፡፡

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ጌታ አላህ ከሱ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩን እመን ወይንም መስክር ሳይኾን ያለው ‹‹ዕወቅ›› በማለት ነው ያዘዘው፡፡ ዕውቀት የሃይማኖቱ ቀዳሚ መርሕ ነውና፡፡ ኢማሙል ቡኻሪይ (194-256 ሂጅ.) ረሒመሁላህ፡ በኪታባቸው ‹ሶሒሕ አል-ቡኻሪይ›› ላይ ይህን አንቀጽ መሰረት በማድረግ ዕውቀት ከንግግርና ከሥራ በፊት ቀዳሚ መኾኑን ይገልጻሉ፡፡ (ሶሒሕ አል-ቡኻሪይ፡ ኪታቡል ዒልም፡ 10ኛ ባብ)፡፡

ከቅዱስ ቁርኣን ለመጀመሪያ ጊዜ የወረደው 96ኛው ሱራ ሱረቱል ዐለቅ ከ1-5 ያለው አንቀጽ ነው፡፡ ይህ አንቀጽም መልእክቱን ሲጀምር ‹‹አንብብ!›› በማለት ነው የጀመረው፡፡ ንባብ ሙሉ ሰው ለመኾን አንዱ ወሳኝ ነገር ነውና፡፡ የወረደው የአላህ ቃልም እንዲህ ይነበባል፡-

" يَعْلَمْ لَمْ مَا الْإِنْسَانَ عَلَّمَ * بِالْقَلَمِ عَلَّمَ الَّذِي * الْأَكْرَمُ وَرَبُّكَ اقْرَأْ * عَلَقٍ مِنْ الْإِنْسَانَ خَلَقَ * خَلَقَ الَّذِي رَبِّكَ بِاسْمِ اقْرَأْ " العلق سورة 5-1

"አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡ ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)፡፡ አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤ ያ በብርዕ ያስተማረ፡፡ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን፡፡" (ሱረቱል ዐለቅ 96፡1-5)፡፡

የአላህ ቃል የኾነው ቅዱስ ቁርአን፡ ያላውቅናቸውንና ያልተረዳናቸውን ነገሮች የዕውቀት ባለቤቶች ዘንድ በመኼድ ጠይቀን መረዳት እንዳለብን ያሳስበናል፡፡ ይህም የሚያሳየው ኢስላም መጠየቅን ሲያበረታታ እንጂ፡ ሲያስጠነቅቅ አይደለም፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" تَعْلَمُونَ لَا كُنْتُمْ إِنْ الذِّكْرِ أَهْلَ فَاسْأَلُوا إِلَيْهِمْ نُوحِي رِجَالًا إِلَّا قَبْلِكَ مِنْ أَرْسَلْنَا وَمَا " النحل سورة 43

"ከአንተም በፊት ወደእነሱ ወሕይን (ራእይን) የምናወርድላቸውን ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም፡፡ የማታውቁም ብትኾኑ #የዕውቀትን_ባለቤቶች_ጠይቁ፡፡" (ሱረቱ-ነሕል 16፡43)፡፡

" خَبِيرًا بِهِ وَكَفَى بِحَمْدِهِ وَسَبِّحْ يَمُوتُ لَا الَّذِي الْحَيِّ عَلَى وَتَوَكَّلْ * خَبِيرًا بِذُنُوبِ عِبَادِهِ الَّذِي خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَمَا وَالْأَرْضَ فِي سِتَّةِ أَيَّامٍ بَيْنَهُمَا وَمَا فَاسْأَلْ الرَّحْمَنُ الْعَرْشِ عَلَى اسْتَوَى ثُمَّ " الفرقان سورة 59-58

"በዚያም በማይሞተው ሕያው አምላክ ላይ ተመካ፡፡ ከማመስገንም ጋር አጥራው፡፡ በባሮቹ ኀጢአቶችም ውስጠ ዐዋቂ በእርሱ በቃ፡ ፡ ያ ሰማያትና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ፣ ከዚያም በዐርሹ ላይ (ሥልጣኑ) የተደላደለ አልረሕማን ነው፡፡ #ከእርሱም_ዐዋቂን_ጠይቅ፡፡" (ሱረቱል ፉርቃን 25፡58-59)፡፡

ጃቢር ኢብኒ ዐብዲላህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዲህ ይላል፡-

ወደ ሰፈር(ጉዞ) ወጣን፡፡ ከኛ ውስጥ አንድ ሰው ድንጋይ አናቱን ፈነከተው፡፡ ደግሞም ሰውየው ኢሕቲላም (ጀናባ) ኾነ፡፡ ሰውየውም አብረውት የነበሩ ሶሓቦችን ‹‹ከውኃ ይልቅ ተየሙም ማድረግ የሚያስችለኝን ነገር ልታገኙልኝ ትችላላችሁን?›› በማለት ጠየቀ፡፡ እነሱም፡- ‹‹አንተ ውኃን መጠቀም እስከቻልክ ድረስ፡ ወደ ተየሙም የሚወስድህን ፈቃድ አናገኝልህም›› በማለት መለሱለት፡፡ ሰውየውም ውኃን በመጠቀም ታጠበ ወዲያውኑም ሞተ፡፡ ወደ አላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ዘንድ በተመለስን ጊዜም ይህን ነገር ስንነግራቸው፡ እሳቸውም፡- ‹‹ገደሉት! አላህ ይግደላቸው! የማያውቁ ከኾነ አይጠይቁም ነበርን? #የመሃይም_መድኃኒቱ_መጠየቅ_ብቻ_ነው! እሱ በተየሙም ቢጠቀም ይበቃለት ነበር›› በማለት መለሱ፡፡ (አቡ ዳዉድ 336፣ ኢብኑ ማጀህ 615፣ አሕመድ 3112፣ ዳረቁጥኒይ 744)፡፡

2ኛ/ በጌታ አላህ ቃል ‹በቅዱስ ቁርአን› ውስጥ፡ በወቅቱና በዘመኑ የነበሩ ሰዎች ነቢዩ ሙሐመድን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሚጠይቁዋቸው የነበሩ አንዳንድ ጥያቄዎችን ጌታ አላህ በቀጥታ በቁርኣኑ በኩል ምላሽን በመስጠት ቃሉን በመልአኩ ጂብሪል (ዐለይሂ-ሰላም) አማካኝነት ያስተላልፍ ነበር፡፡ ይህም ኢስላም ጠይቆ መረዳትን የሚያበረታታ እምነት መኾኑን በግልጽ የሚያስረዳ ነው፡፡ የተወሰኑትን ለናሙና እንመልከታቸው፡፡ ቦታ ላለማጣበብም የአማርኛውን ትርጉም ብቻ አቀርበዋለሁ፡-

"ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው)፡- እኔ ቅርብ ነኝ፡፡ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡ ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ፤ በኔም ይመኑ፤ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡186)፡፡

"(ሙሐመድ ሆይ!) ከለጋ ጨረቃዎች (መለዋወጥ) ይጠየቁሃል፡፡ እነርሱ ለሰዎች ጥቅም ለሐጅም (ማወቂያ) ጊዜያቶች (ምልክቶች) ናቸው በላቸው…" (ሱረቱል በቀራህ 2፡189)፡፡

"ምንን (ለማን) እንደሚለግሱ ይጠይቁሃል፡፡ ከመልካም ነገር የምትለግሱት፤ ለወላጆችና ለቅርብ ዘመዶች፣ ለየቲሞችም፣ ለድሆችም፣ ለመንገደኞችም ነው፡፡ ከበጎ ነገርም ማንኛውንም ብትሠሩ አላህ እርሱን ዐዋቂ ነው በላቸው፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡215)፡፡

"አእምሮን ከሚቃወም መጠጥና ከቁማር ይጠይቁሃል፡፡ «በሁለቱም ውስጥ ታላቅ ኃጢአትና ለሰዎች ጥቅሞች አሉባቸው፡፡ ግን ኃጢአታቸው ከጥቅማቸው በጣም ትልቅ ነው» በላቸው፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡219)፡፡

"ከወር አበባም ይጠይቁሃል፡፡ እርሱ አስጠያፊ ነው፡፡ ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው፡፡ ንጹሕ እስከሚኾኑም ድረስ አትቅረቡዋቸው፡፡ ንጹሕ በኾኑም ጊዜ አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኙዋቸው፡፡ አላህ (ከኃጢኣት) ተመላሾችን ይወዳል፤ ተጥራሪዎችንም ይወዳል በላቸው፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡222)፡፡

"ከሩሕም ይጠይቁሃል፡፡ «ሩሕ ከጌታዬ ነገር ነው ከዕውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም» በላቸው፡፡" (ሱረቱል ኢስራእ 17፡85)፡፡

"ሰዎች ከሰዓቲቱ ይጠይቁሃል፡፡ «ዕውቀትዋ አላህ ዘንደ ብቻ ነው፤» በላቸው፡፡ የሚያሳውቅህም ምንድን ነው! ሰዓቲቱ በቅርብ ጊዜ ልትኾን ይከጀላል፡፡" (ሱረቱል አሕዛብ 33፡63)፡፡

እነዚህ ለናሙና የቀረቡ ምሣሌዎች ናቸው፡፡ በውስጣቸውም፡- ሰዎቹ በወቅቱ ለሚያነሱት ጥያቄዎች ምላሽን ይሰጣቸው እንደነበረ ማብራሪያን ይዘዋል፡፡ ታዲያ በምን ሂሳብ ነው ኢስላም ጥያቄን አይወድም! የሚል ሂስ የሚሰነዝሩት?

3ኛ/ ኢስላም በጥያቄና መልስ የሚያምን ሃይማኖት ለመኾኑ ሌላው ማስረጃችን ተጨባጩ የሙስሊሞች ሕይወት ነው፡፡ በሁሉም ሀገር ቋንቋዎች የሚተላለፉ የኾኑ ኢስላማዊ የሳተላይት ጣቢያዎችን ብትመለከቷቸው፡ ሁሉም ለራሳቸው ሕዝቦች በገዛ ቋንቋቸው የሚተላለፍ አንድ ፕሮግራም አልለ፡፡ እሱም ‹‹አል-ፈታዋ›› የተሰኘው ዓምድ ነው፡፡ በዚህ ዓምድ ሙስሊሞች ካሉበት ቦታ ኾነው ወደ ፕሮግራም አዘጋጆች በቀጥታ በመደወል፡ ማንኛውንም አይነት ኢስላማዊ ጥያቄዎችን፣ ከሕይወታቸው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ነገራት በጥያቄ መልክ ያቀርባሉ፡፡ ስለ አለባበስ፣ ስለ አመጋገብ፣ ስለ ንግድ፣ ስለ ፖለቲካ፣ ስለ ወላጅ ሐቅ፣ የዝምድና ሐቅ፣ የጎረቤት ሐቅ፣ ስለ ማኅበራዊ ኑሮ፣ ስለ ሐላልና ሐራም የሥራ ዘርፎች ወዘተ ጥያቄዎች በየጊዜው ይጎርፉሉ፡፡ ጥያቄው የሚቀርብለት ዓሊምም ያወቀውን በተረዳው መልኩ ያብራራል፡፡ አፍሪካ ቲቪ የተሰኘውን ብቸኛው ጣቢያችንን እንኳ (አላህ ይጠብቀው) ለአብነት ብንወስድ በውስጡ በኦሮሚኛ፣ አማርኛና ትግርኛ ቋንቋዎች የፈትዋ ዓምድ አላቸው፡፡ ከዚህ በላይ ምን ማስረጃ ትፈልጋላችሁ ታዲያ?

የክርስቲያን የሳተላይት ጣቢያዎችን ስናይ የነሱን ሃይማኖታዊ ስብከትና ትምሕርት ብቻ ነው የምናዳምጠው!፡፡ የታለ የፈታዋ (ምን እንጠይቅልዎ) ፕሮግራሙ? አንድ ክርስቲያን በባንክ ተቀጥሮ ስለ መሥራት፣ ወለድ ስለመብላት፣ በወለድ የሚሰራ ባንክን በማኅበር ስለመክፈት፣ ስለ ሙዚቃና ስለ ዘፈን ሐራምነት ስለ ሃይማኖታዊ አለባበስ ስርአት የምትጠየቁበትና የምትመልሱበት የአየር ጊዜ መች አላችሁና? ወይስ ‹‹ኢየሱስ ጌታ ነው!›› ከሚለው ቃል ሌላ (አስተግፊሩላህ) ህዝቡ ምንም እንዳይሰማ ነው የሚፈለገው? እስኪ ማነው ጥያቄ ከተከታዮቹ እንዳይነሳበት የሚፈራው እምነት?

4ኛ/ እውነታው ከላይ እንዳየነው ኢስላም የዕውቀት፣ የምርምርና የልጠየቅ ልመልስ ሃይማኖት መኾኑን ከተረዳን፡ ‹ወገኖቻችን ከላይ ያነሱት የሱረቱል ማኢዳህ 5፡101-102 ትክክለኛው ፍቺ ምንድነው ታዲያ ወደሚለው ዝርዝር ምላሽ እንሂድ፡፡ ይህ አንቀጽ ወደ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የወረደበት ብዙ ሰበቦችን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡ እነዛን ምክንያቶች ማወቁ ለመልሱ ኢጋዥ ስለሚኾን፡ አንቀጹ የወረደበትን አንድ ሰበብ እንመልከት፡-

عَامٍ كُلِّ أَفِي ، اللهِ رَسُولَ يَا : قَالُوا ، {سَبِيلاً إِلَيْهِ اسْتَطَاعَ مَنِ الْبَيْتِ حِجُّ النَّاسِ عَلَى وَلِلَّهِ} : الآيَةُ هَذِهِ نَزَلَتْ لَمَّا : قَالَ ، عَلِيٍّ عَنْ ؟ أَيُّهَا يَا} : تَعَالَى اللَّهُ فَأَنْزَلَ لَوَجَبَتْ ، نَعَمْ : قُلْتُ وَلَوْ ، لاَ : فَقَالَ ؟ عَامٍ كُلِّ أَفِي : قَالُوا ثُمَّ : قَالَ ، فَسَكَتَ ؟ عَامٍ كُلِّ أَفِي : فَقَالُوا ، فَسَكَتَ تَسْأَلُوا لاَ آمَنُوا الَّذِينَ {تَسُؤْكُمْ لَكُمْ تُبْدَ إِنْ أَشْيَاءَ عَنْ تَسْأَلُوا لاَ آخِرِ إِلَى الآيَةِ. رواه أحمد في مسنده 917.

ዐሊይ ኢብኑ አቢ-ጧሊብ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዲህ ይላል፡- "‹‹ ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው፡ ›› የሚለው አንቀጽ በወረደ ጊዜ፡ ሶሓቦችም ‹‹የአላህ መልክተኛ ሆይ! በየዓመቱ ነውን?›› ብለው ሲጠይቁ፡ እሳቸውም ዝም አሉ፡፡ እነሱም በድጋሚ፡- ‹‹በየዓመቱ ነውን?›› ሲሉ ዝም ተባሉ፡፡ ለሶስተኛ ጊዜ ጥያቄውን በመድገም ‹‹በየዓመቱ ነውን?›› ሲሉ፡ የአላህ መልክተኛም፡ ‹‹አይደለም! አዎ ብያችሁ ቢኾን ኖሮ፡ ግዳጅ ይኾንባችሁና እናንተም አትችሉም

ነበር›› በማለት መለሱ፡፡ ወዲያውኑ አላህም፡- ‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ለእናንተ ቢገለጹ ከሚያስከፏችሁ ነገሮች አትጠይቁ›› የሚለውን አንቀጽ አወረደው" (ሙስነድ ኢማሙ አሕመድ 917)፡፡

ከዚህ ሐዲሥ በግልጽ እንደምንረዳው፡- ሰዎቹ አላህ በናንተ ላይ ሐጅን ግዳጅ አድርጎባችኋልና፡ ግዳጃችሁን ፈጽሙ! ተብለው ከታዘዙ፡ ሰምተናል ታዘንማል በማለት ቀጥታ ግዳጅ የተደረገባቸውን ነገር በአላህ እገዛ ለመፈጸም መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ነው፡፡ እነሱ ግን ‹‹በየዓመቱ ነውን?›› በማለት ሌላ ጥያቄን አስከተሉ፡፡ በየዓመቱ ማድረግ ግዳጃቸው ቢኾን ኖሮ፡ ከመነሻውም አላህ ይነግራቸው ነበር፡፡ ለነሱ እዝነት ተብሎ በዝምታ ሲታለፍላቸው፡ የታዘዙትን ከመፈጸም ይልቅ፡ ያልታዘዙትን ነገር በመፈላፈል በየዓመቱ ነው ወይ የምናደርገው? ብሎ መጠየቃቸው አግባብ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም፡ በጥያቄያቸው መሰረት ‹አዎን!› የሚል ምላሽ ቢሰጣቸው ኖሮ ጉዳዩ ከአቅም በላይ ኾኖ ይከብዳቸውና ጭራሹንም ህጉን በመተው ኃጢአት ውስጥ ይገቡ ነበር፡፡ ለዚህ ነው ኋላ ላይ ከአቅም በላይ ኾኖ እንዳይከፋችሁ፡ ከወዲሁ ባልታዘዛችሁት ነገር ላይ ጥያቄን በማንሳት አታብዙ የተባሉት፡፡

ከኛ የሚጠበቀው የታዘዘውን በአግባቡ መፈጸም እንጂ፡ ጥያቄ በማብዛት በራሳችን ላይ ግዳጅን መጫንና ኋላ ለመፈጸም ሲከብደን ሕጉን ተመልሰን በመካድ ከአጥፊዎች ለመኾን አይደለም፡፡ ቀጣዩ ሐዲሥም ጉዳዩን የበለጠ ያብራራዋል፡-

فَلاَ حُرُمَاتٍ وَحَرَّمَ تُضَيِّعُوهَا فَلاَ فَرَائِضَ فَرَضَ وَجَلَّ عَزَّ اللَّهَ إِنَّ » -وسلم عليه الله صلى- اللَّهِ رَسُولُ قَالَ قَالَ الْخُشَنِيِّ ثَعْلَبَةَ أَبِى عَنْ عَنْهَا تَبْحَثُوا فَلاَ نِسْيَانٍ غَيْرِ مِنْ أَشْيَاءَ عَنْ وَسَكَتَ تَعْتَدُوهَا فَلاَ حُدُودًا وَحَدَّ تَنْتَهِكُوهَا 4445 الدارقطني رواه. عَنْهَا

ከአቢ ሠዕለበህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "ኃያሉ አላህ ግዴታዎችን ደንግጓልና አታባክኑአቸው (ፈጽሙ)፣ ሐራም ነገራትንም ከልክሏልና አትጣሷቸው (አትዳፈሩ)፣ ድንበርን አበጅቷልና ወሰንን አትለፉ፣ አንዳንድ ነገራትን ደግሞ ረስቶ ሳይኾን ለናንተው በማዘን በዝምታ አልፏቸዋልና፡ ስለነሱ አትፈላፈሉ (አጥብቃችሁ አትጠይቁ)" (ዳረቁጥኒይ 4445)፡፡

ከዚህ በፊት የነቢዩላህ ኧሊሕ (ዐለይሂ-ሰላም) ሕዝቦች፡ ነቢያቸውን ኧሊሕን፡ አላህ ግመልን ከቋጥኝ ስር እንዲያወጣላቸው፡ የሱንም ነቢይነት አረጋግጠው እንዲያምኑ በመፈለግ ጥያቄን አቀረቡለት፡፡ እሱም ጌታውን አላህ በመለመን፡ ለነቢይነቱ ምልክት የምትኾነው ግመልም ተሰጠችው፡፡ ከተአምሩ በኋላ ግን፡ የኧሊሕ ሕዝቦች እንኳን ሊያምኑ፡ ግመሊቷንም በመውጋት ገደሏት፡፡ ከመጨረሻው ዓለም (ከአኼራ) ቅጣት በፊትም በዱንያ ቅጣት አላህ አጠፋቸው (ሱረቱ ሁድ 11፡64-68፣ ሱረቱ-ሹዐራእ 26፡ 141-159፣ ሱረቱ-ሸምስ 93፡11-15)፡፡ የማይፈጽመውን ነገር በመጠየቅ እራሱ ላይ ግዳጅን ያመጣና ኋላም ኃጢአት ውስጥ እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ ነው መልእክቱ!!

በዚህ ዙሪያ የቅዱስ ቁርኣን ተንታኞችን (ሙፈሲሮች) ማብራሪያ በማቅረብም ብዙ ማለት ይቻል ነበር፡፡ ግን ጽሑፍ መብዛቱ (ይህም በዝቷል) አንባቢን ስለሚያሰለች፡ በዚህ ላብቃ፡፡ አላህ የበለጠውን እውነታ ዐዋቂ ነው፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

የዓኢሻ (ረ.ዓ.) ቤት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

9፥33 የአላህን ብርሃን በአፎቻቸው ለማጥፋት ይፈልጋሉ፤ አላህም ከሓዲዎች ቢጠሉም እንኳ ብርሃኑን መሙላትን እንጅ ሌላን አይሻም፡፡

መግቢያ

መቼም ሚሽነሪዎች የኢስላም ብርሃን በምን እናጠልሽው ብለው ከተነሱ ጊዜያት አለፉ፤ የኢስላምን መሰረትና ውቅር፣ ዋልታና ማገር፣ ጥልቀትና ስፋት፣ ድርና ማግ በቅጡ ያልተረዱ ስለሆኑ መደበኛ በሆነ መርሃ-ግብርና መዋቅር ከመማር ይልቅ ጎግል ላይ በሰፈረው የተሳቃቀመ ጥራዝ-ነጠቅ መረጃ ድምዳሜ ላይ ሲደርሱ ማየት እጅጉን ያማል፣ አንዱ ሚሽነሪ፡- ነብያችንን"ﷺ" የዓኢሻ"ረ.ዓ." ልብስ ሲለብሱ እና ከእርሷ ጋር ተራክቦ ሲያደርጉ ብቻ ነው ወህይ የሚወርድላቸው ብሎ በትክክል እንኳን ማንበብ የማይችለውን ጩቤ ጥቅስ ጠቅሶ የጨባራ ለቅሶ እና ተስካር የሆነው ውሃ የማይቋጥ ሙግት ሲሟገተኝ ነበር፤ ይህ ስሁት የሆነ ሙግት ሳይርቅ በቅርቡ ሳይደርቅ በእጥቡ ሳይቃጠል በቅጠል እንደሚባለው ከመነሻው አከርካሪውን መመታት አለበት፤ እስቲ ሐዲሱን እንመልከት፡-

ኢማም ቡኻሪይ መጽሐፍ 51 , ሐዲስ 16:

ሂሻም ኢብኑ ኡርዋህ ከዓኢሻ"ረ.ዓ." እንደተረከው....የአላህ መልእክተኛ"ﷺ" ለኡሙ ሰላማ"ረ.ዓ." በአይሻ ጉዳይ አታስቸግሪኝ፤ ወላሂ ከማናቸውም ሴቶች ልብስ ውስጥ ወህይ አይመጣልኝም "ከአይሻ ልብስ በስተቀር አሏት"፤ لاَ " لَهَا فَقَالَ عَائِشَةَ، فِي تُؤْذِينِي لاَ ، وَأَنَا يَأْتِنِي فِي ثَوْبِ امْرَأَةٍ إِلاَّ عَائِشَةَ " ::

ምን ያህት ቅጥፈት እንዳለ ተመልከቱ፤ እዚህ ሐዲስ ላይ የዓኢሻ"ረ.ዓ." ልብስ ለበሱ የሚል የት አለ? ከዓኢሻ"ረ.ዓ." ጋር ተራክቦ ሳደርግ የሚል የት አለ? ወህይ የሚመጣልኝ ከአይሻ ልብስ ውስጥ ብቻ ነው የሚል የት አለ? ይህ ሁሉ ገለባ ሂስ ነው፤ ነብያችን ወህይ የሚመጣላቸው በተለያየ ሁኔታ ቢሆንም ከሌሎች ባለቤቶታቸው ይልቅ የዓኢሻ"ረ.ዓ." ቤት እያሉ ብቻ ነው ወህይ የሚመጣላቸው ማለት "ይልቅ" የሚለው ማነፃፀሪያ ከሴቶቹ ጋር እንጂ አጠቃላይ አይደለም፤ "ሠውብ" ثَوْب የሚለው ቃል በብዙ ይመጣል፡-

"ሂጃብ" حِجَاب "መጋረጃ"፣

"ፊራሽ" فِرَاش ምንጣፍ"፣

"ሊሃፍ" لِحَاف "ፍራሽ"

"በይት" بَيْت "ቤት"

"ሊባሥ" لِبَاس "ልብስ" በሚል ይመጣል፤ ይህንን በተለያዩ ነጥቦች ማየት ይቻላል፡-

ነጥብ አንድ

"ሊሃፍ"

"ሊሃፍ" لِحَاف የሚለው ቃል "ፍራሽ" ማለት ሲሆን "ከአይሻ ልብስ በስተቀር" የሚለው "ከአይሻ ፍራሽ በስተቀር" በሚለው መጥቷል፡-

ኢማም ቡኻሪይ መጽሐፍ 62 , ሐዲስ 122:

ኡሙ ሰላማ ሆይ በአይሻ ጉዳይ አታስቸግሪኝ፤ ወላሂ ከማናቸውም ሴቶች ፍራሽ ውስጥ ወህይ አይመጣልኝም “ከአይሻ ፍራሽ በስተቀር” “ غَيْرِ هَا مِنْكُنَّ امْرَأَةٍ لِحَافِ فِي وَأَنَا الْوَحْىُ عَلَىَّ نَزَلَ مَا وَاللَّهِ فَإِنَّهُ عَائِشَةَ، فِي تُؤْذِينِي لاَ سَلَمَةَ أُمَّ يَا ”. ۚ

ነጥብ ሁለት

“በይት”

“በይት” بَيْت ማለት “ቤት” ሲሆን “ከአይሻ ልብስ በስተቀር” የሚለው “ከአይሻ ቤት” በሚለው መጥቷል፤ ቤት የሚከፋፈለው በመጋረኛ ስለሆነ “ሠውብ” የሚለው በሌላ ሪዋያ ላይ “በይት” بَيْت “ቤት” በሚል መጥቷል፦

ኢማሙ አህመድ መጽሐፍ 6 ሐዲስ 293

የአላህ መልእክተኛም”ﷺ” አሉ፦ ኡሙ ሰላማ ሆይ በአይሻ ጉዳይ አታስቸግሪኝ፤ ወላሂ ከማናቸውም ሴቶች ቤት ውስጥ ወህይ አይመጣልኝም ከአይሻ ቤት በስተቀር፤ على نزل ما والله فإنه عائشة في تؤذيني لا سلمة أم يا قال ثم سلم و عليه الله صلى الله رسول عائشة غير نسائي من امرأة بيت في وأنا الوحي ::

ነጥብ ሶስት

“ሊባሥ”

“ሊባሥ” لِبَاس ማለት ትርጉሙ “ልብስ” ማለት ሲሆን “ሠውብ” ማለት “ሊባሥ” ነው ብንል እንኳን “ልብስ” የሚለው ቃል ሁልጊዜ ሱሪን፣ ቀሚስን፣ ጃኬትን ብቻ ሳይሆን የሚያመለክተው መጠለያን፣ መከለያ፣ መሸሸጊያ ለማመልከት ይመጣል፤ አምላካችም አላህ ለምሳሌ ሴት የወንድ ልብስ ናት ወንድ የሴት ልብስ ነው ይለናል፦

2፥187 በጾም ሌሊት ወደ ሴቶቻችሁ መድረስ ለእናንተ ተፈቀደላችሁ። እነርሱ ለእናንተ “ልብሶች” ናቸው፤ እናንተም ለእነርሱ “ልብሶች” ናችሁ لَّهُن لِبَاسٌ وَأَنتُمْ لَّكُمْ لِبَاسٌ هُنَّ ۗ نِسَآئِكُمْ إِلَىٰ ٱلرَّفَثُ ٱلصِّيَامِ لَيْلَةَ لَكُمْ أُحِلَّ ::

መቼም ልብስ የሚለውን አንዱ የአንዱ መሸሸጊያ ማለት እንጂ አንዱ የአንዱ ጃኬት ወይም ቀሚስ አሊያም ሱሪ ማለት ነው የሚል ቂል የለም፤ አላህ ሌሊትን ልብስ አደረገ፤ ያ ማለት “መጠለያ” ማለት ነው፦

25:47 እርሱም ያ ለእናንተ “ሌሊትን” ልብስ፣ እንቅልፍንም ማረፊያ ያደረገ፤ ቀንንም መበተኛ ያደረገላችሁ ነው وَهُوَ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُمُ ٱلَّيْلَ لِبَاسًا وَٱلنَّوْمَ سُبَاتًا وَجَعَلَ ٱلنَّهَارَ نُشُورًا ::

78:10 ሌሊቱንም ልብስ አደረግን لِبَاسًا ٱلَّيْلَ وَجَعَلْنَا ::

ይህንን ካየን ነብያችን”ﷺ ፦“ከማናቸውም ሴቶች ልብስ ውስጥ ወህይ አይመጣልኝም ከዓኢሻ”ረ.ዓ.” ልብስ በስተቀር” ሲሉ ከዓኢሻ”ረ.ዓ.” ፍራሽ ወይም ቤት ማለታቸው እንደሆነ እሙንና ቅቡል ነው እንጂ ቃላትን ማንሸዋረር እና ማውረግረግ አይቻልም። እንዴት የአንድ ሴት ልብስ ውስጥ አንድ ወንድ ቃል በቃል ሊገባስ ይችላል? ይህ ሆን ተብሎ ድርቅና አላህ በትንሣኤ ቀን በዚያ በእርሱ ትወዛገቡበት በነበራችሁት ሁሉ በመካከላችሁ ይፈርዳል፦

18፥68-69 ቢከራከሩህም «አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው» በላቸው፡፡ አላህ በትንሣኤ ቀን በዚያ በእርሱ ትወዛገቡበት በነበራችሁት ሁሉ በመካከላችሁ ይፈርዳል፡፡

✍ከወንድም ወሒድ ዑመር

ወሰላሙ አለይኩም

አዳም ላጠፋው ጥፋት ንሰሃ ገብቶ እግዚአብሄርን ይቅር እንዳለው ያውቃሉን?

ብዙ ክርስቲያኖች አዳም ላጠፋው ጥፋት ይቅርታ እንዳልጠየቀና እግዚያብሄርም እንዳልማረው ያምናሉ: ሆኖም ግን የተዋህዶ ክርስቲያኖች የአምላክ ቃል ነው ብለው የተቀበሉት መጽሃፈ መቃብያን ሳልስ እግዚያብር የአዳምን ሃጢአት አዳም ንሰሃ ስለገባና ስለ ሃጢአቱ ስላለቀሰ ይቅር እንዳለው እንደማረው በሰፊው ይናገራል!

እውነታውን ለመረዳት ቀጥሎ ያለው የመጽሃፍ ቅዱስ ቃል ያንብቡ! [መጽሃፈ መቃብያን ሣልስ:ምእራፍ 4: አንቀጽ 1-35]

☞" ጌታውም አዳምን ይቤዝው ዘንድ አለው ..... አንተም ታበይህ ዲያብሎስም ተባልከ ሰራዊቶችህም ኢጋንንት ተባሉ ..... ነገር ግን እ/ር በሚፈሩትና ስለ ሃጢአታቸው ጩኸው በሚያለቅሱ ደስ ይለዋል: አንተ በንሰሃ መናዘዝ ተሳነህ: ያ መሬት ግን ስለሃጢአቱ በእ/ር ፊት ፈጽሞ እያለቀሰ በንሰሃተመለሰ..... ያ አመድና መሬት የሆነ ድሃ ግን በልቅሶና በእንባ ወደ ንሰሃ ወደ ሰላምና ወደ ትህትና መንገድ ተመለሰ:: አንተስ ለፈጠረህ ለእ/ር ራስህንና የልብህን ቀፈት አላዋረድከም:: እርሱ ግን በበደለው በደል ራሱን አዋርዶ ተናዘዘ አልታበየምም ..... በድሎ በንሰሃ የማይናዘዝ ሰው ከቀድሞ በደሉ ይልቅ በደሉን ያከፋልና ነገር ግን በድሎ በፈጣሪው በእ/ር ፊት የሚናዘዝና የሚያለቅስ እርሱ በእውነት ንሰሃ ገባ: የጌታውንም ልብ ያራራ ዘንድ የመዳኑን መንገድ አገኘ: በጌታውም ፊት ተናዘዘ: ጌታውም በባርያው ላይ ይቆጣ ዘንድ ቀድሞ ከመከረበት ያቃልልለታል: በብዙ ንሰሃና ስግደት ተናዞአልና: የቀደመ ሃጢአቱንም ይቅር ይለዋል: ወደ ቀደመ በደሉም ካልተመለሰ ይህንም ካደረገ ይህ ፍጹም ንሰሃ ነው: አዳምስ ፈጣሪውን ማሰብንና ለፈጣሪው መናዘዝን አልዘነጋም: አንተም ለፈጣሪህ በንሰሃ ተናዘዝ:..." [መጽሃፈ መቃብያን ሣልስ:ምእራፍ 4: አንቀጽ 1-35]

አዳም ንሰሃ ገብቷል እግዚያብሄርም ይቅር ብሎታል:: ይህም በመሆኑ እየሱስ አዳም ያመጣውን ሃጢአት ለመሰረዝ ተሰቀለ ቢባል ቅጥፈት ይሆናል!

ማነው የጨዋይቱ ልጅ? ማንስ ነው የባሪያይቱ ልጅ?

▶አስደንጋጩ የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሀረግ በመፅሃፍ ቅዱስ አንዳንድ ክርስቲያን ወገኖች እንዲህ ሲሉ ይናገራሉ፦

▶ እኛ ክርስትያኖች የጨዋይቱ(የሳራ) ልጆች የይስሀቅ ዘሮች ነን : እናንተ ሙስሊሞች ደግሞ የባሪያይቱ (የአጋር ወይም ፣ የሀጀር)ልጆች የኢስማኤል ዘሮች ናችሁ ብሎ ያለ እውቀት ለመመፃደቅ ይሞክራሉ አለማወቁ እና መፅሃፉን አለማንበቡ ነው እንጂ እንኳን እናንተ የጨዋይቱ ልጆች ክርስትያን ነን ልትሉ ይቅርና አምላኬ፣ጌታዬ፣አዳኜ፣ፈጣሪዬ ወዘተ.... ብላቹ የምታመልኩት ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የዘር ሀረግ መነሻው የባሪያ ዝርያ እንዳለበት መፅሃፍ ቅዱስ ያስረዳናል ። ይህንንም ስናወራ ዝም ብለን በጥላቻ

እና በጭፍን ያለ እውቀት ሳይሆን ከራሳቹ የእምነት መፅሃፍ ከሆነው ከመፅሃፍ ቅዱስ የኢየሱስ የዘር ሃረግ የባሪያይቱ እንደሆነ በማስረጃ ላስቃኛቸሁ።

አደራ አደራ ማስረጃዎቼን በበጎ ህሊና ደጋግማቹ አንብቡት እና ራሳቸሁን ጠይቁ ከህሊናቹ ጋ አውሩበት።በመፅሀፍ ቅዱስ መሰረተ የእየሱስ የዘር ሀረግ ወደላይ ሲቆጠር የእየሱስ የዘር ሀረግ ውስጥ ባርያ እንዳለበት ያውቁ ኑሯል??

ይህ ብቻ ሳይሆን የእየሱስ የዘር ሀረግ ከላይ መነሻውን ስናይ የነቢዩ የሎጥ ልጆች ከገዛ አባታቸው የወለዱት ልጅ የእየሱስ የዘር ሀረግን እንደሚነካስ ያውቃሉ?

በባይብል መሰረት የሞዓብ ዘሮች ዘራቸው የመጣው የሉጥ ሁለቱ ሴት ልጆቹ ከራሳቸው አባት ከነቢዩ ሉጥ የወለደቸው ከሞዓብ ነው ኦሪት ዘፍጥረት 19 : 36-37 የሎጥም ሁለቱ ሴቶች ልጆች ከአባታቸው ፀነሱ።

ታላቂቱም ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም ☞#ሞዓብ ብላ ጠራችው፤ እርሱም እስከ ዛሬ የሞዓባውያን_አባት ነው።

ተመልከቱ እንግዲህ ሞአብ ማለት አባትና ልጅ በአፀያፊ ዝሙት የወለዱት ልጅ ነው። እንቀጥል አይደል?

☞ከሞአብ ዘር ውስጥ ደግሞ ሩት የምትባል ሴት ባርያን እናገኛለን። ሩት ማለት የሞዓብ ዘር ባሏ የሞተባት እናም አገልጋይ ባርያ ነች (ሩት 3:9) ላይ ተመልከቱ

የቤቴልሄም ምድር ባለርስት የሆነው ቦዔዝ ባርያ የሆነችውን ሩት ተገናኘ (ሩት 3:9) እናም አገባት።.ቦዔዝም ሩትን ወሰደ፥ ሚስትም ሆነችው፤ ደረሰባትም፥ እግዚአብሔርም ፅንስ ሰጣት፥ ወንድ ልጅም ወለደች። መጽሐፈ ሩት 4 : 13 ተመልከት ባሪያዋ ሩት ከቦኤዝ ወንድ ልጅ ወለደች ይለናል;:

እስኪ እንቀጥል ...

ቦዔዝ እና ሩት በመቀጠል ኢዮቤድ የሚባል ልጅ አገኙ። ኢዮቤድ የእስራኤል የዘር መስመር መስራች ሆነ። መጽሐፈ ሩት (4 : 17-22)

የእስራኤል መስራች ማን ሆነ ይለናል? አዎ ኢዮቤድ እሺ ኢዮቤድ የማን ልጅ ነው አባቱ ቦኤዝ እናቱ ደግሞ ባሪያዊት ሩት

እስኪ እንቀጥል ....

ሴቶችም ጎረቤቶችዋ፥ ለኑኃሚን ወንድ ልጅ ተወለደላት እያሉ ስም አወጡለት፤ ስሙንም ኢዮቤድ ብለው ጠሩት። እርሱም የዳዊት አባት የእሴይ አባት ነው።

የፋሬስም ትውልድ ይህ ነው፤ ☞ ፋሬስ ኤስሮምን ወለደ፥ ☞ ኤስሮምም አራምን ወለደ፥ ☞ አራምም አሚናዳብን ወለደ፥ ☞ አሚናዳብም ነአሶንን ወለደ፥ ☞ ነአሶንም ሰልሞንን ወለደ፥ ☞ ሰልሞንም ቦዔዝን ወለደ ☞ ቦዔዝም ኢዮቤድን ወለደ፥ ☞ ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፥ ☞ እሴይም ዳዊትን ወለደ። እዚህ ጋ ልብ በሉልኝ ነቢዩ ዳዊትን ማቴ 1:1 ላይ የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ የማን ዘር ነው አለ? አዎ ኢየሱስ ክርስቶስ የዳዊት ዘር ነው ይለናል።

እሺ ዳዊትስ የማን ዘር ነው አለን? ደዊት ደግሞ የኢሴይ አባት ነው። ስለዚህ ኢሴይ ራሱ ዘሩን ወደኋላ ስንቆጥር ሩት የምትባል ባሪያ ሴት እናገኛለን ደግመን ወደኋላ ስንሄድ ነቢዩ ሎጥ በመጠጥ ተገፈፍቶ ከሁለት ሴት ልጆቹ በዝሙት የተወለዱ ናቸው ማለት ነው።

ይህ ማለት የእየሱስም ሆነ የዳዊት ሀረግ የሚነሳው ከዚሁ ከ ነቢዩ ሎጥ (ነቢዩ ሉጥ ከራሱ ሴት ልጅ በዝሙት ከወለዳቸው ልጆቹ) ነው ማለት ነው የዘር ሀረጉ የሚነሳው(የሚጀምረው)።በተጨማሪም በዘር ግንድ ውስጥ ሩት የምትባል ባርያን እናገኛለን።

እንግዲ ተመልከቱ የእስራኤሎች ዘር በጠቅላላ እየሱስንም,ነቢዩ ዳዊትንም ወዘተ ... ጨምሮ የተነሳው ሎጥ ከልጁ ጋር በፈፀመው ግብረ ስጋ ግኑኝነት አማካኝነት በተወለዱ ልጆች ሲሆን በተጨማሪም በዚህ የዘር ሀረግ መሰረት ከአንድ ባርያ (ሩት) ተብላ ከምትጠራ ሚስት ነበር። ይህች ባርያ የዘር ሀረግ መነሻውን አውራ ቦታውን ነው የያዘችው;;

ታድያ የቱ ጋ ነው የጨዋይቱ ልጆች የሆናችሁት? እስኪ አንተ መፅሃፍ ቅዱስን ምታነብ ከሆነ በማስረጃ አስተባብል?

እስኪ ሌላ ቀላል ማስረጃ ከባይብል ላቅርብ ያእቆብ አራት ሚስት እንደነበረው መፅሃፍ ቅዱስ ይነግረናል።

እነሱም

☞ ሊያ አሪት ዘፍጥረት29-22፡23

☞ ራሄል አሪት ዘፍጥረት 29፡28 ራሄል

☞ባሪያ ሴት ባላን አሪት ዘፍጥረት 30፡4

ሌላ ሴት ዘለፋ አሪት ዘፍጥረት 30፡9 ተመልከት እንግዲህ ከእነዚህ አራት ሴቶች 12 የእስራኤል ልጆች ተወለዱ ይለናል አሪት ዘፍጥረት 35፡23-26 ላይ አሪት ዘፍጥረት 35 : 23 ላይ

☞የሊያ ልጆች፤ የያዕቆብ በኩር ልጅ ሮቤል፥ ስምዖን፥ ሌዊ፥ ይሁዳ፥ ይሳኮር፥ ዛብሎን፤

☞የራሔል ልጆች፤ ዮሴፍ፥ ብንያም፤

☞የራሔል ባርያ የባላ ልጆችም፤ዳን፥ ንፍታሌም፤

☞የሊያ ባሪያ የዘለፋ ልጆችም፤ ጋድ፥ አሴር፤ እነዚህ በሁለቱ ወንዞች መካከል በሶርያ የተወለዱለት የያዕቆብ ልጆች ናቸው።

እንግዲህ ተመልከቱ እነዚህ 12 ልጆች እስራኤልን ፈጠሩ ይለናል አሪት ዘጸአት 1፡1-9። ከ12 ልጆች ውስጥ አራቱ ከባርያ ከነበሩት ሚስቶቹ የተወለዱት ናቸው።

ይህ የሚያሳየን የእስራኤል አንድ ሶስተኛ (1/3) ህዝብ (ዳዊትን ኢየሱስ ክርስቶስን ጨምሮ) የነዚህ ባርያ ሴቶች ልጆች ናቸው ማለት ነው፡፡ስለዚህ አንድ ሶስተኛው የእስራኤል ህዝብ ተነስቶ ህጋዊ አይደለንም ይበሉ ።

እስራኤል ውስጥ ከአራቱ ባርያ ሴቶች ዘር እንዳለበት ለማረጋገጥ እነዚህን ጥቅሶች እንመልከት

መጽሀፈ ዜና መዋዕል 7፡12 7፡13 7፡30

በተጨማሪም ከባርያ የተወለደው የአሸር ዝርያ ከሌሎች ወንድሞቹ የበለጠ እንደሚበዛ ያስረዳል። መጽሀፈ ዜና መዋዕል 7፡40

ከባርያ ሴት የሚወለድ ሰው እንደ ልጅ ካልተቆጠረ ስለዚህ ከእነዚህ ባርያ ሴቶች የሚወለዱት የእስራኤል አንድ እንደ ልጅ አይቆጠሩም ማለት ነውን??

ስለዚህ ክርስትያን ወገኖቻችን "አመድ በዱቄት ይስቃል" እንደሚባለው ዝም ብላቸው ያለ እውቀት እኛ የጨዋይቱ ልጆች ነን እናንተ(ሙስሊሞች) የባሪያይቱ ልጆች ናችሁ የምትለዋ መፈክር ከአሁኑዋ ሰዓት ጀምሮ በማስረጃ ያውም ከመፅሃፍ ቅዱስ እውነቱን አይተናል ::ስለዚህ ወገኖቼ እናምብብ ፣እንመራመር፣ አይምሯችንን እናሰራው ዘመኑ እውቀት እና የማስረጃ ነው ።

የአደም ሚስት ሥሟ ማነው?

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2)። የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)።

ሰሞኑን አንዳንድ ‹ወገኖች› በቅዱስ ቁርአን ላይ ከከፈቱት ዘመቻዎች ውስጥ አንዱ ይህ ነው። እሱም፡- በቅዱስ ቁርአን ውስጥ ስማቸው ያልተጠቀሱ የነቢያት ቤተሰቦችን (ሚስት፣ ልጅ እና ወላጆች) በማንሳት፡ የእንትና ባለቤት፣ ልጅ፣ ወላጆች ማናቸው ሥማቸው? በማለት ጥያቄን ያቀርባሉ። በምላሹም፡- የእገሌ ሚስት ወይም ልጅ ወይም ወላጆች ሥማቸው በቁርአን ላይ አልተዘከረም! የሚል ምላሽ ሲሰጣቸው፡ የነሱም አጸፌታ፡- እንግዲያውስ ቅዱስ ቁርአን ሙሉ መጽሐፍ አይደለም። ታሪክን አጉድሎ ነው የሚያቀርበው! በማለት ክስ ያቀርባሉ። እኛም ለዚህ ትርጉም አልባ ክስ መጠነኛ ምላሽን እንካችሁ ብለናል። አላህ እውነቱን ይገልጽልን፡-

1ኛ/ ከሁሉ በፊት ሊታወቅ የሚገባው ነገር ቢኖር ቅዱስ ቁርአን የእምነት እና የህግ መጽሐፍ እንጂ የታሪክ መጽሐፍ አለመሆኑን ነው። የቅዱስ ቁርአን ዋና የመውረድ ዓላማ፡ ለሰዎች የነቢያትን ቤተሰቦች ሥም ዝርዝር፣ የትውልድ ቦታና ሀገር፣ የትዳር ሁኔታና በዱንያ ላይ ስንት ዓመት እንደቆዩ ለማስተማር የመጣ መጽሐፍ አይደለም። የቁርአን ዋና ተልእኮው ሰውን ማናገር ነው። ሰው እራሱን ፈልጎ እንዲያገኝ መርዳት ነው ዓላማው። እሱም፡- ማን እንደፈጠረው፣ ለምን ዓላማ እንደተፈጠረ፣ በምድራዊ ሕይወቱ የአምላኩን ህግ ጠብቆ እንዴት መኖር እንዳለበት፣ ይህ ምድራዊ ሕይወት ዘለቄታ የሌለውና በሞት የሚያከትም መሆኑን በመግለጽ ለመጪው ዓለም እራሱን እንዲያዘጋጅ ትልቅ ኃላፊነትን ማሸከም፣ በአላህ ራሕመት፡ በመልካም ሥራ ሰበብ በመሆን ለጀነት ብቁ እንዲሆንና፡ ከጀሀነም እሳት ደግሞ እንዲርቅ ከኃጢአት ማስጠንቀቅ ነው ዓላማው። ቀጣዮቹ አንቀጾች ይህንን እውነታ ፍንትው አድርጎ ያስረዳሉ፡-

" إبراهيم سورة " الْأَلْبَابِ أُولُو وَلِيَذَّكَّرَ وَاحِدٌ إِلَهٌ هُوَ أَنَّمَا وَلِيَعْلَمُوا بِهِ وَلِيُنْذَرُوا لِلنَّاسِ بَلَاغٌ هَذَا 52

"ይህ (ቁርአን) ለሰዎች ገላጭ ነው፡፡ (ሊመከሩበት)፣ በእርሱም ሊስፈራሩበት፣ እርሱም አንድ አምላክ ብቻ መኾኑን ሊያውቁበት፣ የአእምሮ ባለቤቶችም ሊገሰፁበት (የተወረደ) ነው፡፡" (ሱረቱ ኢብራሂም 14፡52)፡፡

" النحل سورة " لِلْمُسْلِمِينَ وَبُشْرَى وَهُدًى آمَنُوا الَّذِينَ لِيُثَبِّتَ بِالْحَقِّ رَبِّكَ مِنْ الْقُدُسِ رُوحُ نَزَّلَهُ قُلْ 102

"እነዚያን ያመኑትን ለማረጋጋት ሙስሊሞቹንም ለመምራትና ለማብሰር (ቁርአንን) ቅዱሱ መንፈስ (ጂብሪል) እውነተኛ ሲኾን ከጌታህ አወረደው በላቸው፡፡" (ሱረቱ-ነሕል 16፡102)፡፡

" كَبِيرًا أَجْرًا لَهُمْ أَنَّ الصَّالِحَاتِ يَعْمَلُونَ الَّذِينَ الْمُؤْمِنِينَ وَيُبَشِّرُ أَقْوَمُ هِيَ لِلَّتِي يَهْدِي الْقُرْآنَ هَذَا إِنَّ 9 الإسراء سورة

"ይህ ቁርአን ወደዚያች እርሷ ቀጥተኛ ወደ ኾነችው መንገድ ይመራል፡፡ እነዚያንም በጎ የሚሠሩትን ምእመናን ለእነሱ ታላቅ ምንዳ ያላቸው መኾኑን ያበስራል፡፡" (ሱረቱል ኢስራእ 17፡9)፡፡

2ኛ/ ቅዱስ ቁርአን የነቢያትን ታሪክ በሰፊው ይነግረናል፡፡ ኾኖም የሚተርክልን ታሪክ ከእምነታችን ጋር የሚገናኘውን፣ በምድራዊ ሕይወታችን አርአያ የሚሆነንን፣ ለዘለቄታዊ ሕይወት ደግሞ ጠቀሜታ ያለውን ጎን በማንሳት እንጂ፡ ማወቁም ሆነ አለማወቁ ጥቅምና ጉዳት የሌለውን ክፍል አይደለም፡፡ ቁርአን የነቢያትን ታሪክ ሲነግረን፡- ነቢያት በጠቅላላ ስለ እውነተኛው አምላክ አላህ ሊመሰክሩና እሱን በብቸኝነት ማምለክ እንደሚገባ ሕዝቦቻቸውን ሊያስተምሩ፣ በተጨማሪም ያመነና ጌታውን የታዘዘ ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት ለዘላለማዊ ጀነት እንደሚታጭ ለማበሰር፣ የካደና ከጌታው ትእዛዝ የወጣ ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት ለዘላለም ስቃይ እንደሚዳረግ ለማስጠንቀቅ እንደተላኩ ነው፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" الطَّاغُوتَ وَاجْتَنِبُوا اللَّهَ اعْبُدُوا أَنِ رَسُولًا أُمَّةٍ كُلِّ فِي بَعَثْنَا وَلَقَدْ... النحل سورة " 36

"በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ «አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ» በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል…" (ሱረቱ-ነሕል 16፡36)፡፡

" فَاعْبُدُونِ أَنَا إِلَّا إِلَهَ لَا أَنَّهُ إِلَيْهِ نُوحِي إِلَّا رَسُولٍ مِنْ قَبْلِكَ مِنْ أَرْسَلْنَا وَمَا 25 الأنبياء سورة

"ከአንተ በፊትም እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም፡፡" (ሱረቱል አንቢያእ 21፡25)፡፡

" حَكِيمًا عَزِيزًا اللَّهُ وَكَانَ الرُّسُلِ بَعْدَ حُجَّةٌ اللَّهِ عَلَى لِلنَّاسِ يَكُونَ لِئَلَّا وَمُنْذِرِينَ مُبَشِّرِينَ رُسُلًا 165 النساء سورة

"ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡" (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡165)፡፡

48 الأنعام سورة " يَحْزَنُونَ هُمْ وَلَا عَلَيْهِمْ خَوْفٌ فَلَا وَأَصْلَحَ آمَنَ فَمَنْ وَمُنْذِرِينَ مُبَشِّرِينَ إِلَّا الْمُرْسَلِينَ نُرْسِلُ وَمَا "

"መልክተኞችንም አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን እንጅ አንልክም፡፡ ያመኑና መልካምን የሠሩ ሰዎችም በእነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም፡፡" (ሱረቱል አንዓም 6፡48)፡፡

3ኛ/ የአንድ መጽሐፍ ምሉእነት የሚረጋገጠው፡ ለአንባቢዎቹ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው የተሟላ ጭበጥና ቁም-ነገር ነው፡፡ የነቢያትን ታሪክ ማወቅ የፈለገ ሰው፡- ነቢይነት ምንድነው? የማን ምርጫ ነው? ከማነው የሚመረጠው? ለምን ዓላማ ነው የሚመረጡት? ወዴት ነው የሚላኩት? ምን ሊያስተምሩ ነው? ከምንስ ሊያስጠነቅቁ ነው? ነቢይ መላክ የጀመረው መቼ ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች በቂ ምላሽን ካገኘ፡ መጽሐፉ የተሟላ ታሪክ አለው፡ አንባቢውም ሙሉ ዕውቀት አግኝቷል ይባላል፡፡

ኢስላም ደግሞ ከሌላው እምነት ለየት ባለ መልኩ በነቢያት ዙሪያ ከላይ ለተነሱት ጉዳዮች በቂ ማብራሪያን ይዟል፡፡ ታዲያ ምኑ ላይ ነው የታሪክ ጉድለት የሚኖርበት? የነቢያትን የትውልድ ዘመን? ቦታና ሀገር፣ የትዳር ሁኔታና የልጆች ብዛት፣ ስንት ዓመት እንደቆዩና እንደሞቱ ወዘተ መዘርዘር ነበረበትን? እውን ይህን ማወቅ ለእምነታችን ያለው የነላ ጠቀሜታ ምንድነው? አለማወቁስ ምን ጉዳት ያስከትላል? ነቢዩላህ ኢብራሂም (ዐለይሂ-ሰላም) ፈልስጢናዊ ይሁን ዒራቃዊ ለኛ ጥቅሙ ምንድነው? የኑሕ (ዐለይሂ-ሰላም) ልጆች ሶስት ይሁኑ አሥራ ሶስት ማወቁ ለእምነታችን ምን ይጠቅመናል? የዳዉድና የሱለይማን (ዐለይሂማ-ሰላም) ወላጆች ስማቸው ማን እንደሆነ ማወቁ በሚዛን ላይ የሚቀር መልካም ሥራ ነውን? ኧረ ወገን እየተስተዋለ!

4ኛ/ ወገኖቻችን እንደሚሉት፡ እነዚህ ዝርዝር ታሪኮች በቅዱስ ቁርአን ላይ አለመጠቀሳቸው፡ ቅዱስ ቁርአንን የተሟላ ታሪክ አልያዘም የሚያስብለው ከሆነ፡ የነሱ መጽሐፍስ ከዚህ ከስ የሚድን ይመስላቸዋልን ? ለምሣሌ፡- ጌታችንና መድሃኒታችን ነው የሚሉት የመርየም ልጅ የኾነውን ዒሳን (ዐለይሂ-ሰላም) ብንወስድ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከማርያም በድንግልና መወለዱን ይናገራል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ እስከ 12 ዓመቱ እንዴት እንዳደገ በዝርዝር አይናገርም፡፡ በ12ኛ ዓመቱም ከቤተሰቡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም አብሮአቸው እንደወጣና፡ ከነሱ ተሰውሮ ቤተመቅደስ ለሶስት ቀናት እንደቆየ ከአራቱ ወንጌላት አንዱ ይናገራል (ሉቃስ 2፡41-50)፡፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ እስከ 30 ዓመቱ ስላሳለፈው ሕይወት እንዴት እንደነበር የሚናገረው ነገር የለም፡፡ የማስተማር ሥራውንም የጀመረው ከዚህ በኋላ ነው (ሉቃስ 3፡23)፡፡ እንግዲያውስ ወንጌላትም የኢየሱስን ታሪክ በተሟላ መልኩ አላቀረቡትም ብለን እንደናንተው ክስ እናቅርብ? የእናቱን የመርየምንም (ዐለይሃ-ሰላም) ጉዳይ እናንሳ ብንል፡ መጽሐፍ ቅዱስ ወላጆቿ ማን እንደሆኑ አይናገርም፡፡ አስተዳደጓ ምን ይመስል ነበር? የሚለውንም ጉዳይ አያነሳውም፡፡ እሷን የሚገልጻት ከመልአኩ ጂብሪል (ገብርኤል) ዐለይሂ-ሰላም ወደሷ መላክና በድንግልናዋ ልጅን እንደምትወልድ ከማብሰር ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ታዲያ ከዚህ ክስተት በፊት ሕይወቷ ምን ይመስል ነበር? ለሚለው ጥያቄ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ምላሽ ማግኘት እንችላለን?

ማጠቃለያ፡-

የዚህ ጽሑፍ መነሻ ሀሳብ፡ በእናታችን ሐዋእ (የአደም ባለቤት) ሰበብ ነው፡፡ እሱም የአባታችን አደም (ዐለይሂ-ሰላም) ባለቤት እናታችን ሐዋእ (ዐለይሃ-ሰላም) መሆኗ በሁሉም ሙስሊሞች ዘንድ የታወቀና የታመነበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሥም በቅዱስ ቁርኣን በቀጥታ ባይወሳም፡ በነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሐዲሥ ውስጥ ግን ተጠቅሷል፡፡ (ቡኻሪይ፡ 3330፣ ሙስሊም 3723፣ ሙስነድ አሕመድ 8822)፡፡

የእናታችን ሐዋእ (ዐለይሃ-ሰላም) መጠሪያ በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ ‹‹የአደም ባለቤት›› የሚለው ነው፡፡(ሱረቱ-ኒሳእ 4፡1፣ አል-አዕራፍ 7፡189፣ አዝ-ዙመር 39፡6)፡፡ የግል ሥሟ አለመጠቀሱ የቅዱስ ቁርኣንን ምሉእነት በፍጹም ሊያጓድለው አይችልም፡፡ የአላህም ቃል እንዲህ ይላል፡-

" وَرَحْمَةً وَهُدًى وَبُشْرَى لِلْمُسْلِمِينَ " النحل سورة 89

"በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ ከነሳቸው በእነሱ ላይ መስካሪን የምንቀሰቅስበትን አንተንም በእነዚህ (ሕዝቦች) ላይ መስካሪ አድርገን የምናመጣህን ቀን (አስታውስ)፡፡ መጽሐፉንም ለሁሉ ነገር አብራሪ፣ መሪም፣ እዝነትም፣ ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው፡፡" (ሱረቱ-ነሕል 16፡89)፡፡

ነፍስ ያጠፋን ይቅር ማለት!

በአቡ ሀይደር

በአላህ ሥም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው

ክብርና ምሥጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2) የአላህ ውዳሴና ሰላም የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለኾኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡

1/ ሰሞኑን በሀገረ አሜሪካ፡ በኪንታኪ ግዛት ላይ በፒዛ አከፋፋይነት ሥራ ላይ የተሰማራው ወንድም ሰለሐዲን (አላህ ይዘንለት) መኪናውን አቁሞ የታዘዘውን ለማድረስ፡ ወደ አንድ መኖሪያ ቤት በማቅናት ላይ ሳለ፡ ምሽትን ተገን ያደረገ አንድ ትሬይ አሌክሳንደር የተባለ አሸባሪ ወደሱ በመምጣት፡ በጩቤ ደጋግሞ በመውጋት ከገደለው በኋላ ገንዘቡንም ዘርፎ ከአካባቢው ይሰወራል፡፡ ኋላም በአካባቢው ፖሊስ ከፍተኛ ክትትል ነፍሰ-ገዳይ በቁጥጥር ሥር ይገባል፡፡ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ፡ የፍርድ ሂደቱን የሚከታተሉ ሰዎች በተገኙበት ችሎት ላይ፡ የሟች ወላጅ አባት ዐብዱል-ሙጉዒም በመሐል ዳኛው በኩል የሚናገሩት ነገር ዕንዳለ በተጠየቁ ጊዜ፡ እሳቸውም፡- በኢስላም ሃይማኖት፡ ይቅርታ ማድረግን የመሰለ ነገር የለም! በማለት፡ ወደ ነፍሰ-ገዳዩ ፊታቸውን ያዞሩና፡- ለዚህ ክፉ ሥራ የገፋፋህን ሰይጣን ነው የምኮንነው እንጂ አንተን አይደለም! በማለት ነፍሰ-ገዳዩን በማቀፍ ከልቤ ይቅር ብዬሀለሁ ይሉታል፡፡

እንዲህ አይነት ይቅርታ በቦታው ለነበሩ ሰዎች እንግዳ በመኾኑ በጣም ተገርመው ችሎቱም ለደቂቃዎች በመቋረጥ ዳኛዋን ሁሉ አስለቅሷታል። ይህንን ከስተት የተለያዩ የህገሪቷ ሚዲያዎች ዘግበውታል። ሁሌም ስለ ኢስላምና ሙስሊሞች መልካም ነገርን በሰሙ ሰአት ልባቸው የሚደማ፣ መጥፎ ነገርን በሰሙ ሰአት የደስታ ፍጫቤ የሚረግጡ፣ ልባቸው በኢስላምና ሙስሊሞች ጥላቻ የጠቆረ ካፊሮች ይህ ዜና ለነሱ እንደ መርዶ ስለነበረ አላስደሰታቸውም። ዜናውን ማስተባበል ስላልቻሉ፣ ምላሳቸውን በኢስላም ላይ በማሾል፡- ኢስላም የገደለ ይገደል! ከማለት ውጭ ምን ምሕረት ያውቃልና! በማለት የልባቸውን ቁስል በመጠኑ ለማስታገስ የጥላቻ መርዛቸውን በፌስቡክና መሰል መገናኛዎች ላይ ሲተፉ አስተውለናል። እኔም በጉዳዩ ላይ መጠነኛ ግንዛቤ ለማስጨበጥ፣ ከህሊናው ጋር ያልተጣላም ሰው ካለ፣ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳይወስድ ለማገዝ የተወሰነ መልእክት ለመጻፍ ፈለግሁ። አላህ መልካሙን መረዳት ይግጠመን።

2ኛ/ ኢስላም በደረቁ ‹‹የገደለ ይገደል!›› የሚል ህግ የለውም። ኢስላም ወሰን በማለፍ የሰውን ነፍስ ያለ-አግባብ አውቀው በሚያጠፉት ወንጀለኞች ላይ ያስቀመጠው ህግ ሶስት ነገራትን ነው። እነዚህም ህጎች ነፍስ እንዳጠፉ የነሱም ነፍስ መጥፋት፣ ወይንም የገንዘብ ካሳ መክፈል፣ ወይንም ይቅርታ ማድረግ ነው። ይህንንም ህግ ተፈጻሚ የሚያደርገው የፍርድ ቤት ዳኛ ሳይኾን የሟች ቤተሰቦች ናቸው። እነሱ ይቅር ካሉ የሸሪዐው ዳኛ ወንጀለኛውን መግደል አይችልም። እነሱ የልጃችንን ደም እንዳፈሰሰ የሱም ደም ይፍሰስ ካሉ፣ ደኛው ለገዳይ ይቅርታ የማድረግ መብት የለውም። እሱ ህግ አስፈጻሚ እንጂ ሌላ አይደለምና። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

"ያቺንም አላህ ያወገዛትን ነፍስ ያለ ሕግ አትግደሉ። የተበደለም ኾኖ የተገደለ ሰው ለዘመዱ (በገዳዩ ላይ) በእርግጥ ስልጣንን አድርገናል። በመግደልም ወሰንን አይለፍ፤ እርሱ የተረዳ ነውና።" (ሱረቱል ኢስራእ 17፡33)።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ‹‹ለዘመዱ (በገዳዩ ላይ) በእርግጥ ስልጣንን አድርገናል›› የሚለው ቃል፣ ከላይ ያብራራነውን የሚገልጽ ነው። እነዚህ የሟች ቤተሰቦች (የሱን ንብረት መውረስ የሚችሉት) ከአላህ ዘንድ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት፣ ገዳይ እንደገደለው እሱም እንዲገደል፣ ወይንም በአቅሙ ልክ የደም ካሳ እንዲከፍል ካልኾነም በፍጹም ይቅርታ (በቀልን ያላዘለ) ምሕረት ሊያደርጉለት መብቱ አላቸው ማለት ነው። ዳኛው ደግሞ የነሱን ውሳኔ ተከትሎ ህጉን ያስፈጽማል ማለት ነው። በሌላ አንቀጽ ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በተገደሉ ሰዎች ማመሳሰል በናንተ ላይ ተጻፈ። ነጻ በነጻ ባሪያም በባሪያ ሴትም በሴት (ይገደላሉ)። ለእርሱም (ለገዳዩ) ከወንድሙ (ደም) ትንሽ ነገር ምሕረት የተደረገለት ሰው (በመሓሪው ላይ ጉማውን) በመልካም መከታተል ወደርሱም (ወደ መሓሪው) ገዳዩ በመልካም አኳኋን መክፈል አለባቸው። ይህ ከጌታችሁ የኾነ ማቃለልና እዝነት ነው። ከዚህም በኋላ ሕግን የተላለፈ ሰው ለርሱ አሳማሚ ቅጣት አለው። ለእናንተም ባለ አእምሮዎች ሆይ! በማመሳሰል (ሕግ) ውስጥ ሕይወት አላችሁ። ትጠነቀቁ ዘንድ (ገዳይን መግደል ተደነገገላችሁ)።" (ሱረቱል በቀራህ 2፡178-179)።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ደግሞ የምናገኘው ቁም-ነገር፡- የገደለ ሰው እንዲገደል ህግ መደንገጉን እናያለን። ኾኖም ለገዳዩ ከተገዳይ ቤተሰቦች ውስጥ ለሱ የተወሰነ ምሕረት ቢያደርጉለትና፣ መገደሉ ቀርቶ ካሳ መክፈልን ብቻ ቢጠይቁት፣ ከዚህ በኋላ የጠየቁትን ካሳ ብቻ በመልካም መከታተል እንጂ፣ ተመልሰው ቂምን በልባቸው በማርገዝ መበቀልን እንዳያስቡ ያስጠነቅቃል። ገዳይም የሞት ይቅርታ ተደርጎልኛል በማለት የተጠየቀውን ካሳ ከመክፈል እንዳያፈነግጥ ወይም ከጊዜው እንዳያዘገይ የተጠየቀውን የገንዘብ ካሳ በአግባቡ መክፈል እንዳለበት ይመክራል። ይህ በካሳ የመስማማት ህግ ከአላህ ዘንድ የኾነ የማቃለል እና የእዝነት ህግ ነው። ምክንያቱም የሟች ቤተሰቦች በይቅርታቸው አላህ ዘንድ አጅር ይኖራቸዋል። በገንዘብ ካሳው ደግሞ ጊዜያዊ ችግሮቻቸውን መፍታት ይችላሉ። ገዳይም ከሞት ተርፏል። በቀሪ ሕይወቱም ባሳለፈው ወንጀል በመጸጸት መልካም ሰው ለመኾን ዳግም አዲስ ሕይወት

ይጀምራል፡፡ ህጉ የገደለ ይገደል ብቻ ቢኾንና፡ ይቅርታና የገንዘብ ካሳ ባይኖር ኖሮ ምድር በበቀልና በደም በተሞላች ነበር፡፡ ሚች ዳግም ነፍስን ላይዘራ ገዳይን መግደል ብቻ ለሚች ቤተሰብ ምን ይጠቅማል? በመጨረሻም ‹‹ከዚህም በኋላ ሕግን የተላለፈ ሰው ለርሱ አሳማሚ ቅጣት አለው›› በማለት አንቀጹን ይቋጨዋል፡፡ የተገዳይ ቤተሰቦች ከይቅርታ ማድረግ በኋላ በገዳይ ላይ ተመልሰው የግድያ ወንጀልን የሚፈጽሙ ከኾነ፡ በዚሁ ምድር ላይ ወይንም በመጨረሻው ዓለም ቅጣት እንደሚጠብቃቸው አበክሮ ይገልጻል፡፡

በተጨማሪም ‹‹ለእናንተም ባለ አእምሮዎች ሆይ! በማመሳሰል (ሕግ) ውስጥ ሕይወት አላችሁ፡፡ ትጠነቀቁ ዘንድ (ገዳይን መግደል ተደነገገላችሁ)፡፡›› በማለት፡ አንዳንዴ ደግሞ ገዳይን መግደል በራሱ ሕይወት እንደኾነ ተናገረ፡፡ ምክንያቱም፡- ገዳይ በህጉ መሠረት በመገደሉ፡ ከዚህ በኋላ በሰው ሕይወት ላይ ወሰን ማለፍን የፈለገ አመጸኛ፡ በህጉ መሠረት የሱም ደም እንደሚፈስ ስለሚረዳ እጁን ይሰበስባል ማለት ነው፡፡ በዚህም ሰበብ ማኅበረሰቡ ሰላምና የተረጋጋ ሕይወትን ይኖራል፡፡ አንድን ነፍሰ-ገዳይ በመግደል የሺዎችን ሕይወት በከንቱ እንዳይጠፋ መታደግ በራሱ ሕይወት ነውና ‹‹ወለኩም ፊል-ቂሷሲ ሐያቱን›› (ለናንተም በማመሳሰል ሕግ ውስጥ ህይወት አላችሁ) አለ፡፡ ቀጣዩ አንቀጽ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

"የመጥፎም ነገር ዋጋ ብጤዋ መጥፎ ናት፡፡ ይቅርም ያለና ያሳመረ ሰው ምንዳው በአላህ ላይ ነው፡፡ እርሱ በደለኞችን አይወድም፡" (ሹረቱ-ሹራ 42፡40)፡፡

በዚህ አንቀጽ ደግሞ ‹‹የመጥፎም ነገር ዋጋ ብጤዋ መጥፎ ናት›› በማለት ይጀምራል፡፡ ማለትም፡- የገደለ መጥፎ ሰርቷልና እሱም ቢገደል፣ ያቆሰለ እንዲቆስል ቢደረግ፣ የሰበረ እንዲሰበር ቢደረግ፡ ኃጢአት አይደለም፡፡ ይህ ለመጥፎ ሥራው ተመጣጣኝ ዋጋው ነው፡፡ ኾኖም አንቀጹ ይቀጥልና ‹‹ይቅርም ያለና ያሳመረ ሰው ምንዳው በአላህ ላይ ነው›› በማለት፡ ከመበቀል ይልቅ፡ ይቅርታ ማድረግ አላህ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ መኾኑን እና ምንዳም (ሽልማትንም) የሚያስገኝ መልካም ተግባር መኾኑን ይገልጻል፡፡ አያይዞም አላህ ወሰን አላፊ የኾኑ በደለኞችን እንደማይወድ ይናገራል፡፡ ከይቅርታ ማድረግ በኋላ ወሰን አልፎ ጥፋተኛን መበቀል አይቻልምና፡፡

3ኛ/ በተጨማሪ ልናወቅ የሚገባው ነገር፡ አንድን ነፍስ ያጠፋ ሰው፡ ነፍሰ-ገዳይ ነው ተብሎ ሊፈረድበት የሚችለው፡- ለአካለ መጠን የደረሰ፣ አእምሮው ያልተዛባ፣ ድርጊቱንም ሆን ብሎ ዐውቆ ያደረገው ከኾነ ብቻ ነው፡፡ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ህጻን ወይንም አእምሮው የተዛባ በትክክል ማሰብ የማይችል እብድ ነፍስ አጥፍቶኛል ተብሎ የሞት ፍርድ አይሰጥባቸውም፡፡ ባይኾን ለሚች ቤተሰቦች የማስተዛዘኛ ካሳ እንዲከፍሉ ቤተሰቦቹ ይጠየቃሉ እንጂ፡፡ እንዲሁም ዐውቆ ሳይኾን በስህተት ሰው መግደሉ ከተረጋገጠ፡ ለሚች ቤተሰብ ካሳ ይከፍላል እንጂ፡ ነፍሰ-ገዳይ ተብሎ በሱ ላይ ሞት አይፈረድበትም፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡

"ለምእመንም በስሕተት ካልኾነ በቀር ምእመንን መግደል አይገባውም፡፡ ምእመንንም በስህተት የገደለ ሰው ያመነችን ጫንቃ (ባሪያ) ነጻ ማውጣትና ወደ ቤተሰቦቹም የምትሰጥ ጉማ ምሕረት ካላደረጉለት በስተቀር (መክፈል) አለበት፡፡ እርሱ (ተገዳዩ) ምእመን ሲኾን ለእናንተ ጠላት ከኾኑትም ሕዝቦች ቢኾን ያመነችን ጫንቃ ነጻ ማውጣት (ብቻ) አለበት፡፡ በእናንተና በእነሱ መካከል ቃል ኪዳን ካላቸውም ሕዝቦች ቢኾን ወደ ቤተሰቦቹ በእጅ የምትሰጥ ጉማና ያመነችን ጫንቃ ነጻ ማውጣት አለበት፡፡ ያላገኘ ሰውም ተከታታዮችን ሁለት ወሮች መጾም አለበት፡፡ አላህ መጸጸትን ለመቀበል (ደነገገላችሁ)፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡" (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡92)፡፡

በዚህ አንቀጽ መሠረት፡ ዐውቆና ኾን ብሎ ሳይኾን ሳያስበው በስህተት የሰውን ሕይወት ያጠፋ ሰው፡ በስህተት መኾኑ ከተረጋገጠ ሊገደል እንደማይገባው እንማራለን፡፡ ይልቁኑ፡ ለዚህ ስህተቱ ማካካሻ ይኾን ዘንድ አቅም ካለው፡ በባርነት ቀንበር ውስጥ ያለን አማኝ ባ...ሪያን ገንዘብ ከፍሎ እሱን ነጻ ማውጣት እና ለሟች ቤተሰቦቹም ይቅርታ ካላደረጉለት የደም ካሳን መክፈል ነው፡፡ ይህንን ስህተት ጠላቶች ከኾኑት ሕዝቦች በኩል ያመነ ነፍስ ላይም ቢኾን የፈጸመው፡ ገንዘብ ከፍሎ አማኝ ባሪያን ከባርነት ቀንበር ነጻ ማውጣት ነው ያለበት፡፡ ወይንም ይህን በስህተት መግደል በኖና በነሱ መካከል ጦርነት ላለመክፈት ከተስማማናቸው የከሀዲያን ሕዝቦች በኩልም ቢኾን የፈጸመው፡ ለሟች ቤተሰቦች የደም ካሳን መስጠት እና ያመነችን ነፍስ ከባርነት ቀንበር ነጻ ማውጣት ይኖርበታል፡፡ ይህ በስህተት ገዳይ የኾነው ሰው ይህን ያመነን ባሪያ ነጻ ለማውጣት የሚያስችል አቅሙ ከሌለው ደግሞ፡ ሁለት ወር በተከታታይ መጾም ነው ያለበት፡፡

ከአቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "ሶደቃህ መስጠት ከገንዘብ ላይ ምንም አያጎድልም፡፡ አላህ ለአማኝ ባሪያው በይቅርታ አድራጊነቱ ሰበብ ክብርንና የበላይነትን ቢጨምርለት እንጂ (ይቅርታ

+..... በማድረጉ) ምንም አይጎዳም፡፡ ለአላህ ብሎ ማንም ሰው አይተናነስም አላህ ከፍ ቢያደርገው እንጂ" (ሙስሊም 6757፣ ቲርሚዚይ 2161)፡፡

4ኛ/ ማጠቃለያ! ኢስላም ነፍሰ-ገዳዮችን በተመለከተ በምድር ላይ የሚጠበቃቸው ሸሪዐዊ ፍርድ ለሟች ቤተሰቦች (ወራሾች) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሶስት ነገር ነው፡፡ ነፍስ እንዳጠፉ ነፍሳቸው እንዲጠፋ፣ ወይንም በሞት ምትክ የደም ካሳ እንዲከፍሉ፣ ካልኾነም ሞቱም ካሳውም ቀርቶላቸው በይቅርታ እንዲሰናበቱ መደረግ ነው፡፡ ለገዳዮች ይቅርታ ከማድረግና እንዲሞቱ ሀጉን ከመጠየቅ የቱ ይበልጣል? የሚባል ከኾነ፡ ጥቅሙ ያመዘነው ይበልጣል የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡ ማለትም፡- ገዳይን እንዲሞት በማድረግ መቅጣቱ፡ በወቅቱ የተስፋፋውን ህገ-ወጥ የነፍስ ግድያ ወንጀል የሚያስቆመውና፡ ወሰን አላፊዎችም እጃቸውን እንዲሰበስቡ ትምሕርት ሰጪ ከኾነ፡ ለሟች ይቅርታ ከማድረግ ይልቅ በሞት መቅጣቱ የተሻለ ነው፡፡ ከግለሰብ ጥቅም ይልቅ የማኅበረሰቡ ጥቅም መቅደም አለበትና፡፡ ወይንም ደግሞ፡ ለገዳይ ይቅርታ ማድረጉ፡ በሰዎች መካከል መተዛዘንን የሚያስተምር፡ ፍቅርን የሚያመጣና መቢቃቀልን የሚያጠፋ መኾኑ ከታመነበት፡ ለገዳይ ይቅርታ ማድረጉ በላጭ ነው፡፡ ይህ የማኅበረሰብን ጥቅም ታሳቢ ከማድረግ አንጻር ነው፡፡ ከዛ ውጭ ግን ይቅር ማለት እና የደም ካሳ መጠየቅ በፍጹም ሊወዳደሩና ሊነጻጸሩ የሚችሉ ነገራት አይደሉም፡፡ ይቅርታን የመሰለ ምንም ነገር የለምና፡፡ አማኞችም የነገውን ዘላለማዊ ሕይወት ተስፋ የሚደርጉት፡ ከመልካም ሥራቸው ይልቅ የአላህን ይቅር ባይነት በማመን ነው፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

5ኛ/ ሌላው ሊታወቅ የሚገባው ነገር፡ ‹‹የገደለ ይገደል!›› የሚለው ህግ የመጽሐፍ ቅዱስ ህግ መኾኑን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈስሳል፤ ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና። ዘፍጥረት 9፡6

ሰው ሰውን ቢመታ ቢሞትም፥ እርሱ ፈጽሞ ይገደል። ዘጸአት 21፡12

ሰውንም እስኪሞት ድረስ የሚመታ ፈጽሞ ይገደል። ዘሌዋውያን 24፡17

እንስሳውንም የሚገድል ካሣ ይተካ፤ ሰውንም የሚገድል ይገደል። ዘሌዋውያን 24፡21

በብረት መሣርያ እስኪሞት ድረስ ቢመታው ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳዩም ፈጽሞ ይገደል። ሰውም በሚሞትበት በእጁ ባለው ድንጋይ ቢመታው የተመታውም ቢሞት፥ እርሱ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳዩም ፈጽሞ ይገደል። ሰውም በሚሞትበት በእጁ ባለው በእንጨት መሣርያ ቢመታው የተመታውም ቢሞት፥ እርሱ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳዩም ፈጽሞ ይገደል። ደም ተበቃዩ ራሱ ነፍሰ ገዳዩን ይግደል፤ ባገኘው ጊዜ ይግደለው። እስኪሞት ድረስ በጥላቻ ቢደፋው፥ ወይም ሸምቆ አንዳች ነገር ቢጥልበት፥ ወይም በጥላቻ እስኪሞት ድረስ በእጁ ቢመታው፥ የመታው ፈጽሞ ይገደል፤ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ደም ተበቃዩ ባገኘው ጊዜ ነፍሰ ገዳዩን ይግደለው። ዘኹልቁ 35፡16-21

አንዳንድ የዋህ ወገኖች፡ ይህ በብሉይ ዘመን የነበረ የድሮ ህግ ነው ይሉናል፡፤ የኛም ጥያቄ፡-

1/ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረ ህግ ከኾነ፡ ህጉን ማን ነው የደነገገው ? አምላክ ነው ካላችሁ፡ የአምላክ ህግ ደግሞ ፍትሐዊ እንጂ በደል ስላልኾነ፡ የገደለ መገደሉን አግባብነት እንዳለው አምናችኋል ማለት ነው፡፡ የገደለ መገደል የለበትም ካላችሁ ደግሞ፡ የአምላክ ህግ ስህተት አለበት እያላችሁ ነው፡፡ ኣይ ህጉን ያወጣው አምላክ ሳይኾን እስራኤላውያን ራሳቸው ናቸው ካላችሁ ደግሞ፡ የህጉ መጽሐፍ (ኦሪት) አምላካዊ ሳይኾን ሰዋዊ ነው ማለት ነው፡፡ ከሶስት አንዱን መምረጥ የናንተ ድርሻ ነው፡፡

2/ ይህ የብሉይ ኪዳን ህግ እንጂ፡ የአዲስ ኪዳን ህግ አይደለም ስትሉ፡ በአዲስ ኪዳን ተሸሯል ማለታችሁ ነውን ? አዎን! ከኾነ መልሳችሁ፡ ማን ህጉን እንደሻረውና የቱ ጋር እንደተሻረ ማስረጃ አቅርቡልን፡፡ ኢየሱስ ህግን ልሽር አልመጣሁም ልፈጽመው እንጂ ካለ (ማቴዎስ 5፡17) የሻረው ማን ሊኾን ነው ? ደግሞስ ህጉ በአዲስ ኪዳን የተሻረ ከኾነ፡ አንድ ህግ የሚሻረው በምትኩ ሌላ ነገር ሲበጅለት ነውና፡ በቦታው የተተካው አዲሱ ህግ ምን ኾነ? ገዳይ ያለ-ምንም ተጠያቂነት እና ቅጣት በምድር ላይ የሰው ነፍስ እያጠፋ ሊኖር ወይስ ምን? ገዳይ በአምላክ ዘንድ ይጠየቃል ከኾነ መልሳችሁ፡ የሚች ቤተሰቦችስ ጉዳይ? ደማቸው ፈስሶ በከንቱ ሊቀር ነው? ማኅበረሰቡስ ያለ-መረጋጋት ሊኖር ነው? ምክንያቱም ገዳይ ላይ የተላለፈ ምድራዊ ቅጣት የለምና፡፡ ህገር በሚመሩ መንግስታት ህግ ነው የሚዳኘው ካላችሁ ደግሞ፡ የኦሪት ህግ በመንግስታት ህግ ተሸረ እንጂ በአዲስ ኪዳን ተሸረ ማለት እንዴት እንችላለን ታዲያ? በማለት እንጠይቃችኋል::

አላህ(ሱወ) የሰዉ ልጅ በመጀመርያ ሲፈጠር የት እንዲኖር ነበር የፈጠረዉ?

አላህ(ሱወ) አዳምን(ዐሰ) ከመፍጠሩ በፊት የሰዉ ዘር የመፍጠር እቅድ እንደነበረዉ እና የዚህ ፍጡር መኖሪያም ምድር እንደሆነ ገልፆዋል ።ስለዚህ “ አዳም(ዐሰ) ባይሳሳት ኖሮ ገነት እንኖር ነበር›› የሚለዉ አስተሳሳብ አዳምን(ዐሰ) ሃጢአተኛ ለማደረግና በዚህም ‹‹ኦሪጅናል ሲን ›› (የውርስ ሀጢያት) ይመለከተናል የሚል መደምደምያ ላይ ያደረሰናል። መጀመርያዉኑ ስንፈጠር እንድንኖር የታሰበዉ ዘላለማዊትዋ ገነት ዉስጥ ሳይሆን ምድር ላይ ነዉ !!

ለዚህም አላህ(ሱወ) በቁርአኑ ለመላእክት ‹‹ምትክን በምድር ላይ እንደሚፈጥር ›› እንጂ በገነት እንደሚፈጥር አልነገራቸዉም፡፡ ቁርኣን 2፡30

(ሙሐመድ ሆይ) ጌታህ ለመላእክት፡- «እኔ በምድር_ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ፤» ባለ ጊዜ (የኾነውን አስታውስ፤ እነርሱም) «እኛ ከማመስገን ጋር የምናጠራህ ላንተም የምንቀድስ ስንኾን በርሷ ውስጥ የሚያጠፋንና ደሞችንም የሚያፈስን ታደርጋለህን?» አሉ፡፡ (አላህ) «እኔ የማታውቁትን ነገር አውቃለሁ» አላቸው፡፡ (30)

እንደሱ ከሆነ ለምን አደምንና ሀዋን አላህ ከፈጠራቸዉ በሁዋላ ‹ገነት› ዉስጥ እንዲኖሩ አደረገ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ? አባታችን አዳም(ዐሰ) ‹‹አድርግ አታድርግ›› ለሚሰኙት የአላህ ትእዛዛት ለመገዛት ነዉ እነኝኂህ መለኮታዊ ትእዛዛት ሲጠበቁ ምድሪቱ ጤናማ በሆነ መልኩ ታብባለች በተቃራኒዉ ደግሞ ቸል ሲባል ታላቅ ጥፋትን ይደረሳል፡፡ አባታችን አደም (አሰ) የአላህን(ሱወ) መመሪያ ከማክበር እና የተረገመዉ ሰይጣን መደለያ ከመቀበል የትኛዉ አዋጪ እንደሆነ ያስተዉል ዘንድ በተግባራዊዉ የሕይወት መመዘኛ (ተሞክሮ) ሰር ማለፉን አሰፈላጊ ሆነ ። ስለዚህም ኑሮዉን ‹ጀነት› በተሰኘችዉ አለማዊት አፀድ እንዲመሰረት ተወሰነ፡፡

የቀረችዋ አንዷ ጣኦት!!

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና የዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ የተገባ ነው፡፡ የአላህ ውዳሴና ሰላም፡ የሰላም አለቃና መምህር ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ ይሁን፡፡ ድልና የበላይነት ሐቅን ለማንገስና ሀሰትን ለማርከስ፡ በደልን አጥፎ ፍትህን ለማስፈን ዕውቀታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ህይወታቸውን መስዋእት በማድረግ ለሚታገሉት ይሁን፡፡

ሀሰት ሲደጋገም እውነት ይመስላል! እንዲሉ ሆነና፡ ሰዎች የራሳቸውን ነውር ለመሸፈን፡ በሃይማኖታቸው ላይ የህሊና ጥያቄ እንዳይነሳባቸው፡ ተቃራኒያቸውን በአልባሌ ጥያቄ ጊዜ ማሳጣትና ሁሌም የነሱን ጥያቄ በማስተናገድ ብቻ ተከላካይ እንጂ አጥቂ የመሆን ዕድልን ለመንፈግ በጣም ይጥራሉ፡፡ ነገሩ ከተከላካይ ሜዳ የተመታ ኳስ ግብ ሊያስቆጥር እንደሚችልም የተረዱ አይመስልም፡፡

ይህ ከንቱና ገለባ ክስ፡- ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) በመካ ውስጥ ይመለኩ ከነበሩት 360 ጣኢታት መካከል፡ 359ኙን በማፈራረስ አንዱን ጣኦት ብቻ አስቀርተዋል፡፡ ዛሬም ሙስሊሞች የምታመልኩት ይህን አንድ ጣኦት ነው! የሚል ነው፡፡

ከጣኦት አምልኮ በማራቅ፡ አንዱንና እውነተኛውን አምላክ አላህን እንድናመልክ ሙስሊም አድርጎ ለፈጠረን፡ እስካሁንም ሙስሊም አድርጎ ላቆየን አምላክ ምስጋና ይድረሰው፡፡ አልሐምዱ ሊላሂ ረቢል-ዓለሚን፡፡ ሰው ግን እንዴት እራሱ በጣኦት አምልኮ ላይ ተዘፍቆ፡ ሌላውን በሌለበት ነገር የሚከስ አእምሮ ይኖረዋል?

በጣም የገረመኝና ያሳቀኝ፣ የጠያቂዎቹንም ከዕውቀት ጡሀራ መሆናቸውን ያሳየኝ፡ ማስረጃ ብለው የጠቀሱት የቁርኣን ክፍል ነው፡፡ አንቀጹ እንዲህ ይነበባል፡-

" يَرْجِعُونَ إِلَيْهِ لَعَلَّهُمْ لَهُمْ كَبِيرًا إِلَّا جُذَاذًا فَجَعَلَهُمْ " الأنبياء سورة 58

"(ዘወር ሲሉ) ስብርብሮችም አደረጋቸው፤ ለነሱ የሆነ አንድ ታላቅ (ጣዖት) ብቻ ሲቀር ወደርሱ ይመለሱ ዘንድ (እርሱን ተወው)።" (ሱረቱል አንቢያእ 21፡58)፡፡

ይህን የአላህ ቃል ይዘው ነው እንግዲህ የሚሞግቱን!! የኛም መጠነኛ ምላሽ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1ኛ፡- በዚህ ምድር ላይ ከጣኦት አምልኮ በመራቅ ፍፁም አንድ አምላክ ብቻ መኖሩን የሚያውጅ ሃይማኖት ቢኖር ኢስላም ብቻ ነው፡፡ ፍፁም አንድ አምላክ ማለት ደግሞ፡- በአንድነቱ ሶስትነት የሌለበት፣ በአምላክነቱ ሰዋዊነት የማይንጸባረቅበት፣ በፍፁም ሕያውነቱ ፈጽሞ የማይሞት ማለት ነው፡፡

ይህ አምላክ በ‹አንተ›ነቱ የሚመለክና የሚለመን፣ በ‹እሱ›ነቱ የሚሰበክና ለሰው የሚነገር፣ በ‹እኔ›ነቱ እራሱን የሚገልጥና የሚያስተዋውቅ፣ በ‹እኛ›ነቱ ኃያልነቱንና ስራዎቹን የሚናገር ማለት ነው፡፡ ይህ አምላክ ‹‹ናቸው!›› ተብሎ አይነገርለትም፡፡ ‹እነሱ› ተብሎ አይጠራምና!፡፡ እና ይህንን አምላክ በዚህ መልኩ የሚገልጽ ከኢስላማዊው አስተምህሮ ውጪ የት ይገኝ ይሆን?

ከኢስላማዊው አስተምህሮ አንዱና ቀዳሚው የሆነው ‹ከሊመቱ-ሸሀዳህ› ነው፡፡ ‹‹ላ ኢላሀ ኢልለሏህ›› የሚለው የሙስሊሞች ምስክርነት ‹ቃለ-ተውሒድ› በራሱ የጣኦት አምልኮን በእጅጉ የሚቃረን ነው፡፡ እንዴት የሚሉ ከሆነም፡ ወደ ትርጓሜው እንምጣ፡-

‹‹ላ ኢላሀ ኢልለሏህ›› የሚለው ቃል ፍቺው፡- ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም ማለት ነው፡፡ በዚህ ፍቺ ውስጥ ሁለት ነገሮች ታቅፈዋል፡፡ የመጀመሪያው፡- ከአላህ ውጪ ለማንኛውም አካል ምንም አይነት አምልኮ እንደማይገባው መግለጽ ሲሆን፡ ሁለተኛው ደግሞ፡- አምልኮን ለአንድ አላህ ማጽደቅና ማረጋገጥ ማለት ነው፡፡ ይህ በዐረብኛው ‹ነፍይ› እና ‹ኢሥባት› ተብሎ ይጠራል፡፡

‹ነፍይ› ማለት፡- ማግለል እና ማራቅ ማለት ነው፡፡ ይህም ከአላህ ውጪ ያሉት ፍጥረታት በጠቅላላ አምልኮ የማይገባቸው መሆኑን በማወቅና በማመን፡ እነሱን ከማምለክ እራስን ማግለል እና በነሱም አምልኮ መካድ ማለት ነው፡፡

‹ኢሥባት› ማለት ደግሞ፡- ማንኛውንም አይነት አምልኮ ለአላህ ብቻ እንደሚገባ በማመን፡ አምልኮን ለአላህ ማጽደቅና እሱን ብቻ መገዛት ማለት ነው፡፡

እንግዲያውስ የ‹ላ ኢላሀ ኢልለሏህ› ምስክርነት፡ አላህን በብቸኝነት ማምለክ እና ከሱ ውጭ ያለ ማንኛውንም አምልኮ ጣኦት መሆኑን በማመን ከሱ መራቅን ከጠየቀ፡ እንዴት ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) አንድን ጣኦት አስቀሩ ብሎ ማሰብ ይቻላል?

2ኛ/ ቅዱስ ቁርአን በብዙ ስፍራዎች ላይ ከጣኦት አምልኮ እንድንርቅ፡ በርሱም እንድንከድ አበክሮ ያዘናል፡፡ በአላህ ማመንም ትርጉም የሚኖረው በጣኣታት ከመካድ ጋር አብሮ ሲሆን እንደሆነ ይገልጻል፡፡ አንድ ሰው በጣኦት አምልኮ ካልካደ በአላህ ማመኑ ብቻውን አይጠቅመውም፡፡ አላህ በሱ ማጋራትን አይወድምና፡ በሱ አምላክነት ስናምን ከሱ ውጭ በሚመለኩ ነገራትም መካድ ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" لَا إِكْرَاهَ فِي الدِّينِ قَدْ تَبَيَّنَ الرُّشْدُ مِنَ الْغَيِّ فَمَنْ يَكْفُرْ بِالطَّاغُوتِ وَيُؤْمِنْ بِاللَّهِ فَقَدِ اسْتَمْسَكَ بِالْعُرْوَةِ الْوُثْقَى لَا انْفِصَامَ لَهَا وَاللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ " البقرة سورة 256

"በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡ በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ፡፡ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡256)፡፡

" الَّذِينَ اجْتَنَبُوا الطَّاغُوتَ أَنْ يَعْبُدُوهَا وَأَنَابُوا إِلَى اللَّهِ لَهُمُ الْبُشْرَى فَبَشِّرْ عِبَادِ * الَّذِينَ يَسْتَمِعُونَ الْقَوْلَ فَيَتَّبِعُونَ أَحْسَنَهُ أُولَئِكَ الَّذِينَ هَدَاهُمُ اللَّهُ وَأُولَئِكَ هُمْ أُولُو الْأَلْبَابِ " الزمر سورة 18-17

"እነዚያም ጣዖታትን የሚግዝት ከመሆን የራቁ ወደ አላህም የዞሩ ለነርሱ ብስራት አላቸው፤ ስለዚህ ባሮቼን አብስር። እነዚያን ንግግርን የሚያዳምጡትንና መልካሙን የሚከተሉትን፣ (አብስር)፤ እነዚያ፣ እነርሱ አላህ የመራቸው ናቸው። እነዚያም እነሱ ባለ አእምሮዎች ናቸው።" (ሱረቱ-ዙመር 39፡17-18)።

"... الزُّورِ قَوْلَ وَاجْتَنِبُوا الْأَوْثَانِ مِنَ الرِّجْسَ فَاجْتَنِبُوا..." 30 الحج سورة

"...ከጣዖታት ርከሰት ተጠንቀቁ፤ ሀሰትንም ቃል ራቁ።" (ሱረቱል ሐጅ 22፡30)።

የአምላክ ቃል የሆነው ቁርአን ጣኦታትን ከማምለክ ራቁ ብሎ ሲመክር እንጂ፡ አንዷን ብቻ ሲቀር ብሎ ሲያስተምር አላነበብንም። ከየት የመጣ የሀሰት ወሬ ነው ታዲያ?

3ኛ/ ከላይ ወደተጠቀሰው ማስረጃ ስንመለስ ደግሞ፡- ይህ የቁርአን ክፍል የሚናገረው ስለ ነቢዩላህ ኢብራሂም (ዐለይሂ-ሰላም) ነው፡ ፡ ኢብራሂም አባቱንና የተላከበትን ማኅበረሰብ ወደ አላህ መንገድ ጠርቷቸዋል። ከጣኦትም አምልኮ ኢንዲርቁ አስጠንቅቋቸዋል። ከህዝቦቹም በኩል የተቃውሞ ምላሽ በገጠመው ጊዜ፡ በሌላ መንገድ ሊያስተምራቸው ፈለገ። እሱም ጣኦቶቻቸውን እነሱ በሌሉበት መሰባበርና አንዱን ብቻ ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ ሲመለሱ እንዲያዩት ማድረግ። እንዳለውም አደረገ።

እነሱም ሲመለሱ ጣኦቶቻቸው መሰባበራቸውን ሲያዩ በቁጣ ስሜት፡- ‹‹አማልክቶቻችን ላይ ይህን የፈጸመ ማነው?›› አሉ። ኋላ ላይም ኢብራሂም ከዚህ ቀደም በመጥፎ ሲያነሳቸው ሰምተናል ይሉና እሱን ጠርተው ይህን ያደረገው እሱ እንደሆን ይጠይቁታል። ኢብራሂምም፡- ‹‹ኧረ ታላቃቸው ነው ይህን የፈጸመው! ካላመናችሁም የተሰባበሩትን ጣኦታት ጠይቋቸው!›› ብሎ መለሰ። እነሱም አንገታቸውን በማቀርቀር እርስ በርስ መወቃቀስ ጀመሩ። ጣኦቶቹ የማይጠቅሙና የማይጎዱ መሆናቸውን፡ እንዲሁም መናገር የማይችሉ መሆናቸውን በተግባር አሳያቸው። ታላቁ ጣኦታቸውም ይህ ሁሉ ሲፈጸም ዝም ማለቱ፡ አቅመ-ቢስ መሆኑን ገለጸላቸው፡ ፡ በዚህ መልኩ ነበር ኢብራሂም ያስተማረው። ታዲያ ጉዳዩን ከነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ጋር ማያያዙ ድፍረት የሞላው አለማወቅ ካልሆነ ምን ይባላል?። ይኸው ሙሉ ክስተቱን ከቁርአን እንየው፡-

" لَهَا آبَاءَنَا وَجَدْنَا قَالُوا * عَاكِفُونَ لَهَا أَنْتُمْ الَّتِي التَّمَاثِيلُ هَذِهِ مَا وَقَوْمِهِ لِأَبِيهِ قَالَ إِذْ * عَالِمِينَ بِهِ وَكُنَّا قَبْلُ مِنْ رُشْدَهُ إِبْرَاهِيمَ آتَيْنَا وَلَقَدْ وَالْأَرْضِ السَّمَاوَاتِ رَبُّ رَبُّكُمْ بَلْ قَالَ * اللَّاعِبِينَ مِنَ أَنْتَ أَمْ بِالْحَقِّ أَجِئْتَنَا قَالُوا * مُبِينٍ ضَلَالٍ فِي وَآبَاؤُكُمْ أَنْتُمْ كُنْتُمْ لَقَدْ قَالَ * عَابِدِينَ إِلَيْهِ لَعَلَّهُمْ لَهُمْ كَبِيرًا إِلَّا جُذَاذًا فَجَعَلَهُمْ * مُدْبِرِينَ تُوَلُّوا أَنْ بَعْدَ أَصْنَامَكُمْ لَأَكِيدَنَّ وَتَاللَّهِ * الشَّاهِدِينَ مِنَ ذَلِكُمْ عَلَى وَأَنَا فَطَرَهُنَّ الَّذِي النَّاسِ أَعْيُنِ عَلَى بِهِ فَأْتُوا قَالُوا * إِبْرَاهِيمُ لَهُ يُقَالُ يَذْكُرُهُمْ فَتًى سَمِعْنَا قَالُوا * الظَّالِمِينَ لَمِنَ إِنَّهُ بِآلِهَتِنَا هَذَا فَعَلَ مَنْ قَالُوا * يَرْجِعُونَ أَنْفُسِهِمْ إِلَى فَرَجَعُوا * يَنْطِقُونَ كَانُوا إِنْ فَاسْأَلُوهُمْ هَذَا كَبِيرُهُمْ فَعَلَهُ بَلْ قَالَ * إِبْرَاهِيمُ يَا بِآلِهَتِنَا هَذَا فَعَلْتَ أَأَنْتَ قَالُوا * يَشْهَدُونَ لَعَلَّهُمْ وَلَا شَيْئًا يَنْفَعُكُمْ لَا مَا اللَّهِ دُونِ مِنْ أَفَتَعْبُدُونَ قَالَ * يَنْطِقُونَ هَؤُلَاءِ مَا عَلِمْتَ لَقَدْ رُءُوسِهِمْ عَلَى نُكِسُوا ثُمَّ * الظَّالِمُونَ أَنْتُمْ إِنَّكُمْ فَقَالُوا تَعْقِلُونَ أَفَلَا اللَّهِ دُونِ مِنْ تَعْبُدُونَ وَلِمَا لَكُمْ أُفٍّ * يَضُرُّكُمْ 67-51 الأنبياء سورة "

"ለኢብራሂምም፣ ከዚያ በፊት ቅን መንገዱን በእርግጥ ሰጠነው፤ እኛም በርሱ (ተገቢነት) ዐዋቂዎች ነበርን። ለአባቱና ለሕዝቦቹ፡- ይህቺ ቅርጻ ቅርጽ፣ ያቺ እናንተ ለርሷ ተገገሪዎች የሆናችሁት ምንድን ናት? ባለ ጊዜ (መራነው)።፡-አባቶቻችን ለሯ ተገገሪዎች ሆነው አገኘን አሉ። እናንተም አባቶቻችሁም፣ በእርግጥ በግልጽ ስሕተት ውስጥ ነበራችሁ አላቸው። በምሩ መጣልህን? ወይንስ አንተ ከሚቀልዱት ነህ? አሉት። አይደለም፣ ጌታችሁ የሰማያትና የምድር ጌታ ያ የፈጠራቸው ነው፤ እኔም በይሃችሁ ላይ ከመስካሪዎቹ ነኝ፣ አለ። በአላህም ስም እምላለሁ ዞሪዎች ሆናችሁ ከኼዳችሁ በኋላ ጣዖቶቻችሁን ተንኮል እሰራባቸዋለሁ፣ (አለ)።(ዘወር ሲሉ) ስብርብሮችም አደረጋቸው፤ ለነሱ የሆነ አንድ ታላቅ (ጣዖት) ብቻ ሲቀር ወደርሱ ይመለሱ ዘንድ (እርሱን ተወው)። ፡- በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራ ማነው? እርሱ በእርግጥ ከበደለኞች ነው፣ አሉ። (ኢብራሂም) የሚባል ጎበዝ (በመጥፎ) ሲያነሳቸው ሰምተናል ተባባሉ። ይመሰክሩበት ዘንድ በሰዎች ዓይን (ፊት) ላይ አምጡት አሉ። ኢብራሂም ሆይ! በአማልክቶቻችን ይህንን የሠራህ

አንተ ነህን? አሉት። አይደለም፣ ይህ ትልቃቸው ሠራው፤ ይናገሩም እንደ ሆነ ጠይቋቸው፣ አለ። ወደ ነፍሶቻቸውም ተመለሱ። እናንተ (በመጠየቃችሁ) በዳዮቹ እናንተው ናችሁም ተባባሉ። ከዚያም በራሶቻቸው ላይ ተገለበጡ፤ እነዚህ የሚናገሩ አለመሆናቸውን በእርግጥ ዐውቀሃል፤ (አሉ)።ታዲያ ለናንተ ምንም የማይጠቅማችሁንና የማይጎዳችሁን ነገር ከአላህ ሌላ ትግገዛላችሁን? አላቸው። ፎህ! ለናንተ፣ ከአላህ ሌላ ለምትግገዙትም ነገር አታውቁምን? (አለ)።" (ሱረቱል አንቢያእ 21፡51-67)።

4ኛ/ ከላይ የተሰጠው በቂ ምላሽ ሆኖ ሳለ፡ ሐቅን መስማት የማይፈልጉ ግን፡ ለምን ታዲያ ወደ ከዕባህ ዙሪያችሁ ትሰግዳላችሁ ? ደግሞስ ሐጀሩል አስወድንስ ለምን ትስማላችሁ? ይሉናል። ምላሻችንም፡-

ሀ/ ወደ ከዕባህ ዞረን የምንሰግደው፡- ጌታችን አላህ ‹‹ወደሱ ዙሪችሁ ስገዱ›› በማለት ስላዘዘን እንጂ፡ ከከዕባህ ጋር ሌላ ጉዳይ ኖሮን አይደለም። አምልኮ ደግሞ ትርጉም የሚኖረው በመስገድና በመጾም ብቻ ሳይሆን፡ አተገባበራችንም እንደታዘዝነው ሲሆን ነው። የአላህ ትእዛዝ በማክበር የእሺታን ምላሽ መስጠት በራሱ ትልቅ አምልኮ ነው። እሱ ካዘዘን ውጪ በራሳችን መንገድ እኛ እንደፈለግነው፡ ወይም በጉባኤ ስብሰባ እንደተወሰነው ስግደትና ጾምን መፈጸም ከአላህ ትእዛዝ መውጣት እንጂ አምልኮ አይደለም። በዚህ መልኩ ማን አዘዛችሁና! ተብለን መወቀሱ አይቀርምና። አላህን ስናመልከው እሱ እንዳዘዘን መሆን አለበት። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" شَطْرَهُ وُجُوهَكُمْ فَوَلُّوا كُنْتُمْ مَا وَحَيْثُ الْحَرَامِ الْمَسْجِدِ شَطْرَ وَجْهَكَ فَوَلِّ خَرَجْتَ حَيْثُ وَمِنْ..." البقرة سورة 150

"ከየትም ከወጣህበት ስፍራ ፊትህን ወደ ተከለለው መስጊድ አግጣጫ አዙር። በየትም ስፍራ ብትኾኑ … ፊቶቻችሁን ወደ አግጣጫው አዙሩ።" (ሱረቱል በቀራህ 2፡150)።

ለ/ ከዕባህ የሙስሊሞች የስግደት አቅጣጫ ከመሆኑ በፊት ሙስሊሞች ይሰግዱ የነበረው ወደ በይቱል መቅዲስ ‹‹መስጂዱል አቅሷ›› ነበር። ነቢያችን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ከሶሓቦቻቸው (ረዲየላሁ ዐንሁም) ጋር በመሆን በመዲና ለአስራ ስድስት ወራት ወደ መስጂዱል አቅሷ በመዞር ሰግደዋል። እንግዲያውስ የመጀመሪያው አምላካቸው ‹‹መስጂዱል አቅሷ›› ነበር ማለት ነው? ወደ አንድ አቅጣጫ ዞሮ መስገድ እና ለዛ ነገር መስገድ የተለያዩ መሆናቸውን መረዳት ያልቻለ ጭንቅላት፡ ጣአት ታመልካላችሁ! ብሎ ሲከስ እጅግ አሳፋሪ ነው። ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመዱ ያፍር ነውና እኛ እንፈርላቸው እንጂ!።

አላህ ግን የአቅጣጫዎች ሁሉ ባለቤትና ፈጣሪ በመሆኑ ወደፈለገው ስፍራ ዞራችሁ ስገዱ! በማለት ማዘዝ ይችላል። እኛ ግን ከታዘዝነው ውጪ ወደፈለግነው አቅጣጫ ዞረን ሶላትን መፈጸም አንችልም!፡-

" قِبْلَتِهِمُ عَنْ وَلَّاهُمْ مَا النَّاسِ مِنَ السُّفَهَاءُ سَيَقُولُ

" مُسْتَقِيمٍ صِرَاطٍ إِلَى يَشَاءُ مَنْ يَهْدِي وَالْمَغْرِبُ الْمَشْرِقُ لِلَّهِ قُلْ عَلَيْهَا كَانُوا الَّتِي البقرة سورة 142

"ከሰዎቹ ቂሎቹ «ከዚያች በርሷ ላይ ከነበሩባት ቂብላቸው ምን አዞራቸው?» ይላሉ፤ «ምሥራቁም ምዕራቡም የአላህ ነው፤ የሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል» በላቸው።" (ሱረቱል በቀራህ 2፡142)።

ሐ/ ማንኛውም ሙስሊም ፊቱን ወደ ከዕባህ አቅጣጫ አዙሮ ሲሰግድ፡ ልቡና ሀሳቡ በጠቅላላ የሚያርፈው ለስግደት የሚጠቀምባቸው የሶላት አዝካሮች ላይ እንጂ፡ ከዕባህ ላይ አይደለም። ማንም ሰው ለሶላት ሲቆም ከዕባህ ትዝ ብሎት አያውቅም።

እንኳን በውጭ ሀገር ያለነው ሙስሊሞች ይቅርና በመስጂዱል ሐረም ውስጥ ሉ የአላህ ባሮች እንኳ በሶላት ወቅት ሶፍ (ሰልፍ) ማስተካከላቸውን እና የኢማሙን ተክቢራ መጠባበቃቸውን ያስባሉ እንጂ፡ የከዕባህ ምንነት ትዝ አይላቸውም፡፡ ሶላታቸውንም አጠናቅቀው አላህን ለመለመን እጃቸውን ወደላይ ሲያነሱ፡ ልባቸው አብሮ ወደላይ በመነሳት ከሰማያት በላይ ያለውን አላህን ያስባል እንጂ ከዕባህ ትዝ አይላቸውም፡፡ ታዲያ ከዕባህ የሚመለክ አምላክ ከነበር እንዴት ልባችን እና ሀሳባችን ከሱ ሊርቅ ቻለ? ወገኖች! ጭንቅላት የተሰራው ልናስተነትንበት እንጂ፡ ኮፍያ ልናስቀምጥበት አይደለም! የሚል ምክር አልሰማችሁምን?

መ/ ከዕባህ የሙስሊሞች የስግደት አቅጣጫ መሆን የሚችለው፡ አቅጣጫውን ያወቅንና የቻልን ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ከዛ ውጭ አንድ ሙስሊም በመንገድ ወይም በአየር ጉዞ ላይ ሆኖ የከዕባን አቅጣጫ ማወቅ ባይችልና፡ የሚነግረውንም ሰው ፈልጎ ባያገኝ፡ ይሆናል ብሎ ባሰበው አቅጣጫ መስገድ ይችላል፡፡ ሶላቱን ከጨረሰ በኋላ አንድ ሰው መጥቶ የከዕባህ አቅጣጫ እኮ አንተ ከሰገድክበት አቅጣጫ ውጭ ነበር! ቢለው እንኳ ሶላቱን ደግሞ መስገድ አይጠበቅበትም፡፡ ይህም የሚያሳየው ጉዳዩ አላህን ከማምለክ ጋር እንጂ ከከዕባህ ጋር የተገናኘ አለመሆኑን ነው፡፡

ሶሓቦች (ረዲየላሁ ዐንሁም) በአንድ ወቅት በለሊት የፈጅርን ሶላት በጨለማው ሰበብ ቂብላ ይጠፋቸውና ከከዕባህ ውጭ ይሰግዳሉ፡፡ ባነጉም ጊዜ መሳሳታቸውን ሲረዱ ወደ አላህ መልክተኛ ጉዳያቸውን ሊያቀርቡ መጡ፡፡ የአላህ ቃልም እንዲህ አላቸው፡- " وَلِلَّهِ الْمَشْرِقُ وَالْمَغْرِبُ فَأَيْنَمَا تُوَلُّوا فَثَمَّ وَجْهُ اللَّهِ إِنَّ اللَّهَ وَاسِعٌ عَلِيمٌ " البقرة سورة 115

"ምሥራቁም ምዕራቡም የአላህ ነው (ፊቶቻችሁን) ወደ የትም ብታዞሩ የአላህ ፊት እዚያ ነው፡፡ አላህ ችሮታው ሰፊ ዐዋቂ ነውና፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡115)፡፡

ሠ/ ወደ ሐጀሩል አስወድ ስንመጣ ደግሞ፡- እሱ የሚሳመው አምላክ ስለሆነ አይደለም!!፡፡ የሚጠቅም የሚጎዳ ስለሆነም አይደለም፡፡ አይችልምና!! በማንነቱ ግኡዝ ፍጥረት ከመሆን የዘለለ ሚና የለውም፡፡ እኛ በሐጅ ወቅት የምንስመው የአላህ መልክተኛ ስለሳሙት ብቻ ነው፡፡ ፈለጋቸውን ተከታይ ስለሆንን ብቻ ነው፡፡ መሳም ማለት ግን ማምለክ ይሆናል ያለው ማነው? እኛ ምስል ሰርተንለት ቤታችን አልሰቀልነው! ወይ በደረታችን አላቀፍነው! ወይም በቲሸርት ላይ አሰርተን አልለበስነው!በምን መልኩ ነው ተመለከ የሚባለው?

ሐጅን ያልፈጸሙ ስንትና ስንት ሚሊየን ሙስሊሞች አልሉ፡፡ በጤና መታወክ፡ ወይንም በገንዘብ እጥረት ሰበብ ማለት ነው፡፡ ሐጀሩል አስወድን ስላልሳሙ ምንም አይሆኑም :: ደግሞም እምነታቸው ጎዶሎ አይደለም፡፡ ሐጀሩል አስወድንም መሳም ሃይማኖታዊ ግዳጅ አይደለም፡፡ ‹ሱንና› የተወደደ ተግባር ቢሆን እንጂ፡፡ ይህ ማለት የተወው ሰው ኃጢአተኛ አይደለም ማለት ነው፡ : ይህ ያልገባው ግን የአምልኮ ቦታዎችን አጥር እየሳመ፡ ለምስል እየሰገደና እየተንበረከከ ሙስሊምን ለመንቀፍ ይቸኩላል፡፡ ምናለ ጉድፍን ማጥራት ከራስ ቢጀምር!!

ወገኖቻችን፡- ከአንዱና ከእውነተኛው አምላክ ውጭ ሌላ ጌታና አምላክ ስለሌለ፡ የዘላለም ህይወትን ጀነትን ታገኙ ዘንድ ወደ አላህ መንገድ ጥሪ እናቀርብላችኋለን፡-

" فَذَلِكُمُ اللَّهُ رَبُّكُمُ الْحَقُّ فَمَاذَا بَعْدَ الْحَقِّ إِلَّا الضَّلَالُ فَأَنَّى تُصْرَفُونَ " يونس سورة 32

"እርሱ እውነተኛ ጌታችሁ አላህ ነው፡፡ ከእውነትም በኋላ ጥመት እንጂ ሌላ ምን አለ? (ከውነት) እንዴት ትዞራላችሁ" (ሱረቱ

ዩኑስ 10፡32)፡፡

18.አታስቀኝ

አሰቃቂና አፀያፊ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች

1.ልጇን ቀቅላ የበላች እናት መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ6፡26-29

2.ባሏ ስለሞተባት ሴት ወንድሙን ታግባ፤በስሙይጠራ፤ እንቢካለ ፊቱ ላይትትፋ ኦሪት ዘዳግም25፡5-10

3.በልጁ ላይ ዝሙት ሉጥ (ኦሪት ዘፍጥ 19.30-38 (ይሁዳ ኦሪት ዘፍጥ 38.15-24)

4.እግዚአብሔር በግብጽ ወንዝ ዳርቻ ያለውን ዝምብ በአሦርም አገር ያለውን ንብ በፉጨት ይጠራል። ትንቢተ ኢሳይያስ 7:18

5.ዝሙት አንደ መብት (ኦሪት ዘፍጥ 35.22 & 49.4)

6.ሶስት አመት በራቁቱ የሄደ ነብይ ትንቢተ ኢሳያስ 20፡1-3

7.ለጸሎት የጥጃ ምስል ጣኦት የሰራ ነብይ አሮን (ኦሪት ዘጽአት 32.2-4)

8.የግል ደብዳቤ እኔ ጋር እንድትመጣ፤የስቀመጥኩትን አምጣልኝ.. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ 4፡9-13

9.የ 100 ሰዎች ሞት ለዳዊት ጥሎሽ (መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 18:25-27)

10.በባሎቻቸው ስለሚጠረጠሩ ሴቶች የተሰጠ የመመርመሪያ ዘዴ ኦሪት ዘኁልቁ 5፡12-25(1980 የተሻሻለ)

11.የማይሰራበት ጥቅስ ከግብረስጋ ግንኙነት ቡኃላ (አሪት ዘሌዋውያን 15.16-18)

12.ስካር በእርቃን (ኖህ፤ዳዊት..) (ኦሪት ዘፍጥ 9.20-25)(1 ኛ መጽ ሳሙኤል 19:23-34)

13.በዚያም ቀን ግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጉር ይላጨዋል ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላል ትንቢተ ኢሳይያስ 7:20

14. እግዚአብሔር ሚስት አላውን ? (ትንቢተ ህዝቄኤል 16: 1-5 & 23.1-5) ትንቢተ ኢሳያስ 54፡5

15.እንደዚህ ታምኜ ስመካ የምናገረው፥ በሞኝነት እንጂ ጌታ እንዳዘዘኝ አልናገርም።2ኛ ቆሮንቶስ 11:17

16.‹…ከእናንተ ጋር ኵሳቸውን ይበሉ ዘንድ ሽንታቸውንም ይጠጡ ዘንድ..›መጽ ነገሥት ካልዕ 18:27

17. ሥጋቸውም እንደ አህየች ሥጋ ዘራቸውም እንደ ፈረሶች ዘር የሆነውን… ትንቢተ ሕዝቅኤል 23:20

18 ‹…ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም› ወደ ዕብራውያን 12:8

19. የጳውሎስ ዘረኝነት ፡‹እኛ በፍጥረት አይሁድ ነን ኃጢአተኞችም የሆኑ አሕዛብ አይደለንም፤ ገላቲያ 2፡15

20‹ቍላው የተቀጠቀጠ ብልቱም የተቈረጠ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ።ኦሪት ዘዳግም 23፡1

21.ሙሴ ኦሪትን ጽፎዋል ? መሞቱን አንዴት ሊጽፍ ቻለ‹.. በዚያ በሞዓብ ምድር ሞተ። ዘዳግም 34፡5

ዳጉ (የአፋር ባሕላዊ ኢንተርቪው)

አንድ አፋር ለሥራ አዲስ አበባ መጥቶ የሆነ ክርስቲያን የሥራ ባልደረባው ቤት ለዚያራ ሄዶ ግድግዳ ላይ የሆነ ፎቶ ተሰቅሎ አይቶ ,,, መቸም የዚህ የጥቁር ጓደኛው እናትም ዘመድም አልመስልህ ቢለው

አፋሩ ፡- ያ የማን ፎቶ ነው?

ደገኛው ፡- የድንግል የማርያም

አፋሩ ፡- ዘመዳችሁ ናት?

ደገኛው ፡- ኧረ አይደለም የእግዚአብሔር እናት ናት

አፋሩ ፡- አሁን በሕይወት አለች?

ደገኛው ፡- አይ የለችም ሞታለች

አፋሩ ፡- ማን ገደላት?

ደገኛው ፡- እግዚአብሔር።

አፋሩ ፡- እኮ ልጇ ?

ደገኛው ፡- አፈር ብላ

ጉድ በል , የመፅሀፍ ቅዱሱ ሳይሆን የቤተ ክርስትያኑ እግዚአብሔር እናቱን ገደለ ሲል ፡፡

አላህ ሂዳያ ይስጣቸው።

ሀጅ ያሲን (አይ)

አንድ ታሪክ ላንሳ

ወሎ ላይ የሚካአል ቤተክርስቲያን ሸዋበር መስጂድን አልፎ የሚገኝ ነዉ። ታድያ በአንድ ወቅት ታቦቱ በመስጂዱ አጠገብ ሲያልፍ መስጂዱጋ ሲደርስ አልሄድም ብሎ ቆመ። ታቦቱን አጅቦ የነበረዉም ሰዉ በሙሉ አብሮ ቆመ ።

ይህ መስጅድ ይፍረስ እና ታቦቱ ይለፍ ነዉ የመቆማቸው ምክንያት። ታዲያ ይህ ጥያቄ ለመስጂዱ ኢማም ይደርሳል። በወቅቱ የመስጂዱ ኢማም ሀጅ ያሲን(አይ) የአልአሙዲ አያት ናቸዉ። የተቀበሩት እዚያው ሸዋበር መስጂድ አካባቢ ነው እንደዉም እሳቸው የተቀበሩበት እና የአካባቢዉ ሰዉ መቃብር ቦታ እየተናደ እና ቆሻሻ አካባቢዉ ስለነበር አልአሙዲ የመቃብሩን አካባቢ ዙሪያ በሙሉ በግንብ እንዲታጠር ያስደረገው ።

እናም ታቦቱ አልሄድም መስጂዱ ካልፈረሰ አልሄድም ብሎ እንደቆመ ነው የሸዋበር መስጊድ ኢማም ሀጅ ያሲን እንደሰሙ መጡና ወጥተዉ ህዝቡም ታቦቱን አጅቦ አንደቆመ እንዲህ አሉ።

" አምጣው እኔ ልያዘው እና አልሄድም ካለ ወላሂ ይህን መስጂድ ሳይሆን ጠቅላላ የደሴን መስጂድ አፈርሳለሁ አምጣው" ሲሉ ወዲያው ከመስጂዱ ታቦቱን ይዘዉ አለፉ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የሚካኤል ታቦት በ ሸዋበር መስጊድ አልፎ አያውቅም በታች በሰኞ ገበያ በኩል እያለፈ ይገኛል። አልሀምዱሊላህ

ማን ይሞክር ?

ማርቆስ 16:16

ማርቆስ 16 ወንጌሉ ተከፍቶ ክርስቲያን ሙስሊምን ለውይይት ጠርቶ አንድ ቀን ጉድ ታየ በአደባባይ ወጥቶ

ለጥ ባለ ሜዳ ሰዉ ተመቻችቶ እውነተኛን መጽሃፍ ለማወቅ ታስቦ ዉጤቱን ለመስማት ሁሉም እየታታ መጽሃፍ ቅዱስ ወይስ ቁርአን ዛሬ የሚያሸጋ ስንቱ ገደል ገባ ስኩዋርን ፍለጋ ትንሽም ሳይቆይ ወዲያው ተጀመረ ክርክሩ ይሁን ውጤቱ ያማረ

ሜዳው ተጣበበ ሰዉ እየጨመረ::

ሙስሊሙን በመወከል እኔ ተመድቤ የነሷራ ወኪል ብቅ አለ ደርቤ

እውነት አሸናፊናት አውቃለው በልቤ

ዋሂዱል ቀሃርም ነበር አጠገቤ

የውይይት ርእስ ሲመረጥ ከቤቱ

ነሷራና ሙስሊም ዋና ልዩነቱ

አልዋጥ ብሎን ነው ኢሳ ጌትነቱ

በስቅለት ያመነ ጀነትን መግባቱ

አንድነቱ ቀርቶ አምላክ ሦስትነቱ

ሰው እየከፈረ በቀን በለሊቱ

ቶሎ ጀምሩልን ይሰማ ዉጤቱ

ያመነ የተጠመቀ

ከሃጢአት ሁሉ በእውነት የራቀ

ሰይጣንን ያወጣል ምንም ሳይቸግረው

አዲስ ቋንቋ ይፈጥራል ምንም አይበግረው

እባብን ይይዛል ከነህይወቱ

ይህ ብቻም አይደለም ተአምር መስራቱ

መርዝ እንኳ ቢጠጡ አማኞች አይሞቱ

ብሎ ተናገረ ማርቆስ በመልእክቱ

እስከዚህ ድረስ ነው አማኝ ብርታቱ

ሁሌ ያሸንፋል ኢየሱስ ጌትነቱ

እየሱስን አምልኩ እንዳትሳሳቱ

ይህን ለማጣራት ማርቆስን ክፈቱ

ብሎ ሲያበቃ ተራውን ደርቤ

ማላታይን ገዛሁ ልሳጠው አስቤ

በኢየሱስ ያመነ መርዝ እንኳ ቢጠጣ

አይሞትም ብለሃል ይኸው እንካ ጠጣ

ይህን ብዬ ስለው መልሶ ተቆጣ

አንስቼ ብሰጠው መርዙን ለደርቤ

እያየሁ አልሞትም አንሳ ካጠገቤ

አነበብኩኝ እንጂ አላምንም ከልቤ

ሰድቦኝ ፈትለክ አለ ጎበዙ ደርቤ

ውሸት ተጋለጠ እኔ ተሰድቤ

ዞር ብዬ ባየው የለም ካጠገቤ

ግራ ተጋባና አማኝ በእለቱ

መርዝ እንኳ ቢጠጡ ፔንጤዎች አይሞቱ

ትንሽዋ ብርሌ ማላታይን ይዛ

አንድ ብር ብቻ ናት ከሱቅ ስትገዛ

ሰአትም አትፈጅ ለማድረግ ጀናዛ

ለመስጠት ስፈልግ ወዲያው ለደርቤ

መድረክ ለቆ ኖሮ የለም ካጠገቤ

ማን ይሞክር ብዬ ደጋግሜ ብጣራ

መርዝ የሚጠጣ ከቶም የለም ፋራ

ብሎ ሰደበኝ ጎበዙ ደርቤ

አገር ቀያረና አሁን ገባ ሮቤ

በሙስሊም አሸናፊነት አበቃ ክርክር

ዛሬም ይቻትና መርዝዋን ማን ይሞክር

እቺ አነዋር መስጂድ የተፃፈች መፅሃፍ ቅዱስ ነች አለኝ

By ኻሊድ ያስፈልገናል

አንዱ ሙስሊም ባዬ ቁጥር ስበክ ስበክ የሚለው ክርስትያን ወገናችን ከኔ ጋር መወያየት ፍላጎቱ እንደሆነ ነግሮኝ እኔም ፍቃዴን ችሬው ውይይቱን ለመካታተል 7 የክርስትና እምነት ተከታዮች ባሉበት በአንድ የክርስትያን ወገኖች ቤት ተሰባሰብን።እነዚህ 7 ወገኖች በውይይት ቦታው መታደም እኔን ደስ ብሎኛል።በአላህ (ሱወ)መልካም ፍቃድ በራሳቸው ቤት ኢስላም ሊሰበኩ ነውና።

«አላሃምዱሊላህ»

ሁሉም ቦታ ቦታውን ከያዘ በኃላ ጋባዢ ሲያመልጠው ይሁን ሲያዳልጠው ባላውቅም በምን እርዕስ ላይ ነው እንድንወያይ የምትፈልገው ስለው

•ሰውን መግደል ወይም ጦርነት በእስልምናና ክርስትና የሚል ይሁን አለኝ እኔም ይሁና ጡሩ ስል ተስማማሁ።

ውይትቱ ተጀመረ።በተነሳው እርዕስ ላይ መጀመሪያ የመናገሩን እድል እኔ ለርሱ ሰጠሁት።ተወያዬም አላህ(ሱወ)ጦርነትን እንዳዘዘ፣ ቁረአኑም በጦርነትና ከእስልምና ውጭ ያሉ ሰዎችን ግዱሉ በሚል አናቅፆች እንደታጨቀ፣ነብዩ ሙሐመድም(ሰዐወ)የጦር አዝማች ጦረኛ አነንደሆኑ ለጆሮ በሚገማ የቃላት አገላለፅ እረጅም ሰዓት የውስጡን የጥላቻ ቋጠሮ ዘረገፈ።እኔም ይሄን ደግሞ የአላህን፣ የመልህተኛውን፣ የሙስሊሞችን ጥላቻ በመርፌ ነው መሰል የሰጡት እያልኩ ምድር ከተሸከመችው እጅግ መሪር ነገሮች እንደቀመሰ ሰው ንግግሩ ምርግግ፣ምርር ቢለኝም ይጨርስ ብዬ ጆሮዬን ሰጠሁት።

የእርሱ ጭፍን የጥላቻና ልቅ ዘለፋ እርሱ አልገባውም እንጂ ቀደም ድሮ ከክፉ መምህራኖቹ አንደበት፣በቴፕ ካሴቶቻቸው፣ከቪዲዮ ዲስኩራቸው ፣ከመፅሃፍቶቻቸው አውቃቸዋለሁ። አሁን ደክሞት ይሁን ይሄን ሁሉ ሰአት ዝም ብዬ መስማቴ ግራ ገብቶት ባላውቅም። ቆይ ይሄን ጉድ አንተስ ምን ትላለህ? እውነተኛ አምላክ አንዲህ ያዛል?

እውነተኛ ነብይ እንዲህ ሰው ይፈጃል?

እውነተኛ የፈጣሪ ቃል ይሄን በውስጡ ይይዛል?

አስላምስ እንዴት የሰውን ዘር እንዲህ እያስፈጅ በምን ምንገድ ትክክለኛ ሃይማት ሆነ?

ኢስላምስ የተስፋፋው በሰይፍ አይደል? ንግግሩን አበቃ ስል በጥያቄ ድርድራ ዙሩን አከረረው።

የሚለው አጥቶ የመስለኛል በመጨረሻ ለኔ የመተንፈሱን እድል ስጥቶ ወደ 7ቱ ታዳሚዎቻችን በኩራት እየተመለከተ ጨርሻለሁ አለ።

«አለሃምዱሊላህ አትሉም?»

እኔም አሳች ከሆነው የእርሱ አናጋሪ ሰይጣን በአላህ ስም ተጠብቄ ለጌታዬ እጅግ በጣም ላቅ ያለ ምስጋና አድርሼ በውዴ ነብዩ ሙሐመድ (ሰዐወ)ላይ ሰለዋት አውርጄ በአላህ ስም ወደ ውይይቱ ሜዳ ዘው አልኩ ወገኔ ከላይ ለዘረዘርከልኝ መረጃ ከመፅሃፍ ቅዱስህ እሻለሁ ብዬ ፅጥ አልኩ። ምን? ከመልሃፍ ቅዱስ ስለ ቁረአንና ሙሐመድ አንዳሳይህ ነው የፈለከው? ሲል በአግራሞት እየሳቀ ይሁን እየተሳቀቀ ባለየለት ሁናቴ ጠየቀኝ።እኔም እየሳቅኩ አዎ አልኩ።መፅሃፍ ቅዱስ ስለ ሙሐመድም ሆነ ቁረአናችሁ ምንም ነገር አይልም።

እሺ መፅሃፍ ቅዱሱ ምንም ካላለ ከቁረአን አሳየኝ ስል በእጄ የነበረውን የቁአን ትርጉም ዘረገሁለት አሁንኳ ሳቀ እረ እኔ ቁረአን አላውቅም። ከማለቱ ይሄን ሁሉ ሰዓት የፈጀ ንግግርህ መረጃ ቢስ ከሆነ ከንቱ ንግግር ነዋ ስታድርግ የዋልከው ብዬ ያነሳቸዋል ስል የጠበቅኳቸው የውሸት መምህራኑ የቆርጦ ቀጥል ስራዎችን ባለማቅረቡ ደስ ባይለኝም አንዲህ ስል አስረዳው ጀመርኩ

እየውልህ ወገኔ በሃይማኖት ማስገደድ በኢስላም ቦታ የለውም።እውነተኛው አምላካችን ኣላህ በሃይማኖት ማስገደድ እንደሌለ በተከበረው ቁርአኑ እንዲህ ይለናል:

"በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡ በጣዖትም የሚኸድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ፡፡ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው፡፡"(2:256)

«እውነቱም ከጌታችሁ ነው፡፡ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ» በላቸው፡፡"(18:29)

ስለዚህ ሃይማኖትን በማስገደድ ሰዎች ላይ መጫን በኢስላም ክልክል ነው።ደግሞስ ተገዶ ሰልሞ ምን ሊሰራ።

•ክብር የሆነውን የሰውን ልጅ መግደልንም አስመልክቶ አላህ እንዲህ ብሏል

«ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው፡፡»(5:32)

ያቺንም አላህ ያወገዛትን ነፍስ ያለ ሕግ አትግደሉ፡፡"(17:33)

ኢስላም የተስፋፋው በሰይፍ ነው የሚለውም ስህተት ነው እንዴት ሰላም በሰይፍ ይድፋፋል ተብሎ ይታመናል?

ኢስላም ማለትኮ ሰላም ማለት ነው።ነብዩ ሙሐመድም ሰይፍ አላነሱም።ሰይፍ ተነስቶባቸው እርሳቸው ከሃገር ተነኝባረሩ፣ ተከታዮቻቸው ተገደሉ ነበረረት ተዘረፈ።የመከራ ናዳ አስተናገዱ።እናም ጦር የለም። እርሳቸው ውዴ ነብዩ ሙሐመድ የተላኩት ለዚህች አለም እዝነት ተደርገው ነው። አላህ እንዲህ ይገልፃቸዋል

«ሙሃመድ ሆይ ለአለማትም እዝነት አድርገን እንጂ አላክንህም»ቁረአን 21:107

ካልኩት በኃላ "የራሷ አሮባት የሰው ታማስላለች"እንዲሉ አደረኩበት ነገሩን።

ቆይ እኔ የምልህ መፅሃፍ ቅዱስ ላይ በዙ የጭፍጨፋ አንቀፆችን አይቼ ነበር ልታብራራልኝ ትችላለህ?

መፅሃፍ ቅዱስ? ውስጥ ጭፍጨፋ? እኛ ጋር ጭፍጨፋ ብሎ ነገር የለም ፍቅር ሰላም ብቻ ይሰበካል አለ።

ጡሩ ነዋ መፅሃፍ ቅዱሱ ፍቅር፣ሰላም ሰባኪ ከሆነ አናቅፆቹን አብረን እንያ? እሺ ይቻላል

እኔም ቀጣዮቹን ስቅጣጭ የመፅሃፍ ቅዱስ አንቀዘፆች አንድ ሁለት እያልኩ ዘርግፌበት የሚለውን ለመስማት ጓጉቻለሁና

ዘረገፍኩበት አዎ ዘረገፍኩበት!!

1ኛ •የሌዊም ልጆች ሙሴ እንዳለ አደረጉ፤ በዚያም ቀን ከሕዝቡ ሦስት ሺህ ሰዎች ሞቱ።አሪት ዘጸአት 32 : 28

2ኛ •እርሱም። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የእናንተ ሰው ሁሉ ሰይፉን በወገቡ ላይ ይታጠቅ፥ በሰፈሩም ውስጥ በዚህና በዚያ ከበር እስከ በር ተመላለሱ፥ የእናንተም ሰው ሁሉ ወንድሙን ወዳጁንም ጎረቤቱንም ይግደል አላቸው። አሪት ዘጸአት 32 : 27

3ኛ •ማናቸውም ሰው ቢኰራ፥ በዚያም አምላክህን እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚቆመውን ካህኑን ወይም ፈራጁን ለመስማት ባይወድድ፥ ያ ሰው ይሙት፥ ከእስራኤልም ዘንድ ክፋትን አስወግድ፤ አሪት ዘዳግም 17 : 12

4ኛ •አሁንም ሄደህ አማሌቅን ምታ፥ ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፥ አትማራቸውም፤ ወንዱንና ሴቱን ብላቴናውንና ሕፃኑን በሬውንና በጉን ግመሉንና አህያውን ግደል። መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15 : 3

5ኛ •እኔም እየሰማሁ ለሌሎቹ። እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ መካከል አለፉ ግደሉም፤ ዓይናችሁ አይራራ አትዘኑም፤

ሽማግሌውንና ጐበዙን ቄንጆይቱንም ሕፃናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ፤ ነገር ግን ምልክቱ ወዳለበት ሰው ሁሉ አትቅረቡ፤ በመቅደሴም ጀምሩ አላቸው። በቤቱም አንጻር ባሉ ሽማግሌዎች ጀመሩ። ትንቢተ ሕዝቅኤል 9 :5–6

6ኛ• በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም።ሰውን ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፥ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤የማቴዎስ ወንጌል 10 :34–35

7ኛ •ነገር ግን እነዚያን በላያቸው ልነግሥ ያልወደዱትን ጠላቶቼን ወደዚህ አምጡአቸው በፊቴም እረዱአቸው።የሉቃስ ወንጌል 19 : 27

8ኛ •እርሱም። አሁን ግን ኮረጆ ያለው ከእርሱ ጋር ይውሰድ፥ ከረጢትም ያለው እንዲሁ፤ የሌለውም ልብሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ። የሉቃስ ወንጌል 22 : 36

አሁን ችግር ተፈጠረ

ከላይ ያሉት የመፅሃፍ ቅዱስ አንቀፆች እንዳነበብኩ ልጅ በአይነ ሂሊናችሁ ትስሉት ዘንድ በጣም ቀይ ወጣት ነው።ቀና ብዬ ሳየው ፊቱ ቲማቲም መስሎ ላብ አጥምቆታል። አይኑ ደግሞ ደም መስሏል።ሰውነቱ ይርዳል።

ቆይ ቆይ አንተ? ምንድን ነው የምታነበው? ሲል አይኑን በኔ ላይ አጉረጠረጠ።

«ፈረህ ወይ አትሉኝም? ኣይ ያመመው ነው የመሰለኝ»

መፅሃፍ ቅዱስ ነዋ አልኩና ምነው ተናደድክ አልኩ አምጣው እሲኪ መፅሃፍ ቅዱስህን ብሎኝ ከመንጠቅ ባልተናነሰ መፅሃፉን ተቀብሎኝ ማስታወሻ ላይ የፃፋቸውን ከላይ ያሉትን አቀፆች መፅሃፍ ቅዱሱ ላይ መኖራቸውን አረጋገጠ።

በፍፁም የሄ የኛ መፅሃፍ ቅዱስ አደለም።

እቺ_አነዋር_መስጂ_የተፃፈች_መፅሃፍ_ቅዱስ_ናት_ብሎኝ_ዘሎ ተነሳና የሰበሰባቸውን ሰዎች ተነሱ ከነዚህ ጋር መከራከር አያስፈልግም ብሎ በቤታቸው ቁጭ አድርገውኝ በር ከፍተው ፈረጠጡ።ጓዳ ተደብቃ ውይይቱን ስትከታተል የነበረች አንድ በአስራወቹ አጋማሽ ላይ የምትገኝ እንስትም በሩን ከፍታ በሳሎን አድርጋ ምንም ሳትለኝ እነርሱን ተከትላ ከቤት ወጣች።

እኔም ደግሞ ሌላ ችግር እንዳይፈጥሩብኝ ብዬ ልጅቱን ተከትዬ ከግቢው ወጣሁ የውጨም በር ክፍት ነብርና እህት ሂጃለሁ በሩን ዝጉት ብዬ።

ነዞ ወደ ጌጆዬ ከሳሽ የተከሳሺን መልስ ባወቀ ኖሮ……

አጃቢዎቹስ?

መንግስተ ሰማያት(ጀነት) ለ144,000 እስራኤላውያን ብቻ ተዘጋጅ ሲሆን ሌላው የጀህነም መሆኑ መፅሀፍ ቅዱስ ያስተምራል።

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንግስተ ሰማያት ለ144,000 እስራኤላውያን ብቻ ተዘጋጅቶ ሌሎች የሰው ዘሮች በሙሉ የሚቃጠሉ መሆኑን የሚገልጽ ከሆነ የመረጥነው ጎዳና ምን ያህል ቀጥተኛ ነው ብለን ህሊናችንን መጠየቅ አለብን፡፡ የዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 7:1-8 እና ምዕራፍ 9 በምናይበት ጊዜ በጣም ያስደነግጣል ተስፋም ያስቆርጣል፡፡

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ አገላለጽ መሠረት ለመንግሥት ሰማያት የታጨት አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ / 144,000 ሰዎች ብቻ ሲሆኑ እነርሱም ከአሥራ ሁለት የእስራኤል ልጆች (ነገዶች) ከእያንዳንዳቸው ደግሞ አሥራ ሁለት ሺህ /12,000 ቁጥር ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡

ይኸውም ከእስራኤል ከመጀመሪያው ከአይሁዳ ነገደ 12,000 እስከ ብኒያም ነገደ 12,000 12 ነገደ × 12,000 =144,000 የእግዚአብሔር ማህተም በግንባራቸው ይታተምባቸውና ሌሎች የሰው ዘሮች በሙሉ ይቃጠላሉ ይባላል፡፡

ይህንን የሚተነትነው የዮሐንስ ራዕይ 9 ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡

1/ ከእያንዳንዱ የእስራኤል ነገደ ለመንግስተ ሰማያት የሚመረጡት ከ12,000 ሊበልጡና ሊያንሱ ያለመቻላቸው.12,000+1 ወይንም 12,000-1 አለመሆናቸው እራሱ ሌላ ጥያቄ ያስነሣል:: ኮታው ቀድሞ ከታወቀና ለ12ቱ የእስራኤል ነገዶች በእኩል ከተከፋፈለ የሌላው ድካም ሁሉ ያለ ውጤት ይቀራል ለማለት ያስደፍራል::

2/ እስራኤላውያን እስከ ዛሬ የሚተዳደሩት በሙሴ /ዐሰ) ሕግጋቶች ሆኖ የኢየሱስን ነብይነት እንኳን ሣይቀበሉ እንዴት መንግስተ ሰማያት እንደ ሚገቡ ፍጹም አጠያያቂ ጉዳይ ነው::

ይህ ምናልባት መንግስተ ሰማያት መጀመሪያውኑ ለእስራኤል ልጆች ሽልማት የተዘጋጀች ስለሚያስመስል ሚስጥሩን የመጽሐፍ ቅዱስ ሰባኪዎች ይፍቱት እንጂ መልሱ እንዲያው ዝም ነው::

ትውልድ በሙሉ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት:: ለራስ ሲቆርሱ እያሳነሱ እንደሚባለው ሁሉ አይሁዶችና ነሳራዎች መንግስተሰማያትን በግላቸው የተቆጣጠሩ ይመስላል:: ፈጣሪ በግል የሚያዝ ሳይሆን የአለማት ጌታ ነው::

መንግስተሰማያት ደግሞ የንፁህን ናት እንጂ የአንድ ጎሳ ብቻ አይደለችም:: ሁመቱም እንዲህ ሲሉ ራሳቸውን እንደሚያሞካሹ ቁራአን ግልፅፅ አድርጎታል :: አላህ (ሱ,ወ) እንዲህ ይላል "እኛ የአላህ ልጆቹና ምርጦቹ ነን" በል " ለምንስ በወንጀላችሁ ይቀጣችኋል" 5:18

19.ንጽህና

የኃጢአት ስርየት

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2)። የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)።

ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን። ይህ ኃጢአት በውርስ የተገኘ ሳይሆን በግብር (ባለመታዘዝ) የመጣ ያለ-ፍጽምናችን ውጤት ነው። ኃጢአት ደግሞ በጌታ አላህ ዘንድ በይቅርታ ካልታለፈ ዋጋ ያስከፍላል። ዋጋውም ሞት ሳይሆን የጀሀነም እሳት ነው (ወል-ዲያዙ ቢላህ)።

እስከዛሬ በሕይወት የቆየነውም በመልካም ሥራችን ብዛትና በእምነታችን ጥንካሬ ሳይሆን፡ በአላህ ታጋሽነትና ቻይነት፣ እንዲሁም ለቅጣት ባለመቸኮሉ ሰበብ ነው። ባጠፋን ጊዜ ወዲያው በቅጣት የሚይዘን ቢሆን ኖሮ፡ በዚህ ምድር ላይ አንድም ተንቀሳቃሽ አይኖርም ነበር። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" وَلَوْ يُؤَاخِذُ اللَّهُ النَّاسَ بِمَا كَسَبُوا مَا تَرَكَ عَلَى ظَهْرِهَا مِنْ دَابَّةٍ وَلَكِنْ يُؤَخِّرُهُمْ إِلَى أَجَلٍ مُسَمًّى فَإِذَا جَاءَ أَجَلُهُمْ فَإِنَّ اللَّهَ كَانَ بِعِبَادِهِ بَصِيرًا " فاطر سورة 45

"አላህም ሰዎችን በሰሩት ኀጢያት ቢይዝ ኖሮ በወለሏ (በምድር) ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ ባልተወ ነበር፤ግን እተወሰነ ጊዜ ድረስ ያቆያቸዋል፤ ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት (በኀጢያታቸው ይቀጣቸዋል)፤ አላህ በባሮቹ ሁኔታ ተመልካች ነውና።" (ሱረቱ ፋጢር 35፡45)።

ዛሬ አላህ ፈቃዱ ከሆነ የሰዎች ኃጢአት በአላህ ዘንድ ይቅርታን ሊያገኙ ከሚችሉባቸው መንገዶች የተወሰነውን ነው። ለዚህም ጽሑፍ መነሻ ምክንያት የኾነኝ አንድ ከርስቲያን ወገን ‹‹ሙስሊሞች ኃጢአታችሁ ይሰረዝ ዘንድ በእሾህ መወጋት አለባችሁ?›› ወይ በማለት በአንድ ሐዲሥ ላይ የተሳሳተ ግንዛቤን በመያዙ ነው። መልካም ንባብ፡-

1/ ተውበት (ንሰሀ) ፡-

ይህ አንዱና ዋነኛው መንገድ ነው። ማንኛውም ኃጢአት በተውበት ይሰረዛል። ተውበት የማይሰርዘው ምንም ኃጢአት የለም። በመሆኑም አንድ ሰው ለሰራው ኃጢአት ኹሉ የአላህን ይቅርታ በመፈለግ ከልብ ተጸጽቶ ወደ አላህ ተውበት ካደረገ፡ አላህ ኃጢአቱን ይምረዋል። እንድን ዘንዳም ሁላችን ወደ አላህ በተውበት እንመለስ። ቃሉ እንዲህ ይላልና፡-

" وَتُوبُوا إِلَى اللَّهِ جَمِيعًا أَيُّهَ الْمُؤْمِنُونَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ النور سورة 31 "...

"...ምእምናኖች ሆይ! ትድኑ ዘንድ ሁላችሁም ወደ አላህ (በመመለስ) ተጸጸቱ።" (ሱረቱ-ኑር 24:31)።

" بَعْدِهِ مِنْ تَابَ ثُمَّ بِجَهَالَةٍ سُوءًا مِنْكُمْ عَمِلَ مَنْ أَنَّهُ الرَّحْمَةَ نَفْسِهِ عَلَى رَبُّكُمْ كَتَبَ عَلَيْكُمْ سَلَامٌ فَقُلْ بِآيَاتِنَا يُؤْمِنُونَ الَّذِينَ جَاءَكَ وَإِذَا رَحِيمٌ غَفُورٌ فَأَنَّهُ وَأَصْلَحَ " الأنعام سورة 54

"እነዚያም በተአምራታችን የሚያምኑት (ወደ አንተ) በመጡ ጊዜ «ሰላም በእናንተ ላይ ይኹን። ጌታችሁ በነፍሱ ላይ እዝነትን ጻፈ። እነሆ ከእናንተ ውስጥ በስሕተት ክፉን ሥራ የሠራ ሰው ከዚያም ከእርሱ በኋላ የተጸጸተና ሥራውን ያሳመረ እርሱ (አላህ) መሓሪ አዛኝ ነው» በላቸው።" (ሱረቱል አንዓም 6:54)።

2/ ታዛዥነት (መልካም ሥራ)፡-

ሌላው ሁለተኛው መንገድ ነው። አላህ ያዘዘውን መልካም ሥራ መፈጸም የኃጢአት ስርየትን ያስገኛል። ይህ ኃጢአት ግን ታላላቅ ከተሰኙት ውጭ ያለውን ነው። ታላላቅ ኃጢአት በተውበት እንጂ በመልካም ሥራ ብዛት ይቅር አይባልምና። ወላሁ አዕለም። ይህ በመኾኑም በመልካም ሥራ ላይ (ፆም፣ ሶደቃህ፣ ዘካህ፣ መልካም ንግግር...) ሳንሳነፍ መበረታታት ይገባናል። የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" لِلذَّاكِرِينَ ذِكْرَى ذَلِكَ السَّيِّئَاتِ يُذْهِبْنَ الْحَسَنَاتِ إِنَّ اللَّيْلِ مِنَ وَزُلَفًا النَّهَارِ طَرَفَيِ الصَّلَاةَ وَأَقِمِ هود سورة 114

"ሶላትንም በቀን ጫፎች፤ ከሌሊትም ክፍሎች ፈጽም፤ መልካም ሥራዎች ኀጢአቶችን ያስወግዳሉና፤ ይህ ለተገዛጮች ግሣጼ ነው። " (ሱረቱ ሁድ 11:114)።

حَسَنٍ بِخُلُقٍ النَّاسَ وَخَالِقِ تَمْحُهَا، الحَسَنَةَ السَّيِّئَةَ وَأَتْبِعِ كُنْتَ، حَيْثُمَا اللهِ اتَّقِ :وَسَلَّمَ عَلَيْهِ اللَّهُ صَلَّى اللهِ رَسُولُ لِي قَالَ :قَالَ ذَرٍّ أَبِي عَنْ.

ከአቢ-ዘር (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው፡ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉኝ፡- ‹‹አላህን የትም ስፍራ ኾነህ ፍራው! መጥፎን በሰራህ ጊዜ መልካም ሥራን ወዲያው አስከትል። (መጥፎውን) ታጠፋልሀለችና፣ ሰዎችንም በጥሩ ስነ-ምግባር ቅረባቸው›› (ቲርሚዚይ 1984)።

3/ ውሀ፡-

በየሱቁ እየገባን፣ በየቧንቧው እየተደቀንን፣ በየቦኖው እየተሰለፍን ለመጠጣትና ለመቅዳት እንዳንቸኩል!። ለማለት የፈለግሁት በውሀ የሚፈጸም የዉዱእ ትጥበትን ነው። ዉዱእ ከንጽህናውም ባሻገር ኃጢአትን የመደምሰስ ኃይል አለው። በአላህ ፈቃድ በዉዱእ ስነ-ስርኣት ብቻ ትናንሽ ኃጢአትን ማስወገድ ይቻላል። የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ይላሉ፡-

مِنْ خَرَجَ وَجْهَهُ فَغَسَلَ -الْمُؤْمِنُ أَوْ -الْمُسْلِمُ الْعَبْدُ تَوَضَّأَ إِذَا" :وسلم عليه الله صلى الله رسول قال :قال عنه، الله رضي هريرة، أبي مَعَ يَدَاهُ بَطَشَتْهَا كَانَ خَطِيئَةٍ كُلُّ يَدَيْهِ مِنْ خَرَجَ يَدَيْهِ غَسَلَ فَإِذَا -الْمَاءِ مَعَ أَوْ آخِرِ قَطْرِ مَعَ -الْمَاءِ مَعَ بِعَيْنَيْهِ إِلَيْهَا نَظَرَ خَطِيئَةٍ كُلُّ وَجْهِهِ

مِنْ نَقِيًّا يَخْرُجَ حَتَّى -الْمَاءِ قَطْرِ آخِرِ مَعَ أَوْ -الْمَاءِ مَعَ رِجْلَاهُ مَشَتْهَا خَطِيئَةٍ كُلُّ خَرَجَتْ رِجْلَيْهِ غَسَلَ فَإِذَا -الْمَاءِ قَطْرِ آخِرِ مَعَ أَوْ -الْمَاءِ الذُّنُوبِ". مسلم أخرجه (244).

ከአቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው፡ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- ‹‹አንድ ሙስሊም (ሙእሚን) ዉዱእን በሚያደርግ ጊዜ፡ ፊቱን ሲያጥብ (ያልተፈቀደለትን ነገር) በአይኑ ተመልክቶ የነበረው ኃጢአት ዅሉ ከውሀው ጠብታ ጋር ይወገዳል፡፡ ሁለት እጆቹን ሲያጥብ ደግሞ፡ በእጁ (ያልተፈቀደለትን ነገር) ይዞ (ጨብጦ) የነበረው ኃጢአት ዅሉ ከውሀው ጠብታ ጋር ይወገዳል፡፡ ሁለት እግሮቹን ሲያጥብ ደግሞ፡ እግሮቹ (ወዳልተፈቀደ ስፍራ) ተጉዘውበት የነበረው ኃጢአት ዅሉ ከውሀው ጠብታ ጋር ይወገዳል፡፡ በዚህ መልኩ ከኃጢአት ዅሉ የጠራ ኾኖ እስኪወጣ ድረስ (ኃጢአቱ ይወገዳል)›› (ሙስሊም 244)፡፡

4/ ዚክር (ውዳሴ)፡-

ጌታ አላህን መዘከር፡ የርሱን ታላቅነት በማውሳትና ለባሮቹ የዋለውን ጸጋ በማስታወስ እሱን ማወደስ፡ የኃጢአት ስርየት ከሚገኝባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ አላህን በማውሳትና በማወደስ ላይ ልንበረታ ይገባናል፡፡ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ይላሉ፡-

اللهَ وَكَبَّرَ وَثَلَاثِينَ، ثَلَاثًا اللهَ وَحَمِدَ وَثَلَاثِينَ، ثَلَاثًا صَلَاةٍ كُلِّ دُبُرِ فِي اللهَ سَبَّحَ مَنْ وَسَلَّمَ عَلَيْهِ اللهُ صَلَّى اللهِ رَسُولِ عَنْ هُرَيْرَةَ، أَبِي عَنْ قَدِيرٌ شَيْءٍ كُلِّ عَلَى وَهُوَ الْحَمْدُ وَلَهُ الْمُلْكُ لَهُ لَهُ، شَرِيكَ لَا وَحْدَهُ اللهُ إِلَّا إِلَهَ لَا :الْمِائَةَ تَمَامَ وَقَالَ وَتِسْعُونَ، تِسْعَةٌ فَتْلِكَ وَثَلَاثِينَ، ثَلَاثًا الْبَحْرِ زَبَدِ مِثْلَ كَانَتْ وَإِنْ خَطَايَاهُ غُفِرَتْ " مسلم 1380.

ከአቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው፡ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- ‹‹ከእያንዳንዱ ፈርድ ሶላት በኋላ አላህን 33 ጊዜ ‹‹ሱብሐነላህ፣ 33 ጊዜ ‹‹አልሐምዱ ሊላህ››፣ 33 ጊዜ ‹‹አላሁ አክበር›› በማለት፡ በድምሩ 99 ጊዜ ያወሳና ያወደሰ ሰው፡ በመቶኛውም ‹‹ላ ኢላህ ኢልለሏህ ዋሕደሁ ላሸሪከ ለህ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምድ፣ ወሁወ ዐላ ኩልሉ ሸይኢን ቀዲር›› ያለ ከኾነ፡ ኃጢአቱ የባሕር አረፋ ቢያህል እንኳ ይሰረዝለታል›› (ሙስሊም 1380)፡፡

5/ ሙሲባህ (መከራና እንግልት)፡-

የአላህ ባሪ የኾነ ሙስሊም በምድራዊ ሕይወቱ ላይ ማንኛውም አይነት ችግር ገጥሞት፡ በደረሰበት ችግር አምላኩን ከማማረር ይልቅ ታጋሽ ኾኖ ቢያልፈውና ከአላህም ዘንድ በምትኩ መልካም ነገርን ተስፋ የሚያደርግ ከኾነ፡ በእያንዳንዱ በሚደርስበት ምድራዊ እንግልቶች ዅሉ የኃጢአት ስርየትን ያገኛል፡፡ አላህ ትግስትን ይወፍቀን፡፡ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ይላሉ፡-

غَمٍّ، وَلَا أَذًى وَلَا حُزْنٍ وَلَا هَمٍّ وَلَا وَصَبٍ، وَلَا نَصَبٍ مِنْ الْمُسْلِمَ، يُصِيبُ مَا» :قَالَ وَسَلَّمَ عَلَيْهِ اللهُ صَلَّى النَّبِيِّ عَنِ :هُرَيْرَةَ أَبِي عَنْ خَطَايَاهُ مِنْ بِهَا اللَّهُ كَفَّرَ إِلَّا يُشَاكُهَا، الشَّوْكَةِ حَتَّى» البخاري 5641.

ከአቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው፡ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- ‹‹አንድን ሙስሊም ድካምም ኾነ በሽታ፣ ፍርሀትም ኾነ ትካዜ፣ መከራም ኾነ ጭንቀት፣ እንዲሁም የሚወጋውም እሾሕ ቢኾን አይደርስበትም፡፡ አላህ በነዚህ ሰበብ ኃጢአቱን የሰረዘለት ቢኾን እንጂ!›› (ቡኻሪይ 5641)፡፡

አምላካችን አላህ ሆይ! ከሞት በፊት ትክክለኛ ተውበትን፣ በሞት ጊዜ ሸህዳን፣ በቀብር ፈተና ጽናትን፣ በአኼራ ደግሞ ከእሳት ተርፎ ጀነትን በራሕመትህ ወፍቀን! አላሁመ አሚን፡፡

ትጥበት እና ሃይማኖታዊ ብያኔው!

በአላህ ሥም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ክብርና ምሥጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን(አል-ፋቲሓ 2)፡፡ የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡

1/ ትጥበት በኢስላም፡- ባህላዊ ስርአት ወይም ግለሰባዊ ፍልስፍና ሳይኾን፡ ሸሪዐዊ መሠረት ያለው፡ በጌታ አላህ የታዘዘ፡ አጅርንም የሚያስገኝ አንድ የእምነት አካል ነው፡፡ የጌታ አላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እናንተ የሰከራችሁ ኾናችሁ የምትሉትን ነገር እስከምታውቁ፡ የረከሳችሁም ስትኾኑ መንገድን አላፊዎች ካልኾናችሁ በስተቀር (አካላታችሁን) #እስከምትታጠቡ ድረስ ስግደትን አትቅረቡ፡፡ በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትኾኑም፥ ወይንም ከእናንተ አንዱ ከዓይነምድር ቢመጣ፥ ወይንም ሴቶችን ብትነካኩና ውሃን ባታገኙ፣ ንጹሕ የኾነን የምድር ገጽ አስቡ፡፡ ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁንም (በርሱ) አብሱ፡፡ አላህ ይቅር ባይ መሓሪ ነውና፡፡" (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡43)፡፡

ከአቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "እያንዳንዱ ሙስሊም በሰባት ቀን ውስጥ (በሳምንት) ቢያንስ አንድ ጊዜ ገላውን ሊታጠብ ይገባዋል" (ቡኻሪይ 897፣ ሙስሊም 2000)፡፡

ትጥበት ብዙ ጥበቦችና ጥቅሞች አሉት፡፡ ንጽህና የኢማን አንድ ክፍል ነው፡፡ በመኾኑም ከልባዊ ንጽህና ቀጥሎ አካላዊ ንጽህና በራሱ አጅር ያለው ተግባር ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ‹‹ንጽህና የኢማን አንድ ክፍል ነው›› በማለት አስተምረዋል (ሙስሊም የዘገበው)፡፡

በትጥበት ሰበብ ንጽህና ይገኛል፡፡ በላብና መሰል ነገራት ሰውታችን ላይ የሚኖሩ መጥፎ ጠረኖች በትጥበት ሰበብ ይወገዳሉ፡፡ ሰዎችም ዘንድ በመጥፎ ሽታችን የራቁን ከመኾን ይልቅ፡ የተወደድን ኾነን እንቀርባለን፡፡ ትጥበት ንቃትን ያመጣል፡፡ ድብርትን እና ጫንታን በማስወገድ፡ ኃይልንና ጉልበትን ያጎናጽፋል፡፡

ትጥበት ሃይማኖታዊ ብይኑ ለሁለት ይከፈላል፡፡ (ዋጂብ) ግዳጅ የኾነና (ሙስተሐብ) ተወዳጅ የኾነ ማለት ነው፡፡ ግዳጅ የኾነ ማለት፡- መፈጸሙ ከአላህ ዘንድ አጅር የሚያስገኝ፡ አለመፈጸሙ ደግሞ የሚያስጠይቅና የሚያስቀጣ ዋጂብ የኾነ ማለት ነው፡፡

ተወዳጅ የኾነ ማለት ደግሞ፡- መፈጸሙ ከአላህ ዘንድ አጅር የሚያስገኝ፡ አለመፈፀሙ ደግሞ የማያስጠይቅ እና የማያስቀጣ የኾነ ሱንና ተግባር ማለት ነው፡፡ የግዳጅ ትጥበት የሚባሉት፡-

ሀ/ የዘር ፈሳሽ መውጣት፡- አንድ ሙስሊም የኾነ ሰው በግንኙነት ወይም በህልም ወይም ብልት በመነካካት ወይም ባለቤቱን በማሻሻት ሰበብ ከብልቱ የዘር ፈሳሽ (ስፐርም) ከወጣው፡ ይህ ሙስሊም ሶላት ለመስገድ ወይንም የአላህን ቃል ቁርኣንን ለማንበብ፡ ትጥበት ግድ (ዋጂብ) ኾኖበታል ማለት ነው፡፡ ዐሊይ ኢብኑ አቢ ጧሊብ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዲህ ይላል፡- "የአላህ መልክተኛን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ስለ መዚይ ጠየቅኳቸው፡፡ እሳቸውም ‹‹መዚይ ውዱእ ያስደርጋል፡ መኒይ ደግሞ ገላን ያስታጥባል›› አሉኝ፡፡" (ቲርሚዚይ 114፣ ኢብኑ ማጀህ 504)፡፡

‹‹መዚይ›› ማለት፡- ሰውየው ግኑኝነትን በሚያስብበት ወቅት ከሰውነቱ የሚወጣ፡ የሚያጣብቅ ቀጠን ያለ ነጭ መልክ ያለው፡ በመውጣቱ ለግለሰቡ ምንም ስሜት የማይሰጠው፡ ተስፈንጣሪ ያልኾነ ሲሆን፣ ‹‹መኒይ›› የሚባለው ደግሞ፡- የወንዱ ወፍራምና ነጭ፡ በስሜት ተስፈንጥሮ የሚወጣ ሲኾን፡ የሴቷ ደግሞ፡ ቀጭንና ዳለቻ መልክ ያለው ነው (ኢማሙ ነወዊይ፡ ሸርሑ ሶሒሕ ሙስሊም፡ 3/222) ፡፡

ነገር ግን፡ ግለሰቡ በበሽታ ወይም በብርድ ሰበብ ያለ-ምንም ስሜት (ሸህዋ) መቀስቀስ፡ የዘር ፈሳሽ (መኒይ) ቢወጣው፡ ቦታውን በውሀ ማጠብ እና ዉዱእ ማድረግ እንጂ ጥትበት አይወጅብበትም፡፡ በስዑዲ የሚገኘው የዑለማእ ቋሚ ምክር ቤት ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ለቀረበለት ጥያቄ እንዲህ መልሷል፡-

ጥያቄ. አንድ ሰው ከእርካታ ስሜት ጋር በተያያዘ ከሰውነቱ የዘር ፈሳሽ ወጣው፡፡ ሌላኛው ግለሰብ ደግሞ ያለ-ምንም የእርካታ ስሜት የዘር ፈሳሽ ወጣው፡፡ ሶስተኛው ሰው ደግሞ፡ የዘር ፈሳሽ ሳይወጣው የእርካታ ስሜት ተሰማው፡፡ ጥያቄው፡- ከሶስቱ ትጥበት የሚወጅበው በማንኛቸው ላይ ነው?

መልሲ የመጀመሪያው የዘር ፈሳሽ ከእርካታ ስሜት ጋር የወጣው ሰውዬ ጀናባ ኾኗልና ከጀናባ መታጠብ ግድ ይለዋል፡፡ ሁለተኛው ያለ-ምንም የእርካታ ስሜት የዘር ፈሳሽ የወጣው ግለሰብ ምንም ትጥበት የለበትም፡፡ ኢስቲንጃእ እና ዉዱእ ማድረግ ብቻ ነው የሚጠበቅበት፡፡ ሶስተኛው ግለሰብ ደግሞ፡ የእርካታ ስሜት ስለተሰማው ብቻ ምንም አይነት ትጥበትም ኾነ ዉዱእ ማድረግ አይጠበቅበትም፡፡ (ፈታዋ-ለጅነህ 4/ 162-163፡ ፈትዋ ቁ. 20514)፡፡

አሽ-ሸይኽ ሷሊህ አል-ሙነጂድ (ሐፊዘሁላህ) እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹መኒይ (የዘር ፈሳሽ) ያለ-ምንም ስሜት ከሰውነት ቢወጣ፡ ፍርዱ ምን ይኾናል? በሚለው ዙሪያ የኢስላም ሊቃውንቶች በሀሳብ ተለያይተዋል፡፡ የተሻለውና በላጩ አስተያየት ግን፡ ያለ-ስሜት የወጣ የዘር ፈሳሽ ትጥበትን ሳይኾን ኢስቲንጃእና ዉዱእን ብቻ ነው ግድ የሚያደርገው የሚለው ነው፡፡ ለዚህም ማሥረጃው ቀጥሎ ያለው ሐዲሥ ነው፡፡

وصححه (206) داود أبو رواه (فَاغْتَسِلْ المَاءَ فَضَخْتَ إِذَا) :عنه الله رضي طالب أبي بن لعلي وسلم عليه الله صلى النبي قول والدليل
وبتدفق بشهوة خروجه : هو الماء وفضخ . (125) "الإرواء" في الألباني

ረሱል (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ዐሊይ ኢብኒ አቢ-ጧሊብን (ረዲየላሁ ዐንሁ)፡- ‹‹ውሀን በረጨህ ጊዜ ታጠብ›› ብለውታል፡፡›› (አቡ ዳዉድ 206፣ ነሳኢይ 193)፡፡ በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ‹‹ፈዶኽተ›› የሚል የዐረብኛ ቃል አልለ፡፡ ፈድኽ ማለት፡- በስሜትና

በፍጥነት የዘር ፈሳሽን መርጨት የሚል ትርጉም ነው ያለው፡፡ (https://islamqa.info/ar/47693)፡፡ በተጨማሪም፡- (ሙሐመድ ሙኽታር አሽ-ሺንቂጢይ፡ ሸርሑ ዛዱል-ሙስተቅነዕ 17/5 ይመልከቱ)፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

ለ/ ግብረ-ሥጋ ግኙኝነት፡- አንድ ሙስሊም ከባለቤቱ ጋር ግብረ-ሥጋ ግኙኝነት ከፈጸመ፡ የዘር ፈሳሽ ወጣውም አልወጣውም፡ ከባለቤቱ ጋር በመገናኘቱ ብቻ ትጥበት ግዴታ ኾኖበታል፡፡ የሁለቱም ብልት የግርዛት ቦታው ከተነካኩ፡ የሱ ብልት ወደሷ ማጎፀን ከገባ ትጥበት ይወጅባል ማለት ነው፡፡ ረሱል ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ይላሉ፡- "ሁለቱ ግርዛቶች (ወንዱና የሴቷ ብልት) ከተገናኙ፡ የዘር ፈሳሽ ባይወርድም ትጥበት ግድ ኾኗል፡፡" (ኢብኑ ማጀህ 611፣ ቲርሚዚይ 109)፡፡

ሐ/ የወር አበባ ደም መቋረጥ፡- አንዲት ሙስሊም እሕት የወር አበባ ደሟ (ሐይድ) በተለመደው ቀን በቆመ ጊዜ ወዲያው መታጠብ ይኖርባታል፡፡ በወር አበባ ወቅት ባል ከሚስቱ ጋር ግብረ-ሥጋ ግኙኝነት መፈጸም ክልክል ነው፡፡ የግድ ከደሟ እስክትነጻና እስክትታጠብ መጠበቅ አለበት፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

"ከወር አበባም ይጠይቁሃል፡፡ እርሱ አስጠያፊ ነው፡፡ ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው፡፡ ንጹሕ እስከሚኾኑም ድረስ አትቅረቡዋቸው፡፡ #ንጹሕ በኾኑም ጊዜ አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኙዋቸው፡፡ አላህ (ከኃጢአት) ተመላሾችን ይወዳል፤ ተጥራሪዎችንም ይወዳል በላቸው፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡222)፡፡

መ/ የወሊድ ደም መቋረጥ፡- የወሊድ ደም (ደሙ-ኒፋስ) ተብሎ ይጠራል፡፡ እናት ልጅን መውለዷን (ከማኅፀኗ መውጣትን) ተከትሎ የሚፈስ ደም ነው፡፡ ከዚህ የወሊድ ደም መቆም በኋላ፡ ልክ እንደ የወር አበባ ደም (ደሙል-ሐይድ) ትጥበት፡ ገላዋን መታጠብ ግድ ይኾንባታል ማለት ነው፡፡ በሐይድ ደም ላይ የሚሰጡ ሃይማኖታዊ ህግጋት በጠቅላላ፡ በወሊድ ደምም ላይ በተመሳሳይ መልኩ ይሰጣሉ ማለት ነው፡፡ ኢብኑ-ሐዝም (384-456 ሂጅ.) ረሒመሁላህ እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹የወሊድ ደም የሐይድ ደም የሚከለክላቸውን ነገራት በጠቅላላ እሱም ይከለክላል፡፡ ይህ በአንድም ሰው ዘንድ ልዩነት የሌለበት ጉዳይ ነው፡፡ እንዲሁም ከወሊድ ደም መቆም በኋላ መታጠቡም፡ ከሐይድ በኋላ መታጠቡ ግድ እንደኾነው ለሱም ግድ ይኾናል›› (አል-ሙሓልላ ጥ.261)፡፡

ሠ/ የሙስሊም መሞት፡- አንድ ሙስሊም ምድራዊ ቆይታው ተጠናቆ፡ አጀሉ ደርሶ ቢሞት፡ ጀናዛው ሊታጠብና ሊከፈን፡ በተወሰኑ ሙስሊሞችም ሶላቱል-ጀናዛህ ሊሰገድበት፡ የሙስሊሞች መካነ-መቃብርም በክብር ሊቀበር ሃይማኖታዊ መብቱ ነው፡፡ በሙስሊሞችም ላይ ይህንን መፈጸም ፈርዱል-ኪፋያህ (በተወሰኑት ላይ የተጣለ ግዳጅ) ነው፡፡ ነገር ግን የአላህን ቃል የበላይ ለማድረግ ከከሀደት ሠራዊት ጋር እየተፋለመ በዛው ትግል ላይ እያለ የተገደለ (ሸሂድ የኾነ) ሙስሊም አይታጠብም፡ አይሰገድበትምም፡፡

ረ/ ወደ ኢስላም መግባት፡- ካለበት የከህደት እምነት በመላቀቅ ወደ ኢስላም ብርሀን የተመለሰ ካፊር የትጥበት ስርአት መውሰድ አለበት፡፡ ይህ ትጥበት በሱ ላይ ዋጂብ ነው ወይስ ሱንና በሚለው በዑለሞች መሐል ኺላፍ አለበት፡፡ የሻፊዒያህ እና የሐነፊያህ መዝሀብ ሊቃውንት መታጠቡ ተወዳጅ እንጂ ግዳጅ አይደለም ይላሉ፡፡ የማሊኪይ እና የሐንበሊይ ሊቃውንት ደግሞ በላጩ ረእይ መታጠቡ ግዳጅ ነው ይላሉ፡፡ ሱንና ነው የሚሉት ሊቃውንት የሙዓዝን ሐዲሥ እንደ-መረጃነት ያጣቅሳሉ፡፡ ሙዓዝ (ረዲየላሁ

ዐንሁ) ወደ የመን አህሉል-ኪታቦች በተላከ ጊዜ፡ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም)፡- ‹‹አንተ ወደ መጽሐፉ ሰዎች ዘንድ ትሄዳለህና፡ ለነሱ የመጀመሪያ ጥሪህ ወደ ላ ኢላሀ ኢልለሏህ ምሥክርነት ይኹን፡፡ ይህን ከተቀበሉህ፡ በቀጣይነትም አላህ በቀንና በለሊት የአምስት ወቅት ሶላትን ግዴታ እንዳደረገባቸው አሳውቃቸው ….›› ብለውታል፡፡ (ቡኻሪይና ሙስሊም)፡፡

በዚህ ሐዲሥ መሠረት፡ ሙዐዝ (ረዲየላሁ ዐንሁ) ከሸሀደተይን ቀጥሎ ሶላትን እንዲያስተምራቸው እንጂ፡ እንዲታጠቡ ማስተማሩን ትእዛዝ አልተሰጠውም፡፡ ይህም የሰለመ ሰው ትጥበት ተወዳጅ መኾኑን እንጂ ግዳጅ መኾኑን አያሳይም ይላሉ፡፡ በተጨማሪም በሳቸው የነቢይነት ዘመን እጅግ ብዙ ሰዎች ሰልመዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ትጥበትን ታዘው ቢኾን ኖሮ፡ በዚህ ዙሪያ የተዘገቡ ሐዲሦችን ባገኘን ነበር፡፡ አለመገኘቱ የሰለመ ሰው ትጥበት ግዳጅ አለመኾኑን እንረዳለን ይላሉ፡፡

ትጥበቱ ግዳጅ ነው የሚሉት ሊቃውንት ደግሞ፡- በይሀቂይ እና ኢብኑ ኹዘይማህ በዘገቡት ሐዲሥ ላይ፡ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ዓሲም ኢብኑ ቀይስ (ረዲየላሁ ዐንሁ) በሰለመ ጊዜ፡ እንዲታጠብ አዝዘዉት እንደነበር የሚናገረውን ሐዲሥ በመጥቀስ፣ እንዲሁም ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሥ ላይ፡ ሡማማህ ኢብኑ አሣልን (ረዲየላሁ ዐንሁ) ከሰለመ በኋላ መልክተኛው እንዲታጠብ ማዘዛቸውን በመጥቀስ፡ የሳቸው ትእዛዝ ግዳጅን ያመላክታል ይላሉ፡፡ ለማንኛውም ከኺላፍ ለመውጣትና (ከኺላፍ መውጣቱ በራሱ የተወደደ ነውና) ከጥርጣሬም ነጻ ለመኾን፡ ለሰውየውም ንጽህና ሲባል፡ የሰለመን ሰው እንዲታጠብ መምከሩና ማስታወሱ መልካም ነው፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

ሰ/ የጁምዓህ ቀን ትጥበት :- በዕለተ ጁምዓህ ገላን ታጥቦ፡ (ለወንዶች) ሽቶን በሰውነቱ ላይ ነስንሶ፡ ያማረ ልብስ ለብሶ፡ ወደ አላህ ቤት በጊዜ መሄድ ተወዳጅ ተግባር ነው፡፡ ሰሙረህ ቢን ጁንዱብ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዳስተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "የጁምዓ ቀን ዉዱእ ያደረገ ሰው፡ እሱ (ዉዱእ ማድረጉ) ምንኛ ያማረ ነው፡፡ የታጠበ ሰው ደግሞ መታጠቡ በላጭ ነው" (አቡ ዳዉድ 354፣ ኢብኑ ማጀህ 1091፣ ቲርሚዚይ 497፣ ነሳኢይ 1380)፡፡

ሸ/ የሚድ ሶላት ትጥበት፡- በሁለቱ ዒዶች (ዒዱል-ፊጥር እና ዒዱል-አድሓ) ታጥቦ ወደ ሶላት መውጣት ሱንና ነው፡፡

ቀ/ የሞትን ሰው ያጠበ ሰው ራሱ መታጠብ፡- ከአቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "የሞተን ሰው ያጠበ ሰው ይታጠብ" (ኢብኑ ማጀህ 1463፣ አሕመድ 7987)፡፡

በዚህ ዙሪያ ሌሎች ያልተነሱ ነጥቦችም አሉ፡፡ የኢሕራም ትጥበት፣ ወደ መካና መዲና ለመግባት ትጥበት፣ በዐረፋ ተራራ ላይ ለመቆም ትጥበት…. የመሳሰሉ ሱንና እንጂ ግዳጅ ያልኾኑ ትጥበቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ግን አንባቢን ላለማድከም እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት በአብዛኛው በኛ ህይወት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ስለኾኑ በነሱ ለመብቃቃት በማሰብም ጭምር የቀሩትን ከመዘርዘር ተቆጥበናል፡፡ አላህ ባነበብነው ተጠቃሚ ያድርገን፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

ምንጭ፡- ኡስታዝ ዱክቱር፡ ሐሰን ዐብዱል-ገኒይ አቡ-ጉድዳህ፡ መሊክ ስዑድ ዩኒቨርስቲ የፊቅህ መምህርና ፕሮፌሰር.

20. ስለ ፈጣሪ

የእግዚአብሔር ባህሪ በመፅሀፍ ቅዱስ

1•ምላጭ እሚከራይ ፈጣሪ(አምላክ)

” በዚያም ቀን እግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጕር ይላጨዋል፤ ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላል።”(ትንቢተ ኢሳያስ 7:20)

2•በፉጨት ተጣሪ አምላክ

“በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል እግዚአብሔር በግብጽ ወንዝ ዳርቻ ያለውን ዝምብ በአሦርም አገር ያለውን ንብ በፉጨት ይጠራል(ትንቢተ ኢሳይያስ 7:18)

3•እሚጮህ (ጩሀታም) አምላክ

“እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይወጣል እንደ ሰልፈኛም ቅንዓትን ያስነሣል ይጮኻል ድምፁንም ያሰማል በጠላቶቹም ላይ ይበረታል። ”(ትንቢተ ኢሳይያስ 42:13)

4•እንደ ኣንበሳ እሚያገሳ አምላክ

“እግዚአብሔርን ይከተላሉ፥ እርሱም እንደ አንበሳ ያገሣል ባገሣም ጊዜ ልጆች እየተንቀጠቀጡ ከምዕራብ ይመጣሉ:”(ትንቢተ ሆሴዕ 11:10)

5•ከፈጠረ በኃላ የሚያርፍና የሚተነፍስ አምላክ

“እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀን ስለ ፈጠረ፥ በሰባተኛውም ቀን ከሥራው ስላረፈና ስለ ተነፈሰ” (ኦሪት ዘጸአት 31:17)

6•የሚፀፀት ፈጣሪ(አምላክ)

“እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ”(ኦሪት ዘፍጥረት 6:6)

7•በፈጠረው ፍጡር የሚሸነፍ አምላክ

“አለውም፦ ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና”

(ኦሪት ዘፍጥረት 32:28)

8•በእንቅልፋሞችና በሰካራሞች እሚመሰል አምላክ

“እግዚአብሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፥ የወይን ስካር እንደ ተወው እንደ ኃያልም ሰው” (መዝሙረ ዳዊት 78:65)

9•የስህተትን ኣሰራር የሚልክ አምላክ

“እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል”(2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2:12)

10•ኣታላይ አምላክ (ፈጣሪ)

“አቤቱ፥ አታለልኸኝ እኔም ተታለልሁ፥ ከእኔም በረታህ አሸነፍህም ቀኑን ሁሉ መሳቂያ ሆኛለሁ፥ ሁሉም ያላግጡብኛል”(ትንቢተ ኤርምያስ 20:7)

11•ሰውን በማጥፋትና ሰውን በማፍረስ የሚደሰት ፈጣሪ (አምላክ)

” እግዚአብሔር ሲያጠፋችሁ ሲያፈርሳችሁም ደስ ይለዋል”(ኦሪት ዘዳግም 28:63) ሰዎን በማጥፋትና ሰውን በማፍረስ የሚደሰት አካል እንዴት ሆኖ አምላክ ሊሆን ይችላል?

12•በመጥፎ ነገር የሚያዝ አምላክ

” ለጥፋት ለቀረበው ሰው ብርቱ መጠጥ ስጡት፥ ነፍሱ ለመረረውም የወይን ጠጅ ስጡት7 ይጠጣ ድህነቱንም ይርሳ፥ ጕስቍልናውንም ከእንግዲህ ወዲህ አያስብ”(መፅሃፈ ምሳሌ 31:6) ፈጣሪ ሰዎች ከአስካሪ መጠጥ እንዲርቁ ነው እሚያዘው ወይስ “ብርቱ መጠጥ” ጠጥተው እንዲሰክሩ? ያውም ደሀውን መርጦ።

13•በዝሙት የሚያዝ አምላክ (ፈጣሪ)

” እግዚአብሔር መጀመሪያ በሆሴዕ በተናገረ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ሆሴዕን፦ ምድሪቱ ከእግዚአብሔር ርቃ ታላቅ ግልሙትና ታደርጋለችና ሂድ ጋለሞታን ሴትና የግልሙትናን ልጆች ለአንተ ውሰድ አለው” (ትንቢተ ሆሴእ 1:2)

ፈጣሪ ሰዎች ከዝሙት እንዲርቁ ነው እሚያዘው ወይስ “ሂድና ጋለሞታን ሴትና የግልሙትናን ልጆች ለአንተ ውሰድ”?

14•ለጨቅላ ህፃናት ርኅራሄ የሌለው ጨካኝ አምላክ

“ሸማግሌውንና ጕበዙን ቄንጆይቱንም ሕፃናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ ” (ትንቢተ ህዝቂኤል 9:6) . ጨቅላ ህፃናትና ሸማግሌዎች እንዲገደሉ እሚያዝ አካል እንዴት አምላክ ሊሆን ይችላል?

15•ከተማና ግንብ ለማየት ከሰማይ ወደ ምድር የሚወርድ አምላክ

“እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ”(ኦሪት ዘፍጥረት 11:5) የተሰራው ግንብ ለማየት የግድ ወርዶ ማየት አለበት? ባለበት ሆኖ የተሰራው ግንብ ማየት አይችልምን?

16•ልጅና ሚስት ያለው አምላክ

“እስራኤል የበኵር ልጄ ነው”(ኦሪት ዘጸአት 4:23)

“ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፥ ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው”(ትንቢተ ኢሳይያስ 54:5) ፈጣሪ ልጅና ሚስት ምን ይሰራለታል?

17•አንዱ በሰራው ሃጢኣት እስከ 10 ትውልድ ድረስ ሃጢኣተኛ እሚያደርግ አምላክ (ፈጣሪ)

“ዲቃላ ወደ እግዚአብሔር ጕባኤ አይግባ እስከ አሥር ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ጕባኤ አይግባ”(ኦሪት ዘዳግም 23:2)

ሁለት ሰዎች በሰሩት ኃጢኣት እስከ አስር ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሄር ጉባኤ እንዳይገቡ መከልከል ከፈጣሪ ፍትሃዊነት ጋር እንዴት ይታያል?

18• ነቢያትን አታላይ አምላክ (ፈጣሪ)

“እግዚአብሔር በእነዚህ በነቢያትህ ሁሉ አፍ ሐሰተኛ መንፈስ አድርጎአል እግዚአብሔርም በላይህ ክፉ ተናግሮብሃል” (መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 22:23)

“ነቢዩም ቢታለል ቃልንም ቢናገር፥ ያንን ነቢይ ያታለልሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ” (ትንቢተ ሕዝቅኤል 14:9)

ለሰዎች ሞዴል አርአያ ሆነው እንዲያስተምሩ የላካቸው ነቢያት ማታለልና በነሱ ላይ ሐሰተኛ ማንፈስ ማድረግ ለምን? ማታለል የፈጣሪ ባህሪ ነውን?

19• ለራሱም ብርሃን ያጣ ፈጣሪ

“ሰሎሞንም። እግዚአብሔር፦ በጨለማ ውስጥ እኖራለሁ ብሎአል”(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 6:1)

“የእግዚአብሔርን ቀን ለምትፈልጉ ወዮላችሁ! የእግዚአብሔርን ቀን ለምን ትፈልጋላችሁ? ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን አይደለም”(ትንቢተ አሞጽ 5:18)

እግዚአብሄር በጨለማ ውስጥ መኖር ለምን አስፈለገው?

ለራሱ ብርሃን ያላገኘን አካል(ፈጣሪ) ለኛ እንዴት ብርሃን ሊለግሰን ይችላል?

20• የሚተኛ ፈጣሪ

“አቤቱ፥ ንቃ ለምንስ ትተኛለህ? ተነሥ፥ ለዘወትርም አትጣለን”(መዝሙረ ዳዊት 44:23)

እግዚአብሄር እውነተኛ አምላክ ከሆነ መተኛት ለምን አስፈለገው?

ተኝቶ በፍጡራን እሚቀሰቀስ አካል እንዴት ሆኖ አምላክ ሊሆን ይችላል?

አምላክ በተኛበት ሰአት ፍጥረተ አለሙ በማን ቁጥጥር ስር ነበር?

21• ለፈጣሪ ጫማ ምን ይሰራለታል?

“እንዲህም አለኝ። የሰው ልጅ ሆይ፥ በእስራኤል ልጆች መካከል ለዘላለም የምቀመጥበት የዙፋኔ ስፍራና የእግሬ ጫማ መረገጫ ይህ ነው።”(ትንቢተ ሕዝቅኤል 43:7)

ይህ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ እግዚአብሄር ጫማ እንዳለው ይናገራል። እግዚአብሄር እውነተኛ አምላክ ከሆነ ለአምላክ የሚገባው ጫማ ምን አይነት ጫማ ነው?ደግሞስ ጫማ ምን ይሰራ?

አላህ (ሱወ) VS እግዚአብሄር

እግዚአብሄር መጪዉን አላወቀም ነበር!

☞{ዘ ፍጥረት 6፣6-7} እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ።

እግዚአብሔርም፦ የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ፥ ከሰው እስከ እንስሳ እስከ ተንቀሳቃሽም እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቼአለሁና አለ።

The LORD was sorry that he had made man on the earth, and it grieved him in his heart.

The LORD said, “I will destroy man whom I have created from the surface of the ground—man, along with animals, creeping things, and birds of the sky—for I am sorry that I have made them.”

[ቅዱስ ቁርአን 29፣62] እንዲህ ይላል፦ አላህ ሁሉንም ነገር አዋቂ ነው።

Indeed Allah is, of all things, Knowing ."

እግዚአብሄር አዳም ተሰውሮበት ሲፈልገው ነበር!

{ዘ ፍጥረት3፣9} እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ ወዴት ነህ? አለው።

The LORD God called to the man, and said to him, “Where are you?”

[ቅዱስ ቁርአን 3፣5] እንዲህ ይላል፦ አላህ በምድርም በሰማይም ምንም ነገር በርሱ ላይ አይሰወርም።

Indeed, from Allah nothing is hidden in the earth nor in the heaven.

እግዛብሄር ደክሞት፣አረፈ፣ ተነፈሰም!

{ዘ ፀአት31፣17} እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀን ስለ ፈጠረ፣ በሰባተኛውም ቀን ከሥራው ስላረፈና ስለ ተነፈሰ።

for in six days the LORD made heaven and earth, and on the seventh day he rested, and was refreshed.’”

[ቅዱስ ቁርአን 50:38] እንዲህ ይላል፦ ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውን ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ በእርግጥ ፈጠርን ድካምም ምንም አልነካንም።

And We did certainly create the heavens and earth and what is between them in six days, and there touched Us no weariness.

እግዚአብሄር ር ከያዕቆብ ተደባድቦው ተዘረረ!!!

{ዘፍጥረት32፣28} አለውም፦ ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና። He said, “Your name will no longer be called Jacob, but Israel; for you have fought with God and with men, and have prevailed.”

[ቅዱስ ቁርኣን 22፥74] እንዲህ ይላል

አላህ ተገቢ ክብሩን አላከበሩትም አላህ በጣም ጎያል አሸናፊ ነው። They have not appraised Allah with true appraisal. Indeed, Allah is Powerful and Exalted in Might.

እኔን ጨምሮ አብዛኞቹ ሰዎች ከምሁር \ከጀምስ በር\ አባባል ጋር ይስማማሉ፡-"ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልማዶች ያለኝ አመለካከት የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤት ናቸው የሚል ነው።የሰው ልጅ የራሱን እምነት ያሰፈረበት መጽሐፍ ነው።" ብሏል። The Bible in the Modern World, By James Barr, 1973, p. 120 የማይስማማ አለ!?

=>"በልም እውነት መጣ፣ውሸትም ይወገድ፣እነሆ ውሸት ተወጋጅ ነውና።

And say, "Truth has come, and falsehood has departed. Indeed is falsehood, [by nature], ever bound to depart." Qur'an 17፥81

እግዚአብሔር ያማልዳልን?

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው።።

ብዙ የኢትዮጵያ ኦርቶርቶዶክስ መምህራን በግልፅና በማያሻማ የኢየሱስን እማላጅነት በሮሜ 8፥34 ላይ ለማስተባለብ ኢየሱስ አማላጅ ከሆነ ተማላጅ ማን ነው? ብለው ይጠይቃሉ፤ መልሱ እግዚአብሔር ነው ተማላጅ ሲባሉ ገልብጠው በኤርሚያስ ላይ እግዚአብሔር አማላጅ ነው ብለው አማርኛ እንኳን በቅጡ እንደማያነቡ ያሳብቅባቸዋል፤ እስቲ ጥቅሱ በሰከነና በሰላ እዕምሮ እንየው፡-

ኤርምያስ 7፥25 “አባቶቻችሁ ከግብጽ ምድር ከወጡበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በየዕለቱ “እየማለድሁ” בַּם־אַשְׁכֵּם ባሪያዎቼን “ነቢያትን” ሁሉ ልኬባችሁ ነበር”

ልብ አድርጉ “እየማለድሁ” ተብሎ የተቀመጠው ቃል “ሃስከም” בַּם־אַשְׁכֵּם ሲሆን “ሸከም” בַּם־אָשָׂא ማለትም “ማለዳ” ከሚል ቃል የመጣ ሲሆን “ጠዋት” ማለት ነው፤ ይህ ቃል በኤርሚያስ መጽሐፍ ላይ 11 ጊዜ የመጣ ሲሆን “ምልጃ” ከሚለው ቃል ጋር የትየለሌ የሆነ የሃሳብ ሆነ የቃላት ልዩነት አላቸው፤ “እየማለድሁ” ማለት “ማለዳ” ማለት መሆኑን ተመሳሳይ ሃሳብ ሆኖ ሌሎች ጥቅሶች “”ማለዳ” ባሪያዎቼን “ነቢያትን” ሁሉ ልኬባችሁ” እያለ ይናገራል፡-

ኤርምያስ 29፥19 ይህም የሆነው ቃሌን ስላልሰሙ ነው፥ ይላል እግዚአብሔር “በማለዳ” בַּם־אַשְׁכֵּם ተነሥቼ ባሪያዎቼን “ነቢያትን” ወደ እነርሱ ሰድጃለሁና እናንተ ግን አልሰማችሁኝም፥ ይላል እግዚአብሔር፡-

ኤርምያስ 26፥5 ያልሰማችሁትን “በማለዳ” בַּם־אַשְׁכֵּם ተነሥቼ ወደ እናንተ የላክኋቸውን የባሪያዎቼን “የነቢያትን” ቃል ባትሰሙ፥

ኤርሚያስ 35፥15 ለእናንተና ለአባቶቻችሁም በሰጠሁት ምድር ትቀመጣላችሁ እያልሁ “በማለዳ” בַּם־אַשְׁכֵּם ተነሥቼ “ባሪያዎቼን ነቢያትን ሁሉ ልኬባችሁ” ነበር እናንተ ግን ጆሬአችሁን አላዘነበላችሁም እኔንም አልሰማችሁኝም።

ኤርሚያስ 44፥4 “በማለዳም” בַּם־אַשְׁכֵּם ተነሥቼ ባሪያዎቼን ነቢያትን ሁሉ ሰደድሁባችሁና።

ኤርሚያስ 7፥13 አሁንም ይህን ነገር ሁሉ ስላደረጋችሁ፥ “በማለዳም” בַּם־אַשְׁכֵּם ተነሥቼ በተናገርኋችሁ ጊዜ ስላልሰማችሁ፥ በጠራኋችሁም ጊዜ ስላልመለሳችሁ፥

ኤርሚያስ 11፥7 አባቶቻችሁን ከግብጽ ምድር ካወጣሁበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፥ “በማለዳ” הַשְׁכֵּם ተነሥቼ እያስጠነቀቅሁ። ቃሌን ስሙ በማለት አስጠንቅቄአቸው ነበር።

በተጨማሪም “ማለደ” ጠዋት ተነሳ ነው፡-

ዘፍጥረት 20፥8 አቢሜሌክም በነጋታው “ማለደ”וַיַּשְׁכֵּם ፥ ባሪያዎቹንም ሁሉ ጠራ…

1ሳሙኤል 15፥12 ሳሙኤልም በነጋው ሳኦልን ለመገናኘት “ማለደ”וַיַּשְׁכֵּם ።

ይህንን የቋንቋ እና የአንብቦ ያለመረዳት ችግር ተማሪዎቻቸው ጋር ብቻ ይመስለኝ ነበር፤ ግን አስተማሪዎቹ ቢያንስ እንኳን እብራይስጡን ባይደፍሩት “እየማለድሁ” በእንግሊዝኛው “daily rising up early” የሚለው አይተው እርምት እንዲወስዱ ይህንን ፅሑፍ የምታነቡ ኦርቶዶክሳውያን አድርሱላቸው። ወሰላሙ አለይኩም

እውን ማርያም ትመለካለችን?

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

5:116 አላህም፡- «የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ ! አንተ ለሰዎቹ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ አምላኮች إِلَٰهَيْنِ አድርጋችሁ ያዙ اتَّخِذُونِي ብላሃልን?» በሚለው ጊዜ አስታውስ ::

ኢላህ إِلَٰه *አምላክ

ፕሮቴስታንት ክርስቲኣኖች ይህ የቁርአን አንቀጽ ትክክል አይደለም ይሉናል ለምን ስንላቸው? እኛ ፕሮቴስታንት ክርስቲኣኖች ማርያምን አናመልክም ይሉናል ። በመቀጠል መልሳችን የፕሮቴስታንት ቁጥራችሁ ከሁለት ቢሊዮን ክርስቲኣንኖች 6.15% ናችሁ ስለዚህ ማጆሪቲው ማለትም ካቶሊክ 16.85% ፣ ኦርቶዶስ 3.96%፣ አንግሊካን 1.26% የመሳሰሉት አበይት አንጃዎች ማርያምን ያመልካሉ።

በ 5:116 ላይ አምላክ ተብሎ የተተረጎመው ቃል ኢላሃይኒ إِلَٰهَيْنِ ሲሆን ለኢሳና ለመርየም በሙተና የገባ ነው፣ በነጠላ ሲሆን ኢላህ إِلَٰه ማለት ነው ትርጉሙም *የሚመለክ* ማለት ነው፣

ዱዓ دُعَآء የሚለው ቃል 22 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን ትርጉሙ ልመና፣ ጥሪ የሚል ፍቺ ሲኖረው ለአንዱ አምላክ የሚቀርብ መነባደድ፣ መተናነስ፣ መለማመንን ያሳያል፣ ዱዓ በቀውል ከሚደረጉ የአምልኮ አይነት አንዱ ነው፣ ሰውን በአካል ማየት፣ መስማት፣ መናገር እስከቻለ ድረስ ማነጋገሩ ተፈጥሯዊ ነው፣ ነገር ግን የሚያይበት አይን፣ የሚሰማበት ጆሮ፣ የሚናገርበት አፍ በሞት ጊዜ ስለሚፈራርሱ አይሰማም፣ አይናገርም፣ አያይም። በክርስትና ማለትም ካቶሊክ፣ ኦርቶዶክስና አንግሊካል ወደ ማርያም ጥሪ፣ ልመና፣ መተናነስ፣ መነባደድ ይደረጋል፣ ይህ አይን ያፈጠጠና ጥርስ ያስገጠጠ ሃቅ ነው፣ ታዲያ ማርያም ይህን ዱዓ ትሰማለች ወይ? አይ ከተባል ለምን ወደ ማርያም ዱዓ ያረጋሉ? አዎ ትሰማለች ከተባለ በምኗ? ሰውን የምትገናኝበት ህዋሳቷ አፈር ሆኖ የለ እንዴ? በሰው ልብ ያለውን መለኮት ካልሆነች እንዴት ታውቃለች? ከአላህ ሌላ ማንነት ሆነ ምንነት መለማመን፣ መነባደድ፣ መተናነስ፣ መጥራት ሽርክ ነው፡-

46:5 እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስም ለርሱ የማይመልስለት لَا يَسْتَجِيبُ ከአላህ ሌላ ከሚጠራ ሰው ይበልጥ የተሳሳተ ማነው? እነርሱም ከጥሪያቸው غَافِلُونَ ዘንጊዎች ናቸው::

7:194 እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትጠሯቸው تَدْعُونَ ፣ ብጤዎቻችሁ ተገዢዎች ናቸው፤ እውነተኞችም እንደሆናችሁ ጥሩዋቸውና فَلْيَسْتَجِيبُوا ፤ አይችሉም።

ማርያም ሆነ ሌሎች ሰዎች ከሞቱ ወዲህ የሚደረግላቸው ዱዓ እስከ ቂያማ ቀን አያቁም ዝንጉዎች ናቸው፣ በቂያማ ቀን ግን ያንን ዱዓ ሰምተው እንደማያውቁ ይመሰክሩባቸዋል፣ በሰው ልብ ያለውን የሚያውቅ፣ የሁሉንም ልመና በአንድ ጊዜና በተለያየ ቦታ አይቶና ሰምቶ የሚመልስ አንዱ አምላክ አላህ ብቻ ነው፡-

2:186 ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ ፡- እኔ ቅርብ ነኝ፡፡ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ دَعَانِ إِذَا الدَّاعِ دَعْوَةَ أُجِيبُ ፡፡ ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ፤ በኔም ይመኑ፤ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና፡፡

60:1 እኔ የምትደብቁትንና የምትገልጹትን የማውቅ ስሆን ወደነርሱ በፍቅር ትመሣጠራላችሁ፤

34:11 እኔ የምትሠሩትን ነገር ሁሉ ተመልካች ነኝና ።

አህዝ أَخْذ *መያዝ*

ክርስቲኣኖች በተለይ ካቶሊክ፣ ኦርቶዶስ፣ አንግሊካን *እኛ ማርያም አምላኬ ብለን አንጠራም* በማለት ሂስ ለመስጠት ሲቃጣቸው ይደመጣል፣ *ያዙ* የሚለው ትዕዛዛዊ ግስ*imperative verb* ኢትተሂዙኒ اتَّخِذُونِي ሲሆን አምላክ ብሎ መጥራት ሳይሆን የሚያሳየው አምላክ አድርጎ መያዝን ነው፣ ያ ማለት ለአምላክ የሚሰጠውን የአምልኮ ክፍል ለሌላ ማንነት ሆነ ምንነት መስጠትን ያመለክታል፡-

25:43 ፍላጎቱን አምላኩ አድርጎ የያዘውን اتَّخَذَ ሰው አየህን ? አንተ በርሱ ላይ ጠባቂ ትሆናለህን ?

አንድ ሰው ፍላጎቱን አምላኩ አድርጎ ያዘ ማለት ፍላጎቱን አምላኬ ብሎ ጠራ ማለት ሳይሆን ለአምላክ የሚሰጠውን የአምልኮ ክፍል ለፍላጎቱ ቅድሚያ ሰጠ ማለት ነው። ክርስቲኣኖች ሊቃውንቶቻቸውና መነኮሳቶቻቸውን አማልክት አድርገው ይዘዋል የተባለውም በዚህ ሂሳብ ነው፣ ምክን ያቱም፡- ፈርድ፣ ሙስተሃብ፣ ሙባህ፣ መክሩህ፣ ሃራም ማለት የሚችለው አላህ ሆኖ ሳለ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸዉን የሚያወጡትን ህግ እንደ አምላክ ህግ መቀበል ቅድሚያ ለእነርሱ መስጠት ነውና አምላክ አድርጎ መያዝ ማለት ይህ ነው፣ በተጨማሪም መላእክትንና ነቢያትን መለማመን፣ መነባደድ፣ መጥራት፣ መተናነስ አምላክ አድርጎ መጥራት ነው፡-

9:31 ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለዉን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ *ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸዉን* የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ اتَّخَذُوا ፤

3:80 *መላእክትንና ነቢያትንም* አማልክቶች አድርጋችሁ እንድትይዙ تَتَّخِذُوا ሊያዛችሁ አይገባዉም፤ እናንተ ሙስሊሞች ከሆናችሁ በኋላ በክሕደት ያዛችኋልን?

18:102 እነዚያ የካዱት፣ ባሮቼን *ከእኔ* ሌላ አማልክት አድርገው መያዛቸውን يَتَّخِذُوا የማያስቆጣኝ አድርገው አስቡን?

ማጠቃለያ

ከቁርአንን ንግግ ባሻገር ዛሬ በተጨባጭ ለአምላክ የሚሰጠውን አምልኮ ክርስቲኣኖች በተለይ ካቶሊክ፣ ኦርቶዶስ፣ አንግሊካን ለማርያም እየሰጡ ይገኛሉ። ወደ ማርያም መለማመን፣ ስለት መሳል፣ መስገድ፣ እጣን ማጠን፣ መዘመር የመሳሰሉት አምልኮ እየሰጡኣት አይደለምን?

በ 375 AD የተነሱት ኮላደሪያን ክርስቲኣኖች ማርያምን ቴአ ማለትም ሴት አምላክ*goddess* ብለው ይጥሩኣት አልነበረምን ?

በ 431 AD የኤፌሶን ጉባኤ ማርያምን ቴኦቶኮስ ማለት የአምላክ እናት*Mother of God* አላሉኣትምን ?

ክርስቲኣኖች በተለይ ካቶሊክ፣ ኦርቶዶስ፣ አንግሊካን ማርያምን በግሪክ ኪርያ ማለትም ሴት ጌታ ይሉኣታል፣ በሀገራችን ኦርቶዶክሶች ደግሞ እግዚኢት ትባላለች። እግዚኢት ሴት ጌታ ማለት ሲሆን እግዚእ ወንዱ ጌታ ማለት ነው። ኢየሱስን እግዚኢነ ማለትም ጌታችን እንደሚሉት ሁሉ ማርያም እግዚኢትነ ማለትም ጌታችን ይሉኣታል። ከዚህ የበለጠ ማርያምን አምላክ አድርጎ መያዝ አለን?

ትድኑ ዘንድ ከዚህ ሽርክ ሁላችሁም ወደ አላህ በተውበት ተመለሱ፣ አላህ ተውበትን የሚቀበል አዛኙ ነው፡-

2:160 እነዚህም በነሱ ላይ ጸጸታቸውን እቀበላለሁ፤ እኔም ጸጸትን በጣም ተቀባይ አዛኙ ነኝ።

15:49 ባሮቼን እኔ መሓሪው አዛኙ እኔው ብቻ መኾኔን ንገራቸው።

21..ስለ ሰይጣን

እዉን ሴይጣን መላእክ ነበረን ?

ይህ ጥያቄ በተደጋጋሚ ከሚጠየቁና ሁሌም ቢነገር የማይረዱት ሰዎች ብዙ ናቸዉ እስኪ አብረን እንየዉ እነዚህ ወገኖች ሁሌም ሴጣን ከጅን ለመሆኑ የሚያቀርቡት መረጃ አላህ ለመላእክት ስገዱ ብሎ አብሮ ሴጣንንም ጠቅሶታል እናም ይህ አባባል ሴጣን ከመላእክት ወገን ነበር የሚል መከራከሪያ ያነሳሉ ፡፡ ነገር ግን ነገሩን ሰፋ አድርጎ ላየዉ ሰዉ የተገላቢጦሽ ነዉ አላህ ሰዉንና ጂንን(ኢጋንንትን) ነጻ ፈቃድ ተሰጥቶዋቸዋል

- (ቁርአን 76፡2 እኛ ወይ አመሰጋኝ ወይም ከሓዲ ሲኾን መንገዱን መራነው፤ (ገለጽንለት) ለሰዉ ልጅ
- 72፡14 «እኛም ከእኛ ውስጥ ሙስሊሞች አልሉ፡፡ ከእኛም ውስጥ በዳዮች አልሉ፡፡ የሰለሙም ሰዎች እነዚያ ቅንን መንገድ መረጡ፡፡» (14) ይህ ደግሞ ለኢጋንንት፡፡ ስለዚህ የሰዉ ልጅና ኢጋንንት በሚሰሩት ነገር ይጠየቃሉ የመቀበል ያለመቀበል መብት አላቸዉ እዉነታዉ የትንሳኤ ቀን ይሆናል፡፡ መለኣክተን በተመለከተ ደግሞ ሲፈጥራቸዉ ያላቸዉን ባህሪ ሲነግረን በቁርአን እንዲህ ይለናል፡-

1. ቁርአን 66፡6 እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ደንጋዮች ከኾነች እሳት ጠብቁ፡፡ በእርሷ ላይ ጨካኞች፣ ኀይለኞች የኾኑ መላእክት አልሉ፡፡ አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም፡፡ የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ፡፡ (6)

2. ቁርአን 21፡26-27 «አልረሕማንም (ከመላእክት) ልጅን ያዘ» አሉ፡፡ ጥራት ተገባው፡፡ አይደለም (መላእክት) የተከበሩ ባሮች ናቸው፡፡ (26) በንግግር አይቀድሙትም፤ (ያላለውን አይሉም)፡፡ እነርሱም በትእዛዙ ይሠራሉ፡፡(27)

3. ቁርአን 16፡49-50 ለአላህም በሰማያት ያለው ከተንቀሳቃሽም በምድር ያለው ሁሉ፣ መላእክትም ይሰግዳሉ፡፡ እነርሱም አይኮሩም፡፡ (49) ጌታቸውን ከበላያቸው ሲኾን ይፈሩታል፡፡ የታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ፡፡ (50)

4. 21:19-20 በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉም የእርሱ ነው፡፡ እርሱ ዘንድ ያሉትም (መላእክት) እርሱን ከመገዛት አይኮሩም፡፡ አይሰለቹምም፡፡ (19) በሌሊትና በቀንም ያጠሩታል፤ አያርፉም፡፡ (20) ከእንዚህ የቁርአን ጥቅሶች የምናየዉ መላእክት ጌታችን ያዘዛቸዉን ሁሉ የሚፈጽሙ ትእዛዙን የማይጥሱ ናቸዉ ስለዚህ ለዚህም ነዉ ሴጣን ከመላእክት አይደልም የምንለዉ፡፡

ስለዚህ ሴጣን ምንድ ነዉ ለሚለዉ በቀጥታ መልስ የሚሰጠን ኪታች ያለዉ አንቀፅ ይሆናል 18፡50 ለመላእክትም ለአደም ስገዱ ባልናቸው ጊዜ (የኾነውን አስታውስ)፡፡ ወዲያውም ሰገዱ፤ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር፡፡ ከጋኔን (ጎሳ) ነበር፡….› ሴጣን ከመላእክት ጋር አብሮ ስለነበረ ትእዛዙ ሲደረሰዉ (ነጻ ስለሆነ- እምቢ ወይንም እሺ የማለት) ባህሪ ስለተሰጠዉ መላእክት ግን ይህ ባህሪ መጀመርያዉኑም አልተሰጣቸዉም ለአላህም ትእዛዝ እጅ ሰጡና አጎነበሱ እሱ ግን ከጋኔን ጎሳ መሆኑን እዚያዉ አንቀጽ ላይ የሚነግረን ጋኔኖች ነጻ ነት (ፍሪዊል) ስላላቸዉና ሴጣንም ከነሱ ስለሆነ ይህንን ባህሪዉን ተጠቅሞ እምቢ አለ እናም በሌላ አንቀፅ ላይ ደግሞ ምክንያቱን ነግሮናል፡፡

ይህም ኩራቱና ትእቢቱ ለኣዳም አልተናንሰም ባይነቱ እንዲሁም ቅናቱ ነበር ለዚህም ‹‹ንገረኝ ይህ ያ በእኔ ላይ ያበለጥከው ነውን… ›› በማለት የመበለጥ ስሜቱን በግልፅ ተናግሮ በቁርአን 17፡61-62 ላይ ‹‹እኔ የምበልጠዉ ሆኖ ሳለ ›› በሚል አነጋገር የአላህን ትእዛዝ አሻፈረኝ ያለዉ፡፡ ከመላእክት ቢሆን ኖሮ ለትእዛዙቱ ተግባራዊነት እጁን ይሰጥ ነበር አልሰጠም ይህም ‹‹እምቢ›› የማለት

ምርጫ ስላለዉ ነዉ መልእክት ግን የታዘዙትን ላለመፈፅም ‹‹እምቢ›› የማለት ነጻነቱ እንኩዋን የላቸዉም ስለዚህ በተዘዋዋሪ መልኩ እሱ ከእነሱ ወገን እንዳልነበር ግልጽ ነዉ፡፡

ለምን ለኣዳም አትሰግድም ሲባል ከሰጠዉ መልስ የምንረዳዉ እሱ ከእሳት እንደተፈጠር እራሱ ተናግሮል ይህ በራሱ የሚያሳየዉ እሱ ከጂን ወገን እንደነበረ ነዉ ምክንያቱም ጂኖች ከእሳት ነዉና የተፈጠሩት፡፡ • 7:12 (አላህ) «ባዘዝኩህ ጊዜ ከመስገድ ምን ከለከለህ» አለው፡፡ «እኔ ከርሱ የበለጥኩ ነኝ፡፡ ከእሳት ፈጠርከኝ፡፡ እርሱን ግን ከጭቃ ፈጠርከው» አለ፡፡(12) • 38:75 (አላህም) «ኢብሊስ ሆይ! በሁለት እጆቼ (በኃይሌ) ለፈጠርኩት ከመስገድ ምን ከለከለህ? (አሁን) ኮራህን? ወይስ (ፊቱኑ) ከትዕቢተኞቹ ነበርክ?» አለው፡፡ (75) «እኔ ከእርሱ በላጭ ነኝ፡፡ ከእሳት ፈጠርከኝ፤ ከጭቃም ፈጠርከው» አለ፡፡ ስለዚህ ሴጣን አብሮ ከመላእክት ጋር ስለተጠራ ብቻ መላእክት አይሆንም- አፈጣጠሩም -ባህሪዉም ከመላእክት ጋር ሳይሆን ከጂን ጋር እንደሚያመሳስለዉ እራሱም ተግባሩም ያሳያልና፡፡

መላእክት ቢሆን ኖሮ ‹‹ ከብርሃን ፈጠረከኝ እንጂ ከእሳት ፈጠርከኝ ማለት አልነበረበትም እንዲሁም እንደእነሱ ትእዛዛትን እንደማይጥሱት የተሰጠዉን ትእዛዝ ብቻ መፈፀም ነበረበት›› ነገር ግን አላደረግም ምክንያቱም ከመላእክት አይደልምና፡፡

አላህ (ሱወ) የበለጠውን ያዉቃል።

ሰይጣን የማጥመሚያ ቃል?

ዛሬ በአላህ ፍቃድ የሰይጣን አንቀጽ Satanic Verses በቁርሃን ውስጥ ተካቶ ነገር ግን አላህ አስወግዶታል ተብሎ ስለሚነዛው አሉባልታ መሰረተ ቢስ መሆኑን ላሳያቹ እውዳለው፡፡

በመጀመሪያ መሰረተ ቢሱ አሉባልታ ይህን ይመስላል ‹‹‹‹ ሙሃመድ(ሰዐወ) በአንድ ወቅት ለአላህ ቃልና ሐሳብ ተቃራኒ የሆኑ ነገር የተናገሩት ሰይጣን አሳስታቸው እንደሆነና ቁርሃን 53 እያነበቡ እያለ አል ላት አል ሁዛ እና አል መናት ‹‹‹እነዚህ የተከበሩ ጣኦታት አማላጅነት ተስፋ ይደረጋል››› የሚለውን ሲያነቡ የዚህን ግዜ ባልደረቦቻቸው እንደተሳሳቱ ሲነግራቸው የሚከተለው መገለጥ መጣላቸው፡- ‹‹ከመልእክተኛና ከነቢይ ከአንተ በፊት አንድም አልላክንም ባነበበና ዝም ባለ ጊዜ ሰይጣን በንባቡ ላይ የማጥመሚያ ቃል የሚጥል ቢሆን እንጅ ወዲያው አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል፡፡ ከዚያም አላህ አንቀፆችን ያጠናክራል፡፡› (22፡52) ይህ የሚሽነሪዎችና ኦሪየንታሊስቶች ይህችን ተረት በብዛት ያቀርባታል ግን በዘገባቸው ማጣሪያ ሚዛን እዚህ ግባ የማትባል ከንቱ ነገር ናት፡፡

የነብዩ መሃመድ ጠላቶች የነበሩት የቁረይሽ ጣኦታውያን የነዙትን ሐሰት የትችት መነሻ ማድረጋቸው ያሳዝናል ግን ቁርሃን 22፡52 ከከስተቱ ጋርም ምንም አይነት ግንኙነት የላትም በወቅቱ የሆነውን የታሪክ ምሁራን እንዲህ ዘግበውታል፡-

‹‹በአራተኛው የነብይነት አመት የረመዳን ወር ነብዩ(ሰዐወ) ወደ ተከበረው የሐረም መስጊድ ሄዱ፡፡ ቁረይሾች ተሰብሰበዋል ባላባቶችም በብዛት አሉ፡፡ ድንገት ከመካከላቸው ቆሙና ‹‹አልነጅም›› የተሰኘውን የቁርሃን ምህራፍ ያነቡ ጀመር ::

ካጠገባቸው የተሰበሰቡት ከሃዲን ከዚህ ቀደም የአላህን ቃል ሰምተው አያውቁም ነበር ምክንያቱ ደግሞ የነሱ ፓሊሲያቸው እንዲህ የሚል ነበር ‹‹‹ከነዚያ የካዱት ሰዎች ፡- ‹ይህንን ቁርሃን አታዳምጡ:: ታሸንፋም ዘንድ (በሚነበብበት ወቅት) ድምፃቹን ከፍ አድርጋቹ ተንጫጩ› አሉ (ፉሲለት 26) እና በድንገት ነብዩ(ሰዐወ) አል ነጅም የቁርአን ከፍልን ሲያነቡላቸው ቃላት ሊገልፁት ከሚችሉት በላይ እጅግ የተዋበ መለኮታዊ ቃል ወደ ጆሮአቸው ሲገባ በጣም ማረካቸው:: እናም ሁሉም ጆራቸውን ለርሱ ሰጡ:: ወደ ሌላ ነገር ማተኮር አልቻሉም ::ነብዩ(ሰዐወ) ምእራፉን አጠናቀው ‹‹ለአላህ ሰገዱ፤አምልኩትም›› ከሚለው የቁርሃኑ መቃጫ ላይ ሲደርሱ ሱጁድ ወረዱ:: እንደ እውነቱ ከሀድያኑ የሰገዱት የሀቅ ውበትና ድምቀት በትእቢተኞችና በፈዘኞች ልቦና ውስጥ የነበረውን እልህ በማሸነፍ ራሳቸውን መቆጣጠር ስላቃታቸው ነበር።

(Narrated Ibn Abbas: The Prophet (pbuh) prostrated while reciting An-Najm and with him prostrated the Muslims, the pagans, the jinns, and all human beings. (Bukhari, Book 19, Hadith 177)::

የሰይጣን፣የይሁዳ እና የሮም ወታደሮች ውለታ እንዴት ተዘነጋ?

Adem Seid

የክርስትያኖች ነገር ብርቱካኑን በልተው አፈሩን ፣ ውሀውን እና ፀሐዩን መጥላት እንደማለት ነው::አንድ ብርቱካን አድጎ ፍሬ ለመስጠት ዉሀ ፣ አፈር እና የፀሐይ ብርሀን እንደሚስፈልጉት ሁሉ ኢየሱስም ተሰቅሎ ክርስቲያኖችን ከሀጥያተታቸው ነፃ ለማውጣት ሰይጣን ፣ ይሁዳ እና የሰቀሉት የሮማ ወታደሮች አስፈልገውታል::

ስለዚህ ብርቱካኑን በልተን የአፈሩን የውሀውን እና የፀሀይ ብርሀኑን ውለታ እንደማንዘነጋው ሁሉ ክርስቲያኖችም የይሁዳን የሰይጣንን እና የሮማ ወታደሮችን ውለታ መርሳት የለባቸውም::ምክንያቱም:

ከአሥራ ሁለቱ ከኢየሱስ ደቀመዝሙሮች አንዱ በሆነው ይሁዳ ሴጣን ባይገባ ወይም ባያድርበት ኖሮ ይሁዳ እየሡሥን ለጠላቶቹ አሣልፎ አይሠጠውም ነበር። እየሡሥ በይሁዳ አልፎ ባይሠጥ ሊሠቀል አይችልም ማለት ነው።

ክርሥቶስ ካልተሠቀለ ደሞ ክርሥቲያኖች ለዘላለሙ አትድኑም ነበር ማለት ነው። በርግጥ እየሡስ ከፈለልን የምትሉት መሥዋትም በመፅሀፍ ቅዱሥ በቂ ማሥረጃ የላችሁም ሆኖም ግን ባጭሩ እናንተ እንደምትሉት የዘላለም ድነትን የምታገኙት በክርሥቶስ ሥቅለት ከሆነ ታዲያ ክርሥቶሥ እንዲሠቀል ሠበብ የሆነው ዲያቢሎሥ (ሰይጣን፣ይሁዳ፣የሮም ወታደሮች) ባለውለታቹ አይሆንምን?

የሚገርመው ደሞ ክርሥቶስ ለኛ ሲል መከራን ተቀበለ እልፍ መከራንም ተቀበለ መሥዕዋት ሆነልን ማለታቹስ አግባብ ነውን?። መሥእዋት ማለት በፈቃደኝነት ለተደረገ ነገር ነው። ታዲያ ክርሥቶስ በፈቃደኝነት ነው እንዴ የተሠቀለው? ክርሥቶስስ በአይሁድ ላለመያዝ ብዙ ጥረቶችን አላደረገም? በርግጥ ክርሥቶስ አልተሠቀለም ምክንያቱም ጌታው ጠባቂው አሸናፊው እና ጥበበኛው አላህ በመሆኑ አይሁዶች ጫፉን አልነኩትም። ዝንቡን እሸ አላሉም። ግን እንደናንተ አባባል ብንሄድ እንኳ ክርሥቶሥ በፈቃደኝነት ሣይሆን መሥዋት የሆነው በግድ በሀይል ነ የተገደለው ታዲያ አንድ ሠው ተገዶ የፈፀመው ነገር መሥዋት ሊባል ይችላልን?

ነቢዩ ዳዊት ለምን በሞት አልተቀጣም ?

የባይብሉ "ነብዩ " ዳዊት የሰራው ወንጀል በሞት የሚያስቀጣው መሆኑን ያውቃሉን ?

ዳዊት አንድ ተራ ሰው እንኳን የማይፈጽመውን ፤አምላክ የኮነነውን ዝሙት ፈጽሟል። ዳዊት በድብቅ ከባልንጀራውን ሚስት ጋር ተኝቷል። ይህ ዘግናኝ ወንጅል በባይብል ህግ በሞት የሚያስቀጣ ቢሆንም እግዚአብሔር ግን እንዳይቀጣ አድርጎታል።

ዳዊት ነብይ ወይስ _?

በመጽሃፍ ቅዱስ ህግ መሰረት ዝሙተኝነት እና የባልንጀራ ሚስት መመኘት በሞት ያስቀጣል በማለት እንዲህ ሲል ይበይናል።

ማናቸውም ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ተኝቶ ቢገኝ፥ አመንዝራውና አመንዝራይቱ ሁለታቸው ይሙቱ እንዲሁም ክፉውን ነገር ከእስራኤል ታስወግዳለህ። (ኦሪት ዘዳግም 22:22)

ማናቸውም ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ወይም ከባልንጀራው ሚስት ጋር ቢያመነዝር አመንዝራውና አመንዝራይቱ ፈጽመው ይገደሉ። (ኦሪት ዘሌዋውያን 20:10)

☞የባልንጀራህን ቤት አትመኝ

☞የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም

☞ገረዱንም በሬውንም አህያውንም

☞ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ

☞ማናቸውንም አትመኝ። (ኦሪት ዘጸአት 20:17)

አሁን ዳዊት ባይባል ላይ የባልንጀራውን ሚስት ምን እናዳደረገ እንመልከት.....

መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 11

1 እንዲህም ሆነ በዓመቱ መለወጫ ነገሥታት ወደ ሰልፍ በሚወጡበት ጊዜ፥ ዳዊት ኢዮአብን ከእርሱም ጋር ባሪያዎቹን እስራኤልንም ሁሉ ሰደደ። የአሞንም ልጆች አገር አጠፉ፥ ረባትንም ከበቡ ዳዊት ግን በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር።

2 እንዲህም ሆነ ወደ ማታ ጊዜ ዳዊት ከምንጣፉ ተነሣ፥ በንጉሥም ቤት በሰገነት ላይ ተመላለሰ በሰገነቱ ሳለ አንዲት ሴት ስትታጠብ አየ ሴቲቱም መልከ መልካም ነበረች።

3 ዳዊትም ልኮ ስለ ሴቲቱ ጠየቀ አንድ ሰውም። ይህች የኤልያብ ልጅ የኬጢያዊው የኦርዮ ሚስት ቤርሳቤህ አይደለችምን? አለ።

4 ዳዊትም መልእክተኞች ልኮ አስመጣት ወደ እርሱም ገባች፥ ከርሱሰትዋም ነጽታ ነበርና ከእርስዋ ጋር ተኛ ወደ ቤትዋም ተመለሰች።

መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 12

7 ናታንም ዳዊትን አለው። ያ ሰው አንተ ነህ። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። በእስራኤል ላይ ንጉሥ ልትሆን ቀባሁህ፥ ከሳኦልም እጅ አዳንሁህ

8 የጌታህንም ቤት ሰጠሁህ፥ የጌታህንም ሚስቶች በብብትህ ጣልሁልህ የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ ይህም አንሶ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ እጨምርልህ ነበር።

መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 12

12 አንተ ይህን በስውር አድርገሽዋል እኔ ግን ይህን በእስራኤል ሁሉ ፊትና በፀሐይ ፊት አደርገዋለሁ።

13 ዳዊትም ናታንን፡- እግዚአብሔርን በድያለሁ አለው። ናታንም ዳዊትን፡- እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል አትሞትም።

14 ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና ስለዚህ ደግሞ የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል አለው። እግዚአብሔር በዳዊት ፍንታ " የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል "ከማለት ይልቅ ዳዊትን በሞት እንዲቀጣ ለምን አላደረገውም ?

እውን እግዚአብሔር ለነብይነት የሚልካቸውና ለሰዎች ልጆች ምሳሌ የሆኑ ነቢያት እንደዚህ አይነት ስብእና የተላበሱ ናቸውን? ወይስ ይህ በ መጽሃፍ "ቅዱስ" ጸሐፊያን አማካይነት የተቀጠፈ ሐሰት ነው?

ነብያት የሰው ልጅ አስተማሪዎች ፤የአምላክ ቅን አገልጋዮች ናቸው።የአምላክን ቃል የሚያደርሱ መምሆሮች መሆናቸው እየታውቀ አንድ ተራ ሰው እንኳ የማይፈጽመውን ዝሙት ይፈጽማሉ ተብሎ ይታሰባል? የኛ አርአያ ናቸው ከምንላቸው ነቢያት ምን እንማር?

VS

በተጻራሪው ቁርአን ውስጥ የተጠቀሱት ነብያቶችን ስንመለከት እውነተኛ የ አላህ ታዛዦችና ቅን አገልጋዮች፤የመላካም ስራ ተምሳሌቶች፤ለሰው ልጅ በቃልም በተግባርም እውነተኛ የእምነት መምህራን ናቸው።

አላህም ነብያቶች ቅኑን መንገድ የተመሩ መሆናቸውን ብሎም መላው የሰው ልጅ አር አያ አድርጎ መከተል እንዳለባቸው እንዲህ ሲል በቅዱስ ቃሉ ይናገራል:--

"እነዚህ አላህ ቅኑን ጎዳና የመራቸው(ነብያት) ናቸው።የነርሱን ቅን መመሪያ ተከተል"።

(አል አንዓም 90)

ታዲያ የቱን ይመርጣሉ?

ሀ) ዝሙተኞችን ለነብይነት የሚልከው እግዚብሔርን? ወይስ?

ለ) ☞ ቅኑን ጎዳና የተመሩትን ለነብይነት የመረጠው አላህን?

መልሱን ለህሊናዎ

የአላህ ሰላም፣እዝነት፣ርህራሄና በረከት ቅኑን መንገድ በተከተለ ላይ ሁሉ ይስፈን።

ግብረ-ሰዶም

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ክብርና ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን፡፡(አል-ፋቲሓ 2) የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡

ጌታ አላህ እሱ በብቸኝነት ይመለክ ዘንድ ሰዎችንና ጂንኒዎችን ፈጥሯል (አዝ-ዛሪያት 51፡56)፡፡ ትክክለኛ አምልኮ ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚፈጸም፡ በንግግርም ሆነ በተግባር አርአያ በመሆን ያሳዩ ዘንድ፡ ከሰዎች መካከል ሰዎችን መርጦ፡ የመረጣቸውን ሰዎች የነቢይነት እና የመልክተኝነት ማዕረግ በመስጠት ወደ ህዝቦቻቸው ልኳቸዋል (አን-ነሕል 16፡36)፡፡ ለከፊሎቹም መለኮታዊ መጽሐፍን ሰጥቷቸዋል (አል-ሐዲድ 57፡25)፡፡

ከነዚህ ቀደምት ነቢያትና ሩሱሎች ውስጥ አንዱ ሉጥ (ዐለይሂ-ሰላም) ነው (አስ-ሷፍፋት 37፡133)፡፡ ሉጥ (ዐለይሂ-ሰላም) የነቢዩላህ ኢብራሂም (ዐለይሂ-ሰላም) የወንድሙ ልጅ ነው፡፡ መልክተኛ ሆኖ የተላከውም፡ ሰዱም (ሰዶም) ተብላ ወደምትጠራው መንደር እና በአካባቢዋ ለሚገኙት ነው፡፡ የዚህ መንደር ነዋሪዎች ሶዶማውያን በመባል ይታወቃሉ፡፡ ከክህደታቸው በተጨማሪ (ካፊር ከመሆናቸውም ሌላ) ሌላ የሚታወቁበት አስቀያሚ የኃጢአት ተግባር አልለ፡፡ እሱም፡- የተመሳሳይ ፆታ ግብረ-ስጋ ግኙኝነት (HOMO sexual) ነው፡፡

አላህ ፈቃዱ ከሆነ ለዛሬ የምንነጋገረው በዚህ አስቀያሚ ተግባር ላይ ኢስላም ያለውን አቋም በመጠኑ ዳሰሳ በማድረግ ይሆናል ኢንሻአላህ፡፡ መልካም ንባብ፡-

1/ የተወገዘ ኃጢአት መሆኑ፡-

ሀ/ ጌታ አላህ በባሪያዎቹ ላይ ከዋላቸው ከማይቆጠሩ ጸጋዎቹ የተወሰኑትን እያነሳ ሲያስታውሰን፡ አንደኛውን የገለጸው ‹‹ለኛ የትዳር አጋር የምትሆነን ሴትን›› ከኛው መፍጠሩን በመጠቆም ነው፡፡ ይህም ከአስደናቂ ምልክቶቹ መሆኑን አያይዞ ይነግረናል፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

"وَمِنْ آيَاتِهِ أَنْ خَلَقَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَاجًا لِّتَسْكُنُوا إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُم مَّوَدَّةً وَرَحْمَةً إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ " سورة الروم 21

"ለናንተም፣ ከነፍሶቻችሁ (ከጐሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፤ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፤ በዚህ ውስጥ ለሚያስውሉ ሕዝቦች ታምራቶች አሉ።" (ሱረቱ-ሩም 30፡21)፡፡

"وَاللَّهُ جَعَلَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَاجًا وَجَعَلَ لَكُم مِّنْ أَزْوَاجِكُم بَنِينَ وَحَفَدَةً وَرَزَقَكُم مِّنَ الطَّيِّبَاتِ أَفَبِالْبَاطِلِ يُؤْمِنُونَ وَبِنِعْمَتِ اللَّهِ هُمْ يَكْفُرُونَ " سورة النحل 72

"አላህ ከነፍሶቻሁ (ከጐሶቻችሁ) ለናንተ ሚስቶችን አደረገ፤ ለናንተም ከሚስቶቻሁ ወንዶች ልጆችን የልጅ ልጆችንም አደረገላችሁ፤ ከመልካሞችም ጸጋዎች ሰጣችሁ፤ ታዲያ በውሸት (በጣዖት) ያምናሉን? በአላህም ጸጋ እነሱ ይክዳሉን?" (ሱረቱ-ነሕል 16፡72)፡፡

"فَاطِرُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ جَعَلَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَاجًا وَمِنَ الْأَنْعَامِ أَزْوَاجًا يَذْرَؤُكُمْ فِيهِ لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ " سورة الشورى 11

"ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ነው፤ ከነፍሶቻችሁ (ከነሶቻችሁ) ሴቶችን፣ ከቤት እንስሳዎችም ዓይነቶችን (ወንዶችና ሴቶችን) ለእናንተ አደረገላችሁ፤ በርሱ (በማድረጉ) ያበዛችኋል፤ የሚመስለው ምንም ነገር የለም፤ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።" (ሱረቱ-ሹራ 42፡11)፡፡

ከነዚህ ሶስት አንቀጾች በግልጽ የምንረዳው ነገር፡- ጌታ አላህ ለኛ ተጣማሪን (የትዳር አጋር) ያደረገልን፡ ከሴቶች ጋር እንጂ፡ ከተመሳሳይ ፆታ ጋር አለመሆኑን ነው፡፡ ይህ የተቃራኒ ፆታ በጋብቻ መጣመር ከአላህ የሆነ ኒዕማ (ጸጋ) ከሆነ፡ ከዛ በተቃራኒው ሆኖ

መገኘት (ወንድ ከወንድ ወይም ሴት ከሴት ጋር) ደግሞ እርግማንና ቁጣ እንጂ ሌላ አይሆንም፡፡ በዚህም ሰበብ ተግባሩ ኃጢአት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ለ/ የሉጥ (ዐለይሂ-ሰላም) ህዝቦች ነቢያቸውን በማስተባበልና ባለመቀበላቸው ከሀዲ ሆነዋል፡፡ ከክህደት የሚበልጥ ኃጢአት የለም፡፡ ከዚህ ክህደታቸው ጋር ደግሞ በተጨማሪ የተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት በመፈጸማቸው አላህ አጥፍቷቸዋል፡፡ ይህም የሰዶምች ስራ (ግብረ-ሰዶም) የኃጢአት ተግባር ለመሆኑ ሌላ ማስረጃ ነው፡፡ ቀጣዮቹ ቅዱስ ቁርአናዊ አንቀጾች ይህን ይገልጻሉ፡

"قَوْمٌ أَنتُمْ بَلْ النِّسَاء دُونِ مِّن شَهْوَةً الرِّجَالَ لَتَأْتُونَ إِنَّكُمْ * الْعَالَمِينَ مِّن أَحَدٍ مِنْ بِهَا سَبَقَكُم مَا الْفَاحِشَةَ أَتَأْتُونَ لِقَوْمِهِ قَالَ إِذْ وَلُوطًا الْغَابِرِينَ مِنَ كَانَتْ امْرَأَتَهُ إِلاَّ وَأَهْلَهُ فَأَنجَيْنَاهُ * يَتَطَهَّرُونَ أُنَاسٌ إِنَّهُمْ قَرْيَتِكُمْ مِّن أَخْرِجُوهُم قَالُواْ أَن إِلاَّ قَوْمِهِ جَوَابَ كَانَ وَمَا * مُّسْرِفُونَ الْمُجْرِمِينَ عَاقِبَةُ كَانَ كَيْفَ فَانظُرْ مَّطَرًا عَلَيْهِم وَأَمْطَرْنَا * 84-80 الأعراف سورة "

"ሉጥንም ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤ አስቀያሚን ሥራ ትሰራላችሁን? በርሷ ከዓለማት አንድም አልቀደማችሁም። እናንተ ከሴቶች ሌላ ወንዶችን በመከጀል በእርግጥ ትመጡባቸዋላችሁ፤ በውነቱ እናንተ ወሰንን አላፊዎች ሕዝቦች ናችሁ። የሕዝቦቹም መልስ (ሎጥንና ተከታዮቹን) ከከተማችሁ አውጧቸው፣ እነሱ የሚጥራሩ ሰዎች ናቸውና ማለት እንጂ ሌላ አልነበረም። እርሱንና ቤተሰቦቹንም አዳንናቸው፣ ሚስቱ ብቻ ስትቀር፤ እርሷ (ለጥፋት) ከቀሩት ሆነች። በነርሱም ላይ (የእሳት) ዝናምን አዘነምንባቸው፤ የኃጢአተኞችም መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከት።" (ሱረቱል አዕራፍ 7፡80-84)፡፡

"نَادِيكُمُ فِي وَتَأْتُونَ السَّبِيلَ وَتَقْطَعُونَ الرِّجَالَ لَتَأْتُونَ أَئِنَّكُمْ *الْعَالَمِينَ مِّنَ أَحَدٍ مِنْ بِهَا سَبَقَكُم مَا الْفَاحِشَةَ لَتَأْتُونَ إِنَّكُمْ لِقَوْمِهِ قَالَ إِذْ وَلُوطًا الْمُنكَرَ فَمَا قَوْمِهِ جَوَابَ كَانَ إِلَّا أَن قَالُوا ائْتِنَا بِعَذَابِ اللَّهِ مِنَ كُنتَ إِن الصَّادِقِينَ " العنكبوت سورة 29-28

"እናንተ በእርግጥ ወንዶችን ትመጣላችሁን? መንገድን ትቆርጣላችሁን? በሸንጎችሁም የሚነወርን ነገር ትሠራላችሁን? (አላቸው)፤ የሕዝቦቹም መልስ ከውነተኞቹ እንደ ኾንክ የአላህን ቅጣት አምጣብን ማለት እንጂ ሌላ አልነበረም።" (ሱረቱል ዐንከቡት 29፡28-29)፡፡

"النمل سورة " تَجْهَلُونَ قَوْمٌ أَنتُمْ بَلْ النِّسَاء دُونِ مِّن شَهْوَةً الرِّجَالَ لَتَأْتُونَ أَئِنَّكُمْ * تُبْصِرُونَ وَأَنتُمْ الْفَاحِشَةَ أَتَأْتُونَ لِقَوْمِهِ قَالَ إِذْ وَلُوطًا 55-54

"ሉጥንም ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤ «እናንተ የምታዩ ስትኾኑ ፀያፍን ነገር ትሠራላችሁን?፡፡ «እናንተ ከሴቶች አልፋችሁ ወንዶችን ለመከጀል ትመጣላችሁን በእውነቱ እናንተ የምትሳሳቱ ሕዝቦች ናቸሁ፡፡»" (ሱረቱ-ነምል 27፡54-55)፡፡

ሐ/ በቅዱስ ቁርአን ውስጥ የስጋ ፍላጎትን ከሚስቶች ወይም በእጆቻችሁ ካሉ (ባሪያዎች) ጋር ብቻ ነው ይልና፡ ከዚህ ውጪ የሚፈልግ ግን እሱ ወሰን አላፊ ኃጢአተኛ ነው ይለናል፡፡ ‹‹ከዚህ ውጪ›› በሚለው አነጋገር ውስጥ የተመሳሳይ ጾታ ግኙኝነትም አብሮ ይካተታል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የተወገዘ ተግባር ነው፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

"الْعَادُونَ هُمُ فَأُوْلَئِكَ ذَلِكَ وَرَاء ابْتَغَى فَمَنِ * مَلُومِينَ غَيْرُ فَإِنَّهُمْ أَيْمَانُهُمْ مَلَكَتْ مَا أَوْ أَزْوَاجِهِمْ عَلَى إِلَّا * حَافِظُونَ لِفُرُوجِهِمْ هُمْ وَالَّذِينَ " المؤمنون سورة 7-5

"እነዚያም እነርሱ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች የሆኑት (አገኙ)፡፡ በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው በያዟቸው (ባሪያዎች) ላይ ሲቀር፡፡ እነርሱ (በነዚህ) የማይወቀሱ ናቸውና፡፡ ከዚህም ወዲያ የፈለጉ ሰዎች እነዚያ እነርሱ ወሰን አላፊዎች ናቸው፡፡" (ሱረቱል ሙእሚኑን 23፡5-7)፡፡

الْعَادُونَ هُمُ فَأُوْلَئِكَ ذَلِكَ وَرَاء ابْتَغَى فَمَنِ * مَلُومِينَ غَيْرُ فَإِنَّهُمْ أَيْمَانُهُمْ مَلَكَتْ مَا أَوْ أَزْوَاجِهِمْ عَلَى إِلَّا * حَافِظُونَ لِفُرُوجِهِمْ هُمْ وَالَّذِينَ" المعارج سورة 31-29 "

"እነዚያም እነሱ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች የሆኑት። በሚስቶቻቸው ወይንም እጆቻቸው በያዙዋቸው (ባሮች)፣ ላይ ሲቀር። እነሱ (በነዚህ) የማይወቀሱ ናቸውና። ከዚያም ወዲያ የፈለገ ሰው፣ እነዚያ እነሱ ድንበር አላፊዎች ናቸው። " (ሱረቱል መዓሪጅ 70:29-31)።

መ/ ተመሳሳይ የፆታ ግኑኝነት በመፈጸም የሉጥ ህዝቦችን አይነት ስራ በመስራት የተሰማሩ ሰዎች በነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) አንደበት ለእርግማን ተዳርገዋል። እርግማኑ የሚያመላክተው ደግሞ፡ ኃጢአቱ እጅግ የከፋ ተግባር መሆኑን ነው፡። ሐዲሡ እንዲህ ይነበባል፡-

لَعَنَ ، لُوطٍ قَوْمِ عَمَلَ عَمِلَ مَنْ اللَّهُ لَعَنَ) : قَالَ وَسَلَّمَ عَلَيْهِ اللَّهُ صَلَّى اللَّهِ نَبِيَّ أَنَّ عنهما الله رضي عَبَّاسٍ ابْنِ عَنِ (2915) أحمد وروى المسند تحقيق في الأرنؤوط شعيب وحسنه (ثَلَاثًا ، لُوطٍ قَوْمِ عَمَلَ عَمِلَ مَنْ اللَّهُ .

ዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) እንደነገረን የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም)፡- "የሉጥ ህዝቦችን አይነት ስራ የሚሰራን ሰው አላህ ከራሕመቱ ያርቀው፣ የሉጥ ህዝቦችን አይነት ስራ የሚሰራን ሰው አላህ ከራሕመቱ ያርቀው በማለት ሶስት ጊዜ ደጋግመው ተናግረዋል፡፡" (ሙስነድ ኢማሙ አሕመድ 2915)፡፡ ሹዐይቡል-አርነኡጥ ሰነዱ ሐሰን መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

في امرأةً أو رجلًا أتَى رجلٍ إلى وجلَّ عزَّ اللهُ ينظرُ لا" :- قال وسلم عليه الله صلى النبي أن : عنهما الله رضي عباس بن عبدالله عن دبرِها". والترهيب الترغيب -: 3/273

ከዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) በድጋሚ እንደተላለፈልን የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ:– "አንድ ወንድ መሰል ብጤውን ወንድን ወይም ሴትን ከቆሻሻ መውጪያ ከተገናኘ አላህ (በራሕመት እይታው) አይመለከተውም" (አት–ተርጊብ ወት–ተርሂብ 3/273)።

የትንሳኤ ቀን (የውሙል ቂያም) የጌታውን ራሕመት (እዝነት) ማግኘት ያልቻለ ሰው: የሚጠበቀው ቅጣት ነው ማለት ነው።

ሠ/ ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ለኡመታቸው እጅግ በጣም አሳቢ ናቸው፡፡ አንድም ነፍስ እንዲጠፋ አይፈልጉም፡፡ ስለሆነም፡- መልካም ሆኖ እኛን የሚጠቅመንን ነገር ሳይጠቁሙንና ሳያነሳሱን፡ መጥፎ ሆኖ እኛን የሚጎዳንን ነገር ሳያስጠነቅቁንና ሳይገስጹን በፍጹም አያልፉም፡፡

ወደፊት ለኡመቶቼ ይከሰታል ብዬ ከምፈራላቸው አስፈሪ ነገር አንዱ፡ የተመሳሳይ ፆታ ግኑኝነት መሆኑን ጠቁመውናል፡፡ ይህም ተግባሩ በኢስላም የተወገዘ መሆኑን ያመላክታል፡፡ እንዲህ ብለው ነበር፡-

لُوطٍ قَوْمِ عَمَلُ أُمَّتِى عَلَى أَخَافُ مَا أَخْوَفَ إِنَّ » -وسلم عليه الله صلى- اللَّهِ رَسُولُ قَالَ قَالَ اللَّهِ عَبْدِ بْنِ جَابِرِ عَنْ ». ابن ماجه 2563 , الترغيب في الألباني حسنه , وحسنه الترمذي 1457 الحاكم 4/357 وصححه ووافقه الذهبي .

ጃቢር ኢብኑ ዐብዲላህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደነገረን የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "እኔ በህዝቦቼ (ኡመቶቼ) ላይ ከምፈራላቸው ነገራት የበለጠ እጅጉኑ አስፈሪው ነገር የሉጥ ህዝቦች ስራ ነው" (ኢብኑ ማጀህ 2563፣ ቲርሚዚይ 1457፣ ሓኪም አል-ሙስተድረክ 4/357)፡፡

ሸይኽ አልባኒይ (ረሒመሁላህ) በተርጊብ ወት-ተርሒብ ላይ የዚህን ሐዲሥ ሰንሰለት መልካም እንደሆነ ሐሰን በማለት ገልጸውታል፡፡

2/ ሸሪዐዊ ቅጣቱ፡-

ከነቢያችን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) በተገኘው ሐዲሥ መሰረት፡ በዚህ ተግባር ላይ ሆኖ ንሰሀ (ተውበት) ከማድረጉ በፊት በአይን ምስክሮች የተገኘ፣ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ቅጣቱ ‹‹መገደል›› ነው፡፡ ይህም የድርጊቱን አስቀያሚነት፡ ማኅበረሰብ የሚበክል ትውልድ እንዳይቀጥል የሚያደርግ እንቅፋት በመሆኑ ነው፡፡ ሐዲሡ እንዲህ ይነበባል፡-

عَلَيْهِ اللَّهُ صَلَّى اللَّهِ رَسُولُ قَالَ : قَالَ عنهما الله رضي عَبَّاسٍ ابْنِ عَنْ (2561) ماجه وابن (4462) داود وأبو (1456) الترمذي وروى
الترمذي صحيح في الألباني وصححه (بِهِ وَالْمَفْعُولَ الْفَاعِلَ فَاقْتُلُوا لُوطٍ قَوْمِ عَمَلَ يَعْمَلُ وَجَدْتُمُوهُ مَنْ) : وَسَلَّمَ .

ዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) እንደነገረን የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም)፡- "የሉጥ ህዝቦችን አይነት ስራ የሚሰራን ሰው ካገኛቸሁት የሚፈጽመውንም፣ የሚፈጸምበትንም ሰው ግደሉ" (ቲርሚዚይ 1456፣ አቡ ዳዉድ 4462፣ ኢብኑ ማጀህ 2561)፡፡

3/ የሰውየው ማንነት፡-

በሸሀደተይን ሙስሊምነቱ የተረጋገጠ፣ ለጌታው አላህ በቀን አምስት ጊዜ የሚሰግድ የአላህ ባሪያ፡ ይህን ሸሀደተይን ሊያፈርስ የሚችል የሺርክ/ኩፍር ተግባር እስካልፈጸመና እስካልተናገረ ድረስ፡ በከባኢረ-ዙኑብ (በታላላቅ ኃጢአት) ኃጢአት ላይ መዘፈቁ፡ ከኢስላም አጥር አያስወጣውም፡፡

ኃጢአቱ በውስጡ ያለውን ኢማን ያዳከመዋል እንጂ፡ ኩፍር ውስጥ አይከተውም፡፡ በዚህ ተግባር ላይ ሁኖ ያለ ተውበት ቢሞትም እንኳ፡ ጉዳዩ ወደ አላህ የሚመለስ (አላህ ከፈለገ ሊምረው፣ ካልሆነም የኃጢአቱን ያህል ሊቀጣው) እንጂ እኛ የምንፈርድበት አይደለም፡፡

ግብረ-ሰዶም ከታላላቅ ኃጢአት ተርታ የሚመደብ እንጂ በራሱ ኩፍር የሆነ ተግባር አይደለም፡፡ ይህ አስቀያሚ ስራ ከአንድ ሙስሊም ላይ ቢገኝ እና ያ ሙስሊም ያለ ተውበት ቢሞት፡ የሰውየው ጉዳይ ወደ አላህ ይመለሳል እንጂ፡ ማንም ሰው እሱ የጀሀነም ነው ማለት አይችልም፡፡

ሰውየውን ሊያከፍረው የሚችለው ይህ አስቀያሚ ተግባር ሐላል ነው ብሎ ካመነ ወይም ከተናገረ ብቻ ነው፡፡ የዛኔ ስራው ላይ ባይገኝም በዚህ እምነቱ ብቻ ይከፍራል፡፡ ከዛ ውጪ ተግባሩ ኃጢአት መሆኑን ልቡ ያመነ ሙስሊም፡ በነፍሲያው ፍላጎት ኃጢአቱ ላይ ቢወድቅ ከፈረ አይባልም፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

ማጠቃለያ፡-

የሰዶማውያን ተመሳሳይ የፆታ ግንኙነት በቀላሉ ቀጥሎ ያሉትን ግላዊና ማኅበራዊ ችግሮች ያስከትላል፡-

ሀ/ ከተፈጥሮአዊ ማንነት መጣረስን፡- ይህን ተግባር ንጹህ ህሊና ያወግዘዋል፡፡ ስሜታችንም አይቀበለውም፡፡ በዚህ ስራ ላይ መገኘት ከተፈጥሮ ስርአት መውጣት ነው፡፡

ለ/ ወጣቱን አካል ማኮላሸትን፡- ወጣቶች ከወዲሁ እራሳቸውን ተጣማጃቸውን በመፈለግ በትዳር ካልታቀፉ፡ ለዚህ ተግባር በቀላሉ ተጠቂ ይሆናሉ፡፡ ስሜታቸውም ያለ አግባብ ይባክናል፡፡

ሐ/ የዘር መቋረጥ፡- ዘር ሊገኝ የሚችለው በወንድና ሴት ጋብቻ እንጂ፡ በተመሳሳይ ፆታ አይደለም፡፡ በዚህ ሁኔታ ሰው ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ግንኙነትን ከቀጠለ፡ ትውልዱ ቀጣይነት አይኖረውም፡፡ ዘር ይቋረጣል፡፡

መ/ የሴቶች ብሉሹነት፡- ባለቤቶቻቸው ፊታቸውን ወደ መሰል ፆታቸው ካዞሩ፡ ሴቶችም ስሜታቸውን ለማብረድ በመፈለግ ወደ ሐራም ተግባር የመዘፈቅ እድሉ የሰፋ ይሆናል፡፡

ሠ/ ያልተፈቀደ ግንኙነት፡- ከወንዶች ጋር ያንን አስቀያሚ ተግባር የለመደ ሰው፡ ወደ ሴቶችም ሲመጣ ስሜቱን ማርካት የሚፈልገው ዘር ከሚገኝበት ቦታ ሳይሆን፡ ከተወገዘው ሌላኛው ስፍራ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ትልቅ ብሉሹነት ነው፡፡

ረ/ የቤተሰብ መበታተንን፡- ተግባሩ በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ፡ የቤተሰብ ህይወት ይናጋል፡፡ በመሀከላቸውም ጸብና ጥላቻ ይሰፍናል፡፡ ህይወት ይበላሻል፡፡ ሌሎችም…

አላህ ወንድሞችንና እህቶቻችንን ከዚህ አስቀያሚ ተግባር ይጠብቅልን፡፡

የጨረቃ ጥቅም በእስልምና እና በክርስትና

እኛ ሙስሊሞች ጨረቃን አይተን የምንፆመው እንዲሁም ጨረቃን አይተን የምናፈጥረው(በአልን የምናከብረው) ከፈጣሪያችን አላህ(ሱወ) ታዘን ነው።

✔ቅዱስ ቁርአን እንዲህ ይላል✔

- 6:96 እርሱም ጎህን ከሌሊት ጨለማ ፈልቃቂ ሌሊትንም ማረፊያ ፀሐይንና ጨረቃንም ለጊዜ መቁጠሪያ አድራጊ ነው፡፡
- 41:37 ሌሊትና ቀንም፣ ጸሐይና ጨረቃም፣ ከምልክቶቹ ናቸው፤
- 2:189 ከለጋ ጨረቃዎች ይጠየቁሃል፡፡ እነርሱ ለሰዎች ጥቅም ለሐጅም ማወቂያ ጊዜያቶች ምልክቶች ናቸው በላቸው፡፡
- 10:5 እርሱ ያ ፀሐይን አንጸባራቂ ጨረቃንም አብሪ ያደረገ ነው፡፡ #የዓመታትን ቁጥርና ሒሳብን ታውቁ ዘንድም ለእርሱ መስፈሪያዎችን የለካ ነው፡፡
- 41:37 ሌሊትና ቀንም፣ ጸሐይና ጨረቃም፣ ከምልክቶቹ ናቸው፤ ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፤ ለዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ፤ እርሱን ብቻ የምትግዙ እንደሆናችሁ፣ ለሌላ አትስገዱ፣

መፅሀፍ ቅዱስምም የሚያስተምረው ይህንኑ ነው:

- መጽሐፈ ሲራክ 43÷6-7 *"ጨረቃም ለሁሉም የዘመን መለኪያ ናት"*፤ ለዓለም ሁሉ ምልክት ናት፤ *"በእርሷም ቀን ይለያል፤ በጨረቃም የበዓላት ምልክት ይታወቃል"*።
- መዝሙረ ዳዊት 104፥19 "ጨረቃን ለጊዜዎች" አደረገ ፀሐይም መግቢያውን ያውቃል።
- ዘኍልቍ 10፥10 ደግሞ በደስታችሁ ቀን፥ በበዓላታችሁም ዘመን፥ "በአዲስ ጨረቃ" ፥ በሚቃጠል መሥዋዕታችሁና በደኅንነት መሥዋዕታችሁ ላይ መለከቶቹን ንፉ እነርሱም በአምላካችሁ ፊት ለመታሰቢያ ይሆኑላችኋል እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ። NIV Bible
- መዝሙር 81፥3 "በአዲስ ጨረቃ" ቀን በከፍተኛው በዓላችን ቀን መለከትን ንፉ፤ NIV Bible
- ዘፍጥረት 1:14፤ እግዚአብሔርም አለ። ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ፤ #ለምልክቶች #ለዘመኖች

#ለዕለታት #ለዓመታትም ይሁኑ፤ (ዘፍጥረት 1:14)

ስለዚህ ከላይ እንደተመለከትነው ጨረቃን አይተን የምንዖመው እንዲሁም ጨረቃን አይተን የምንፈታው ፈጣሪያችን አላህ(ሱወ) ጨረቃን የግዜያት መቁጠሪያ አድርገን እንድንጠቀምበት ስላዘዘን ነው። ለዚህም ደግሞ ምስጋና ይገባው።

አልሀምዱሊላሂ ረቢልዓለሚን።

♥♥ለእርድ የቀረበው ማን ነው?♥♥

♥♥እስማኤል? ወይስ ይስሀቅ?♥♥

ስለታሪኩ ሙስሊሙም ክርስቲያኑም በስፋት ወደዚያ አልገባም ግና ለእርድ የቀረበው ማነው ? በሚለው መሰረታዊ ነጥብ ላይ የምናገኘው መልስ ለየቅል ነው አንድ ታሪክ :-

>ሁለት መልስ ሙስሊሙ ለዕርድ የቀረበው ((እስማኤል)) ነው ሲል ክርስቲያኑ ደግሞ አረ ((ይስሐቅ ነው)) ይላሉ።

እኔም ባይብለን በአስተውሎት ቃኘሁት ነገሩ በአንድ ራስ ቢሆንብኝም ዕውነታው ግን በአስገራሚ ሁኔታ "በተዘነጋጅ" አንዲት ቃል እና ዝርዝር መረጃዎች ላይ መስፈሩን ተገነዘብኩ ይህው ልብ ያለው ልብ ይበል ::ባይብል በዘፍጥረት22፡2

‹‹የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ።››ዘፍጥ 22፡2

ይህ አንቀጽ ሆነ ሌሎችም አንደ ዘፍጥረት 22፡16 እንደሚያሳዩት አብረሃም ((አንድያ ልጁን))፤ ((አንድ ልጁን))፤ መስዋእት እንዲያደረግ እንደታዘዘ ይናገራል ::መልካም ይህ አንድያ ልጅ ማነው ? ከአብርሃም ልጆች እስማኤል ወይስ ይስሐቅ?

አንደኛነታቸው ቀዳሚነታቸው ለማወቅ የግድ እድሜያቸው ማየት ስለሚኖርብን ተጨማሪ ታሪካቸው የሚያስቃኙን መረጃ የሆኑ ጥቅሶችን ማየቱ ግድ ስለሆነ እንመልከት ። ትኩረቶን ጨምር ያርጉ …

1 እስማኤል ሲወለድ አብርሀም እድሜው 86 ነበር። ይህው ‹‹ኢጋር እስማኤልን ለአብራም በወለደችለት ጊዜ አብራም የሰማንያ ስድስት ዓመት ሰው ነበረ።›› (ዘፍጥ 16፡16)

ትኩረት–›› ዕድሜ ☞ እስማኤል=0 (ውልደት) አብርሃም = 86 ነበር።

2. አስማኤል ሲገረዝስ ፡- አብረሃም 99 አመቱ እስማኤል 13 አመቱ።

☞‹‹ አብርሃምም የቁልፈቱን ሥጋ በተገረዘ ጊዜ የዘጠና ዘጠኝ(99) ዓመት ሰው ነበረ። ልጁ እስማኤልም የቁልፈቱን ሥጋ በተገረዘ ጊዜ የአሥራ ሦስት ዓመት ልጅ ነበረ። (ዘፍጥ 17፡24-25)

ትኩረት–›› ዕድሜ ☞ እስማኤል= 13 ዓመቱ አብረሃም= 99 ዓመቱ ።

3. ጥያቄው ይስሐቅ ሲወለድስ ? ነው።አብርሃም እድሜው ስንት ነበር ? ስንል እስማኤል በተገረዘ ጊዜ የአሥራ ሦስት ዓመት ልጅ ነበረ። (ዘፍጥ 17፡24-25

ገና ከአንድ አመት ቡኃላ ይስሐቅ መወለዱን ባይብል ያበስረናል የቱ ጋር ? መልሱን እኔው ልስጥ

☞‹‹አብርሃምም ልጁ ስሐቅ በተወለደለት ጊዜ የመቶ ዓመት ዕድሜ ነበረ። (ዘፍጥ 21፡5) ልብ በሉ ይስሐቅ ሲወለድ አብርሃም መቶ ዓመቱ ነበር ::አሁን ከላይ ያሳለፍናቸውን ትኩረቶቻችንን ሰብስብ ሰናራጋቸው አንዲህ ይሆናሉ ‹‹—››

-›ዕድሜ እስማኤል=14 አብርሃም = 100 ይስሐቅ=0(ውልደት)

—>ቀዳሚው ማነው ? የወቅቱ((አንድያ ልጁ)) እስማኤል ካልሆነ ስናጠቃለው

☞አብርሃም 100 ሲሞላው ይስሐቅ ተወለደ እስማኤል ደግሞ በጊዜው 14 ዓመት ሞላው ((አንድ ልጅህን)) አንድያ ልጅ ስለተባለ ይስሐቅ ከመወለዱ በፊት አንደሆነ ;እሱም እስማኤል መሆኑን ያሳያል። ምክንያቱን ይስሐቅ ሲወለድ አንድያ ልጅ አይሆንምና። እስማኤል ቀድሞት ተወልዶዋልና እንደ ባይብል ይስሐቅ ሲወለድ አብርሃም 100 ዓመቱ ነበር። (ዘፍጥ 21፡5)

ከአንድ አመት በፊት በ99 ዓመቱ ደግሞ አብራሃም እንደተገረዘ ልጁ እስማኤልም 13 ዓመቱ እንደሆነ (ዘፍ 17፡24-25) ይነግረናል፡ :

ስለዚህ ይህ <የልጅህን መስዋት አቅርብ> ታሪክ የተፈጸመው አብርሃም አንድ ልጅ (ቀዳሚው እስማኤል) ባለው ጊዜ ይስሀቅ ከመወለዱ፤ ጋና ሳይታሰብ በፊት አንደሆነ ይጠቁማል::

((بَلَؤُا۟ ۚ إِنَّ هَٰذَا لَهُوَ ٱلْ ١٠٥ قَدْ صَدَّقْتَ ٱلرُّءْيَآ ۚ إِنَّا كَذَٰلِكَ نَجْزِي ٱلْمُحْسِنِينَ ١٠٤ وَنَدَيْنَٰهُ أَن يَٰٓإِبْرَٰهِيمُ ١٠٣ لِلْجَبِينِ وَتَلَّهُۥ فَلَمَّآ أَسْلَمَا ١٠٧ وَفَدَيْنَٰهُ بِذِبْحٍ عَظِيمٍ ١٠٦ ٱلْمُبِينُ)) አልሳፋት 37፡104….

‹‹ ሁለቱም ትዕዛዙን በተቀበሉና በግንባሩም ጎን ላይ በጣለው ጊዜ (የሆነው ሆነ)::ጠራነውም፤ (አልነው) «ኢብራሂም ሆይ! ራእይቱን በእውነት አረጋገጥክ::» እኛ እንደዚሁ መልካም ሠሪዎችን እንመነዳለን:: በታላቅ ዕርድም (መስዋዕት) ተቤዠነው ፡ ››))(ሱረቱል አልሳፋት 37፡104)

ሰላም ቅኑን መንገድ በተከተለ ላይ ይሁን:: አሚን

የእስራኤል እና የቡድሂስት መነኮሳት ወዳጅነት

የፅዮናዊቷ እስራኤል መንግሥት የማይናማርን የቡድሂስት መነኮሳት መንግሥት በወታደራዊ ልምምድ እና የጦር መሣሪያ ድጋፍ እንደምያደርግ እና የጀመሩትን ሙስሊሞችን ከምድረ ገፅ የማጥፋት ስራ አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸውና እስራኤልም ከጎናቸው ሆና እንደምትደግፋቸው አስታወቀች።

"The Israeli government is unmoved by ethical concerns and human rights.":@ Israel arms and trains Myanmar military ‘supporting genocide’ against Rohingya muslim stories.top

ምንጭ:-http://muslim-stories.top/israel-arms-and-trains-myanmar-military-supporting-genocide-against-rohingya/

ለጠቅላላ እውቀት ይሆነን ዘንዳ

ይህን የሰይጣን ስራ የደገፈችው እስራኤል ማን ናት? ምንድናት? የሚለውን ማወቁ አይከፋም።እስራኤል የሚለው ትክክለኛ ትርጉሙ በመፅሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ሰፍሯል ቃሉን ብንሰነጥቀው እንደሚከተለው ነው::

"እስራ-ኤል" የእብራይስጥ ቃል ነው። *እስራ* ማለት *መታገል* ማለት ሲሆን *ኤል* ማለት ደግሞ *አምላክ* ማለት ነው ትርጉሙ *ከአምላክ* *ጋር የሚታገል* ማለት ነው። ለዛም ነው ያእቆብ ስሙ እስራኤል የተባለው እግዚአብሔርን ታግሎ ስላሸነፈ። የሚከተለውን ማረጋገጫ እንመልከት። አለውም። ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል፤ ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና። ኦሪት ዘፍጥረት 32 : 28

ምናልባት ሙሉ ሀሳቡን ቆርጠህ ነው ያቀረብከው እንዳትሉኝ ሙሉ ቃሉ እንደሚከተለው ይነበባል።

ዘፍጥረት 32:22፤ በዚያች ሌሊትም ተነሣ፥ ሁለቱን ሚስቶቹንና ሁለቱን ባሪያዎቹን አሥራ አንዱንም ልጆቹን ወስዶ የያቦቅን ወንዝ ተሻገረ።

23፤ ወሰዳቸውም ወንዙንም አሻገራቸው፥ ከብቱንም ሁሉ አሻገረ።

24፤ ያዕቆብ ግን ለብቻው ቀረ፤ አንድ ሰውም እስከ ንጋት ድረስ ይታገለው ነበር።

25፤ እንዳላሸነፈውም ባየ ጊዜ የጭኑን ሹልዳ ነካው፤ ያዕቆብም የጭኑ ሹልዳ ሲታገለው ደነዘዘ።

26፤ እንዲህም አለው። ሊነጋ አቀላልቶአልና ልቀቀኝ። እርሱም። ካልባረክኸኝ አልለቅህም አለው።

27፤ እንዲህም አለው። ስምህ ማን ነው ? እርሱም። ያዕቆብ ነኝ አለው።

28፤ አለውም። ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል፤ ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና። (ዘፍጥረት 32:24-28)

እስራ ማለት *ህዝብ* ነው የሚሉ ምንጭ አልባና ሰነድ አልባ ሰዎች ያለ ዕውቀትና ያለ ማስረጃ ሲናገሩ ይደመጣል፤ ይህ ትልቅ ቅጥፈት ነው። ስለዚህ እንደ_መፅሀፍ_ቅዱስ አስተምህሮ እስራኤል ማለት ከአምላክ ጋር የታገለ ህዝብ ከሆነ ይህን ሰይጣናዊ የዘር ማጥፋትን መደገፉና ማበረታቱ ሊገርመን አይገባም። የቡዲስት መነኮሳት መሪ ይህን አዋጅ አወጀ

I born from virgin i am a lord worship me or die

ከድንግል የተወለድኩ አምላክ ነኝ አምልኩኝ አለዝያም ለመሞት ዝግጁ ሁኑ የበርማው የቡዳ ሀይማኖት መሪ በሮሂንግያ ሙስልሞች ላይ ያወጀው አዋጅ;;

እኛ ሙስሊሞች ፍርድ ሆነ ፍትህ ከአንዱ አላህ ብቻ ነው ምንጠብቀው።

የባሃኢ Bahá'u'lláh ዕምነት (ሃይማኖት)

የባሃኢ ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው እ.ኤ.አ በ1933 ሳብሪ ኤሊያስ በሚባል ግብፃዊ አማካኝነት ነው። የዚህ ኃይማኖት ተከታዮች ሁሉ የሚመሩባቸው ቅዱሳን ተብየ መፅሃፎች በዋቢነት ቁርኣንን ይጠቀማሉ፤ እናም ሙስሊሞችን ለማታለል ሊቀል ይችላል።

ስለ ኃይማኖቱ ምንነትና አመሰራረት

"ሚርዛ አሊ ሙማድ(ባቢ) እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1844 ኢራን (የያኔዋ ፐርሺያ) ቴህራን ውስጥ 'እኔ ወደ አላህ መግቢያ በር ነኝ' ሲል አወጀ።

ይህ የ25 አመት ወጣት የሺዓ እና የሱፊ አንጃዎችን እየተማረ ያደገ ነገር ግን ከሺዓ የሸይኽያት ፊርቃ የሚገኝ ተራ ነጋዴ ነበር። (ይህን እንዲሞግት ግን አንድ የያኔዋ ራሺያ ሰላይ እንደጠቆመው ይነገራል)

በማህበረሰቡ ውስጥ የተሰነቀረው ድንቁርናና ጥመት ይህ ሰው ተነስቶ ያሻውን ሲናገር ሀግ የሚለው እንዳይኖር አድርጓል። እንዳውም በቀላሉ ተከታዮችን እንዲያፈራ ረድቶታል።ይህ ሰው ራሱን ባቢ(በር) ብሎ ሲጠራ ተከታዮቹም ራሳቸውን ባቢ እያሉ መጥራት ጀመሩ። እምነታቸውም በፍጥነት ተሰራጨ። ብዙም ሳይቆይ ባቢ እኔ መልእክተኛ ነኝ እንደ ሙሳ፣ እንደ ዒሳ፣ እንደ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በማለት ለፈፈ። እንደውም ከነርሱ እበልጣለሁ ሲል ሞገተ።

.

እኔ ተጠባቂው መህዲ ነኝ ብሎም አወጀ። ተከታዮቹም አሜን ማለታቸውን ቀጠሉ። ውጉብድናው የተደራረበባቸው የሺዓ መሪዎች ሰውየውን ሞግተው አርኪ ምላሽ ሲያጡበት 'ኩፍር' በየኑበት። ባቢያ በተጀመረ በስድስተኛው አመት በ1850 ሚርዛ አሊ ሙማድ በቴህረን አደባባይ ተገደለ!

ሚርዛ ሁሰይን አሊ(ባሀ አላህ) የባቢያን እምነት ከጅማሮ ከተቀበሉት ተከታዮች አንዱ ነበር። ቀስ በቀስ ቀንደኛ አቀንቃኝ እና መሪ መሆን ቻለ።

ባቢያዎች በ1848 በባድሽት/ኹራሳን በረሀ የኢስላም ህግጋት ያስማማናል አያስማማንም ሲሉ ባደረጉት ስብሰባ አያስማማንም የሚለው ሀሳብ አሸናፊ እንዲሆን ያስቻለ ባቢያዎች ዘንድ ተፅእኖ ፈጣሪ ነበር። ከመሪያቸው ባቢ መገደል በኋላ የሚርዛ ሁሰይን አሊ ወንድም ሚርዛ የህያ ተተኪ ተደረገ። ባቢያዎች በፐርሺያ መቀመጫ ሲያጡም ወደ ባግዳድ (የያኔዋ ኦቶማን ቱርክ) ተሰደዱ። (ይህ ስደት የተቀነባበረው እና በፐርሺያ ባቢያዎች እንዳይፈጁ የረዳው የወቅቱ የራሺያ ኤምባሲ ነበር)

.

ይሁንና የባቢ ተተኪ የተደረገው ሚርዛ የህያ በአግባቡ አልመራንም በሚል አብዛኞቹ ባቢዮች ሚርዛ ሁሰይንን(ባሀ አላህ) መከተል መረጡ። [ቀሪዎቹ ጥቂት የሚርዛ የህያ ተከታዮች እስካሁን አዚሊ እየተባሉ ይታወቃሉ]

ይህኔ ሚርዛ ሁሰይን (ባሀ አላህ) በግዞት እየተዘዋወረም ቢሆን የባቢዮችን እምነት እንደ አዲስ አደራጀ።እርሱ ራሱ የጌታ መልእክተኛ እንደሆነና ወህይ እንደሚወርድለት ለፈፈ። ራሱን 'ባሀ አላህ' ተከታዮቹን በሀኢ ሲል ሰየመ።

ከበሀኢ እምነቶች መካከል ...

:-አላህ በባቢ እና በባሀ አላህ ላይ ሰርጓል ብለው ያምናሉ።

:- ባቢ እና ባሀ የአላህ መልእክተኛ ናቸው ይላሉ።

:- ሁሉም መለኮታዊ መፅሀፍት ቁርአንን ጨምሮ በባሀ ኪታብ ተሰርዘዋል ይላሉ።

:- የነቢዩ ሸሪዓ በባቢ ስርአት ተተክቷል ይላሉ።

:- ሀይማኖቶች ሁሉ ልክ ናቸው/አንድ ናቸው ብለው ያምናሉ።

:- ቡድሀ፣ ኮንፊሺየስ እና ብራህማ ነብያት ናቸው ብለው ያምናሉ።

:- ልክ እንደ ክርስቲያኖች ዒሳ ተሰቅሏል ብለው ያምናሉ።

:- አቅጣጫቸው ወደ አካ (የባሀ የቀብር ቦታ) የአሁኗ እስራኤል ያደርጋሉ።

:- ለመንፈሳዊ ጉዞ ወደ እዚሁ ቅዱስ ስፍራቸው ይተማሉ።

:- ጂሀድ ክልክል ነው በማለት ይሰብካሉ።

:- የቂያማ ቀን ባሀ የሚመጣበት እንደሆነ ያምናሉ።

:- ጀነት እና ጀሀነም የሚባል የለም ይላሉ።

ታዋቂው የቀድሞ የሳዑዲ ዓረቢያ ሙፍቲ ሸይኽ ኢብን ባዝ (ረሂመሁላህ) ይህን እምነት የሚከተሉ ካፊሮች መሆናቸውን በይነዋል። [መጅሙዑል ፈታዋ 13/169]

የበሀኢ እምነት ተከታዮች በብዛት በኢራን የሚገኙ ሲሆን በዒራቅ፣ በሶሪያ፣ በሊባኖስ እና ፍልስጤም ይገኛሉ። ቁጥራቸው ይነስ እንጂ በኢትዮጵያ፣ ኡጋንዳ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ፓኪስታን ጭምር እንደሚገኙም ታውቋል።

ጥያቄዎች (ጥ) እና መልሶች (መ)

ጥ: አምላክ ማን ነው?

መ: ኢየሱስ

ጥ: ኢየሱስ የማርያም ልጅ ነውን?

መ: አዎ

ጥ: ማርያምን የፈጠረ ማን ነው?

መ: እግዚአብሔር

ጥ: አምላክ ማን ነው?

መ: ኢየሱስ

ጥ: ኢየሱስ አንድያ ልጅ ነውን?

መ: አዎ

ጥ: አባቱ ማን ነው?

መ: እግዚአብሔር.

ጥ: አምላክ ማን ነው?

መ: ኢየሱስ.

ጥ: ኢየሱስ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውን?

መ: አዎ

ጥ: ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞተልን?

መ: አዎ

ጥ: ማን ከሞት አስነሰው?

መ: እግዚአብሔር.

ጥ: ኢየሱስ መልእክተኛ ነውን?

መ: አዎ

ጥ: ማነው የላከዉ?

መ: እግዚአብሔር.

ጥ: አምላክ ማን ነው?

መ: ኢየሱስ.

ጥ: ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ አምላክን ይጋዛ/የማል ነበር?

መ: አዎ

ጥ: ማንን ይጋዛ/የማልክ ነበር?

መ: እግዚአብሔርን.

ጥ: አምላክ ማን ነው?

መ: ኢየሱስ.

ጥ: አምላክ መጀመሪያ አለውን?

መ: አይ

ጥ: ታዲያ በጎርጎርዮስ የቀን መቁጠሪያ ታህሳስ 25 (የገና በአል) ላይ

የተወለደው ማን ነው?

መ: ኢየሱስ.

ጥ: ኢየሱስ እግዚአብሔር ነውን?

መ: አዎ

ጥ: እግዚአብሔር የት ነው?

መ: በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ.

ጥ: መንግሥተ ሰማይ ውስጥ ስንት አምላክ አለ?

መ: አንድ ብቻ

ጥ: ኢየሱስ የት ነው?

መ: እሱም ከአባቱ በቀኝ በኩል ተቀምጧል.

ጥ: ታዲያ ስንት ናቸው?

መ: አንድ አምላክ ብቻ.

ጥ: ስንት መቀመጫዎች አሉ?

መ: አንድ

ጥ: ኢየሱስ የት ነው?

መ: ከእግዚአብሔር ጎን ተቀምጧል.

ጥ: እንዴት አንድ ወንበር ላይ ተቀምጠው ነው?

መ: ይህንን መረዳት የሚችሉት ቅዱስ መንፈስ የለቸው ሰዎች ብቻ ናቸው. መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል: - (14:33 ቆሮንቶስ)

እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም……:: በመጨረሻም

መ) መልስ ዬለም

ሙስሊም በመሆኔ አልሃምዱሊላህ.